
# ሳዳም ሑሴን

እና

# የባሕረ ሰላጤው ቀውስ

ልዩ ዘገባ



ደራስያን፦
በኒውዮርክ ታይምሷ ጁዲት ሚለር እና በሀርቫርድ ዩኒቨርስቲዋ ላውሪዩ ማይልሮይድ

ትርጉም፦
በጸጋዬ ኃይሉ ተፈራ
እና
በጌታሁን አበበ ወ/ሚካኤል

# ሣዳም ሑሴን
## እና
# የባሕረ ሰላጤው ቀውስ


ደራስያን፡—

ጁዲት ሚለር
ከኒውዮርክ ታይምስ

እና

ላውሪዩ ማይልሮይ
ከሀርቫርድ ዩኒቨርሲቲ


ትርጉም፡—

በጸጋዬ ኀይሉ ተፈራ እና በጌታሁን አበበ ወልደ ሚካኤል


አዲስ አበባ
1983

የተርጓሚዎቹ መብት በሕግ የተጠበቀ ነው ።

# ማውጫ

ሀ· መቅድም ..................... 5
ለ· መግቢያ ..................... 8
፩· ዘረፋ ..................... 15
፪· ታክሪቴው የሥልጣን ቀበኛ ..................... 38
፫· የሸብር አጥቢያ ..................... 57
፬· የናቡከደነፆር ቅርስ ..................... 72
፭· "እመጣጣችን ለመቆየት ነው" ..................... 102
፮· የማያባራ ጦርነት ..................... 124
፯· ድል የለም ፡ ሰላም የለም ..................... 145
፰· ልዩው ግንኙነት ..................... 158
፱· የእልቂት ሸብረብ ..................... 173
፲· ጥቁር ወርቅ ..................... 198
፲፩· እንበሳውና የበግ ግልገሏ ..................... 214
መደምደሚያ (ቅድመ ጦርነት) ..................... 238
አባሪ — 1
ካርታ ..................... 254
፲፪· የባሕረሰላጤው ጦርነት ..................... 255
ሀ· የበረሃው ጋሻ ዘመቻ ..................... 256
ለ· የበረሃው ማዕበል ዘመቻ ..................... 281
ከጦርነቱ በኋላስ? ..................... 328
አባሪ — 2
ዜና መዋዕል ..................... 336
ተረፈ ዜና መዋዕል ..................... 338

# መቅድም

## ይህን መጽሐፍ ለምን መተርጐም አስፈለገ?

1· ይህ መጽሐፍ ሊልቦለድ ፡ ልዩ ጥናታዊ ዘገባ ነው ። ይህ ዘገባ ደግሞ ማ፤ ምን፤ የት፤ እንዴት፤ ለምን፤ መቼ፤ …ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ የምናገኝበት ነው ። እነዚህን ጥያቄዎች ያልጠየቀ ፡ የማይጠይቅ መቼም የትም ኖር አያውቅ ፡ አይኖርምም ። ሰው ይቅርና እንስሳትና አራዊት ለህላዌያቸው ፡ ለደህንነታቸው ስለ አካባቢያቸው በማያሠልስ ሁኔታ መረጃ ይሻሉ ።

የጋዜጠኝነት ሙያ መሠረትና እምብርት የሆነው ዜና ትርጉም የሚኖረው ሲተነተን ፡ ሲገናዘብ ፡ ሲነፃፀርና ሲመረመር ነው ።

ዜና ከዕለተለት ኑሮ ልማድ ለየት ያለ ድርጊት በመሆኑ ጆሮ ይስባል ፡ ዓይን ይማርካል ።

ዛሬ ከመንፈቅ በላይ በዓለም መገናኛ ብዙኃን የዐበይት ዜናዎች በውራ ሆኖ ሲነገርና ሲዘከር የኖረውን የሣዳም ሑሴንና የፋርስ ባሕረሰላጤ ቀውስ ዜና መነሻ ፡ መገስገሻና መድረሻ በጥልቀት ፡ በምጥቀትና በምልዓት ማወቁ ስለሚያጓጓ ይህንኑ የዛሬ ዜና አድማጭ፡ ተመልካችና አንባቢ ትኩረት ለረጅም ጊዜ ከማንኛውም ሌላ ዜና በላይ ስቦ የቆየ የጦርነት ዜና ትንተና ለኢትዮጵያዊ ሁሉ በቂ ግንዛቤ ለማስገኘት ተተረጐመ ።

2· ዜና ጠቃሚና ጉጂ አለው ። በፋርስ ባሕረሰላጤ የተካሄደው ጦርነት ኢትዮጵያውያን ኩዌትን ስለወረሩት የኢራቅ ዐምባገነን መንግሥት መሪ ስለ ሣዳም ሑሴን ማንነትና ስለ ፋርስ ባሕረሰላጤ

ፖለቲካ ለማሳወቅ ሲባል ይህን መጽሐፍ መተርጐም አስፈለገ ።
የእኛን ረሀብ ፣ ድህንት ፣ በሽታ ፣ ለማቃለል በገፍ ይፈሱን የነበሩ መንግሥታት በዚህ ጦርነት በመጠመዳቸው የእኛ ችግር አስታዋሽ ያጣ ያኸል በመሆኑ ለተወሰነ ጊዜ በእኛ ላይ ጉዳት ማድረሱ አይካድም።

በሌላ አነጋገር ስለሳዳም ሑሴንና ስለ ፋርስ ባሕረ ሰላጤ ቀውስ መነሾ ማወቅ ለካባቢያችንን ፣ ማጤን ስለሚሆን መጽሐፉን ተርጉሞ ለኢትዮጵያዊ ሁሉ ማቅረብ አስፈላጊ ይሆናል ።

የጁዲት ሚለርና የላውሪዩ ማይልሮይ "Saddam Hussein and the Crisis in the Gulf" የልዩ ዘገባ መጽሐፍ ርእስ በአማርኛ ቃልበቃል ሲተረጐም "ሣዳም ሑሴንና የባሕረሰላጤው ውስጥ ቀውስ" ይሰኛል ። እኛ ግን ለአፍ ይቀለጥፋል ብለን በማመን "ሣዳም ሑሴንና የባሕረሰላጤው ቀውስ" ማለቱን መርጠናል።

ደራስያኑ በመጽሐፉ ያካተቱት የቀውሱን ዝርዝር መነሾ ታሪካዊ ለመጣጥ — ማለትም ኢራቅ ኩዌትን እስከወረረችበት እስከሐምሌ 26/1982 ነው ።

እኛ ተርጓሚዎቹ ግን የባሕረሰላጤውን ጦርነት ዓለም አቀፍ ዕውቀና ካላቸው ከታይምና ከኒውስዊክ እንግሊዝኛ መጽሔቶች ለውጣጥተን በመተርጐም አክለናል ።

ደራስያኑ በመጽሐፋቸው በአባሪነት (Appendix) ባካተቱት እስከ ወረራው ባለው ዜና መዋዕል ላይ "ተረፈ ዜና መዋዕል" በሚል ኩዌት ነፃ እስከወጣችበት ቀን ድረስ ያሉትን ሀበይት ክንውናች ጨምረናል ።

በአንፃሩም ደራስያኑ በዚሁ በአባሪያቸው ውስጥ፡—
— Human Rights in Iraq
በሚል ርእስ "Human Rights watch/ Yale University press" በኖቬምበር 1990 ያሳተመውን "Human Rights in Iraq" በሚል ርእስ Middle East Watch ያወጣውን አስፈቅደው በመጽሐፋቸው በ13 (237—249) ገጽ ቢያወጡትም ሰብአዊ መብት በማንኛውም የአዳኒ አገር ወህኒ ቤቶች ፣ በተለይ የፖለቲካ እሥረኞች ሰብአዊ መብት የሚገፈፍበትና የሚጣስበት መልክ በየጊዜው የሚታይና የሚሰማ ፣ ለዓይንና ለጆር የሚቀፍ በአካል ላይ የሚፈጸም አሰቃቂ ፣ ቆፈና



ዘገናኝ ስለሆነ ፣ "የአንባቢያችንን ኅሊና ያቆስላል ፣ ያሸማቅቃል" ፣ ብለን ስለገመትን ማስቀረቱን መርጠን ተተነዋል ።

ከዚህም ሌላ ደራስያኑ በአባሪያቸው ውስጥ Amnesty International የተባለውን ድርጅት በማስፈቀድ በኤፕሪል 1989 "Iraq: Children, Innocent Victims of Political Reprssion" በሚል ርእስ ካወጣው ዘገባ ጨምቀው በመጽሐፋቸው በ12(250—261) ገጽ በኢራቅ ውስጥ በተለይ ልጅነት ባላቸው የፖለቲካ እሥረኞች ላይ የሚፈጸመውን አሰቃቂ ግርፋት ፣ ድብደባ ፣ ...ሌላም የአካል ቁምስቅልና የገፍ ገድያ "Torture, Ill - Treatment, and Death in Iraq" በሚል ርእስ ቢያወጡትም ቀደም ሲል መተዋችንን የጠቀስነውን ርእስ በተውንበት ምክንያት አስቀርተናል ።

የዚህ መጽሐፍ ተርጓሚዎች ለረጅም ጊዜ አንድም በመምህርነት ለልያም በተርጓሚነት በተለይ ደግሞ በዜና ዝግጅትና ትንተና ላይ የተሠማሩን ጋዜጠኞች በመሆናችን ይህን ከፍተኛ ወቅታዊነት ያለው እንዳንጣሚ በሌሎች ሁለት ሰዎች የተደረሰ የልዩ ዘገባ መጽሐፍ እነሆ ለኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን በማቅረብ የሙያ ግዴታችንን ፣ ቀንጣት ያኸልም ቢሆን ፣ እንደተወጣን ስለምንቆጥር ለዚህ በመታደላችን በአንባቢዎቻችን ፊት ክብርና ኩራት ይሰማናል ።

# መግቢያ

## ይህ መጽሐፍ ለምን አስፈለገ?

ጉልማሳው አሜሪካዊ ባለሌላ ማዕረግ የጠረፍ ባሕረኛ ባለቤቱ የበኩር ልጃቸውን ስትገላገል አጠገቧ አልነበረም ። ሌላውም ባለሌላ ማዕረግ ታንከኛ በሳዑዲ በረሀ የሙቀት ወላፈን መቀቀሉ እንቦት ከመርዛም እባብ ለመሠወር በታንኩ እናት መተኛቱን መርጧል ።

የቀድሞዋ የአሜሪካ የባሕር ኃይል አባል ጉልማሳ ወደምትገኝበት ተጠባባቂ ኃይል በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ ለዘመቻ ለመከተት ተዘጋጅታ በማንኛውም ሰዓት የሚደርሳትን የስልክ ጥሪ እንድትጠባበቅ ተነግሯታል ።

ዲፕሎማቶች ሁሉ እስከ ነሐሴ 24/1982 የኩዌትን ዋና ከተማ — ኩዌትን ለቀው እንዲወጡ ወራሪዋ ኢራቅ ካዘዘች በኋላ ይህንኑ ለማፋጠን መብራትና ውሀ ቆርጣባቸዋለች ። ነገር ግን ኩዌት የነበረው የአሜሪካ ኤምባሲ የበላይ ሠራተኞች ብዙ መቶ አሜሪካውያን በኩዌት የአሚር ግዛት በኩዌት መዲና እንድም ተሸሽገው ፣ አልያም ተይዘው እያሉ ለቀው ለመሄድ አልፈቀዱም ።

ኢራቅ ኩዌትን እስከወረረችበት እስከ ሐምሌ 26/1982 ድረስ ኩዌት መዲና ውስጥ በዓመት 15 ሺ ዶላር ያኸል ደሞዝ እያገኘ ተቀጥሮ በመሥራት ወደሀገሩ ገንዘብ እየላከ ዘመዶቹን በመርዳት ጭምር ይኖር የነበረ ሕንዳዊ ባለቤቱ ወረራው በተፈጸመ በሁለተኛው ቀን ትወልዳለች። የተራበውን የኢራቅ ወራሪ ጦር በመፍራት ደሞዙን ከባንክ የሚያወጣበት ቼክ ማግኘት አልቻለም ። ብቻ እራስ ባለቤቱ እንደበረታች ፣ ብር ብለው ካገር ለመውጣት ወስነው ፣ እንደነሱው ከተሸበረ ሌላ አራት ቤተሰብ ጋር ባንዲት ሚኒ ባስ ተጨናንቀው የበረሀው ረሞጫ ሙቀትና በጥበቃ ላይ የተሠማሩ ኢራቃውያን ወታደሮች እየገረመሟቸው በመኻላቸው ደፍረው አለፉ ። ከሦስት ቀን ጉዞ በኋላ (መቼም እንዳይደረስ የለ) ወሰን አልፈው ዮርዳኖስ ገቡ ። ዳሩ ግን (ምን ያደርጋል!)



መዲያው በእዚያ ወደተሰናዳላቸው ስደተኞች ሠፈር እንደደረሱ (ያልታደለችው) ሕፃን በጠና ታመመች ። ይህ አንድ ወቅት ኩሩ የነበረ ሰው ቤት የለሽ ፣ ቤሳ ቤሲቲኒ የለሽ ሆኖ ለዳቦና ለውሀ የየዕለት መቁነን እስኪደርሰው ማለቂያ ወደሌለው ወረፋ ጠባቂ ምጽዋተኛነት ተለወጠ — ከኩዌትና ከኢራቅ ፈርጥጠው ወደዮርዳኖስ የስደተኞች መጠለያ ገብተው መጤ ፣ ወይም እንዴት ወደየአገራቸው እንደሚመለሱ እያውቁ ከነበሩት 400 ሺ ያኸል እስያውያን የቅርብ ምሥራቅ ስደተኞች መኻል አንዱ ሆነ ።

ወደራሷ ወደተወራሪዋ ወደኩዌት ቤቶች ስቆታ እንመለስ ፣ ከብዙ ሺ የወረራው ሰለባ ኩዌታውያን አንዱ ነው ። የኢራቅ ታንኮች ወዳገሩ እስከጐረፉበት ጊዜ ድረስ ፣ ሁሉ በእጁ ሁሉ በደጁ ነበር ። ከሼክ ግዛቷ ከኩዌት እጅግ ባለጸጋና ተደማጭ ቤተሰቦች የአንዱ ወገን ነው ። ብዙ ቤተሰብ ያስተዳድር ነበር ። ትዳር አለው ።ደስታ ግን የተለየው ጊዜ አልነበረም ። እየተስፋፋ በመሄድ ላይ በነበረ የመዋዕለ ንዋይ ንግድ ሥራ ላይ ነበር የተሠማራው ። በኩዌት መዲና የደርባባ ቤት ጌታ ነበር ። አልፎ ተርፎም በአውሮፓም የዕረፍት ጊዜውን የሚያሳልፍባቸው ቤቶች አሉት። በባሕረ ሰላጤው ፣ በአውሮፓና በአሜሪካ ወዳጆች አፍርቷል ። አሜሪካ ውስጥ በደቡባዊ ካሊፎርኒያ ዩኒቨርሲቲ ተምሯል ። ስለዚህም ይመስላል — "አልቃባስ" የተሰኘው የቤተሰቡ ጋዜጣ በዓረቡ ዓለም እጅግ ከተከበሩት ጋዜጦች አንዱ እንዲሆን ተረድቷል ። ኢራቅ ኩዌትን በወረረችበት ወቅት ፣ እንደሌሎች ብዙ ኩዌታውያን ሁሉ ፣ ከነቤተሰቡ አውሮፓ ውስጥ በዕረፍት ላይ ነበር ። መሐመድ አሳገር ቅንጦት ሳይለየው እንኳን ቢሆን ስደቱ እስከነአካቴው ሊሆን እንደሚችል ሲያስበው ይዘገንነዋል ። የኩዌት መንግሥት ከነሐሴ 26/1982 ጀምሮ መሐመድ አሳገር ፣ አልቃባስ ጋዜጣን በሳዑዲ እርዳታ ለንደን ውስጥ እያተመ ሲያወጣ ቆይቷል ። በዚህም አገራቸው ለተወረረችባቸው ለኩዌታውያን የብሶት መግለጫ መድረክ ሆኗቸዋል ።

ከተወራሪዋ ከኩዌት ወደወራሪዋ ወደ ኢራቅ ስንገባም ሳዳም ሑሴን ዜጐቻቸውን ለስደት ፣ ...የዳረጉ መሆናቸው ይታያል ። ከአገር ተሰደው በአውሮፓ ሲኖሩ ብዙ ዘመን ሆኗቸዋል ። ግልጽ ለሆነ ምሁር በሳዳሚት ኢራቅ ውስጥ መኖር እንደማይቻል ይናገራሉ ። የተሰደዱት

የማዳም ሑሴንን መንግሥት ለመቃወም ከወሰኑበት ጊዜ ጀምሮ "ሪፐብሊክ ኦፍ ፌር" በሚል ይበል የሚያሰኝ ርእስ ስለኢራቅ መጽሐፍ ደርሰዋል ። አንድ የዩኒቨርሲቲ አሳታሚ ድርጅት በ1981 ለይስሙላ ያኸል አሳትሞላቸዋል ። ከዚያ በፊት ግን ከስድሳ በላይ አሳታሚ ድርጅቶችን እንዲያሳትሙላቸው ጠይቀው ለፍቶ መና ሆነዋል ። ሣዳም ሑሴን በሽብርና በማስፈራራት ስለመጠቀማቸው በማስረጃ የበለጸገ መጽሐፋቸው በፀምባገነኑ እንዳልነበር ከመሆን አምልጧል ። ሳሚርል ኸሊል የሣዳም ሑሴንን መንግሥት በቀል በመፍራት ትክክለኛ በማቻውና አድራሻቸው ከጥቂት ወዳጆቻቸው በስተቀር በማንም በማይታወቅበት ሁኔታ እየኖሩ ናቸው ። ስለሆነም ሳሚር አልኸሊል የመጽሐፋቸውን ያኸል እንኳ ሳይታደሉ ይኖራሉ ።

ሣዳም ኩዌትን ሐምሌ 26 1982 በመውረራቸው የአሜሪካውያን ፡ የእስያውያን ፡ የኩዌታውያን ፡ የኢራቃውያንና የሌሎች ዓረቦች ሁሉ (እያንዳንዱ እስከ ወዲያኛው) ኑሮ ያለመጠን ተለውጧል ። ብዙ አሜሪካውያን ከአገራቸው የውቅያኖስ ዳርቻ ከ16ሺ ኪሎሜትር በላይ ርቆ እየተፈጸመ ያለው ይህ ድርጊት ጉድቷቸዋል ። ወይም በቅርቡ ይጐዳቸዋል ። (እየጐዳቸውም ነው) ከቪየትናም ወዲህ አሜሪካ ከባሕር ማዶ ካዘመተችው ጦር ሁሉ የላቀው በዚህ ሠራዊት ውስጥ እያንዳንዱ አሜሪካዊ ዘመድ ወይም ወዳጅ ይኖረዋል ። ለሌሎች ጉዳዩ በየአካባቢያቸው ለሚገኙ ነዳጅ ማደያዎች የበለጠ በመከፈል የተወሰነ ነው ። ግን ለብዙ የአሜሪካ ፡ የአውሮፓና የመካከለኛው ምሥራቅ ሕዝብ በ1982 ነሐሴና በ1983 መስከረም የደረሰው ቀውስ ፡ በኢራቅ እርምጃ ማግሥት ከደረሰባቸው በጣም የባሰ ጉዳት ሊያስከትል የሚችል የጉዳት ዝናም ያዘለ ጉም አምጥቷል ።

ሆኖም አሜሪካንና ምዕራቡን ዓለም በባሕረ ሰላጤው ስለተደገሰላቸው ቀውሱን በመቆጣጠሩ የተመሰገነው የቡሽ መስተዳድር ፡ በሚያስገርም ሁኔታ የሚለዋወጥ ፡ እንዲያውም አንዳንዴ ጉልህ ትርጉም የለሽ መግለጫ አቅርቧል ። ከመነሻው አሜሪካ ጣልቃ የመግባት ሐሳብ እንዳልነበራት የተናገሩት ፕሬዚዳንት ቡሽ ከሰዓታት በኋላ አባባላቸውን ለውጠዋል ። ወደክልሉ ጦር ለመላክ መወሰናቸውን ነሐሴ 2/1982 ባስታወቁበት ጊዜ ተልእኮቸው "የመከላከል ብቻ" እንደሆነ አበከሩ ።



ሆኖም ፡ ቀስበቀስ የግቡን ዝርዝር እንደየክብደቱ እንዳንዱን አለባብሰው፡ ሌላውን አፍረጥርጠው እያሰፉት መጡ ። ቡሽ ቀጥለውም ሣዳም በኩዌት ላይ ያካሄዱት ወረራ "የአሜሪካውያንን የህላዌ ስልት" ጉዳት ላይ ለመጣል የተካሄደ ያኸል መሆኑን አፍታቱ ። የሣዳምን የግዛት ወረራ ሂትለር ካካሄደው ጋር ለማመሳሰል አላመነቱም ። በዚህም ቡሽ ፦

ከጅምሩ ሲገታ ይቻል የነበረና የቀነታ ወረራን ለማሳረፍ አገራችንና ዓለም ትልቅ መሥዋዕት ከፍለዋል ። ያንን ስሕተት እንደገመውም ።

ብለዋል ። የውጪ ጉዳይ ሚኒስትሩ ጀምስ ቤከር በነሐሴ 1982 መጨረሻ ወደ አንድ የሸንጐ ኰሚቴ ፊት ቀርበው ሲያስረዱ ይህን የፕሬዚዳንቱን ኃይለቃል አብራርተዋል ። በማብራሪያቸውም ኢራቅ የፈጸመችው ወረራ ለቀዝቃዛው ጦርነት ማግሥት ዓለም የቀረበ የፖለቲካ ፈተና መሆኑን ጠቅሰው ዘመኑ አዲስ ምዕራፍ መተለሚያ ፡ በታሪክ አሳባቢ የሽግግር ወቅት መሆኑን አውስተዋል ። የቀዝቃዛው ጦርነት ማክተም በኃይል የመጠቀም ወይም የማጭት ማክተም ማለት እንዳልሆነም አረጋግጠዋል ፡

አሜሪካና ተባባሪዎቿ ቀዳል ምርጫ ነበራቸው፦
ወረራ ከኢንተርናሲዮናል ማኅበረሰብ ብርቱ ተቃውሞ በለገጠመው የመፈጸሙ እድል የበለጠ በመነመነበት ወመናዊ ሥነምግባር ሥራ ላይ የሚውልበት ዓለም ለመኖር እንፈልጋለን? ወይስ—ወረራ ባይነታ መፈጸም በሚችልበት በማንኛ ግንኙ የምንቁጠርበት ትን የኃይል በጉ ፈቃድ ማግኘት በለተሳነ ወረራ ድልን በሚቀዳጅበት ዓለም ውስጥ መኖር እንፈልጋለን!

ሌሎች ግን የተለየ ሐሳብ ታያቸው ። እንደ "ኒውዮርክ ታይምስ" ጋዜጣው የዲፕሎማሲ ጉዳይ ዜና አጠናቃሪ እንደቶማስ ፍሪድማን በዕውነቱ የምዕራብ ኢኮኖሚ መተኪያ የለሽ ሞተር የሆነውን ነዳጅ ዘይት እንደልብ የማግኘቱና የእርሱንም ዋጋ በውጤታማ መንገድ መቆጣጠር የመቻሉ እድል ለአደጋ ተጋልጧል ። ኢራቅ ኩዌትን ገና በወረረች በዓሥር ቀኑ ፍሪድማን የዋሽንግተንን መስተዳድር ባሸማቀቀው የወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታ ግምገማው የአሜሪካ ልጆች ነዳጅ ዘይት "አምስቱ ሊትር አምስት ሳንቲም" ከሚጨመርባቸው ሞትን እንዲመርጡ እየተጠየቁ መሆናቸውን ያለምንም ይሉኝታ ተናግሯል ።

ቀውሱ ከተፈጠረ ጀምሮ በዕውነት ለአደጋ የተጋለጠው በድምፅ አሳጣጡ — ፕሬዚዳንቱ የሚያገኙት ድጋፍ ፡ እንደገና የመመረጥ እድላቸው ወይም ከሁሉም ጉልቶ አሜሪካውያን ነዳጅ ዘይት ለመቅዳት

የሚያሳዩትን የአልጠግብ ባይ ስግብግብነት መቀጠል ይችሉ ዘንድ የቤንዚን ዋጋ ዝቅ ማለት ነው — የሚለውን አስተያየት የአሜሪካ አስተዳደር በጥብቅ ተቃውሟል ። የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር ቤከር ቀደም ሲል ጋዜጠኛው ምንም ሳይቆጠቡ የሰነዘሩትን ትችት ንዴት ባጐረነነው እንደበታቸው ሲያስተባብሉም በየአካባቢው ማደያ የአምስት ሊትር ነዳጅ ዘይት የመጨመሩ ጉዳይ ሳይሆን በማናለብኝነትና ማንም ሳይተናቀ ነው ሁሉም ዋጋ እስከሚገርበት ሆነ ኢኮኖሚው ወዳድቆ እንጦርጦስ እስከሚገባ ድረስ እንኳን ቢሆን በትእዛዝ እየወሰን የዓለምን የኢኮኖሚ ሥርዓት ሊያነቅ ስለሚችል ሀምባንን እንደሆን አስረድተዋል። እያይዘውም የነዳጅ ዘይት ዋጋ ንረት ጫና አሜሪካን ብቻ ሳይሆን በ1981 በምሥራቅ አውሮፓ የተጀመረውን ፀረ ኮሙኒስት እንቅስቃሴ ፣ እንዲሁም ደግሞ የማእከላዊ አሜሪካን ፣ የደቡብ እስያንና የአፍሪካን ክፍላተ ዓለም ጉስቁላ አገሮች ያሰጋል ።

የትኛው ትርጓሜ ነው ትክክለኛው? ይህ ቀውስ በዕውነት እንደ ዓይን ብሌን ባለና እጅግም በቋፍ ላይ በሚገኝ የዓለም ክፍል ወረራ ቸል ይባልና አይባል ፣ የሚል ጥያቄ የሚያስነሣ ነው? ወይስ ሪፐብሊካዊው ተንታኝ ኬቪን ፊሊፕስ አበክረው እንደተናገሩት ይህ በዕውነት አሜሪካ በኢኮኖሚክስ ጉዳይ የተነካ ፣ ማለትም በነዳጅ ዘይት የተነካ ልትዋጋ የተነሣችበት የመጀመሪያ ጦርነት ነው? በዕውነቱ በባሕረሰላጤው የአሜሪካ ምኗ ለአደጋ ተጋለጠ?

ሣዳም ሑሴንስ ማናቸው? ቀደም ብለው በወረራው ማግሥት በጋዜጦች ላይ የሠፈሩ ረጃጅም ጽሑፎች "የባግዳዱ አራጅ" የሚል ቅጽል ስም ያወጡላቸው የዘመናችን ሂትለር ናቸው? ወይስ የዓረብና የምዕራባውያን አገሮች ዲፕሎማቶች እንደገለጿቸው ይቅርታ የለሽ ፣ ተንኰለኛ ፣ የነዳጅ ዘይትን አቅርቦት ፈጥቶ በመያዝ የመካከለኛውን ምሥራቅና የምዕራቡን ዓለም አገሮች የማንበርከክ ሐሳብ ያላቸው ናቸው?

የሣዳም ሑሴን ኢራቅ ምን ዓይነት አገር ናት? ኢራቃውያን ስለመሪያቸው የሚሰማቸው እቅጩ ምንድነው? ሕዝባቸው አንዱ ከስምንት ዓመት ጦርነት በኋላ በኢራናውያን ላይ ድልን ለመቀዳጀት ያስቻላትን የጦር መሣሪያ በመግዛት የረዳቻትን ዓረባዊት ጐረቤት አገር ማጥቃታቸውን ለምን ይደግፋል? በዘመናችን አንዱ የዓረብ አገር በሌላው



የዓረብ አገር ላይ በቅጽበታዊ ጦርነት ድንበር ጥሶ ሲገባ የመጀመሪያው የሆነውን የሣዳምን ወረራ ለምን ይኸን ያኸል ብዙኃን ዓረቦች አልተቃወሙትም? የአሜሪካ ተባባሪዎች ኢራቅ ኩዌትን ለቃ እንድትወጣ ለማስገደድ ለተያያዙት ዘመቻ አስተዋጽኦ ከተጠየቁት አገሮች መኻል አንዳንዱ ለምን ፣ መልስ ለመስጠት በጣም እስከመቀናጣት የደረሰ ብዙ ዳተኝነት አሳዩ?

በኢራቅ ድርጊት ላይ ከሞላ ጐደል መንግሥታት ሁሉ ዕጢያቸው ለምን ዱብ አለ? አሜሪካ ፣ አውሮፓና ሶቪየት ኅብረት የሰጡቸው ድጋፍ ሣዳምን በኩዌት ረገድ የሚከተሉትን ፖሊሲ እንዲያለዝቡ ያደርጋቸዋል የሚል እምነት ለምን አደረባቸው? የምዕራባውያን አገሮች ርዳታ ሣዳም ኃይለኛ ሠራዊት አደራጅተው ወደ አውሬነት እንዲለወጡ ገፋፍቷቸዋል? ኬሚካል ጦር መሣሪያ አላቸው? ምን ዓይነት ሥነሕይወታዊ ጦር መሣሪያ አላቸው? የኑክሌር ቦምብ አላቸው?

በመጨረሻው ፣ የዓረቡ ዓለም ከቶ እንደነበረ ይቀያል? ወይስ አሜሪካ? ቀውሱ የአሜሪካን ጥቅም በባሕረ ሰላጤው ባላት ሚናና ፣ እንዲሁም ከዓረብ አገሮችና ከእሥራኤል ጋር ባላት ግንኙነት ላይ ምን ተጽእኖ ያደርጋል? በእርግጥም በዚህ ሁኔታ እሥራኤልን ምን እድል ይጠብቃታል?

በግንቦት 1982 እንደእነዚህ ስላሉ ጥያቄዎች ቀርቶ ስለኢራቅ ያሰቡ አሜሪካውያን ይኖራሉ ማለት ዘበት ነው ። ዛሬ ፣ በድንገት ከ100ሺ (ከ470ሺ) በላይ የአሜሪካ ወታደሮች ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ከዘመቱ ወዲህ ብዙ አሜሪካውያን የጥያቄዎቹን መልስ ማግኘትና ስለግጭቱ በበለጠ ጥልቀት መረዳት ያጓጓቸዋል ። ዳሩ ግን ለተራው አንባቢ የሚሆን ስለሣዳም ሑሴን ፣ ስለ ኢራቅ ፣ እና ስለሰላጤው ፖለቲካ ምንም ያኽል መጻሕፍት የሉም ። ጥቂትም ቢኖሩ በምሁራን ለምሁራን የተጻፉ ናቸው። ይህ መጽሐፍ እነዚህን ዓይነተኛ ጥያቄዎች ያነሣል ። መሠረታዊ መልስ ለመስጠትም ይሞክራል ። እናም ሣዳም ሑሴን ምን ዓይነት ሰው እንደሆኑ፣ ያደራጁትን ዓይነት ማኅበረሰብ ፣ እንዲሁም ዓረብ ጐረቤቶቻቸው ፣ ከአሜሪካና የምዕራብ አውሮፓ አገሮች በምን መንገድ አፀፋ እንደሰጧቸው ፣ በሰውዬው ላይ አንዳንድ መሠረታዊ ጥልቅ አስተውሎት ለማቅረብ ይሞክራል ። በድምሩም ፣ የዚህን ግጭት ጠለቅ ያለ የቅርብና

ወረራውን በማውገዝ ፤ አምስት (እስከ ጦርነቱ እሥራ ሁለት) ውሳኔ በአፋጣኝ አከታትሎ አጸደቀ ። ያለአንዳች ቅድመ ሁኔታ ሣዳም ኩዌትን ለቀው እንዲወጡና ምናልባትም ቢጠቁ የጦር ሠፈሮቻቸውንና ኬሚካል የጦር መሣሪያ ማምረቻዎቻቸውን እንዳይመቱባቸው ከመካከላቸው ጥቂቱን ፤ በእነዚህ ተቋሞች እንደቁራኛ ያሠፈሯቸውን ጨምሮ ፤ ሦስት ሺ አሜሪካውያንና በሺ የሚቆጠሩ ምዕራባውያን በአስቸኳይ እንዲለቁ ጠየቀ ። በተጨማሪም የተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት እንደልማዱ በርእዮተ ዓለምና በጥቅም ምክንያት ሳይከፋፈል ፤ በአንድ ድምፅ ፤ በኢራቅ ላይ ፤ የገንዘብና የንግድ ፤ እንዲሁም ለአገሪቱ ዘጠና አምስት በመቶ የውጭ ምንዛሬ በሚያስገኘው የነዳጅ ዘይት ሽያጭ ላይ የኢኮኖሚ ማዕቀብ እንዲጣል ውሳኔ አስተላለፈ ።

በስተሰሜን የሣዳም ጠላት የሆነችው ቱርክ አለች ። ቱርክ የኔቶ አባል ከመሆኗ ሌላ ፤ የአሜሪካ ውለታ አለባት ። ቱርክ ከአውሮፓ ማኅበረሰብ ጋር ፈጥና ለመቀላቀል ካላት ጉጉት የተነሣ ፤ ከአሜሪካ ጐን በመጀመሪያ ከተሰለፉት አገሮች አንዷ ሆነች ። የቱርክ ፕሬዚዳንት ቱርጉት ኦዛል ራሳቸው ፤ ኩዌት በተወረረችበት ዕለት ሌሊቱን ከፕሬዚዳንት ቡሽ ጋር በቴሌፎን ባደረጉት ንግግር ፤ በቱርክ በኩል የሚያልፈውን የኢራቅ ነዳጅ ዘይት ቧንቧ መሥመር እንደሚዘጉ አረጋገጡ ። ይህም ኢራቅ በጠቅላላው ለውጭ ገበያ ከምትልከው አንድ ሦስተኛውን ቀነሰባት። በወረራው ማግሥትም ፕሬዚዳንት ኦዛል ለሌሎችና ለሳዑዲ ዓረቢያ ንጉሥ ፋሀድ ጭምር ለኢራቅ ዛቻ እንዳይንበረከኩ በቴሌፎን አሳሰቡ።

በስተምዕራብ ደግሞ ፤ በሣዳም ብርቱ ጠላት በፕሬዚዳንት ሐፌዝ አል አሳድ የምትመራው አገር ሶርያ ትገኛለች ። ይህች አገር እንደ ኢራቅ በባዓዝ ፓርቲ የምትመራ ብትሆንም በሁለቱም አገሮች መካከል በነበረው የርእዮተ ዓለም ልዩነትና በመሪዎቹ የግል ግጭት ምክንያት በጠላትነት ሲተያዩ ቆይተዋል ። በተለይም በቅርቡ ሲካሄድ የነበረው የኢራቅና የኢራን ጦርነት ፤ ሶርያ ፤ የዓረብ አገር ያልሆነችውን ኢራንን በጥልቅ ስሜት ስትደግፍ መቆየቷ ይታወሳል ። ሶርያ ፤ እስራኤልንና በአካባቢው ሰፍኗል የምትለውን የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም አጥብቃ የምትቃወም አገር ናት ። በተጨማሪም በ1980 ስኮትላንድ ውስጥ



በሎከርቢ የፓን አሜሪካን አየር መንገድ አውሮፕላን በ103 በረራው ላይ እንዳለ በፈንጂ ያጠቁትን ጨምሮ ለአሸባሪዎች ተገን ሆናለች ። ይህም ጥቃት በአሜሪካ ሰላማዊ ሰዎች ላይ ወደር የሌለው ከፍተኛ ጉዳት አደረሰ። ሆኖም ደግሞ በአሜሪካ የሚመራውን በኢራቅ ላይ የተጣለ ማዕቀብ በመደገፍ ፈጥና ተባበረች ። ፕሬዚዳንት አሳድ አዲሱን የጠላታቸውን — ጠላት በመርዳት ሳዑዲ ዓረቢያን ከኢራቅ ወረራ ለመከላከል ለመጀመሪያ ጊዜ 3 ሺ 200 የሶርያ ወታደሮች ልከዋል ። ይህንንም በማድረግ ከባሕረ ሰላጤው አካባቢ ውጭ በቅድሚያ ከተባበሩት ሦስት የዓረብ አገሮች መካከል አንደኛዋ ሶርያ ሆነች ። ከዚህ ሌላ ፤ በነሐሴ 1982 መጨረሻ ሶርያ ተጨማሪ 20 ሺ ብረት ለበስ ጦር ፤ 270 በሶቭየት የተሠራ ታንክና ከባድ መሣሪያ እንደምትልክ ለሳዑዲ ዓረቢያ ቃል ገባች ።

የርዳኖስ ከሶርያ በስተደቡብ ፤ ከኢራቅ በስተምዕራብ የምትገኝ አገር ናት ። ከወረራው በኋላ ፤ ንጉሥ ሑሴን ሳዑዲ ዓረቢያን ከጥቃት ለመከላከል ዋሽንግተን ወታደር መላኳን መተቸታቸው የቡሽን አስተዳደር አስገረመው ። ከእስራኤል ጥቃት የምትጠብቃትን ፤ አጠቃላይ ብሔራዊ የነዳጅ ዘይት ምርቷ ሃያ አምስት በመቶ የሚሆነውንና አማን ከውጭ ከምታገኘው የነዳጅ ዘይት መጠን ዘጠና አምስት በመቶውን የምታቀርብላትን ኢራቅን ለማስቀየም ንጉሡ እንደማይፈልጉ ሣዳም ያውቃሉ ። እንዲሁም ኢራቅ ከኢራን ጋር ጦርነት ስታካሄድ በነበረበት ወቅት ከሣዳም ጋር ንጉሡ የቅርብ ወዳጅነት መሥርተዋል ። ሣዳምን ፤ ከጀማል አብዱል ናስር በኋላ ፤ ለመጀመሪያ ጊዜ ምዕራባውያንን ብቻቸውን የተቋቋሙ የዓረብ መሪ አድርገው በአድናቆት ይመለከቷቸው ነበር ። ነገር ግን ፤ "ደፋሩ ኩሩሩ ንጉሥ" በመባል በዲፕሎማቶች አካባቢ ለረጅም ጊዜ የታወቁት ሑሴንም ቢሆኑ ማዕቀቡን ለማክበር ተስማሙ ። በነሐሴ 1982 መጨረሻ ላይም ወደ ኬኔባንክፖርት — አሜሪካ ተጣድፈው በመሄድ ለምን ፈጥነው እንዳልተባበሩ ለፕሬዚዳንት ቡሽ ቢገልጹም ፕሬዚዳንቱ አልመሰላቸውም ። ያም ሆነ ይህ ከስመ ሞክሼነት በስተቀር ከሣዳም ጋር የሥጋ ዝምድና የሌላቸው ንጉሥ ሑሴን ኢራቅን ይረዳሉ — ተብለው ስለሚጠረጠሩ እምነት ሊጣልባቸው አልተቻለም ።

ከኢራቅ በስተምሥራቅ የምትገኘው የሺዓ እስላሞች አክራሪ አገር ኢራን ናት ። ኢራን በአካባቢው የበላይነትን ለመያዝ ሣዳምን የምትፎካ

የሩት ሥረመሠረት ለመረዳት በር ከፋችና አቅጣጫ አመልካች ለመሆን ይሞክራል ።

የተባበሩት መንግሥታት ቀደም ሲል ያጸደቁትን ማዕቀብ ለማጠናከር እስከ ሐምሌ 26/1982 በኢራቅ ላይ በተወሰነ ኃይል መጠቀምን ለመደገፍ ድምፅ ከሰጡ በኋላ በድርጅቱ የአሜሪካ አምባሳደር ቶማስ ቢከሪንግ ድርጊቱ ለአሜሪካና ለተባበሩት ምንግሥታትም "ታሪካዊ" እንደሆነ ተናግረዋል ። ሚስተር ቢከሪንግ አንዱን ዘጋቢ "በአሸዋው መኻል እንድ የከረረ መሥመር አሥምረናል" ብለውታል ።

የእርሳቸውን ቃል የሰሙ እንድ ደጋፊያቸው የዓረብ ዲፕሎማትም፣ "ማለፊያ ፣ እንግዲያውስ ነፋሱን ልንቆጣጠረው እንችል ዘንድ እንጸልይ" በማለት መልሰውላቸዋል ።



# ፩

# ዘረፋ

በዓሥራ ስምንተኛው ምእታዓመት ይኖር የነበረው ፣ ሁለተኛው የኢራቅ ኸሊፍ ፣ አቡ ጃፈር አል መንሱር ፣ በጥንታውያን ሱመርና ባቢሎን ከተማ ፍርስራሽ ላይ ፣ ለኃያሉ ግዛቱ ተስማሚ ርእሰ ከተማ ለመገንባት ወሰነና ዝነኛ የቤት ፕላን ነዳፊውን አስጠርቶ ከዚያ ቀደም ተሠርቶ የማያውቅ ፣ እፁብ ድንቅ የከተማ ፕላን እንዲነድፍለት አዘዘ ።

ፕላን ነዳፊውም ከዚያ በፊት ታይቶና ተሰምቶ የማይታወቅ ፣ ቅርጸ ክብ የከተማ ፕላን ነድፎ አቀረበ ። ይኸው ፕላን የኸሊፋን ተከታዮች አንዱ ከሌላው ሳይርቅ ከከተማው መኻል — ከኸሊፋ ቤተ መንግሥት ዙሪያ ከከተማው ዳር ያሉትን ጭምር ሁሉም በእኩል ርቀት ላይ እንዲሠፍሩ የሚያደርግ ነበር ።

መንሱር ግን በንድፉ መሠረት የሚገነባው አዲስ ከተማ ቅርጽ አልከሠትልህ አለው ። ፕላን ነዳፊውም ረዳቶቹን ከተማዋ ልትገነባበት በታቀደው መሬት ዙሪያ ጉድጓድ እንዲቆፍሩና ዕንጨትና ገለባ እንዲሞሉት አደረገ ። ቀጥሎም ኸሊፋን በአካባቢው ወደ ሚገኘው ጉብታ ላይ አብረው እንዲ ወጡ ጠየቀው ። ከዚያም ኸሊፋ የወደፊት ርእሰ ከተማውን — የባግዳድን አቀማመጥ ለማየት እንዲችል ዕንጨትና ገለባውን በእሳት ኢንዲለኩሱ አዘዘ ። እሳቱም ተያይዞ ዙሪያውን በፍጥነት እየተቀጣጠለ ዙሪያው በእሳት የተከበበ ቁልጭ ያለ የቀለበት ቅርጽ ፈጠረ ።

እንዲሁም፣ መስከረም 5/1983 ሣዳም ሑሴን ፣ ራሳቸው በለኮሱት የፖለቲካ እሳት ወላፈን በመከበብ — በመኻል ባግዳድ በሚገኘው የፕሬዚዳንቱ መኖሪያ ግቢ ውስጥ ባለው — የግል መኖሪያ ክፍላቸው ውስጥ ተቀመጡ ።

ትንሿን አገር ኩዌትን ሣዳም ወረው መያዛቸው ወይንም ደግሞ ፣ የኢራቅ መንግሥት በሚቆጣጠራቸው ጋዜጦች "የሐምሌ 26 አብዮት" በማለት ቱልቱላ እንደነፉለት ሳይሆን ባልጠበቁት መንገድ ዓለምን አስቆጣ ። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትም በአሜሪካ አሳሳቢነት

ክር ጠላት ናት ፣ በ1973 ሳዳም ጦርነት ከፍተውባት ሁለቱም ሳይሸናነፉ ስምንት ዓመት ተዋጉ ። ቴህራን ለመጀመሪያ ጊዜ ማዕቀቡን ደገፋ ነበር። በሐምሌ 1082 ውስጥ ሳዳም የኢራንን ጠላትነት ለመበወገድ ሲሉ በጦርነቱ ያገኙትን ውድ ምርኮ ፣ ሻት አል ዓረብ የተባለውን የባሕር መተላለፊያ በይ ለኢራን መልሰው ለመስጠት ተገደዱ። ይኸው የባሕር መተላለፊያ በይ ሳዳም ኩዌትን ከመያዛቸው በፊት በባሕረ ሰላጤው አካባቢ የነበረው ብቸኛ መውጫ መግቢያ በር ነው ። ሳዳም ሳዳም ይህን በር የያዙት አንድ ሚሊዮን ሰው ካስጨረሱ በኋላ ነው ። የኢራቅና የኢራን ጦርነት በዓሥራ ሦስተኛው ምእታመት ከተፈጸመው የምንጕል ወረራ ወዲህ ፣ በአካባቢው ደም እንደጐርፍ የወረደበት ጦርነት ነው ።

ቴህራን የሳዳም ሑሴንን ተግባር ያደነቀች ትመስላለች ። ነሐሴ 6/1982 የኢራን ከፍተኛ የሃይማኖት መሪ አያቶላ አሊ ኽሚኒ በሬዲዮ ባሰሙት ዲስኩር ፣ በዩናይትድ ስቴትስ ላይ "የሃይማኖት ጦርነት" እንዲታወጅና የአሜሪካ ወታደሮች ከባሕረ ሰላጤው በኃይል ተገደው እንዲወጡ ጥሪ አቀረቡ ። እንዲሁም ምግብ ፣ መድኃኒትና ሌላም ሰብአዊ እርዳታ ኢራን ለኢራቅ እንደምትሰጥ አያቶላ አሊ ኽሚኔ ተናገሩ ። ይሁን እንጂ የኢራን መሪዎች በሐሳብ መከፋፈላቸውንና ቴህራን በጦርነት የተጐዳችውን አገሯን መልሳ ለመገንባት በጣም የሚያስፈልጋትን የምዕራባውያን የገንዘብ ብድርና ቴክኖሎጂ ላለማጣት ማዕቀቡን መደገፍ እንደሚጐዳት እየታወቀ ፣ ኢራን ኢራቅን እረዳለሁ ማለቷ ማታለል እንደሚሆን ሳዳም ዐወቁ ። ይህ ዕውነት ነው ፣ ኢራቅ ከኢራን እርዳታ የምታገኝ አልሆነም ። ከዚህም በላይ ፣ ኢራን ማዕቀቡን በሚገባ ብታከብር ፣ የሚያስገኝላት ዋጋ ምን ያኸል እንደሚሆን የባሕረሰላጤው አካባቢ አገሮች ማስተዋል እንዳለባቸው የኢራን ባለሥልጣናት አበክረው አስረድተዋል ። ይህም ብቻ አይደለም ፣ በኢራቅና በኢራን መኻል ያለው ጥላቻ ሥር የሰደደ ከመሆኑም በተጨማሪ በመኻላቸው ከፍተኛ ያለመተማመን አለ ። ስለዚህ ኢራን ለኢራቅ የገባችው የእርዳታ ቃል በጥንቃቄ መያዝ እንዳለበት ሳዳም ዐውቀውታል ።

ሆኖም ከሌላው ሁሉ ይበልጥ ያሳሰባቸው በስተደቡብ የምትገኘው የሳዑዲ ዓረቢያ ሁኔታ ነው ። ከኩዌት ወረራ በፊት አንድም የአሜሪካ ወታደር ሳዑዲ መሬት ላይ እንዲሠፍር ሪያድ አልፈቀደችም ። ሌላው



ቢቀር ፣ ሳዑዲ ከአሜሪካ በቢሊዮን ዶላር የገዛችውን ዘመናዊ የጦር መሣሪያ ለመጠበቅ በቂ የቴክኒክ ባለሙያዎች ወደ አገሯ ማስገባቷ ብቻ እንኳ ሳዳምን ውጥረት ላይ ጣላቸው ። ለቀውሱ መፍትሔ ለመሻት ትዋከር የነበረችውን ሪያድን ሳዳም ኩዌትን መውረራቸው እጅግ አስደንገጣት ፤ ስለ ንጉሥ ፋሀድ ደህና አድርገው ውስጡን የሚያውቁ የዜና ምንጮች እንዳሉት በኩዌት ወረራ ሌሊት ንጉሡ ፣ "በፍርሃት ሊሙኙ" አድረዋል ። ሆኖም መስከረም 5/1982 ላይ ፣ ምንጊዜም ጠንቃቃዎቹ ሳዑዲዎች ከወዳጅ ዓረብ አገር መሪዎችና ከጆርጅ ቡሽ ጋር በግል እየተገናኙ ሳዳም ሑሴን — ቋራሽ ከሥልጣን እንዲወገዱ ጠይቀዋል ። ከዚህም ሌላ ፣ ከሃያ በላይ አገሮች የመጡ ፣ በአጠቃላይ 200 ሺ (በኋላ ወደ 700 ሺ) ወታደሮችና ከነዚህም ውስጥ 140 ሺ (በኋላ ወደ 430 ሺ) ያኸል አሜሪካውያን በሚገባ አስተናግደዋል ።

በስደት ላይ የነበረው ፣ የኩዌት መንግሥት በበኩሉ ፣ የአሜሪካን እርዳታ አጸፋ ለመመለስ ፣ አገሪቱን የሚገዛ የሳባህ ንጉሣዊ አገዛዝ ወደ ሥልጣን ከተመለሰ ፣ በሺኺ ግዛቱ ውስጥ ቋሚ የጦር ሠፈር ለመስጠት ቃል ገባ ። ባሕሬይን ደግሞ ፣ ለአሜሪካና ለብሪታንያ ወታደራዊ አገልግሎት የሚሰጠውን ጦር ሠፈር የሚቆጣጠሩ ጥቂት ወታደሮች በግዛቷ በቋሚነት እንዲሠፍሩ ለመፍቀድ ወሰነች ። እንዲሁም ከኢራኑ ሻህ ውድቀት በኋላ ዋና የአሜሪካ መረጃ ማጠናቀሪያ ጣቢያ የሆነችው ኦማን ፣ በጣም ጠቃሚ ሆና ተገኝታለች ። የኢራቅ ታሪካዊ ተፎካካሪ ግብጽም ፣ በአካባቢው ከሳዳም ቀጥሎ ከፍተኛው ጦር ያላት ስትሆን ፣ በመጀመሪያ ወደ ሳዑዲ ያዘመተችውን 2ሺ የአየር ወለድ ኃይል ከፍ በማድረግ ሁለት ተጨማሪ ክፍለ ጦር ማለትም 30 ሺ የሚሆኑ ወታደሮች፣ ስምንት ታንክና ከባድ መሣሪያ የጫኑ የንግድ መርከቦች ለመላክ ነሐሴ 1982 መጨረሻ ተስማማች ።

ከአሜሪካና ከዓረብ ጦር ወታደሮች በተጨማሪ ሳዳምን ያጋጠማቸው ከሳዑዲ (ውስጥ ወይም) ድንበር ተንሥቶ ኢራቅ ውስጥ የሚገኙ ዒላማዎችን ሁሉ ሊመቱ በሚችሉበት ክልል ውስጥ የገባው አስፈሪና አስደንጋጭ የአሜሪካ ዘመናዊ የጦር መሣሪያ ነው ። በመቶ የሚቆጠሩ ኤም—1 ታንኮች ፣ ብረት ለበስ የወታደር ማመላሻዎች ፣ የኢራቅን ተዋጊ አውሮፕላኖች ለይተው እንዲመቱ የአሜሪካንና የሳዑዲን አብራሪዎች የሚረዱ ኤዋክስ ባለ ራዳር አውሮፕላኖች ፣ የባግዳድን የኤሌክትሮኒክስ

አውታሮች የሚያደናግሩ ኢ ኤፍ 111 እና ኢ ሲ—130 ኤሌክትሮኒክስ አፋኝ አውሮፕላኖች ፣ ከ፳ በላይ ሄሊኮፕተሮች ፣ ተዋጊ አውሮፕላኖች ፣ በምብ ጣይ አውሮፕላኖች ፣ የባስ አዋቂና በምብ ጣይ አውሮፕላኖች ፣ ከነዚህም ጋር ኤፍ–15 ፣ ኤፍ–16 ፣ ኤ–10 እና ሐሪየር ፣ እንዲሁም ቱርክ ውስጥ ሰፍረው የሚገኙ ኤፍ 111 እና ኤፍ–117 የተባሉ ተዋጊ አውሮፕላኖችና በተጨማሪም አይዘንሀወር ፣ ኢንዲፔንደስና ሳራቶጋ በተባሉት ተዋጊ አውሮፕላን ተሸካሚ መርከቦች ላይ የተጫኑ ኤፍ 14 ፣ ኤፍ ኤ– 18 እና ኤ– 6 ከተበሉ ተዋጊ አውሮፕላኖች ፣ ሌላ በሕንድ ውቅያኖስ ከምትገኘው ከዲያጎ ጋርሺያ ደሴት እየተነሡ የሚያጠቁ ቢ 52 የተባሉ በምብ ጣይ አውሮፕላኖች ናቸው ።

ራሳቸውን የዓረብ ጦር ኃይሎች የበላይ አዛዥና መሪ ብለው የሾሙት ሣዳም ፣ በመስከረም 5/1983 ላይ ፣ የራሳቸውን ሀላዌ ወደ ሚያስጋ ወታደራዊና ኢኮኖሚያዊ አጣብቂኝ (ምርሳ) ውስጥ ገቡ ።

ይህ እንዴት ሊመጣ ቻለ?

የምዕራብና የዓረብ ፖለቲካ ተንታኞች ፣ ሣዳም በጐረቤት አገር ላይ መቼና እንዴት ለመዝመት ስለመወሰናቸው በአስተያየት ይለያያሉ ። በዋሽንግተን አብዛኞቹ የመንግሥት ባለሥልጣኖች የመካከለኛው ምሥራቅ ፖለቲካ ዐዋቂዎች የሣዳም እንቅስቃሴ ያልታሰበበት እንደሆነ ይናገራሉ ። እነሱም ምንም እንኳን ከወረራው በፊት ሣዳም በመጀመሪያ 30 ሺ ፣ ቀጥሎም 70 ሺ ፣ ከዚያም 100 ሺ ወታደሮችን ከአንድ ወር ባነሰ ጊዜ ውስጥ ወደ ኩዌት ድንበር ቢያንቀሳቅሱም ፣ ኩዌት ጥያቄያቸውን እንድትቀበል ለማስፈራራት ያደረጉት "የጦር ስበቃ" መሆኑን ተናግረዋል ። ይህን አባባል ግን ጉዳዩን በቅርብ የሚያውቁ የዓረብና አንዳንድ የአሜሪካ ባለሥልጣኖች አልተቀበሉትም ። እነሱም በአንፃሩ ሲከራከሩ የሣዳም እንቅስቃሴ ያልታሰበ ወይንም ድንገተኛ እንዳልነበር በማስረዳት ፣ እንዲያውም ተከራካሪዎቻቸው የሣዳምን ዕውነተኛ ፍላጎት ለማወቅ እንዳልቻሉ ጠቆሙ ። በተጨማሪም ተከራካሪዎቻቸው ነገሩን ወደኋላ መለስ ብለው ቢመረምሩት ቀጥተኛና ግልጽ እንደሚሆንላቸው አመልክተው ፣ ሣዳም ሐሳቡን ኩዌትን የወረሩት ፣ ለገንዘብና ለግዛት ዝርፊያ እንደሆነ ፣ ተግባራቸውም በሚገባ የታቀደና እቅዱንም በሥራ ላይ ማዋል የጀመሩት ስድስት ወር ከወረራው በፊት በየካቲት 1982 መጨረሻ መሆኑን ገለጹ ።



የምዕራብና የዓረብ የፖለቲካ ተንታኞች ቢያንስ ቀጥሎ ባለው አስተያየት ይስማማሉ ፣ የኢራቅ መሪ ፣ በኩዌትና በባሕረ ሰላጤው አካባቢ ጐረቤት አገሮቹ ላይ ያላቸው ቁጭት የተንግማው ፣ በኢራቅና በኢራን ጦርነት ከሐምሌ 1982 ተኩስ አቁም ጊዜ ጀምሮ ነው ። ስለዚህ ጉዳይ ፣ በፕሬዚደንት ሬገን የአስተዳደር ዘመን ለመካከለኛው ምሥራቅና ለደቡባዊ እስያ ጉዳይ ምክትል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት ሪቻርድ ዳብልዩ መርፊ ሲናገሩ ፣ ሣዳምና ጓደኞቻቸው ጦርነቱ በሚካሄድበት ጊዜ ሁሉ ቁጭታቸውን ያንጸባርቁ እንደነበር ጠቅሰው ፣ በአደገኛው የእስልምና አክራሪነት እምነቷ መላ አካባቢውን ሥጋት ላይ ከጣለችው ከኢራን ጋር ለሚያካሂዱት ውጊያ የሚሰጣቸው ድጋፍ በቂ እንዳልሆነ መናገራቸውን ገለጹ ።

መርፊ ንግግራቸውን በመቀጠል ፣ ስለኢራቅ መሪዎች በማውሳት በ1980 ዓረቦችም ሆኑ ሌላው ዓለም ከኢራን ጋር በተደረገው ጦርነት ኢራቅ ለከፈለችው መሥዋዕት ተገቢውን እጸፋ አለመመለሳቸውን የኢራቅ መሪዎች በተደጋጋሚ በምሬት ሲናገሩ መስማታቸው እጅግ አሳስቧቸው እንደነበርና ኢራቅ ለፈጸመችው ተግባር ሁሉም አንድም አገር ወሮታውን እንዳልከፈለ ገልጸው ፣ አሜሪካ ራሷ ከኢራቅ ጋር በግንባር ቀደምትነት በመጋፈጧ ፣ በቅርቡ ለተባባሪዎቿ ተመሳሳይ አቤቱታ ማሰማቷ እንደማይቀር ተናገሩ ።

በሣዳም አስተያየት ፣ ምንም እንኳን ጦርነቱን ራሳቸው ቢጀምሩትም ፣ የአካባቢውን የሼክ ግዛቶች ፣ ዓረብ ባልሆነችው በኢራን ከመታወክና ከመወረር ለመከላከል ፣ ኢራቃውያን ከኢራን ጋር ባካሄዱት ጦርነት ደምተዋል ፣ ሞተዋል ። ይህ ሁሉ ሲሆን በአንፃሩ የባሕረ ሰላጤው አገሮች ኑሮ ሳይታወክ ቀጥሏል ። ጦርነቱ ከቆመ በኋላ ፣ ሣዳም ለጓደኞቻቸውና ለዲፕሎማቶች ሲናገሩ ፣ በእርግጥ ፣ የባሕረ ሰላጤው አካባቢ አገሮች ለጦርነቱ የገንዘብና የጦር መሣሪያ እርዳታ እንደሰጧቸው እምነው ፣ ነገር ግን በቂ እንዳልነበር ገልጸዋል ።

ሣዳም ፣ ኩዌትን ለመውረር ስምንት ቀን ብቻ ሲቀራቸው በባግዳድ የአሜሪካ አምባሳደር የሆኑትን አፕሪል ግላስፒን ተቀብለው ሲያነጋግሯቸው አምባሳደሯ ለዋሽንግተን ያስተላለፉት ቴሌግራም እንደሚያስረዳው ፣ የባሕረ ሰላጤውን አገሮች ከኢራን ለመከላከል ፣ ከሳቸው ሌላ ማንም ሊዋጋ እንዳልቻለና ኢራንን ለማቆም ማንም ሌላ በምድር

እንዳልተዋጋ ሣዳም በመዘርዘር ፣ አሜሪካም ብትሆን የሕዝብ አስተያየት ፖሊሲዋን እንዳያስቀይራት ሳትሰጋ በአንድ ሳምንት ውስጥ በአንድ ውጊያ ብቻ 10 ሺ ወታደር እጥታ ለሚቀጥለው ዙር ደግሞ ሌላ 10 ሺ ወታደር ማሰለፍ እንደማትችል በመግለጽ የተናደዱበትን ነገር ተነፈሱ ። አዎን ፣ አነሰም በዛ ኢራቅ ከጦርነቱ በድል አድራጊነት ወጥታለች። ኢራንም ሣዳምን ከሥልጣን ለማውረድ ባለመቻሏ የመሪዋ የአያቶላ ሩሆላ ኾሜኒ ዛቻ መና ቀርቷል ።

ቴህራን እርቀ ሰላም ጠየቀች ። የኢራቅ ድል ግን ፣ ፍሬ ቢስ ነበር ። አገሪቱ ደቃለች ። ዓሥር ዓመት ገደማ በፈጀው ጦርነት የሕዝቧ ቁጥር ተመናምኗል ። በአስተማማኝ ግምት እንደተመለከተው በጦርነቱ 120 ሺ የሚሆኑ ኢራቃውያን አልቀዋል ። 300 ሺ የሚሆኑ ደግሞ በመቁሰል ፣ ዕድሜ ልካቸውን አካለ ስንኩል ሆነው ቀርተዋል ።

ይበልጥ አስቸጋሪው ደግሞ የኢራቅ የገንዘብ ሁኔታ ነው ፣ አገሪቱ ከስራለች ። የአሜሪካና የኢራቅ ንግድ ሥራ መሪ ማርሻል ዊሊ እንዳሉት ፣ ጦርነቱ ሲጀመር ሣዳም 30 ቢሊዮን ዶላር ጥሬ ገንዘብ በእጃቸው ነበረ ቸው ፣ በጦርነቱ ማለቂያ ላይ ግን ባግዳድ ከሌላው ዓለም በተበደረችው 70 ቢሊዮን ዶላር ዕዳ ተዘፍቃለች ። ከዚህም ውስጥ ግማሽ የሚሆነው ለባሕረ ሰላጤው አገሮች የሚከፈል ነበር ። ሆኖም ፣ ይህ ዕዳ ፈጽሞ እንደማይከፈል ሣዳምና ሁሉም ዓረቦች ዐውቀዋል ። እንዲያውም አንድ ዲፕሎማት እንዳሉት ሳውዲ ዓረቢያማ ዕዳውን ጉዳዩም አላለችው ። ነገር ግን ጦርነቱ ካበቃ በኋላ ኢራቅ የግዛት ወይም የገንዘብ ጥያቄ ባነሣች ቁጥር ፣ ኩዌት ደግሞ ፣ ለመከራከሪያ የእዳውን ጉዳይ በተደጋጋሚ ታነሣ ነበር ። በኢራቅና በኩዌት መካከል ባለው የድንበር ጭቅጭቅ ምክንያት ኩዌቶች ከኢራቅ የሚደረግባቸውን ግፊት ተላምደውታል ። ይኸው የድንበር ጭቅጭቅ እየተነሣ እየወደቀ ፣ ከኃምሳ ዓመት በላይ ቀጥሏል ። ኩዌቶች በትሕትና ፣ ግን አክብደው ብድሩ እንዲከፈላቸው ከመጠየቃቸ ውም በላይ ፣ ሣዳምን ዕዳውን እንዲምሯቸውና ድንበራቸውን ያከብሩላ ቸው ዘንድ እርሳቸውም በአፀፋው ግፊት ያደርጉ ነበር ። ይህንንም የኩዌት የማይለወጥ አቋም ፣ ሣዳም እንደ ውርደት ስለቆጠሩት እጅግ በጣም አስቆጣቸው ። አንዳንድ ዲፕሎማቶች ነገሩን ወደኋላ ተመልሰው በመመልከት እንዳሉት ፣ ኩዌት የኃያሏን የጐረቤት አገር መሪ ማንነት



ብትረዳ ኑሮ ፣ የኢራቅን ወረራ ለመከላከል ወይንም ለሌላ ጊዜ ለማስተላለፍ ትችል ነበር ። አንድ ባለሥልጣን ደግሞ ፣ ("ቀድሞ ነበር እንጂ መጥና መደቆስ ፣ አሁን ምን ያደርጋል ድስት ጥዶ ማልቀስ" እንዲሉ) "እንበላ ራት ሲሻው የለም አይሉት" በማለት ኩዌትን ተርተውባታል ።

ጥቂት ዲፕሎማቶችና የፖለቲካ ተንታኞች በጊዜው ቢገነዘቡትም ችግሩ ይበልጥ የተባባሰው በየካቲት 1980 ነበር ። እስራኤላውያን ግን የኢራቅን የጦረኝነት እንቅስቃሴ ቢያንስ ከወረራው አንድ ዓመት በፊት ተገንዝበውታል ። ለምሳሌ ወታደራዊ የመረጃ ማጠናቀሪያዎች ኢራቅ በድንበሯ ሦስት አቅጣጫዎች ላይ ሦስት አዳዲስ የክላስተር ሚሳይል መወንጨፊያ በተከለች ጊዜ እጅግ በጣም ተደናግጠዋል ። የአሜሪካ ፖለቲካ ተንታኞች ግን ፣ ሁኔታውን ወደኋላ መለስ ብለው እንዳጤኑት በኢራቅና በምዕራብ አገሮች መካከል የነበረውን ውጥረት ለማባባስ የታቀደውን ፖሊሲ ሣዳም በየካቲት 1980 ተግባራዊ ማድረግ ጀመሩ ። የዚህም ውጥረትን የማባባስ ፖሊሲ ዋነኛ ዓላማ አብዛኛውን የጐረቤት አገር ሀብትና የባሕረ ሰላጤውን ግንባር ድርጅት ንብረት በዘረፋ ለመውሰድ ሲሆን ፣ በከፊል ደግሞ የዓረብን ሕዝብ ድጋፍ ለማግኘትና ዕውነተኛው ዓላማ እንዳይታወቅ ለመሸፋፈን ነበር ። ሣዳም ደካማዎቹ የባሕረ ሰላጤው አገሮች ጥያቄያቸውን እንዲቀበሉ በመገፋፋት ላይ አተኮሩ ። ለአሜሪካና ለእስራኤል ካልተመለሱት ከሣዳም ጥያቄያቸውን እንቀበልም ያሉትን መከላከያ የሌላቸውን ደካማ የባሕረ ሰላጤውን አገሮችማ ምን ይጠብቃቸው ይሆን? የዓረብ ዜና ምንጮች እንደሚሰማ ሙት ፣ የሣዳም ኃይል እየጨመረ በሄደ መጠን የባሕረ ሠላጤው አገሮችም ሥጋት በዚያው መጠን እያደገ ሄደ ። ከዚህ ሌላ ፣ ሣዳም ጽዮናዊነትንና ኢምፔሪያሊዝምን ለመቋቋም ያደርጉት የነበረ ረጅምና የድፍረት ዲስኩር ፣ የዓረብ ምሁራን እንደሚሉት ፣ በብዙኃኑ የዓረብ ሕዝብ ዘንድ ተቀባይነትን አስገኝላቸው ። ይህም ፣ የአንዱ የሣዳም ልብ ትርታ የሁሉም ዓረቦች የልብ ትርታ ነፀብራቅ ሆኖ እንዲታይና ሣዳም ንም ለዓረብ ሕዝብ መብት ታጋይ ሆነው እንዲታዩ አደረጋቸው ። ሣዳም በጽዮናዊነትና በኢምፔሪያሊዝም ላይ የሚሰነዝሩት ዘለፋ ፣ የባሕረ ሰላጤው አገሮች የእሥራኤል አለኝታ የሆነችውን አሜሪካን ለርዳታ መጥራት አስቸጋሪ እንዲሆን አደረገው ። በመጨረሻም ሣዳም እስራኤል

ጋና አሜሪካን በተመለከተ የሚያደርጉት ረጅምና ዛቻ የተመላበት ዲስኩር ገንዘብና ግዛት ለማግኘት ያላቸውን ውስጣዊ ፍላጐት ለመሸፈን እጅግ በጣም ጠቀማቸው ።

ከየካቲት 1980 ጀምሮ የተፈጸሙት ድርጊቶች እንደሚያመለክቱት የሣዳም የረጅም ጊዜ እቅድ ደህና ሥራ ። የካቲት 5/1980 የአሜሪካ ፣ የመካከለኛው ምሥራቅና የደቡብ እስያ ጉዳይ ምክትል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጆን ኬሊ የባሕረ ሰላጤውን አካባቢ አገሮች ከጐበኙ በኋላ በመጨረሻ ወደባግዳድ ሄደው ከሣዳም ሑሴን ጋር ተነጋገሩ ። በዓረብና በአሜሪካ ዘገባዎች መሠረትም የንግግሩ ውጤት የተሳካ ሆነ ። ኬሊ ግን የሣዳም ዋንኛ ችግር የገንዘብ እጥረት ስለመሆኑና በባሕረ ሰላጤው አገሮች ላይ ያላቸው ቁጣ እየተጠናከረ ስለመምጣቱ ምንም ያኽል ፍንጭ ያገኙ አይመስልም ።

ዋሽንግተን ውስጥም ጉብኝቱ ገንቢና ሣዳምን ለማለዘብ ፣ በባግዳድና በዋሽንግተን መኻል ጥሩ ግንኙነት የመሠረተ የአሜሪካ ጥረት መሆኑን የአሜሪካ ባለሥልጣኖች አረጋገጡ ። ሆኖም ከሁለት ቀን በኋላ የአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ ባሰራጨው ሐተታ ፣ ሣዳምን ጨምሮ ፣ በዓለም ዙሪያ ያሉ ፀምባገነን መሪዎች ከሥልጣን እንዲወርዱ ጥሪ አቀረበ ። አምባሳደር ግላስፒ በበኩላቸው በሬዲዮ የተሰራጨው ሐተታ የአሜሪካን ይፋ ፖሊሲ የሚያንጸባርቅ እንዳልነበር ለኢራቃውያን አረጋገጡ ፣ ሆኖም በዋሽንግተን የጸደቀ ነበርና ኬሊ እግራቸውን ጋና ከባግዳድ እንዳነሡ ኢራቃውያንን አስቆጣ ፤ በንገሩም አለመደሰታቸውን እንዲያሳውቁ አደረጋቸው ።

በየካቲት 12/1980 በባግዳድ የዓረብ ተራድኦ ምክር ቤት የድርጅቱን ምሥረታ ለማክበር የመጀመሪያውን የጠቅላይ ሚኒስትሮች ጉባኤ አካሄደ ። የድርጅቱ አባሎች የአካባቢው አገሮች ብቻ ሲሆኑ ፤ እነርሱም ኢራቅ ፣ የመን ፣ ዮርዳኖስና ግብጽ ናቸው ። የተቋቋመው የኢራቅና ኢራን ጦርነት ከአበቃ በኋላ ሲሆን ፣ ዓላማውም በኢራቅና በቅርብ ወዳጆቿ መካከል የኢኮኖሚና የጸጥታ ትብብር ማድረግ ነው ። ሳዑዲዎች ግን ፣ ኩዌት የኢራቅን ትኩረት ከባሕረ ሰላጤው ይልቅ በጤግሮስና በኤፍራጥስ ወንዞች መካከል ወደሚገኘው የዓረብ ዓለም ፣ "ለም ምድር"



ይመልሰዋል ብላ በመከራከር አጸደቀችው ። ስለዚህ ጉዳይ የኩዌት ምክትል የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በየካቲት 12/1982 በሰጡት ቃለ ምልልስ ኢራቅ ፣ በአካባቢው ሚና የምትጫወትበትን መንገድ ስትፈልግ እንደነበርና የዓረብ ተረድኦ ምክር ቤት መመሥረትም ይህን መንገድ በጥሩ ሁኔታ እንደከፈተው ተናግረዋል ።

የዓረብ ተራድኦ ምክር ቤት ጉባኤ በተካሄደበት ጊዜ ሣዳም አሜሪካ መርከቦቿን ከባሕረ ሰላጤው ማስወጣት እንዳለባት በመናገር አባል አገሮችን አስደነገጡ ። ዋሽንግተን ውስጥ የአሜሪካ ባለሥልጣኖች ሣዳም በሰጡት አስተያየት ተደናገጡ ። ይሁን እንጂ ለአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ ርእሰ አንቀጽ አጸፋ መመለሳቸው ይሆናል ብለው ነገሩን ችላ አሉት ። ከአምስት ቀን በኋላ ፣ ዮርዳኖስ ዋና ከተማ አማን ላይ ፣ የዓረብ ተራድኦ ምክር ቤት የመሪዎች ጉባኤ ተካሄደ ። ሣዳም በጉባኤው ላይ ተገኝተው ፣ በባግዳዱ ጉባኤ ላይ አሜሪካ ከባሕረ ሰላጤው እንድትወጣ የሰጡትን አስተያየት በማስፋፋት እንደገና ኃይለ ቃል አሰሙ ።

ከዚህ ጋር ለአቻዎቻቸው የጉባኤ ተሳታፊዎች ፣ ከቀዝቃዛው ጦርነት በኋላ በመካከኛው ምሥራቅ አሜሪካ ብቸኛዋ ኃያል መንግሥት እንደምትሆን በማስገንዘብ አስጠነቀቁ ። በመቀጠልም ፣ የአሜሪካም ዋና ፍላጐት የእሥራኤልን ጥቅም ማስጠበቅ እንደሚሆን ገለጹ ።

ከዚህም አስከትለው ፣ አሜሪካ ከባሕረ ሰላጤው እንድትወጣ በድጋሚ ጥሪ ካቀረቡ በኋላ ፣ በሚቀጥለው አምስት ዓመት እሥራኤል ዓረቦችን ልታጠቃ እንደምትችል ሣዳም ተነበዩ ። በዚህ የመሪዎች ጉባኤ ዲስኩራቸው "የቅድስት ኢየሩሳሌምን ደጃፍ መብራት ማየት እንችላለን፣" ካሉ በኋላ ፣ "ስለዚህ የኢየሩሳሌም ነፃ መውጣት ተስፋ ብሩህ ሆኖ ይታያል" አሉ ።

ከዚህ በላይ ያለው ሣዳም በአደባባይ የገለጹት አቋም ነው ። ሆኖም ግን በጓል ፣ ገንዘብ የሚያገኙበትን መንገድ በማስላሰል ይጠመዱሉ ። አንድ የታወቀ ዲፕሎማት እንዳስረዱት ፣ በመሪዎቹ ጉባኤ ላይ ፣ ሣዳም ሲናገሩ የባሕረ ሰላጤው አገሮች ያበደሯቸውን ገንዘብ ሊምሯቸው ፈቃደኛ ቢሆኑም ፣ ግድ እንደሌላቸውና ነገር ግን ተጨማሪ ገንዘብ እንደሚፈልጉ ተናግረዋል ። (ይህን ያሉት ዕዳውን እንደማያስከፍሏቸው በማመንና ለመክፈልም ሐሳብ ስለሌላቸው ነበር ።) በተጠቀሰው አስተማማኝ የዜና ምንጭ መሠረት ፣ ሣዳም ለመሪዎቹ ሲናገሩ ፣ "ሌላ 30 ቢሊዮን

ዶላር ተጨማሪ ገንዘብ ያስፈልገኛል ፣ ሂዱና ለሳውዲ ዓረቢያና ለባሕረ ሰላጤው አገሮች ንገሯቸው ፣ ገንዘቡን ካልሰጡኝ እንዴት አድርጌ እንደምወስደው በውቀዋለሁ ።” አሉ ።

ግንፍልነት የማያጠቃቸው የግብጹ መሪ ፕሬዚዳንት ሆስኒ ሙባረክ፡ በመቆጣት “እኔ የዝርፊያ ግብረ አበር አልሆንም ፤” በማለት መለሱ።

ሣዳምም በድንገት ተነሥተው ሲሄዱ ፣ ጉባኤው ተቋረጠና ተበተነ።

በየካቲት 30/1982 ሣዳም ሌላ ያልተጠበቀና ከሌላው ሁናቴ ጋር ግንኙነት የሌለው አድራጐት ፈጸሙ ። በዚህም ፋርዛድ ባዞፍት የሚባል በትውልዱ ኢራናዊ የብሪታንያ ነዋሪ የ“ዚ—ኦብዘርቨር” ጋዜጠኛ በድንገት ለፍርድ አቀረቡ ። ጋዜጠኛው ለፍርድ የቀረበው ለእሥራኤል በመሰለል ተከሶ ለአምስት ወራት በኢራቅ እሥር ቤት ከማቀቀ በኋላ ነው ። ባዞፍት ተይዞ የታሠረው ፣ ከባግዳድ በስተደቡብ በሚገኘው የኢራቅ የሚሳይል ፋብሪካ ላይ በመስከረም 1982 ስለደረሰው ፍንዳታ ምስጢር ዘግቦ ማስተላለፍ ለመሞከር ፋብሪካውን በየዋህነት ከጐበኘ በኋላ ነበር ። አብዛኛው ዲፕሎማት የብሪታንያን ጋዜጠኛ ለፍርድ በማቅረብ ፣ ከኢራን ጋር ጦርነት ላይ በነበረችበት ጊዜም የረዳቻትን ብሪታንያን ኢራቅ ማስቆጣት እንደማትፈልግ ገምተው ነበር ። ስለዚህ ባዞፍት በድንገት ኢራቅ ፍርድ ቤት ቀርቦ ሲታይ ፣ ምዕራባውያን ጋዜጠኞችና የፖለቲካ ተንታኞች ተደናገጡ ። የይስሙላው ችሎት በተለይ በለንደን ውስጥ ታላላቅ ኢራቃውያን ከብሪታንያ ምሁራንና ዲፕሎማቶች ጋር የሁለቱን አገሮች ግንኙነት ለማሻሻል የታለመ ስብሰባ በሚያካሄዱበት ጊዜ ስለነበር የትንኮሳ ባሕርይ ነበረው ። በዚያው ሳምንት ኢራቅ ውስጥ በወንጀል ከተከሰሱ ሰዎች በአብዛኞዎቹ ላይ እንደተፈጸመው ሁሉ ባዞፍትም ከአንድ ወር በፊት መሰለሉን በመናዘዝ ፣ የይሙት በቃ ፍርድ ተበይኖበት ተፈጽሞበታል ።

ጥቂት አጋጣሚ ሁናቴዎች ደግሞ ፣ የአካባቢውን ውጥረት ለማባባስና በኢራቅና በምዕራብ አገሮች መኻል ያለው ግንኙነት መበላሸት ትኩረት እንዲስብ ያላቸውን ግብ ለማሟላት ለሣዳም ጠቀሟቸው ። በመጋቢት 13/1982 ጀራልድ ቡል ፣ ብራሴልስ ውስጥ ፣ በሠለጠኑ ነፍሰ ገዳዮች ተገደሉ ። ቡል አንገቱ ላይ በአምስት ጥይት ተመቶ ፣ በአፍጢሙ



ተደፍቶ የተገኘው ፣ ከመኖሪያው ሕንፃ ፊት ለፊት ፣ በኪሱ 20 ሺህ ዶላር እንደያዘ ነው ። ቡል የአሜሪካ ተወላጅ ያልሆነ ፣ ግን ፣ የአሜሪካን ዜግነት የተሰጠውና ኢራቅ ብዙ ሺህ ኪሎ ሜትር ርቀት ፣ የከባድ መሣሪያ ጥይት ለመተኮስ የሚችል ፣ ልዕለ ጠመንጃ ለመሥራት ያላትን ዕቅድ ካወጡት መኻል ቁልፍ ቦታ የነበረው ሰው ነው ። በስፋት እንደተዘገበው ፣ ቡልን የገደሉት ሞሳድ የተባለው ፣ የእሥራኤል ስለላ ድርጅት ሠራተኞች ናቸው ። በመጋቢት 19/1982 አሜሪካና ብሪታንያ በዘመቻ አያሌ ኢራቃውያንን ማሠር ጀመሩ ። ይህም የጦር መሣሪያ ክፍሎችን የያዘ ፣ ከዚህም ውስጥ ሚሳይልን በየደረጃው ለመለያየት የሚረዳ ፣ እጅግ ዘመናዊ የኤሌክትሪክ መጠበቂያ (ካፓሲተርስ) በሕገ ወጥ መንገድ ፣ ወደ ባግዳድ ለማስገባት የሚጥረውን የኢራቃውያን ቡድን አውታር ለመበጣጠስ ነው።

በመጋቢት 24/1982 ሣዳም ሁሉንም የሚዳስስ ረጅም ዲስኩር በማድረግ ፣ በጀራልድ ቡል መገደል የተሰማቸውን መሪር ኀዘን ገለጡ ። በዚሁ ዲስኩራቸው ፣ ኢራቅ ፣ የሁለትዮሽ (የባይናሪ) ኬሚካል ጦር መሣሪያ ባለቤት መሆኗን አረጋገጡ ። ከዚህም አያይዘው ፦— “አላህ ምስክሬ ነው ፣ እሥራኤል በኢራቅ ላይ አንዳች ነገር ለማድረግ ብትቃጣ ፣ እሳት ግማሽ ምድሯን እንዲበላው እናደርጋለን” በማለት ዛቱ ። በ1980፣ የሰሜን ኢራቅን አማጽያን ፀጥ ለማሰኘት ፣ ሣዳም በሰላማዊ የኩርድ ብሔረሰብ ላይ የኬሚካል ጦር መሣሪያ ሲጠቀሙ እንደሆነው ሁሉ ፣ በድንገት ዋሽንግተንን ጨምሮ ፣ መላው ዓለም በኢራቅና በኬሚካል ጦር መሣሪያዋ ላይ አተኮረ ።

በሚያዝያ 1982 የመጀመሪያ ሳምንት ፣ ሣዳም ለኢራን ፕሬዚዳንት ሀሺሚ ራፍሳንጃኒ የግል ደብዳቤ ላኩ ። ደብዳቤው ፣ የሁለቱን አገሮቻቸውን ግጭት ለምንጊዜም ለማስቀረት ለቴህራን ያልተወሰነ ግዛትና አገራቸው ከማረከቻቸው ኢራናውያን የጦር እሥረኞች መካከል ጥቂቱን ለመልቀቅ ፈቃደኛ መሆናቸውን ያበሥራል ። የምዕራባውያን መረጃ ምንጮች ይህን ጉዳይ የደረሱበት ከአንድ ወር በኋላ ነው ፣ የአሜሪካ ባለሥልጣኖችም ከጊዜ በኋላ ደብዳቤውን የተመለከቱት ፣ ኢራቅ ሌላ አዲስ ግጭት ከመጀመሯ በፊት ፣ ከቀድሞ ጠላቷ ጋር ያላትን ነባር ግጭት ለማቆም ለመደራደሪያ እንዲሆን አድርገው ነው ። በዚያው

ወር ውስጥ ፣ ኢራቅ ከምንጊዜም ፍጆታዋ በላይ ፣ የአሜሪካንን ስንዴና ሌላም ሸቀጣሸቀጥ ለማስመጣት አበዛች ።

በግንቦት 1982 ሁለተኛ እጋማሽ ባግዳድ ውስጥ በተካሄደው የዓረብ ሊግ የመሪዎች ጉባኤ ሣዳም ሌላ ዛቻ ሠነዘሩ ። ራሳቸውን የዓረብ አገር ጀግና አድርገው ለማቅረብ ፣ ዓረቦች ኢየሩሳሌምን ነፃ እንዲያወጡ ያቀረቡትን ጥሪ ፣ በድጋሚ በአደባባይ ተናገሩ "ለጽዮናውያን ሀሳቢ" ሲባል አሜሪካ የምትሰጠው ወታደራዊና ኢኮኖሚያዊ ድጋፍ የፍልስጥኤም ሕዝብ በባርነት ቀንበር ሥር እንዲኖር ያለው በመናገር አሜሪካን ወቀሱ። ሣዳም የተጠቀሙበት ጽዮን የሚለው ቃል አክራሪ ዓረቦች እሥራኤልን ሲጠሩ የሚጠቀሙበት ነው ። ይህን አባባል የዓረብ መሪዎች ቀደም ብለው ትተውታል ። ግን በንግግራቸው ፣ አንዳንድ ግዛትን ነፃ ለማውጣትና ጠቀም ያለ ገንዘብ ከኩዌት ለማግኘት ያላቸውን ቀጻሚ ፍላጐት አላነሡም ። ይህም እንደገና የሚገጻበረቀው ፣ በአደባባይና በግል በሚይዙት አጀንዳ መኻል ያለውን ሰፊ ልዩነት ነው ። ሣዳም የገንዘብ ጥያቄያቸውን በመሪዎቹ ጉባኤ ዝግ ስብሰባ ላይ ለማቅረብ መረጡ ። "ዘ—ኒው ዮርክ ታይምስ" ፣ በመስከረም 1982 ውስጥ ባቀረበው ዘገባ መሠረት ፣ "የዚህ ዓይነቱ የኢኮኖሚ ጦርነት በኢራቅ ላይ ሲካሄድ ትዕግሥት አይኖረንም ፣" በማለት ሣዳም ተናገሩ ። ከኩዌት ብቻ ወደ ሃያ ሰባት ቢሊዮን ዶላር ይፈልጋሉ ። ኩዌታውያን ደግሞ ይህን ያክል ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ እንዲላቸው ተጠይቀው እንደሌላቸው መመለሳቸውን እሁንም በድጋሚ አስተማማኝ ዘገባዎች ገልጸዋል ።

ሆኖም ፣ በሣዳም ጠብ አጫሪነት ኩዌት መብረክረኳ አልቀረም ። ወዲያውኑ የመሪዎቹ ጉባኤ እንዳበቃ ፣ የኩዌት አሚር ፣ ሼክ ጃቢር አልአህመድ አልሳባህ ፣ ለረጅም ጊዜ የነዳጅ ዘይት ሚኒስትር የነበሩትን ዘመዳቸውን ሼክ ኸሊፋ አልሳባህን ወደ ገንዘብ ሚኒስትርነት አዛወሯቸው ። በአሜሪካ የተማሩት ኸሊፋ ፣ በዓለም የነዳጅ ዘይትን ዋጋ ዝቅ አድርጐ በዘላቂነት ለማቆየት ፣ ከነዳጅ ዘይት ምርት ማደግ ፖሊሲ ጋር ስማቸው የተቆራኘ ነው ።

ሰኔ 1982 መጨረሻ ሳምንት የነዳጅ ዘይት ላኪ አገሮች ድርጅት (ኦፔክ) ፣ በጣም አስፈላጊ ስብሰባ ከማድረጉ አንድ ወር በፊት ፣ የኢራቁ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ሳዱን ሐማዲ ኩዌትንና ሌሎችን የሼኮች ግዛቶች ጐበኙ ። ጉብኝቱን ከላይ ሲያዩት ፣ ነዳጅ አምራች ዓረብ አገሮች



የነዳጅን ዋጋ ከፍ ለማድረግ ፣ ኦፔክ ከወሰነላቸው ድርሻ በታች ፣ እንዲያመርቱና ይህንንም አሠራራቸውን አጥብቀው እንዲከታተሉ ፣ ለመገፋፋት ይመስላል ፣ አንድ ከፍተኛ ዓረብ ባለ ሥልጣን እንዳሉት ውስጥ ውስጡን ግን ፣ ሳዱን በጐበኟቸው አገሮች ውስጥ ፣ እያንዳንዱ አገር አሥር ቢሊዮን ዶላር እርዳታ እያዋጣ እንዲሰጣቸው ሣዳም ያቀረቡትን ጥያቄ እንዲቀበሉ ጭምር ገፋፍተዋል ። ለጥያቄው እጅግ አሳሳቢነት ክብደት ለመስጠት ሳዱን ኩዌት በቂ ገንዘብ እንዳላትና እርዳታውንም ልትሰጥ እንደምትችል ለማረጋገጥ ፣ ኩዌት ያላትን ተቀማጭ ገንዘብ የሚዘረዝር ማስረጃ ፣ አውጥተው አሳዩ ። ኩዌትም በመደናገጥ ፣ ከተጠየቀው ጥቂቱን 500 ሚሊዮን ዶላር (በኢራቅ ዓይን ዋጋ ቢስ የሆነውን) ለመክፈል የሦስት ዓመት ጊዜ እንዲሰጣት ጠየቀች ።

በሐምሌ 3/1982 ፣ የባሕረ ሰላጤው የነዳጅ ዘይት ጉዳይ ሚኒስትሮች ፣ ኢራቅ ባቀረበችው ጥያቄ ላይ ለመወያየት ጂዳ ውስጥ ተሰበሰቡ ። ኦፔክ ለገበያ እንዲያቀርቡ የወሰነላቸውን የምርት መጠን በስፋት በመጣስ የታወቁት ሁለት አገሮች—ኩዌትና የተባበሩት የዓረብ ኤሚሮች ግዛቶች ፣ ከኢራን ፣ ከኢራቅና ከሳዑዲ ዓረቢያ በተደረገባቸው ጫና ሳቢያ የተወሰነላቸውን የምርት መጠን አጥብቀው ለማክበር ተስማሙ ። ያም ሆኖ፣ ተጨማሪ ጥሬ ገንዘብ ለማግኘት ኢራቅን ጥያቄ ከማቅረብ አልገታታትም ። ከስድስት ቀን በኋላ ሐምሌ 9/1982 ፣ የኢራቅ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጣሪቅ አዚዝ ፣ ኩዌት የተወሰነላትን የምርት መጠን (ኮታ) በመጣሷና በጋራ ከሚካፈሉት ከሩሜይላ ነዳጅ ዘይት ማመንጫ ጉድጓድ የኢራቅን ነዳጅ ሠርቃለች ፣ ሲሉ በመክሰስ ፣ ለወቅቱ የዓረብ ሊግ ዋና ጸሐፊ ለቻድሊ ክሊቢ ደብዳቤ ላኩ ። በዚያው ቀን ቱኒዚያ ውስጥ በተደረገው ስብሰባ ላይ ፣ አዚዝ ሲናገሩ ፣ "አንዳንድ የዓረብ መንግሥታት በኛ ላይ እንዳሴሩ እርግጠኞች ነን ፣ አገራችን እንደማትንበረከክ እንድታውቁ እንፈልጋለን ፣ ሴቶቻችን ሴተኛ አዳሪ አይሆኑም ፣ ልጆቻችንም ምግብ እንዲያጡ አይደረግም ።" አሉ ።

ሐምሌ 11/1982 ሣዳም ለአገራቸው ሕዝብ ባደረጉት ዲስኩር ኩዌትና የተባበሩት የዓረብ ኤሚሮች ግዛቶች ፣ ታማኝነታቸውን ቢያረጋግጡም ፣ ከመጠን በላይ ነዳጅ ዘይት አምርተዋል ፣ በማለት ሁለቱንም አገሮች አስፈራሩ ። ሁለቱም አገሮች በተባለው ካልተስማሙ ፣ ሣዳም

ለመጀመሪያ ጊዜ ወታደራዊ እርምጃ እንደሚወሰድ ዛቱ ። በዚሁ ጊዜ ሣዳም "ቃላት ሊከላከሉልን ካልቻሉ ሁኔታውን ለማስተካከል ያለን አማራጭ ውጤት ያለው ተግባር በመፈጸም መብታችን መከበሩን ማረጋገጥ ነው ።" አሉ ።

ሐምሌ 11/1982 የኩዌት ካቢኔ ተሰበሰበ ። በስብሰባው ላይ የተመዘገበው የለንደኑ "ዘ—ፋይናንሺያል ታይምስ" መጀመሪያ እትም ያወጣው ቃለ ጉባኤ እንደሚያንፀባርቀው ኩዌት ግራ ተጋብታለች ፤ የሣዳምን ዓላማ ባለማወቋ ተደናግራለች ። ሣዳም የጠየቁትን የዓሥር ቢሊዮር ዶላር እርዳታ ኩዌት የማትሰጥ መሆኗን ካቢኔው ከወሰነ በኋላ ኢራቅ ላቀረበችው ሌላ ጥያቄ መልስ ለመስጠት ይዘጋጅ ጀመር ። በዚህ በት ከሩሜይላ የነዳጅ ዘይት ማመንጫ ጉድጓድ ኩዌት "ሠርቃለች" ለተባለው ነዳጅ ዘይት ከ2-4 ቢሊዮን ዶላር እንድትከፍል ይጠይቃል ። የዚሁ የነዳጅ ዘይት ማመንጫ ጉድጓድ አብዛኛው ክፍል ኢራቅ ውስጥ ይገኛል ። ትንሿቱ ክፍል ደግሞ ኩዌት ውስጥ ስለሆነ ኢራቅ ኩዌትን ከሚገባት ድርሻ በጣም የበለጠ ነዳጅ ዘይት ለመሥረቅ አስችሏታል ባይ ነች ።

ስለዚህ ጉዳይ ፡ የኩዌት ፍትሕ ሚኒስትር ዳሪ አልዑስማን በሰጡት አስተያየት "የኢራቁ ማሳሰቢያ የመጀመሪያው ነው ፤ እስከየት ድረስ እንደሚገፋ የሚያውቀው አላህ ነው ።" ካሉ በኋላ "የነዳጅ ዘይት ጉዳይ ግን ፤ ሌላ ነገር ለመፈለግ ሰበብ ነው" በማለት ተከራከሩ ። የኩዌት ብሔራዊ ሸንጐ ሚኒስትር ባድር አልያዕቁብና የካቢኔ ጉዳይ ሚኒስትሩ አብዱል ራህማን አልአዋዲ "የኢራቅ ፍላጐት ገንዘብ ለመዝረፍ ብቻ ነው" ፤ ሲሉ የበኩላቸውን ክርክር አቀረቡ ። ሌሎች ሚኒስትሮች ደግሞ "ወታደራዊ ጥቃት ሊሠነዘርብን ይችላል" ሲሉ አረጋገጡ ። ካቢኔው ለወታደሮቹ የሚሰጠው ፈቃድ ሁሉ እንዲሠረዝና ወታደሩ በተጠንቀቅ እንዲጠባበቅ ጥሪ እንዲተላለፍ ወሰነ ። ከዚያም የኩዌት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሼክ ሰባህ አልአህመድ አልሳባህ የባሕረ ሰላጤውን ተራድኦ ምክር ቤት አስቸኳይ ስብሰባ ጠሩ ። ይኸው የመከላከያ ድርጅት በኢራቅና በኢራን ጦርነት ጊዜ ተመሠረተ ። አባሎቹም ፤ ኩዌት የተባበሩት የዓረብ ኢሚሬቶች ግዛቶች ፤ ኦማን ፤ ኳታር ፤ ባሕሬይንና ሳዑዲ ዓረቢያ ናቸው ። ከዚህም ሌላ ፤ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ የዓረብ ሊግ ባል.ቃ



እንዲገባ መጠየቅ እንዳለበት አሳሰቡ ። ወታደራዊ ጥቃት ይፈጸምብን ይሆናል ፤ ብለው የተከራከሩት ሚኒስትሮች ሳይቀሩ ሣዳም በይገባኛል ጥያቄ ከሚያጨቃጭቀው ግዛት ጥቂት ክፍሉን ብቻ እንጂ ፤ መላ አገሪቱን ይይዛሉ ብለው አልገመቱም ነበር ።

ዋሽንግተን ውስጥ ፤ ሐምሌ 14/1982 ሲ አይ ኤ ኢራቅ 30 ሺህ ወታደሮቿን ከኩዌት ወደሚያዋስትና ድንበሯ ማንቀሳቀሷን ዘገበ ። የሲ አይ ኤ ሥራ አስኪያጅ ዊሊያም ኤች ዌብስተር በዚህ ክረምት ወራት በአስፔን ኮሎራዶ ውስጥ በግል ጉባኤ ላይ ስለቀውሱ ሲወያዩ እንዳሉት ፤ የሰለላው ድርጅት መጀመሪያ ላይ የደረሰበት መደምደሚያ ፤ ሣዳም በማስፈራራት የነዳጅ ዘይትን ዋጋ ከፍ ለማድረግና ሌላውን ጥያቄያቸውን ለማሟላት ብቻ ያደረጉት እንቅስቃሴ ነው የሚል ነበር ።

ሐምሌ 15/1982 ሣዳምን ከኩዌት ጋር ለማስታረቅ ከሄዱት ከግብጹ ፕሬዚዳንት ሙባረክ በባግዳድ ከተገናኙ በኋላ ፤ የኢራቁ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጣሪቅ አዚዝ ኩዌትንና የተባበሩት የዓረብ ኢሚሬቶች ግዛቶች በድጋሚ ተቹ ። ፕሬዚዳንት ሙባረክ ጉዟቸው መሳካቱንና ኢራቅ በኩዌት ላይ እንደማትዘምት ከሣዳም "ዋስትና" ማግኘታቸውን ለአሜሪካው ፕሬዚዳንት ቡሽ ተናገሩ ። በኋላ ግን ፤ የኢራቅ ባለሥልጣኖች ሣዳም ድርድሩ እስከቀጠለ ድረስ በኩዌት ላይ ምንም ነገር አይደርስባትም ማለታቸውን ብቻ ገለጹ ።

ሐምሌ 17/1982 ኢራቅ በኩዌት ድንበር ላይ ወታደር ፤ ጦር መሣሪያና ስንቅ ማንቀሳቀሷን ስለቀጠለች አጸፋውን ለመመለስ አሜሪካ ከተባበሩት የዓረብ ኢሚሬቶች ግዛቶች ጋር በመተባበር ስድስት አጥቂ የጦር መርከቦችን በማሰለፍ የጋራ ጦር ልምምድ አደረገች ። የቡሽ አስተዳደርም ፤ በሠለጠነው ዓለም ውስጥ በኃይል ማስፈራራት ቦታ የለውም ፤ ሲል አስጠንቀቀ ። የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አፈጉባኤ ማርጋሬት ቱትዊለር በተጨማሪ አሜሪካ የባሕረ ሰላጤው ወዳጆቿ በግልም ሆነ በጋራ ራሳቸውን ለመከላከል አስፈላጊውን እርዳታ ለመስጠት ቃል መግባቷን ገለጡ ። በመቀጠል ፤ ከኩዌት ጋር ግን ፤ የመከላከያ ስምምነት አለመኖሩንና በዚህም ምክንያት ለኩዌት የሚሰጡት የመከላከያም ሆነ የደኅንነት ጥበቃ እርዳታ እንደሌለ አስረዱ ።

በማግሥቱ የአሜሪካ አምባሳደር ግላስፒ ከሣዳም ጋር ተገናኝተው ለመነጋገር ተጠሩ—አምባሳደሯ ከሣዳም ጋር በግል ሲገናኙ በ1980

ማብቂያ ላይ ተሾመው ከመጡ ወዲህ የመጀመሪያቸው ነው ። ሣዳም አንድ ሰዓት የፈጀ ገለጻ በማድረግ ፣ ቆሸንግተን ችግራቸውን እንዳልተረዳ ችላቸውና አገራቸውም ጥሬ ገንዘብ እጅግ በጣም እንደሚያስፈልጋት ለአምባሳደሯ አበክረው አስረዱ ። ከዚህ ንግብ በኋላ—በቆይታው ወቅት ስለተነጋው እርስ በርስ የሚጋጭ ታሪክ አለ ። ኢራቅ ስለቆይታው ያጠናቀረችውን ዘገባ ከኩዌት ወረራ በኋላ የአሜሪካ ዜና ማሰራጫ ኤ·ቢ·ሲ· ተቀብሎ ለመጀመሪያ ጊዜ ይፋ አወጣው ። በዚሁ ዜና መሠረት ሣዳም ላቀረቡት ጥያቄ ኩዌት ምላሽ ካልሰጠች መወረር እንደማይቀር ላት ፣ ሣዳም በግልጽ ተናግረዋል ። ግላስፒም ፣ "ከኩዌት ጋር እንዳለው ዓይነት የድንበር ክርክር በዓረብና በዓረብ መካከል ለሚፈጠር ግጭት ፣ እኛ ምንም አስተያየት የለንም ።" ማለታቸው ተዘግቧል ። ነገር ግን ፣ አምባሳደሯ ወደ ቆሸንግተን ባስተላለፉት ቴሌግራም ፣ በሚቀጥለው ሳምንት ሳውዲ ዓረቢያ ጂዳ ላይ ስብሰባ እንደሚኖር ፣ በዚህም ጊዜ ሳውዲ ዓረቢያ ኢራቅን ከኩዌት ጋር ለማስታረቅ እንደምትሞክር ፣ እንደነገሯቸውና ኩዌት ቁጥቋጣ ካልሆነች እንደማይወሯት ከሣዳም ማረጋገጫ ማግኘታቸውን ጽፈዋል ። አምባሳደሯ ቆይታቸውን ጨርሰው ሲወጡ ፣ ሣዳም ኩዌትን እንደማይወሩ ተማምነው ነበር ። ወይም በቴሌግራሙ መሠረት ሣዳም ኩዌትን ቢወሩም ግፋ ቢል ከአከራካሪው ግዛት ትንሹን ክፍል ይይዛሉ ፣ አልያም ከኩዌት ጠረፍ ማዶ ከሚገኙት ደሴቶች አንዱን ይወስዳሉ ። በኋላ ፣ "ዘ—ኒው ዮርክ ታይምስ" ለተባለው ጋዜጣ አምባሳደሯ በሰጡት አስተያየት ፣ "ኢራቃውያን መላ ኩዌትን ይወራሉ ብዬ—እኔ አላሰብኩም—ሌላውም እንዲሁ ።" ብለዋል ። እንዲሁም በዚያው ዕለት የግብጹ ፕሬዚዳንት ሙባረክ ፣ ሣዳም ፣ "ኩዌትን የመውረር ሐሳብ የለኝም" በማለት እንዳረጋገጡላቸው ተናግረዋል ።

ሐምሌ 19/1982 የኦፔክ አባል አገሮች ጄኔቭ ውስጥ ተሰበሰቡ ። ዜናው አስተማማኝ ነበር ፣ ኩዌት የነዳጅ ዘይት ምርቷን ቀንሳ ዋጋውን ከፍ ለማድረግ ተስማማች ። ነገር ግን ፣ ሣዳም ሌላ 30 ሺ ጦር ወደ ኩዌት ድንበር ማንቀሳቀስ ጀመሩ ።

ሐምሌ 21/1982 ቅዳሜ ፣ የአሜሪካ የነዳጅ ዘይት ጉዳይ ባለሙያና የቀድሞው መስተዳድር ባለሥልጣን በለባሕረ ሰላጤው ቀውስ ደህና አድርገው ከሚያውቋቸው ከኢራቅ መስተዳድር ከፍተኛ ባለሥልጣን ጋር ተነጋገሩ ። በዚሁ ጊዜ አሜሪካዊው ባለሥልጣን ፣ "ኢራቅ ምን



ለማድረግ ታቅዳለች ?" ሲሉ ጠየቁ ። የኢራቁ ባለሥልጣንም ፣ "በሚቀጥለው ሳምንት ታያለህ" የሚል መልስ ሰጡ ። የአሜሪካው ነዳጅ ዘይት ጉዳይ ባለሙያም ኢራቅ ወታደራዊ እርምጃ ለመውሰድ ታስባለች እንዴ ?" ሲሉ በመቀጠል አጥብቀው ጠየቁ ። "አዎን ፣ በሚቀጥለው ሳምንት ።" አሉና በማስከተል "የኩዌትን ሕዝብ እንከላከላለን ።" ሲሉ ኢራቃዊው መለሱ ፣ አሜሪካዊው "አሜሪካውያንስ ?" ቢሏቸው ፣ ኢራቃዊው ፣ ለጥቂት ጊዜ ዝም ካሉ በኋላ ፣ "አሜሪካውያን የወረቀት ነብር ናቸው ። ምንም አያደርጉም ።" አሉ ።

የነዳጅ ዘይት ጉዳይ ባለሙያው ፣ ስለአደረጉት ውይይት ዘገባ ለማቅረብ ለአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ይደውላሉ ፣ ግን ፣ በነገሩ መጨነቅ እንደሌለባቸው ፣ የአሜሪካ መስተዳድር ኢራቅ የምትፈጽመውን ተግባር በሚገባ ቢያውቅም ፣ ሣዳም መቃጣት ብቻ እንጂ ወረራ እንደማያካሄዱ ያመነበት መሆኑ ይነገራቸዋል ።

ሐምሌ 23/1982 በኩዌት ድንበር ላይ የሠፈረው የኢራቅ ኃይል ወደ 100 ሺ ወታደርና 300 ያኸል ታንክ እንደሆነ ፣ ሲ አይ ኤ ዘገበ ። ሁሉቱም የኢራቅ ኃይሎች ብዛት ግምት ከፍ ተደርጐና የአሜሪካ መስተዳድር "ኢራቃውያን ከመቃጣት አያልፉም" ሲል የሰጠውን ማረጋገጫ በማስከተል ፣ ዘ—ቆሸንግተን ፖስት ጋዜጣ ዘገበ ። በዚያው ዕለት አምባሳደር ግላስፒና የዐቪየቱ አቻቸው ለዕረፍት ከባግዳድ ወጡ ።

ሐምሌ 24/1982 የአሜሪካ ምክትል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኬሊ ፣ የአሜሪካ አቋም ወዳጆቿ ስጋት ላይ ሲወድቁ የምትችለውን ድጋፍ መስጠትና መረጋጋትን ማስከበር መሆኑን ለአሜሪካ ምክር ቤት ገለጹ ። በዚሁም ጊዜ ፣ የኢንዲያና ፌዴራል ክልል የምክር ቤት እንደራሴ ሊ. ሃሚልተን ፣ አሜሪካ ከእንድም የባሕረ ሰላጤው አገር ጋር የመከላከያ ውል እንዳልተዋዋለች ባቀረቡት ሐሳብ ሚኒስትሩ ተስማሙ ። ሐምሌ 25/1982 በኋይት ሀውስ ስለቀውሱ የተደረገው ስብሰባ ሲ አይ ኤ የደረሰበትን መደምደሚያ አጸመጠ ። ይህም መደምደሚያ ወረራው ፣ "ሊካሄድ የሚችል ነው ፣ ተዘጋጅተዋል ፣ ይገቱበታል ።" ይላል ።

በሌላ በኩልም ሐምሌ 25/1982 ኩዌትና ኢራቅ በሳውዲ ዓረቢያ ጂዳ ውስጥ ለእርቅ ተገናኙ ። የኩዌት አልጋ ወራሽና ጠቅላይ ሚኒስትር ሼክ ሰዓድ አል አብዱላሂ አልሳቤህ ስብሰባው በሁለቱ አገሮች መካከል

ለሚካሄደው ክርክር መፍትሔ ይሰጣል ብለው በተስፋ የሚጠባበቁ መሆኑን ተናገሩ ።

በዚህ ወሳኝ ስብሰባ ላይ የተፈጸመው ምን እንደሆን አከራካሪ ሆኖ ቀርቷል ። በአሜሪካ የኢራቅ አምባሳደር — መሐመድ አልማሻት እንደሚሉት ፤ ኩዌታውያን ወደ ስብሰባው የመጡት መጥፎ እምነት ይዘው ነበር ። ለመስማት ወይንም ከልብ ለመደራደር ፈቃደኛ አልነበሩም። እንደማሻት አባባል አብረተኛ ነበሩ፤ ኩዌታውያን በስብሰባው ላይ ያሳዩት የነበረው ጠባይ ልክ እንደመደዴ ባለመሸታ ቤትና ኮማሪ ነበር ፤ ልዩነቱ የማይታረቅ ሆነ ፤ ስለዚህ ስብሰባው ያለ ውጤት ተፈጸመ ።

ኩዌታውያን ስለስብሰባው ያላቸው አስተያየት ቢለይ እያስገርምም። በኩዌት ባለሥልጣን አባባል መሠረት ፤ የኢራቁ ልዑካን ቡድን መሪ ፤ ስብሰባውን የከፈቱት የጥያቄዎችን ዝርዝር ብቻ በማንበብ ነበር ። በኩዌቱ ተደራዳሪ አመለካከት የኢራቆች ቡድን መሪ የፈለጉት ፤ ኩዌት ኢራቅ ይገባኛል የምትለውን ግዛትና ነዳጅ ዘይት በቧንቧ መሥመር ወደ ባሕረሰላጤው የማስተላለፍ መብት እንድትሰጣት ነበር ። ከዚህም ሌላ ባግዳድን ዓሥር ቢሊዮን ዶላር እንድትረዳት ነው ። የኩዌታውያን ወገን ይህ ሁሉ ትእዛዝ እንጂ ድርድር እንዳልሆነ በማለጽ መለሰ ። የኢራቅ ልኡካን ኩዌታውያን ተደራዳሪዎች ጥያቄዎቹን እንደገና ሊሲቱን እንዲያስቡባቸው አሳሰቡ ። አልጋወራሽ ሰዓድ በጉዳዩ ሲያስቡበት ካደሩ በኋላ ኢራቃዊ አቻዎቻቸውን ለብቻ አንድ በአንድ አነጋገሩ ፤ ነገር ግን በውይይቱ ላይ እንዳሉ፤ የኢራቃዊው ተደራዳሪ ወገን መሪ በንግሩ ኃይለኛ ራስ ምታት የያዛቸው በማስመሰል በመንጫኒያ ወደ መኝታ ቤታቸው ተመለሱ ። ሰዓድ እንዲቆዩ ቢለምኗቸውም ሰሚ አላገኙም ፤ ከዚያም የሳዑዲ አልጋወራሽ አብዱላሂ ሊያግባቧቸው ቢሞክሩም አልሆነላቸውም። አንድ የኩዌት ባለሥልጣን እንዳሉት ፤ "ጂዳ ውስጥ በአንዳችም ቁም ነገር ላይ ውይይት አልተደረገም ።"

ባለሥልጣን ንግግራቸውን በመቀጠል ፤ አስፈላጊ ከሆነ ፤ ኩዌት ለጥያቄዎቹ ምላሽ ለመስጠት ተዘጋጅታ ነበር ፤ ኩዌታውያን በተለይም ኢራቅ ያለባትን ብድር ለመሠረዝና በባሕረ ሰላጤው ካሉት የኩዌት ደሴቶች፣ አንዷን ለኢራቅ በኮንትራት ለመልቀቅ ዝግጁ ነበሩ ። ዳሩ ግን የልኡካን ቡድን ተጨማሪ መመሪያዎች ያስፈልገው ነበረና በጥቂት ቀናት ውስጥ ፤



በባግዳድ ተገናኝተው በስፊው ለመነጋገር ሁለቱም ወገኖች ተስማሙ ።

በማግሥቱ ከሌሊቱ በስምንት ሰዓት ፤ የኢራቅ ጦር ኃይሎች የኩዌትን ድንበር በማጥለቅለቅ ተሻግረው በስድስት ሰዓት ውስጥ ፤ ኩዌትን በመያዝ ወደ ግዛታቸው ጨመሯት ።

የሣዳም ስልት ሥራ ። በጸደይ መጀመሪያ በድንገት በእሥራኤልና በአሜሪካ ላይ የተሰነዘረው ነቀፌታ ለረጅም ጊዜ ኢራቅን ያግባቡ የነበሩትን የአሜሪካ ዲፕሎማቶች አደናገጠ ፤ እንዲሁም አደናገረ ። በኢራቅና በኢራን ጦርነት ጊዜ አሜሪካ ከባግዳድ ጋር አልወገነችም? ሕዝቧ ከሚመገበው ከመቶ ሰባ አምስቱን ከውጭ ለምታስገባው ለኢራቅ ስንዴና እኽል መሸመቻ ብዙ ሚሊዮን ዶላር ገንዘብ አሜሪካ አልከፈለችም? ባግዳድ ልትሸነፍ ስትል ስለ ኢራን እንቅስቃሴና ሥምሪት አሜሪካ ለሣዳም እጅግ አስፈላጊ መረጃ አላቀበለችም? በ1979 ኢራቅ ነዳጅ ዘይት የምትልክበትን በጣም ጠቃሚውን የሻት አል ዓረብ የባሕር መተላለፊያ ዐይ ኢራን ለመዝጋት በዛተችበት ጊዜ አሜሪካ አውሮፕላን ተሸካሚና ደምሳሽ መርከቧቿን ወደ ባሕረሰላጤው በመላክ የአሜሪካውያንን ሕይወት ለአደጋ አላጋለጠችም? የኢራቅ ሚሳይል በድንገተኛ አደጋ ዩ ኤስ ኤስ ስታርክ የተባለችውን የጦር መርከብ በመምታት ፤ ሠላሳ ሰባት የባሕር ኃይል አባላቷን ስትገድልባት አሜሪካ ፤ እዮታ እንዳላየች አልሆነችም? የኢራቅና የኢራን ጦርነት ካበቃም በኋላ እንኳ አሜሪካ ኢራቅን መርዳቷን አልቀጠለችም? በኩርዶች ላይ በኬሚካል ጦር መሣሪያ ስትጠቀም አሜሪካ ከባግዳድ ጋር የነበራትን ጥሩ ግንኙነት አልቀጠለችም? ይህም ሁሉ ሆኖ የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሣዳም ፊታቸውን ሲያዞሩ በመታለሉ ግራ ተጋብቷል ። የአሜሪካ ፖሊሲ አውጪዎች ኢራቅ የባሕረ ሰላጤውን ጉረቤቶቿን ስታስፈራራና ስትዝትባቸው በቂ ትኩረት አላሳረፉበትም ።

ማደናገሩ ሠርቷል ። ምዕራቡ ዓለም በእሥራኤል ላይ አትኩሮ ነበር። ዓረቦች በነዳጅ ዘይት የምርት መጠን ቁጥጥርና ዋጋ ላይ አትኩረው ነበር ። ኢራቅም በኩዌት ላይ አትኩራ ነበር ።

ወረራው ኩዌትን ፤ አሜሪካንና ዓለምን አስደንግጧል ። ሲ አይ ኤ ብቻ ነበር ፤ ኢራቅ ኩዌትን እንደምትወር ያስጠነቀቀው ። አንድ የኋይት ሀውስ ባለሥልጣን ግን ፤ ማስጠንቀቂያው ታግዶ ከቆየ በኋላ ይፋ የወጣው በወረራው ዋዜማ መሆኑን ገለጹ ። በመጨረሻም ፤ ግምባር

ቀደም የአሜሪካ መንግሥት ፖለቲካ ተንታኞች ኢራቅ ኩዌትን ከወረረች ከአከራካሪው ግዛት የተወሰነ ክፍሉን ብቻ ለመጨምደድ እንደሆነ ተሰማው ። ምናልባት ዓረቦች ይህንኑ በትዕግሥት ሊያልፉት ይችሉ ነበር፡ እንዲሁም ዋሽንግተን ። የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የቀድሞ ባለሥልጣን ሪቻርድ መርፊ በቅርቡ እንዳሉት ፣ ሣዳም ለወረራ ሐሳብ እንደሌላቸውና እንዲሁ ብቻ በመቃጣት ለማስፈራራት እንደሆነ የተከራከሩት ሰዎች ፣ ሣዳም ሳያቋርጡ ወታደራዊ ክተት በማካሄድ ባካባቢው ውጥረት በመጨመራቸው መወቀስ የለባቸውም ፣ ይህም ችር አተረጓጐም፡ ሣዳም ለወረራው ለመዘጋጀት ቢያንስ ሁለት ሳምንት የሚያስፈልጋቸው በመሆኑ ሐሳብ ላይ ከእሥራኤልና ከአሜሪካ ወታደራዊ መረጃ ተንታኞች ጋር ይጋጫል ። ከዚህም በላይ ሣዳም በድንገት ከማጥቃታቸው በፊት ባለፉት ሳምንታትና ወራት አስፈራርተው በምስጢር ገንዘብ ለመዝረፍ ጥያቄ ማቅረባቸውን ሐሰት ያስመስለዋል ።

ሣዳም ፣ እንቅስቃሴያቸው ፣ ዓለምን በማደናገሩ ረገድ ግምታቸው ትክክለኛ ነበር ። ነገር ግን አስቀድመው መገንዘብ የተሳናቸው የምዕራቡን ዓለም ዋነኛ የነዳጅ ዘይት ምንጭ መውረራቸው አሜሪካን ምን ያኸል ሊያስቆጣና ሊያሳስባት እንደሚችል ነበር ። ሣዳም እንዲህ ያለ ታላቅ የማገናዘብ ስሕተት ሲያደርጉ ይህ የመጀመሪያቸው አልነበረም ። በ1982 ኾሚኒ ከወታደሩና ከገዢው መደብ የማይፈልጓቸውን ሰዎች በማስወገዳቸው ፣ እንዲሁም የተማረው ወገን አገር ጥሎ በመሸሹ ሣዳም ኢራንን ወረው በሁለት ሳምንት ድል መቀዳጀት የሚችሉ መስሏቸው ነበር ። ኢራናውያን አገራቸውን ከወረራ ለመከላከል ምን ያኸል ቁርጠኛ እንደሆኑና መንግሥቱ ሳይሸነፍ ምን ያኸል ጊዜ መቆየት እንደሚችል በቅድሚያ ማወቅ ተስኗቸዋል ። የዓረቡና የምዕራቡ ዓለም ኢራንና አክራሪ የሺዓ እስላሞች በመካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ ድል እንዳይቀዳጁ ያለመፈለጋቸው ብቻ የዚያን ያኸል እስኪ መስለው ያልታዩአቸውን ሣዳምን አዳናቸው ።

በዓሥር ዓመታት ልዩነት ሣዳም የፈጸሙት ሁለት ስሕተት ዓረብ ያልሆኑ ወገኖችን ጥቅሞች ክፉኛ ተጻረረ ። አሜሪካ የምታደርገውን ቆይተው ለማየት ስላሰቡት ስለአብዛኛዎቹ የዓረብ መንግሥታት የመጀመሪያ አፀፋ ሣዳም በትክክል ገምተዋል ። ዓረቦች መጀመሪያ እንደሚደነግጡና በመጨረሻ ግን ዞረው ከሳቸው ጐን እንደሚሰለፉ ዐወቁ። ሆኖም



እንደ እያቶላህ ኾሚኒና እንደ ጆርጅ ቡሽ ያሉትን ሰዎች ማወቅ አልተቻላቸውም ። በሁለቱም ሰዎች አንፃር የራሳቸውን ጥንካሬ ከሆነው በላይ አድርገው ገምተዋል ።

የተሳሳተው ግምታቸው ከዚህም በላይ ሣዳም ከኢራቅ ውጭ በአሳፋሪ ሁኔታ ስለሌላው የዓለም ክፍል ምንም ዕውቀት የሌላቸው ሰው መሆናቸውን ያንጸባርቃል ። አመጣጣቸውና አስተዳደጋቸው ሲታይ ሥልጣን ላይ መውጣታቸው ራሱ ያስገርማል ። ዘመናዊ አስተሳሰብ ካልደረሰባት ኋላ ቀር የገጠር መንደር የተገኘው ፣ ገጠሬነቱ በሙላ ሕይወቱ ላይ አሻራውን ትቶበት ያለፈው ገጠሬው ልጅ ሣዳም ሑሴን በማያውልስ የሥልጣን ጥምና የከበሬታ ፍላጐት በዓሥር ዓመት ውስጥ በዓለም ላይ ለሁለት ታላላቅ ቀውስ ምክንያት ሆኗል ።

፮

# ታክሪቲው የሥልጣን ቀበኛ

ሣዳም ሑሴን ፣ "ጎድፋዘር" የሚባለውን ፊልም ይወዳሉ ። ከፊልሞቹ ሁሉ እጅግ የሚያፈቅሩትና ደጋግመው ያዩት ነው ። በተለይ የፊልሙ ኮከብ ተዋናይ ዶን ኮርሊዮኒ (ጎድፋዘር) የተሸኘው ገጸ ባሕርይ እጅግ ማርኳቸዋል ። ዶን ኮርሊዮኒ ያጣ የነጣ ደሀ ልጅ የነበረ ፣ በኋላ ግን አግኝቶ የከበረ–ያለፈለት ፣ ቀን የወጣለት ነው ። ከቤተሰቡ ከሚያስቀድመው—ለሥልጣን ካለው ጥልቅ ስሜት ብቻ በስተቀር ቤተሰቡን አክባሪ ሰው ነው ። የዶን እንደ ብረት የጠነከረ ባሕርይ ፣ ኢራቅን የሚገዙት ምስጢራዊ ሰው አምሳያ ስለሆነ ፣ በአብዛኛው የእሳቸውን ማንነት ሊናገር የሚችል ሞዴል ነው ። ሁለቱም ከትቢያ ፣ ከደሀው ገበሬ መንደር የተነሡ ናቸው ፤ ሁለቱም ሥልጣናቸውን የያዙት በጉልበት ነው ፤ እንዲሁም ለሁለቱም ቤተሰባቸው ቁልፋቸው ነው ፤ ለሥልጣን የሚያበቃ ቁልፍ ። ለነሱ ፣ ቤተሰብ ሁሉም ነገር ማለት ነው ። ሣዳም ፣ እንደ ጎድፋዘር እስከመጨረሻው ማንንም ፣ የቅርብ ሥጋ ዘመዳቸውን እንኳ ፣ አያምኑም። ለሁለቱም ማሰባሰል ፣ ሥነሥርዓት አክባሪነት ፣ ታማኝነትና ምሕረት የለሽነት የሰው ጠባይ መለኪያቸው ናቸው ።

ሆኖም ልዩነት አለ ። ዶን ግለኛና ሁሉን ነገር በምስጢር የሚይዝ ፣ ሁልጊዜ ወንጀሉን ባልታወቀ ስም ለመሸፋፈን የሚፈልግ የስውሩ ዓለም ሰው ነው ። ሣዳም ግን የሕዝቡን የፖለቲካ ሥልጣን የቀሙ ፣ የአደባባይ ሰው ናቸው ። ባገኙት እድል ሁሉ በመጠቀም ኃይላቸውን በማስተዋወቅ፣ የእሳቸው አገዛዝ አማራጭ እንደሌለው ሕዝባቸውን ለማሳመን የሚፈልጉ ሰው ናቸው ። ኢራቅን መጎብኘት ፣ ወደ ዐምባገነን ምድር መግባት ማለት ነው ። ጥቁር ዞማ የራስ ጠጉርና ሪዝ ያለው የሣዳም ሑሴን ግዙፍ ምስል ሥልጣን የተላበሰና ያልተለመደ ፀጥታ የሰፈነበት ፊታቸው፣ ቁልቁል አትኩሮ ፣ መላዋን ባግዳድ ይመለከታል ። ፎቶግራፎቻቸው በየትም ቦታ ይገኛል — በወርቅ የእጅ ሰዓት ላይ ሳይቀር ተቀርጿል ። ሱሜሪያውያን ያጸጸፍን ጥበብ በፈለሰሙባት ምድር ላይ የሊቃውንት



ጉባኤ ተሽሮ አገር ባጥለቀለቀ አንድ ምሥል ተወርሷል ።

ይህ ልዩነት ግን ፣ ምናልባት ፣ ምንም ዓይነት ለውጥ አያመጣም ። ምክንያቱም ፣ ዶንና ሣዳም ፣ ለሥልጣን ይጓጓሉ ፣ መከበርን ይሻሉ ፣ ሁለቱም ግጣት ምን ማለት እንደሆነ እያገጣጠሟቸው ስለሚያውቁት ፣ ፍላጎታቸው ምንጊዜም እንደጨመረ ነው ። ትንሽም ይሁን ትልቅ ስድብ ተሰድቤ ይሆናል ብለው ከጠረጠሩ ፣ ሁለቱም በምንም ዓይነት ቂማቸውን አይረሱም ፣ ሁለቱንም ራሳቸውን መጠበቅ ያስቻላቸው ዕውቀት ፣ ማሪዮ ፑዞ (የጎድ ፋዘር ደራሲ) በፈጠራ ድርሰቱ ገጸባሕርይ ላይ እንደታዘበው ነው፣ "በዚህች ዓለም ላይ ከሰዎች ሁሉ ደካማ የተባለው ፣ ከተከታተለ ፣ ከሁሉም በላይ ኃያል የተባለውን ሰው ፣ ሊበቀለው የሚችልበት ጊዜ ይመጣል ።" በዚህም ተመሳሳይነታቸው ውስጥ ፣ ምናልባት ፣ የሣዳም ሑሴንን ምኞት ለመረዳት የሚያስችለውን ቁልፍ ለማግኘት ይቻል ይሆናል ።

ሣዳም ሑሴን ፣ ከኀምሳ ዓመት በፊት በሚያዝያ /1929 ተወለዱ ። ቤተሰቦቻቸው መሬት የሌላቸው በጣም ደሀ ገበሬዎች ነበሩ ። የተወለዱባት መንደር አልአጃ ፣ በጤግሮስ ወንዝ ዳርቻ ፣ ታክሪት ከተማ አጠገብ ፣ ከባግዳድ በስተሰሜን መቶ ስድሳ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች ። (ምንም እንኳ እስላሞች የተወለዱበትን ቀን በማክበር የምዕራቡን ባህል ባይጋሩም ፣ ሣዳም የልደት ቀናቸውን ፣ ኢራቅ ውስጥ ብሔራዊ በዓል እንዲሆን አድርገዋል) ታክሪት ሱኒ እስላሞች በሚኖሩበት የኢራቅ ክፍል መኻል ናት ። ነገር ግን ኢራቅ ውስጥ ሱኒዎች አነስተኞች ናቸው ። በአገሪቱ ከግማሽ በላይ ያኸሉ የሱኒ ታሪካዊና ሃይማኖታዊ ተፎካካሪ የሆኑት ሺዓዎች ናቸው ። ታክሪት የበለጸገችው በ19ኛው ምእታመት ሲሆን ፣ የታወቀችው አየር በተሞላ ስልቻ አማካይነት የምትንሳፈፍ ከብ ጀልባ በመሥራት ነው ። ሆኖም የጀልባ ሥራው ኢንዱስትሪ ሲወድቅ ፣ ከተማዋም አብራ ወደቀች ። ሣዳም በተወለዱበት ጊዜ ከተማዋ ደሀይቷ ነበር ።

ከውጪው ዓለም ጋር የነበራት መገናኛ በጣም አስቸጋሪ ነበር ። ከባግዳድ እስከ ሞሱል የተዘረጋው የምድር ባቡር ሐዲድ በታክሪት አቋርጦ እንዲያልፍ ይዘረጋ በነበረበት ጊዜ ፣ ከተማዋ አንድ ጥርጊያ መንገድ ብቻ ነበራት ። በአካባቢው የምትገኘው የሣዳም መንደር ደግሞ

ይበልጥ በባሰ ሁኔታ ላይ ነበረች ። መንገዱ ኮረኮንች ብቻ ነበር ። የመንደሩ ነዋሪዎች ፣ የማዳምን ቤተሰቦች ጨምሮ ፣ ከጭቃና ከሸንበቆ የተሠሩ ጐጆዎች ነበሩ መኖሪያዎቻቸው ፣ ማገዶቸው ኩበት ነበር ። ታክሪትና አልኡጃ የኤሌክትሪክም ሆነ የቧምቧ ውሀ መሥመር አልተዘረጋላቸውም ። አካባቢውን ማእከላዊው መንግሥት በውል የሚያውቀው አይመስልም ፣ ሥልጣን በጥቂት ፖሊሶች መኖር ብቻ ተወስኗል ።

ያንጊዜ ኢራቅ ስለመንግሥት ምንነት ትንሽ ብቻ በሚያውቁ ሰዎች የምትገዛ እሳት ላይ ተጥዳ የምትንተከተክ የፖለቲካ ማሰሮ ነበረች ። ከዓሥር ዓመት አጭር የብሪታንያ ቅኝ አገዛዝ በፊት ፣ ዑስማናውያን ቱርኮች ኢራቅን አምስት መቶ ዓመት ገዝተዋል ። ብሪታንያ ኢራቅን የለቀቀችው በ1922 ፣ ማዳም ለመወለድ አምስት ዓመት ብቻ ሲቀረው ነበር ። ኢራቅ ነፃነቷን በተቀዳጀች በአራት ዓመቷ በብዙ መቶ የጥንታዊ ክርስትና ተከታይ አሶራውያን ፣ በኢራቅ ጦር ኃይል ተጨፈጨፉ ። ከአምስት ዓመት በኋላም ፣ ባግዳድ ውስጥ በአይሁድ ጥንታዊ ሠፈር ተመሳሳይ ጭፍጨፋ ተካሄደ ። በነፃነትና በማዳም ልደት መኻል ባለው ጊዜ ውስጥ የኢራቅ ጦር በእጥፍ አደገ ። ያን ጊዜ የጦር ኃይሉ "በግድያ ሙያው" አገሪቱን በሃይማኖት ፣ በጐሣና በዘር ተከፋፍሎ ፣ በመርከከር ፣ እርስ በርሱ ከሚተራረደው ወገን እጅ በማውጣት አንድ ብሔራዊ መንግሥት እንደሚመሠርት ፣ እንደአዲሱ የኢራቅ መንግሥት አካል አድርጐ ራሱን ይመለከት ነበር ። እንደዚህ ትተራመስ በነበረችው የዓለም ክፍል ነበር ማዳም የተወለዱት ።

የማዳም ሑሴን የልጅነት ታሪክ ግልጽ አይደለም ። ይፋ ግለ ታሪካቸው ስለልጅነት ጊዜ ታሪካቸው የሰጠው ትንተና በቂ አይደለም ። ማዳም በልጅነታቸው ያሳለፉት ጭካኔ የተመላበት ፣ የታሪካቸው መጥፎ ገጽታ እንዲታወቅ አይፈልጉም ። ሁልጊዜ እንደሚባለው ፣ የማዳም አባት ሑሴን አልመጂድ የሞቱት ማዳም ከመወለዳቸው በፊት ወይንም ደግሞ ፣ ማዳም ከተወለዱ ከጥቂት ወራት በኋላ ነው ። ግን የማዳም የግል ጸሐፊ የነበረ ሰው በሰጠው አስተያየት አባትየው ሚስታቸውንና ሕፃናት ልጆቻቸውን በመተው ኮብልለዋል ። ዕውነቱ የትኛው እንደሆነ ባይታወቅም ፣ ባልየው ከሄዱ በኋላ ፣ የማዳም እናት ሱብሀ ፣ ባለትዳሩን ኢብራሂም ሐሰንን እስካገቡ ድረስ በብቸኝነት ኖረዋል ። ከጥቂት ጊዜ በኋላም ኢብራሂም ሚስታቸውን ፈተው እንዲያገቧቸው አግባብተዋል ። በእስል



ምና ሕግ መሠረት ኢብራሂም አራት ሚስት እንዲያገቡ ቢፈቀድላቸውም ሱብሀ በእሳቸው ብቻ እንዲወሰኑ አድርገዋቸዋል ።

እንጀራ አባቴ ጨካኝና ያልተማሩ ገበሬ ስለነበሩ ማዳምን በማንገላታት አሰቃይተውታል ። ስለዚህ ሁናቴ ፣ ማዳም ከብዙ ዓመታት በኋላ በምሬት ሲናገሩ ፣ የእንጀራ አባታቸው ጧት በማለዳ ይነሡና ከአልጋቸው ጐትተው በማውረድ ፣ አጥንት የሚሰብር ስድብ አስቀድመው ፣ በመቀጠል "ተነሥተህ በጐቹን ጠብቅ ።" እያሉ በመጮኽ ሲያስታዩዋቸው እንደነበር ያወሳሉ ። ኢብራሂም በማዳም ምክንያት ከሱብሀ ጋር በመጨቃጨቅ ፣ "እኔ አልፈልገውም" እያሉ ያማርሩ ነበር ። የማዳም አጐት ልጅ ፣ በኋላ የኢራቅ መከላከያ ሚኒስትር የሆኑት አድናን ኼይራላህ ትምህርት ቤት ሲገቡ ፣ ማዳምም አብረዋቸው መግባት ፈለጉ ። ነገር ግን ኢብራሂም "ልጁን ማስተማር አያስፈልግም ፣ እንዲያውም ቤት እየዋለ በጐቹን መጠበቅ አለበት" አሉ ። ሆኖም በመጨረሻ ማዳም አሸንፉና በ1939 ዓሥር ዓመት ሲሆናቸው ትምህርት ቤት ገቡ ።

ማዳም ወደ አድናን አባት ወደ ኼይራላህ ቱልፋህ ሄደው እዚያ መኖር ጀመሩ ። ኼይራላህ ቱልፋህ የእናታቸው ወንድም አጐታቸው ናቸው ። ባግዳድ ውስጥ አስተማሪ ነበሩ ። በ1933 ኼይራላህ ናዚን በሚደግፍ የመንግሥት ግልበጣ ሴራ ውስጥ በመግባታቸው ከኢራቅ ጦር ኃይል ተባረዋል ። የመንግሥት ግልበጣ ሙከራውን ያከሸፈው የብሪታንያ ጦር ስለነበር ኼይራላህ በብሪታንያና "በኢምፔሪያሊዝም" ላይ ሥር የሰደደ ጥላቻ አደረባቸው ። ማዳም ወደአጐታቸው ቤት ወደባግዳድ የሄዱት የእንጀራ አባታቸው ከቤታቸው ስላባረሯቸው ይሁን ወይም በራሳቸው አነሣሽነት እንደሆነ ግልጽ አይደለም ። በኋላ የባግዳድ ከንቲባ የሆኑት ኼይራላህ በማዳም አስተሳሰብ ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ለማሳደር መብቃታቸው ግን እርግጥ ነው ።

ማዳም ፣ ኼይራላህ ዘንድ ለመኖር ከሄዱ በኋላ ፣ የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ጀምረው ፣ የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ፈጸሙ ። እንደ አጐታቸውም የጦር መኰንን ለመሆን ፈልገው ነበር ፣ ዳሩ ግን የነበራቸው ዝቅተኛ ነጥብ ወደታወቀው የባግዳድ ወታደራዊ አካዳሚ ከመግባት አገዳቸው ። በዓሥራ ዘጠኝ አርባዎቹና በዓሥራ ዘጠኝ ሃምሳዎቹ ውስጥ በመንግሥት ግልበጣ ሥልጣን ከያዙት የዓረብ መሪዎች ትውልድ ውስጥ ፣ ወታደራዊ የሥራ ልምድ ያልነበራቸው

ሳዳም ሑሴን ብቻ ነበሩ ። ምንም እንኳ ይፋው ግለ ታሪካቸው ፣ የጠመንጃ ፍቅር ያደረባቸው ዓሥር ዓመት ከሞላቸው ጀምር መሆኑን ቢያመለክትም ፣ በ1969 ራሳቸውን ሌተና ጄኔራል (ከጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ጋር የሚስተካከል ማዕረግ) በመሾም ምኞታቸውን አሟልተዋል ። በ1972 ፣ ሳዳም ፕሬዚዳንት ሆኑ ። አሁንም ራሳቸውን ወደ ፊልድ ማርሻል ማዕረግ ከፍ አድርገው በመሾም ከኢራን ጋር ሲካሄድ የነበረውን ጦርነት ይመራሉ ።

ባግዳድ ፣ ሳዳም ከመጡበት አልኡጃ ከነበረው ዓለም ፈጽሞ የተለየች ነበረች ፣ ቢሆንም ሳዳም ከታክሪቲዎች ጋር ይኖሩ ነበር ። የኼይራላህ መኖሪያ ቤት ይገኝ የነበረው ከጤግሮስ ወንዝ ዳርቻ በስተምዕራብ ፣ አልካርካህ በሚባለው የታክሪት ወረዳ በአብዛኛው ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የነበራቸው ታክሪቲዎች የሚኖሩበት ሠፈር ነበር ። እንደአብዛኛው የመካከለኛው ምሥራቅ ከተማ ሁሉ በባግዳድም ከአንድ አካባቢ የመጡ ገበሬዎች ከተማ ሲገቡ በመረዳዳትና የገጠሩን የዝምድና ግንኙነት እንደያዙ በአንድ አካባቢ በጉርብትና አንድ ላይ የመኖር አዝማሚያ አላቸው ።

ሳዳም ባግዳድ ውስጥ ተማሪ በነበሩበት ጊዜ ፣ ወቅቱ ያልተለመደ የመታወክና ያለመረጋጋት ሁናቴ የበዛበት ነበር ። በ1944 ሌተና ኰሎኔል ጀማል አብደል ናስር መፈንቅለ መንግሥት በመምራት የግብጽን የዘውድ አገዛዝ ገረሰሱ ። ቀደም ብሎ አሜሪካ የግብጹን መሪ ናስርን በጣም ብትደግፍም ወዲያው ናስር ከምዕራቡ ዓለም ጋር ተጋጩ ። በ1947 ናስር ከሶቪየት ኅብረት ብዙ ጦር መሣሪያ በመግዛታቸውና በ1948 የስዊዝ ቦይ በኃይል በመያዝ ብሔራዊ ንብረት እንዲሆን በመውረሳቸው በዚያው ዓመት ፈረንሣይ ፣ ብሪታንያና እሥራኤል ግብጽን እንዲያጠቁ አደረገ ። ጦርነቱ ሲቆም ፣ እሥራኤል ከሲና በረሀ እንድትወጣ ስትገደድና የስዊዝ ቦይ ተመልሶ በግብጽ ቁጥጥር ሥር ሲውል ፣ አብዛኛው ግብጻዊ ፣ በእርግጥም አብዛኛው ዓረብ ፣ በናስር አማካይነት የዓረብ ብሔረተኛነት ፣ ከፍተኛ ድል መቀዳጀቱን አመነ ። ለዚህ ውጤት አሜሪካ ብቻዋን ተጠያቂ ነበረች ፣ አድራጐቷ ናስር በዓረቦች ዘንድ የነበራቸውን ገደብ የለሽ ተወዳጅነት አልቀነሰውምና ።

ሳዳም ፣ ወዲያውኑ ከአሰልቺው ከትምህርት ይልቅ ወደሚያባብለውና ወደሚስበው የፖለቲካ ዱለታ ዓለም ውስጥ ጭልጥ ብለው ገቡ ።



በ1948 በባግዳዱ የዘውድ አገዛዝ ላይ ተሰንዝሮ በከሸፈው መፈንቅለ መንግሥት ተሳተፉ ። በቀጣዩ ዓመት በሃያ ዓመት ዕድሜያቸው ፣ በመላው የዓረብ ዓለም ካንሰራፉት እያሌ ለውጥ ፈላጊ ብሔርተኛ ድርጅቶች መካከል የአንዱ የባዓዝ ፓርቲ አባል ሆኑ ። ግን በዚያን ጊዜ ፣ ኢራቅ ውስጥ የነበረው ባዓዝ ከሌላው ሲተያይ በጣም አነስተኛ ፣ ሦስት መቶ ፣ አባላት ያሉት ዐቅመ ቢስ ቡድን ነበር ።

በ1950 የባዓዝ አባል ያልሆኑ ብሔረተኛ የጦር መኰንኖች በጄኔራል አብዱል ካሪም ቃሲም መሪነት ዳግማዊ ፈይሳልን በተሳካ ሁኔታ ገረሰሱ ። የዘውድ አገዛዙ መወገድ በመከፋፈል እርስ በርሳቸው በሚፎካከሩት የኢራቅ አንጃዎች መካከል የነበረውን አድማ አባባሰው ። ቃሲም መንግሥት በገለበጡ በዓመቱ ባዓዞች በቃሲም መኪና ላይ ቀን በቀን የአውቶማቲክ ጠመንጃ ተኩስ በመክፈት ሥልጣን ለመያዝ ሞከሩ ። ያን ጊዜ ሳዳም (የስማቸው ትርጉም "ተጋፋጩ") የተኩስ ከፋቹ ቡድን አባል ነበሩ ። ቀደም ሲል ሳዳም ጉብዝናቸውን ወይንም ደግሞ በአሜሪካ ኅቡዕ የወንበዴዎች ዓለም አነጋገር ፣ "ልባቸው መደንደኑን" አስመስክረዋል ። ታክሪት ውስጥ የቃሲምን ኰሙኒስት ደጋፊ በመግደል አሳይተዋል ። ኰሙኒስቶች ፣ የባዓዝ ጠንካራ ባላንጣ ነበሩ — እንደ ዕውነቱ ከሆነ ሳዳም የገደሉት ፣ የአጎታቸውን ባል ነበር ። በቤተሰቡ መኻል የፖለቲካ ግጭት ተፈጥሮ ነበርና አጐታቸው ኼይራላህ ሰውየውን እንዲገድሉ አንግቢቸው ። ሳዳምና ኼይራላህ ቢታሠሩም ወዲያው ተፈቱ ። የዘውድ አገዛዝ ከተገረሰሰ በኋላ ባግዳድ ውስጥ ሕግና ተይዘው ሥርዓት በመፍረሱ ግርግር ተንሥቶ ነበር ፣ የፖለቲካ ወንጀሎች በየቦታው እየተፈጸሙ ፣ በአብዛኛው ያለቅጣት በቸልታ ይታለፉ ነበር ።

የኢራቅ ፕሮፓጋንዳ ፣ ቃሲምን ለመግደል በተሠነዘረው ሙከራ ሳዳም የነበራቸውን ሚና ፣ ውሸት በመጨመር ፣ አጋና ደፋርና ጀግና አስመስሎ ያቀርባቸዋል ። እንደተባለው ጥቃት በተፈጸመበት ጊዜ በጥይት ተመተው በጣም ይቆስሉና የደም አበላ ይወርዳቸዋል ። ከዚያም ጓደኛቸው እግራቸው ውስጥ የቀረውን ጥይት በቢላ ምላጭ በጥቶ እንዲያወጣላቸው ያዙታል ፣ ቀዶ ሕክምናውም በጣም የሚያስቀይ ስለነበር ራሳቸውን ስተው ይወድቃሉ ። በመጨረሻም ራሳቸውን ዘላን በረኸኛ ጉሣ በማስመሰል ፣ የጤግሮስን ወንዝ በዋና ከተሻገሩ በኋላ ፣

ራሳቸውን ለማዳን ፤ በአህያ ጀርባ ጅው ያለውን በረሀ በማቋረጥ ወደ ሶርያ ይሸሻሉ ።

ዕውነተኛው ታሪክ ግን እስከዚህም የሚደንቅ አይደለም ፤ ባልተሳካው የግድያ ሙከራ ውስጥ ሣዳም የነበራቸው ሚና አነስተኛ እንደነበር በጊዜው የተጠናቀረው መረጃ ያስረዳል ። ቁስላቸው መጠነኛ ሲሆን ያቆሰላቸውም የገዛ ጓደኞቻቸው በስሕተት ተኩሰባቸው ነበር ። አንድ የፓርቲው ደጋፊ ዶክተር እሳቸውንና ሌሎች በጣም የተጐዱ ብዙ ሰዎችን በፓርቲው ምስጢራዊ ቦታ ውስጥ አክመዋቸዋል ። ሣዳምም ዶክተሩ ላደረጉላቸው እርዳታ በኋላ ውለታ ለመመለስ እድል አግኝተዋል። በ1960 መጨረሻ የባዓዝ ፓርቲ ተሳክቶለት ሥልጣን ሲይዝ ዶክተሩ የባግዳድ ዩኒቨርሲቲ ሕክምና ኮሌጅ ዲን ሆነው ተሹመዋል ፤ ይህንንም ሥልጣን ከሣዳም ጋር እስኪተጣሉበት እስከ 1971 ድረስ እንደያዙ ቆይተዋል ።

ሣዳም ከሶርያ ወደ ካይሮ በመሄድ አራት ዓመት ኖሩ ፤ በግብጽ የቆዩበት ጊዜ ሌላው ተጨማሪ የውጭ አገር የመኖር ልምዳቸው ነበር ። የግብጽ መንግሥት በሚሰጣቸው የኪስ ገንዘብ በመረዳት ሣዳም የፖለቲካ ተግባራቸውን ቀጠሉ ፤ በመጨረሻም በሃያ አራት ዓመት ዕድሜያቸው ፤ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀቁ ። ካይሮ ውስጥ ሁለት ጊዜ ታሥረው ፤ ሁለቱንም ጊዜ ቶሎ ተለቀዋል ። መጀመሪያ ለመታሠር ያበቃቸው በፖለቲካ ልዩነት ሰበብ አንድ የአገራቸውን የኢራቅ ሰው ለመግደል መዛታቸው ነው ። ለሁለተኛ ጊዜ ፤ ሊያሣሥራቸው የቻለው ደግሞ እንደእርሳቸው የባዓዝ ፓርቲ አባል የነበር ሶርያዊ ተማሪ ጓደኛቸውን ለመውጋት ጩቤ መዘው በካይሮ ጐዳናዎች ስላባረሩት ነበር።

ተባራሪው ተማሪ በኋላ የዮርዳኖስ ማስታወቂያ ሚኒስትር እስከመሆን ደርሰዋል ።

በ1956 ፣ ሣዳም ለመማር ካይሮ ዩኒቨርሲቲ ገቡ ። ከጊዜ በኋላ በባግዳድ በ1962 የአገራቸው መንግሥት ሁለተኛ ባለሥልጣን ከሆኑ በኋላ በሕግ የክብር ዲግሪ ተቀብለዋል ።

በ1955 ሣዳም ካይሮ ውስጥ ይኖሩ በነበሩበት ጊዜ ፤ የአጐታቸውን የኼይሩላህን ልጅ ሳጂዳን አገቡ ። ግብጽ ውስጥ ትምህርታቸውን ያቋረጡት በድንገት በየካቲት 1955 የባዓዝ ፓርቲ ጦር መኰንኖች



በሌሎች ዓረብ ብሔርተኛ መኰንኖች ቡድን ጋር በመተባበር ፤ ጀኔራል ቃሲምን ገልብጠው ከገደሏቸው በኋላ ነው ። ቃሲም ፤ በተለይ በተራው የኢራቅ ሕዝብ ከፍተኛ ተወዳጅነት የነበራቸው መሪ ነበሩ ። ስለቃሲም ፤ ሃና ባታቱ የተባሉት እምነት የሚጣልባቸው ፤ ትክክለኛ የኢራቅ ታሪክ ጸሐፊ እንዳሉት "በኢራቅ ዘመናዊ ታሪክ ውስጥ ከነበሩት ገዢዎች ሁሉ ይበልጥ ፤ ሕዝቡ በዕውነት የሚያፈቅረው ቃሲምን ብቻ ነበር ።"

አብዛኛው ሕዝብ የቃሲምን መሞት አላመነም ፤ አምልጠው እንደተደበቁና በቅርብ ጊዜ ውስጥ እንደሚወጡ ፤ ወሬ ተሰራጨ ፤ በዚህ ጊዜ የባዓዝ ፓርቲ አባላት ቃሲም እንደሞቱ የሚያስረዳ ሙሾ ዓይነት ትርኢት በቴሌቪዥን አቀረቡ ። በጥይት የተበሳሳውን ፤ የቃሲምን ሬሳ ፤ በተከታታይ በየምሽቱ አሳዩ ። ሰሚር አልኸሊል "ሪፑብሊክ ኦቭ ፊር" በተባለው የላቀ መጽሐፋቸው ስለቴሌቪዥን ትርኢት ሲናገሩ "ስቱዲዮው ውስጥ ሬሳው እንደ መድረክ ዕቃ በወንበር ላይ ተቀምጧል ፤ አንድ ወታደር ከሬሳው ቁርጥራጭ አካል አንዱን ይዞ ሲንጐራደድ ያሳይና ፤ ካሜራው በማቋረጥ ፤ ቃሲም የመጨረሻ መቋቋም ያደረጉበትን ፤ በጦር መሣሪያ የፈራረሰውን የመከላከያ ሚኒስቴሩን ሕንፃ አካባቢና የተቆራረጠውን የቃሲምን ተከታዮች (የአልማህዳዊን ፤ የጥሰፋ ጣሂርንና የሌሎችንም) ሬሣ ያሳያል ። እንደገና ካሜራው ወደ ስቱዲዮው በመመለስ ፤ በቃሲም ሬሣ ላይ ጥይት የገባበትንና የወጣበትን ሽንቁር ፤ በቅርበት ያሳያል ። ሙሾ ዓይነቱ ትርኢት የሚያልቀው በተመልካቾች ዘንድ ለዘለዓለም ተቀርጾ በሚቀር ሁናቴ ነው ። ወታደሩ የሚቀባበሰውን ጭንቅላት ፀጉር ጨምድዶ ይዞ ፤ እፊቱ ላይ ምራቁን ሲተፋበት በጣም አቅርቦና አግዝፎ በማሳየት ይዘጋል ።"

ሣዳም ይህን ሲሰሙ በጣም ተደሰቱ ። በእመጹ ውስጥ ተሳትፎቸውን ለመቀጠል ተጣድፈው ወደ ባግዳድ ተመለሱ ። ያን ጊዜ ዕድሜያቸው ሃያ ስድስት ዓመት ነበር ።

ሣዳም በአዲሱ መንግሥት ውስጥ ወዲያው ሥራ ያዙ ። በቃሳር አልኒሃያህ ወይም በ"ፍጻሜው ቤተመንግሥት" ውስጥ መርማሪና ገራፊ ሆኑ ። "የፍጻሜው ቤተመንግሥት" መባሉ በ1942 ንጉሥ ፈይሳልና ቤተሰባቸው የተረሸኑበት ቤተመንግሥት ስለ ነበር ነው። በባዓዝ ፓርቲ አመራር ሥር ቤተ መንግሥቱ ሰውን ማሰቃያና መግረፊያ ክፍል በመሆን አገልግሏል ።

በተጠቀሰው ቤተመንግሥት ውስጥ የግዳምን ተግባር የሚያውቁ ምዕራባውያን ጥቂት ናቸው ። ነገር ግን በባዓዝ ፓርቲ ላይ አሲሯል ተብሎ የታሰረ አንድ ኢራቃዊ በዚያው ቤተመንግሥት ውስጥ በግዳም እጅ የደረሰበትን ስቃይ ሲናገር ፡ "እጅና እግሬ በገመድ ከተጠፈረ በኋላ በታሠርኩበት ገመድ በጣራው ላይ ከተንጠለጠለው ሜንጦ ላይ ተሰቀልኩ ። ከዚያም ጠጠር በተሞላበት የአትክልት ማጠጫ ጐማ ፡ በተደጋጋሚ ተገረፍኩ ።" ብሏል ። ይህም ሰው በአጋጣሚ በሕይወት ለመትረፍ ችሏል ፡ ሌሎች ግን እንደሱ አልታደሉም ። የባዓዝ ፓርቲ በውስጥ ቅራኔው ሳቢያ ስለተከፋፈለ ፡ ሥልጣን በያዘ በዘጠኝ ወሩ ፡ በኅዳር 1955 በጦር ኃይሉ ሲገለበጥ ፡ "በአልኒሃያህ ቤተመንግሥት ምድር ቤት ውስጥ" አስደንጋጭ አስፈሪ ነገር ተገኘ ። ሃና ባታቱ ፡ የመንግሥትን ይፋ ዜና ምንጮች መሠረት በማድረግ በጻፉት ታሪክ ውስጥ እንዳሉት ፡ "ሁሉም ዓይነት አስፈሪ ፡ ሰውን ማሰቃያ መሣሪያ ተገኝቷል ፡ ከዚህም ውስጥ የኤሌክትሪክ ሽቦዎች እስከ መቆንጠጫቸው ፡ እሥረኞች ተገደው የሚቀመጡባቸው የሾሉ የብረት ችካሎችና የጣት መቁረጫ ማሽን እስከነተቆረጠበት ምልክት ፡ እዚያና እዚህ ተበታትኖ የተቆለለ በደም የተነከረ ልብስ ፡ እንዲሁም እወለሉ ላይ ደም የሚጠራቀምበት ጉድጓድና ደም የተቀባ ግድግዳ ።" ይገኛል ።

በ1955 ፓርቲው ሲከፋፈል ፡ ግዳም ድጋፋቸውን የሰጡት በፈረንሳይ ለተማሩት ዕርያሚ ፡ የፓርቲው ተቀዳሚ የርእዮተዓለም መሪና ተባባሪ መሥራች ለሚሸል ዓፍለቅ ነበር ። በቀጣዩ ዓመት ግዳም ለሰጡት ድጋፍ ወሮታ ፡ ሚሸል ዓፍለቅ ኢራቅ ውስጥ የፓርቲው ከፍተኛ የአመራር ቦታ የሆነውን የቀጠና አዛዥነት ቦታ ሾሟቸው ። ግዳም ይህን ሹመት ካገኙ በኋላ ፡ በፓርቲው ውስጥ በፍጥነት ማደግ ጀመሩ ።

ለግዳም እያደጉና እየታወቁ መሄድ አስተዋፅኦ ያደረገው ደግሞ የትልቁ አጐታቸው የጄኔራል አህመድ ሐሰን አልባክር ድጋፍ ነው ። ጄኔራሉ በፓርቲው የተከበሩ ፡ ልውቅ የጦር ሰው ነበሩ ። ከፓርቲው መሥራች አባላት አንዱ ናቸው ። የግዳም ባለቤት ባክርንና ባለቤታቸውን ይበልጥ በማቀራረብ አግዘዋል ። ሁለት የባክር ወንድ ልጆች ሁለቱን እኅቶቻቸውን እንዲያገቡ በማግባባትና ጋብቻውን በማስፋፋት የባክርን ሁለት ሴት ልጆች ሁለቱ ወንድሞቻቸው እንዲያገቡ በማድረግ የግዳም ባለቤት ትልቅ ሚና ተጫውተዋል ። ከዚህ በኋላ የፓርቲው ጉዳይ



በፍጥነት የቤተሰብ ሥራ እየሆነ ሄደ ። በ1957 ባክር የፓርቲው ዋና ጸሐፊ ሆኑ ። በቀጣዩ ዓመት ግዳም በፓርቲው ውስጥ የምክትል ዋና ጸሐፊነቱን ቦታ ያዙ ።

ግዳም በፓርቲው የሥልጣን ደረጃ ላይ መውጣት በጀመሩበት ወቅት ለአጭር ጊዜ እሥር ቤት ገብተው ነበር ፡ ከጥቅምት 1956 ጀምሮ ከእሥር ቤት እስካመለጡበት እስከ 1958 ገደማ ታሥሩ ። በነዚህ ጊዜያት ውስጥ ግዳም በኋላ እንደተረኩት በእሥራት ዘመናቸው ፓርቲውን ተከፋፍሎ ከሥልጣን ለመወገድ ያበቃውን ስሕተት አጡኑ ። እንዲሁም ፡ "የ1955 እመጽ" የቀኝ ክንፍ ወታደራዊ የበላይ መኰንኖች ከባዓዝ ፓርቲ ከሀዲ አባሎች ጋር ኅብረት በመፍጠር ፓርቲያቸው ሥልጣን መቀማቱን አመኑበት ። በዚያን ጊዜ ፡ ከአንድ ሺ በታች ሙሉ አባላት ብቻ የነበሩት ባዓዝ ፓርቲ ዳግም መከፋፈል እንደሌለበት ተገነዘቡ ። አባላትን በማባረርም ሆነ በመግደል ፡ የተከፈለው ዋጋ ተከፍሎ ፡ አንድነት መከበር እንዳለበት ፡ አንድነት ደግሞ ለሥልጣን አስፈላጊ እንደሆነ ተረዱ ። ከዚህ በኋላ ግዳም በፓርቲው ውስጥ ታማኝ ክፍሎችን ለመፍጠርና የተገኘው ድል መጠበቁን ለማረጋገጥ ፡ ተጠሪነቱ ለእርሳቸው ብቻ የሆነ ፡ የደኅንነት ኃይል በፓርቲው ውስጥ ለመዘርጋትና ለማደራጀት ቆርጠው ተነሡ ።

ከእሥር ቤት ካመለጡ በኋላ ግዳም ፈጥነው የፓርቲውን ውስጣዊ የደኅንነት አውታር "ጂሃዝ ሃኒን" ወይም "የወንድማማችነት መሣሪያ" በማደራጀት የፓርቲውን ጠላቶች ለመግደል ፡ ተቀናቃኝ እንጃዎችን ደግሞ ለማስፈራራት ተነሡ ። ግዳም በሽብር ስልትና እቅድ አውጭነት ታዋቂነታቸው እየጨመረ ሄደ ።

ከሁለት ዓመት በኋላ በነሐሴ 1960 ግዳምና የባዓዝ ፓርቲ አባል ጓደኞቻቸው የመንግሥት ሥልጣን ለመያዝ በቁ ። ባክር ፡ ከባዓዝ ፓርቲ ዋና ጸሐፊነትና ከለውጡ የበላይ እዝ ምክር ቤት ሊቀመንበርነት በተጨማሪ ፕሬዚዳንትና የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ሆኑ ። እንዲሁም ግዳም ፡ የውስጥ ደኅንነት ኃላፊና የምክር ቤቱ ምክትል ሊቀመንበር ሆኑ። በፓርቲው ውስጥ ያላቸውን ድጋፍ ለማስፋት ፡ ለማጠናከርና ለመቆጣጠር ፈጥነው እንቅስቃሴ ጀመሩ ። የደኅንነቱ አገልግሎት በምስጢር አንድ መቶ የግዳም ደጋፊዎች አስመረቀ ። ከነዚህም መካከል የግዳም ወንድሞች ፡ ባርዛን ፡ ሳባዊና ዋዝባን ይገኛሉ ። ሌላው ተመራቂ ደግሞ

አጐታቸው አሊ ሐሰን አልመጂድ ነበሩ ። እርሳቸው ከብዙ ዓመት በኋላ በኢራቅና በኢራን ጦርነት ጊዜ ፡ ኩርዶችን በመጨቆንና ገሌ ከገሌ ሳይሉ በመጨፍጨፍ ፡ እንዲሁም በኩዌት ወረራ ግንባር ቀደም ሚና በመጫወት ይታወቃሉ ከነዚህ ሌላው ተመራቂ አርሻድ ያሲን ፡ አጐታቸውና አማቻቸውና ናቸው ። እርሳቸውም በኋላ ስትዋር ሎከውድ የተባለው ወጣት እንግሊዛዊ "እንግዳ" ስለአገሩ ቅንጦት እንዲነግራቸው ለማድረግ ሣዳም እየሞከሩ ሳለ "ተናገር!" እያሉ ጭንቅላቱን በመደጋገም በመኮርኮማቸው በዓለም የታወቁ አንጋች ናቸው ።

ሣዳም በሠላሳ አንድ ዓመት ዕድሜያቸው እንኳ በነበራቸው ክብረ ሥልጣናቸውን የማረጋገጥ ዝንባሌ የታወቁ ነበሩ ፡ ዛሬ ስድሳ የማዕረግ ስም አላቸው ። ያንጊዜ ፡ "የተከበሩ ምክትል' ተብዬ መጠራት አለብኝ" ስላሉ ፡ በዚያው ይጠሩ ነበር ። ከሳቸው በስተቀር ኢራቅ ውስጥ በዚህ ማዕረግ የሚጠራ ሰው ፈጽሞ የለም ። ምንም እንኳ ፡ "የተከበሩ ምክትል" እየተባሉ በመጠራት ዓሥር ዓመት ቢቆዩም ከነበረው መንግሥት ባለሥልጣኖች ሁሉ የሚፈሩ ኃይለኛ ባለሥልጣን እሳቸው ብቻ መሆናቸው ይበልጥ እየታወቀ ሄደ ።

ብዙ ሳይቆይ የአዲሱ መንግሥት ምንነት ታወቀ ። ከመንግሥት ግልበጣው በኋላ ሦስት ወር ባልሞላው ጊዜ ውስጥ አዲሱ መንግሥት የጽዮናውያን ከፍተኛ የስለላ መረብ ተበጣጥሶ እንደተደመሰሰ በጥቅምት 1960 አስታወቀ ። በጥር 1961 ዓሥራ ሰባት "ሰላዮች" ለፍርድ ቀርበው ዓሥራ አራቱ በስቅላት ተቀጡ ። ከነዚህም ውስጥ ዓሥራ አንዱ አይሁድ ነበሩ ። ስቅላቱ የተፈጸመው ባግዳድ ውስጥ በነፃነት አደባባይ ብዙ መቶ ሺ ሕዝብ በተገኘበት ነበር ። አስከሬናቸው ተንጠልጥሎ እየተወዛወዘ ፡ ለመቀጣጫ ለብዙ ጊዜ እንዲታይ ተደረገ ። "አልአህራም" የተባለው የግብጽ ጋዜጣ ሳይቀር ፡ የዓሥራ አራቱ ሰዎች በአደባባይ መሰቀል የሚያስደስት ትርኢት ወይም ለበዓል ማክበሪያ ምክንያት መሆን እንደሌለበት በመተቸት የዓለም ጋዜጦች አወገዙ ። የባግዳድ ሬዲዮም አንዳችም ነገር ባለማድረጉ ፡ በሚያሳፍረው በዓለም አቀፍ ውግዘት ላይ "እኛ የሰቀልነው ሰላዮችን ነው ፡ ነገር ግን አይሁድ ክርስቶስን በመስቀል ላይ ሰቀሉት" በማለት አፌዘ ። ከአንድ ዓመት ተመንፈቅ በኋላ ደግሞ "የከሀድትን ጉንጉን ተረተርነው" ተባለና የማያቋርጥ የውግዘትና የግድያ ትርኢት ተከተለ ። ሰለባዎቹ እንደቀድሞው አይሁድ አይደሉም ፡



ጥቂት እንኳ ሳይቆይ በአብዛኛው እስላሞች ሆነዋል ፡ አዲሱ መንግሥት የፖለቲካ ተቀናቃኞቹን ለማጥፋት የነበረውን ዕውነተኛ እቅድ ሥራ ላይ ለማዋል አይሁድን እንደሰበብ ተጠቅሞባቸዋል ። የባዓዝ ፓርቲ አገዛዙን ደም በማፍሰስ ጀመረ።

የተከበሩት የግብጽ ምሁር ሰዓድ አህዲን ኢብራሂም እንደዚህ ያሉትን ገዥዎች በኋላ "የሪፑብሊክን ካባ የደረቡ አዳዲስ ነገሥት" በማለት ሰይመዋቸዋል ። አዳዲሶቹ የኢብራሂም "ፍጹም ለውጥ ፈላጊ መሪዎች "ትውልድ ሥልጣን ላይ ሲወጡ ፡ የዓረብን ኅብረተሰብ ወደተሻለ የኑሮ ደረጃ ለማሸጋገር የገቡትን ቃል ባለማክበራቸው የደረሰባቸውን ውድቀት ሲደመድሙ ፡ "የፖለቲካ ፓርቲ ቢኖርም ፡ ሕዝባዊ ኮሚቴ ቢኖርም ፡ ፕሬዚዳንቱ ከሕዝቡ መኻል አንዱ ነኝ ቢሉም ፡... ገዢው የተጠቀሱትንም ነገሮች ሆነ ፡ ወይንም ብዙ ዓመት አብረውት የታገሉትን ጓደኞቹን ካንጀቱ አያምንም ። ሊያምን የሚችለው አንደኛ ፡ የቤተሰቡን አባላት ፡ ሁለተኛ ጐሳውን ፡ ሦስተኛ የሚያምንበትን የእስልምና ዘርፍ ብቻ ነው ። ስለዚህ ያለንበት ጊዜ ፡ በዓረብ አገሮች አዳዲስ ነገሥታት የበቀሉበት ነው ።"

"ነገሩ ዘመድ በቁልፍ የሥልጣን እርከን ላይ በማስቀመጥ አልተወሰነም ፡ ነገር ግን የእነዚህ ተጀሚዎች አገሪቱ የግል ርስታቸው እንደሆነች ሁሉ ያሻቸውን ለማድረግ ፡ በሁሉም ረገድ ፡ ማለትም በሕግ ፡ በገንዘብና በሞራል በኩል ያለተጠያቂነት አጉራ ዘለል መሆን ነው ።" ብለዋል ።

ከመነሻው ጀምሮ የሣዳም የሥልጣን መሠረት የደኅንነት አገልግሎቱ ነው ። በእርሱ አማካይነት ፓርቲውን ይቆጣጠራሉ ። ሣዳም ለሥልጣናቸው መሠረት ማጠናከሪያ ከመንግሥት ካዝና ውጪ ገንዘብ ማግኛ ዘዴ ከመጀመሪያው በአዲስ ዓይነት መንገድ ቀይሰዋል ። ምንም እንኳ በእስልምና ቁማር የተከለከለ ቢሆንም ፡ በዘውዱ አገዛዝ ዘመን የፈረስ እሽቅድምድም ተወዳጅ ስፖርት ነበር ። እሽቅድምድሙን ቃሲም አገዱት ፡ ሣዳም እንደገና ፈቀዱት ። በውርርድ ከግልቢያው የሚሰበሰበውን ገንዘብ ፡ ከመንግሥት ካዝና ውጪ እንደተገኘ የግል ምንጭ አድርገው በመጠቀም እንደልብ ያዙበት ገቡ ። ከ1965 በኋላ ፡ የነዳጅ ዘይት ዋጋ በአራት እጥፍ ሲያድግ ግን ፡ በዚያው መጠን የሣዳም የገንዘብ ምንጭም አደገ ። ለፓርቲያቸውና ለደኅንነት አገልግሎታቸው ፡ እጅግ በጣም ጠቀም ያለ ገንዘብ እየመዘዙ በማውጣት በአብዛኛው በውጭ አገር

ባንኮች የማጠራቀሚያ ሒሳብ ማስቀመጥ ጀመሩ ። ይህ የማጠራቀሚያ ሒሳብ ሁሉ ለኩዌት ወረራ እጁ ፤ በተጣለው ዓለም አቀፍ ማዕቀብ ምክንያት ታግዶ ነበር ።

ከ1960 በኋላም ባክር በልክ መኖራቸውን ቢቀጥሉም ፤ ሳዳምና ጓደኞቻቸው በዕውንም ይሁን በዓይነገቢና ዕድሜ ልካቸውን ቢገፉት የኖሩትን የግል ተወራጅነት ወደመለወጡ ያዘነበሉ ነበሩ ። ሳዳም አዲሱን የፖለቲካ ሥልጣናቸውን ለረጅም ጊዜ ሲቋምጡለት የነበረውን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልዕልና ለማግኘት ተጠቀሙበት ። የትግልና የአመፅ ዓመታት ፤ ሥልጣንን ከቀሙት ሕዝብ ይበልጥ በስታምና ራስ ወዳድ አደረጋቸው ። በሥልጣን ለመቆየትም ያላቸው ቁርጠኝነት ይበልጥ አይምሬ አደረጋቸው ፤ እርሳቸውን ለመቀናቀን ፤ ወይንም አገዛዛቸውን ለመፈታተን የሚነሡ የሚመስሏቸውን ሁሉ ለመደምሰስ ይበልጥ ጨካኝ ሆኑ ።

ሳዳምና ጓደኞቻቸው የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ኑሮ ጥቅም አሳዳጅ ሆኑ ። በ1961 የሳዳም ታላቅ ወንድም ባርዛን ፤ የአሊዊያ ክበብ አዲስ ሥራ አስኪያጅ ሆነው ተሾሙ ። አሊዊያ የዘመኑ ቅኝ አገዛዝ ገናና አገር ፤ የብሪታንያ ሉሌዎችን ያጠመደ እያጣቸው የነበረበት ፤ ቀደም ሲልም በዚሁ ምእታመት በኢራቅ የመጀመሪያውን የብሪታንያ የበላይ ገዢ ሰር ፐርሲ ኮክስና ከኤምባሲው የምሥራቅ ጉዳይ ጸሐፊ የነበሩትን ደፋሩን ገርትሩድ ቤልን በመሳሰሉ በታሪክ ዕውቅ ሰዎች ይዘወተር የነበረ ክቡር ክበብ ነው ።

የኢራቅ ዜና ምንጮች እንደገለጹት ፤ የባዝዝ ፓርቲ አባላት በልታይ ባይነት በጣም ውድ በሆነ ልብስ ሽክ ብለው ከሚስቶቻቸው ጋር ወደዚሁ ክበብ በመግባት ይደሰታሉ ። ጊግጊጣቸውንም — ከለበሱት ጋር ማመሳሰል ይወዳሉ ፤ የወንድየውና የቤትየዋ እጅጌ ቁልፍ ፤ እንዲሁም የቤትየዋ ጉትቻ በአንድ ዓይነት ክቡር ድንጋይ የተቀረጹ ናቸው ። ሳዳም አርመን ልብስ ሰፊ ቀጥረዋል ። እሱም ኮታቸውን የሚሰፋው ፤ ከራባታቸው በተሠራበት ዓይነት የሐር ክር ነው ። የሳዳም ኑሮ እያደገ ዘመናዊ እየሆነና እየተራቀቀ ሲሄድ ፤ ልብሶቹን ለማሰፋት አርመኑ ልብስ ሰፊ ወደ አውሮፓ ተላከ ።

ለብሔራዊ አገልግሎት ሲባል ፤ ከተንደላቀቀ ኑሮ ይልቅ ፤ በሥነሥርዓትና በልክ የመኖርን በፓርቲው መንፀባረቅ ያለበት ግዴታ



ሳዳምና በጣም የቅርብ ጓደኞቻቸው በመዘንጋት ፤ ከሕዝቡ ርቀውና ከሚጠበቀው በላይ ሆነው በማናለብኝነታቸው ይበልጥ መታወቅ ጀመሩ። በቤተሰብ ብቻ ስለተወሰነው የግፈያ መስል ታሪካቸውና ቁካኣያቸው ኢራቅ ውስጥ የሚወራው አሉቶ መሥፈርት የለውም ፤ ከድምበር ባሻገር ግን ፤ አልፎ አልፎ ካልሆነ በቀር ፤ ተነሥተው አያውቁም ። ጥቂቱ ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ናቸው ፦

ሳዳም ሁለተኛ ሚስት ከታወቀ የተከበረ የባግዳድ ነጋዴ ቤተሰብ ያገቡበት አንዱ ምክንያት በኅብረተሰቡ ዘንድ ለመከበር ጥልቅ ስሜት እያላቸው ፤ በውስጣቸው ግን ይህንን ክብር በሚገባ ያገኙ መስሎ ስላልተሰማቸው ነው ። ለግላጋና ውቧ ሰሚራ ሻህ ባንዳር ፤ ለመጀመሪያ ጊዜ ከሳዳም ጋር ከመተዋወቃቸው በፊት ፤ ከኢራቁ አየር መንገድ ባለሥልጣን ከኑረዲን አልሳፊ ጋር ተጋብተው ይኖሩ ነበር ። ቢሆንም ፤ ሳዳም እንዲያገቧቸው ፤ አልሳፊ በጥንቃቄ ገለል በማለታቸው የአየር መንገዱ ኩባንያ ሥራ አስኪያጅ ሆነው ተሹመዋል ።

ከጋብቻው በኋላ ፤ ፋሩቅ የሚባል የሻህ ባንዳር ጉሳ አባል በግል መኝታ ቤታቸው ውስጥ የሚሰማቸው የሌለ መስሎት ሰሚራ ትክክለኛ የሻህ ባንዳር ቤተሰብ አባል ያለመሆናቸውንና የአባታቸው ስም ከነጋዴ ዎቹ ቤተሰብ ስም ጋር መመሳሰሉ በአጋጣሚ መሆኑን ለሚስቱ ይነግ ራል። ፋሩቅ በመኝታ ቤቱ ውስጥ ድምፅ መቅረጫ መሣሪያ መጠመዱን አላወቀም ። እሱና ሚስቱ ተይዘው ፤ የዕድሜ ይፍታህ እሥራት ተበይኖባቸው ተጋዙ ። እሁንም እንደተጋዙ ናቸው ።

ሳዳም ፤ ራሳቸውን የሚያሸሟቅቁና ወይም የቤተሰባቸውን አባል የሚያንጓጥጥ ሰው አይታገሡም ። አንድ ጊዜ ሌላው ታክሪቲ ጄኔራል ዑመር አልሃዛዛና ሴት ጓደኞቻቸውን ወደመኖሪያ ቤታቸው ሄደው ሲጠይቋቸው ፤ ከሳዳም እናት አንድ ቀን ተዳርተው እንደነበር በጉራ መልክ ተናገሩ ፤ በቤትየዋ ቤት ላይ ድምፅ መቅረጫ መሣሪያ ተጠምዶ ነበር ። ሳዳም የተቀረፀው የቴፕ ክር ሲደርሳቸው በምስጢር ያንድ አካባቢ ታክሪቲዎችን ሰብስበው ጠርተው የቴፑን ክር አስሟቸው ። አንድ የግድያ ምስክር እንዳለው ሳዳም በግልጽ ሎቸው አለቀሱና ፤ "እንደዚህ ያለውን ሰው ምን እንዳደርገው ትጠብቃላችሁ ?" በማለት ጠየቁ ። መልሱ በቅድሚያ የታወቀ ነው ። ሃዛዛና እና የፕሬዚዳንቱ አንጋች ሙኑጌን ከሆነው ልጃቸው ጋር ተይዘው ተገደሉ ። መኖሪያ ቤታቸው

በዑልዶዘር እንዳልነበር ሆነ ። የጀኔራሉ ቤት ጓደኛም ተገድለው ተሰቀሉ።

ማዳምና እናታቸው ሱባህ ፣ ከአንድ ወንዝ ነው የተቀዱት ፣ ከሰባህ ልጆች አንዷ ባለትዳር ፣ በእርግዝና የተነሣ ከፍተኛ ትኩሳት ሲይዛቸው ወደ እናታቸው ይሄዳሉ ። ከዚያም በታወቁ የግብፅን ሐኪም ወደሚመራው በባግዳድ ውስጥ ወደሚገኝ የሴቶች የግል ሆስፒታል ይወስዳሉ ፣ ዶክተሩ ከመረመሯቸው በኋላ ፣ ብዙ የሆስፒታሉ ሠራተኞች ቆመው በነበሩበት መተላለፊያ ላይ ፣ ሱባህ ሐኪሙን በማስቆም ፣ ጮክ ብለው "አንተ የውሻ ልጅ ፣ ልጄ ትሞትና መስቀያውን እዚሁ ሆስፒታል ፊት ለፊት አስተክዬ ነው የምበቀልህ !" ሲሏቸው ፣ ሐኪሙ ራሳቸውን ስተው ወደቁ ።

የማዳም እኅት ኬራላህ ቁልፋህ ከመጨረሻዎቹ ስግብግብ ታከሪቲዎች መካል ናቸው ። ሀብት ለማካበት የቻሉት የባዝ ፓርቲ ሥልጣን እንደያዘ ብዙም ሳይቆዩ የባግዳድ ከንቲባ ሆነው በመሾም ነበር ። እጅግ ሲበዛ ጉቦኛ በመሆናቸው ማዳም ከሥልጣን ሊያስነሷቸው ተገደዋል ፣ ጻሩ ግን የአገሪቱን ብርቱካን ፣ ሎሚና ትርንጉ ፣...ምርት ከሞላ ጐደል በሞኖፖል ይዘው ስለነበር ከሥልጣን ቢወገዱም ባለብዙ ሀብት ናቸው። ባለመሬቶችን ተመጣጣኝ ያልሆነ ዋጋ በመክፈል ፣ እምቢ ሲሉ በማስገደድ ፣ ብዙ መሬት ቀምተዋል ። በ1973 አንድ መሬቱን የነጠቁት ኢራቃዊ በመናደድ ፣ እከሳለሁ ሲል ፣ ፎከረባቸው ። እድለቢሱ ባለመሬት እንደተናገረው ኬይራላህ በሰውዬው ቶከራ ተገረሙና ግድየለኝም እንደማለት ትከሻቸውን ከፍ ዝቅ በማድረግ "ለምን ጊዜህን ታጠፋለህ ? በሥልጣን ላይ ከቆየን ምንም አታገኝም ፣ ራስክን ብቻ ነው የምትጐዳው ፣ ከሥልጣን ከተወገድን ደግሞ ከሥጋዬ ቅንጣትም አታገኝም ። እኔን ለመቆራረጥ የሚጠባበቁ ብዙ ሰዎች ናቸውና ።" በማለት መለሱለት ።

ኬይራላህ በማስረጃ ባልተደገፈ አስተያየታቸውና ፍርዳቸው የማያፍሩ ፣ ባለጌና ማይም ናቸው ። ለምሳሌ በ1973 የመንግሥቱ ማተሚያ ቤት እሳቸው የጻፉትን አሳፋሪ የፖለቲካ ጽሑፍ ፓምፍሌት አሠራጭቷል ። የጽሑፉ ርእስ "አላህ መፍጠር ያልነበረበት ፈረሳውያን ፣ አይሁድንና ዝንብን" ነው የሚል ሲሆን ኬይራላህ ሲያብራሩ ፣ "ፈረሳውያን — አላህ በሰው አምሳል የፈጠራቸው እንስሳት ናቸው ፣ አይሁድ ደግሞ ፣ የተለያየ ሕዝብ ዝቃጭና ትርፍራፊ ድብልቅ ናቸው ፣ እንዲሁም ዝንብ ፣ ምንነቷን



ማወቅ የሚገድደን እጥኪ ፍጥረት ስትሆን እነዚህን አላህ ለምን ተግባር እንደፈጠራቸው ሊገባን ያልቻለ እንቆቅልሽ ነው" ብለዋል ።

ሌላት ለማዳምና ለቅርብ ምስጢረኞቻቸውና የጥቅም ተካፋዮቻቸው እንደሚል ሁዳድ ትመራለች ። ማዳም የኢኮኖሚ ክፍሉን በቁጥጥር ሥር አውለው እንደልብ እንዲያልቡ ፣ ለቤተሰቦቻቸውና ለቅርብ ጓደኞቻቸው በመስጠት የሀገሪቱን ሀብት ያደላድላሉ ። እኅታቸውና አማቻቸው ሑሴን ካሚል አልመጂድ የወታደራዊው ዕቃ ግዥ ኀላፊ ናቸው ። የዓረብ ዜና ምንጮች እንደዘገቡት ፣ በ1979 አንድ መቶ ሃያ የቻይና ስኩድ ሚሳይል በተገዛበት ጊዜ ፣ ሑሴን ካሚል ለግላቸው "160 ሚሊዮን ዶላር ኮሚሽን" ተቀብለዋል ። ኬይራላህ ፣ እንደሚታወሰው፣ ገንዘብ የሚያጋብሱት ከመሬት ነው ። የማዳም የመጀመሪያ ሚስት የሳጂዳ የገቢ ምንጭ የንግዱ ዘርፍ ነው ። የሃያ ስድስት ዓመቱ የማዳም የበኩር ልጅ ኡዴ በአገር ውስጥ ንግድ የመሰለውን ያለገደብ በማድረግ በንግዱ ዘርፍ ተንሠራፍቶበታል ። ዶሮ እርዶ የሚያሽግ ግዙፍ ፋብሪካ ባለቤት ነው ። የዶሮ ገበያውን በሞኖፖል ከመያዙ ሌላ "ዘ አብዘርቨር" የተባለው ጋዜጣ ባወጣው ጽሑፍ መሠረት አይብ ፣ ዕንቁላልና የከብት ሥጋ ለገበያ ያቀርባል ። ከዚህም በላይ "ዚ ዌቭ" ተብሎ የሚጠራው የአይስ ክሬም ኩባንያም የራሱ ነው ። በ1980 አብዘርቨር እንደተዘገበው መንግሥት የከሰሩትንና የአስተዳደር ጉድለት ያለባቸውንና ብቃት የሚያንሳቸውን መንግሥታዊ ድርጅቶች ለግል ለመስጠት ባደረገው ጥረት ብሔራዊ የሥጋ ኩባንያው ለሽያጭ ቀረበ ። በዚህን ጊዜ ኡዴ ወደ ማእከላዊው ባንክ ተጠባባቂ ገዥ ወደ ሱቢሂ ፋራንኮል ሄዶ በመንግሥት የምንዛሬ ተመን መሠረት አንዱን ዲናር በሦስት ዶላር ሒሳብ በመመንዘር ዓሥር ሚሊዮን ዲናር ከአገር ውጭ ባንክ እንዲያዛውሩለት ነገሩቸው። ፍራንኮልም አገሪቱ የውጭ ምንዛሬ እጥረት እንዳለባት ስለሚያውቁ ጥያቄው ከተለመደው አሠራር ውጭ ሆነባቸውና ማዳምን ጠየቁቸው ። እርሳቸውም "እርግጥ ነው ፣ ያድርግ ፣ ገንዘቡ ነው" አሉ ። ኡዴም ከማእከላዊው ባንክ ካወጣው 30 ሚሊዮን ዶላር ከመንግሥት ይፋ የምንዛሬ ተመን በላይ በዘጠኝ ጊዜ እጥፍ በማግኘት 8.5 ሚሊዮኑን ዶላር በሕገ ወጥ መንገድ ወደዲናር በመመንዘር የሥጋውን ኩባንያ ለመግዛት በቂ ጥሬ ገንዘብ ከማግኘቱም ሌላ ፣ 20 ሚሊዮን ዶላር አተረፈ ።

ኡዲ የንግድ ሥራ ለማካሄድም ሆነ በትልበት ለመጠቀም ዝንባሌው አለው ። በትልበት የመጠቀም ዝንባሌውን ከሚያንፀባርቀው ተግባሩ አንዱ ግሬንጋሜ ፣ የአባቱን ቤት አልባሽ መግደሉ ነው ። ግንፍልንት እንደሚያጠቃው ግንም ደህና አድርጉ ያውቀዋል ። ቀደም ሲል ቤት ልጅ ላይ የሚፈጽመውን ኢሰብአዊ ተግባር የተቃወሙ ሁለት ሰዎች በመግደሉ ፣ "ልቡ መድንደኑን ፣ አስመስክሯል ።" አሁን ደግሞ ቁጣው የሚያርፍባት ተረኛ ለዓመታት ስታበግነው የነበረችው የአባቱ ቤት አልባሽ ነች ። ከግል ሃና ጎጅሉ ለግዳም ብዙ ውለታ ሠርታለች ። ከዚህም ሌላ አግቺ በመሆን ለግዳም ሁለተኛ ዋን ሚስት አስገኝታለች ። ኡዲ ፣ አዲስ የተገኘችው ቤትና አባቱ ከተጋቡ የአባቱን "አልጋ" ለመውረስ እንቅፋት እንዳትሆንበት ፈርቷል ። ኡዲ ለግብጹ ፕሬዚዳንት ባለቤት ለሱዚ መባረክ መስተንግዶ በሚደረገው የራት ግብዣ (ፓርቲ) ላይ ለመበቀል በጥቅምት 1980 ወሰነ ፣ ስለዚህ ነገር የግብዣው አስተናጋጅ የኢራቅ ምክትል ፕሬዚዳንት ጣሀ ሞሂዲን ግእሩፍ በቅድሚያ ቢያውቁም የግዳም ስድአደግ ልጅ እንዳይበቀል ለመከልከል ምንም ሥልጣን አልነበራቸውም ። ከእንጋቾቹ ጋር ግብዣው ሥፍራ እንደደረሰ ግእሩፍን ወደ ጉን ገፍትሮ በግልፍ ጎጅአን በቆመጥ ቀጥቅጦ ገደላት ። ግዳም ስለ አድራጎቱ በሰሙ ጊዜ በጣም መናደዳቸውን ያዩት የመጀመሪያዎቹ ባለቤታቸው ሳጂድ ፣ ወንድማቸውን የመከላከያ ሚኒስትር አድናን ኬይራላህን በመጥራት ፕሬዚዳንቱ ልጃቸውን እንዳይገድሉ ለመገላገል አብቅተዋቸዋል ።

በተፈጠረው ድርጊት መላ ቤተሰቡ በፍርሀት ተዋጠ ፣ ጭንቀቱ ባሰ ውጥረቱ ጨመረ ። በየካቲት 1981 ሀምባጋርው በተነግ በአራተኛው ወር፡ ከፍተኛ የኩዌት ልኡካን ቡድን ወደ ባግዳድ በሄደበት ጊዜ ፣ አድናን ለሕይወታቸው እንደሚያሰጋቸው ለኩዌታውያኑ አዋይተዋቸዋል ። በዚሁ ጊዜ እንደተናገሩት ወታደራዊ የዕቃ ግዢ ሲከናወን አይካፈሉም ። በወታደራዊ መረጃ ስብሰባ ላይም እንዲሁ ። ከዚህ ቀጥሎ "ሪፑብሊካን ጋርድ" በሚባለው ምርጥ ሠራዊት ላይ የነበራቸውን ሠልጣን አጥተዋል ። በተከታዩ ወር የለንደኑ "ዘ—ሳንደይ ታይምስ" አድናን ከሥልጣን ለመባረር ስለመቃረባቸው ጭምጭምታ መኖሩን ዘገበ ። ዳሩ ግን አድናን ከሁለት ወር በኋላ በሄሊኮፕተር አደጋ ሞቱ ።



አድናን የግዳም አጐት ፣ እንዲሁም አሳዳጊ አባት ፣ የኬይራላህ ቱልፋህ ልጅ መሆናቸው መዘንጋት የሌለበት ነው ። ከዚህም በተጨማሪ፣ የግዳም አብሮ አደግና አማች ናቸው ። ግዳም ማንንም አያምንም ። ግዳምን የግብጹ ፕሬዚዳንት ሆስኒ ሙባረክ "ሳይኮፓዝ" (ሰውን በማሰቃየት የሚደሰት ገክ) የሚል ቅጽል ስም እንዳወጡላቸው ሳዑዲዎች ደግሞ "ሳይኮቲክ" (የአእምሮ በሽተኛ) እንዳሏቸው አብረዋቸው ብዙ የቆዩ ሰዎች ያውቃሉ ።

ግዳም አልፎ አልፎ ወደ ውጭ አገር ፣ ወደ አብዛኛው ዓረብ አገር ፣ ሁልጊዜ ስንቃቸውን ምግብ ሳይሰንቁና ለዚያውም እንኳ ቀማሽ ሳያስከትሉ አይሄዱም ። ወንበራቸውን ሳይቀር አስይዘው ይሄዳሉ ይባላል ። ይህም ጠላት ትንሽ መርዛማ ምስማር ወይም መርፌ እወንበሩ መቀመጫ ላይ በምስጢር ሽጦ እንዳይወጋቸው ለመከላከል ነው ። በስብሰባ ወቅት ከመቀመጣቸው በፊት ታማኝ አንጋቾቻቸው ፣ ወንበሩን በፍጥነት ያስተውሉላቸዋል ፣ ስብሰባው ሲያልቅም የቅርብ ረዳታቸው ያነሣዋል ። በዓረብ ተራድኦ ምክር ቤት የካቲት 1982 የመሪዎች ጉባኤ ለአጭር ጊዜ መብራት ጠፋ ። የዓረብ ዜና ምንጮች እንዳሉት ፣ ሕይወታቸውን ለማጥፋት ይሞከር እንደሆን በመፍራት ግዳም ዘለው እጠረጴዛ ሥር ተደበቁ ። በጉባኤው ላይ ከነበሩት አራት መሪዎች ፣ መሬት ይዘው የተገኙት እሳቸው ብቻ ናቸው ።

ግዳም እንግዳ ሲቀበሉም እንደልማዳቸው መጠርጠራቸውን አይተዉም ። በ1978 አንድ የዓረብ የሙያ ማኀበር ልዑካን ቡድን ወደ ባግዳድ ሄዶ ነበር ። ከግዳም ጋር ብዙ ጊዜ የማያጋጥመው ታላ ምልልስ የማድረግ እድል በድንገት ለቡድኑ ተሰጠ ። ከልኡካኑ አንዱ እንደገለጹት ፣ ሁሉም ተገድደው ልብሳቸውን አውልቀው ተፈተሹ ። የድንገቱ ቁጥጥር ገመናን ማሳየት እንደመሆኑ በጣም አሳፋሪ ከመሆኑ የተነሣ አንዲት ሴት መልእክተኛ ድርጊቱን በመቃወም እየጮኹ ከማልቀሳቸውም በላይ ግዳም ፊት መቅረብ እንደማይፈልጉም ገልጸዋል ።

ግዳም ሑሴን እዚህ ለመድረስ ረጅም መንገድ ተጉዘዋል ። ሥልጣን ላይ ለመውጣት ጠንክረው ታግለዋል ። ሥልጣን እንደያዙ መቆየት ቀላል ነገር አይደለም ። ለአደጋ ባለመጋለጥ ብልጠትና ትዕግሥት ፣ አልበገሬነትና ፍላጐት ያስፈልጋል ። እነዚህ ምኞትና ብልሃት ያለው ደካማ ሰው በመጨረሻ ወንጀለኛ ወይም ተራ ሌባ ሆኖ

ያርፈዋል ። ነገር ግን ሣዳም ስለወደፊቱ ዕጣቸው ፈጽመው እምነት አጥተው አያውቁም ። የሚኖሩባትን ዓለም በሙሉ የሚይዝ ሰው መንፈስ አላቸው ። ሥልጣናቸው እየሰፋ በሄደ መጠን ሕልማቸውና አስመሳይነታቸውም ዕውን እየሆነ መጣ ። ሣዳም የጉልዳፋ ገጠሬነት መሠረታቸውን ማመን አለመፈለጋቸው ከመኳንንት ዘር ተወላጅ እንደሆኑ ይናገሩ ዘንድ ገፋፍቷቸዋል ። ለኢራቅ ሕዝብ የቤተሰባቸውን ዘር ሐረግ አቅርበዋል ፤ ይህም ሐረግ ሲመዘዝ ሥሩ ወደ ነቢዩ መሐመድ ይደርሳል ። ሣዳም ሑሴን ሲናገሩ ፤ "የዓረቦች ታላቅነት የሚነሣው ከኢራቅ ታላቅነት ነው ። በታሪክ ውስጥ ኢራቅ ባየለችና በበለጸገች መጠን የዓረብ አገሮች አይለዋል ፤ በልጽገዋል ። ለዚህም ነው ኢራቅን ኃያል ፤ የማትደፈርና የሠለጠነች አገር ለማድረግ የምንጥረው ።" ብለዋል ።

የተመረጠው መንገድ በሰባተኛው ምእታመት ፤ አሁን ኢራቅ የምትባለውን ሲገዙ የነበሩት ፤ አልሐጃጅ በተናገሯቸው ቃላት ውስጥ በትልልቅ ሆሄያት ቁልጭ ብሎ ተጽፎ ተቀምጧል ። ማርሻል ሆጅሰን "ዚ ቬንቸር ኦቭ ኢዝላም" በተሰኘው መጽሐፋቸው ውስጥ የአልሐጃጅን ዘመነ መንግሥት "ግልጽ ሽብር" በማለት ገልጸውታል ። አልሐጃጅ የተናገሯቸው ቃላት በእያንዳንዱ የኢራቅ አዳጊ ወጣት ተማሪ ዘንድ የታወቁ ናቸው ። "ከፊት ለፊቴ ሊቀነጠሱ የደረሱ ጭንቅላቶች ይታዩኛል ፤ የምቀነጥሳቸውም እኔ ራሴ ነኝ ፤ እናም በአንገት ጥምጣሞችና በጢሞቹ መኻል ደም እያንዘባረቀ ሲወርድ ይታየኛል ።"



# ፫
# የሽብር አጥቢያ

የሣዳምን ዘመነ መንግሥት ዓይነተኛ ባሕርይ የአገዛዛቸውን ውስጣዊ ምንነት ሐምሌ 1971 ወደ ፍጹም ሥልጣን ለመውጣት ሳፈሰሱት ደም ከመታጠባቸው ይበልጥ የሚገልጸው የለም ። ሣዳም ከትልቁ አጉታቸው ፤ ከባዓዝ ፓርቲ መሪና ከሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት ከአህመድ ሐሰን አልባክር ጋር ሠምና ወርቅ ሆነው ዓሥራ አንድ ዓመት ሠሩ ። እንዲሁም ፤ ታማኝና ምሕረት የለሽ ምስጢራዊ የፖሊስ ድርጅት ለማቋቋም ፤ ለብዙ ዓመት ጥረዋል ። ይህን ሁሉ ሲያደርጉ ግን ፤ ላይ ላዩን ደህና ቢመስልም ፤ ውስጥ ውስጡን በሣዳም ላይ ችግር እየተፈጠረ ነበር ።

በጥር 1971 ፤ አያቶላ ሮሆላ ኾሚኒ በኢራን ሻህ ላይ የተቀዳጁት ድል ፤ ኢራቅ ውስጥ ያሉትን ፤ ሺዓ እስላሞች አነሣሣ ። ኢራቅ ውስጥ ሺዓ እስላሞች ከአገሪቱ ሕዝብ ኀምሳ አምስት በመቶ ቢሆኑም ፤ አንዳችም የፖለቲካ ሥልጣን አልነበራቸውም ። የኢራቅ መንግሥት የሺዓዎችን ዋና ሃይማኖት መሪ ካሠረ በኋላ ፤ ከባግዳድ በስተምሥራቅ የሚገኘው የሺዓ እስላሞች መኖሪያ ቁጭራ ሠፈር ሕዝብ በቁጣ ገንፍሎ ተነሣ ። የዚያ ክልል የባዓዝ ፓርቲ መዋቅርም ተንኮታኮተ ። ሁከቱ ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሣ የፓርቲው ዋና ጸሐፊ ፤ አልባክር በፓርቲው ውስጥ የሺዓ እስላሞችን አስተያየት ያለመቀበል ያላዋቂነት መሆኑን ደመደሙ ። ሣዳም ግን ለድርድር ለመቅረብ ፈቃደኛ እንዳልሆኑ ገለጹ ። እንዲያውም የፓርቲው አባል ሺዓዎች በሌሎች ሺዓ አድመኞች ላይ እርምጃ ባለመውሰዳቸውና እንዳልተቆጣጠሯቸው በመጠርጠር ፤ ከፓርቲው መወገድና መቀጣት እንዳለባቸው አመኑ ። በፓርቲው ውስጥ ከሣዳም ጋር ይተባበሩ የነበሩት ሺዓ እስላሞች በአልባክር ዙሪያ ተሰባሰቡ ። ሌሎች ሺዓ ያልሆኑ ኢራቃውያንና እንዲሁም የጦር መኰንኖች ወደ እነርሱ ተቀላቀሉ ፤ እንዚህም አንድ ላይ በመሆን የሣዳም ሑሴን ሥልጣን የሚገደብበትን መንገድ ይፈልጉ ጀመር ።

ሣዳም ራሳቸው መንገዱን እንደዘበት አዘጋጅተውላቸዋል ። በ1970 በልግ ኢራቅና ሶርያ በሁለት ብርቱ ተወዳዳሪ ባዓዝ ፓርቲ ሲመሩ ቢቆዩም ፣ በድንገት ውሕደት እንፈጥራለን ሲሉ አስታወቁ ። የዚህ ፖሊሲ ንድፍ አውጪ ሣዳም ናቸው ። ግብጽ ከእሥራኤል ጋር የሰላም ስምምነት በማድረጓ ፣ ዓረብ አገሮች ሁሉ ከግብጽ ጋር ያላቸውን ግንኙነት እንዲያቋርጡ ፣ ሣዳም ይፈልጋሉ ። የተሰጠው ሽፋን ግብጽን ለመቅጣት ይምሰል እንጂ ፣ የሣዳም ዓላማ ፣ በጣም አስፈላጊና ብዙ ሕዝብ ያላትን የዓረብ አገር ፣ ግብጽን ከዓረብ ኅብረተሰብ ማግለሉ ከተሳካላቸው ፣ ኢራቅ በዓረቡ ዓለም የበላይነትን ለማግኘት እንድትችል መንገዱን ለመጥረግ ነበር ። ሣዳም ቢያንስ በመጀመሪያ እርምጃቸው ተሳክቶላቸዋል ። በኅዳር 1970 ፣ የዓረብ መሪዎች ጉባዔ በባግዳድ በተካሄደ ጊዜ ፣ ሣዳም ኩዌትን አጠቃለሁ ሲሉ ዛቱ ፣ የሶርያው ፕሬዚዳንት ሀፌዝ አልአሳድ ደግሞ ፣ "ሞርኑቱ መኝታ ቤታችሁ ድረስ እንዲመጣ አደርጋለሁ ።" በማለት ሳውዲዎችን አስጠንቀቁ ። ስለዚህ የዓረብ አገሮች ከግብጽ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ሁሉ ለማቋረጥ ተስማሙ ።

ይሁን እንጂ ፣ ከሶርያ ጋር የሚደረገው ውሕደት ኢራቅ ውስጥ የሣዳምን ፖለቲካ መሠረት እንዲያናጋ አሠጋ ። ብዙም ሳይቆይ ፣ ባክር የሶርያና የኢራቅ ፌደሬሽን ፕሬዚዳንት ፣ አሳድ ምክትል ፕሬዚዳንት ፣ ሣዳም ደግሞ ፣ በሥልጣን ሦስተኛው ሰው እንደሚሆኑ ግልጽ ሆነ ። የሣዳም ተቀናቃኞች ግን ውሕደት የሣዳምን ምኞት ሊገታ የሚረዳ መንገድ ሆኖ ስላገኙት ደገፉት ፣ ሣዳም ግን በበኩላቸው የተቀናቃኞቻቸው ፍላጎት ሊሳካ እንደሚችል ይበልጥ እየተገነዘቡት ሄዱ ።

ለመዋሐድ የቀረበው ሐሳብ አደጋ እንደሚያስከትልባቸው ሣዳም ሲገነዘቡ ፣ የታክሪት ተወላጆችም ከብዙ ጥቅም ጋር በሞኖፖል የያዙት ሥልጣን ሥጋት ላይ መውደቁን ተረዱ ። ሣዳም ቤተሰቦቻቸው ድጋፍ አድርገው የስድሳ አራት ዓመቱ ባክር ፣ ሥልጣናቸውን በፈቃዳቸው እንዲለቁና በምትካቸው እርሳቸው ፕሬዚዳንት ለመሆን እንዲችሉ ለመገፋፋት ወሰኑ ። የኢራቅ የዜና ምንጮች እንደሚሉት ፣ ኬይራላህ ተልፋ በልጃቸው በአድናን እየተደገፉ ፣ ለጤናቸው ደህንነት ሲሉ ባክር ከሥልጣን እንዲወርዱ ገፉ ። የብሪታንያው ጋዜጠኛ ፓትሪክ ሲል፡ እንዳለው ፣ ባክር በቅድሚያ የውሕደቱ ድርድር እንዲፋጠን በመጠየቅ



ለአሳድ በምስጢር ፣ "ውሕደቱ ፍሬ ከመስጠቱ በፊት መጥቶ በእምቡጡ ለመቅጨት የቸኮለ ውርጭ እዚህ አለ ።" በማለት መልእክት ካስተላለፉ በኋላ ከሥልጣን ለመውረድ ተስማሙ ።

በሐምሌ 19/1971 ፣ ፕሬዚዳንት ባክር በጤና ምክንያት ሥልጣናቸውን በፈቃዳቸው መልቀቃቸው በይፋ ተነገረ ። ሣዳም ሑሴን ፕሬዚዳንት ሆነው ተሾሙ ። እንዲሁም የኢራቅ ባዓዝ ፓርቲ ዋና ጸሐፊ ፣ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ፣ የመንግሥቱ መስተዳድር መሪና የአብዮታዊው እዝ የበላይ ምክር ቤት ሊቀመንበር ሆኑ ።

ሣዳም ፣ ያካሄዱት መፈንቅለ መንግሥት ተሳካላቸው ፣ በሐምሌ 1971 በከፍተኛ አመራር ላይ የሚገኙትን አንድ ፳ የባዓዝ ፓርቲ ካድሬዎች ለስብሰባ በመጥራት ፣ የፕሬዚዳንትነት ሹመታቸውን ለማስመረቅ ፣ አስገራሚ ትርዒት አከናወኑ ። ይህም ስብሰባ በቪዲዮ ተቀርጾ ፣ ለፓርቲው ተሰራጭቷል ። የዚህ ክር ቀቂት ክፍል በአሜሪካ ቴሌቪዥን ለጥቂት ደቂቃዎች ተላልፏል ፣ በሌላ ቦታም ገለጻ ተሰጥቶበታል ። ነገር ግን ስለአስቸኳይ ስብሰባው ሙሉ ሂደት ከዚያ በፊት በቅድሚያ አልታተመም ነበር ። ከዚህ ቀጥሎ ያለው ታሪክ ፣ የመጽሐፉ ደራሲያን ስለስብሰባው ያገኙትን በቴፕ የተቀረፀውንና የስብሰባውን ሂደት ያየ ግለሰብ የሰጠውን የዓይን ምስክርነት መሠረት በማድረግ የቀረበ ነው ።

ስብሰባው የተካሄደው ፣ በአብዮታዊ እዙ የበላይ ምክር ቤት ዋና ጸሐፊና ከሃያ ዓመት በላይ የባዓዝ ፓርቲ አባል በነበሩት በሙሂ አብዱል ሑሴን አል ማሻዓዲ ፣ በሶርያ ደጋፊነት ተጠንስሶ ፣ በተባለው ሴራ ተካፋይ መሆናቸውን የሚያጋልጥ የፈጠራ ታሪክ በማንበብ ነበር ። ሙሂ ያነበቡት በችኮላና ፣ ይኸው ትብብራቸው ምሕረት እንደሚያስገኝላቸው የተስፋ ቃና ባለው ድምፅ ነበር (ሆኖም አልተሳካም) ። ከዚያም ሣዳም ስለከሀዲዎች ፣ ስለፓርቲ ታማኝነትና ሌላውንም ሁሉ የሚነካካ ረጅም ዲስኩር ካደረጉ በኋላ ፣ "ስማቸውን የምጠራቸው ሰዎች ፣ የፓርቲውን መፈክር በመድገም የስብሰባ አዳራሹን ጥለው ይውጡ!" በማለት አስታወቁ ። ሲጃራ ለመለኮስ እየቃጡ ደጋግመው እያቋረጡ ፣ ማንበቡን ጀመሩ ። አንድ ነጥብ ላይ ሲደርሱ የመጀመሪያውን ስም "ጋኒም" በማለት ካነበቡ በኋላ ሐሳባቸውን በመለወጥ ወደ ሁለተኛው ስም ተሻገሩ።

የተወገዙትን ሰዎች ስም ዝርዝር አንብበው ከጨረሱ በኋላ ፣ የስብሰባው ተካፋዮች "ረጅም ዕድሜ ለግዳም" እና "እኔ ልሙት! ረጅም ዕድሜ ለኢዲ (የግዳም የበኩር ልጅ) አባት እያሉ መጮኽ ጀመሩ ። ጩኸቱ ረጅምና ስሜታዊ ነበር ። ጩኸቱ ሲያበቃ ግዳም መናገር ጀመሩ። ግን ፣ መሀረብ ለማውጣት በድንገት ንግግሩን ያቋርጣሉ ። በፊታቸው እንባ መውረድ ይጀምራል ፣ እንባቸውን በመሀረብ ሲያብሱ ተሰብሳቢው በመጮኽ በሲቃ ይሰረቀረቃል ።

ግዳም ነፍሳቸውን ሳያውቁ ይናገራሉ ፣ "እርግጠኛ ነኝ ብዙዎቹ ጓደኞቻችን የሚሉት አላቸው ፣ ስለዚህ እንነጋገርባቸው ፣" የፓርቲው አባላት ፣ ፓርቲው በስፋት እንዲጸዳ አሳሰቡ ። አንድ ሰው ይነግና ፣ "ግዳም ሑሴን በጣም ታጋሽ ናቸው ። በፓርቲው ውስጥ ለረጅም ጊዜ ብዙ ችግር ነበር ።...በጥርጣሬና በሽብር ፣ እንዲሁም ባልተመዛዘነ ዲሞክራሲ መካከል ወሰን አለው ። ከመጠን በላይ ስለሆነው የመታገሥ ችግር ፓርቲው መነጋገር ያስፈልገዋል ።" ከዚያም የግዳም አጉት አሊ ሐሰን አልመጂድ "ባለፉት ጊዜያት ያደረጉት ሁሉ ጥሩ ነው ፣ ወደፊትም የሚያደርጉት ነገር ሁሉ ጥሩ ይሆናል ፣ ይህንንም የምለው በፓርቲውና በእርስዎ አመራር ላይ እምነት ስላለኝ ነው" በማለት ይናገራሉ ። ፓርቲው ከሀዲዎችን ፈልጐ እንዲያወጣ ለፓርቲው ታማኞች ብዙ ጥያቄ ካቀረበ በኋላ ግዳም ውይይቱን ይዘጋሉ ። ከሃያ በላይ ታላላቅ የታወቁ ኢራቃውያን የሚገኙባቸው አባላት ከስብሰባው አዳራሽ ተወስደዋል ። ግዳም ዲስኩራቸውን "ከሀዲዎችን ለመቅጣት የስታሊንን ስልት እንከተልም ፣ እኛን የሚያስፈልገን የባዓዝ ዘዴ ነው" በማለት ሲደመድሙ ቤቱ በጩኸትና በጭብጭባ ይንንፍላል ።

በሚቀጥሉት ቀናት ግዳም ከፍተኛ የፓርቲ አባላትና የመንግሥት ሚኒስትሮችን በማስገደድ በሥራ ልምድና በእነልግሎት ከነሱ በላይ የሆኑትን የቀድሞ ጓደኞቻቸውን በግንባር ተገኝተው በመግደል እንዲተባበሯቸው አደረጉ ። ከተገደሉትም ውስጥ በሥልጣን ላይ ያለው የአብዮታዊ እዝ የበላይ ምክር ቤት አባል መሐመድ አየሽ ፣ የሠራተኛ ማኅበር መሪ ቢደን ፋድቢል ፣ ምክትሉ ሺዓ እስላምና የቀድሞ የግዳም የቅርብ ተባባሪ ጋኒም አብዱልጀሊል ፣ እና የርዳኖሳዊው ግሊብ አልሳውል ናቸው ። ሁለቱ የግዳም እጅግ ደመኛ ጠላቶች ግን ከሐምሌ 15/1971 ስብሰባ በፊት ተገድለዋል ። ከፍተኛ የጦር መኰንንና የግዳም ተቃዋሚ



ሁድን መሪ ጄኔራል ዋሊድ መሐመድ ሲራት እንዲሰቃዩ ከተደረገ በኋላ ሰውነታቸው እንዲቆራረጥ ተደርጓል ። ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አድናን ሐምዳኒ ለመንግሥት ሥራ ወደ ሶርያ ሄደው ሲመለሱ ከአውሮፕላን ማረፊያ ተይዘው ወዲያው ተገድለዋል ። አንዳንድ ምንጮች እንደሚያምኑት ፣ ልክ ሂትለር ባከናወነው መልክ በተፈጸመው በዚህ የግዳም ጭፍጨፋ ሴሲቱን እስከ አምስት መቶ ሰዎች በምስጢር ተገድለዋል ። ዕውነተኛው ቁጥር ፈጽሞ ሊታወቅ አይችልም ።

በግዳም አረመኔያዊ ድል የተፈለገው ግዳምን የማይደፈሩና የማይሸነፉ አስመስሎ ለማሳየት ነው ። ተቀናቃኞቻቸው ተደምስሰዋል ። ከሁሉም በላይ ፣ የግዳም ፈላጭ ቆራጭነት ተጠብቋል ። መንግሥቱን በፓርቲው እንዲተካ አድርገው ነበር ፣ አሁን ደግሞ ፣ ፓርቲውን ራሳቸው ተኩት ፣ ሕይወትም ፣ ሞትም ፣ ይለግሳሉ ። እርሳቸው የሚያሠራጩት ሽብር ሰዎችን ፈሪና ተለማማጭ ያደርጋቸዋል ፣ አልፎ አልፎም ለጥቂቶች ምሕረት ሲደረግ እንዲያመሰግኑ ያደርጋቸዋል ። ግዳም በ1963 ከገቡት ቃል ጥሩ ያደረጉት ፣ "በፓርቲያችን ዘዴ ፣ ግንም ከኛ ጋር ባለመስማማቱ ብቻ ወደ አንድ ወይም ወደሁለት ታንኮች ዘሎ በመግባት መንግሥትን ለመገልበጥ አንድም እድል የለውም ።" በማለት በገለጹበት ጊዜ ነው ። ከ1912 እስከ 1971 ባለው ጊዜ ውስጥ ኢራቅ ዓሥራ ሦስት መፈንቅለ መንግሥት አይታለች ። ግዳም የእርሳቸው መፈንቅለ መንግሥት የመጨረሻው ሆኖ እንዲቀር ቆርጠው ተነሥተዋል።

"የግዳምን አገዛዝ ለመረዳት" ይላሉ ፣ "ሪፐብሊክ ኦፍ ፌር" የተሰኘው መጽሐፍ ደራሲ — ሳሚር አልኸሊል በስውት አስተያየት "ቁልፉ ያለው በተራቀቀ መንገድ መንግሥት ተራውን ሰው ፓርቲው በሚፈጽመው ደም የማፍሰስ ተግባር ተካፋይ እንዲሆን በማድረግና ወደገዢው የመጨቆኛና የመጨፍጨፊያ መሣሪያ አካል ውስጥ እንዲገባ ከማድረጉ ላይ ነው ።" ኸሊል እንደጻፉት ፣ "ውጤትን መቀዳጀት የሚቻለው ኅብረተሰቡ ራሱን ለመጠበቅ በተዘጋጀበት መጠን ነው ። ወሬ አቀባዩ ማን ነው? በባዓዝ ፓርቲ በምትገዛዋ በኢራቅ ውስጥ ፣ መልሱ ሁሉም ነው።" አንድ ባግዳድ ውስጥ የሚኖር ዲፕሎማት ለ"ኒውዮርክ ታይምስ" ጋዜጣ ዘጋቢ እንደተናገረው ፣ "ቢያንስ ሦስት ሚሊዮን ኢራቃውያን ሌላውን ዓሥራ አንድ ሚሊዮን እንደሚጠብቁ ፣ ግንም ይስማማል ።"

'ዲፕሎማቱ ግምገማ የተጋነነ አይደለም ። ኢራቅ ውስጥ ካሉት ሃያ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች በጣም ሰፊው የአገር ውስጥ ጉዳይ ...ቴር ነው ። ኽሊል በሰጡት ግምት ፥ "ፖሊስና ሕዝባዊ ሠራዊቷ ተደምሮ አንድ ላይ በመደበኛው ጦር ሠራዊት ይበልጣል ። በትክክለኛው ሒሳብ ፥ በሻሁ ጊዜ ኢራን ውስጥ የነበረውን በሁለት እጥፍ የሚበልጥ ማለት ነው ።" በተጨማሪም የኢራቅ ሕዝብ ከኢራን ሕዝብ በአንድ ሦስተኛ ያንሳል ።

በ1976 ከሕዝቡ 25ሺ ያኸሉ የባዓዝ ፓርቲ ሙሉ አባል ሆነ ። 1.5 ሚሊዮን ኢራቃውያን የፓርቲው ተባባሪ ወይንም ደጋፊ ነበሩ ። የመጀመሪያዎቹ በአጠቃላይ የፓርቲውን መሥመር ለመከተል የተዘጋጁ ነበሩ ። ሁለተኛዎቹ ግን አንዳንድ ጊዜ በፓርቲው ውስጥ የሚገቡት ለውጫዊ ምክንያት ነበር ፥ የሥራቸው ጠባይ የፓርቲ አባልነትን የሚጠይቅ ሊሆን ይችላል ። ምንም እንኳን ከፓርቲው ጋር ያላቸው ግንኙነት የላላ ቢሆንም ፥ የሥርዓቱ አካል ናቸው ፥ በሳምንታዊ የፓርቲ ስብሰባ ላይ እንዲገኙ ይገደዳሉ ። አንድ ሰው እያንዳንዱን አባል በአራት ወይም በአምስት ተጎኞቹ ቢያባዛ የባዓዝ ፓርቲ ከመላው የሕዝብ ብዛት ከግማሽ በታች የሚሆነውን የተግባሩ ተካፋይ አድርጉታል — ማለት ይቻላል ። ለሥራ ብቁ ከሆነው ሕዝብ ውስጥ ሠላሳ ከመቶውን መንግሥት ይቀጥራል ። በዚህ ላይ መደበኛ ጦሩና ሕዝባዊ ሠራዊቱ ሲጨመር የከተማው ሠራተኛ ኃይል ወደጎምሳ በመቶ ከፍ ይላል ። ከዚህም ኅብረተሰብ ስድሳ አምስት በመቶ የሚሆነው ዜጋ በከተማ ውስጥ ይኖራል ። ለማንኛውም ተግባራዊ ሥራ መንግሥትና ፓርቲው ተመሳ ላይ ናቸው ።

በዓሥራ ዘጠነኛው ምእታመት መጀመሪያ ላይ በዛር (የንጉሡ የማዕረግ ስም) ትገዛ የነበረችውን ሩሲያን ማርኩዊስ ዲካስቲን ከጎበኘ በኋላ በሰጠው አስተያየቱ ፥ "የተጨቆኑ ሕዝቦች ምንጊዜም የእጃቸውን ያገኛሉ ፥ ዐምባገነንነት የሚመጣው ፥ በአጠቃላይ በአንድ አገር ሕዝብ ነው ፥ የአንድ ግለሰብ ብቻ የሥራ ውጤት አይደለም ።" ብሏል ። ፍርዱ ምናልባት ከባድ ሊሆን ይችላል ፥ ሆኖም ደግሞ ሙሉበሙሉ ስሕተት አይደለም ። ሲሞን ሊይስ ፥ የማኦን ቻይና እንደታዘባትና እንዲሁም ለሳዳሟ ኢራቅም በትክክል ተመሳሳይነት እንዳለው ፥ "ዐምባገነንነት



ማለት ብዙኃን ንጹህ ዜጐቹ በጥቂት ዐምባገነን ሰዎች ቡድን ፥ የሚጨቆኑበት ሥርዓት ከሆነ ፥ በእንፃሩ ደግሞ ይህን ሥርዓት መገልበጥ ቀላል ነው ። እንደ ዕውነቱ ከሆነ ፥ የሥርዓቱ ያልተለመደ መተማመን የሚኖረው ሰለባዎቹን ራሳቸው ኸብር ለማካሄድ በየቦታው ባቋቋሟቸው ድርጅቶች ሁሉ ፥ በማስገባት ገዳዮቻቸው በሚፈጽሙት ወንጀል ሁሉ ተካፋይ በማድረግ ወደ ጎቱ ተባባሪነትና ተከታይነት በመለወጥ ነው ። በዚህ ዓይነት ሰለባዎቹ የሚያሰቃያቸውንና የሚደቁሳቸውን አገዛዝ ፥ ከጥቃት በመከላከልና በመጠበቅ የግል ድርሻ አላቸው ።"

ኢራቅ ውስጥ የፖሊስና ከፖሊስ ጋር የተያያዘ ሥራ እንደ ታላቅ ሙያ ይቆጠራል ። በ1970 ፥ ከ150ሺ በላይ ሰዎች ፥ በአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር በተለያዩ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ተቀጥረው ሠርተዋል ። እነሱም ከመንግሥት ሠራተኞች ውስጥ ሃያ ሦስት በመቶውን ይዘዋል ። (የቀድሞዋ ምሥራቅ) ጀርመን የኢራቅን የደኅንነት ጥበቃ ኃይል ለረጅም ጊዜ በማሠልጠንና በማማከር ሠርታለች ። የኢራቅ ደኅንነት ፖሊስ ምናልባት (የቀድሞዋ ምሥራቅ) ጀርመን ከነበራት ጋር ተመሳሳይ ሲሆን፥ የሁለቱም አገሮች የሕዝብ ብዛት እንዲሁ ተመሳሳይ ነበር ። (በቀድሞዋ ምሥራቅ) ጀርመን ውስጥ ከአንድ ሺ በላይ ሰዎች ስልክ በቴፕ በመቅረፅ የመጥለፍ ሥራ ያከናውኑ ነበር ። ሁለት ሺ ሰዎች ፖስታዎችን በቅርብ ይከታተሉ ነበር ። አምስት ሺ ደግሞ ሌሎችን ሰዎች ይከታተሉ ነበር ። ኢራቅ ውስጥ ተመሳሳይ ሥራ የሚፈጽሙት ሰዎች ቁጥር (ከቀድሞዋ ከምሥራቅ) ጀርመን ጋር እኩል ወይም ከዚያ በላይ ይሆናሉ ፥ ምክንያቱም የኢራቅ ኅብረተሰብ ፥ ከ(ከቀድሞዋ ምሥራቅ) ጀርመን ይልቅ ይበልጥ በቁጥጥር ሥር የዋለ ነው ።

የኢራቅ የደኅንነት ፥ ግማሹ የሠሩትን ሌሎቹ ደግሞው የሚሠሩ ፥ እርስ በርስ የሚወዳደሩና እያንዳንዳቸው የራሳቸው እሥር ቤት ያላቸው ፥ ብዙ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች አሉት ። ከመጀመሪያው ሲቋቋሙ በዜጐች ላይና እርስ በርሳቸው አንዱ ሌላውን እንዲሰልል ተደርጉ ነው ። ቀጥሎ ያሉት በጣም አስፈላጊ—ከሚባሉት መካከል ናቸው ።

አጠቃላይ የመረጃ ክፍል (ወይም ሙኻባራት) የሚባለው ከባዓዝ ፓርቲ ምስጢራዊ ፖሊስ በመውጣት የተደራጀው ነው ፥ ጀሃዝ ሀኒን ፥ በ1952 በሣዳም ሑሴን የተመሠረተና አሁን መንግሥታዊ ድርጅት በመሆን የአገር ውስጥና የውጭ አገር ጉዳይን የሚከታተል ነው ። ይህም

ድርጅት መጀመሪያ ከ1966 እስከ 1975 በግዳም ወንድም በታከሪቲው ባርዛን ኢብራሂም ሲመራ ቆየ ። ባርዛንን በኋላ የባከር የቅርብ ረዳት ፈድል ባራክ እስከ 1975 ከረምት በበላይ ኃላፊነት ተካው ። ከዚያም በእናት በኩል የግዳም አጐት ፈድል ሰልፈግ ተጠባባቂ ኃላፊ ሆነው ከሠሩ በኋላ በ1981 መጨረሻ የግዳም ወንድም ሳባዊ ተረከቡት ።

የአገር ውስጥ ደኅንነት ድርጅት (ወይም አማን አልአማን) አልፎ አልፎ በውጭ አገር ተልእኮ ተካፋይ ቢሆንም ፣ ዋና እንቅስቃሴው በአገር ውስጥ ነው ። በአስተማማኝ ዘገባ እንደገለጸው ዋና ኃላፊው የግዳም ታናሽ ወንድም ዋዝባን ነው ።

ወታደራዊ መረጃ ክፍል (ወይም ኢስተኽባራት) ደግሞ ዋና ተግባሩ በጦር ኃይል ውስጥ ያለውን ደኅንነት መቆጣጠርና የውጭ ጦር ኃይልንም መሰለል ሲሆን ፣ በውጭ አገር ባሉት የኢራቅ ኤምባሲዎች ውስጥ ደግሞ ለወታደራዊ አታሼ ይመድባል ። ከዚህ ሌላ አጠቃላይ የመረጃ ክፍል ከሚባለው ድርጅት ጋር በመተባበር ፣ በውጭ አገር በስደት በሚኖሩት ተቃዋሚ ኢራቃውያንና በውጭ አገር ተቋሞች የሽብር ዘመቻ ያካሂዳል፡ እንደዚህም በማድረግ ፣ "የአብዮቱ ክንድ ፣ ጠላቶች ባሉበት ቦታ ሁሉ ይደርሳል ።" ሲሉ ግዳም የሠነዘሩትን ዛቻ ተግባራዊ ያደርጋል ። ተቃዋሚ ኢራቃውያን ፣ ቢያንስ ፣ በስዊድን ፣ በእንግሊዝ ፣ በግብጽ ፣ በሱዳንና በአሜሪካ ውስጥ ተገድለዋል ። እንዲሁም ቢያንስ አንድ የግድያ ሙከራ በፓሪስ ተደርጓል ። በተጨማሪም በትንሹ አራት የግድያ ሙከራዎች በዲትሮይት—አሜሪካ ውስጥ ከ1959 እስከ 1975 በኢራቃውያን ስደተኞች ላይ ተፈጽሟል ። ይህም ተግባር የግዳም ሑሴን እንደሚሆን ተጠርጥሯል ። በለንደኑ የእሥራኤል አምባሳደር በሻሎም አርጐቭ ላይ ጥቃት ለመፈጸም የተላከውን ቡድን የመራው ወታደራዊ ደኅንነት አባል ብሪታንያ ፍርድ ቤት ቀርቧል ። በዚህም ተግባር ሳቢያ በ1974 እሥራኤል ሊባኖስን ወራለች ።

የፕሬዚዳንታዊ ጉዳይ ክፍል (ወይም አማን አልካስ) ደግሞ በቀጥታ ከግዳም ሑሴን ጽሕፈት ቤት ጋር የተያያዘ ነው ። የዚህም ድርጅት ዋና ሥራ ፣ በውጭ አገር ባንክ ውስጥ ያለውን ሒሳብ መቆጣጠርና በሕገወጥ መንገድ ዕቃና የውጭ ምንዛሪ ለመሰብሰብ ባልታወቀ ስም ሽፋን ኩባንያዎችን ያካሂዳል ። የግዳም አጐትና አማች ፣ እንዲሁም ደግሞ



የወታደራዊ እንዱስትሪ ግንባታ ሚኒስትሩ ሑሴን ከማል ከዚህ ድርጅት ጋር የቅርብ ግንኙነት አላቸው ።

የፓርቲ ደኅንነት (ወይም አማን አልሒዝብ) በፓርቲ አባላት ላይ የሚደረገውን ክትትል ያስተባብራል ፣ በተጨማሪም ፣ የአገሪቱን ልዩ ልዩ አውራጃ የፓርቲ ሕዋሳትና ጽሕፈት ቤቶች ይቆጣጠራል ።

ከዚህም ሌላ ፣ ጠረፍ ጠባቂ ዘቦች ፣ ተዘዋዋሪ የፖሊስ አጥቂ ኃይል ፣ የብሔረሰብ አጠቃላይ ክፍልና አጠቃላይ የፖሊስ ክፍል የሚባሉት የደኅንነት ድርጅቶች አሉ ።

የኢራቅ ሕዝብ በጥርጣሬ ዓይን መታየቱንና በቁጥጥር ሥር እንዲውል መደረጉን ፣ በጭፍጨፋና በጭቆና ተረግጦ መገዛቱን ፣ የስቃይና የመከራ ኑሮ ሲገፋ መኖሩን ፣ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ድርጅትና ቅርንጫፍ ሰብአዊ መብት ጠባቂ ክፍሉ ከ"ሚድል ኢስት ዎች" ጋር በመተባበር በሚያሳምን ሁኔታ በዝርዝር ዘግበውታል ። ሁለቱም አትራፊ ያልሆኑ ፣ ነፃ የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ቡድኖች ናቸው ።

"ሚድል ኢስት ዎች" በ1982 ፣ ትዝብቱን "ሰብአዊ መብት በኢራቅ" በሚል ርእስ ባወጣው ዘገባ እንዳሠፈረው ፣ "ኢራቅ ፣ በባዓዝ ፓርቲ አገዛዝ የስላይ ወይም የወሬ አቀባይ አገር ሆናለች ። የፓርቲ አባላት፣ ስለቤተሰቦቻቸው ፣ ስለጓደኞቻቸው ፣ ስለሚተዋወቋቸው ሰዎችና ስለሌሎች የፓርቲ አባላት ጭምር ፣ ጥቆማ እንዲያደርጉ ይፈለጋል። ... አስተማሪ ሁሉ የፓርቲ አባል እንዲሆን ይገደዳል ። ፈቃደኛ ያልሆነው ወይንም የፓርቲ አባል ለመሆን ብቁ ያልሆነው ከሥራ ይባረራል ። አስተማሪዎች ተማሪዎቻቸውን ስለወላጆቻቸው ያላቸውን አስተያየት እንዲሰጡ ይጠይቃሉ ፣ ይህም በመሆኑ ፣ ወላጆች አስተሳሰባቸውን ከልጆቻቸው ለመሠወር ተገደዋል ። አልጠቁምም ማለት ቅጣቱ ከባድ ነው ። መሥሪያ ቤቱ ለንደን ውስጥ የሆነው "ኢንዴክስ ኦን ሴንሰርሺፕ" እንደሚለው ፦

አንድ የባሻዝ ፓርቲ የቀድሞ ከፍተኛ ባለሥልጣን በሙድ በነሐሴ 1979 ፣ በግዳድ ውስጥ ታሠረ ። የታሠረበትም ምክንያት ለፕሬዚዳንት ግዳም ሑሴን (ግብቂያ) ቀልድ ሲነገር ፣ ተሰብስበው ከነበሩት ሰዎች እንዲ ስለነበርና ስለዚሁ ጉዳይ ፣ ለፓርቲ አባልነቱ ፣ ለባለሥልጣናት ሳይጠቁም ከመቅረቱም ሌላ የመንግሥት ጠቋሚ በሱ ላይ ስለጠቆሙበት ነው ። የቤተሰቡ አባላት በሙሉ – ሦስት ወንድ ልጆችና አንድ አማቾቹ ተይዘው በምርመራ ጊዜ እንዲሰቃዩ ተደርገዋል። ... ከዚያም በኋላ ፣ አምስቱም በሙሉ

ተገድለዋል ። የቤተሰቡ መኖሪያ ቤቱም በቡልዶዘር ተደርምሶ ፣ እንዳልነበር ተደረገ ።

ፕሬዚዳንቱን ፣ ወይም የመንግሥቱንም ሆነ የፓርቲውን ከፍተኛ ተቋሞች በአደባባይ መሳደብ በዕድሜ ልክ እሥራት ወይንም በሞት ያስቀጣል ። የኢራቅ መንግሥት ፣ በሞት የሚያስቀጣ ሃያ አራት የጥፋት ዓይነት ዝርዝር አውጥቷል ። "ሚድል ኢስት ዎች" የተባለው የሰብአዊ መብት ጠባቂ ድርጅት እንደዘገበው ፣ "ኢራቅ ውስጥ ብዙ ሰው ባንድ ላይ መቅጣት ሁልጊዜ ተደጋግሞ ይፈጸማል ። በኩርዶች አካባቢ ፣ በኢራቅ ወታደሮች ወይም ባለሥልጣኖች ላይ ጥቃት ሲደርስ ፣ አጸፋውን ለመመለስ ፣ በአጋጣሚ በአካባቢው የተገኙ ሰዎች ተከበው በጥይት ይደበደባሉ ። ሁልጊዜ አንድ ሰው በፖለቲካ ወይንም በደኅንነት ወንጀል ተፈልጎ ሊገኝ ካልቻለ ፣ ሁልጊዜ የቤተሰቡ አባላት ተይዘው ይታሠራሉ፣ አንዳንድ ጊዜም አሰቃይተው ይገድሏቸዋል ። ኸሊል ፣ "ሪፐብሊክ ኦቭ ፊር" በተባለው መጽሐፋቸው ስለድርጊቱ ሲገልጽ ፡-

> ኢራቅ ውስጥ ሰዎች ይጠፋሉ ፣ ከሳምንታት ፣ ከወር በኋላም ሊሆን ይችላል ፣ ሬሳ ነው ይባልና በአንድ የታሸገ ሣጥን ለቤተሰብ ኃላፊው ተመልሶ ይሰጠዋል ፣ ተከትሎም ሰውየው በእሳት አደጋ ፣ በመኪና አደጋና በመሳሰለው ምክንያት መሞቱን ባረጋገጠው የአስከሬን ምርመራ የምስክር ወረቀት ላይ እንዲፈርም ከቤተሰቡ አንዱ ይጠየቃል ፣ እንዲሁም ከቤተሰቡ አንዱ ፖሊስ ጣቢያ ተከትሎ ይሄድና ሥርዓተ ቀብሩ ይፈጸማል ፣ ነገር ግን በምንም ዓይነት ከቤተሰቡ አንዱ ወይም አንዷ ሬሳውን እንድታይ እንዲያይ አይፈቀድም። የዚህ ሁሉ ወጭም በቅድሚያ እንዲከፈል ስለሚደረግ ፣ ሁሉም ነገር መጀመሪያ በር ካንኳኩበት ጊዜ ጀምሮ ባለው የአንድ ሰዓት ጊዜ ውስጥ ያልቃል ።

በልዩ ልዩ መንገድ የማሰቃየቱ ታሪክ ምንጊዜም ያለና ማስረጃውም በሚገባ የተጠናቀረ ነው ። በ1973 "አምነስቲ ኢንተርናሽናል" (ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ድርጅት) በኅዳር 1970 የኢራቅ ባለሥልጣኖች አንድ ወጣት ጋዜጠኛ ማሠራቸውን አስመልክቶ እንደዘገበው ፡-

> በመጀመሪያዎቹ ቀናት ወደ ልዩ ልዩ ክፍል ተወስዶ ፣ በዱላ ፣ በብረት ዘንግና በአለንጋ ተደበደበ ፣ ... በአንዱ ክፍል ውስጥ አባለዘሩ ከተኛ ተቀጠቀጠ ፣ ከዚያ ሲወጣም ተገረፈ ። ቀጥሎም በዚሁ በየአንዳንድ ወይም በየሁለት ሰዓት ልዩነት ጭንቅላቱን በኃይል ሲገርፉትና ሲመቱት ነፍሱን ሳተ ፣ ... ነፍሱን ሲያውቅ አንድ ሹል ነገር ላይ ያስቀመጡት መሆኑ ታወቀ ።

ግፈኛው አገዛዝ ፣ ሊይዛቸው ያልቻለውን ሰዎች ለመቅጣት ወይም ይዞ ባሠራቸው ሰዎች ላይ ግፊት ለማድረግ የቤተሰብ አባላትን ያሰቃያል። ባለሥልጣኖቹ የሚፈልጉትን ተጠርጣሪ ሰው ሲያጡ ዘመዶቹን በመክበብ በማጎሪያነት ይይዛሉ ። በቅድሚያ የተያዙ ወላጆቻቸውን



አስገድደው ለማናዘዝ ፣ ሕፃናቱን ሳይቀር ፣ በማሠር ያሰቃዩአቸዋል ።

ኩርዶች በተለይ አገዛዙ ጭቆናውን በይበልጥ የሚያሳርፍባቸው ወገኖች ናቸው ። ኩርዶች ሱኒ እስላሞች ሲሆኑ ፣ ዓረብ ያልሆኑና ፣ ከኢራቅ ሕዝብ ሃያ ከመቶ የሚሆኑ ናቸው ። የአንደኛው የዓለም ጦርነት አሸናፊ ወገኖች ከኡስማናውያን ግዛት ቆርጠው በመከለል ፣ የኩርድ መንግሥት ለማቋቋም ቃል ገብተውላቸው ነበር ፣ የተባለው የኩርድ መንግሥት ግን ዕውን ሊሆን ባለመቻሉ በባግዳድና በኩርዶች መካከል ምንጊዜም መፋጠጥ አለ ። ይህም ሆኖ እንደሣዳም ያለ ጨካኝ ፣ አረመኔያዊ የኢራቅ አገዛዝ አጋጥሟቸው አያውቅም ።

በኩርዶች ላይ ድል የተገኘበት ውጊያ የተካሄደው ለሰብአዊ መብት እንዳችም ርኅራኄ ሳይደረግ ነበር ። ለምሳሌ በአንድ ማስረጃው በሚገባ በተጠናቀረ አሰቃቂ እልቂት ላይ ስድሳ ሴቶችና ልጆች በመድፍ ከመደብደብ ለማምለጥ በአንድ ዋሻ ውስጥ ተደብቀው ተገኙ ፣ እነዚህን ሰዎች ፣ አገዛዙ እሳት እንዲበላቸው አድርጓል ። በመጋቢት 1966 ፣ እያንዳንዱ 25ሺና 20ሺ ነዋሪ ያላቸውን ሁለት የኩርድ ከተሞች እንዳሉ ደምስሷል ። ሁልጊዜ ናፓልም ቦምብ በኩርዶች ላይ ያወርድባቸው ነበር። ብዙ መቶ ሺ ኩርዶች አገር ጥለው ለመሸሽ ተገደዋል ። "ዚ ታይምስ ኦቭ ለንደን" ለተባለው ጋዜጣ በስፋት ስለጦርነቱ የጻፈው ጋዜጠኛ ኤድዋርድ ሞርታይመር በሰጠው ግምት ፣ 1.5 ሚሊዮን ከሚሆነው አጠቃላይ ኩርድ ፣ ግማሽ የሚያኽለው ከቦታው ተፈናቅሏል ፣ ከ100ሺ በላይ ያኽሉ ደግሞ ወደ ኢራን ለመሰደድ ተገደዱ።

የኩርድ አማጽያን ለመንግሥቱ ወታደሮች እጃቸውን ከሰጡና ትጥቃቸውን ከፈቱ በኋላ ምንጊዜም ይጨፈጨፋሉ ። አልፎ ተርፎም ፣ መላ ቤተሰቡንና መላ መንደርተኛ በሰፋት ከነበረበት አካባቢ አፈናቅሎ በማጓጓዝ በሌላ ቦታ እንዲሠፍርም ተደርጓል ። ከቦታው የተፈናቀለ ቤተሰብ እንዲሠፍር የተደረገው በኢራቅ ደቡብ ምዕራብ በረሃማ ክፍል ነበር ። በዚህ መርሀ ግብር የሠፈሩ ተፈናቃዮች ብዛት በትክክል ባይታወቅም ፣ "ዚ ኢኮኖሚስት" መጽሔት ተቃዋሚዎችን ጠቅሶ በሰጠው ግምት ከ50ሺ እስከ 350ሺ ይደርሳል ።

በተለይ ሣዳም በፍርሀት በመዋጥ ፣ ያላንዳች የኅሊና ፀፀትና

ያለማመንታት ኩርዶቹን እፍኖ ለመግዛት የኬሚካል ጦር መሣሪያ መጠቀማቸው ፣ ኢራቅን በዓለም ለመጀመሪያ ጊዜ በሕዝቧ ላይ የኬሚካል ጦር መሣሪያ የተጠቀመች አገር አድርጓታል ። በጥቅምት 1980 ፣ የአምነስቲ ኢንተርናሽናል ባለሥልጣኖች ከዕልቂቱ ከተረፉት ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ፣ ተራፊዎቹ በሰጡት ቃል ፦

> የኬተሰበቸው አባላትና ሕፃናት ጭምር በኬሚካሉ ተቃጥለው ምክንያት ወዲያውኑ ሞተዋል። ሌሎቹ ደግሞ ከቀኖ ስለቆሰሉ ለማምለጥ አልቻሉም ። እንዳሉት የኢራቅ ወታደሮች ወደ አንድ መንደር ሲገቡ በቅድሚያ በኬሚካል ጦር መሣሪያ ይጠቀማሉ። ከዚያም በኬሚካሉ ወደተጎዳው መንደር በመግባት ቤቱን በደማሚት ያፈርሱታል ወይም በቡልዶዘር በመደርመስ እንዳልነበረ እስኪሆን ይረመርሙታል ።

የሣዳም ፣ ሽብርን እዘወትሮ እንደ መንግሥት መመሪያ የመጠቀም ዓላማ ፣ የሰላማዊውን ኅብረተሰብ መልካም ግንኙነት ለማፈራረስና ተቃዋሚ (ወደፊት ተቃዋሚ ሊሆን የሚችል) ኃይል እንዳይፈጠር ፣ ሁሉንም አንቆ ለማስቀረት ነው ። ሕዝቡ በእርሳቸው ላይ በመተባበር እንዳይነሣባቸው ለማድረግ ፣ አንዱ በሌላው ላይ እምነት እንዳይኖል ፣ በአገሪቱ ውስጥ የመጠራጠርን መንፈስ ያስፋፋሉ ። አንድ ሰው ገደብ የሌለው ሥልጣን በመያዝ በሚገዛበትና ሁሉም ሥልጣን ተጠቃሎ በአንድ ዐምባገነን እጅ ውስጥ ባለበት አገር ሽብር እንደ ችግር መፍትሔ ይቈጠራል ። ግለሰብ መብት የለውም ፣ ሁሉም ተካቶ ለመንግሥት ፍላጐት ተገዢ ነው ፣ መንግሥት ደግሞ ለሣዳም ተገዢ ነው ።

ኩዌት ከተወረረች በኋላ ፣ ሣዳም በይንብሔራዊ ሕግንና ስምምነትን ያላገናኛ ሀፍረት በመጣሳቸው ፣ በአድራጐታቸው ብዙ ሕዝብ አፍሯል ። ሣዳም የጄኔቫን ስምምነት በመጣስ የኩዌትን ሕዝብ ፣ ልደትና ሞት ፣ ብዛትና ማንስ ፣ እድገትና ውድቀት ፣ በአጠቃላይ የኅብረተሰቡን እቋም ለመለወጥ ፈልገዋል ። የኩዌት የዜግነት ሰነዶች ወደባግዳድ ተወሰደዋል ። ኩዌታውያን አገር ጥለው እንዲሸሹ በማስፈራራት ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ኢራቃውያን ወደኩዌት እንዲገቡ አበረታቱ ። ሣዳም ፣ የውጭ አገር ዜጐችን በማስገደድ ፣ ወታደራዊ ዒላማዎች እንዳይመቱ በመያዣነት ተገን ለማድረግ አግተው ያዙ ። የኢራቅም ወታደሮች የኤምባሲዎችን ልዕልና ባለመድፈር ያላገናኛ ማመንታት ፣ በኃይል እየገቡ ነዋሪዎቹን ያዙ ። ቀደም ሲል ሣዳም በሕዝባቸውና ከውጪው ዓለም ቀጥረው ባመጧቸው ሰዎች ላይ ሥልጣናቸውን የሚጠቀሙበት ዘዴ የተለያየ ነበር ። አሁን ግን ፣ ከውጪው ዓለም ካመጧቸው ሰዎች ጋር



ያላቸው ግንኙነት ፣ ለረጅም ጊዜያት በኢራቃውያን ላይ ይሠሩበት ከነበረው ጋር ተመሳሳይነት አለው ። በጉልበት ብቻና ጉልበታቸውን እስከ መጨረሻው አረመኔያዊ ዐቅማቸው ለመጠቀም በማስፈራራት ነው።

ሣዳም ፣ ከአገራቸው ውጭ ኃይል ለማሳየት ያላቸው ችሎታ በአገር ውስጥ ያለውን የሥልጣን ዘመን ለማራዘም እንደሚረዳቸው ያውቃሉ ። በሌሎች መንግሥታት ላይ መዛትና እነሱን ማስፈራራት ፣ በአገር ውስጥ ክልል ያልመሸንፍን ስሜት ለመናኘት አስተዋጽኦ ያደርጋል ። ከኢራቅ ድንበር ባሻገር የሚፈጽሙት ጀብዱ ፣ ዐምባገነን መንግሥታቸው ለሚያከናውነው ሽብር ተቀባይነትን ያገኛል ። ያልተረጋጋውንና በአመራራቸው ያልተደሰተውን ሕዝብ በጦርነት እንዲጠመድ ያደርጋሉ ። በተለይም ሕዝቡንም ለመጫን ጭምር ያደረጁት የጦር ኃይል ኀትር ይደገዛላቸዋል ። በዚህ ለዘመናት በነበረው ክሥተት ላይ በዘመናቸው እያሉ ዐምባገነኖችን ከሚያውቁት ጥንታዊ ግሪኮች መኻል እፍላጦንና ደቀመዝሙሩ አርስጣጣሊስም ዐምባገነኖችን የታዘቡት በዚሁ እንደነበር ጽፈዋል።

ሣዳም ፣ በብዛት እጅግ ግዙፍ የሆነው የጦር ኃይላቸው ወደ ራሳቸው እንዳይዞርባቸው ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው ። የጦር ኃይሉን ለመቆጣጠር የተጠቀሙበት ዘዴ የአገር ውስጥ የደኅንነት ጥበቃ ኃይላቸውን ለመቆጣጠር ከተጠቀሙበት ጋር ይመሳሰላል ። በጦሩ ውስጥ የፓርቲ ደጋፊዎች ብቻ እንዲቀሩና አዲስና ታማኝ የጦር መኰንኖች ቡድን እንዲመሠርቱ ለማድረግ በመጀመሪያ ወታደራዊ ተቋሞችን ባዶ ለማስቀረት አሰቡ ። ፈጣን ወታደራዊ ኮርሶች ተከፈቱ ። በእጣፈ ወታደራዊ ኮርሶች ብዙ መቶ የባዓዝ ፓርቲ መኰንኖች ሠለጠኑ ። እነዚህን የጦር ኃይል መኰንኖች ለመቆጣጠር ደግሞ "የፖለቲካ ኮሚሳሮች" የፖለቲካ ሥርዓት ተመሠረተ ። እነዚህንም ኮሚሳሮች በተራቸው የባዓዝ ፓርቲ ወታደራዊ ኮሚቴ ይቆጣጠራቸዋል ።
የመኰንኖች የማዕረግ እድገት ለማግኘት የመጀመሪያው መመዘኛ የፖለቲካ ታማኝነት ሆነ ። ነገር ግን ፣ ሣዳም የጦር ኃይሉ ለእርሳቸው ታማኝ ወይም የሚያከብራቸው ስለመሆኑ እርግጠኛ መሆን ፈጽሞ አይችሉም ። በጦር ኃይሉ በኩል ያላቸው እያያዝ ሁልጊዜ እንዳስቸገራቸው ነው ። ወታደራዊ ልምድ የላቸውም ። የተንሎትም ከጦር ኃይሉ

ውስጥ የፖለቲካ መሠረት ሳይኖራቸው ነው ። ስለዚህም አንድ ወታደራዊ መሪ በጣም ኃይለኛ እንዳይሆንባቸው ማዳም መኰንኖቹን ሁልጊዜ ከቦታ ቦታ ይቀይራሉ ። አደገኛ ተቃዋሚ ሊሆኑ የሚችሉት ደግሞ ይገደላሉ ። እንደሚባለው ኢራቅ ከኢራን ጋር ጦርነት ስታካሂድ በነበረችበት ጊዜ በመጀመሪያ በደረሰው ሽንፈት ላይ አንድ መኰንን በኢራናውያን አክራሪ ወጣቶች በድንገት ተከቦ ጥቃት በተሠነዘረበት ወቅት ወኔው የከዳውን መኰንን ራሳቸው በመገሠጽ ፣ እዚያው ሽጉጣቸውን መዘው ገድለዋቸዋል ። ማዳም በ1974 ከ(ምዕራብ) ጀርመኑ መጽሔት ከ"ስተርን" ጋዜጠኛ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ፣ከኢራን ጋር ባካሄዱት ጦርነት ኸራ ምሻር በተደረገው ውጊያ ኃላፊነታቸውን በሚገባ አልተወጡም በማለት ከፍተኛ የጦር መኰንኖችን በሞት መቅጣታቸውን አረጋግጠዋል ።

በዚህ ዓይነት መንገድ የጦር ኃይሉን ታማኝነት ለማረጋገጥ ፣ ከኢራን ጋር በተካሄደው ረጅም ጦርነት ውስጥ አስቸጋሪ ሆነ ። ይህም አፈጻጸም የጦር ኃይሉን የውጊያ ብቃት ብዙ ቀንሶታል ። በዚህም ሳቢያ፣ ማዳም ውሎ አድሮ ለጦር ኃይሉ ራሱን የቻለ ነፃ ሥልጣን መልሶ ለመስጠት ፣ ተገደዱ ። እንደተፈራው አልቀረም ፣ ጀኔራሎቹ በሕዝብ ዘንድ እየታወቁና ዝነኛ እየሆኑ ሄዱ ። ጦርነቱ ሲያበቃ ግን ቁጥጥራቸውን ለማጥበቅ ማዳም ጥረታቸውን እጥፍ ድርብ አደረጉ ። ከታኅሣሥ 1980 እስከ መጋቢት 1981 ባለው ጊዜ ውስጥ ብዙ መቶ መኰንኖች አሠሩ ፣ ብዙዎችንም ረሸኑ ። እንዲሁ ልጃቸውን ለማዳም ልጅ ፣ ለቁሴይ የዳሩት ፣ በጦርነቱ ጀግና የነበሩትና ፣ ኢራቅ ውስጥ በጣም የተከበሩት ጀኔራል ማኸር አብዱል ረሺድ ፣ በአደባባይ ከመታየት ተሠወሩ ።

ማዳም ሕዝባቸውን ለመከራና ስቃይ ለምን እንዳደረጉት ለማወቅ ፣ ምናልባት አስቸጋሪ ይሆናል ። ከሁሉም በላይ ኢራቅ ከፍተኛ የነዳጅ ሀብት አላት ፣ ታዲያ ራሳቸው ባመጡት መዘዝ ፣ በመካከለኛው ምሥራቅ ደረጃ እንኳ ቢለካ ፣ እጅግ ከመጠን በላይ በሆነ መንገድ ፣ ያገሪቱን ወጣት ለምን ለሞት ይማግዳሉ? ያገሪቱንስ ሀብትና መጪ እድል ለምን ያባክናሉ? ለምንስ ይጨርሳሉ? በማዳም ባሕርይ ውስጥ አንድ ነገር አለ ። "ዘ ግሬት ቴረር" የተባለው ጥናታዊ መጽሐፋቸው ደራሲ ሮበርት ኮንኴስት ፣ ስለስታሊን የደሴት ወሀኒ ፀምባ በጻፉት የማሳደድ ዓላማ ፣ ማሳደድ ነው ። የማሰቃየት ዓላማ ፣ ማሰቃየት ነው ። የሥልጣን ዓላማ ሥልጣን ነው ።" በማለት በከፊል መልሰውታል ። አሁንም ቢሆን ፣



እያንዳንዱ አድራጐት ካለፈው በበለጠ ቁጣና ጭካኔ በተመላበት የሚፈጸመው ፣ ሰውን የማስወገድ ፣ መጨረሻ የሌለው ተግባር ፣ ምን ማለት እንደሆነ መረዳት ያስቸግራል ።

፬

# የናቡከደነጾር ቅርስ

ሣዳም አገዛዛቸውን ለማጠናከርና ተቀባይነት እንዲኖረው ለማድረግ ፡ ያለማወላወል በሽብር የመጠቀማቸው ባሕርይ በታሪክ ውስጥ ጥልቅ መሠረት አለው ። የኢራቅ ሕዝብ እንደ ግብጽ ዓይነት ፡ ዓረብ ሕዝብ ሳይሆን ፤ በባእድ ኃይሳት የተሰባሰቡ ግለፍተኛ ጐሳዎች የሚገኙበት ውጥንቅጥ ሕዝብ ነው ። የሣዳም አገዛዝ ከዚህች የተለያየ ብሔረሰብ ካለባት አገር በመነሣት ፤ በዚህ በያዝነው ምእታመት መነሻ ገደማ ላይ የአውሮፓ ቅኝ ገዢዎች የከለሉትን ነባር ብሔራዊ ድንበር ባለመቀበል፣ በመላው ዓረብ ስም ፡ የማይሆነውን አንድወጥ ብሔር ለመመሥረት አስበዋል ። ስለሀገር ፍቅር የሚደረገው ቅስቀሳ ፡ ከቅኝ አገዛዝ በፊት ያለውን ታሪክ በማውሳት ፤ በቀድሞው ታሪክ ስም ነው ። ይህ ያለፈ ጊዜ ግን ፡ ኢራቅ ራሷ ያልነበረችበት ጊዜ ነው ።

ሣዳም ወደፊት ክብርን ለማግኘት እንዲያገለግላቸው ፡ ያለፈውን ታሪክ ለመመዝገብ የያዙት ዘመቻ በከንቱ ውዳሴ መደለላቸውን ያመለክታል ። የራሳቸው ዓይነት ጥንታዊ ባቢሉን ለመገንባትም ግዙፍ እቅድ አውጥተዋል ። ብዙ ሚሊዮን ጡብ ተሠርቷል ፡ በብዙ ጡብ ላይ "የናቡከደነጾር ባቢሉን ፤ በሣዳም ሑሴን ዘመን እንደገና ተገነባች" የሚል ጽሑፍ ተቀርጾባቸዋል ። ሣዳም በስፋት የኋለኛውን ዘመን ናቡከደነጾር ተመስለው ይታያሉ ፣ ናቡከደነጾር ከክርስቶስ ልደት በፊት ፣ በስድስተኛው ምእታመት የባቢሉን ገዥ ነበር ፤ ዝክረ ታሪኩን ብሉይ ኪዳን እንዳቆየው ፡ ኢየሩሳሌምን ድል አድርጐ የገዛ ፡ ዕብራውያንን በምርኮ የወሰደ መሪ ነው ። በአንድ የሕዝብ በዓል ምሽት ላይ በተደረገ ግብዣ ዲፕሎማቶችና ሌሎችም ተጋባዥ እንግዶች ወደ ጥቁሩ የበረሃ ሰማይ ዓይናቸውን እንዲያቀኑ ተጠየቁ ፡ ቀና ሲሉ ከበላያቸው ባለው ጨለማ ላይ በሌዘር (ኃይለኛ ብርሃን የሚፈነጥቅ መሣሪያ) ጨረር ተወርውሮ ያረፈ ፡ መንታ ምስል ጐን ለጐን ሆኖ አዩ ፡ የሣዳምና



የናቡከደነጾር ምስል ነበር ፤ ከናቡከደነጾር ጥንታዊ ቅርጽ ምሥል ጋር እንዲቀራረብ ፡ የሣዳም ምስል ከተለመደው ውጭ የተቀረጸና የጠነከረ መልክ ተሰጥቶቷል ።

የኢራቅ ያወደፊት እድል ፡ ምስጢራዊ ሐሳብ ካለው ከጥንታዊ ሜሶፖታሚያ ታሪክ ጋር ተያይዟል ። ግሪኮች ፣ ኢራቅን "ሜሶፖታሚያ" የሚለውን ስም ሰጥተዋታል ፡ ትርጉሙም "በሁለት ወንዝ መኻል የሚገኝ መሬት" ማለት ነው ። በርግጥም ጤግሮስና ኤፍራጥስ የአሁን ጊዜዋ ኢራቅ እምብርት ናቸው ። የባግዳድ ከተማ በጤግሮስ ወንዝ ላይ ትገኛለች ። የጤግሮስ ወንዝ ከቱርክ ተነሥቶ ወደ ደቡብ ይፈስሳል ። የኤፍራጥስ ወንዝ ደግሞ ከበስተምዕራብ ፡ ከሶርያ ፡ ተነሥቶ ሁለቱም ወንዞች ከባስራ ከተማ በላይ ይቀሐዳሉ ። ከኢራቅ ከተሞች በትልቅነት ሁለተኛዋ ባስራ ፣ የደቡብ ኢራቅ ዋና ከተማ ናት ። ወንዞቹ ከተቀሐዱ በኋላ ፣ የባሕር መተላለፊያ ቦይ —ሻት አል ዓረብን ፡ "የዓረቦች ወንዝ" ይፈጥራሉ ። ሻት አልዓረብ ከባስራ በስተደቡብ በኢራንና በኢራቅ መኻል እንደ ድንበር ሆኖ ያገለግላል ።

ከካሊፎርኒያ ሰፋ ያለችው ኢራቅ አሥራ ሰባት ሚሊዮን ሕዝብና ልዩ ልዩ የመሬት አቀማመጥ አላት ። ከኢራቅ ሕዝብ ሃያ በመቶ ያኸሉ የሱኒ እስላም ዓረቦች ከባግዳድ በስተሰሜን በሁለቱ ወንዞች መኻል ይኖራሉ ። ከባግዳድ በስተደቡብ የሚገኘው ለምና ሜዳማ መሬት ደግሞ ከኢራቅ ሕዝብ 55% የሚሆኑት የሺዓ እስላም ዓረቦች ተፋፍገው ይገኛሉ። ሺዓዎች ከጠቅላላው ሕዝብ ግማሽ የሚያልፉት ለጥቂት ቢሆንም ከሌሎች የበለጠ ሁለገብ ናቸው ። የዓረብ ዘር የሌላቸው ፡ በአብዛኛው የሱኒ እስላሞቹ ኩርዶች ደግሞ ከአገሬው 20% ሲሆኑ በኢራቅ ሰሜናዊ ተራራማ ቦታዎች ይኖራሉ ። ምዕራብ ኢራቅ ፡ በአቀማመጡ የታላቁ የሶርያ በረሃ አካል በመሆኑ አልፎ አልፎ ዘላን የዓረብ ጐሣዎች ብቻ ይኖሩበታል ። በረሃው በምዕራብ ዮርዳኖስና በምሥራቅ ሳዑዲ ዓረቢያ መኻል በማለፍ ፡ እስከ ማእከላዊ ሶርያ ይደርስና የግማሽ ጨረቃ ምሥል ቅርጽ ይይዛል ።

የኤፍራጥስና የጤግሮስ ወንዞች የኢራቅን እምብርት ይወስናሉ ። የዘመናችን ኢራቅ በ1908 ብሪታንያና ፈረንሳይ በአንደኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ፣ የዑስማናውያንን ግዛት ለመከፋፈል በቅድሚያ ካደረጉት

ስመ ጥሩ የስኪስ-ፒኮት ስምምነት ተገኘች ። ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ፣ ብሪታንያ ፣ ሦስት የቀድሞ የዑስማናውያንን ግዛት በማዋሐድ ባግዳድን ፣ ባስራንና የሰሜኗን ከተማ ሞሱልን ማእከል በማድረግ አዲሷን የኢራቅ መንግሥት መሠረተች ።

ሰው ሠራሽ ያልሆነው የኢራቅ ድንበር ፣ ከኢራን ጋር የሚያዋስነው ብቻ ነው ። ይህ ድንበር በፋርስና በዑስማናውያን ግዛት መኻል አዋሳኝ በመሆን ለ250 ዓመት ቆይቷል ። ከዚህ ድንበር በስተቀር ፣ አብዛኛው ሌላው የኢራቅ ድንበር-በስተደቡብ ከኩዌትና ከሳዑዲ ዓረቢያ ፣ እና በስተምዕራብ ከዮርዳኖስና ከሶርያ ጋር ያሉት ድንበሮች ሁሉ ትንሽ ቢወላገዱም በአሸዋማው መሬት ላይ በብሪታንያ የተሠመሩ ቀጥተኛ ወሰኖች ናቸው ። ነገር ግን የኢራቅና የቱርክ ድንበር ያው የቀድሞው የዑስማናውያን ሞሱል ክፍለ ግዛት ድንበር ነው ። ሆኖም ይህም የኢራቅና የቱርክ ድንበር እዚያ የሚኖረውን የኩርድ ሕዝብ ለሁለት ይከፍላል ።

መልክአምድር በኢራቅ ላይ ጨክኖባታል ፣ ኢራቅ ነፃ አገር ብትሆንም የሰፊው የዑስማናውያን ክፍለ ግዛት ሳለች ያልነበረ ችግር አሁን እየጐዳት ነው ። መጀመሪያ ነገር ፣ ኢራቅ የተፈጥሮ መከላከያ የላትም ። ኢራቅ ሁልጊዜ እንደምትመሳሰላት እንደጀርመን በጠላት ኃይሎች የመከበብ ችግር ያጋጥማታል ፣ በኤፍራጥስና በጤግሮስ ወንዞች ዙሪያ ያለው መሬት ጭው ብሎ የተንጣለለ ሜዳ ከመሆኑ አኳያ ፣ የሜሶፖታሚያ አካባቢ በታሪክ ውስጥ ከሁሉም አቅጣጫ በቀላሉ ለወረራ ተጋልጦ መቆየቱ አያስገርምም ።

እልፍ ተርፎ ፣ ሁለት የኢራቅ ታላላቅ ከተሞች ለጥቃት በጣም የተጋለጡ ናቸው ። ባግዳድ ከኢራን ድንበር 112 ኪሎሜትር ርቃ ስትገኝ፣ ባስራ ደግሞ 20·8 ኪሎሜትር ብቻ ትርቃለች ። በኢራቅና በኢራን ጦርነት ጊዜ ፣ ኢራቅ የሚሳይል መርሀግብሯን ዘርግታ በእኩልነት ደረጃ ከመሰለፏ በፊት ባግዳድ ለኢራን ሚሳይል የተጋለጠች ነበረች ፣ በሌላ በኩልም ባስራ ሁልጊዜ ከመከበብ የምታመልጠው ለጥቂት ነበር ። ከዚህም በላይ ኢራቅ በማንኛውም በኩል ሰፊ የባሕር በር የሌላት አገር ናት ። ወደ ባሕር መግቢያ ያላት በፋርስ ባሕረ ሰላጤ ጠረፍ ላይ በ41·6 ኪሎሜትር የተወሰነ በር ፣ ወደ ኢራቅ መርከብ የሚያስገባው ፣ የሻት



አልዓረብ የባሕር የመተላለፊያ ቦይ ብቻ ነው ። በ1972 የተነካው የባሕረ ሰላጤው ጦርነት የሻት አልዓረብ የባሕር መተላለፊያ ቦይ ሲዘጋው ፣ ኢራን የኢራቅን የባሕረ ሰላጤ ወደቦች መግቢያና መውጫ እንዲቋረጥ አደረገች ። በጦርነቱ ጊዜ ፣ ኢራቅ ወደ አገር ውስጥ አስፈላጊ አቅርቦት በማስገባት ረገድ ሙሉ በሙሉ የአጐራባች አገሮች ፣ በተለይም የዮርዳኖስ ጥገኛ ሆነች ።

ሳዳም ሑሴን ሥልጣኔ የተጀመረባት ምድር መሪ መሆናቸው የሚገርም የታሪክ አጋጣሚ ነው ። በዘመናችን ባግዳድ ካለችበት በስተደቡብ ባለው የሜሶፖታሚያ ሜዳ ላይ ከክርስቶስ ልደት 3 ሺ ዓመት በፊት ይኖሩ የነበሩት ሱሜራውያን ፣ በዓለም የመጀመሪያውን የአጻጻፍ ሥርዓት ፣ የከተማ ኑሮ ባህልና የአስተዳደር ሥርዓት አፍልቀው አስፋፉ ።

ከአንድ ዓመት በኋላ ሜሶፖታሚያ በሁለት የተለያየ አገዛዝ ተከፋፈለች ፣ በባህልና በሳይንሳዊ ግኝታቸው የታወቁት ባቢሎናውያን የደቡቡን ክፍል ገዙ ። ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ1ሺ 792 እስከ 1ሺ 750 የኖረው ታላቁ ንጉሥ ሐሙራቢ ፣ የመጀመሪያውን በልምድና በባህል ላይ የተመሠረተ ድንጋጌ በማውጣት ፣ የኅብረተሰብ መተዳደሪያ ሕግ ጻፈ ። በባሕረሐሳብ ጥናት የታወቁት ባቢሎናውያን ፣ ከእነርሱ በመቀጠል ዓለም በአሁኑ ጊዜ የሚጠቀምበትን የጊዜ መለኪያ ሥርዓት ፈለሰሙ ። ያንዱን ሰዓት በስድሳ ደቂቃ ፣ አንዱን ደቂቃ ደግሞ በስድሳ ሰኮንድ ከፋፈሉት ። ለዚህም ዋናው ምክንያት ስድሳ የባቢሎናውያን አገዛዝ ሥርዓት መሠረት በመሆኑ ነው ።

የባቢሎናውያን ተወዳዳሪ የነበሩት አሦራውያን የሞሶፖታሚያን ሰሜናዊ ግማሽ በእጃቸው አስገቡ ። ዋና ከተማቸውን ነነዌን የአሁኗ ሞሱል ከተማ ካለችበት አጠገብ መሠረቱ ። ጦረኛና የግዛት ይዞታ ፍላጐት የነበራቸው አሦራውያን የመጀመሪያውን ወታደራዊ ባህል አበለጸጉ ። ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ744 እስከ 727 የነበረው የአሦርያ ታላቅ ግዛት አስፋፊ ግልባዊ ቲግላዝ ፒሌሰር በግዛታቸው ውስጥ – በጽኑ የፖለቲካ አስተዳደር ሥርዓት ቁጥጥር ሥር ፣ መደበኛ ሠራዊት እንዲኖር ሐሳብ አመንጭተው አስፋፉ ። አሦራውያን ፣ በተጨማሪ በጭካኔያቸው የታወቁ በመሆናቸው ፣ አገዛዛቸው በሚገዙት ሕዝብ ላይ ያልተፈለገ ውጤት አስከተለ ። ሕዝቡ ዘወትር ስለሚያምጽባቸው

ግዛታቸው በቀላሉ የሚፈረካከስ ሆነ ።

እንደ ሌላው ጥንታዊ ነገር ሁሉ አሶራውያንም ትልቅ ድንጋይ ፈልፍለው ፣ ምሥላቸውን ይቀርጹ ነበር ፣ ከክርስቶስ ልደት በፊት በሰባተኛው ምእታመት ፣ ከ668 እስከ 627 የነበረው የንጉሥ አሱርባኒፖል ምሥል ፣ የአሶራውያንን ጭካኔ ይመሰክራል ። ዛሬ ባግዳድ ውስጥ እንደሚገኘው ፣ በጦርነት በወደቁ ወታደሮች የተጨራመቱ ራስ ቁሮች በላይ ፣ እጁን እንደጨበጠ አውጥቶ ከንዱ እንደሚታየው የሳዳም የነሐስ ሐውልት ፣ የአሱርባኒፓልም ከድንጋይ የተፈለፈለ ምሥል ከዛፍ ላይ ከተንጠለጠለ የጠላቱ ጭንቅላት ፊት ቆሞ ፣ ሁሪያውን በሬማ ከምር ተከቦ ይታያል ። ምንም እንኳ የአሶርያው ከድንጊያ የተፈለፈለው ምሥል እንደ ታላቅ ጥንታዊ የኪነጥበብ ሥራ ቢቆጠርም ሲያገለግል የነበረው ግን እንደ ሳዳም የቪዲዮ ቴፕና አምልኮተ ግለሰብ ፣ በአጠቃላይ የመሪዎቹን ኃያልነትና ጭካኔ ለተገዢው ሕዝብ ለማስታወስና ሥልጣናቸውንም የማይደፈርና የማይገሰስ ለማድረግ ነው ። እንዲሁም በጥንታዊቷ አሶርያና በዘመናዊቷ ኢራቅ መኻል ሌላ ተመሳሳይነት አለ ። አንድ በችሎታው የተከበረ የታሪክ ቅርሶች ተመራማሪ ፣ በሰጠው ማስረጃ እንዳለው የአሦራውያን የግዛት ፍለጋ ያልተቋረጠ ጦርነት ምክንያት ውስጣዊ ችግር ነው ። ለመስፋፋት የተነሡት ደግሞ ፣ "ከሥርዓቱ ድክመት ብቻ" ነው ።

ከክርስቶስ ልደት በፊት በ500 ገደማ ጥንታዊ የሜሶፖታሚያ ሥልጣኔ ፍጻሜ ላይ ደረሰ ። ባቢሎንና አሶርያ በታላቁ ንጉሥ ቂሮስ እጅ ወደቁ ። በሚቀጥሉት ዓሥራ አንድ ምእታመታትና ከዚያም በላይ ዘመናት ልዩ ልዩ የግሪክና የፋርስ ገዢዎች ሜሶፖታሚያን አስገብረዋል። ይሀም የዓረብ እስልምና ወረራ ፍጹም አዲስ ነገር እስካመጣበት እስከ ሰባተኛው ምእታመት ቆየ ።

ሳዳም ሑሴን ከኢራን ጋር ያካሄዱትን ጦርነት "ቃዲሲያት ሳዳም" ብለው ሰይመውታል ። ይህን ያሉበት በ629 ፣ ቃዲሲያት ላይ በተደረገው ውጊያ አዲስ የእስልምና ተከታይ የዓረብ ጎሳዎች የዞራስተር ሃይማኖት ተከታይና የሜሶፖታሚያ ገዥ የነበሩትን ፋርሶች ድል ያደረጉበትን ዕለት በማስታወስ ፣ የዚያን ጊዜ መንፈስና ትዝታ ለአሁኑ ትውልድ ለማላበስ ነው ። እስላሞች ወደ ሜሶፖታሚያ ሃይማኖታቸውን ይዘው መምጣት ብቻ ሳይሆን በአገሪቱ ውስጥ የዓረብን የበላይነት በማሥፈን ፣



"ኢራቅ" የሚለውን ዘመናዊ ስሟን ጭምር አወጡላት ። ሆኖም ኢራቅ የተመሠረተችበት የመጀመሪያው መቶ ዓመት የእስላሞች አገዛዝ ሁከት የበዛበት ነበር ። በእስልምና ውስጥ ፣ ገና ከመነሻው የታየው መከፋፈል ፣ ኢራቅ ውስጥ በሚገኘው ውጥረት ይንፀባረቅ ነበር ። ከዚህ መከፋፈል ዋነኛው ፣ የሱኒና የሺዓዎች መለያየት ነበር ። የዚህ መለያየት መነሻ ምክንያት ፣ የነቢዩ መሐመድ ወራሽ ማን ይሁን ? የሚለው ጭቅጭቅ ወይም ክርክር ነበር ። አንዱ ቡድን ፣ የነቢዩ አጐትና አማች የአሊ ሺዓ ወይም "ፓርቲ" ፣ አሊ የነቢዩ መሐመድ ወራሽ እንዲሆን ፈለገ ። ሱኒ የተባለው ሁለተኛው ቡድን ደግሞ የቀድሞዎቹ የመካ ባላባቶች እንዲወርሱ ፈለጉ ። መካ እስልምና የተወለደባትና ከሁሉም ይልቅ የተቀደሰች የእስልምና መካን ናት ። ሱኒዎች አሸንፈው ሦስት ሰው መረጡና እነዚህ ሰዎች በተከታታይ እስልምናን መሩ ። ነገር ግን ፣ በ648 የዓረብ ወታደሮች ሦስተኛው ኸሊፋ—ዑስማን ፣ ፍትሕ የማይከተሉና በዘመድ አዝማድ የሚመሩባቸው ብለው ስላመኑ በቁጣ ሁከት አንሥተው ኸሊፋ ዑስማንን በመግደል አሊን ኸሊፋ ማድረጋቸውን አወጁ ።

ይሀም የርስበርስ ጦርነት አስከተለ ። አሊ ከዛሬይቱ ባግዳድ በስተደቡብ ምዕራብ ወደምትገኘው የዚያን ጊዜ የኢራቅ ዋና ከተማ ወደ ኩፋህ አፈገፈጉ ። የተገደሉት የኸሊፋ ዑስማን አጐት ፣ የሶርያው ገዥ ሙዋያኽ ለመበቀል ተነሡ ። አዲሱ ኸሊፋ አሊም ልበተል ባዩን ሙዋያኽን ውጊያ ለመግጠም የጦር ኃይላቸውን ይዘው ወደ እርሳቸው ገሠገሡ ። አሸናፊው ካልለየበት ትንሽ ግጭት በኋላ አሊ ከሙዋያኽ ጋር ለመታረቅ ተስማሙ ፣ ነገር ግን ፣ የአሊ ግትር ደጋፊዎች መደራደሩን የፍትሕን መንገድ እንደመቀበል በመቁጠር አሊን ገደሏቸው ። ቀጥሎም ሙዋያኽ ኸሊፋ በመሆን አዲሱን የኡማያድ ሥርወ መንግሥት መሠረቱ። የእስልምናን መንበርም ወደ ደማስቆ አዛወሩ ። ኸሊፋ አሊም ናጃፍ ውስጥ ተቀበሩና ናጃፍ በጣም ተፈላጊ የሺዓ እስላሞች ቅዱስ የመስጊድ ከተማ ሆነች ። በ1960 ዎቹ አያቶላኽ ኾሚኒ በዚያች ከተማ ወስጥ ብዙ ዓመት በስደት ኖረዋል ። የአንድ ትውልድ ዘመን ካለፈ በኋላ ፣ የነቢዩ መሐመድ የልጅ ልጅ የአሊ ልጅ ሑሴን ፣ አባታቸው ሲሞቱ በመተካት በኸሊፋ በሙዋያኽ ልጅ ላይ አመጹ ። በ672 የኩፋህ ሕዝብ ሑሴን አመጻቸውን እንዲመሩላቸው በመጋበዝ ፣ ሑሴንን ጠየቁ ። ሑሴን ከመምጣታቸው በፊት ግን የኡማያድ ባለሥልጣኖች ኩፋህያኖችን

በማስፈራራት ጸኖ ስላደረጋቸው ሑሴን በቀውጢ ጊዜ ለኩፋህ ሕዝብ እንዳችም ድጋፍ ሳይሰጡ ቀሩ ። ብዛት ያለው የኡማያድ ጦር ሠራዊትም ሕዝቡ የከዳቸውን ሑሴንንና ጥቂት ተከታዮቻቸውን ካርባላህ አጠገብ ባለው ሜዳማ ቦታ ላይ ከበው ፈጇቸው ። የሑሴን ሰማዕትነት የሺዓዎ መመሪያ ትምህርት ሆነ ። በጀግንነት ሞትን ፊትለፊት ተጋፍጠው ራሳቸውን ማሠዋታቸው ደግሞ ጥልቅ ስሜትና ወኔ ለሚቀሰቅሱ ተውኔቶች መነሻና መወያያ ርእስ ሆነ ። ካርበላህ በተራዋ ኢራቅ ውስጥ የሺዓዎች ሁለተኛ ቅዱስ መስጊድ ከተማ ሆነች ።

እስከ 686 የኡማያድ ባለሥልጣናት ምሕረት የለሹን አልሃጃጅን ገዥ አድርገው እስከ ሾሙ ድረስ ኢራቅ አልተረጋጋችም ። አልሃጃጅ ወደ ኩፋህ ሲገቡ ፡ ሕዝቡን ሰብስበው የሚከተለውን ዲስኩር አሰሙ ፡—

> እርስበርስህ የማትስማማው ግብዙ የኢራቅ ሕዝብ ሆይ ··· ለብዙ ብዙ ችኩል በመሆንህ የተደራረበ ስሕተት በመፈጸም ፡ ሁከትን አስፍነሃል ። በእሳህ ኃይል እንደ ቅርፊት እልተሃለሁ ፡ እንደ ጭራሮ እጠፍርሃለሁ ከመንጋው እንዳፈነገጠ ግመል እገርፍሃለሁ ፡ ··· በእሳህ ኃይል የገባሁትን ቃል እከብራለሁ ፡ ያሰበኩትን እፈጽማለሁ ፡ የለካሁትን እቆርጣለሁ

ምንም እንኳ ፡ አልሃጃጅ ስሙ ጥፉ ጨካኝ ቢሆንም ፡ ለኢራቅ ሰላምን እንዳመጣ ፡ ንግድና እርሻ እንዳስፋፋ ብቃት ያለው ገዢ ተቆጥረዋል ።

አዲሶቹ እስላም መሪዎች ባግዳድን በመንግሥት ርእስ ከተማቸው አደረጓት ። ከ642 እስከ 1250 በነበረው የአባሲድ ኸሊፍ ዘመን መንበረ እምነቱን ይዘው በቆዩባቸው ዘመናት እስልምና ከፍተኛውን የባህል ደረጃ ተቀዳጀ ። ከሜሶፖታሚያ ሥልጣኔ ጀምሮ እስካለንበት ዘመን ለሁለት ሺ አምስት መቶ ዓመት የቆየው የአባሲዶች ዘመን ኸሊፍነት ኢራቅ የደረሰችበት ከፍተኛ ፖለቲካዊና ባህላዊ የእድገት እርከን መለያ ምልክት ሆኗል ።

አባሲዶች ከዛሬይቱ አፍጋኒስታን ጀምሮ እስከ ሰሜን አፍሪካ ድረስ ላለው እጅግ በጣም ሰፊ ክልል የእስልምና መሪዎች ሆነዋል ። በዚህም ክልላቸው ውስጥ የፋርስ፣ የግሪክና የዓረብን ዐውደ ጥበብ በማጣመር እንዲስፋፋ አበረታተዋል ፡ ከዚህም ጥምረት በልዩ ልዩ የትምህርት ሥርዓት ፈጣን የፈጠራ ሥራ ተኽኑደኑደ ። ሒሳብ ፡ ኬሚስትሪ ፡ ሥነፈለክ (አስትሮኖሚ) ፡ ሕክምና ፡ መልክአ ምድርና ሥነ ጽሑፍ ተስፋፋ ። እንዲሁም አባሲዶች ዝነኛውን የጥናትና ምርምር ቤተ



መጻሕፍት "ቤይት ኧል—ሒክማ" ወይም "የዕውቀት ቤት" አቋቋሙ ። የዓሥራ ሰባተኛው ምእታመት ሴሰኛ ገጣሚ አቡናዋስ ፡ ግጥሙን ያዋለው ለፍቅርና ለወይን ነበር ። ኢድሪስ ፡ የመጀመሪያውን የዓለም ካርታ ሣለ ። ከስሙ "አልጉሪዝም" ና "ሎጋሪዝም" የሚባሉት ስያሜዎች የወጡት፣ የሒሳብ ሊቁ "አልካዋሪዝሚ" የአልጀብራን ጥናት በማጠናቀር "አልጀብራ" የሚባለውን መጽሐፍ አዘጋጁ ። ከዚህም መጽሐፍ ከሒሳብ ትምህርት አንዱ— "አልጀብራ" ተሰየመ ።

አባሲዶች የኢራቅ ገናና የእስልምና መሪዎች የሆኑትን ያኸል ፡ ድክመት ያየለባቸው የኢራቅ የሃይማኖት መሪዎችም እነሱው ነበሩ ። የጥንታዊት ፋርስ ነገሥታት በዘመናቸው ከነበሩት የአሶርያ ነገሥታት የሚጋሩት ጭካኔና ፍጹማዊ የንጉሥ አገዛዝ ልማድና ሥርዓት ነበራቸው። አባሲዶችም ዓረቦች ቢሆኑም የፋርስን ልማዳዊ የአገዛዝ ሥርዓት ተከትለዋል ። የኡማያድ ኸሊፍ ሥርወ መንግሥት ከተገለበጠ በኋላ ከ742 እስከ 746 የነበሩት የመጀመሪያው አባሲድ ኸሊፍ አልሳፋህ የቀድሞዎቹን የገዢ ቤተሰቦች አባላት ያለምሕረትና ልዩነት አርደው ፈጇቸው ። የአባሲድ ተባባሪዎች እንኳን ሳይቀሩ በዚህ የጭካኔ አመራር በቀላሉ አልታለፉም ። ሺዓዎች ለምሳሌ ፡ ቁልፍ የአባሲድ አመጽ ደጋፊዎች ስለነበሩ ራሳቸውን የማስተዳደር ነፃነት አግኝተው ነበር ። ኸሊፍ አልመንሱር ፡ የአልሳፋሽ ወራሽ ፡ የሺዓዎችን መሪ ገድለውባቸዋል ። ይህን ያደረጉትም ለእርሳቸው ፍጹም ተገዢ ያልሆነ ተቀናቃኝ ኃይል እንዳይኖር ለማጥፋት ነበር ። የእያንዳንዱን የሺዓዎች ክፍለ አስተዳደር ዝርዝር ተግባር ለመቆጣጠር አልመንሱር ሰፊ የአስተዳደር ሥርዓት ከመዘርጋታቸውም ሌላ ፡ የራሳቸውን ቤተሰብ ሥልጣን ላይ ለማውጣት የሚያሴሩትንም ለመከላከል ትልቅ የስለላ መረብ ዘረጉ ።

አባሲዶች የፋርስን ነገሥት ቤተ መንግሥት የዕለት ተዕለት የአሠራር ልምድ ሆን ብለው ቀሰሙ ። በዚህም የአሠራር ልምድ ኸሊፋን ከሰውነት ተራ አውጥተው ድንቅ መለኮታዊ ሥልጣን እንዳለው ፍጡር በመቁጠር አንዳንድ ጊዜ ሳይጠበቅ በድንገት ለሚናገሯቸው ቃላት እንኳ እንደመለኮታዊ ሕግ መታዘዝን ግዴታ አደረጉት ። ኸሊፋን ቀርበው ሊያነጋግሯቸው የሚችሉት ልዩ መብት የተሰጣቸው ጥቂት ሰዎች ብቻ ሆኑ ። እፊታቸው ለመቅረብ ፡ ጫማቸው ሥር ወድቆ መሬት መሳምን ጨምሮ፣ ጥንቃቄ የተሞላበት ዝርዝር ሥነ ሥርዓት ወፈን ።

ይሁን እንጂ ፣ የአባሲድ ኸሊፎች ከጊዜ በኋላ ፣ ፍጹማዊ አስተዳደራቸውን ለማጠናከር ቅጥረኛ የቱርክ ወታደሮች አመጡ ። በስምንተኛው ምእታመት ማለቂያ ላይ ግን ቱርኮች በቤተ መንግሥቱ ውስጥ የበላይነትን አገኙ ። የባግዳድ ዕውነተኛ ገዢዎች እነሱ ሆኑ ። የኸሊፋን ሥልጣን ገፈው ፣ የይስሙላ ገዢ ብቻ እንዲሆን ካደረጉ በኋላ ሥልጣኑን በፈቃዳቸው እንዲለቁ እያስገደዱ በየጊዜው ኸሊፍ መለዋወጥ ጀመሩ ። ይህም ተግባር በበኩሉ መንግሥቱ እንዲዳከምና ሕገ አልባነት በማንኛውም ቦታ እንዲስፋፋ አደረገ ።

በዚህም ምክንያት ፣ የሞንጉል ጦር ሠራዊት በኢራቅ ድንበር ላይ ብቅ ባለበት ጊዜ ፣ ቀደም ሲል የነበረው የኢራቅ ገናናነትና ክብር ከሥፍራው ጠፍቶ ነበር ። ከዓረብ መንግሥታት መካከል በሞንጉል እጥፈ ወረራ የተመታችው ኢራቅ ብቻ ነበረች ። ይህም ወረራ በመውደቅ ላይ የነበረችውን አገር ሙሉ በሙሉ መልሳ እንዳታንሠራራ ውድቀቷን ደመደመ ። በ1250 ፣ የጀንጂስ ካኻን የልጅ ልጅ ፣ የሞንጉል መሪ— ሁላጉ ባግዳድን በመርገዝ አገሪቱን አወደመ ። ለአንድ ሳምንት ያኸል ብዙኃኑ የኢራቅ ሕዝብ እንዳለ መደዳውን በጉራዴ ስለተጨፈጨፈ ፣ የጤግሮስ ወንዝ የደም አበላ ይዞ ጐረፈ ። የታሪክ ሊቃውንት እንደገመቱት ያንጊዜ ፣ ከመቶ ሺ በላይ ሰዎች ታርደዋል ። ባግዳድ ተዘረፈች ። የአባሲድ አገዛዝ ባህልና ትምህርት ፣ ዓይነተኛ መለያ የነበረው ቅርሳቅርስ በሙሉ ተደመሰሰ ። ተጣዮቹ ምእታመታት ፣ የፖለቲካ ብጥብጥ የተስፋፋባቸው ፣ የኢኮኖሚ ቀውስ የተባባሰባቸውና ማኅበራዊ መንኮታኮት የጀመረባቸው የጨለማ ዘመናት ነበሩ ። ኢራቅ ለባዕድ ጦር ኃይል ዝርፊያና ለዘላኖች ድንገተኛ ወረራ ተጋለጠች ። የታሪክ ተመራማሪው ፊሊ ግር እንዳጠኑት ፣ ከአባሲድ ገናናነት ይልቅ ፣ የሃያኛዋን ምእታመት ኢራቅ አካባቢና ባሕርይ ፣ "ለእድገት ሳትንቀሳቀስ ለብዙ ምእታመታት ማንቀላፋቷ" አጥብቆ ገሪው ።

ኢራቅ ውስጥ የተረጋጋና ዘላቂ መንግሥት ተመልሶ መቋቋም የተቻለው ከአሥራ ስድስተኛው ምእታመት በኋላ ነው ። ነገር ግን ይህም አገዛዝ ቢሆን የሕዝቡን ችግር ለማቃለል ያደረገው ጥቂት ነበር ። በዘር ሐረጋቸው የቱርክ ጐሳዎቹ ዑስማናውያን ከማእከላዊ እስያ ፈልሰው በአሥራ ሦስተኛውና በአሥራ አራተኛው ምእታመት ሰፊ ግዛት



መሥርተው ነበር ። በ1445 ውስጥ ቆስጠንጥንያን ወረው ከያዙ በኋላ እንደገና "ኢስታንቡል" ብለው ርእሰ ከተማቸው በማድረግ አገዛዛቸውን አስፋፍተው ከፍተኛ ደረጃ ደረሱት ። ቀስበቀስ ዑስማናዊው ሡልጣን የኸሊፍነትን ማዕረግ ተቀዳጅተው ዑስማናውያን ሱኒ እስልምና የመሆናውን ያኸል በእስልምና ውስጥ የበላይነትን ሥልጣን ያዙ ።

በ1526 ዑስማናውያን ቱርኮች ኢራን ውስጥ ከሚገኘው ከሺዓው ሳፋቪድ ሥርወ መንግሥት ጋር ለረጅም ጊዜ ጦርነት ካካሄዱ በኋላ ኢራቅን ለመጀመሪያ ጊዜ ገዙ ። ከዚያ በኋላ ፣ በተከተሉት ሁለት ምእታመታት ግን በባግዳድ ገዢዎች ስለተፈራረቁ ፣ ኢራቅ የጦር ሜዳ ሆነች ።

ወርር በመግዛትና ተመልሶም ተወርር በመገዛት ተደጋጋሚ ረጅም ጦርነት በኢራቅ የተለያዩ የእስልምና ዘርፍ ተከታዮች መኻል የእርስበርስ ጥላቻ እየተራገበ ፣ ፋርሶች ባግዳድን ወርረው በያዙ ጊዜ ሁሉ ዑስማናውያንን የሚያሞካሹ ሱኒ እስላሞችን ይበቀሏቸዋል ። ዑስማናውያን ባግዳድን እንደገና መልሰው በያዙ ቁጥር ደግሞ የሱኒ እስላሞች የመበተል ጥያቄ ቸል ስለማይባል ፣ ሺዓዎች በተራቸው ሰለባ ይሆናሉ ። መተላለቁ ዑስማናውያን ባግዳድን በ1630 ለመጨረሻ ጊዜ ይዘው ያልተቋረጠ አገዛዝ እስከመሠረቱበት ጊዜ ድረስ ቀጠለ ።

ነገር ግን እስከ አሥራ ዘጠነኛው ምእታመት ድረስ የቱርኮችና የፋርሶች ጠላትነት ብልጭ ድርግም እያለ ጭራሽ ሳይጠፋ ቆይቷል ። ዑስማናውያን ሺዓዎችን መጠርጠራቸው ስለቀረ በአገሬው ሱኒዎች የሰላማዊና ወታደራዊ የበላይ አስተዳዳር ክፍሎች ላይ እምነታቸውን ጣሉ ወይም ሡልጣኑን ሳያገለግሉ ዓረብ ባልሆኑ ወገኖች ላይ እምነታቸውን ጣሉ ። እነዚህ የኋለኞች ትውልዶች ቀስ በቀስ የዛሬይቱ ኢራቅ ከተሜ ሱኒ ባላባቶች አንዱ ክፈል ሆኑ ።

በዑስማናውያን ዘመነ አገዛዝ በሙሉ ደቡብ ኢራቅ ውስጥ በመሥፈር ይኖር የነበረው ሕዝብ ፣ ጭካኔና ነፃነት የነበራቸው ሺዓ ዓረቦች ነበሩ ። የሺዓዎች ቅዱስ ማእከሎች ከርባላና ነጃፍ ዙሪያቸውን በነበረው የገጠር ሕዝብ ላይ ጠንካራ የሃይማኖትና የባህል ተጽእኖ አሳድረዋል ። የደቡብ ኢራቅ ዓረብ ጐሳዎች ቅድመ አያቶች ከዓረቢያ

ወደ ደቡብ ኢራቅ የፈለሱት በዑስማውያን ዘመን አገዛዝ የመጨረሻ ስደት ነበር ። ይህም በተወሰነ ጊዜ የሚደረገው ስደት የዓረቢያና የሜሶፖታሚያ ግንኙነት የረጅም ጊዜ ባሕርይ ነው ።

እነዚህም የዓረብ ጐሳዎች በናጃፍና በካርባላ የሃይማኖት ማእከሎች ተጽእኖ ሥር ሲገቡ ሺዓ ሆኑ ።

ከጊዜ በኋላ የዑስማናውያን ሥልጣን በዋና ዋና ከተሞች ብቻ ከመወሰን በስተቀር ተሻግሮ ሊሄድ አልቻለም ። የገጠሩን አካባቢ የሚቆጣጠሩት የጐሳ መሪዎች ትራንስፖርትና መውጫ መግቢያ በር እንደመጠቀም ያለውን የተወሰነ መብት እስከፈቀዱላቸውና ለሥልጣኑ የይስሙላ ታማኝነት እስካሳዩ ድረስ ዑስማናውያን የዓረብ ጐሳዎቹ እንዳሻቸው እንዲሆኑ ተዉዋቸው ። ዘመናዊው የኢራቅ መንግሥት ሲመሠረት አብዛኛው ሕዝብ ከማንኛውም ማእከላዊ ሥልጣን ጋር የነበረው ትውውቅ ወይም ለእርሱ የነበረው ታማኝነት ዝቅተኛ ነበር ። ከእዚሁ ፣ ካልተለመደውና ተፈጥሯዊ ስሜት ከሌለው የኢራቅ ብሔራዊ ስሜት ይልቅ ጐሰኝነት ፣ በሃይማኖት ዘርፍ ተከታይነት ላይ የተመሠረተ ልዩነትና ለአካባቢ ታማኝነት ይበልጥ ጥንካሬ ነበራቸው ።

ኢራቅን በጦርነትና በሃይማኖት መከፋፈል ካደረሰባት ውድመት ሌላ በተጨማሪ የጐዳት ከኢስታንቡል ርቃ መገኘቷ ነው ። (ከባግዳድ ይልቅ ቪየና ለኢስታንቡል ቅርብ ናት ።) በዚያን ጊዜ በነበረው ኋላቀር መጓጓዣና ዝግተኛ መገናኛ የተነሣ ርቀት ከዛሬው ይበልጥ ረጅም ነበር ። ያኔ ኢራቅ የሥልጣኔ ጭላንጭል ያልታየባት የዑስማናውያን ግዛት ነበረች ። በቤተመንግሥቱ ዘንድ ፊት የተነሡ ሰዎች በከፊልም በግዞተኝነት ጭምር በአስተዳዳሪነት ወደ ኢራቅ ይላኩ ነበር ። የዑስማና ውያን ግዛት ማኅበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እድገት ፣ ኢራቅ የሚደርሰው ከብዙ ዓመት በኋላ እጅግ በጣም ተበርዞ ነበር ። በእርግጥ ኢራቅ ከኢስታንቡል ብቻ ሳይሆን ፣ በይበልጥ ደግሞ ከአውሮፓ እጅግ በጣም ርቃ ትታይ ነበር ። አውሮፓውያን የዑስማናውያን ግዛት ክፍል ከሆነው በሜዲቴራኒያን ባሕር ዳርቻ በሠፈሩበት ጊዜ ፣ ወደ ባግዳድ የመጡት በጣም ጥቂት ናቸው ። በዓሥራ ዘጠነኛው ምእታመት ፣ የአውሮፓ የቴክኖሎጂ እድገት ወደ ካይሮና ወደ ደማስቆ ሲደርስ ፣ ባግዳድ ብዙ ርቀት ወደ ኋላ ቀርታለች ።



ኢራቅ ውስጥ የነበረው የዑስማናውያን አገዛዝ በ1909 አበቃ ። ኢስታንቡል ማእከላዊ ኃይላትን (ጀርመን ፣ አስትሪያንና ሃንጋሪን) በመደገፍ ወደ አንደኛው የዓለም ጦርነት ገባች ። የብሪታንያ ጦር ኃይል ከቱርክ ጋር በረሃ ለበረሃ በጦርነት ላይ በነበረበት ጊዜ አገረ መንግሥቱን ኢራቅን ወረረ ። በጦርነቱ ግፊትና ወደፊትም የሚገኝበትን ጥቅም በማሰብ ብሪታንያ መላ አገሪቱን ከከባድ ጦርነት በኋላ ያዘች ። ጦርነቱ እንዳበቃ ፣ ታላቋ ብሪታንያ ቱርክን ተክታ ሜሶፖታሚያን ያዘች ።

በ1912 የኅብረት ኃይላት የጦር ምርኮ ለመከፋፈል በኢጣሊያ ሳን ሬሞ ውስጥ ተሰበሰቡ ። በዚህ ጊዜ ኢራቅ በብሪታንያ ሞግዚትነት ሥር እንድትተዳደር በተገለጸ ጊዜ በአገሪቱ ውስጥ ትልቅ አመጽ ተለኮሰ ። የጐሳ መሪዎች ፣ የሺዓዎች መሪዎችና ሱኒ እስላም የጦር መኰንኖች ውስጥ ተከታዮቻቸውን አነሣሡ ። ምንም እንኳ ለረጅም ጊዜ በሱኒዎች ተጨቁነው መገዛታቸው የፖለቲካ ንቃት እንዳይኖራቸው ቢያደርግም ዑስማናውያን በተሸነፉ ጊዜ ፣ አጋጣሚውን በመጠቀም የፖለቲካ መብታቸውን ለማግኘት አለመታጋላቸው ሺዓዎች የፖለቲካ ችሎታ እንደሌላቸው ያስረዳል ። በምትኩ ፣ "እስላሞች እስላም ባልሆኑ ወገኖች መገዛት የለባቸውም" ፣ በሚል ምክንያት ብቻ "የብሪታንያን አገዛዝ አንቀበልም" ፣ አሉ ። ስለዚህ ምንም እንኳ በአብዛኛው አምጹው የተዋጉት ፣ የደቡብ ኢራቅ ሺዓ እስላም ጐሳዎች ቢሆኑም ውጤቱ መልኩን የለወጠ የሱኒ እስላሞች የበላይነት ማግኘት ነበር ።

ብሪታንያ የዓረብን አገዛዝ በመፈለግ ለቀረበው ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት አሚር ፈይሳልን በኢራቅ ላይ አነገሡት ። ፈይሳል በምዕራብ ሳውዲ ዓረቢያ የሚገኙትን የእስላም ቅዱስ መካናት የሚገዙት ፣ የሃሺማይት ቤተሰብ ወጣት አባል ሲሆኑ ፣ በአንደኛው የዓለም ጦርነት ዓረቦች በዑስማናውያን ላይ ባመጹ ጊዜ (በኋላ "ላውረንስ ኦቭ ዓረቢያ" በሚል ርእስ በ1954 ዴቪድ ሊን ባዘጋጀው ፊልም የተወደሰው) ከብሪታንያ ጐን በመሰለፍ ዑስማናውያንን ተዋግተዋል ። ጦርነቱ ካበቃ በኋላ ሀሺማይቶች ከፋርስ ባሕረ ሰላጤ ጀምሮ እስከ ሜዲቴራኒያን ባሕር ጠረፍ የሚደርስ ፣ ነፃ የዓረብ መንግሥት እንደሚገዙ ፣ ብሪታንያ የፈይሳልን አባት አሳምና ነበር ። በዚህም አግባብ መሠረት ነበር በጦርነቱ ጊዜ ፈይሳል ከዓለም ጽዮናውያን ድርጅት መሪ ከቻይም

ቺዝማን ጋር ተገናኝተው የባልፎርን ዲክሌራሲዮን በሥራ ላይ እንዲውል በመሠረተ ሐሳቡ የተስማሙት ። የባልፎር ዲክሌራሲዮን ፍልስጥኤም ውስጥ ለአይሁድ መኖሪያ አገር ለመስጠት ብሪታንያ የገባችው ቃል ነው። ነገር ግን ብሪታንያ በጦርነቱ ጊዜ ለሀሺማይቶች የገባችውን ቃል ፈጽማ አላከበረችም ። ያ የተለየ ስምምነት የመሳካት እድል የነበረው ቢሆንም ተጨናግፏል ።

በዚያ ፋንታ ግን ከጦርነቱ በኋላ ፣ የቀድሞ የዑስማናውያን ግዛት የነበሩት የዓረብ ምድሮች በስኮስ — ፒኮት ስምምነት መሠረት በብሪታንያ ወይም በፈረንሳይ ሞግዚት አስተዳደር ሥር ተመደቡ ። አውሮፓውያን በዓረብ አገሮች ውስጥ የራሳቸውን ዓይነት መንግሥት አቋቋሙ ። ብሪታንያ ኢራቅ ውስጥ ፈይሳልን በማንገሥ ሥርዓትን የተከተለ በሕገ መንግሥት የሚመራ የራሷን ዓይነት ሸንጓዊ የዘውድ አገዛዝ መንግሥት መሠረተች ። ነገር ግን ፣ አውሮፓ ውስጥ የሠራው ግዴታ በሌላውም ቦታ ይሠራል ፣ ማለት አይደለም ። ብሪታንያ በተሰጣት ሥልጣን መሠረት የበላይነትን በመያዝ ተጽእኖ ማድረግ ጀመረች ። ብሪታንያ ኢራቅ ውስጥና በሌላውም የዓረብ ዓለም የነበራት ሚና በአገሬው ሕዝብ ዘንድ ፈጽሞ ተቀባይነት አልነበረውም ። ሕዝቡ በዲሞክራሲያዊ መንገድ በሚገለጸው ፍላጐቱና ብሪታንያ በምታደርገው ቁጥጥር መኻል ፣ መሠረታዊ ቅራኔ ነበር ። የብሪታንያን አቋም በመቃወም የማያቋርጥ ቅስቀሳ ተካሂዶ ነበር ። እንዲሁም በባግዳድ ጐዳናዎች ላይ ዘወትር ሰላማዊ ሰልፍ በመደረጉ ሁኔታው በመንገዳገድ ላይ ለነበረው የኢራቅ መንግሥት ያለመረጋጋት ችግር ምንጭ ሆነ ። ብሪታንያ ኢራቅ ውስጥ ያላትን ይዞታ ባለመልቀቅ በቁርጠኝነት መቆሟን በመቃወም መርሀ ግብራቸውን እንድትቀበል ለማስገደድ ፣ ምንም ዓይነት መንገድ እንደሌላቸው ቢያውቁም ፣ የኢራቅ ፖለቲከኞች ብሪታንያን በመቃወም ረገድ እርስ በርሳቸው በመጠራጠር አንዱ ከሌላው በልጦ በመሄድ ሁልጊዜ ተፎካካሪያቸውን ለማዳከም ይፈልጉ ነበር ።

ከብሪታንያ ጥያቄ ሌላ ሕዝቡን የሚወክል ምክር ቤት ያለው ዲሞክራሲያዊ አሠራር እንኳ ኢራቅ ውስጥ ፈጽሞ ሥር አልሰደደም ። ምርጫ የሚካሄደው በማጭበርበር ነበር ። የፖለቲካ ፓርቲዎቹ የጥቂት የግል ጓደኞች ቡድን እንጂ ብዙ ተከታይ አልነበራቸውም ። መንግሥትም በባግዳድ ከተማ ምርጥ ወገኖች መኻል ፣ ሙዚቃ እያዳመጡ



ወንበሮችን በመዞር ድንገት ሙዚቃው ቀጥ ሲል ቀድሞ ወንበር ላይ ለመቀመጥ ወደሚሽቀዳደሙበት "ሚሪጐራውንድ" የትንንሽ ልጆች ጨዋታ ደረጃ ዝቅ በማለት የሥልጣን መፈራረቅ ብቻ ሆነ ። በዘውድ አገዛዙ ሥር የአንድ ካቢኔ ማእከላዊ ዕድሜ ከዓሥራ ስምንት ወር አነሰ ።

ንጉሥ ፈይሳል ሥልጣን እንዲይዙ የተደረገው ኢራቅ ዓረብ ንጉሥ እንዲኖራት ላቀረበችው ጥያቄ ምላሽ ቢሆንም በአገሪቱ ጥልቅ ሥር አልሰደደም ። ፈይሳል በዑስማናውያን ላይ የዓረብ አመጽ በተነሣበት ጊዜ ፣ አብረዋቸው በተዋጉት የጦር መኰንኖች ላይ ከመጠን በላይ እምነታቸውን የጣሉ የዓረብ ልዑል ነበሩ ። የኢራቅ ጦር መኰንኖች ጠንካራ ዓረብ ብሔረተኛ ነበሩ ፣ ሆኖም ፈቃደኝነታቸው ብሪታንያ በያዘችው ሥልጣን ክልል ብቻ ለመሥራት ነበር ። የሚገርመው አንዳንዶቹ ለብሪታንያ ይሰጡት የነበረው ከጥልቅ ስሜት የመነጨ ድጋፍ ነው ። በተለይም ብዙ ጊዜ በጠቅላይ ሚኒስትርነት ያገለገሉት ፣ ኑሪ ሰይድ የብሪታንያ ግንባር ቀደም ደጋፊ ነበሩ ።

በንጉሥ ፈይሳል አጃቢዎች ውስጥ የነበሩት የጦር መኰንኖች ሱኒ እስላሞች ናቸው ። እነሱም የራስን ዕድል በራስ ለመወሰን መርህና ለአገራቸው ክብር በሐቀኝነት ከመቆማቸው ሌላ ፣ ለዓረብ ብሔረተኝነት የሰጡት ድጋፍ ኢራቅን በስፋት የሱኒ የበላይነት ካለው የዓረብ ዓለም ጋር አጐዳኝቷታል ። በተጨማሪም አብዛኞቹ ሱኒ ዓረብ ባልሆኑባት በኢራቅ የአገዛዝ ዘመናቸውን ለማራዘም በቂ ምክንያት በመሆን አገልግሏል ። እነዚህ የጦር መኰንኖች ወደ ወታደራዊ ኮሌጅ የሚገቡትን አዳዲስ ተቀጣሪዎች በመመልመልና የኢራቅ ጦር ኃይል መኰንኖች በብዛት ሱኒ ዓረብ መሆናቸውን በማረጋገጥ ፣ በጦር ኃይሉ ላይ ያላቸውን ቁጥጥር እንደያዙ ለመቆየት ጥንቃቄ አድርገዋል ።

ሱኒ ዓረቦች የፖለቲካ ቁጥጥሩን በእጃቸው ይዘው ቢቆዩም እንኳ እጂሉ የኢራቅ ንጉሣዊ አገዛዝ በዘር ፣ በሃይማኖት ዘርፍ ክፍፍልና በማኅበራዊ ኑሮ ተለያየ ። በመጀመሪያዎቹ ዘመናት አገዛዙ በብዙ የትጥቅ አመጽ ታውኮ ነበር ። በስተሰሜን ኩርዲስታን ውስጥ ፣ በስተደቡብ ደግሞ በሺዓ የዓረብ ጐሳዎች መካከል ብጥብጥ ነበር ። ይህን ሁኔታ በማንፀባረቅ ንጉሥ ፈይሳል በ1920ዎቹ መጀመሪያ ላይ ተጽፎ ያለውን ጽፈዋል ፦

ይህ መንግሥት አብዛኞዎቹ ግድም የሆኑበትን የኩርድ ወገኖች ያስተዳድራል ። እነዚህም ወገኖች የግል ፍላጎት ያላቸውና መንግሥቱ ከነሱ ዘር ስላልሆነ ጥለውት እንዲሄዱ የሚገፋፉ ሰዎችንም ጭምር ያጠቃልላል ። እንዲሁም ዘራቸው ከመንግሥቱ ጋር አንድ የሆኑትን ብዛት ያላቸው ሺዓዎች ያስተዳድራል ። ነገር ግን በሁለተኛውም አንፃር ሺዓዎች በመንግሥት ጉዳይ ተካፋይ እንዳይሆኑ በመከልከል በሺዓዎች ላይ ልዩነት ይደረግባቸው ስለነበር በሁለቱ የተለያዩ የእስልምና ዘርፍ ተከታዮች መካከል ሕግ መጣስ ይበልጥ እየተስፋፋ ሄደ ። ብዙ ሌሎች ጉሳዎች ደግሞ አሉ ። በራሳቸው ፍላጎትና በሼኮቻቸው ምኞት ምክንያት ማንኛውንም መንግሥትን የሚመለከት ነገር ላለመቀበል ይፈልጋሉ ። ... እስከ አሁን ኢራቅ ውስጥ ኢራቃዊ ሕዝብ የለም ፤ ይህንንም ስል ልቤ በኀዘን ተሞልቶ ነው ።

ንጉሥ ፈይሳል ገና ርዕቻቸውን ከመግለጻቸው ኢራቅ ነፃ መንግሥት ሆነች ። ላለፉት ዓሥር ዓመታት ለተደረገው ያልተቋረጠ የፖለቲካ ቅስቀሳ ምላሽ ለመስጠት ብሪታንያ የተሰጣትን የሞግዚትነት ሥልጣን ለመጨረስ ተስማማች ። በ1924 ኢራቅ ከነበረችበት የሞግዚትነት አጥም ነፃ ወጥታ የዓለም መንግሥታት ማኅበር አባል ለመሆን የመጀመሪያዋ ዓረብ አገር ሆነች ። ሆኖም ፡ ብሪታንያ ኢራቅ ውስጥ የነበራትን ይዞታ ለወደፊት ግን በጣም አስፈላጊ ሆኖ ስላገኘችው ጨርሳ መልቀቅ አልፈለገችም ። ስለዚህም የኢራቅ ነፃነት ለድርድር ቀርቦ ከብሪታንያ ጋር የትብብር ስምምነት ለመዋዋል ተገደደች ። ስምምነቱ በይበልጥ የብሪታንያን ጥቅም የሚጠብቅ ፤ በተለይም በአገሪቱ ውስጥ የነበረውን የብሪታንያን ጦር ሠፈር የሚያስከብር ነበር ። ብሪታንያ ኢራቅ ውስጥ የነበራት ይዞታ ለቀረው ጊዜ የሁከትና ያለመረጋጋት ችግር ምንጭ ሆኖ ቆይቷል ።

ኢራቅ ነፃ አገር ከሆነች አንድ ዓመት በኋላ ንጉሥ ፈይሳል በኀምሳ ስድስት ዓመታቸው በድንገት ሞቱ ። ኢራቅም እርቆ አስተዋይና መርሀን የሚከተሉ አንድ ሰው አጣች ። እኚህ ሰው ብሔራዊ ጥቅምን እናስተደም በሚል ሐሳብ አገሪቱን አንድ አድርገው ለመያዝ ብቃትና ተቀባይነት ነበራቸው ። ብሔራዊውን ጥቅምና ከእርሱ ጋር የሚጋጨውን የብሪታንያን ሚና ሚዛንም ይጠብቁተዋል ። የፈይሳል ልጅና ወራሽ ጋዚ በጣም ወጣት ፤ ደካማና ችኩል በመሆን ጠንካራ መሪ መሆን አልቻለም ። ጋዚም ከስድስት ዓመት በኋላ በመኪና ግጭት አደጋ ሞተ ። ትንሽ ልጁ ፈይሳል ዘውድ በመጫን ዳግማዊ ፈይሳል በመሰኘት ነገሡ ። ከርሱም ጋር አጐቱ



አብደላ በባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴነት ተሾሙ ።

ከንጉሥ ፈይሳል ሞት በኋላ በእርሳቸው አገዛዝ ጊዜ ሳይቀር የአገሪቱ ምሰሶ የነበረው የጦር ኃይሉ በኢራቅ የፖለቲካ ሕይወት ውስጥ በፍጥነት ወደ ላይ መውጣት ጀመረ ። የጦር ኃይሉ የመጀመሪያ ዋና ተግባር በሰሜን ኢራቅ የተነሣውን የአሦራውያን አመጽ በጭካኔና ደም በማፋሰስ ማዳፈን ነበር ።

አሦራውያን ጥንታዊ ክርስቲያን ኅብረተሰብ የነበሩና በአንደኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ በሁስማናውያን ላይ ከማመጻቸው በፊት በቱርክ ኩርዲስታን ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ናቸው ። ከዚያ በኋላ ግን መኖሪያቸውን ጥለው እንዲሸሹ በመገደዳቸው ብሪታንያ በሰሜን ኢራቅ አሥፍራቸዋለች ። ለብሪታንያ ወታደራዊ ምልመላ ፤ የሚቀጠሩትን በማቅረብ ዋና ምንጭ በመሆን አገልግለዋል ። በቀጠሉት ዓሥር ዓመታት በአሦራውያንና በኢራቆች መካከል ግጭት የሚያስከትል ብዙ ምክንያት ተፈጠረ ። በመጨረሻም በነሐሴ 1925 መጀመሪያ የድንበር ግጭት ተፈጥሮ ሠላሳ የኢራቅ ወታደሮች ሞቱ ። በዚህም ሳቢያ ፀረ ብሪታንያና ፀረ አሦርያ ስሜት ሠረጸ ። ኩርዶችና ሌሎችም ሰሜናዊ ጉሳዎች አሦራያውያንን እንዲያጠቁ ተገፋፉና አሦራያውያን በተገኙበት እየታደኑ ይገደሉ ጀመር። ከዚያም የኢራቅ ጦር ኃይል አመጹን ለማከሸፍ ተንቀሳቀሰ ። በጀኔራል ባክር ሲድቂ አዛዥነት የኢራቅ ጦር ኃይል መሣሪያ ያልታጠቁ ከሦስት መቶ በላይ አሦራውያንን ጨፈጨፈ ። አብዛኞቹን መንደሮቻቸውንም ከዘረፈ በኋላ ደመሰሰ ።

እስከዚያ ድረስ በመጠኑ ይታወቁ የነበሩት ሲድቂ የኢራቅ ጀግና ሆኑ ። ወደ ባግዳድ በሚመለሱበት ጊዜ በሞሱል ደማቅ አቀባበል ተደረገላቸው ። በሞሱል አካባቢ ቀደም ሲል ተነሥቶ የነበረውን አመጽ ለማከሸፍ አሦራውያን የተጫወቱት ሚና በተለያዩ ጉሳዎች መካል ለተነገው ውጥረት አስተዋጽኦ አድርጉ ነበር ። የድል አድራጊ ቅስቶች ሲድቂን "እንኳን ደኅና መጡ" አሏቸው ። አንዳንዱ ቅስት ያጌጠው ደም በተቀባና ጩቤ በተሰካበት ክርቡሽ ነበር ። የባግዳድ ከተማም በተመሳሳይ ሁናቴ በሆታና በእልልታ ተቀበለቻቸው ። የጦር ኃይሉ በፈጸመው ተግባር ታላቅ ግዳታውን እንደተወጣ ተቆጠረ ። እሳቸውም ለብሔራዊ አንድነት አሸናፊ ታጋይ ተብለው ተጠሩ ።

ሲድቂ ፥ በሕዝብ ዘንድ ያገኙትን አዲስ ተወዳጅነት በፍጥነት ወደ ፖለቲካዊ ጥቅም ለወጡት ፤ በ1928 ከታወቁት የኢራቅ ለውጥ ፈላጊ ፖለቲከኛ ከሂክማት ሱሌይማን ጋር በመተባበር ንጉሡ አዲስ መንግሥት እንዲያቋቁሙ ለማስገደድ ሲድቂ መግሪያቸውን አነሡ ። ሱሌይማን ጠቅላይ ሚኒስትር ፥ ሲድቂ ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ሆኑ ። ይህም የመጀመሪያው የዘመናችን የዓረብ መንግሥት ግልበጣ ነበር ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የኢራቅ ፖለቲከኞች ሥልጣን ለመያዝ ወደ ወታደራዊ ግልቃ ገብነት ወይም ከተለያዩ የጦር መኰንኖች አንጃዎች ጋር ወደ ማበር ሽምጥ ብለው ገቡ ። የኢራቅ ጦር መኰንኖች ከበስተጀርባ ካቢኔውን መቆጣጠር ያዙ ። የጦር ኃይሉም ቁጥጥሩ ስለጣመው ለማቋረጥ ፈቃደኛ አልሆነም ።

ሳሚር ኸሊል እንደሰይፍ በሚቆርጠው አነጋገራቸው እንደገለጹት የአሶርያ ጉዳይ ልማዳዊው የሃይማኖት ባላንጣነት በአዲስ ስሜት መተካቱን ያመለክታል ። ይህም አዲስ ስሜት "ፀረ ኢምፔሪያሊዝም" ተሰኝቷል። ኢራቅ በፍጥነት ዘመናዊ የሆነችበት ዓሥሩ የብሪታንያ አገዛዝ ዘመን ውጥረቷንና ጭንቀቱን አባባሰው እንጂ አላቃለለውም ። የፀረ ኢምፔሪያሊስት መፈክር መጀመር የዘመኑን ሥልጣኔ ለመወሰን አመቺ ሁኔታ ይፈጥራል ። ኸሊል እንዳስተዋሉት "የዚህ ውጤቱ ብዙ አደናጋሪ ምእታመታትን በማሻገር የተወነጨፈ ዓለም ነበር ።"

በ1920ዎቹ ፥ ኢራቅን ጨምሮ ፥ በአብዛኛው የዓረብ ዓለም የተድሞ ሥርዓት እንዲዳከም ተደርጓል ። ሆኖም ምን እንደሚተካው ግልጽ አልነበረም ። ለዘብተኛ ብሔረተኝነት የሕዝብ ድጋፍ ያለውን ራስን በራስ የማስተዳደር ሐሳብ አበከሮ ቢይዝም ፥ በብዙ ቦታ በ1781 ከፈረንሳይ ጀምሮ ፥ ጀርመንን ፥ ኢጣሊያንና ምሥራቅ አውሮፓን ጭምር፥ ብሔረተኝነት ወደ ፀምባገነንነት ፥ ትምክህተኝነትና የፖለቲካ አክራሪነት አመራ ።

ኢራቅ ውስጥም ተመሳሳይ ሁናቴ ተፈጽሟል ። ሞስኮ ውስጥ ኮሙኒዝም የነበረው ክብርና በተለይም አውሮፓ ውስጥ የፋሺዝም መነሣት ለለውጥ ለሚቸኩለው ወጣት ትውልድ የሚያስፈንድቅና የሚማርክ ሞዴል አቀረበ ። በአገራቸው ውስጥ ካለው የምግዚት አስተዳደር ባለሥልጣኖች ጋር ያልተጣጣሙ ሶርያውያንና ፍልስጥኤማ



ውያን ኢራቅ ውስጥ በስደተኝነት መኖር ጀመሩ ። ፍልስጥኤም ውስጥ በዓረቦችና በአይሁዶች መካከል የነበረው ውጥረት መባባስ ኢራቅ ውስጥ የብሔረተኞችን ፀረ ብሪታንያ ስሜቶች አጠናከሩ ። የፍልስጥኤም ጥያቄ ፈጽሞ ባይኖርም እንደዚህ ያለው ስሜት ለመኖሩ በግልጽ በቂ ምክንያት ነበር ። ሶርያዊው ምሁር ፥ ባሳም ጢቢ እንደገለጹት፦

> በቅድሙ ቅኝ አገዛዝ --- የዓረብ ብሔረተኝነት ለማስፋፋት ይፈልግ የነበረው ለዘብተኛ ነፃነትና የገዑበ ክበርቱ ዲሞክራሲ --- በቅኝ አገዛዝ ጊዜ ወደአድርባይነት ፥ ወደአድኃሪነት ፥ አንዳንድ ጊዜም ወደ ሕዝባዊነት አመለካከት አመራ ።

በተለይ ጀርመን ጠንካራ የመሳብ ኃይል ነበራት ። የሱኒ ዓረብ ብሔረተኞች የጦር መኰንኖችን ጨምሮ ፥ ኢራቅን እንደ ዓረቡ ዓለም ፕሩሲያ ማየት ጀመሩ ። ትልሙ ኢራቅ ቀድሚ ነፃ የወጣች የዓረብ አገር የመሆኗን ያኸል ፥ በጦር ኃይሏ አማካይነት ዓረቦችን እንድታዋሕድ ነበር። ናዚዎች ኢራቆችን በዚህ መንገድ በርትተው ማረቅ ጀመሩ ። እንዲሁም የሂትለር ብሪታንያንና ፈረንሳይን የመዳፈር ተግባር መሳካት የከተሜ ወጣት ምሁራንና የጦር መኰንኖች ጀርመንን የመደገፍ ስሜት አሳደገው ።

ነገር ግን እንዲሁ ብሪታንያን ለመበቀል ብቻ ከመነሣት ይልቅ ለፋሺዝም ይደረግ የነበረው ቅስቀሳ ይበልጥ ተቀባይነት ነበረው ። አገራቸውን በፍጥነት ወደ ዘመናዊ ሥልጣኔ ደረጃ ለማድረስ ጥድፊያ ያስከተለው ግትር ወግ አጥባቂ ማኅበራዊ ሥርዓት የጀርመንንና የጃፓንን በወታደራዊ ኃይልና ምግባር መተማመን (ሚሊታሪዝም) አስከተለ ። ኢራቅ ውስጥም ተመሳሳይ ድርጊት ነበር ። በ1930 ይህ ሁናቴ የጊዜው መለያ ምልክት በመሆኑ ለዚህ ጥልቅ ስሜት የነበሩት የዓረብ ብሔረተኛ ሳሚ ሻውካት በ1930 የትምህርት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ሆነው ተሾሙ። ሻውካት ሙሶሊኒን የሚያደንቁ ፋሺስት ነበሩ ። አንድ ጊዜ ንግግር ሲያደርጉ፥ "በፈረሶች ኮቴና በባዕዳን ጦር ኃይሎች ቦት ጫማ ሥር መሞትን ካልፈለግን የዕልቂት ፋብሪካውን የጦርነት ሙያ ፥ የተቀደሰውን ወታደራዊ ሙያ በጥረት ማስፋፋት ግዴታችን ነው ።" ብለዋል ።

በዚያን ጊዜ በርግጥ በመላው የዓረብ ዓለም ፋሺዝም በስፋት አድማጭ ነበረው ። ወደመንሻው ገዶግ ጀማል አብዶል ናስር የግብጽ "አረንጓዴ ሸሚዝ ለባሽ" ቡድን አባል ነበሩ ። አሁን የፍልስጥኤም ነፃ

አውጭ ሕዝባዊ ግንባር የሚባለውን የሐርነት ንቅናቄ ጀርጅ ሀባሽ ቀድሞ ሲመሠርቱ መፈክራቸው "መመዋት ፡ መፋጀት ! መግደል ! የሚል ነበር ። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፋሺዝም ከተሸነፈ በኋላ ግን ፡ ፋሺዝምን ተቀብለው የነበሩት ናስርንና ሀባሽን የመሳሰሉት ትሬታቸውን ፡ በጊዜው በሕዝብ ዘንድ መከበርን አትርፎ በነበረው በግራ ክንፍ ርዕዮተ ዓለም አማካይነት ማንፀባረቅ ጀመሩ ። ይህ ሁሉ ርዕዮተ ዓለም ያንኑ አንድ ዓይነት ስሜት ለመቀስቀስ የታለመ ነበር ፡— ያም ስሜት የአውሮፓውያንን የበላይነት መቃወም ነበር ፡ ያ ስሜት በየአገራቸው ውስጥ አንድ ጉድለት ስለመኖሩ የሚያብከነክናቸው ነበር ፡ ለእያንዳንዱም ያ ስሜት ሁሉንም እኩል የሚያይ ፡ የተሻለ ማኅበራዊ ሥርዓት ፍላጐት ነበር ። ነገር ግን መርሀ ግብራቸው ተጨባጭነት ያለውን ያክል እንኳ በሥራ ተተርጉሞ በቀላሉ መታየት አልቻለም ። የኢራቅን ርዕዮተ ዓለማዊ ፖለቲካ በጣም ልዩ የሚያደርገው በጥቂት ማኅበረሰብ ላይ መመሥረቱ ነው ። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በጣም የታወቁ ኮሙኒስቶች ለመሆን ዝንባሌ የነበራቸው ሺዓዎች ፡ ኩርዶችና ሌሎችም ወገኖች ነበሩ ። ከነዚህ አንዳቸውም ከሌሎች ዓረቦች ጋር የመዋሐድ ፍላጐት አልነበራቸውም ። ኢራቅን እንደአገራቸው በመቆጠር ብቻ ረክተዋል ። በከፍተኛና መካከለኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የተገኙ ሱኒዎች ዓረብ ብሔርተኛ ነበሩ ። እነሱም የፖለቲካ ሥልጣን በግላቸው ለመያዝ የሚያስችላቸውን "መላውን ዓረብ ማጠቃለል" የሚል አስተሳሰብ ነበራቸው ። የባዝ ፓርቲ ደግሞ ለመያዝ የሚፈልገው በኑሮው በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኘውን የሱኒ ዓረብና አንዳንድ ሺዓዎችን ነበር ። ምክንያቱም በሃይማኖትና በዘርፍ በመከፋፈል አላምን ባይና መርሀ ግብሬ ሶሻሊስት ነው የሚል በመሆኑ ነበር ።

የሁለተኛው ዓለም ጦርነት መነሣት ፡ በዓረብ ብሔረተኞችና በብሪታንያ መካከል ግልጽ ግጭት አስከተለ ። ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴና ጠቅላይ ሚኒስትር—ኑሪ ሰይድን ከባግዳድ እንዲወጡ በሚያዝያ 1933 የኢራቅ ጦር ኃይል መኰንኖች ባስገደዱ ጊዜ ውስጥ ውስጡን ይካሄድ የነበረው ድርጊት አደባባይ ወጣ ። የጦር መኰንኖቹ እርዳታ ከጀርመን ጠየቁ ፡ ሂትለርም በንዓዳቱ ፈረንሳይ (በናዚ ያልተያዘችው) እጅ ተይዛ በነበረችው በሶርያ በኩል ጥቂት አውሮፕላኖች ላከ ።



የብሪታንያ ጦር ኃይልም በብሪታንያ የጦር መኰንኖች በሚመራው የዓረብ ጦር ሠራዊት እየታገዘ ተጠናክሮ ለሁለተኛ ጊዜ ኢራቅን ለመያዝ ወደፊት ገፋ ። የጦር ኃይሉ የመጣው ከ(ትራንስ) ዮርዳኖስ ተነሥቶ በረሃ በማቋረጥ ነበር ። ከዚያም ኑሪ ሰይድን ወደ ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴና ጠቅላይ ሚኒስትርነት ሥልጣናቸው መለሷቸው ።

አማፂ መኰንኖች በተሸነፉ ጊዜ የከተማዪቱን ሀብታምና ጥንታዊ የአይሁድ ኅብረተሰብ እንዲያጠቁ ሕገወጥ ሰዎችን በመገፋፋት በቀላቸውን ተወጡ ። አንዳንድ የጦሩ ወገኖች ብጥብጡን ብዙ ቀን ቀጠሉ ። ብዙ ዝርፊያ ከመካሄዱ ሌላ አንድ መቶ ሰማንያ የባግዳድ አይሁድ ተገድለው ሌሎች ብዙ መቶ የሚሆኑ ደግሞ ቆሰሉ ። ጊዜው ከሚጠበቀው በላይ የሠለጠነ ነበርና ወደሥልጣን የተመለሰው መንግሥት ጉዳዩን የሚያጣራ ሕጋዊ አካል አቋቋመ ። መርማሪው አካል ጥፋተኞቹ የጦር ኃይሉ ጥቂት ወገኖች እንደሆኑና ለግድያውም ተጠያቂ መሆናቸውን ፊት ለፊት በመግለጽ ከጽኑ እሥራት ጋር ቅጣት በየነባቸው። ከዚህ ቀጥሎ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት እስካበቃ ድረስ ባግዳድ ፀጥ አለች ። ኢራቅ በ1935 በአብዛኛው ድጋፏን ለመግለጽ በአክሲዝ ኃይላት ላይ ጦርነት ከማወጇም በላይ አሜሪካ ለሩሲያ የምትሰጠው ወታደራዊ እርዳታ የሚደርስበትን ሁኔታ በማመቻቸት የኅብረት ኃይሉ ለሚያደርገው ጥረት አስተዋጽኦ አደረገች ።

የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማብቂያ ፡ እንሰም በዛ ፡ የኑሪ ሰይድን መንግሥት በሥልጣን ላይ ለረጅም ጊዜ መቆየት አስከተለ ። ብዙው ሕዝብ ፀረብሪታንያ ስሜት ቢኖረውም ፡ እንዲሁም ፍልስጥኤም ውስጥ የአይሁድ መንግሥት መመሥረት ... አብዛኛው ሕዝብ ፀረ ምዕራብ ስሜት ቢፈጥርም ፡ የኑሩ ሰይድ መንግሥት ብሔራዊ መመሪያ ምዕራቡን ዓለም የሚደግፍ ነበር ። በ1940 በዓረቦችና በእሥራኤል መካል በተካሄደው ጦርነት እንዲዋጉ ኢራቅ ወታደሮች ላከች ። የእሥራኤል ድል ፡ በማንኛውም የዓረብ ዓለም ቅሬታ አስከትሎ ነበር ። ግብጽ ውስጥ የ1948ቱን የጦር መኰንኖች መፈንቅለ መንግሥት አመጣ፡ ኢራቅ ውስጥ ደግሞ እሥራኤል ልታሸንፍ የቻለችው በመንግሥት መሪዎች ተንኮል እንደሆነ ፡ የጽዮናዊውን ኃይል የኢራቅ ጦር ኃይል እንዳይደመስስ መሪዎቹ አስፈላጊውን ትእዛዝ ለመስጠት ስላልፈቀዱ እንደሆነ ተጸርጐ ተወራ ። ይህም የፈጠራ ወሬ የጦር ኃይሉ ለበውድ አገዛዝ

የነበረውን ታማኝነት በመቀነስ ትልቅ ሚና ተጫውቷል ።

የአዲሱ የግብጽ ፕሬዚዳንት የጀማል አብደል ናስር ታላቅ የዓረብ ብሔረተኛ ሆኖ መነሣት ፣ ምንጊዜም ጉጂ የነበረውን ከብሪታንያ ጋር ያለ ግንኙነት ጥያቄ ይበልጥ አስቸጋሪ አደረገው ። በዓለም አቀፍ ፖለቲካ ፣ የኢራቅ መንግሥት በማያወላውል ሁኔታ የተሰለፈው ከብሪታንያና ከአሜሪካ ጋር ነበር ። የምዕራብ ኃይሎች በመካከለኛው ምሥራቅ ስለ አካባቢ ደኅንነት ጥበቃ ለመዋዋል የነበራቸውን ፍላጐት ለመቀበል ኢራቅ ተዘጋጅታ ነበር ። ይሁን እንጂ ናስር ይህን ሐሳብ በጥብቅ ተቃወሙ ። ከዚህ በኋላ በናስርና በኑሪ መካከል ወዲያውኑ የተባባሰ ፉክክር ተፈጠረ ።

ከ1947 እስከ 1950 ባለው ጊዜ ውስጥ ናስር በዓረቦች ዘንድ የነበራቸው ተወዳጅነት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደረሰ ። በመስከረም 1948 ከሶቪየት የጦር መሣሪያ ለማግኘት የመጀመሪያው የዓረብ መሪ ሆኑ ። ናስር ለምዕራቡ ዓለም አላጐበድድ ማለታቸውን የዓረብ ሕዝብ አድንቆ ከሶቪየት ኅብረት ያገኙትን ጦር መሣሪያ ፍልስጥኤምን ነፃ ለማውጣት ይጠቀሙበት ይሆናል በማለት ጠበቀ ።

በግብጽና በምዕራቡ ዓለም መካከል ያለው ውጥረት መጨመሩን ቀጠለና በግንቦት 1948 አሜሪካ ለግብጽ የአስዋን ከፍተኛ ግድብ ታላቅ እቅድ የምትሰጠውን እርዳታ አቋረጠች ። ናስር በሐምሌ 1948 የስዊዝን መተላለፊያ በይ ብሔራዊ ንብረት በማድረግ "ብድራቸውን መልሰው" ግድቡን ለማሠራት የሚያስፈልጋቸውን ገቢ አገኙ ።

በዚያን ጊዜ በመካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ የበላይነት የነበራቸው የምዕራብ ኃይሎች ብሪታንያና ፈረንሳይ ፣ አካባቢው ደህና ሊሆን የሚችለው ናስር ሲወገዱ ብቻ እንደሆነ ወሰኑ ። እንዲሁም የስዊዝ መተላለፊያ በይ ብሔራዊ ንብረት እንዲሆን በተደረገበት ጊዜ ለንደን ውስጥ የነበሩት ኑሪም የናስርን መወገድ ደገፉ ። ስለሆነም የብሪታንያ ጠቅላይ ሚኒስትር አንተኒ ኤደን "በፍጥነት ይምቱት ! አጠንክረው ይምቱት !" በማለት አሳሰቡ ። በጥቅምት 1949 ብሪታንያና ፈረንሳይ ናስርን ለማጥቃት ከእሥራኤል ጋር አበሩ ። እቅዳቸውን ግን አሜሪካ በምስጢር ያዘች ።

እስከ አሁን ፈጽሞ ግልጽ ባልሆነ ምክንያት ፣ (የአሜሪካ መንግሥት የዚያን ጊዜውን የዲፕሎማቲክ ሰነዶች አሁንም በምስጢር እንደያዘ



ነው) ፕሬዚዳንት ድዋይት ዲ አይዘንሀወር የነበረት ኃይሉ ከግብጽ ያለአንዳች ቅድመ ሁኔታ እንዲወጣ ማስገደድ እንዳለባቸው ግዴታቸው ሆኖ ተሰማቸው ። ሆኖም የአይዘንሀወር ተግባር ናስርን ታላቅ ጀግና አደረጋቸው ። ናስር በእሥራኤል ጦር ኃይል እጅ የወደቀውን የሲና ደሴተ ክልል በፍጥነት ለመከላከል ያለመቻላቸውን የቅርብ ትዝታ የዓረብ ሕዝብ ረሳው ፣ ወይም ደግሞ የግብጽ ግዛት እንዲመለስ ያደረገችው አሜሪካ መሆኗን ፣ የዓረብ ብሔረተኝነት ታላቅ ድል አግኝቷል በሚል ስሜት የታወረውን ዓይኑ ጎሊናቸውን ሊከፍተው አልቻለም ። ከሁለት ዓመት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ግብጽና ሶርያ አንድ ላይ ሆነው የተባበሩት የዓረብ ሪፐብሊክን መሠረቱ ። የዓረቦች ኅብረትና የቅኝ ገዢዎች የሰለሉት ድንበር መሻር የቀረበ መሰለ ።

በዚያ በደመነፍስ እንቅስቃሴ መንፈስ ውስጥ የዓረብ ብሔርተኛ የጦር መኰንኖች ቡድን በጀኔራል አብድል ካሪም ቃሲም መሪነት ሐምሌ 6 1950 በኢራቅ የዘውድ አገዛዝ ላይ የተሳካ መፈንቅለ መንግሥት አካሄደ ። ምንም እንኳ ፣ ቤተ መንግሥቱን ያጠቃው ጦር ኃይል ጥቂት (ከአንድ መቶ ያነሱ ሰዎች) እና የታጠቀው ቀላል መሣሪያ ቢሆንም 1·6 ኪሎ ሜትር ርቀት የሠፈረውን 2ሺ 500 ሰው የሚገኝበትን በደንብ የታጠቀ የንጉሡን የክብር ዘበኛ ክፍለ ጦር ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴው አብዱላህ መልሶ እንዲያጠቃ ማዘዝ ሳይችሉ ቀሩ ። የአብዱላህ በፈቃዳቸው ሥራ መልቀቅና መሸነፍ ፈጽሞ በአጥጋቢ ሁኔታ አልተገለጸም ። የንጉሡ ክብር ዘበኛ ጦር ዋና አዛዥ አመጸኞችን ለማጥቃት የአብዱላህን ፈቃድ ጠይቆ ተከለከለ ። ከሁለት ሰዓት ከበባ በኋላ በለሙሉ ሥልጣን እንደራሴው ወጣቱ ቀዳማዊ ንጉሥ ፋይሳል የአብዱላህ እናትና እኅት ከጥቂት የቤት አሽከሮች ጋር በኦቶማቲክ ጦር መሣሪያ ጥይት ታጨዱ ።

መፈንቅለ መንግሥት በመካሄድ ላይ እያለ ፣ የቃሲም ረዳት ተባባሪ ኰሎኔል አብዱል ሰላም አሪፍ ኢራቅ ውስጥ የዘውድ አገዛዝ ማክተሙን በሬዲዮ አወጁ ። በአንድ ሰዓት ውስጥ የባግዳድ ችግረኞችና መሬት አልባው ድሀ በኑቂስ በአመጽ ወደ መንገድ ወጥተው ተሰበሰቡ ። ከዚያም እየጮኹና እየዘፈኑ ለመበቀል ጠየቁ ። በቁጣ ከተማውን እየዞሩ የብሪታንያን ኤምባሲና ሌሎችንም ዲፕሎማቶች አጠቁ ። ብዙ የዮርዳኖስ

ሚኒስትሮችንና በአካባቢው ሆቴል ውስጥ የተያዙ ምዕራባውያን ነጋዴዎችን ገደሉ ። እንዲሁም የአብዱላህን ሬሳ አግኝተው መቆራረጥና በመንገድ ላይ መጐተት ቀጠሉ ። ኑሪ ሰይድ እንደሴት በመልበስ ለማምለጥ ሞክረው በማግሥቱ ተገኙና ወዲያው በጥይት ተደብድበው ተገደሉ ። አመጸኞቹ ቆይተውም የኑሪን ሬሳ ቆፍረው በማውጣት አብዱላህ ላይ የፈጸሙትን ዓይነት አሰቃቂ ድርጊት ፈጸሙበት ።

አዲሱ መንግሥት የኢምፔሪያሊዝም አገልጋይ "ብልሹ ቡድን" እንደገረሰሰና "ሕዝባዊ ሪፐብሊክ"ም እንደሚመሠረት አወጀ ። ዳሩ ግን "ሪፐብሊኩ" ቃሲምን እንደ "ብቸኛ መሪው" በማድረግ ወዲያውኑ ወደፀምባገነንነት አገዛዝ ተለወጠ ። ብዙም ሳይቆይ መጀመሪያ በነበረው ኅብረት ውስጥ መከፋፈል ታየ ። በጣም አስቸጋሪ የነበረው አንጃ በናስር አይዞህ ባይነት ቃሲምን በመደጋገም የተፈታተናቸው የዓረብ ብሔረተኛ ወገን ነው ።

የግብጹ ፕሬዚዳንት የተፎካካሪያቸው የኑሪ ሰይድ መገደል ቢያስደስታቸውና አዲሱን የኢራቅ መንግሥት በደኅና ቢቀበሉም ቃሲም የናስርን መሪነት ለመከተል ፍላጐት አልነበራቸውም ። በተለይም በየካቲት 1950 በግብጽና በሶርያ ከተመሠረተው ከተባበረው ዓረብ ሪፐብሊክ ጋር ለመቀላቀል እቅድ አልነበራቸውም ። ምንም እንኳ የቃሲም አባት ሱኒ እስላም ዓረብ ቢሆኑም እናታቸው ደግሞ ሺዓ ኩርድ ናቸው ። ቃሲም የሚያንፀባርቁት ፖሊሲ በዚያን ጊዜ ኢራቅ ውስጥ የነበረውን በአገሪቱ ላይ የሚያተኩረውን እንጂ የመላውን ዓረብ አንድነት አልነበረም ። ቃሲም የመላውን ዓረብ አንድነት (ፓን ዓረቢዝም) በሚመለከተው ጉዳይ ላይ ቀዝቀዝ ስላሉ ፣ ናስርና ኢራቅ ውስጥ ያሉት ናስራውያን (የናስር ደጋፊዎች) በፍጥነት በእርሳቸው ላይ ተነሡባቸው ። በቅድሚያ ችግሩ የጀመረው ከቃሲም ሸሪክ ከአሪፍ ነበር ። አሪፍ የዓረብ ብሔረተኛ አስተያየታቸው ከሱኒ ዓረብ ጦር መኰንኖች ጋር የሚመሳሰልና ከናስር ጋር መልካም ግንኙነት እንዲኖራቸው የሚፈልጉ ሰው ነበሩ ። ግንኙነታቸውም ፀረለውጥ ጥቃት ቢነሣ ለመከላከል እንዲቻል እርዳታ ለመጠየቅ ከመፈንቅለ መንግሥቱ ሁለት ቀን በፊት አሪፍ ወደ ደማስቆ ሄደው ነበር ። ነገር ግን ደግሞ ኢራቅ ወደተባበሩት ዓረብ ሪፐብሊክ ትቀላቀላለች ፣ እያሉ በመለፈፍ የናስርን እጅ ይዘው በአደባባይ ታይተዋል ።



አሪፍ የቃሲምን ሥልጣን ለራሳቸው እንደሚፈልጉት ብዙ ሳይጠብቁ አንድ ባንድ ማስረጃ ሰጥተዋል ። አሪፍ ከአገር እንዲወጡላቸው ስለፈለጉ በ(ቀድሞዋ ምዕራብ) ጀርመን ውስጥ የአምባሳደርነት ሹመት በአማራጭ ቃሲም አቀረቡላቸው ፣ አሪፍ ግን አልተቀበሏቸውም ። ጥቅምት 1951 በቃሲም ጽሕፈት ቤት በተደረገው ስብሰባ ላይ ነገሮች እየባባሱ ወጡ ። ከአምስት ሰዓት ፍሬቢስ ውይይት በኋላ አሪፍ ሽጉጣቸውን መዘዙ ። ቃሲም ሽጉጡን ለመንጠቅ የቻሉት በአንድ ሰው እርዳታ ብቻ ነበር ። ነገር ግን ቃሲም እኒህን ቁርጠኛ ጠላታቸውን አላስወገዱም ። ቃሲም ከእርሳቸው በኋላ የተተኩት ሁሉ ያሳዩትን ርኅራኄ ለአሪፍ በማሳየት አገሪቱን ለቀው እንዲሄዱ በድጋሚ ጠየቋቸው። አሪፍ እምቢታቸውን እንደቀጠሉ ተይዘው ታሠሩ ።

በሌላ በኩልም ቃሲም ከመላው የዓረቦች አንድነት ደጋፊዎች ጋር ያላቸውን ትግል ቀጠሉ ። በ1933 ፣ በብሪታንያ በታፈነው በናዚ ደጋፊ መንግሥት ውስጥ በጠቅላይ ሚኒስትርነት ያገለገሉት ረሺድ አሊ በስደት ካይሮ ውስጥ ከሚኖሩበት በመስከረም 1934 ወደባግዳድ ተመለሱና ቃሲም ራሳቸው ብሔራዊ ጀግና አድርገው በደስታ ተቀበሏቸው ። ረሺድ አሊ በናስር ገንዘብ ፣ በጉሳ ሼኮችና የሁሉም ዓረብ አንድነት ደጋፊ ጦር መኰንኖች እየታገዙ ፣ በሽምግልና ጊዜያቸው በቃሲም ላይ ማሴር ጀመሩ። ሆኖም ቃሲም ሴራውን በታኅሣሥ 1934 ስለደረሱበት አሳሰሯቸው ። ረሺድ አሊ በሞት እንዲቀጡ ቢፈረድባቸውም ፍርዱ አልተፈጸመባቸውም ። በሌላ በኩልም የሳዳም አጐትና አብዛኛው ኢራቃዊ እንደ ጀግና የሚያያቸው ኬይራላህ በኢራቅ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ራሱን ለውጥ አምጪ አድርጎ በሚያየው መንግሥት መታሠራቸው እስከ ዛሬ ሊያስገርም ይኖራል ።

የመላው ዓረብ አንድነት ደጋፊዎች ተቃውሞ ቃሲምን ከሌላ ድጋፍ እንዲፈልጉ አደረጋቸው ። በከፊል የብሔረተኞችን የኃይል ሚዛን ለመጠበቅ ሞስኮ ውስጥ በስደት ይኖሩ የነበሩትን የኩርዶች መሪ ሙስጠፋ ባርዛኒን ወደ ባግዳድ እንዲመለሱ ጠየቋቸው ። ባርዛኒ ንጉሣዊ አቀባበልና መስተንግዶ ተደረገላቸው ። በቀድሞው የኑሪ ሰይድ ልጅ ቤተመንግሥት ውስጥ እንዲኖሩም ተደረገ ። መኪናና የክብር መጠበቂያ ገንዘብ ተሰጣቸው ። ነገር ግን ቃሲም ለኩርዶች ራሳቸውን የማስተዳደር ነፃነት እንዲሰጡ ያቀረቡላቸውን ጥያቄ እንደማያሟሉላቸው ባርዛኒ መጠርጠር

ጀመሩ ። በእርግጥም የዚህ ዓይነቱ ጥያቄ አወንታ መልስ ማግኘት ወደኩርድ ነፃነት ሊያመራ ስለሚችል ቓሲም መፍራት ጀመሩ ። ቀጥሎ የባግዳድና የኩርዶች ግንኙነት እየተበላሸ ሄደ ። በመስከረም 1954 በኩርዶችና በኢራቅ ጦር ኃይል መካከል የእርስ በርስ ጦርነት ተከፈተ ። ግጭቱ ጉልበት፣ ሀብትና ጊዜ የሚያሟጥጥና በቓሲም አገዛዝ ላይ አደጋ የሚያስከትል ሆነ ።

ነገር ግን የቓሲም አገዛዝ ቢያንስ ሥልጣን በያዘ ማግሥት እንደምስሶ ደግፎ የያዘውና በጣም የጠቀመው የኢራቅ ኮሙኒስት ፓርቲ ነበር ። ናስር ግብጽ ውስጥ ስለአፈኗቸውና ስለጨቆኗቸው፣ እንደገናም ሶርያ ውስጥ ከ1950 ውሕደት በኋላ ኮሙኒስቶችን ስለደገሟቸው በመካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ ያሉት ኮሙኒስቶች ሁሉ ናስርን እምርረው ይጠሏቸው ነበር ። ስለዚህ የኢራቅ ኮሙኒስቶች የቓሲምን መፈንቅለ መንግሥት በፍጥነት ደገፉ ። ከዚህም በላይ ፓርቲው በብዛት ሺዓዎችን፣ ኩርዶችንና ሌሎችንም ክፍሎች በአባልነት ያሰባሰቧቸው ቓሲም አገር ውስጥ ጉዳይ ላይ ብቻ ለማትኮር ካላቸው አመለካከት ጋር ይጣጣማል ።

ከመፈንቅለ መንግሥቱ በኋላ የኮሙኒስት ፓርቲው አባላት በጣም በዙ ። እነሱም በርካታ ሕዝብ በመሰብሰብና በየመንገዱ በማሰለፍ ናስራውያንን መቋቋም ቻሉ ። በተጨማሪም ኮሙኒስቶች "ሕዝባዊ የመከላከያ ኃይል" መሠረቱ ። ይህም ሕዝባዊ ሠራዊት የተዘጋጀው ቓሲምንም ለመደገፍ ጭምር ነበር ። ምንም እንኳ አንዳንድ ጊዜ ከመጠን በላይ ሲያልፉ ቓሲም ለመግታት ቢሞክሩ፣ በምንም ዓይነት የኮሙኒስቶችን ድጋፍ ቓሲም ይፈልጉ ነበር ። ሕዝባዊ የመከላከያ ኃይሉ በገደብ የለሽ የማሰር ሥልጣን በመጠቀም በፍርሃት የተዋጠውን ሕዝብ ማሸበር ጀመረ ።

የኮሙኒስቶች ኃይል እያደገ መሄድ የፖለቲካ ውጥረቱን እያከረረው ሄደ ። ከዚህም ጋር በመጋቢት 1951 ከናስራውያን ጋር የነበረቸው ቶክክር ደም እስከማፋሰስ ደረሰ ። መሠረታቸው ከአገሪቱ በስተሰሜን የሱኒ ዓረብ የጦር መኰንኖችና የጐሳ ሼኮች እንደገና በናስር ድጋፍ በቓሲም ላይ ለማመጽ አቀዱ ። አመጻቸውንም ለመጀመር የወሰኑት የኮሙኒስት ደጋፊዎች በሰሜናዊቷ ከተማ በሞሱል ታላቅ ስብሰባ በሚያደርጉበት ቀን ነበር ። ከሁለት መቶ ሺ በላይ ሕዝብ ከመላው ኢራቅ ወደ ከተማይቱ ጐረፈ ። አመጸኞች አጠቋቸው ። ነገር ግን የመንግሥት



ኃይሎች ፈጥነው ጥቃቱን በመመለስና አመጹን በመደምሰስ የተሳካ ውጤት አገኙ ። ቢሆንም ኮሙኒስቶች ብሔረተኞችን በመፍጀትና በሞሱል ውስጥ የሚገኙትን አንዳንድ ከበርቴዎች መኖሪያ ቤት በመዝረፍ በአማጺፊ የበቀል እርምጃ ወሰዱ ። በዚህም ሁለት ሺ ያኸል ሰው አለቀ ።

ቓሲም አሁን ኮሙኒስቶች በጣም ኃይለኛ እንደሆኑ ተገነዘቡ ። ቀስ በቀስም ሥልጣናቸውን ማገድ ጀመሩ ። እንደዚህ በማድረጋቸው በሌላ በኩል የነበረቸውን የተደራጀ የፖለቲካ መሠረትና ከኢራቅ ብዙኃን ሕዝብ መኻል በስፋት ድጋፍ እንዲያገኙ ብቃት ባለው መንገድ ሕዝቡን የሚያንቀሳቅስላቸውን ብቸኛ መዋቅር አጥተዋል ።

የኮሙኒስቶች ኃይል እያደገ መሄድ ትንሽና ቀድሞ ከቁጥር የማይገባው ባዓዝ ፓርቲ የመጀመሪያውን የሥልጣን ሽሚያ ሙከራ እንዲያደርግ መነሻ ምክንያት ሆነ ። በጥቅምት 1952 የባዓዝ ፓርቲ በቓሲም ላይ የግድያ ሙከራ ለማድረግ አቀደ ። በዚህም ሙከራ የሃያ ሁለት ዓመቱ ጐረምሳ ሣዳም ሑሴን ተካፍሏል ። የባዓዝ ፓርቲ ከብሔረተኛው የጦር መኰንኖች ቡድን ጋር በማበርና በምስጢር የናስርን ድጋፍ በማግኘት ሥራውን ያከናውን ነበር ። በግድያ ሙከራው ላይ የቓሲም ሹፌር ሲገደል ከረዳቶቻቸው አንዱ ከቶኛ ቆሰለ ። ራሳቸው ቓሲም ጭምር ተመትተዋል ። ከቶኛ መቁሰላቸውም ሊረጋገጥ የቻለው ሆስፒታል ገብተው ላንድ ወር ያኸል ሲታከሙ በመቆየታቸው ነው ።

ቓሲም በሕይወት ተረፉ ። አመጸኞች ነፍሳቸውን ለማዳን ተፍጨረጨሩ ። ጥቂቶቹ ሣዳምን ጨምር ከኢራቅ ውጭ ለመሸሽ ቻሉ ። ነገር ግን ሌሎች ሰባ ሰምንት ተይዘው በመታሰር ለፍርድ ቀረቡ ። ብዙዎቹ በእሥራት ሲቀጡ፣ ጥቂቱ ደግሞ በሞት እንዲቀጡ ተፈረደባቸው ። ሆኖም አንዱም የሞት ቅጣት አልተፈጸመ ።

የቓሲም አገዛዝ እየተሻሻለ ሲሄድ፣ የበጐ ተግባር አዝማሚያ ማንጸባረቁ ያንኑ ያኸል ከፍ እያለ ሄደ ። ቓሲም በሁሉም በኩል ጨዋና ሰላማዊ ሰው ነበሩ ። ቓሲም ሊገድሏቸው የሚችሉ ብዙ ሰዎች ነበሩ ። ነገር ግን ከማድረግ ተቆጥበዋል ። የአገራቸውን ችግር ለማቃለል የነበራቸውን ልባዊ ፍላጐት የሚጠራጠሩ ጥቂት ነበሩ ። ከሁሉም በላይ በቅርብ ከትትል ለሕዝብ "ትንንሽ ቤቶች" አሠርተዋል ። ምናልባትም ይህ በጣም ጠቃሚና ዘላቂ ከሆነው ኢኮኖሚያዊ መመሪያቸው አንዱ

ነበር ። ከእያንዳንዱ ዓመታዊ ባጀት ውስጥ ሃያ አምስት በመቶ ገደማ የሚሆነው የሚመደበው ለሕዝብ የቤት ሥራ ነበር ። በኋላ ከጠላቶቻቸው ጋር በተፋጠጡበትና ሞትን በተጋፈጡበት ጊዜ ራሳቸውን ለመከላከል ሲናገሩ "በደሃው ስም ራሴን በጣም አሠርቻለሁ ። ለደሃው ብዙ ሺ ትንንሽ ቤት አሠርቻለሁ ።" ብለዋል ።

ነገር ግን ቃሲም የማይጨበጥና ተለዋዋጭ ሐሳብ ያላቸው ሰው ነበሩ ። በሌላው መስክ በጣም በሚታወቀው በግብርናው ይዞታ ለውጥ መርሐ ግብራቸውን በሥራ ላይ እንዴት እንደሚተረጉሙት ግልጽ ሐሳብ አልነበራቸውም ። አገራቸውን በድንገት የእርሻ ሰብል ምርት እጥረት ገጠማት ። በ1953 ኢራቅ እንደቀድሞው ጊዜ ሁሉ ወደውጭ ገብስ መላክ አልቻለችም ። እንዲሁም ከፍጆታዋ ግማሽ የሚሆነውን ሩዝና ስንዴ ከውጪ አስመጣች ። ያም ሆነ ይህ ፣ የቃሲም ይበልጡ ችግር መሠረታዊ የአሠራር ልምድ ያለመኖር ነበር ። አንድ ሥራ ወዳድ የቃሲም የካቢኔ ሚኒስትር በኋላ እንዳንፀባረቁት እሳቸውና የሥራ ጓደኞቻቸው ኢራቅን ማስተዳደር የቀን ያኸል ሰፊ ተግባር እንደሆነ ምንም ዓይነት ሐሳብ አልነበራቸውም ። እኒህ ሰው የተሰማቸውን በተጨማሪ ሲናገሩ ፣ የተቋቋመውን ሥርዓት በማውረድ ለሌሎች በጐ የሚያስብና የወደፊቱን የሚያይ አገዛዝ ያስከትላል ማለት ይቅርታ የማይደረግለት ስሕተት እንደሆነ ተችተዋል ።

ሌላው ተርቶ የቃሲም ስመ ጥፉ ማኸዳዊ ፍርድ ቤት ጭካኔ እንኳ ሁኔታው እንደሚጠይቀው ፍርድ አያከብድም ነበር ። ፍርድ ቤቱ መጀመሪያ የተቋቋመው የቀድሞውን አገዛዝ መሪዎች ፍርድ ለመመር መር ሲሆን ዳኝነቱን የቃሲም አጐት ፈድል አባስ አልማኸዳዊ መርተ ዋል። ከጊዜ በኋላ ግን ፍርድ ቤቱ ሰርከስ (የእንስሳት ጨዋታ ትርኢት መድረክ) ሆነ ። ፍርድ ቤቱ እንደ ችሎት ተቀምጦ ለመላው አገሪቱ በቴሌቪዥን ተላልፏል ። ተመልካቹ ሕዝብ ፣ በተከሳሹ ላይ ትችት በመስጠትና በመዛት በችሎቱ ላይ ተካፋይ እንዲሆን ተፈቅዶ ነበር ። ማኸዳዊ ራሳቸውንና ቃሲምን የሚከብና የሚያወድስ የከንቱ ውዳሴ ግጥም ሲያዳምጡ ችሎቱ በየጊዜው ይቋረጥ ነበር ። ማኸዳዊ ፍርድ ቤቱ ውስጥ ለሕዝብ እንዲታይ ያደረጉትን የሌኒንን የፍትሕ ሜዳይ ሶቪየት ኅብረት ሸልማቸዋለች ። እንደ ዕውነቱ ከሆነ ፍርድ ቤቱ የሞት ቅጣት የበየነው ለአጭር ጊዜ ነበር ። ያም ሆኖ ፣ ምስጢሩ ከወጣ በኋላ



ከሚታወቀው ጋር ሲነፃፀር ያስፈጸመው የሞት ቅጣት ብያኔ የተወሰነ ነበር ። በነሐሴ 1951 እና በመስከረም 1952 በማኸዳዊ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ዓሥራ አራት ሰዎች ተገድለዋል ፣ ይህም በ1971 ሣዳም በፓርቲው ጉባዔ ጊዜ ከገደሏቸው ሰዎች ያነሰ ነበር ።

በዚህ ሁኔታ ቃሲም የኰሙኒስቶችን ኃይል መገደብ እንደጀመሩ አገዛዛቸው ምንም ያኸል የተደራጀ ድጋፍ አልነበረውም ። በነበራቸው ተለዋዋጭ መንገድ የእያንዳንዱን የአገሪቱን ፖለቲካዊ ቡድን ቁንጮ መሪዎች ፈጥነው ለማለያየት ቻሉ ። ኢራቃውያንም ቃሲምን እንደ ስታሊን አይደሉም ፣ በማለት ይታገሷቸው ነበር ። ቢሆንም ሁኔታዎች እየተበላሹ እንደሚሄዱ በአንዳንድ መንገድ በውቀው ነበርና እንዳሰቡ ትም ትክክለኛ ሆኑ ።

በየካቲት 1/1955 መጀመሪያ በእስላሞች ቅዱስ የረመዳን ወር ቃሲም ላይ መፈንቅለ መንግሥት ተካሄደ ። በ1951 የባዝ ፓርቲ አባላት ጦር መኰንኖች ከዓረብ ብሔረተኞች ጋር ኅብረት ፈጥረው በሳቸው ላይ ተነሡባቸው ። ቃሲም በቅርቡ ከእሥር የለቀቋቸው አሪፍ በብሔረተኞቹ ስም መፈንቅለ መንግሥቱን መሩ ። እሳቸውም አዲሱ ፕሬዚዳንት ሆነው ተሾሙ ። የታወቁት የባዝ ፓርቲ አባል የጦር መኰንን ኩሉኔል አህመድ ሐሰን አልባክር ደግሞ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኑ ።

መፈንቅለ መንግሥቱ አስገራሚና ደም ያፋሰሰ ነበር ። የብሔረተኞቹን አቋም ደጋፊ የነበሩ የአየር ኃይል አብራሪዎች በመከላከያ ሚኒስቴሩ ውስጥ የነበረውን የቃሲምን ጽሕፈት ቤት በቦምብ ደበደቡ ። አንድ ብሪጌድ ጦር ደግሞ ከባግዳድ ውጭ በመምጣት የመከላከያ ሚኒስቴሩን ከበበ ። ንጋት ላይ የባዝ ፓርቲ የግድያ ቡድን በተሰጠው መመሪያ ዒላማዎችን አጠቃ ፣ ሌሎች ደግሞ የቃሲምን መንግሥት የታወቁ ባለሥልጣኖች አሠሩ ።

ቃሲም በተኩሱ ድምፅ ተቀስቅሰው ፣ ሕዝቡን ለማነጋገር በመኪና ከተማውን ዞሩ ፣ ያገኙት ምላሽ ደካማ ነበር ፣ በአጠቃላይ ድጋፍ አጡ ። ከዚያም እንደምንም ብለው ወደ መከላከያ ሚኒስቴራቸው ገብተው መሸጉ ። ይህም አደገኛ ስሕተት ነበር ። እንዲህ በማድረጋቸው በከተማው ከነበራቸው የሕዝባዊ ድጋፍ መሠረታቸው ተገለሉ ። መፈንቅለ መንግሥቱን ለማክሸፍ በጦር ኃይሉ ብቻ እምነት ጣሉ ። የጦር ኃይሉ የሱኒ ዓረብ አሰልጣኝና ግርፍ ቢሆንም የባዝ ፓርቲ አባላትና

ናስራውያን በብዛት ሠርገው ገብተውበት በለንበር ቻሲምን መርዳት ሳይሳካለት ቀረ ። ቻሲምም ወዲያው ተሸንፈው ከብዙ ደጋፊዎቻቸው ጋር ተያዙ ።

ቻሲም ባግዳድ ውስጥ ወዳለው ቴሌቪዥን ጣቢያ ከተወሰዱ በኋላ በከፍተኛ የክህደት ወንጀል በልዩ ፍርድ ቤት ተከሰሱ ። በአፋጣኝ የሞት ፍርድ ተበየነባቸው ። የፍርዱ ብያኔ በተነገራቸው ጊዜ ከቀድሞ ጓደኞቸው ከአረፍ ጋር ለመገናኘት ፈቃድ ጠየቁ ። አረፍን የፈለጉቸውም በ1951 እሳቸው እንዳደረጉት አረፍም ሕይወታቸውን ለማዳን እንዲረዷቸው ለመለመን ነበር ፤ ነገር ግን አረፍ ጉዳዩ ከዐቅማቸው በላይ እንደሆነ መለሱላቸው ። ቻሲም በቴሌቪዥን ጣቢያው ውስጥ በሚገኘው በዓረብኛ ሙዚቃ አዳራሽ በተኳሽ ቡድን በአጣዳፊ ተገደሉ ። ከቻሲም ጋር አብረው የተገደሉት ብዙዎቹ የራሳቸው ባለሥልጣኖችና ማኸዳዊ ሙዋር ነበሩ ። ማኸዳዊ የተገደሉት በዱላ ተቀጥቅጠው ነበር ። ይህም የተፈጸመው ያን ጊዜ የባዓዝ ፓርቲ ዋና ጸሐፊና በአዲሱ አገዛዝ ደግሞ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር በሆኑት በአሊ ሳላህ አልሳዓዲ ትእዛዝ መሠረት ነው ።

አዲሱ አገዛዝ በአገሪቱ ላይ ለነበረው ቁጥጥር ዋስትና ለማግኘት የቻሲም መሞት በማንኛውም ዓይነት መንገድ በቂ ነበር ። ውጊያው በባግዳድ የተለያዩ ቦታዎች እንደተጧጧፈ ነበር ። የከተማዋ ሕዝብ መፈንቅለ መንግሥቱን በመቃወም ሁለት ቀን እምርር ተዋጋ ። የጦር ኃይሉ ከተማዋን በከባድ መሣሪያ ደበደበ ። የአቶማቲክ መሣሪያ ጥይትም በየመንገዱ ከመጠን በላይ እርከፈከፈ ። ይህም ከአንድ ሺ በላይ ሲቪሎችን እልቂት አስከተለ ። የመንግሥት ግልበጣው ጠባይ በይበልጥ ወደፊት ስለሚመጡት ነገሮች የሚጠቁም ነበር ። ብዙ ሺ ሰዎች ከየመኖሪያ ቤታቸው ተወስደው ተገድለዋል ። በተለይ ኮሚኒስቶች ታድነዋል ። እሥር ቤቶች ሲሞሉ የተረፉት ወደ ስፖርት ስታዲዮሞች እንዲመለሱ ተደርጓል ። ብዙ እሥረኞችም በአሰቃቂ ምርመራ ላይ እንዳሉ ሞተዋል ።

እንደሞት ጥላ በማንዣበብ የሚቼ ቻሲም መንፈስ ፤ የአዲሱን አገዛዝ መሪዎች እያሳደደ አስጨነቃቸው ። ሕዝቡም የቻሲምን መሞት አላምን አለ ። ይህም እምነት የቻሲም ደጋፊዎች ውጊያቸውን እንዲቀጥሉ አበረታታቸው ። በዚህ ጊዜ ባዓዞች በተቀነጀለ መንገድ በመገናኛ



ብዙኃኑን ወደ መጠቀሙ ዞሩ ። ከዚህ ቀደም ባለው ምዕራፍ እንደተገለጸው የቻሲምን ሬሳ የደንብ ልብሱን አልብሰው በቴሌቪዥን አቀረቡ ። አንድ ወታደር ሬሳውን በወንበር ላይ አስቀምጦ ፤ የሚቀላበሰውን ጭንቅላት ፀጉር ይዞ ወደ ላይ አቅንቶ መልሶ ሲጥል በመደጋገም ታየ ። ይህም አድራጎት ሰውየው መሞታቸውን ያለጥርጥር ለተመልካቹ ሕዝብ ለማረጋገጥ ነበር ።

እሥራኤላዊው የታሪክ ምሁር የዓረብ አገሮችን ታሪክ እንዳስተዋሉት "የግብጽ ሕዝብ ውስጣዊ ሕይወት የሚያሳየው ባሕርይ የሚገለጠው በለዘብተኝነት ፤ የሶርያ በውጥረት ፤ የኢራቅ በአክራሪነት" ነው ። በዓረቡ ዓለም ውስጥ ኢራቃውያን ከሌሎች ዓረቦች ይልቅ ጉበዞችና መከራን እንደሚችሉ አድርጐ የማየት ሙከራ አለ ። በአንዳንድ በኩል ምናልባትም ናቸው ። ባግዳድ ከሚለው ቃል የመጣ "ታባግዳድ" የሚል የዓረብኛ ግሥ አለ ። ትርጉሙ ፤ "እየተወላገዱ ወይም ከወዲያ ወዲህ እየዘመሙ መሄድ" ማለት ነው ። የኢራቅ ማኀበራዊ ኑሮ ምሁር (ሶሲዮሎጂስት) አሊ አልዋርዲ ፤ ስለኀብረተሰባቸው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ስሜት ያልተቀላቀለበት አስተያየት እንዐባርቀዋል:—

> የአንድ እሥራኤላዊ ግለሰብ ስብእና ጣምራ ነገሮችን ይዟል ። ከሌሎች ይበልጥ አንድ እሥራኤላዊ በንግግሩ ውስጥም ሆነ በጽሑፉ የሚጠቀምባቸውን ከፍተኛ አስተሳሰብ ያፈቅራል ። ነገር ግን ከዚህ አስተሳሰብ ውጭ ይበልጥ የሚያፈነግጠው ደግሞ እርሱ ራሱ ነው ። አንድ እሥራኤላዊ 'ከሃይማኖት ጋር ቁርኝታቸው በጣም ከላላ' ወገኖች መካል ነው ። በሃይማኖት ዘርፍ በመከፋፈል በሚነካው ጊዜ ግን ጥልቅ ስሜት ያለው እርሱ ነው ።... እሥራቅ ውስጥ ሁለት የክብር አሰጣጥ ሥርዓት አለ — አንደኛው ፡ ቀንከፊን ፡ ጀግንነትንና ድፍረትን አቅርና ደግፎ የያዘው ነው — ሁለተኛው የአሸናፊ ጀግና መለያዎች ናቸው ። ከዚህ ጐን ለጐን ደግሞ ሌላ የክብር መስጫ ሥርዓት አለ ። ይህም በሥራና በትሕትና የሚያምን ነው ።...የእሥራቅ ሕዝብ የሚታወቀው ሁከተኛችና ግብዝ ሕዝብ በመሆን ነው ። እሥራኤላዊ ግን በሰውነቱ ከሌሎች ሰዎች የተለየ አይደለም ። ልዩነት ያለው ከልባዊ አስተሳሰቡ ላይ ነው ። በተግባር ላይ በሚያውለው መርህ ያበላል ። ሊደርስበት በሚይችለው ግብ ይተራል ።

## ፳

# "እመጣጣችን ለመቆየት ነው"

## የባዓዝ እንግዳ

በየካቲት 1955 በቻሲም ላይ የተከናወነው መፈንቅለ መንግሥት ፣ በኢራቅ ፖለቲካ ውስጥ አዲስና ምሕረት የለሽ ሰው መግባቱን ያመለከታል — የአህመድ ሀሰን አልባክርና በኋላም የሣዳም ሑሴን ባዓዝ ፓርቲ። ባዓዝ (በዓረብኛ ዳግም ልደት) በ1922 ሶርያ ውስጥ የፖለቲካ ንቅናቄ ሆኖ ተጀመረ ። ወዲያው ከ1920 እስከ 1924 በሶርቦን (የፈረንሳይ ዩኒቨርሲቲ) አብረው የተማሩ ሁለት የደማስቆ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን ሚሼል ዓፍለቅና ሳላህ ቢጣር ፣ በፓርቲው ውስጥ የበላይነቱን ያዙ ። ዓፍለቅ ፣ የፓርቲው የታወቀ የርእዮተ ዓለም መሪ ሲሆን ከኢራቅ አገዛዝ ጋር በ1981 እስከሞቱበት ድረስ ቆይተዋል ። የተቀበሩትም ባግዳድ ውስጥ በሚገኘው የባዓዝ ብሔራዊ ፓርቲ ዋና መሥሪያ ቤት ነው።

ዓፍለቅ ፣ ፓሪስ ውስጥ በነበሩበት ጊዜ ፣ ያኔ አውሮፓ ውስጥ እንደፋሽን ይታይ በነበረው በፋሽስት አስተሳሰብ ተማረኩ ። የሶርያው ተወላጅ የታሪክ ምሁር በሳም ጢቢ እንዳሉት ዓፍለቅ ለሌሎች የጀርመን ፋሽስቶችና "ለሂትለር መልካሙን ሁሉ ይመኙ ነበር ።" ዓፍለቅ በብሔረተኝነትና በሶሻሊዝም መካከል ሁለቱንም አጣምሮ የሚይዝ ሥርዓት ለመፍጠር ለነበራቸው ሐሳብ ናዚ ጀርመን በሞዴልነት ልታገለግላቸው እንደምትችል ተሰማቸው ። በ1933 የናዚ ጀርመን ደጋፊው ረሺድ አሊ በባግዳድ መፈንቅለ መንግሥት ባካሄዱ ጊዜ ፣ ዓፍለቅና ቢጣር ፣ "ኢራቅን የሚረዳ ማኅበር" መሠረቱ ። ይህም በኋላ የአገሪቱ ባዓዝ ፓርቲ እስኳል ሆነ ። በአሜሪካ የፕሪንስተን ዩኒቨርሲቲ የታሪክ ምሁር ቤርናርድ ሉዊስ በተናገሩት መሠረት ከለዘብተኞቹ ብሔረተኞች ይልቅ ዓፍለቅ ስለዓረብ ብሔረተኝነት የነበራቸው አስተያየት ፣ በጣም የመተሳሰብ ስሜት ያለውና ይበልጥ ተረጋጅ የነበረ ነው ።



"ከዘለዓለማዊ ተልእኮ ጋር አንድ የዓረብ ብሔር" በሚለው የባዓዞች መፈክር እንደተገለጸው ዓረቦችን ፣ እንደ አንድ ዘር ታላቅ ክብር ዓፍለቅ ከፍ አደረጉ ። የፓርቲ መሠረታዊ እምነት "አንድነት ፣ ነፃነት ፣ ሶሻሊዝም" የሚሉ ሦስት ቃላትን ይዟል ። ይሁን እንጂ በነዚህ መመሪያዎችም ሆነ ከፍ ያለ የዓፍለቅ ረቂቅ ሐሳብ ባለበት ጽሑፍ ውስጥ፣ የቀረበ ተጨባጭ ፖሊቲካዊ መርሀ ግብር የለም ።

ምንም እንኳ ባዓዞች ጠንካራ ፀረ ኮሙኒስት ቢሆኑም የተደራጁት በሌኒን መርሀ መሠረት እንደ ኅቡዕ የፖለቲካ ፓርቲ ነው ። ራሱን የቻለ የፓርቲው መሠረታዊ ክፍል ሕዋስ ነው ። ሕዋስ ከአራት ያልበለጡ አባላትንና መሪውን ይይዛል ። የሕዋስ መሪዎች ደግሞ በራሳቸው ሕዋስ በመደራጀት ከታች ወደ ላይ በሥልጣን ተዋረድ እስከእያንዳንዱ የዓረብ አገር የክልል ፓርቲ ኮሚቴ ድረስ ይሄዳሉ ። የክልል ፓርቲ ኮሚቴዎች ደግሞ በአንድ ላይ በመሆን ለጠቅላላው ዓረብ "ብሔር" ማእከላዊ ኮሚቴ ይሆናሉ ። በተግባር በእያንዳንዱ አገር ውስጥ የክልል ፓርቲ ኮሚቴዎች በባዓዞች የፖለቲካ ሥራ የበላይነት አላቸው ። የባዓዝ ፓርቲ ሥልጣን ላይ ሲወጣ ግን ማእከላዊ ኮሚቴው ሥልጣን ለያዘው የክልል ኮሚቴ ወዲያው የበታች ታዛዥ ሆነ ።

በ1955 በአዲሱ የባዓዝ አገዛዝ ኢራቅ በይፋ የምትመራው የአብዮታዊ እዝ ብሔራዊ የበላይ ምክር ቤት አካል ነው ። አገዛዙ ከእድገኛ ባሕርዩ ሌላ ፣ የበላይ ምክር ቤቱ አባልነት ኅቡእ ሆኖ ቀርቷል ። ምንም እንኳ መፈንቅለ መንግሥቱን ያካሄደው የጦር ኃይሉ ቢሆንና ኰሎኔል አብዱል ሰላም አሪፍ የአገዛዙ የይስሙላ ቁንጮ ባለሥልጣን ቢሆኑም የባዓዝ ፓርቲ የአብዮቱን እዝ በበላይነት ይዞታል ። የእዙ አባል የሆኑ የባዓዝ ፓርቲ አባል በኋላ ታሪኩን እንደገና ሲናገሩ ፣ "እኛ ውሳኔዎችን እናስልፋለን ፣ አሪፍ አይቀበሏቸውም ፣ ሆኖም በውሳኔያችን እንገፋለን።" ብለዋል ። "የባዓዝ ፓርቲ አባላት በጣም በማነሳቸው በኢራቅ ኅብረተሰብ የነበራቸው ተሰሚነት ከሕዝቡ ብዛት ጋር ተመጣጣኝ አልነበረም ። ሥልጣን በያዙበት ጊዜ የጠቅላላ አባላት ብዛት ከአንድ ሺ ያነሰ ነበር ። ከዚህም በላይ አባላቱ ወጣቶች ነበሩ ። የክልል ፓርቲ ኮሚቴ አባላት አማካይ ዕድሜ ሠላሳ ዓመት ብቻ ነበር ።

ባዓዞች የሥልጣን ይዞታቸውም እንዲጠበቅ ለማድረግ ብሔራዊ

ዘብን ለማስፋፋት ተንቀሳቀሱ ። በመፈንቅለ መንግሥቱ ማግሥት አዲሱ አገዛዝ ለብሔራዊ ዘብነት አዲስ የቅጥር ማስታወቂያ አውጥቶ ብዙ ጂ ወጣት ወንዶችን በአፋጣኝ መለመለ ። አንድ ኢራቃዊ ኮሙኒስት መሪ ዘቡን ሲገልጹ ፣ — "በአገር ፍቅርና በውጭ አገር ጠላትነት ላይ በተመሠረተ ፕሮፓጋንዳ ናላቸው የዞረ ጉርምሶችና ከኅብረተሰቡ የተለያዩ ክፍሎች የተለቀሙ ዱርዬዎች ናቸው ።" ብለው ነበር ። ነገር ግን ብዙም ሳይቆይ ይህን ዘብ የጦር ኃይሉ በጣም አስጊ ጠላት አድርጎ ተመለከተው ።

ባዓዞች ሥልጣን በያዙበት ጊዜ ብዙ ደም ቢያፈሱም ፣ መነሻው ላይ ከኢራቅ ኅብረተሰብ ውስጥ ኮሙኒስቶችን ከሚቃወሙና ፣ ነጋዴውን ኅብረተሰብ ጨምሮ ፣ በኩሎኔል አረፍ አሸናፊነት ከሚመሩት ከሱኒ ዓረቦች ከሚጣሉት ወገኖች አጥጋቢ ድጋፍ አግኝተው ነበር ።

ኢራቅ ውስጥ የባዓዝ ፓርቲ ተሳክቶለት ሥልጣን እንደያዘ የሶርያ ባዓዝ ፓርቲም ተመሳሳይ ሙከራ ለማድረግ ተደፋፈረ ። በመጋቢት 1955 የሶርያ ባዓዚስቶች ደማስቆ ውስጥ ምክር ቤት የነበረውን አገዛዝ ከሥልጣን ማውረዱ ተሳካላቸው ። ይህም ስኬት እንደገና የተገኘው ከናስራውያን ጦር መኰንኖች ጋር በመተባበር ነበር ። ሁለቱም ባዓዞች አገዛዝ በዓረብ አንድነት ርእዮተ ዓለም የፀና በመሆን የጀማል አብድል ናስርን ድጋፍ በማግኘት በአገሩ ውስጥ ያለውን የሥልጣን ይዞታ ለማጠናከር ፈለገ ።

መጀመሪያ ላይ ግብጽ ጥቂት ካመነታች በኋላ በዓረብ አንድነት ላይ ለመደራደር በሚያዝያ 1955 በካይሮ ስብሰባ ተደረገ ። በ1953 ከተባበሩት ዓረብ ሪፐብሊክ ሶርያ በመገንጠሏ ናስር ስለተመረሩ ፣ ለባዓዝ አገዛዝ ድጋፍ ለመስጠት ፍላጎት አልነበራቸውም ። ስብሰባው ተራዝሞ ነበርና ናስርም ይህን አጋጣሚ ባዓዝ ፓርቲን ዋጋ ለማሳጣት ተጠቅመውበታል። በስብሰባው ላይ የተደረጉ ዲስኩሮች በቴፕ ተቀርጸው በካይሮ ሬዲዮ ተሰራጭተው ነበር ። በዚሁ ዲስኩር ናስር የባዓዝን ልዑካን ቡድን በአደገኝነታቸው በታወቁት በሚሼል ዓፍለቅ ቁጥጥር የሚንቀሳቀሱ ፣ አንዱንም ሳይዙት ፣ ሁሉንም የሚደባብሱ ጉርምሶች አድርገው አቅርበዋቸዋል ።

የአንድነቱ ንግግር አለመሳካትና የናስር የጥላቻ አስተያየት እየጨ



መረ መምጣት ኢራቅ ውስጥ ባዓዝን አዳከመው ። ከዚህም ጋር የጦር ኃይሉና የባዓዝ ግንኙነት እየሻከረ ሄደ ። የኢራቅ ሕዝብ አስተያየትም ትዕግሥት እያጣና ከቁጥጥር ውጭ እየሆነ ሄደ ። የባዓዝ ፓርቲ የሕዝብ ድጋፍ ጭራሽ ያጣው በከተማዎች ውስጥ ብሔራዊ ዘቡ ሕዝቡን ለማስፈራራት ዘመቻ ሲጀምር ነበር ። የዘቡ አባላት መኖሪያ ቤቶችን እየሰበሩ በመግባት ነዋሪዎችን በማስፈራራት ንብረት መዝረፉን ተያያዙት ። ሰውን ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ የማሰር መብት ለራሳቸው በመስጠት ሕዝቡን እያሠሩ ወጣቱ ግዳም ሴቴን ሰውን ወደሚያሰቃዩበት ወደ ቀድሞው የኢራቅ ንጉሥ ቤተ መንግሥት በመውሰድ ለምርመራ ያጉሩ ነበር ።

የሕዝቡ ቅሬታ እየተባባሰ መሄድ ለኩሎኔል አረፍ አመቺ ሁኔታ ፈጠረላቸው ። በ1955 ክረምት ወራት በባዓዝ ፓርቲ ውስጥ ውጥረት እየጨመረ ሲሄድ አረፍ ጊዜውን ሊጠቀሙበት ፈለጉ ። በባዓዝ ፓርቲ ውስጥ መከፋፈልን ያስከተለው በከፊል የሥልጣን ሽሚያ ፣ በከፊል በሲቪሉና በጦር ኃይሉ መካከል የተነሣው ጠብ ፣ በከፊልም የእምነት መመሪያ ጥያቄ ነበር ። በጥቅምት 1955 ስድስተኛው ብሔራዊ (መላው ዓረብ) የፓርቲ ጉባኤ ተካሄደ ። በዚሁ ጊዜ አሊ ሳላሽ አልሳዓዲና አንጃዎቹ ተመርጠው የፓርቲውን ከፍተኛ ሥልጣን ያዙ ። ሳዓድ የባዓዝ እምነት መመሪያ አፍላቂ ነበሩ ። የሳዓድ የፓርቲ እምነት መመሪያ አተረጓጎም ተራማጅ ስለነበር የኢራቅ የባዓዝ አባል የጦር መኰንኖች የእርሳቸውን መመረጥ ከፉኛ በመቃወም አሸናፊነቱን በጦር መሣሪያ ኃይል ዋጋ ቢስ አደረጉት ። ሌላ ምርጫም ተካሂዶ አክራሪ ያልሆነ ሰው ኢራቅ ውስጥ የፓርቲውን የበላይ አመራር እንዲይዝ አሳሰቡ ። ከዚያም ሳዓዲንና አራት ተባባሪዎቻቸውን ይዘው በማሰር ወደ ኢራቅ መልሶ የማያስገባ ፓስፖርት በመስጠት በአውሮፕላን አሳፍረው ወደ ማድሪድ ሰደዷቸው ።

ሰዎቹ ተገደው ከአገር ውጭ መላካቸውን በመቃወም ብሔራዊ ዘቡ ለብዙ ቀናት የቆየ ግርግር ፈጠረ ። የሳዓዲ ደጋፊ የአየር ኃይል አባላት የፕሬዚዳንቱን ቤተ መንግሥት በቦምብ ደበደቡ ። የኢራቅ ባዓዞች ፣ ሚሼል ዓፍለቅና ሌሎችም ከፍተኛ የፓርቲ ባለሥልጣናት ከሶርያ ተጠርተው በኅዳር 1955 መጀመሪያ ባግዳድ ገቡ ። በዚህ ጊዜ የፓርቲውን መበታተን አጉልተው በመናገርና የኢራቅን ጉዳይ ለመምራት

የውጭ አገር ሰዎች እንዲገቡ ተደርጓል ፡ (ዓፍለቅ ሶርያዊ ብቻ ሳይሆን ክርስቲያንም ጭምር ነበሩ) በማለት አሪፍ በኅዳር 11/1955 እንቅስቃሴ አደረጉ ፡፡ የአሪፍ ታማኝ ክፍለ ጦሮች ባግዳድን ያዙ ፡፡ እንዲሁም የባዓዝን መሪዎች አሰሩ ፡፡

አሪፍ ፕሬዚዳንት እንደሆኑ ቆዩ ፤ ባዓዞች ግን ተባረዋል ፡፡ ሆኖም በመጀመሪያ የባዓዝ ተባባሪ የነበሩ ጥቂት ታክሪቲ የጦር መኰንኖች በአሪፍ መንግሥት ውስጥ ለመቆየት መረጡ ፡፡ ለእነዚህ ባክርና ሓዳም ፈጽመው ይቅርታ አላደረጉላቸውም ፡፡ በዚህ ዓይነት የኢራቅ የባዓዝ ፓርቲ የመጀመሪያው የመንግሥት ሥልጣን ይዞ መቆየት ሙከራ ተፈጸመ ፡፡ በመንግሥት ሥልጣን ላይ የቆየው ዘጠኝ ወር ነበር ፡፡

የባዓዝ ፓርቲ ከሥልጣን ከተባረረ በኋላ አገሪቱ ትልቅ እፎይታ አገኘች ፡፡ ጥሩ ምኞትና ተስፋ አዲሱን መንግሥት ተቀበለው ፡፡ ይኸው መንግሥት ታላቅ የንግግርና የተግባር ነፃነት ሰጠ ፡፡ በተጨማሪም ብሔራዊ ዘቡን ጨምሮ የባዓዝ መጨቆኛ መሣሪያ የነበሩትን ሁሉ ለማፈራረስ ተነሣ ፡፡

ነገር ግን የኢራቅን ኅብረተሰብ ዘለዓለም የሚያውኩት ችግሮች አገረሹ ፡፡ ምንም እንኳ አሪፍ ተኩስ የሚቆምበትን መንገድ ለማዘጋጀት ሙከራ ቢያደርጉም በኩርዶች ላይ የተነሣው ያገር ውስጥ ጦርነት ቀጠለ፡፡ መንግሥት በሺዓዎች ላይ በነበረው ፍራቻም በጥርጣሬ እንዲያዩዋቸው ተገደደ ፡፡ ከናስር ጋር ያለው የማያስደስት ግንኙነት መፍትሔ ሳያገኝ ቀርቷል ፡፡ ናስር የመላው ዓረብ አንድነት እንደሚመሠረት እምነት ቢኖራቸውም አሪፍ የኢራቅን ጥቅም ማስጠበቅ ከግብጽ ጋር ትርጉም ያለው አንድነት መመሥረትን የሚከለክል ሆኖ አግኝተውታል ፡፡ ናስር ግን ኢራቅን ለመቆጣጠር ግፊት ማድረጋቸውን ቀጠሉ ፤ ኢራቅ ኅብረት በመውረስ ወደሶሻሊዝም መመሪያ እንድትጠጋ አንዳንድ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ናስር አሪፍን አደፋፈሩ ፡፡ በባግዳድ የናስር አምባሳደርም የግብጽ ዓይነት መርሀ ግብር በሥራ ላይ እንዲውሉ ግፊት አደረጉ ፡፡ በኢራቅ የአስተዳደር መዋቅር ውስጥ ከፍተኛ ሥልጣን የነበራቸውን ናስራውያንም እገዛ አገኙ ፡፡

በሐምሌ 1956 አሪፍ የኢራቅን የኢኮኖሚ ተቋሞች በመውረሳቸው ባህላዊ የሕዝብ መሪዎችና ነጋዴው እርሳቸውን መደገፋቸውን እየተዉት



በመሄዳቸው ወዲያው በውሳኔያቸው ተጸጸቱ ፡፡ ይህም ሆኖ አወራረሳቸው ናስርንና የኢራቅን ናስራውያን አላረካቸውም ፡፡ እነዚህ ወገኖች አሁንም ተጨማሪ እርምጃ እንዲወሰዱ ግፊት አደረጉ ፡፡

በ1957 በልግ ናስራውያን በግብጽ እርዳታ በአሪፍ መንግሥት ላይ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ቢያደርጉም አሪፍ አከሸፉባቸው ፡፡ በቀጣዩ ወራት የናስራውያን ተጽእኖ እያነሰና እየጠፋ ሄደ ፡፡ በ1950 የኢራቅ የዘውድ አገዛዝ ካከተመ ወዲህ አሪፍ ለመጀመሪያ ጊዜ በሾሟቸው ሲቪል ጠቅላይ ሚኒስትር በአብዱልራህማን አልባዛዝ ካቢኔ አስፈጻሚነት ሰፊ ነፃነት የሚያቀዳጅ መመሪያ በማውጣት ለሥራ ተዘጋጁ ፡፡

የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራው ከከሸፈ በኋላ ናስራውያን የጀመሩት የአሪፍን ሥራ የማንኳሰስ ዘመቻ ለባዓዞች እንቅስቃሴ ማንሰራሪያ መንገድ ከፈተ ፡፡ ባዓዞችን ለማጥፋት አሪፍ የወሰዱት እርምጃ በጣም ከባድ አልነበረም ፡፡ የባዓዝ ፓርቲ ተባባሪ ታክሪቲዎች በመንግሥቱ ላይ በነበራቸው ተጽእኖ መጠቀሙን ቀጠሉ ፡፡ ለባዓዞች መስጠት የሚችሉትን እርዳታ መጠበቅ ጀመሩ ፡፡

ኢራቅ ውስጥ በየጊዜው በድንገት በተነሣ "አሸዋ አዘል አውሎ ነፋስ" ምክንያት እየተባለ ከሚደርሰው የተለመደ ምስጢራዊ አደጋ መካከል በአንዱ አሪፍ በሄሊኮፕተር መከስከስ በሚያዝያ 1958 ሞቱ ፡፡ እኅኛውም በደካማው ታላቅ ወንድማቸው በፕሬዚዳንት አብዱል ራህማን አሪፍ ተተኩ ፡፡ ባዛዝም የጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ቦታ እንደያዙ ቀጠሉ ፡፡ ሁለቱም ሰዎች እስከዛሬ ያልተደረገ ለቀቅ ያለ የመደራደር እድል በመስጠት ከኩርዶች ጋር የተኩስ አቁም ስምምነት አደረጉ ፡፡ ይህም በመጨረሻ ለሰሜን ኢራቅ ሰላም አመጣ ፡፡ ይህ የሁለተኛው አሪፍ ፕሬዚዳንትነት ዘመን የመንግሥት ቁጥጥር ይበልጥ የላላበትና የሰብዓዊ መብት መደፈር በሰፋት የተገታበት ጊዜ ነበር ፡፡

ሁለተኛው የናስራውያን የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ በሰኔ 1958 ተካሄደ ፡፡ ነገር ግን እንደገና ከሸፈ ፡፡ አመጸኞቹን በመደምሰስ አብዱል ራህማን አሪፍ በባዓዞች ታገዙ ፡፡ ይህም ድርጊት በእሳቸውና በመንግሥታቸው ላይ የባዓዝን ፓርቲ እንቅስቃሴ ያለ መቆጣጠር ዝንባሌ አሳደረ ፡፡ በ1955 ሳዓዲ ከተጋዘ በኋላ የፓርቲው ዋና ጸሐፊ ባክር የምክትልነቱን ቦታ ለሓዳም በመስጠት የፓርቲውን የሲቪል ትርጓሜ

እንዲያደራጁና የፓርቲውን ውስጣዊ የደህንነት ፖሊሲ እንዲያቋቁሙ አደረጓቸው ። በባከር የበላይ ጠባቂነት በአዲስ መንፈስ ከነበራረው የባዓዝ ፓርቲ ውስጥ ሣዳም አይለው ወጡ ።

ከሁለት ዓመት በኋላ ሐምሌ 11 1960 ባዓዞች በአምስት ዓመት ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ ሥልጣን ያዙ ። የተንቀሳቀሱት እንደ በፊቱ ከዓረብ ብሔረተኞች የጦር መኰንኖች ፣ በዚህ ጊዜ ግን በተለይ ከሪፐብሊኩ ዘቦች ጋር በመጣመር ነበር ። በቀላሉ የሚታለሉና የጋለ ምኞት የነበራቸው የወታደራዊ መረጃ ምክትል ሥራ አስኪያጅ ኰሎኔል አብደል ረዛቅ አልናዮፍ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ለማድረግ ወጣት የጦር መኰንን ግብረ አበር በመፈለግ ላይ ነበሩ ። ቀስበቀስ የባዓዝ ፓርቲውን መረጡ ። ናዮፍ የሪፐብሊካን ዘቦችን በመፈንቅለ መንግሥቱ እንዲያብሩ ለማድረግ የቻሉት ለዋና አዛዡና ለሌሎቹም ዘብ መኰንኖች ከፍተኛ የሥልጣን ቦታ ለመስጠት ቃል በመግባት ነበር ።

እንዲህ ሆኖ እንኳን የባዓዝ ፓርቲውን ገፍቶ ሥልጣን ላይ ለማውጣት በቂ እርዳታ አልነበረም ። የተፈራው ታንከኛ ጦር ዋና አዛዦች በመጀመሪያ ጊዜ ለመፈረም ፈቃደኛ አልነበሩም ። ለዚህ ምክንያቱም ሐምሌ 1959 በጠቅላይ ሚኒስትሩ በጣሂር ያህያና በሰሜን ኢራቅ ጉሳዎች መኻል ክርክር መነሣቱ ነበር ። ይህም ጥል ለሻሚር ሼክ በቅርብ የሚዛመዱትን አያሌ የሪፐብሊኩ ታንከኛ ኻለቃ ጦር ባልደረባ መኰንኖች አስቆጣ ። ይሁንና ከአድመኞቹ ጋር እድላቸውን ለመሞከር ወሰኑ ። ከነዚህም መኻል አንዱ የጦር መኰንን ፣ አራት ታንኮች አሰልፎ አስፈላጊውን ትጥቅ አሟልቶና ተዘጋጅቶ በመጠባበቅ ላይ እንዳለ ጉህ ሲቀድ ሣዳምን ጨምሮ ሠላሳ ባዓዞች ከመፈንቅለ መንግሥቱ ዕለት ማለዳ በፊት ወደ ዘቡ ጦር ሠፈር ገቡ ። በዚህ ጊዜ መኰንኑ ጉራውን ሲነዛ እነሣዳምን ሲገቡ በደንብ እንዳያቸው ገልጾ "በታንኮቼ ባደባያቸው በሚዘሪንበ ድረስ ላፈናጥራቸው እችል ነበር ፣ ታዲያ ምን ያደርጋል 'ጉሳዬን በጣሂር ያህያ ማስደብ ይሆንብኛል' ብዬ ተውኩት ።" በማለት ተናግሯል ።

የሪፐብሊኩ ዘቦች ለመፈንቅለ መንግሥቱ መሳካት በጣም አስፈላጊ ነበሩ ። አሪፍ ራሳቸው የመለመሏቸው ምርጥ የጦር ኃይል ናቸው ፣ ዋና አዛዣቸውን ኰሎኔል ኢብራሂም አልዳውድን አሪፍ ታማኝ የበታች ታዛዥ አድርገው ይቆጥሯቸው ነበር ። የሪፐብሊኩ ዘብ ኃላፊነት



ፕሬዚዳንቱን እንዳይገለበጡና ከመገደል መከላከል ፣ እንዲሁም ባግዳድ ውስጥ ሥነ ሥርዓት ማስከበር ናቸው ። ለመፈንቅለ መንግሥቱ መሳካት ወይም መክሸፍ ወሳኞቹ ወጣት የጦር መኰንኖች የሁኔታው የበላይ ተቆጣጣሪ መሆናቸውን አምነው ነበር ። እነሱ ያሰቡት ባዓዞች የበታችነት ሚና ይዘው ተካፋይ የሚሆኑበት መንግሥት የሚያቋቁሙት ራሳቸው የሚሆኑ መስሏቸው ነበር ። አይደለም—ተሳስተዋል ።

የባዓዝ ፓርቲ አባላት በ1955 ከደረሰው ሁኔታ በጣም ጠቃሚ ትምህርት ገብይተዋል ። ሥልጣናቸውን አስከማጣት ያደረሳቸውን ስሕተት እንዳይደግሙ ለማድረግ ከፍተኛ ጥንቃቄ አድርገዋል ። ባከር አዲሱ የኢራቅ ፕሬዚዳንት ሆኑ ። የባዓዝ ተባባሪዎች ናዮፍና ዳውድ ደግሞ ጠቅላይ ሚኒስትርና የመከላከያ ሚኒስትር ሆነው በቅደም ተከተል ተሾሙ ። ነገር ግን ፣ ከሁለቱ አንዳቸውም በመንግሥት ሥልጣን ላይ ለረጅም ጊዜ ለመቆየት አልታደሉም ። ከ1955 የተገኘው ትልቅ ትምህርት ፣ በመጣመር የሥልጣን ተካፋይ የሆነውን ግብረአበር በአፋጣኝ ማስወገድ አስፈላጊ መሆኑ ነው ። ይህንንም ባዓዞች አድርገዋል ።

በ1955 ሐምሌ መጨረሻ መፈንቅለ መንግሥቱ በተከናወነ በዓሥራ ሦስት ቀኑ ባዓዞች ዳውድን በአውሮፕላን ከአገር ለማስወጣት በተዘጋጁበት ዕለት ባከር ናዮፍን በፕሬዚዳንቱ ቤተ መንግሥት ምሳ ጋበዟቸው ። ከምግብ በኋላ ለሻይ በሕንፃው ውስጥ ወዳንዱ ማረፊያ ቤት ወሰዷቸው ። ከዚያም ፕሬዚዳንቱ ይቅርታ ጠይቀው ናዮፍን በክፍሉ ውስጥ ብቻቸውን ትተዋቸው ሄዱ ። ባከር ግን ፈጽመው አልተመለሱም ፣ በምትኩ ሣዳምና የጦር መግሪያ የታጠቁ ጓደኞቻቸው ገቡ። ሣዳም ሽጉጣቸውን መዘዙና ናዮፍን ከፍ ዝቅ አድርገው መሳደብ ጀመሩ ፣ ከዚያም እዚያው ፊት ለፊት ከሥልጣን መውረዳቸውን ነገሯቸው ፣ ናዮፍም በመደንገጥ ነፍሳቸውን ለማትረፍ ተማጸኑ ። ሣዳም አፈዙባቸውና በአስቸኳይ ወደአውሮፕላን ማረፊያ ላኳቸው ፣ ከዚያም አሳፍረው ወደ ሞሮኮ ሰደዷቸው ። ሲቪል ተባባሪዎቻቸውም ተጠራርገው ከካቢኔው ተባረሩ ። በዚህ መንገድ የናዮፍ የዓሥራ ሦስት ቀናት ሥልጣን አከተመ ። ባዓዞች ወደ ሥልጣን ተመለሱ ። (ከዓሥር ዓመት በኋላ ናዮፍ በሣዳም ትእዛዝ ለንደን ውስጥ ተገደሉ ። ዳውድ ወደ ኢራቅ ፈጽመው አልተመለሱም ። በአሁኑ ጊዜ በስደት ሳዑዲ ዓረቢያ ውስጥ ይኖራሉ) ።

ባዓዞች በወታደራዊ መፈንቅለ መንግሥት ሥልጣን መያዛቸው በአጠቃላይ በአገሪቱ ውስጥ ፓርቲው ደጋፊ እንደሌለው ሌላው ተጨማሪ ምስክር ነው ። በራሱ በፓርቲው ግምት መሠረት በ1960 የባዓዝ ፓርቲ ከአምስት ሺህ በላይ አባል አልነበረውም ። ባዓዞች ሁልጊዜ የባዓዝ ደጋፊ ካልሆኑ የጦር መኰንኖች ጋር በማበር መፈንቅለ መንግሥት መሞከራቸው ፣ ወታደር በጣም በሚሳሳበት ክልል እንኳ ሳይቀር ጥንካሬ እንደሌላቸው ያረጋግጣል ። የ1955ቱን ገደብ የለሽ ድርጊቱን በግልጽ በማስታወስ የባዓዝ ፓርቲ ወደ ሥልጣን መመለስ በመላው የኢራቅ ሕዝብ በታላቅ ፍርሃትና ጭንቀት ታየ ። ነገር ግን በዚያን ጊዜም ቢሆን እንደ ቀድሞው ሕዝቡ ሊያደርግ የሚችለው አንዳችም ነገር አልነበረም ።

ከሐምሌ 1955 መጨረሻ ያልተፈለጉ ሰዎችን የማስወገድ እርምጃ በኋላ የመጀመሪያው የባዓዝ መንግሥት ይዘት በፓርቲው ውስጥ የጦር መኰንኖችን ብዛት እንዘባርቋል ። በሳዳም የበላይነት ከሚመሩት ወጣት ሲቪሎች ጋር ሲነፃፀሩ የጦር መኰንኖቹ በዕድሜ ላቅ ያሉ ፣ ይበልጥ የተደላደሉ ጥቂት ርኅራኄም ያላቸው ናቸው ። ናየፍንና ዳውድን በማባረር ሥልጣን በመጨበጥ በሚገዛው የአብዮታዊ እዝ የበላይ ምክር ቤት ውስጥ ቢያንስ ሕዝብ የሚያውቃቸው አምስት ሰዎች ነበሩ ፦ ባክር ፕሬዚዳንት ሆነው ፣ ወደ ፊልድ ማርሻልነት ከፍ አሉ ። ታክሪቴው ጄኔራል ሃርዳን ፣ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የመከላከያ ሚኒስትር ሆኑ። በዘውድ አገዛዙ ሥር በዋሽንግተን ውስጥ ወታደራዊ አታሼ የነበሩት ጄኔራል ሳላህ ማህዲ አማሽ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትር ሆኑ ። ጄኔራል ሳዱን ጋይዳን የሪፐብሊኩ ዘብ ዋና አዛዥ ሲሆኑ ፣ የባክር አጐት — ጄኔራል ሃማድ ሻሂድ የጦር ኃይሎች ኢታማዦር ሹም ሆኑ ።

ሳዳም ሑሴን የሥልጣን ድርሻቸው ሳይታወቅ እንዲቆይ መምረጣቸው ጉልህ ሚና ነበረው ። ምንም እንኳ የፓርቲው ምክትል ዋና ጸሐፊ ቢሆኑ እስከ ኅዳር 1962 የበላይ ምክር ቤት አባልነታቸው ሳይገለጽ ቆየ ። በ1955 እንደተደረገው ሁሉ የባዓዝ ፓርቲ እንደገና ከሥልጣን እንዳይባረር ፈሩ ፤ በዚያም ሁኔታ አለመታወቁን ፈለጉ ።

ከባዓዝ መሪዎች ሁሉ መኻል ስለወደፊቱ በግልጽ ማየት የቻሉት ሳዳም ብቻ ናቸው ። ከባክር የበላይ ጠባቂነት ጋር ሳዳም በስለላው



ድርጅት አማካይነት በፓርቲው ውስጥ የፖለቲካ መሠረታቸውን ገነቡ ። ኢራቅንና ሕዝቧን በአጠቃላይ ለመቆጣጠር ዓላማቸውን በግልጽ ነደፉ ፤ ይህን ዓላማቸውን ከግቡ ለማድረስ አገሪቱን በፓርቲው ቁጥጥር ሥር ለማዋልና ከዚህ በስተጀርባ ደግሞ ራሳቸው ፓርቲውን መቆጣጠር ቀጠሉ ። "ጂኻዝ ኻኒን" የተባለው የመጀመሪያው የፓርቲው የማሸበሪያና የማስፈራሪያ ድርጅት ተስፋፍቶ ሙኻባራት በመባል ተደራጅቶ መረጃ የሚቀርበው ለሳዳም ሆነ ።

የባዓዝን ፓርቲ ሥልጣን ላይ መውጣት ሕዝቡ በደህና እንዳልተቀበለው በማወቅ ባዓዝ በፍጥነት "አመጣጣችን በሥልጣን ላይ ለመቆየት ነው" በሚል አዲስ መፈክር ኃይሉንና ቁርጠኝነቱን ለማሳየት ለሕዝቡ ትርኢት አቀረበ ። ይህን ትርኢት ለማዘጋጀትም ሆነ ለሕዝብ ለማሳየት ኃላፊው ሳዳም ነበሩ ። የቃሲም ትርኢት በማኽዳዊ ፍርድ ቤት አማካይነት ይከናውን የነበረው ይበልጡን ያለምንም ደም መፋሰስ ነበር ፤ የሳዳም ትርኢት ግን በደም ማፋሰስ ላይ አተኮረ ።

በጥቅምት 1981 ሥልጣን በያዘ በሦስት ወሩ "ዋናውን የጽዮናዊ የስለላ መዋቅር ሰባበርኩ" ሲል አገዛዙ አስታወቀ ፤ እንደ ዕውነቱ ከሆነ ግን አገዛዙ የሚጠላቸውን ሰዎች ለማጥፋት ወጥመድ በመዘርጋት ነበር ። ነገሩ እንዲህ ነው ፦ ሳዲቅ ጃፈር የተባለ የስለላ ድርጅት አባል ለዚህ ተግባር እንዲሠራ ተደረገና ባግዳድና ባስራ ውስጥ ለሚገኙ የታወቁ ሰዎች ለእያንዳንዳቸው ደብዳቤ እንዲያድል ተደረገ ። ደብዳቤ የተዘጋጀው በእሥራኤል የስለላ መዋቅር አድራሻ እንደተጻፈ ተደርጐ ነበር ። ከዚያም ሌላ የደኅንነት አባል ብቅ ይልና ነገሩን ደርሶበት ተከታትሎ እንደያዘው ያስመስላል ። በዚህ ዓይነት ፣ ከቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ባዛዝ ጭምር ፣ ዓሥራ ሁለት ያኸል ሰዎች ታሠሩ ።(በ1965 ባዛዝ እሥር ቤት ውስጥ በደረሰባቸው ጉዳት ሞቱ ።)

እነዚህን የታሠሩ ሰዎች እንዲመረምር ታክሪቴውን የክልል ፓርቲ ኮሚቴ አባል — ሳላህ ዑመርን ሳዳም በምርመራ ኃላፊነት ሾሙት ። የቀድሞው ምክር ቤት አባል አብድል ኻዲ አልባኻሪ ከተከሳሾቹ አንዱ ሆኑ ። በርሳቸው ላይ የደረሰው ፍዳ በሌሎችም ላይ የተለመደ ነበር ። በሌሎች ሰዎች ላይ ባታቸውን ቀስረው ሰላይ መሆናቸውን እንዲናገሩ መርማሪዎቹ ቢጠይቋቸውና በአረመኔያዊ መንገድ ቢያሰቃዩዋቸውም

አልናዘዝም ስላሏቸው ፣ ካልሆነ ባለቤታቸውን በማስገደድ የሚያፍሩባቸው መሆናቸውን ዛቱባቸው ። እርሳቸውም ሁኔታው ስላስጋቸው እነርሱ በጠየቁት መሠረት በኑዛዜው ላይ ፈረሙላቸው — ነገር ግን እንዲሰቀሉ ተደረገ ።

እንዲሁም አገዛዙ የኢራቅን አይሁድ አሠረ ። ለመጀመሪያ ጊዜ ባደባባይ ከሚሰቀሉት ዓሥራ አራት ኢራቃውያን ዓሥራ አንዱ አይሁድ ነበሩ ። የሚሰቀሉበት ዕለት ጥር 19/1961 እንደሕዝብ በዓል ታሰበ ። ምንም እንኳን የኢራቅ ከበርቴዎች አድራጎቱን አስጸያፊ አድርገው ቢመለከቱት ፣ የስቅላቱን አፈጻጸም ለማየት ወደ ሁለት መቶ ሺ ሰው ተገኘ ። አብዛኛው የባግዳድ ሠራተኞችና ከአካባቢው ገጠር የመጣ ገበሬ ነበር ። አንዳንዶቹ ትንንሽ ልጆቻቸውን በእጃቸው አንጠልጥለው መጡ። በባግዳድ ፣ "ነፃነት አደባባይ" ላይ ተከሳሾቹ በዕንጨት ቅስት ላይ መደዳውን በረድፍ ተሰቅለዋል ። በዓሉ ለሃያ አራት ሰዓት ቀጠለ ። ባክር ፣ ሳላህ ሁመርና ለሌሎችም በመደንፋት ጥላቻ ፣ ዘለፋና ዛቻ የተሞላ ንግግር አደረጉ ። ተንጠልጥሎ በነፋስ ከሚወዛወዘው ሬሳ በስተጀርባ ሆነው ጽዮናዊነትንና ኢምፔሪያሊዝምን አወገዙ ።

ምንም እንኳ የአገዛዙ ቁጣ ያረፈው ከጽዮናዊነትና ከኢምፔሪያሊዝም ጋር ግንኙነት ባላቸው ፣ በተለይም እየተመናመኑ በሄዱት በኢራቅ አይሁድ ላይ ቢመስልም ዕውነተኛ ዒላማው ከታወቁ የኢራቅ የፖለቲካ ሰዎች ወደፊት የአገዛዙ ተቃዋሚ ኃይል ሊሆን በሚችሉት ላይ ነበር ። የባዓዝን ፓርቲ ሥልጣን እንዴት እናስጠብቅ? የሚለው ችግር በእጁ እያለ ፣ ከዚህ ጋር ግንኙነት የሌላቸውን የጽዮናዊነትና የኢምፔሪያሊዝምን ሙት መናፍስት በማስነሣት አገዛዙ ከኀብረተሰቡ የጥቂት ወገኖችን ድጋፍ በማንቀሳቀስ ሌሎች ጥቂት ወገኖችን ለመግደል ችሏል። እንደዚህ እንደሚደረገው ሁሉ ተመሳሳይ ስልት በመጠቀም በእነርሱም ላይ እንደሚዞርባቸው የኢራቅ ዕውቅ የፖለቲካ ሰዎች ወዲያውኑ ተገንዝበውታል ። ዕውነቱም ይህ ነበር፦ ለመቀጣጫ መሆኑን እንዲያስተውሉት ይፈለጋል ። አንድ የቀድሞ ባለሥልጣን አንድ ቀን ከግዳም ጐን ተቀምጠው በድንገት ግዳም ስለስለላ ሳተላይቶች ሲያወሩ የተናገሩትን ያስታውሳሉ ። ግዳም "የስለላ ሳተላይቶች በጣም የተራቀቁ በመሆናቸው በእጅ ላይ ያለ ወረቀት እንኳን ያነባሉ" በማለት ተናገሩ ። ባለሥልጣኑም "ለምን ታዲያ አይሁድን ሰቀልናቸው?" በማለት ይጠይ



ቃሉ ። ግዳምም ፣ "ሕዝቡን ለማስተማር ነዋ!" በማለት መለሱ ። ያም ትምህርት አገዛዙ ያለማወላወል የጭካኔ እርምጃ ከመውሰድ ወደኋላ እንደማይልና አስፈላጊም ከሆነ በዛሬዪቱ ኢራቅ ታሪክ ውስጥ ተወዳዳሪ የሌለው ጭካኔ ለመፈጸም ዝግጁ መሆናቸውን ማሳወቃቸው ነው ።

ግድያው በብዛት ቀጠለ ። ከዚህም ሌላ ፣ አገዛዙ ሕዝቡን የሚያሸብርበትና በላዩም ፍርሀት የሚለቅበት መንገድ በሥራ ላይ አዋለ። መንግሥት በኃላፊነት የሚመራው ግድያና ጠለፋ በየቦታው ተጀመረ ። የታወቀው ኸብር የመጀመሪያ ሰለባ የቀድሞውን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፣ አንድ ጊዜ በለንደን የምሥራቅና የአፍሪካ ጥናት ዩኒቨርሲቲ መምህር የነበሩና እንዲሁም በዋሽንግተን የኢራቅ አምባሳደር የነበሩት ናስር አልኻኒ ናቸው ። በኅዳር 1981 ወጣት አባላት ብቻ የሚገኙበት ባዓዞች ቡድን ወደ ቤታቸው በመምጣት ፕሬዚዳንት ባክርን ለማነጋገር ወደ ቤተመንግሥት አብረውት እንዲሄዱ ጠየቋቸው ፣ ኻኒም ከእነሱ ጋር ሄዱና ሳይመለሱ በዚያው ቀሩ ። ከጥቂት ቀናት በኋላ ከባግዳድ ውጭ ሬሳቸው በአንድ ቦይ ውስጥ ተገኘ ። ከጥቂት ዓመታት በኋላ የአንድ ባዓዚስት "ሰማዕት" ፎቶግራፍ በባግዳድ ጋዜጦች ላይ ታትሞ በወጣበት ጊዜ እየርላንዳዊዋ የኻኒ ሚስት ባለቤታቸውን ወስዶ የሰወረባቸው ሰው ማንነት ለመለየት ችለዋል ። ይኸው ሰዋሪ በአቶሞቢል "አደጋ" ተገድሏል ። እሚሚቱ ጥንት በነበረው ዘዴ ፣ ገዳይ መልስ በተራው ሲገደል ፣ እንደሚባለው ነው ። ከዚህም ሌላ ቀድሞ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ፣ በጣም ተፈላጊ የባዓዝ ፓርቲ አባልና የግዳም ተወዳዳሪ የነበሩት አብዱል ከሪም አልሼ የከኸሊ በተመሳሳይ ሁኔታ ከዓሥር ዓመት በኋላ በመኪና አደጋ ሕይወታቸውን አጥተዋል ።

ባዓዝ እንዲሁም ከፍተኛ የኑሮ ደረጃ ያለውን የሕዝብ ወገን የሚያሸብርበት አዲስ ዘዴ መጠቀም ጀመረ ። በ1960ዎቹ ውስጥ በባግዳድ በአንድ አካባቢ በኑርብትና የሚኖሩ ባለጸጋዎችን መኖሪያ ቤቶች በርና መስኮት ወርበላ በፋስ ሰባብሮ በመግባት ቤተሰቡን በሙሉ እየቆራረጠ መግደል ጀመረ ። ሕዝቡ በፍርሀት ተናጠ ። በተለይ የወርበላው ቡድን መሪ "የባግዳዱ ባለፋስ" ተብሎ የሚታወቀውን ሰው ፈራው ። ሳይተኙ ሌቱን ሙሉ ቤታቸውን ሲጠብቁ ማደር ጀመሩ ። ከብዙ አስፈሪና አስደንጋጭ ግድያ በኋላ ባለፋሱ ሰው ተያዘ ። ሳሚር

ኸሊል እንደዘገቡት የባለፋሉ ወሮበላ ቡድን ከፖሊስ ለማምለጥ እንዲችል ምስጢራዊ የሬዲዮ መገናኛ ለመከታተል የሚያስችል የባለሙያ ያኸል ዕውቀት አለው ። ስለዚህ ጉዳይ ጠንቅቀው የሚያውቁ ሰዎች በሰጡት መረጃ መሠረት ባለፋሉ የቀድሞ የደኅንነት አባልና አልፎ አልፎ ለዚህ ዓይነቱ ግድያ መንግሥት ያሠማራው የነበረ ነው ።

አገዛዙ ሥልጣኑ ከ – እስከ የሌለው ፍጹም መሆኑን ለማሳየት ሆን ብሎ ኢራቅ ውስጥ የሚገኙትን የታወቁና የተከበሩ ሰዎች የማዋረድ መመሪያ ተከትሏል ። የታወቁት የዓለም ሺዓት እስላሞች መሪ ሰይድ ሙኸሲን አልሐኪም በመስከረም 1962 ባግዳድን ለመጐብኘት ከናጃፍ ተንሥተው በሚጓዙበት ጊዜ በአደባባይ እንዲዋረዱ ተደርጓል ። በከተማይቱ ውስጥ በቆዩበት ወቅት ከሳምንት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ብዙ ሺ ሕዝብ ሊያጠቃቸው መጣ ። አገዛዙ ለራሱ እንኳ ሊያገኘው ፈጽሞ የማይችለውን ታማኝነት ሕዝቡ ለሃይማኖት መሪው በታላቅ አክብሮት በማሳየቱ እጅግ በጣም ታወከ ። ከሳምንት በኋላ አንድ ሰው በኢራቅ ቴሌቪዥን ብቅ አለና የሐኪም ልጅና ወኪሉ ሰይድ ማህዲ ሰላይና አድመኛ መሆኑን አጋለጠ ። ከዚያም ሕዝቡ ሰይድ ሙኸሲንን እንዳይጠይቅ ወይንም እንዳያጅብ መንግሥት አገደ ። እሳቸውንም በአንድ መኪና ብቻ ከካዳሚዎቻቸው ጋር ብቻ ወደ ናጃፍ እንዲመለሱ አስገደዳቸው ። ይህም ሳይወዱ በአርምሞ የተቀበሉት ውርደት ነበር ። ልጃቸው ማህዲም ተሰወረ ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ በሌለበት የሞት ቅጣት ተበየነበት ። እሱ ግን አገዛዙን በብርቱ መቃወሙን ቀጠለ ። ግዳም ማህዲን በ1980 ከሃያ ዓመት በኋላ በካርቱም ሂልተን ሆቴል ውስጥ መተላለፊያ ቦታ ላይ አስገደሉት ።

ይበልጡ የባዓዝ ፓርቲ ደም ማፋሰስ ዓላማ ሌላ የሥልጣን ተቀናቃኝ እንዳይነሣ ሕዝቡን በቅድሚያ በማስፈራራትና በዚህም ተውጦ አሜን ብሎ እንዲገዛ ለማድረግ እንጂ ጠላትን ለማጥፋት አልነበረም ። አገዛዙን የሚያሠጋው ዕውነተኛ ጠላትም ነበር ፤ እሱንም ቢሆን ያለምሕረት ድምጥማጡን አጥፍቶታል ። ጥር 13 1962 በአገዛዙ ላይ ለመፈንቅለ መንግሥት የተነሣ አድማ የተደረሰበት መሆኑን መንግሥት አስታወቀ ። ይህ ግን ዕውነት ነበር ። የባዓዝን አገዛዝ ለመጣል በናየፍና በሁለተኛው አረፍ መንግሥት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር



በነበረ ሰው የሚመራ ሴራ ነበር ። ይህንንም ኢራን ደግፋዋለች ። ይኸው ሴራ ወዲያው እንደተጋለጠ አብዮታዊ ፍርድ ቤት ተቋቋመና በሠላሳ ስድስት ሰዓት ውስጥ አርባ አራት ሰዎች ለፍርድ አቅርቦ በሁሉም ላይ የሞት ቅጣት በይኖ እንዲፈጸምባቸው አደረገ ። ከተገደሉት ሰዎች ብዙዎቹ በእሥራት ላይ የቆዩ ስለነበሩ ከሴራው ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት አልነበራቸውም ። ነገር ግን አገዛዙ አጋጣሚውን በመጠቀም ሌላ ዓላማውን ግምር አግብ አደረሰ ።

የሞት ቅጣት የተፈረደባቸው ሰዎች ፍርዱ እንደተሰጠ ወዲያውኑ ከፍርድ ቤቱ ፊት ለፊት በጥይት ተደበደቡ ። ከነዚህም አንዱ ወጣት የጦር መኰንን የተገደለው በስሕተት እንደ ነበር በኋላ ተደርሶበታል ። አገዛዙም ቢሆን ሊገድለው አልፈለገም ነበር ። ከፍተኛ የመንግሥት ሠራተኛ የነበሩትን አባቱን የባዓዝ ፓርቲ በስሕተቱ አምስት ሺ ዲናር ከፈላቸዋል ። ምን ያድርጉ? ለመቀበል ተገደዱ ።

አገዛዙ ሕዝብ ሳይወድ በግድ ሥልጣኑን ለማጠናከር ከሚያከናውነው ሌላ የፓርቲ መሪዎችም በአገዛዙ ውስጥ ሥልጣናቸውን ለማጠናከር ፈለጉ ። ለመሠረቱ በዚህም ረገድ ተመሳሳይ ዘዴ ነበር የተጠቀሙት ። ምንም እንኳን ሳዳም በፓርቲው ውስጥ ሁለተኛው ባለሥልጣን ቢሆኑ የጦር ኃይሉ በግልጽ የሚደግፋቸውና በስድሚ የገፉ ተወዳዳሪዎችም ነበሯቸው ። ሳዳም እነዚህን ቀስ በቀስ አስወግደዋቸዋል ። በኅዳር 1955 መከፋፈል ከተፈጠረ በኋላ ታክሪቲው ጄኔራል ኻርዳን በአሳድ ዘመን መንግሥት ያገለገሉ ነበሩ ። ይህም በተለይ በሳዳም በኩል ተጠርጣሪ አድርጓቸዋል ።

በሳዳም ግፊት ባክር በሚያዝያ 1962 ኻርዳንን ከመከላከያ ሚኒስትርነት ወደ ምክትል ፕሬዚዳንትነት ከፍ አድርገው ሾሟቸው ። ከዚያም በጥቅምት 1963 በአጠቃላይ ከሥራ አሰናብተው ከአገር አስወጧቸው ። በሚቀጥለው በየካቲት 1963 ኻርዳን ኩዌትን በመጐብኘትና በኩዌት የኢራቅን አምባሳደር በማጀብ ላይ እንዳሉ ተገደሉ ። ገዳዩን ለመያዝም ሆነ ወደኢራቅ ሲያመልጥ ለመከልከል የኩዌት መንግሥት ጨርሶ አልሞከረም ። ሌላው የሳዳም ተወዳዳሪ ጄኔራል ሳሊኽ ማህዲ አማሽ ደግሞ በሚያዝያ 1962 ወደምክትል ፕሬዚዳንትነት ደረጃ "ከፍ" አሉ ። (የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትር ነበሩ ።) ይህም በመስከረም 1964

ከአብዮታዊው እዝ የበላይ ምክር ቤት አባልነት ወጥተው በአምባሳደር ነት ወደሞስኮ ከመላካቸው በፊት ነበር ።

የቀሩት የሳዳም ተወዳዳሪዎች በከዛር የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ እንዳካሄዱ ተሳቦባቸው ጠፍተዋል ። ለረጅም ጊዜ የባዓዝ ፓርቲ አባል የነበሩት ሺዓ ጄኔራል— ናድሂም ከዛር በ1961 የአገር ውስጥ ደኅንነት ኃይል ሥራ አስኪያጅ ሆነው ተሹመው ነበር ። በሰኔ 23/1965 ጄኔራል ባክር ከምሥራቅ አውሮፓ ጉብኝታቸው ሲመለሱ ባግዳድ አውሮፕላን ማረፊያ ላይ እንዲገደሉ ጄኔራል ከዛር ሤራ አውጠንጥነው ነበር ። በዚያን ቀን ፣ ቀደም ብለው ፣ ጄኔራል ሃማድ ሺሃብን እና የመከላከያና የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትሩን ሳዱን ጋሀያዳን ከዛር በመያዣነት ወስደዋቸዋል ።

የባክር አውሮፕላን ሁለት ሰዓት ስለዘገየ የከዛር እቅድ ከሸፈ ። ከዚያም በመያዣነት ያሠሯቸውን ሁለቱን ሰዎች ይዘው ወደ ኢራን ድንበር ሸሹ ። ድንበሩ አጠገብ ሲደርሱ ራሳቸው ከመያዛቸው በፊት ሺሃብን ገደሉ ። ሳዳም ራሳቸው የከዛርን የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ የማክሸፍ ዘመቻ መሩ ። ሳዳም የታጠቁ ሰዎችን ሰብስበው የከዛር ደጋፊዎች ወዳሉበት ወደ ጠቅላይ የደኅንነት ድርጅት ጦር ሠፈር አመሩ። እንደደረሱም የማሠሩንና ብዙ ሰዎችን እዚያው በተገኙበት የመግደሉን ተግባር መሩ ።

ከአንድ ሳምንት በኋላ ፣ ከዛር ፣ ሰባት የደኅንነት መኰንኖችና ዓሥራ ሦስት የጦር መኰንኖች ለፍርድ ከቀረቡ በኋላ ተገደሉ ። በሚቀጥለው ቀን ሠላሳ ስድስት ሲቪሎች ለፍርድ ቀረቡ ። ከነዚህም ውስጥ ዓሥራ ሦስቱ የሞት ቅጣት ተፈረደባቸው ። በእሥራት እንዲቀጡ ከተበየነባቸው መካከል የአብዮታዊው እዝ የበላይ ምክር ቤት አባል የነበሩት አብዱል ኻሊቅ አልሳማራይ ይገኙበታል ። እርሳቸውም በእሥር ቤት ውስጥ ከ1971ዱ ስመ ጥፉ የሐምሌ የፓርቲ ስብሰባ በኋላ ሳዳም እስካስገደሏቸው ድረስ ቆይተው ነበር ። ከዛር በሚሸሹበት ወቅት አንድ ቦታ ላይ ሲደርሱ ሳማራይ መኖሪያ ቤት ውስጥ ለመደራደር ሐሳብ አቅርበው ስለነበር በተዘዋዋሪ ሳማራይን የሚሬው ተባባሪ አስመስለዋቸ ዋል ። እርሳቸው ግን ስለሚሬው የሚያውቁት አንዳችም ነገር አለመኖሩን ተናገሩ ። ብዙ ሰዎች እንደሚያምኑት ሳዳም ብርቱ ተቀናቃኞቸውን ለማስወገድ በአጋጣሚው ተጠቅመዋል ።



በእርግጥ ከከዛር የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ግብረአበሮች የተረፉት የሳዳም ተገዳዳሪዎች ሁሉ መወገድ ነበረባቸው ። በተጨማሪም ሙከራውን ለማክሸፍ ሳዳም ራሳቸው የተጫወቱት ሚና ብዙዎቹን የጦር መኰንኖች አስደንግጧቸዋል ። ከ1965 በኋላ ልክ ከአምስት ዓመት በፊት የበላይነት እንደነበረው የተነገረለት የፓርቲው ወታደራዊ አንጃም ተወገደ ። ሳዳም በአገዛዙ ውስጥ ተወዳዳሪ የሌላቸው ተደማጭ ባለሥልጣን በሆኑበት ጊዜ በሥልጣን ቁልፍ ቦታ ላይ የቀሩት የጦር መኰንን ባክር ብቻ ነበሩ ።

በሰፋት በኢራቅ ዓረብ ኅብረተሰብ ውስጥ ከተካሄደው የሥልጣን ሽሚያ ትግል በተጨማሪ ኩርዶች ሌላ አጣዳፊ ችግር ፈጠሩ ። የባዓዝ ፓርቲ ሥልጣን ከመያዙ በፊት በ1958 ጠቅላይ ሚኒስትር ባዛዝ ከኩርዶች ጋር የቋጠሩት የስምምነት ቋጠሮ እንኳ ሳይቀር መፈታት ጀመረ ። በ1961 ጸደይ የኩርዶች ጦርነት እንደገና ሙሉ ለሙሉ ተጀመረ። ብዙ ሺህ የኢራቅ ኩርዶች ካገር ተባረው ወደ ኢራን እንዲሰደዱ ተደረገ ።

የኩርዶች መሪ ሙስጠፋ ባርዛኒ በ1950 ወደ ኢራቅ ከመመለሳቸው በፊት በስደት ሞስኮ ውስጥ ዓሥራ አንድ ዓመት ኖረዋል ። ሶቪየት ኅብረት መልእክተኛ ወደሳቸው በላከች ጊዜ የኩርድ ጦርነት ለባዓዝ አገዛዝ በጣም አሰጋ ። ባርዛኒ ከኢራቅ አገዛዝ ጋር ሰላም እንዲመሠርቱ ሶቪየት ኅብረት ጠየቀች ። ሳዳም በበኩላቸው ኩርዶችን ለመርዳት የተዘጋጁ የሚያስመስል አቋም ያዙና በ1962 ራሳቸው ኩርዲስታን ድረስ በመሄድ ባርዛኒን አነጋገሩ ። ባዶ ወረቀት ግርጌ ላይ ፊርማቸውን በማስቀመጥ የኩርዱ መሪ ባርዛኒ የሚፈልጉትን ስምምነት እንዲሞሉ ሳዳም ጠየቋቸው ። ይህም ውይይታቸው የኩርዶችን በራስ አደርነት (አቶኖሚ) የሚዘረዝር ባለ ዓሥራ አምስት ነጥብ ስምምነት አስገኘ ። ነገር ግን ከዚያ በኋላ ሳዳም ያንፀባረቁት ጠባይ ስምምነቱን ለማክበር ፍላጐት እንደሌላቸው አሳየ ። ስምምነቱን ተግባራዊ ለማድረግ ደርዝ ያለው ውይይት ማካሄድ ተሳናቸው ። ይህም አልበቃ ብሏቸው ከዚያ በኋላ ባጭር ጊዜ ውስጥ የባርዛኒን ልጅ—ኢድሪስን ለመግደል ሞከሩ ። በመስከረም 1963 ባግዳድ ውስጥ የኢድሪስ መኪና ፣ በአቶማቲክ መሣሪያ፣ ጥይት ተርከፈከፈባት ።

ሳዳም ለባርዛኒም አልተመለሱ ። ከአንድ ዓመት በኋላ እርሳቸው

ንም ለመግደል ሞከሩ ። በግዳም ትእዛዝ በከባር ጠያቂነት የሃይማኖት መሪ ሼኮች ሁድን ባርዛኒን እንጋግር መልስ ይዞ ወደ ፕሬዚዳንቱ ተመለሱ። ከባር ግን እንደገና እንዲመለሱና ባርዛኒን እንዲያነጋግሩ ማድም ጠየቋቸው ። ሁለት የድምፅ መቅረጫ የሚመስል መሣሪያ ሰጧቸውና ባርዛኒ ሳያዩአቸው እንዲከፍቱትና ድምፃቸውን በደንብ ቀርጸው እንዲያመጡ አዘዟቸው ። ሲመጣም ለመስጣት እንደሚፈልጉ ነግረው ወደ ሰሜን ኢራቅ ላኳቸው ። ከባር ወደ ባርዛኒ ዋና ሠፈር—ሐጂ ኡምራን እንደደረሱ ከአርጎቻቸው ጋር ተቀመጡ ። አንደኛው ሼክ ሻይ ሲቀርብ ቁልፉን ለመጫንና ድምፃቸውን ለመቅረጽ ከባር በስውት መመሪያ መሠረት በሁኔታው ለመጠቀም ፈለጉ ። ይህ ሻይ አቅራቢ ከባርዛኒ አይታ ጋርዶቻቸው ነበረና ቁልፉን ሲጫኑት ግን የድምጽ መቅረጫ ቴፕ ነው የተባለው ነገር ፈንዳና የሼኩንና የሻይ አቅራቢውን ሕይወት አጠፋ ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ባርዛኒ ከግዳም ጋር የሚነጋገሩበት አንዳችም ነገር እንደማይኖር ወሰኑ ።

ምንም እንኳ በ1955 ባዓዝ ፓርቲ ከአሜሪካ ጋር ግንኙነቱን በጥሩ ወዳጅነት ቢመራም ወይንም በሌላ በኩል የመለስተኛ የውጭ መመሪያ ቢከተልም ፓርቲው በሁለተኛው ዙር በጣም የተለየ ጠባይ ማሳየት ጀመረ ። እንደ ሁኔታው ከእርእዮተ ዓለም አንጻር ከሚደረገው ንግግር በስተጀርባ ፣ በተግባር የተገለጸ ነገር ቢኖርም ባይኖርም ፣ ከብዙ አቅጣጫ እንደታየው የባዓዝ ፓርቲ የውጭ መመሪያ በጣም ተለወጠ ።

ከዓረብ አገሮች መካከል ከእሥራኤል ጋር ፊት ለፊት ተቀምጦ ለስምምነት መደራደር ከምር አሻፈረኝ ያለች አገር ኢራቅ ብቻ ነበረች ። የባግዳድ አክራሪነት በጣም ብርቱ ከመሆኑ የተነሣ ከዓረቡ ዓለም ውስጥ በዕውነት ተገልላ ነበር ። የአገር ውስጥ ቁጥጥሩን መሠረት ለማስያዝ ትኩረቱን በሱ ላይ ብቻ ማሳረፍ ስለሚፈልግ ምናልባት አገዛዙ መገለሉን በሐቅ ሳይፈልገው አልቀረም ።

ከ1960 በኋላ በይበልጥ ተራማጅ እንጂ የሆነውን የፍልስጥኤም ነፃ አውጪ ድርጅት ኢራቅ የፍልስጥኤምን ሽብር ከፍ በማድረግ ከሌሎች የዓረብ አገሮች በላይ ንቁ ተካፋይ በመሆን እጁን አስገብታለች ። እንደ እሥራኤላዊው ጋዜጠኛ ዮሲ ሚልማን አባባል ከሽብር መሪዎች መካከል በስሙ ጥፋቱ ይበልጥ የታወቀው አቡ ኒዳል በመጀመሪያ ጊዜ የባዓዝ ፓርቲ ደጋፊ ነበር ። በ1960ዎቹ መጀመሪያ ድርጅቱን ማቋቋም



በጀመረበት ጊዜ ከኢራቅ የስለላ ድርጅት እርዳታ አግኝቷል ። እንዲሁም ከባግዳድ ጋር ዓሥር ዓመት ሙሉ በቅርብ ወዳጅነት ተሳሥሮ ቆይቷል ። በዚያን ጊዜ የአቡ ኒዳል ዒላማ ሌሎች ዓረቦች ነበሩ ። በተለይም ከባዓዝ ጋርም ክርክር የነበረው የያሲር አራፋት ድርጅት ፋታህ ነበር ።

ለኢራቅ ባዓዝ ፓርቲ አክራሪነት ምክንያት አንዱ ፣ በከፊል ኢራቅ ከእሥራኤል ጋር ስለማትዋሰንና የራሷ አቋም ብዙ ወጭ የማይጠይቃት በመሆኑ ነው ። ይሁንና በመስከረም 1963 ዮርዳኖስንና የፍልስጥኤምን ነፃ አውጪ ድርጅት ደም ካፋሰሳቸው ግጭት ጊዜ ጀምሮ የኢራቅ ማምረር የዮርዳኖስን አገዛዝ ምርጫ አሳጣው ። ከ1959ኙ ጦርነት ጀምሮ ኢራቅ ዮርዳኖስ ውስጥ ወታደሮች አሥፍራለች ። ነገር ግን በንጉሥ ሑሴንና በፍልስጥኤም ነፃ አውጪ ድርጅት መካከል የነበረው ውጥረት በመፈንዳት ወደ ግልጽ ጦርነት ተለወጠ ። በዚህም ጊዜ ኢራቅ በይፋ ከፍልስጥኤም ነፃ አውጪ ድርጅት ጋር ወገነች ። አሜሪካ የኢራቅ ወታደሮች ፍልስጥኤማውያንን በመርዳት የኃይል ሚዛኑን የሚለውጡት መስሎ ስለታያት ስጋት ነበር ። ሆኖም ይፋ አቋሟ ፍልስጥኤማውያንን ለመርዳት ቢሆንም ዮርዳኖስ ውስጥ ሠፍረው የነበሩት የኢራቅ ወታደሮች ግጭቱ ተጀምሮ እስከለቀ ድረስ በጦር ሠፈራቸው ውስጥ ተቀመጡ ።

የባዓዝ ፓርቲ አመራር ለፍልስጥኤማውያን የገባውን ቃል ባለማክበር ፣ በአባባሉ ተወቀሰ ። በ1965 የዓረብና የእሥራኤል ጦርነት በተጀመረ ጊዜ ፣ ሣዳም የጦር ኃይላቸው በ1962 ሳይቆጋ የቀረበትን ጥርጣሬ ለማስወገድ ፈለጉ ። ስለዚህ ባክር ቢያመነቱም ሣዳም ወደ ጐላን ተራተር ሄዶ የሚቆጋ ብዙ የኢራቅ ክፍለ ጦር ለመላክ ወሰኑ ። ግብጽና ሶርያ ከእሥራኤል ጋር የተኩስ አቁም ስምምነት ለማድረግ መወሰናቸውን ሣዳም አውግዘው ተኩስ አቁሙ ድንገት ቢጣስ ፣ ሶርያ ለአደጋው እንድትጋለጥ ብቻዋን በመተው እዚያ ያሠፈሯቸውን ወታደሮቻቸውን ወዲያውኑ አስወጡ ። ምንም እንኳ ተራማጅ አቋም ቢይዙም ሣዳምን በይበልጥ ያሳሰባቸው መሠረታዊ ጉዳይ ሌላ ነበር ። ይህም የኢራቅ ጦር ኃይሎች ስለአገራቸው ጥቅም መንግሥታቸው የሰጠውን ሐሳብ በሚቃረን መንገድ ተገደው ሊዋጉ በሚችሉበት ሁኔታ ሶርያ ውስጥ መቆየት የለባቸውም የሚለው ነገር ነው ። በእሥራኤልና በዓረብ አገሮች መካከል ወዲያው ድርድር እንደተጀመረ ሣዳም ስምምነቱን ነቀፉ ። ይህን ያደረጉበት ዋና ዓላማ ተቀናቃኞቻቸውን የሶርያን ፕሬዚዳንት ሀፌዝ

እልዓሳድን የማባረር ተሰፋ ነበር ። ሶርያና ኢራቅ ሳያቋርጡ እርስ በርሳቸው ለአምስት ዓመት የፕሮፓጋንዳ ጦርነት ቀጠሉ ።

በባዓዝ አገዛዝ የመጀመሪያ ዓመታት ኢራቅ ከሞስኮ ጋር የቅርብ ወዳጅነት በመፍጠር ከጕኗ ተስፋ ነበር ። የባዓዝ ፓርቲ መፈንቅለ መንግሥት ባካሄደ በአንድ ወሩ በነሐሴ 1960 ሶቪየት ኅብረት ቼኮዝሎቫኪያን ስትወር ኢራቅ ድርጊቱን ደገፋለች ። ፊበ ማር እንደገለጸው ኢራቅ ሶቪየት ኅብረትን በመደገፍ ከጕኗ የተሰለፈችበት ምክንያት በአብዛኛው ኢራቅ የውስጥ ችግር ስለነበራት ነው ።

በየካቲት 1964 ሣዳም ሞስኮን ከጐበኙ ሁለት ወር በኋላ ሁለቱም አገሮች "የወዳጅነትና የትብብር ውል" ተፈራረሙ ። በዚህም ውል መሠረት ባዓዞች የውጭ ጠላቶቻቸውን ለመከላከልና የውስጥ ችግሮቻቸውን ለማቃለል የሚረዳቸው ትንሽ ድጋፍ አግኝተዋል ። ከዚህም በላይ ተቀናቃኞቻቸው የኢራቅ ኮሙኒስት ፓርቲ አደገኛ እንዳይሆንባቸው ውሉ ለባዓዞች ተጨማሪ ዋስትና ነበር ። በኢራቅ ኮሙኒስቶችን የሚጨምር ብሔራዊ ተራማጅ ግንባር እንዲፈጠር ሶቪየቶች ገፋፉ ። ነገር ግን ከሁሉም በፊት ኮሙኒስቶች በባዓዞች እጅ ስለተሰቃዩ እንደዚህ ወዳለ ስምምነት ከመግባት እንደሚታቀቡ ግልጽ ነበር ። ሆኖም ከሞስኮ ብዙ ግፊት ከተደረገ በኋላ ተስማሙና በ1966 ግንባሩ ተመሠረተ ። የኢራቅ ኮሙኒስቶች ምናልባት የመሰላቸውን (ደመነፍሳቸው የነገራቸውን) ማመን ነበረባቸው ። እንደፈሩትም በ1970 አገዛዙ እንደገና በፓርቲው ላይ ጭካኔ የተመላበት እርምጃ ወስዶበታል ።

የወዳጅነቱ ውል በተጨማሪ ነዳጅ ዘይትን በሚመለከት ኢራቅ ድፍረት የበዛበት እቋም እንድትይዝ ፈቀደላት ። የኢራቅን የቢንዚን ኩባንያ በሰኔ 1964 ሣዳም ብሔራዊ ንብረት አድርገው ወረሱት ። ይሁን እንጂ ብሔራዊ ንብረት እንዲሆን መውረሱ ሌሎች የባሕረ ሰላጤው ነዳጅ ዘይት አምራች አገሮች ከነዳጅ ኩባንያዎች ጋር በመደራደር ከሚያገኙት የበለጠ ለኢራቅም ጥቅም አላስገኘላትም ። እንደ ዕውነቱ ከሆነ ኢራቅን በርካታ ገቢ ቀንሶባታል ። በምዕራባውያን የነዳጅ ዘይት ኩባንያዎች መሪነት የኢራቅ ነዳጅ ዓለም አቀፍ ማዕቀብ ስለተጣለበት ገቢዋ ሃያ አምስት በመቶ ዝቅ አለ ። እንዲሁም ብዙ ገበያ አጣች ። ባግዳድ በአንድ ጊዜ ወጪዋን ለመቀነስ ብትገደድም የነዳጅ ዘይት ምርትን ብሔራዊ ሀብት ለማድረግ መውረሱን ባዓዝን የማይፈራ ፓርቲና



የኢምፔሪያሊስት ዋናፖሊስት ኃይሎችን በጀግንነት የሚጋፈጥ አስመሰሎ ለማቅረብ አገልግሏል ።

ነገር ግን የሶቪየት ኅብረትና የኢራቅ ውል በሣዳም ላይ ሌላ ችግር አስከተለ ። በኩርዲስታን ውስጥ በተዘዋዋሪ መንገድ ኢራቅን በማወክ ዕቅድ ላይ ፣ አሜሪካና ኢራንን እንዲስማሙ አደረገ ። እንደዚህ ባለ ዕቅድ ላይ ተካፋይ ለመሆን ባርዛኒ ፈቃደኛ ነበሩ ። ነገር ግን ፈቃኛ የሚሆኑት የባዓዝ አገዛዝ እስኪወድቅ ድረስ አሜሪካ ያለማቋረጥ እንደምትረዳቸው ዘርዘር ዋስትና ካገኙ በኋላ ብቻ እንደሆን ነበር ። ኩርዲስታን ውስጥ በ1965 በሙሉና በ1966 መጀመሪያ ግጭቱ እየተፋፋመ ሄደ ። በመጋቢት መደበኛ ጦርነት ተጀመረ ። ሣዳም ራሳቸው ዘመቻውን በመምራት ተጀምሮ እስካበቃ ድረስ ኩርዲስታን ውስጥ የሲቪል ሰፈሮች በቦምብ ጣይ አውሮፕላኖች በብዛት እንዲደበደቡ አዘዙ ። በቦምቡ ውርጅብኝ ቃላ ዲዘህ በምትባል ከተማ ብቻ ከሁለት መቶ በላይ ሰው አለቀ ። የሆነ ሆኖ በ1966 በልግ ዘመቻው ተገታ ። የጦር ኃይሉ እየተመታ ብዙ ወታደር ስላለቀበትና ምንም ዓይነት ድል ማግኘት ስላልቻለ በመሰላቸት ለቋጥርር አስቸገረ ።

የሣዳም አገዛዝ ተጨባጩን ሁኔታና ያመቸውን መንገድ እየመረጠ ወደኋፈሰበት አብሮ መንፈስን አንፀባረቀ ። ስለሆነም የቀድሞውን የግብጽ ፕሬዚዳንት አንዋር ሳዳትንና የቀድሞውን የአልጀሪያ ፕሬዚዳንት ሁዋሪ ቡመዲንን ሽምግልና ጠይቀው ከቀድሞው የኢራን ሻህ ጋር ለመስማማት ሞከሩ ። በየካቲት 26 1967 በአልጀርስ የነዳጅ ዘይት ላኪ አገሮች መሪዎች ጉባኤ በተካሄደበት ጊዜ ተረታቸው ለፍሬ በቅቶ ሣዳምና ሻህ በድንገት ተስማሙ ። በዚህም ስምምነት መሠረት ኢራን ይገባኛል የምትለውን የሻት አልዓረብ የባሕር መተላለፊያ ቦይ ግማሽ ባለቤትነት ኢራቅ እምና ከመለሰችላቸው ፣ በለውጡ ደግሞ ሻሁ ለኢራቅ ኩርዶች የሚሰጡትን እርዳታ ለማቆም ተስማሙ ። ስምምነቱ ከመፈረሙ በፊትም ቢሆን ኢራን ወደ እርሷ የተሰደዱ ኩርዶችን ጥላቻ በማሳየት ነገር ለማስወጣት ዳርዳር ብላ ፣ በመጨረሻም ለማስወጣት ቆርጣ በመገፋፋት ላይ ነበረች ። ባርዛኒ ፣ ሳግም ላለመመለስ ኢራንን ለቀው እንደወጡ ቀሩ ። ምሬታቸውን በኋላ ሲገልጹ አሜሪካ እንደማትከዳቸው ባይተማመኑ ኖሮ የሻሁን ቃል እምነው ለመቀበል ፈጽመው እይፈልጉ እንደነበር አረጋግጠዋል ።

የአልጀርሱ ስምምነት የኢራቅን አቋም በስፋት ከመለወጥ ጋር የተያያዘ ነበር ። የኢራቅ አክራሪነት እየከሰመ ሄደ ። ግዳም እንደገመቱት የኩርዶች አመጽ ከተደመሰሰ በኋላ በአገር ውስጥ አቋማቸው በሚገባ ስለተጠበቀ ኢራቅ በዓለም ጉዳይ ተቀባይነት ያለው አቋም እንድትይዝ ሁኔታው የሚፈቅድ መስላቸው ። ከዚህም ጋር ኢራቅን ከማግለል ሌላ ፋይዳ ካልነበረው ፤ የኢራቅ ተራማጅነት አገዛዙ የአገር ውስጥ ቁጥጥሩን ማጠናከሩ ተሻለ ። የባዓዝ አክራሪነት ምንም ከዚያ ያለፈ ትርፍ አላስገኘም። ከ1967 በኋላ ግብጽን ፤ ሳዑዲ ዓረቢያንና ዮርዳኖስን ጨምሮ ኢራቅ ከብዙ የዓረብ አገሮች ጋር የነበራትን ውጥረት ማላላት ጀመረች ። ግዳም በአገራቸውና በሌሎች መሃል የነበረውን ውጥረት አርግበው የራሳቸውን ምኞት እግቡ ለማድረስ ቢጥሩ እንደሚሻላቸው በመጨረሻ ተገንዘቡ ።

ከ1965ቱ የዓረብና የእሥራኤል ጦርነት በኋላ የነዳጅ ዘይት ዋጋ በአራት እጥፍ ከጨመረና እንዲሁም ይባስ ብሎ በ1964 ኢራቅ የነዳጅ ዘይት ኩምችቷን በብሔራዊ ንብረትነት ከወረሰች በኋላ ያጣችውን ገበያ ፤ በጦርነቱ ጊዜ የዓረብ አገሮች የነዳጅ ዘይት ምርታቸውን መቀነሳቸውን ባለመደገፍ እንደገና መልሳ በማግኘቷ የግዳምን የውጭ መመሪያ ትልቅ ለውጥ አፋጠነው ። የኢራቅ መንግሥት የነዳጅ ምርቱን ከፍ አደረገ ። "የእሥራኤልን ወረራ እጥብቀው የሚደግፉ ኢምፔሪያሊስት አገሮች" ነዳጅ ዘይት እንዳይላክላቸው አጠቃላይ የነዳጅ ዘይት እገዳ እንዲደረግባቸው እያሳሰበችም እንኳን ኢራቅ ምርቷን መጨመር ቀጠለች ። ሌሎች የዓረብ አገሮች እንደማይደግፏት ኢራቅ እያወቀች ፤ እንደዚህ ያለውን አክራሪ አቋም ችክ ብላ ያዘች ። እንዲህም በማድረግ ሌሎች የዓረብ አገሮች በሥራ ላይ ያዋሉትን ቅጣት አልተቀበለችም ።

ከ1965 በኋላ ኢራቅ ነዳጅ ዘይትን በብሔራዊ ንብረትነት በመውረሷ አጋጥሟት የነበረው የገንዘብ እጥረት ተወገደ ። ኢራቅ በ1966 ከነዳጅ ዘይት ያገኘችው ገቢ ፤ በ1964 ታገኘው ከነበረው ዓሥር እጥፍ ያኽል ሆነ ። መንግሥት በርካታ ሸቀጣሸቀጥ ወደ አገር ውስጥ በማስገባት መርሀ ግብር አማካይነት የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል ገንዘብ አወጣ ። የመንግሥት የኢንዱስትሪ ወጭ በዓሥራ ሁለት እጅ ጨመረ ። ለመንግሥ የሚቀመጠው ገንዘብ በዓሥራ አንድ እጥፍ ፤ ለሕንፃና ለቤት ሥራ



የሚውለውም በዘጠኝ እጥፍ አደገ ። ድንገተኛው እድል ለአገዛዙ የሰጠው ከሁሉም የበለጠ ጥቅም ፤ ሕዝቡ ልባዊ ድጋፉን እንኳ ባይሰጠው፤ ቢያንስ የባዓዝን አገዛዝ ለመታገስ የሚያስችል ተስፋ ነው ።

አዲሱ የኢራቅ ሀብት ከዚህ ሌላ ከልዕለ ኃያላን አገሮች ጋር ያላትን ግንኙነት ለውጦታል ። በሶቪየት እርዳታ ከመተማመን ይልቅ ከፍተኛ ጥራት ያለውን የምዕራቡን የቴክኖሎጂ ውጤት በመፈለግ ባግዳድ ከሞስኮ ጥገኝነት እየተላቀቀችና ነፃ እየሆነች ሄደች ። ከ1969ኙ የዓረብና የእሥራኤል ጦርነት ወዲህ የኢራቅና የአሜሪካ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ተቋርጦ ቢቆይም የኢኮኖሚ ግንኙነቱ እያደገ ሄደ ። በ1972 ኢራቅ ስባት መቶ ሚሊዮን ዶላር የሚያወጣ ሸቀጣሸቀጥ ከአሜሪካ አስመጥታለች ። በባግዳድ የቤልጂግ ኤምባሲ ውስጥ የአሜሪካን ጉዳይ ይከታተል የነበረው ክፍል የዚያኑ ያኽል እየተስፋፋ ሄደ ፤ ነገር ግን ያንጊዜ ኢራቅ ከዋሽንግተን ጋር የነበራትን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት መልሳ ለማደስ ፍላጐት አልነበራትም ። ከሞስኮ ጋር የነበራትን የወዳጅነት ግንኙነት እንኳ ወደጠላትነት እየለወጠችው ብትሄድም ከአሜሪካ ጋር የነበራትን ግንኙነት እንድታድስ ከካርተር አስተዳደር ሁለት ጊዜ የቀረበላትን ጥያቄ አልተቀበለችውም ። በእርግጥ በ1971 ሶቪየት ኅብረት መንግሥቱን በመደገፍ ተቃዋሚ ኃይሎችን ለመዋጋት አፍጋኒስታን በገባች ጊዜ ከመላው ዓረብ ሀገሮች መካከል ኢራቅ ድርጊቱን በይበልጥ በማውገዝ የመኸች አገር ናት ።

ከአልጀርስ ስምምነት በኋላ ፤ የግዳም ምኞት ከኢራቅ የውጭ መመሪያ መለወጥ በስተጀርባ ሞስኮን በመተቸት ፤ ከዋሽንግተንም በመራቅ ማድፈጥ ነበር ። ይህም ድብቅ ዓላማቸው ፤ መጀመሪያ ግልጽ የሆነው ከመስከረም 1971 ካምፕ ዴቪድ ስምምነት በኋላ በኢራቅ አስተባባሪነት ሌላው የዓረብ ዓለም ግብጽን ባገለላት ጊዜ ነው ። ግዳም በወቅቱ በመካከለኛው ምሥራቅ መድረክ ላይ ታላቅ ሚና መጫወት ቢፈልጉም እስከዚያ ድረስ ኢራቅ ከማንኛውም ጋር መተሳሰር እንዳልነበረባት ተሰምቷቸዋል ።

## ፮

# የማያባራ ጦርነት

በ1971 በክረምት ወቅት ሣዳም ሑሴን የኢራቅን ፕሬዚዳንትነት ሥልጣን ሲይዙ ፣ በጋለ ፍላጐትም ይሁን በፍራቻ ተደፋፍረው አገራቸውን በአዲስ መንገድ ለመገንባት ተነሡ ። የጋለ ፍላጐታቸው ኢራቅን በፋርስ ባሕረ ሰላጤና በዓረብ ዓለም የበላይነት ያላት ኃያል አገር ለማድረግ ነበር ። ፍራቻቸው ደግሞ ለዓሥራ አምስት ረጅም ዓመታት ፣ በስደት ከኖሩ በኋላ ፣ በጥር 24/1971 በአሸናፊነት ወደኢራን በተመለሱት በአያቶላ ኾሚኒ ተስታሽና በቃላት ያሸበረቀ ዲስኩር ፣ አብዛኛው የኢራቅ ሺዓዎች ለአመጽ እንዳይነሣሡ ነበር ።

የኢራን ተለዋዋጭ ፖለቲካ ፣ በኢራቅና በአጠቃላይ በአካባቢው አገሮች ላይ ወሳኝ ተጽእኖ አለው ። የኢራንን የመጀመሪያዎቹን ሁለት አብዮታዊ መንግሥታት የመሩት ከሃይማኖት የተገለሉ መሪዎች ነበሩ ። ነገር ግን ከሃይማኖት የተገለሉት የኢራን መንግሥታት ከጐረቤት አገሮች ጋር የተረጋጋ ግንኙነት ይፈልጉ ነበር ። ይሁን እንጂ ከመነሻቸው ጀምረው ከአክራሪ የሃይማኖት መሪዎች ጋር በማያቋርጥ የሥልጣን ትግል የተጠመዱ ነበሩ ። እንዲሁም በባሕረ ሰላጤው አካባቢ አገሮች ውስጥ በመጐዳት ላይ ባለው ሺዓ ኅብረተሰብ መብት በመታገል የኢራንን የእስልምና አብዮት ወደሌሎቹ አገሮች ለማዛመት በኾሚኒ አካባቢ ያሉ ወገኖች በተድፊያ ማሳሰብ ጀመሩ ።

በኢራን ባለሥልጣኖች መካከል መከፋፈል ስለተፈጠረ በቴህራንና በባግዳድ መካከል የፕሮፓጋንዳ ጦርነት ተስፋፋ ። በሰኔ 1971 ኾሚኒ ወደአገራቸው በድል በተመለሱ በአራት ወሩ የሁለቱም አገሮች ሱኒና ሺዓት እስላሞች አንዱ በሌላው ድንበር ውስጥ በሃይማኖት በመከፋፈል ጥል ስለእንግግ ውጥረቱ ተባብሶ ወደድንበር ግጭት ደረጃ ከፍ አለ ። ባግዳድ የኢራንን የፋርስ ዘር ያልሆኑ ተገንጣይ ቡድኖች መርዳት



ጀመረች ። ኢራን በበኩሏ ለሰሜን ኢራቅ የኩርድ አመጸኞች ገንዘብና የጦር መሣሪያ ላከች ። እንዲሁም ኢራቅ በነዳጅ ዘይት ሀብታምና በአብዛኛው ዓረብ ለሆኑት የኢራን የኩዚስታን ክልል ነዋሪዎች እርዳታ መስጠት ቀጠለች ። ከ1916 በፊት ኩዚስታን የራሷ የዓረብ ምስፍና አስተዳደር ነበራት ። ሣዳም ይህችን ክፍለ ክልል ቀድሞ ወደነበረችበት ሁኔታ ለመመለስ ጥረታቸውን በመጀመር የባዓዝን ፓርቲ ሕዋሳት ማንቀሳቀስና ለዚሁም ተግባር ኩዚስታን ውስጥ የሚገኙትን የዓረብ ሺዓ መሪዎች ወንድ ልጆች መለመሉ ። ሣዳም ኾራምሻር ውስጥ በሚገኘው የኢራቅ ቆንሲል በኩል ገንዘብና ጦር መሣሪያ ላኩላቸው ። ኾራምሻር በደቡብ ኩዚስታን በሻት አልዓረብ የባሕር መተላለፊያ ቦይ ላይ የኢራን ዋናና ትልቅ የወደብ ከተማ ናት ። የኢራን የሃይማኖት መሪዎች በፊናቸው ባንድ በኩል የሰሜን ኢራቅን ኩርዶች አመጽ እየደገፉ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የኢራቅ ሺዓዎች መንግሥታቸውን እንዲገረስሱ አሳሰቡ ።

ጥቅምት 25/1972 በኾሚኒ ደጋፊነት ቴህራን ውስጥ አክራሪዎች የአሜሪካን ኤምባሲ በመያዝ ባልደረቦቹን በመያዣነት አገቷቸው ። የኤምባሲው መያዝ ፣ የኢራንን መንግሥት መሪዎች ሥራቸውን በፈቃዳቸው መልቀቅ አስከተለና በፈረንሳይ የተማሩት ምሁር – ማርክሲስት ኢኮኖሚስቱ አቦልሀሳን ባኒሳድር ፕሬዚዳንት ሆኑ ። በተመሳሳይ ጊዜ የሃይማኖት መሪዎቹ አክራሪ እርምጃ እንዲወስድ በሚያደርጉት ቅስቀሳ ሕጋዊውን መንግሥት ማዳከም ቀጠሉ ።

የባሕረ ሰላጤው ዓረብ አገሮች ሁሉ ኢራን ዛቻ እንደሠነዘረችባቸው ተሰማቸው ። ሣዳም የእነዚህን የተቃዋሚ ዓረብ አገሮች የመሪነትና የበላይ ጠባቂነት ወንበር ኢራቅ እንድትይዝ ለማድረግ በኢራን ፖለቲካዊና ርእዮተ ዓለማዊ ዛቻ መጠቀም ስለፈለጉ ይህንኑ የጠባቂነቱን ሚና ለመያዝ ደካማ አሚሮችን ጠየቁ ። ይሁንና የባሕረ ሰላጤው ዓረብ አገሮች የሳቸውን "ጠባቂነት" ከቶም አልፈለጉት ። በባሕረ ሰላጤው ውስጥ ለባግዳድ አዲስ ሚና ለመፍጠር ያደርጉት ጥረት ከአሜሪካ ጋር ወደመወዳደሩ ገፋፋቸው ። በታኅሣሥ 1972 ሶቪየት ኅብረት የአፍጋኒስታንን መንግሥት በመደገፍ ተቀናቃኞችን ለመመከት ወደዚያ ከገባች በኋላ ሳዑዲ ዓረቢያንና የባሕረ ሰላጤውን አገሮች አሜሪካ ከወራሪ እንደምትከላከል የወቅቱ ፕሬዚዳንት ጂሚ ካርተር አስታወቁ ። ይህም አዲስ መመሪያ "የካርተር ዶክትሪን" ተሰኘ ። ከሁለት ሳምንት በኋላ ሣዳም

ሑሴን ተመሳሳይ ድርጊት እንደሚፈጽሙ ገለጹ ። በየካቲት 1/1955 በባዓዞች መፈንቅለ መንግሥት ዓሥራ ሰባተኛ ዓመት መታሰቢያ በዓል ላይ ሣዳም "የመላ ዓረብ ቻርተር"ን "የሑሴን ዶክትሪን" ብለው ስያሜውን መለወጣቸውን አስታወቁ ። ቻርተሩ የዓረብ አገሮች የጋራ መከላከያ ድርጅት እንዲያቋቁሙ አሳሰበ ። በባሕረ ሰላጤው ውስጥ ደግሞ የማንኛቸውንም የውጪ ኃይል መኖር ተቃወመ ። በተጨማሪም "ማንኛውም የዓረብ አገር በሌላው የዓረብ አገር ላይ የጦር ኃይል እንዳያዘምት" አገደ ።

በሚያዝያ 1972 በተከታታይ የተፈጸሙት ድርጊቶች የሣዳም ሑሴንን ዶክትሪን በተግባር ላይ ለማዋል እንዲወስኑ አደረጋቸው ። በሚያዝያ 1972 አብዮታዊው የሺዓ እስላም ፓርቲ — አልዳዋ በተለይ ክርስቲያኑን የኢራቅ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ጣሪቅ አዚዝን ለመግደል ሞከረ ። አዚዝ ከአደጋው በሕይወት ተረፉ ። ከእርሳቸው ጋር የነበሩ ሰዎች ግን ተገደሉ ። ከአራት ቀን በኋላ በመጀመሪያው ጥቃት ሰለባዎች የቀብር ሥነ ሥርዓት ላይ አልዳዋ ሌላ ጥቃት ሠነዘረ ።

ሣዳም ያለርህራሄ አጸፋውን መለሱ ። የአልዳዋ ፓርቲ አባል ሆኖ የተገኘ በሞት እንዲቀጣ ተወሰነ ። ሣዳም ዓሥራ አምስት ሺ ሺዓ ኩርዶችን ከገዛ አገራቸው አባረው ለስደት ዳረጉ ። ከዚህም በተጨማሪ ከኢራቅ ታላላቅ ከተሞች በመካከለኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የነበሩ ሺዓዎችን በብዛት ከገዛ ራሳቸው አገር አሳደው ማስወጣት ጀመሩ ። በክረምቱ ላይ ሠላሳ አምስት ሺ ያኽል ዓረብ ሺዓዎች ከአናት አገራቸው ከኢራቅ ውጪ ተሰደዱ ። ይብሱኑ ይህ የመጀመሪያው ብቻ መሆኑ ተረጋገጠ ።

አያቶላህ መሐመድ ባቅር አልሳድር የታወቁ የኢራቅ ዓረብ ሺዓ የሃይማኖት መሪ ናቸው ። የኾሚኒ ደጋፊም ነበሩ ። ሳድርንና እኅታቸው አሚና ቢንተልሁዳን ሣዳም አሳሥረው ወደ ባግዳድ በማስወሰድ በወቅቱ የደኅንነት ዋና ክፍል - ሙኽባራት ኃላፊ በራሳቸው በሣዳም ወንድም በባርዛን ኢብራሒም እጅ በጭካኔ እንዲሰቃዩ ተደረገ ። ቢንተልሁዳ፣ በወንድማቸው ፊት ተደበደቡ ። ወንድማቸውንም በተራቸው በእኅታቸው ፊት ጢማቸውን በእሳት ለብልቦ በማቃጠልና በጭንቅላታቸው ምስማር በመቸንከር ተገደሉ ። ሬሳቸው ናጃፍ ለሚገኘው ቤተሰባቸው የሬሳ ሣጥናቸው ሳይከፈት እንዲቀበር በማስጠንቀቂያ ተሰጠ ። ነገር ግን ሕይወቱን ለእስልምና የሰጠ ሰው የሚቀበረው በመከፈኛ ጨርቅ ብቻ



እንጂ በሳጥን ስላልሆነ በእስልምና ሕግ መሠረት ሳጥኑ መከፈት ስለነበረበት ተከፍቶ የደረሰባቸው ስቃይ በማስረጃ ተጋለጠ ።

በ1972 ፀደይ ወቅት በኾሚኒ የሚመሩት ኃይላቸው እየጨመረ የሄደው የእስላም አብዮታውያን ጠብ አጫሪነት ቢባባስም አገርን የወል ፣ ሃማኖትን የግል ያደረገው የኢራን ዓለማዊ መንግሥት በእርሱና በኢራቅ መኻል የነበረውን ውጥረት ለማርገብ ተስፋ አድርጐ ነበር ። ይህንንም ሐሳብ ዳር ለማድረስ በሚያዝያ 1972 ማገባደጃ ላይ የኢራን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የባሕረ ሰላጤውን የሼኽ መንግሥታት ግዛቶች ጐበኙ ። ነገር ግን ጉብኝታቸውን ለመጀመር ኩዌት ሲገቡ የኢራቅ ቅጥር ነፍሰገዳዮች ሊገድሏቸው ሞከሩ ፣ ሣዳም ጦርነት ለማንሣት ወሰኑዋል ።

የኢራኑ ሻህ ከሥልጣን ሲሳደዱ ከእርሳቸው ጋር የተሰደዱ ጀኔራሎችና ፖለቲከኞች በባግዳድ ተሰበሰቡ ። ኢራን በቀላሉ ልትጠቃ የምትችል አገር እንደሆነችም ለሣዳም ነገሯቸው ። እንዲያውም ብዙዎቹ የኢራን አየር ኃይል አብራሪዎች ለመብረር ሲፈቀድላቸው ወዲያውኑ በመክዳት አውሮፕላኖቹን ይዘው ወደኢራቅ እንደሚሰደዱ አበሠሯቸው። በተለይ ኩዚስታን ውስጥ የነበሩት የኢራን ብረት ለበስ ክፍለ ጦሮች ፈጽመው መደናገራቸውንም ገለጹላቸው ። እንደ ፖለቲካዊ ፖሊስ ሆኖ የሚሠራን ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የጦር ኃይሉን ተግባርና ጦር መሣሪያ ለመውሰድ በመሞከር ላይ በሚገኝ "አብዮታዊ ዘብ" በተባለ አዲስ ሕዝባዊ ሠራዊት ላይ የጦር ኃይሉ የነበረውን ቅሬታ ተናገሩ ። የተመረጡ ዒላማዎችን ከአየር በቦምብ በመደብደብና ለዚሁም ድጋፍ ሰጭ በሰፋት ብረት ለበስ ክፍለ ጦር ኢራንን ማጥቃት ቢጀምር የጦር ኃይሏን ለመደምሰስ በቂ እንደሆነና አብዮታዊውን መንግሥት እንኳ ሳይቀር ሊያስገረስሰው እንደሚችል ፣ የኢራንን እስላም አብዮት ሸሽተው የመጡት የዘውድ ደጋፊ ስደተኞች ሣዳምን አሳመኗቸው ። በተጨማሪም ኢራን በተለይ በቴህራን የአሜሪካን ኤምባሲ በመያዟ የዓለም ኅብረተሰብ ስለጠላት በመደሰት ፣ ሣዳም ፣ እነሱም በዛ ፣ ሐሳቡን ተቀበሉት ። በዚህ ዓይነት ኢራቅ ኢራንን ብታጠቃ በዓለም አከባቢ አንዳችም ጠንካራ ተቃውሞ የማያስነሣ ወይም በጣም የሚከፋው እንኳ የማይኖር መስሎ ታያቸው ።

በሁለት ወይም በሦስት ሳምንት ውስጥ ሣዳም በፍጥነትና በቀላሉ ኢራንን ድል እንደሚነሡ ጠብቀዋል — እንዲሁም የአሜሪካ መንግሥት

ቁልፍ የሰለላ ድርጅቶችም ገምተዋል ። የኢራቅ የጦር እቅድ ቢያንስ በከፊል በ1933 በባግዳድ ወታደራዊ ኮሌጅ ውስጥ በእንግሊዝ ወታደራዊ አሠልጣኞች በተመራና በሥራ ላይ ለነበሩ መኰንኖች በተሰጠ መልመጃ ላይ ተመሠረቶ የተነደፈ ነበር ። ሣዳም ፣ ኢራቅ ዓላማዋን ብቻዋን በቀላሉ እግቡ ማድረስ እንደምትችል በማመን ፣ ከሌሎች ዓረብ አገሮች እርዳታ አልፈለጉም ወይም አልከጀሉም ። ይህም ዓላማቸው ሦስት ነገሮችን ያጠቃልላል ። የሣዳም ዓላማቸው ቢያንስ ፣ የሻት አልዓረብን የባሕር መተላለፊያ በይ ምሥራቃዊ ዳርቻ ለመያዝና የኢራቅ ማድረግ ፣ ሁለተኛው ዓላማቸው ፣ ነዋሪዎቿ ዓረቦች የሆኑትን ኩዚስታንን ከኢራን እንድትነጠል ማነሣሣት ፣ ምናልባትም ፋርስ ያልሆኑ ጕሳዎችን አመጽ ማቀጣጠል ፣ የመጨረሻው ትልቅ ዓላማቸው ደግሞ የቴህራን መንግሥት የሚገረሰስበትን መንገድ ማመቻቸት ናቸው ። መስከረም 5/1982 ሣዳም በኢራቅ ቴሌቪዥን በመታየት የሻት አልዓረብን የባሕር መተላለፊያ በይ ግማሽ ፣ ለኢራን የለቀቁበትን የ1967ቱ የአልጀርስ ስምምነት ሰነድ ቀደደ ። ከሰባት ቀን በኋላ ፣ ወረሩ።

ሣዳም ፣ ምንም እንኳ ወታደራዊ ልምድ ባይኖራቸው ፣ ጦርነቱን ራሳቸው መሩ ። የማጥቂያውን ጊዜና የማጥቃቱን ዓላማ ራሳቸው ወሰኑ ። ወደግንባር ተድመው እዚያ ከነበረው የዘመቻ ጠቅላይ መምሪያ ወታደራዊ ዘመቻውን መሩ ። ዘወትር ከጦር ኃይሉ ጋር ያከናወኑት የነበረው ተግባር በኢራቅ ቴሌቪዥን ይሠራጭ ነበር ።

ሣዳም ፣ እሥራኤል በ1959 የስድስቱን ቀን ጦርነት ስትከፍት ያሳየችውን አስገራሚና የሠመረ እንቅስቃሴ ለመድገም ሞከሩ ። በጦርነቱ መጀመሪያ ቀን የኢራንን ዓሥር አውሮፕላን ማረፊያዎች በማጥቃት ጀመሩ ። ነገር ግን የኢራን አየር ኃይል ባለመጕዳቱ ጥቃቱ ያላንዳች ውጤት ቀረ ። የኢራን አየር ኃይል በፍጥነት ኢራቅን በመምታት አፀፋውን መለሰ ። የኢራቅ አየር መከላከያ በተራው ፈጽሞ ብቁ እንዳልሆነ ተረጋገጠ ። በዚህም ባግዳድ ከፈረንሳይ ጠንካራ የአየር መከላከያ ዘዴን ለመፈለግ ተገዳለች ።

የኢራቅ አውሮፕላኖች የኢራንን አውሮፕላን ማረፊያ ሲያጠቁ ብረት ለበስ ክፍለ ጦሯ ደግሞ የሻት አልዓረብን የባሕር መተላለፊያ በይ በመሻገር ወደ ኾራምሻር በመወርወር ታላቅ ግፊት አደረጉ ። የኢራን ጦር ኃይል ለመቋጋት ባይዘጋጅም የአካባቢው ሕዝብ ጥቃቱን በኃይል



ተቋቋመ ። በጥቅምት 14/1982 ከተማዋ ከመያዟ በፊት የአንድ ወር ያልታሰበ ከባድ ጦርነት ተካሄደ ። ከዚያም የኢራቅ ወታደሮች ዓሥራ ስድስት ኪሎ ሜትር ወደ ደቡብ ወደ አባዳን ከተማ አቅጣጫ ለመግፋት ሞከሩ ። ሆኖም ብዙ ቢያጠቁም ከተማዋን ለመያዝ አልቻሉም ።

የኢራን አገዛዝ በምንም መንገድ በአንድ ጊዜ ለመውደቅ እንዳልተቃረበ አያጠያይቅም ። የኢራቅ ማጥቃት ግን የኢራንን አብዮት ለማጠናከር በእርግጥ ብዙ ረድቷል ። በዕውነቱ ሣዳም ምንም መድረሻ አልነበራቸውም ። የኢራቅ የአባዳንን ከተማ መያዝ አለመቻል የሻት አልዓረብን ምሥራቃዊ ዳርቻ የመያዝ አነስተኛ ዓላማዋን እንኳ ከግብ ማድረስ እንዳታታት ያሳያል ። ስለዚህ የኢራቅ ጦር ኃይል የኾራምሻር ይዞታውን እንዳጠናከረ ወዲያውኑ ሰባ ሁለት ኪሎ ሜትር ብቻ ወደ ኢራን ዘልቆ ከመግባቱ የመከላከያ ወረዳውን ምሽግ መቆፈር ጀመረ ። ግጭቱን በረጅሙ ወደተቆፈረ የምሽግ ቦይና ወደ አፈር ዲብ እርድ ጦርነት ለውጦት ዕርፍ ! ሆነ ።

ጦርነቱ እየተራዘመ ሲሄድ ሣዳም የኢራቅን ሦስት እጥፍ ያኽል ስፋት ያለው መሬት የያዘን ጠላት ለማንበርከክ ሲሞክሩ ጥልቅ ስትራቴጂ ማለት በዕውነት ምን ማለት እንደሆነ መማር ጀመሩ ። የኢራቅ አየር ኃይል ኩዚስታን ውስጥ መጣሪያ ለመጫን ከማረፉ በስተቀር ታላላቅ ዒላማዎችን ለመምታት ብዙ መቶ ኪሎ ሜትር ወደ ኢራን ዘልቆ መግባት አለበት ። የኢራን አየር ኃይል ግን ኢራቅ ወስጥ ዋና ዋና ዒላማዎችን ለመምታት ከ160 ኪሎ ሜትር በታች ይጓዛል ። ገና ስድስት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ፣ "የኛ ጠላት መልክአምድር ነው ፣" በማለት ሣዳም በአደባባይ ተናገሩ ።

ኢራን ከሁሉም በላይ በፋርስ ባሕረሰላጤና በሕንድ ውቅያኖስ ብዙ ሺ ኪሎ ሜትር ርዝማኔ ያለው የባሕር ጠረፍ አላት ። ኢራቅ ግን በመሠረቱ በየብስ የተከበበች አገር ነች ። አንድ ጊዜ በጦርነቱ መጀመሪያ ላይ የባሕር መውጫና መግቢያ በሯ ተቋረጠ ። በመጀመሪያዎቹ የጦርነት ቀናት የንግድ መርከቧን አሰናከለ ። ይህም ከጦርነቱ ፍርስራሽ ፣ ስብርባሪና ፍንጣሪ ጋር ሻት አልዓረብን መርከብ እንዳያስተላልፍ አደረገው ።

የኢራቅ ትንንሽ የባሕር ኃይል መርከቦች በኢራቅና በኩዌት መካከል እንደደንበር በምታገለግለው የኮር አብዱላሂ ጠባብ የባሕር

መተላለፊያ ቦይ ተደበቁ ። የኢራቁ የኡም ቃስርም ወታደራዊ ወደብ በኮር አብዱላሂ መተላለፊያ ቦይ ላይ ትገኛለች ። ወደ ሰፊው ባሕር ኢራቅን የሚያስወጣት የኩዌት የባሕር ዳርቻ ነበር ። ነገር ግን የኢራንን ቁጣ በመፍራት ኢራቅ የባሕር መተላለፊያውን ቦይ በመጠቀም ወደ ደቡብ በማምራት በኩዌት ባሕር ዘርፍ ላይ ባሉት በዎርባና በቡቢያን ደሴቶች መኻል በማለፍ ወደ አውላላው ባሕር—ወቅያኖስ እንዳትደርስ ኩዌት አልፈቀደችላትም ። የኢራቅ ወደብና የባሕር ጠረፍ በቂ እንዳል ሆነ በሚገባ ተገልጿል ። ከዚህ ሌላ የኢራቅ የባሕር መውጫና መግቢያ በር ችግር አጠቃላይ የበላይነት ካለው የኢራን የባሕር ኃይል ጋር ቢስተያይ እጥፍ ድርብ እንደተበደለች ይስተዋላል ።

እንደዚህ ባለሁኔታ ኢራቅ የነዳጅ ዘይቷን ወደ ውጭ ለመላክ መተማመኛዋ የቧምቧ መሥመር ይሆናል ። ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት ቱርክን አቋርጦ የሚያልፍ አንድ ፣ ሶርያን የሚያቋርጥ ደግሞ ሌላ አንድ ፣ የነዳጅ ዘይት ቧምቧ መሥመር ነበራት ። ቢሆንም እነዚህ ቧምቧዎች በቂ እንዳልሆኑ ወዲያውኑ ታወቀና ኢራቅ ከኢራን ጋር ጦርነት በማካሄድ ላይ እያለች ቱርክንና ሳዑዲ ዓረቢያን አቋርጦ የሚያልፍ ሦስተኛና አራተኛ መሥመር ዘረጋች ። ኢራቅ በተጨማሪ ወደ አገር ውስጥ የምታስገባቸውን እጅግ በጣም አስፈላጊ ነገሮች በየብስ ለማጓጓዝ የሌሎች አገሮች ጥገኛ ሆነች ። ዮርዳኖስ ፣ ኩዌትና ቱርክ ዋናዎቹ የኢራቅ የጭነት ዕቃ መተላለፊያ መሥመሮች ሆኑ ። በእነዚህም አገሮች ውስጥ ብዙ ሺ የጭነት መኪና ጥገና የሚያካሄዱ ጋራዦችን የሚያቅፍ ግዙፍ የመጓጓዣ መሠረታዊ መዋቅር ተዘረጋ ። ግዳምም የኢራቅን የጦርነት ወቅት ፍላጐት የሚያሟላ በአንድ ጊዜ አራት ተሽከርካሪ ሊተላለፍበት የሚችል ዘመናዊ አውራ ጐዳና እንዲሠራ አዘዙ ። አንዱ መንገድ ከባግዳድ ተነሥቶ ወደ ደቡብ በማምራት የጦር ግንባሩን ተከትሎ እስከኩዌት ድንበር ይደርሳል ። ሌላው መንገድ ከባግዳድ በስተምሥራቅ በመነሣት ወደዮርዳኖስ ድንበር ያመራል ።

ግዳም ኢራንን ከወረሩ በኋላ ብዙ ሳይቆዩ ሶቪየት ኅብረት የጦር መሣሪያ ማቅረቧን ስላቋረጠች ፣ ኢራቅ በቀላሉ ለአደጋ መጋለጥ እንደምትችል የሚያሳስብ ሌላ ትልቅ ትምህርት አገኙ ። ጥይት ፣ ፈንጂና መለዋወጫ ዕቃ በብዛት ሶቪየት ኅብረት ላቀረበችላቸው ኃይሎች አዲስ ጦር መሣሪያ ለማግኘት ግዳም ፊታቸውን ወደ ምሥራቅ አውሮፓ ፣



ቻይናና ግብጽ አዞሩ ። አንዋር ሳዳት ከእሥራኤል ጋር የሰላም ውል በመዋዋላቸው ግብጽ ፣ በይበልጡኑ በግዳም አነሣሽነት ፣ ከዓረቡ ዓለም እንድትገለል ከተደረገችበት ሁኔታ የምትወጣበትን መንገድ ማግኘታቸው ታያቸው ። ይሁንና ኢራቅ "በካምፕ ዴቪድ ስምምነት" ላይና "በከሃዲው" ሳዳት ላይ ያላት አክራሪ ርእዮተ ዓለማዊ አቋም እንደተጠበቀ ሆኖ የጦር መሣሪያ ልውውጡ እንደ ተብቅ የንግድ ሥራ ብቻ ሆኖ መታየቱን መረጠች ። ከውጭ ለሚቀርበው እጅግ በጣም አስፈላጊ ወታደራዊ ዕቃ እጥረት መጋለጥን ለማቃለል በጦርነቱ ጊዜ ኢራቅ የራሷን የአገር ውስጥ የጦር መሣሪያ ለመፈብረክ ኢንዱስትሪ አስፋፋች ።

ፖለቲካዊና ወታደራዊ ስሜት የተቀላቀለበት ሌላ ምክንያት በተደራቢ ባግዳድ ውስጥ ያለውን ሁኔታ ወዲያውኑ እንዲለወጥ አደረገው ። በግንቦት 30/1973 ፣ ድፍረት በተመላ ድንገተኛ ጥቃት የእሥራኤል የጦር አውሮፕላኖች ፣ በባግዳድ አጠገብ የሚገኘውን የኦሲራክ ኑክሌር ማመንጫ ጣቢያ በቦምብ ደበደቡ ። ድርጊቱ የግዳምን የአቶሚክ ጦር መሣሪያ የመሥራት ችሎታ ደመሰሰው ። በሌላ በኩል ደግሞ ኢራን ውስጥ የአገሪቱ የጦር ኃይሎች ለመዋጋት አለመዘጋጀትና በኢራቅ ላይ መልሶ የማጥቃት ጦርነት ለመክፈት የውጊያ ብቃት ማጣት ያስከተለው መላቀቅና ተስፋ መቁረጥ በጣም እየተባባሰ ሄደ ። ለዚህ ተወቃሹ ፕሬዚዳንት ባኒሳድር ሆኑ ፤ ባኒሳድር ሰኔ 10/1973 ኽሜይኒ ከሥልጣናቸው እንዳሰናበቷቸው ወዲያውኑ አገሪቱን ጥለው ሸሹ ። የባኒሳድር መባረር ፣ ኢራን ውስጥ የሃይማኖት መሪዎችን አገዛዝ በመቃወም የነበረውን ደም መፋሰስ ይበልጥ አባባሰው ። ሰኔ 21/1973፤ በእስልምና ሪፐብሊክ ፓርቲ ዋና ጽሕፈት ቤት በቦምብ መመታት ሃያ የሃይማኖት መሪዎች መሞታቸው ሁለት ወር ሲካሄድ የነበረውን የእርስ በርስ ደም ማፋሰስ አባባሰው ። ሆኖም የሃይማኖት መሪዎቹ አሸነፉ ። በመሪዎቹም ሰማዕትነት አብዮቱ አዲስ ስሜትና ብርታት አገኘ ።

በ1973 የበልግ ወቅት መጀመሪያ ላይ የኢራን ጦር ኃይሎች በተከታታይ ማጥቃት ጀመሩና በጥቂት ጊዜ ውስጥ የኢራቅን ጦር ኃይል ወደኋላ እስከድንበር ድረስ መለሱት ። በመስከረም 1974 ኩዚስታን ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ኢራናውያን ታላቅ የተሳካ ጥቃት አደረሱ ። በሁለተኛው የማጥቃት እርምጃቸው በኅዳር 1974 ኢራናውያን አዳዲስ ስልት በሥራ ላይ አዋሉ ። በደንብ ያልሠለጠኑና ቀላል መሣሪያ የታጠቁ

ብዙ ሺ አብዮታዊ ዘቦች በወዶ ዘማችነት ዋልቅ በሆነ ሃይማኖታዊ ስሜት ወደውጊያ ገቡ በሃይማኖት መሪዎቻቸው ግምባር ቀደምነት ወደ ጦርነቱ ሲገቡ ሃይማኖታዊው አገዛዝ የሰማዕት ዋጋ ገነት መሆኑን ስለአስተማራቸው ዘቦቹ ምንም ዓይነት የሞት ፍራቻ አላሳዩም ። አዲሱ የኢራናውያን ስልት የኢራቅን ወታደሮች አስደንገጠ። የዚህ ዓይነቱ አሰፋፈር ጥቃት ታሪክ በኢራቅ ከተሞች በሰፊው መወራት ጀመረ። አንድ የኢራቅ የጦር መኰንን ለብሪታንያዊው የወታደራዊ ታሪክ ምሁር ለኤድጋር ኦባላንስ እንደነገራቸው "ዓርብ ዕለት ከመስጊድ እንደሚጐርፈው የሰው ብዛት ዓይነት ሆነው ወደ እኛ መጡ ፡ ተኩስ ስንከፍት የምንተኩስ ያኔውኑ በሞቱ ሰዎች ላይ ነው ፡ አንዳንዶቹ በባለአሾኽ ሽቦ አጥር ላይ ተንጠልጥለዋል ፡ ሌሎቹ ደግሞ በተቀበረ ፈንጂ ላይ በመረማመዳቸው መሬት ላይ ተንባብረው በመዘረር ተከምረዋል ።"

ኢራናውያን በተጨማሪ በተከታታይ ማጥቃት ቀጠሉ ፡ በታኅሣሥ 1974 ኢራን የተሳካ ጥቃት አካሂዳ ዓይነተኛ መስቀልያ መንገድ ያዘች ። ይህም መላውን የደቡብ ክፍል የሚያገናኝ ብቸኛ መንገድ ነው ። ሣዳም ወደ ግንባሩ በመሄድ መልሶ ማጥቃቱን ቢመሩም በየካቲት 1973 የተደረገው አንድ ወር የወሰደ የኢራቅ ጥረት መጋጠሚያውን መንገድ ማስመለሱ አልተሳካላትም ።

በመጋቢት 1973 መጨረሻ ላይ ኢራናውያን አሁንም ሌላ ተጨማሪ አስደናቂ ድል አገኙ ። የኢራቅን ጦር ኃይል ወደ ኋላው 48 ኪሎሜትር በመግፋት ዓሥራ አምስት ሺ ኢራቃውያን ማረኩ ። ከዚያን ጊዜ ጥቃት በኋላ ሦርያ ሙሉ በሙሉ ከኢራን ጐን ተሰለፈች ። ሶርያ በውስጧ ወደ ሜዲትራንያን ባሕር ያልፍ የነበረውን የኢራቅን የነዳጅ ዘይት ማስተላለፊያ የቧምቧ መሥመር በመቁረጧ ባግዳድ በቀን ሠላሳ ሚሊዮን ዶላር ገቢ ቀረባት ። ሶርያ ጦርነቱ እስካበቃ ድረስ የኢራን ወዳጅ ሆና ቆይታለች።

መጋቢት 1973 ኢራን ባደረሰችው ጥቃት ሣዳም ለጥቂት ማምለጣቸው ወዲያውኑ ባግዳድ ውስጥ ተሰማ ። በኢራቅ ድንበር ላይ በተካሄደው የግንባር ውጊያ በስተጀርባ ሣዳም በመኪናቸው በመጓዝ ላይ እንዳሉ የአርሳቸው አጃቢ መኪናዎች የሣዳምን መኖር ባላወቁ የኢራን ወታደሮች ተከበቡ ። ከበባውን ጥሶ ሣዳምን ለማውጣት በቅርብ የነበረው ብቸኛ አንድ ክፍለ ጦር ኃይል የሚታዘዘው ከሣዳም ጋር በተኳረፉት ታክሪቱ



ጀኔራል በማሃር አብዱል ረሺድ ነበር ። ሣዳም ከብዙ ዓመት በፊት የረሺድን እኅት በዘመድ አስገድለው ነበር ። ሣዳም እርዳታውን በጠየቁ ጊዜ በአስገደሏቸው እኅታቸው ሰም እርዳታውን ካልጠየቁ ሣዳምን ከከበባው እንደማያወጧቸው ረሺድ ገለጹ ። ከባድ የቦምብ ውርጂብኝ ከደረሰባቸውና እሳቸውን ለመከላከል አንጋቾቻቸው በላያቸው ከተነባበሩ በኋላ ሣዳም በረሺድ ጥያቄ ተስማሙ ። ረሺድም የተከበቡትን ፕሬዚዳንት በአፋጣኝ አስለቀቁ ። በኋላ ልጃቸው የሣዳምን ልጅ ብታገባም ፡ በሁለቱ ሰዎች መካከል የነበረው አለመጣጣም አልተወገደም። እንዲያውም ጦርነቱ ከማብቃቱ በፊት ረሺድ ለቁም እሥር ተዳረጉ።

ግንቦት 1974 ኢራን ትልቁን የተሳካ ድል አገኘች ። አንድ ወር በወሰደ ዘመቻ የኢራን ወታደሮች የኢራቅን ጦር ኃይል ከተቀረው ቦታ በማስወጣት የኾራምሻርን ከተማ ያዙ ። ከዚህም ጋር ሃያ ሁለት ሺ የኢራቅ ወታደሮችን ማረኩ ።

ሣዳም ለገጠማቸው ተደጋጋሚ ሽንፈት በድንገተኛ መግለጫ ምላሽ ሰጡ ። ሰኔ 3/1974 በተናጠል ብቻቸውን ተኩስ አቁም በማወጅ ወታደሮቻቸው ከኢራን ግዛት እንዲወጡ አዘዙ ። ከዚህም በላይ ኢራቅና ኢራን ጦርነታቸውን በማቆም ከአራት ቀን በፊት ሊባኖስን የወረረችውን እሥራኤልን አብረው እንዲወጉ ሣዳም ሐሳብ አቀረቡ ።

እሥራኤል ሊባኖስን ያጠቃችው ከኢራቅ እንግር አይደለም ፡ ሁኔታው የተፈጠረው በአጋጣሚ ነበር ። የእሥራኤልን ወረራ ሣዳም አቀጣጥለዋል እንዳይባል ፡ የእሥራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ሜናኺም ቢጊንና የመከላከያ ሚኒስትር አርዬል ሻሮን የፍልስጥኤምን ነፃ አውጪ ድርጅት ከሊባኖስ ለማስወጣት መፈለጋቸው በመላው መካከለኛው ምሥራቅ የታወቀ ነው ። ነገር ግን ሰበብ አስፈልጓል ። የሚያስከትለውን በመፍራት ያሲር አራፋት እስከመጨረሻው ድረስ በመታገል እሥራኤል ሰበብ እንዳታገኝ ለማድረግ ሞክረዋል ። ሆኖም ግንቦት 26 1974 በለንደን የእሥራኤል አምባሳደር ላይ ተኩስ ተከፍቶ ለጥቂት ሳታቸው ። ይህ እሥራኤልን አነሣሣት ። በኢራቅ ስለላ ድርጅት ውስጥ የኩሎኔልነት ማዕርግ የነበረውን ይህን የግድያ ሙከራ ያደረገ ሰው ብሪታንያ ይዛ በማሰር ለፍርድ አቅርባለች ።

ሁለት እስራኤላውያን ጋዜጠኞች ዚቭ ሲሺፍና ኢሁድ ያሪ በተጨማሪ እንደዘገቡት ኩርኬሉ ለማድያው የተጠቀመበት ጦር መሣሪያ የተገኘው ለንደን ውስጥ ከሚገኘው የኢራቅ ኤምባሲ ወታደራዊ አታሼ ነበር ። ሲሺፍና ያሪ እንዲሁም ኔው ዮርክ ታይምስ ፣ ዘገባቸውን ሲደመድሙ እሥራኤል ሊባኖስን እንድታጠቅ ኢራቅ ፈልጋ ነበር። ሁኔታውን ከኢራን ጋር የተኩስ አቁም ስምምነት ላይ ለመድረስ ለመጠቀምና በዚህ ባግዳድ በተቸገረችበት ወቅት ቢያንስ ሶርያን ገፍቶ እንዲይዝላትና ደማስቆንም ኢራንን ከመርዳት እንዲገታላት ለማድረግ ነበር ።

ያም ሆኖ ሳዳም ያቀረቡትን የተኩስ አቁም ሐሳብ ኾሚኒ አልተቀበሉትም ። ሐምሌ 7/1974 ኾሚኒ ሌላ ጥቃት በመሠንዘር ለመጀመሪያ ጊዜ ራሷን ኢራቅን አጠቁ ። ስለጦርነቱ አካሄድ በቅድሚያ ለመናገር አስቸጋሪ ባሕርይ እንዳለው የታየው የኢራቅ ወታደሮች አገራቸውን ለመከላከል ጠንክረው በመቋቋማቸው ነው ። ከመስከረም 1974 ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ በቁርጠኝነት ኢራን በኢራቅ ላይ ያደረሰችው ጥቃት የኢራቅን የመከላከያ ወረዳ ጥሶ ለመሄድ አልቻለም ። አሁን ደግሞ የኢራን ወገን ተስፋ ሲቆርጥና ብዙ ወታደር ሲወድቅበት ይታይ ጀመር ። ይህም ብቻ ሳይሆን ፣ የኢራቅን ሺዓዎች ኾሚኒን በመደገፍ፣ አያቶላ እንደጠበቁት፣ እንዲነሡ ለማድረግ ኢራን አለመቻሏ ሌላው ውድቀት ነበር ።

ይሁን እንጂ ባግዳድ የኢራንን ጥቃት ብትቋቋምም ፣ ወደፊት ኢራቅን በጣም አስቸጋሪ ጊዜ እንደሚያጋጥማት የሚጠቁም ፍርፍርታ ነበር ። የሳዳም የገናናነት ሕልም ዕውን ሳይሆን ቀረ ። በመስከረም 1975 የተካሄደውን የገለልተኛ አገሮች የመሪዎች ጉባዔ እንድታስተናግድ ኢራቅ ተመርጣ ነበር ። አገዛዙም በጉዳዩ አስቦበት ለዝግጅቱ ብዙ ጥሯል። ወጪም አውጥቷል ። ሁሉም የባግዳድ አንደኛ ደረጃ ሆቴሎች ለመሪዎቹ ጉባዔ ለመዘጋጀት ታድሰዋል ። ከታደሱት ሆቴሎች መካከል በ1982 ኢራቅ ኩዌትን ከወረረች በኋላ የውጭ አገሮችን ዜጎች ያሰረች በት ይገኙበታል ። ሆኖም በባሕረ ሰላጤው ጦርነት ምክንያት የ1974ቱ የመሪዎች ጉባኤ ወደ ሕንድ ስለተዛወረ ሆቴሎቹ ከቶም ለታቀዱለት ዓላማ አልዋሉም ። ከ1973 በኋላ ጦርነቱ ለረጅም ጊዜ መሸናነፍ ሳይቻልበት መቆየቱ የባግዳዱን መንግሥት ጨፈገገው ፣ እናም ተስፋ



የመቁረጥ መንፈስ ሰፈነ ። ብዙ ቤተሰብ በጦርነቱ ከአንድ በላይ ሰው እየተሠዋ ፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያንዳንዱን ቤተሰብ እየተሰማው የመጣው የሚያልቀው ሰው ብዛት ሕዝቡን በጣም አሳሰበው ። መንግሥቱ ኢራቅን ከእርሷ በጣም ከምትተልቀው ፣ በሕዝብ ብዛትም ከምትበልጣት ጎረቤቷ ጋር ጦርነት ውስጥ ስላስገባት በእርሱ ላይ ሕዝቡ መከፋትና ምሬት አደረበት። ከሞት የሚተርፍበት ምንም መንገድ የሌለ፣ ወደፊትም ምንም የተስፋ ጭላንጭል የሌለ መሰለ ። በተለይም የኢራቅ ወጣቶች ከፍተኛ ብሶት ነበረባቸው ። ብዙዎቹ ወጣት ሴቶች ትዳር ሊመሠርቱ አልቻሉም። ጦርነቱ የማያባራ መሰለ ።

የኢራቅ ጦር መኰንኖች ከውጪ ከኢራን ያንዣበበውን ሥጋት ፣ ከውስጥም የኩርዶችንና የሺዓዎችን ሥጋት እየገቱ መቆየት ይችሉ ዘንድ የሳዳም አገዛዝ ያመጣውን ውርደትና ሽብር ለመቻል በጐ ፈቃድ ነበራቸው ። ሱኒው ዓረብ ሕዝብ በጠቅላላው ከመኰንኖቹ ጋር ተመሳሳይ ስሜት ነበረው ።

ነገር ግን ሺዓው ሕዝብ ከትናንት ዛሬ በባሰ ሁኔታ ሳዳምን በመፍራት ይሸበር ነበር ። በ1971 የተጀመረው የሺዓን ማኅበረሰብ ካገር የማስወጣት ተግባር በጦርነቱም ዓመታት ቀጥሎ በ1973 ፣ በ1975 እና በ1977 ከመቼውም በላይ በዝቶ ተገኘ ። በዚህ ጊዜ ውስጥ 300 ሺ ሺዓዎች ተገድደው ከኢራቅ ወደ ኢራን ተባረሩ ። ሺዓዎች ካገር የሚባረሩት ጭካኔ በበዛበት ሁኔታ ነበር ። ተባራሪዎቹ ሺዓዎች ካገር እንደሚወጡ በተነገራቸው በአጭር ጊዜ ውስጥ ተይዘው ፣ ወይም አንዳንዴ በውሸት ማሳመኛ ተታልለው አንድ ቦታ እንዲሰባሰቡ ከተደረገ በኋላ ፣ በውጊያ መኪናም ቢሆን ወደ ኢራን ድንበር ተጓጉዘው ልክ የቁሻሻ ያኸል እዚያ ይራገፉሉ ። ለምሳሌ በ1973 ፣ 700 ያኸል ግምባር ቀደም ሺዓ ነጋዴዎች ካገሪቱ የንግድ ሚኒስቴር ባለሥልጣናት ጋር ተገናኝተው እንጊውን የገቢ ንግድ የንግድ ፈቃድ ለመቀበል በባግዳድ ውስጥ እንዲሰበሰቡ ካገሪቱ የነጋዴዎች ምክር ቤት የስልክ ጥሪ ይደረግላቸዋል። ወደተባለው ሥፍራ እንደደረሱ ግን ፣ በአውቶቡስ ታጉረው ወደ አንድ የደህንነት ቢሮ ተወስደው እዚያ እንዲያድሩ ይነገራቸዋል ። በማግሥቱ ጉሕ ሲቀድ ተገድደው በካሚዮን ይጫኑና ፣ ወደ ድንበር ከተወሰዱ በኋላ በእግራቸው ወደ ኢራናውያን መከላከያ ወረዳ ያመሩ ዘንድ ይነገራቸዋል ።

ሆኖም ግን ሣዳም ቢያስከፏቸውም ፡ እጅግ አመዛኙ ብዙኃን ሺዓ ኢራቃውያን እንደኾሚኒ ባለው ሃይማኖታዊ ኋላቀር መንግሥት ሥር ለመኖር አይሹም ነበር ። ይልቁንም ፡ ኾሚኒ ጦርነቱን በመቀጠላቸው በእርሳቸው ተመርረው ነበር ። ሺዓዎች በተለይም ደሀዎቹ በኢራቅ የምድር ጦር ውስጥ በብዛት ይገኛሉ ። ኢራቅ ሰሞን ንቅል አድርጋ በከፈተችው ጥቃት ከፍተኛ የሕይወት መሥዋዕትነት የጠየቀው የመጀመሪያው ብርቱ በትር ያረፈው በእነርሱ ላይ ነበር ።

እንግዲያውስ ጦርነቱ እስከፊ አቅጣጫ እየያዘ በሄደ መጠን በሣዳም ላይ የሚሰነዘረው የግድያ ሙከራ እየጨመረ መሄዱ አያስገርምም ነበር ። በሐምሌ 1974 ሱኒና ሺዓዎች ተሰባጥረው ይኖሩበት በነበረ በአንድ የገጠር መንደር በሣዳምና በአጃቢዎቻቸው አቶሞቢሎች ላይ ባልታወቁ ባልታወቁ ሰዎች ተኩስ ተከፈተ ። አጥቂዎቹ ሣዳም ይገኙባት የነበረችውን አቶሞቢል ስለሳቷት መሽከርከሯን ቀጠለች ። ከአራት ሰዓት በኋላ ፡ መንደሯ ናፓልም ቦምብ በሚጥሉ ሄሊኮፕተሮች ተጠቃች ። እያንዳንዱ ቤት እንዲጋይና እንዲፈራርስ ተደረገ ። ቡልዶዘሮች ቤቶቹን ቆፍረው ቀብረቸውና መንደሯ የእርሻ መሬት ሆነ ።

በ1977 በታክሪት በደረሰ አደጋ ፡ ሣዳምና አጃቢዎቻቸው በአቶሞቢል ይጓዙ በነበረበት መንገድ ላይ ፈንጂ የታጨቀች አቶሞቢል ቆማ ነበር ፡ ነገር ግን ሣዳም ወደ ታክሪት ከተማ ከመግባታቸው በፊት … በአቶሞቢሏ ላይ የታጨቀው ቦምብ ፈነዳ ። በወቅቱ እርሳቸውን አጅቦ የነበረ ሳባህ ሚርዛ የታበለ እንጋቻቸው ፕሬዚዳንቱ በእርሳቸው ላይ ያለው ተቃውሞ ትውልድ ከተማቸው እንኳን ሳይቀር መድረሱን እንዳዩ ዓይናቸው እምባ አቅርር እንደነበር ዘግቧል ። የሣዳምን ሕይወት ለማጥፋት በ1976 እና በ1979 ሌላ ሙከራ ተደርጓል ። ከ1974 በፊት ፡ ያገሪቱን ልዩ ልዩ ክፍሎች እዘውትረው ይጐበኙ ነበር ፡ ነገር ግን ከዚያ ወዲህ አድርገውትም አያውቁ ። በፊንታው ፡ አስቀድሞ ብዙ ቦታ የጐበኙዋቸው ዕለታት እርሳቸው በሌሉበት በየቦታዎቹ ይከበሩ ነበር ።

ይህ አከባበር ጊዜ እያለፈና በጦርነቱም አድካሚነት የሣዳምን እንደጣኦት መመለክ ያስከተለ መሆኑን አንፀባርቋል ። በሚያዝያ 1975 የተወለዱበት ዕለት ብሔራዊ በዓል እንዲሆን ተደረገ ፡ ዕለቱንም ለማስብ 2ሺ500 ኛማ ወደጢግርስ ወንዝ ተጣለ ። እፍራ ቢንጂዩ የተበኙ እሥራኤላዊ ምሁር እንደሚሉት እያደገ የሄደው የሣዳም እንደጣኦት



መመለክ ከሞላ ጐደል የእርሳቸውን እንግዝ ሁለት ተግራሪ ገጽታ ፡ እርሳቸው የሚገኙበትን አደገኛ ሁኔታና በበላይነት የመቆጣጠር ችሎታ ያመለክታል ።

ከ1974 በኋላ ፡ መንግሥታቸው በተለይ ለጦርነቱ የሚመድበው የሰውና የሀብት መጠን እየጨመረ ይሄድ ነበር ። በጦርነቱ የመጀመሪያ ሁለት ዓመት ፡ ከባሕረ ሰላጤው አገሮች ባገኘችው የዓሥር ቢሊዮን ያሽል ዶላር እርዳታ እየታገዘች ኢራቅ ስንቅና ትጥቅ (ለሕዝቧና ለሠራዊቷ እንዳስፈላጊነቱ) ማቅረብ ትችል ነበር ። ሣዳም በተለይ ጦርነቱ ያስከተለውን ከባድ ሁኔታ ፡ በተለይም የሚያልቀው ሠራዊት ብዛት እየጨመረ መሄድ ያስከተለውን ብሶት ለመቅረፍ ሞክረው ነበር ። ይህንንም የሞከሩት በቂ የፍጆታ ሸቀጣሸቀጥ ከውጪ በማስመጣት እንደልብ እንዲገኝ በማድረግና በጦርነቱ ለሞቱ ሰዎች ቤተሰብ ጠቀም ያለ እምባ ማድረቂያ በመስጠት ነበር ። እምባ ማድረቂያውም ለአንድ ቤተሰብ አንድ አቶሞቢል ፡ ገጸ ዲናርና እንዲሁም ቤተሰቡ ፡ ቤት ከሌለው ፡ የቤት መሥሪያ ቦታና ገንዘብ ነበር ።

የሚሰላበት ቀን ለሌላ ጊዜ ከተላለፈ ረጅም ጊዜ ቢሆንውም ፡ እየተንባበረ ያለውን የኢኮኖሚ ችግር እምና መቀበል ያስፈልጋል ። በኅዳር 1974 ወደ ውጪ ሀገር መግዝ ከመከልከሉ በተጨማሪ (ወገብን ጠበቅ አድርጉ) በቁጠባ የመኖር መርሀ ግብር ተዘረጋ ። በሚቀጥለው ዓመት ምንም በጀት አልወጣ ። እልፎ አልፎ እንዳንዴም በተከታታይ የምግብ በተለይም የሥጋና የአትክልት እጥረት መታየት ጀመረ ። የገንዘብ የመግዛት አቅም እያዘቀጠ መምጣት ገቢን ቶይዳ እያሳጣው ሄደ፡ እናም በገቢው ለመኖር ያሸል ብቻ ከመላ ጐደል እያንዳንዱ ቤተሰብ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ደሞዝ አስፈለገው ።

የጦርነት ግፊት በፓርቲው ርእዮተ ዓለም ላይ ለውጥ አመጣ ። ሣዳም የኢራቅ ጦር ኃይል የኢራንን ግዛት ለቆ እንዲወጣ ካደረጉ በኋላ ፡ በሰኔ 1974 በከፍተኛ ደረጃ በተካሄደ ስብሰባ ፓርቲው አዲስ የርእዮተ ዓለም መሥመር ነደፈ ። (ቀደም ሲል የተጠቀሱት እሥራኤላዊ ምሁር) ቢንጂዮ እንደገለጹት "የሶሻሊዝም መመሪያነት በጣም ተቀነሰ ፡ የኢራቅ ብሔረተኝነት ከዓረብ ብሔረተኝነት ቅድሚያ ተሰጠው ፡ ፍልስጥኤምን ነፃ የማውጣቱ ጉዳዩ ጨርሶም አልተጠቀሰ ።" ይህ ለውጥ አሻሚና በአደናጋሪ ቋንቋ የተሸፋፈነ ቢሆንም ፡ ጦርነቱ እስከቀጠለ ድረስ ኢራቅ

የምትከተለው ፖሊሲ አጠቃላይ አቅጣጫ ነው ።

የፓርቲው መሥመር የተለወጠው ኢራቅ በከፍተኛ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ስለነበረች ነው ። የሚሸል ዓፍለቅ የጉርምስና ተምኔት ኢራቅን እየታወሰ አስቸገራት ። ባዓቲዝም የዓረቦችን ኅብረት ከጽዮናዊነትና ከምዕራብ ኢምፔሪያሊዝም ጋር በማያልቅ ትግል ውስጥ ከተተው ። ነገር ግን ዓረቦች አልተባበሩም ነበር (ሶርያ ፡ ለምሳሌ ኢራንን ደገፈች) ፡ እና ኢራን ጠላቲቱ ፡ ጽዮናዊም ኢምፔሪያሊስትም አልነበረችም ። እንዲያ ውም ነገሩ ከተንግ ራዒ ምንችክ ብላ ጠላትነቷን በይፋ የገለጸች የሁለቱም ጠላት ናት ። ስለዚህ ኢራቅ ከኢራን ጋር ለተያያዘችው ጦርነት የጽዮናውያንንና የኢምፔሪያሊስቶችን እርዳታ ለማግኘት ትምክር ዘንድ በወራዳነት ፊቷን ወደ እነርሱና ከእነርሱ ጋር ወደ ሚተባበሩ አገሮች ማዞር ነበረባት።

የግዳም የመጀመሪያ እርምጃ ከግብጽ ጋር የበለጠ የቀረበ ግንኙነት መፍጠር ነበር ። በጥር 1975 ውጪ ጉዳይ ሚኒስትር ጣሪቅ አዚዝን ወደ ካይሮ መላክ ነበረባቸው ። ይህም ሳዳት በ1970ው የባግዳድ የመሪዎች ጉባኤ ከተወገዙ ወዲህ በከፍተኛ ደረጃ ለመቀራረብ ያበቃ የኢራቅ ከፍተኛ ባለሥልጣን ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ካይሮ ያደረገው ጉዞ ነበር ። ኢራክ ከሞሮኮ እስከ ሳዑዲ ዓረቢያ ካሉት ፡ ቱባው ባዓቲዝም በፊቶዳልና በአድኃሪነት ከኰነናቸው የነገሥታት መንግሥታት ሁሉ ጋር ልባዊ ግንኙነት እንደመሠረተች ፡ የሣዳምና የዮርዳኖሱ ንጉሥ ሑሴን ወዳጅነ ትም የበለጠ ተጠናከረ ። የኢራቅና የአሜሪካም ግንኙነት በዚህ ጊዜ ማቆጥቆጥ ጀመረ ።

ከ1975 ጀምሮ ጦርነቱ ማባሪያው እስኪታረብ ድርስ ጸንቶ የኖረ አዲስ አቅጣጫ ያዘ ። ኢራን ወትሮ በየዓመቱ የዝናቡ ወቅት በአመዛኙ እግረኛ ለሆነው ጦሯ ታክቲካዊ ረብ በሚኖረው በክረምት ወይም በመፀው አንዱ በሰፊው ማጥቃት ትጀምራለች ። ኢራቅ ፡ በከፊል መንግሥቷ ውጊያው በጠየቀው የሕይወት መሥዋዕትነት በጣም ስለተን ገሸገሸ ፡ ያለመጠን ጽኑ የመከላከል ጦርነት ነበር የምታካሂደው ። እንደ ዕውነቱ በ1974ቱ ፀደይ ኢራቅ በጦርነቱ የሞተባትን ሠራዊት በአኀዝ መግለጽ አቆመች ። ጦርነቱ በዚህ ዓይነት ቢራዘምም ፡ አብዛኛውን ጊዜ ታላላቅ ፍልሚያ አልነበረም።



በ1975ቱ መፀው ኢራን በደቡብ በከፈተችው ጥቃት የኢራቅን ሠራዊት ደመሰሰች ፡ ግን በሰሜን በኩል ችግሯ በታየው በኢራቅ ላይ ብርቱ ሥጋት አላሳደረም ። በሐምሌ 1975 የኢራቅ ጦር ኃይሎች ከታወቀው የኩርዶች መሪ ከሙስጠፋ ባርዛኒ ልጅ ከመስዑድ ባርዛኒ ጋር ተባብረው የሙስጠፋ የዱር የበላይ እዝ የነበረባትን የሐጅ እምራን ትንሽ ከተማ ያዙ። ይህ ድል በጦርነቱ ላይ ወደኋላ መስዑድ ባርዛኒን በመንግሥቱ ላይ የበለጠ ዘመቻ ለማድረግ የሚበጃቸው ጦር ሠፈር ለማቋቋም ረዳቸው ።

ውጊያው ከዓመት ዓመት እንደቀጠለ የኢራቅ ጦር ሠራዊት የኢራንን በቁጥር የላቀ ጦር የመመከት አቅም እያጣ መጣ ። በ1975 ፀደይ ወቅት ኢራቅ ምስጢራዊ ዘመናዊ መሣሪያ እንዳላት በመጥቀስ ግዳም ኢራንን አስጠንቀቁ ። የዚህ ማስጠንቀቂያ ትርጉም ፡ እራን በደቡባዊ ኢራቅ ረግረግ ውስጥ ከፍተኛ የሰው ኃይል እንጋግታ ውጊያ በመግጠም፡ በኢራቅ ላይ በሰፊው ጥቃት ማድረስ ጀመረች ። ኢራቃውያን ረግረጉ በብዙ ጦር ኃይል ሊታለፍበት የማይቻል እንደሆነ በመገመት ኢራናው ያኑ የጣሉት አደጋ ዱብ እዳ ሆነባቸው ። ኢራን በዚህ ውጊያ በጣም ብዙ ሠራዊት ቢሞትባት (20ሺ) ፡ ቢቆስልባትና ቢማረክባትም በነዳጅ ዘይት የበለጸገችውን የመጅኑን ደሴት ይዛ ከመቆየቷም በላይ ጦር ኃይሏም ከባግዳድ ወደ ባስራ የሚያመራውን ስትራተጂያዊ አውራ ጐዳና ለአጭር ጊዜ በተለያዩ ቦታዎች ቆረጠው ። ኢራን የከፈተችው ጥቃት እጅግ አስጊ ስለመሰለ ግዳም ኬሚካል ጦር መሣሪያ ጥቅም እንዲውል አዘዙ ።

ከ1976 በኋላም ግዳም ከጦሩ ጋር ያላቸውን ግንኙነት በመጠኑም ቢሆን በተለየ መንገድ ይመሩት ገቡ ። አስቀድሞ አይጠቀስ የነበረው የጦር አዛዦች ስም ለመጀመሪያ ጊዜ ባደባባይ እንዲጠቀስ መፍቀድ ጀመሩ ። በግልጽ ለፍቱን አዛዥነት ተገቢውን ማበረታቻ ለመስጠት እንዲህ ዓይነት ውሳኔ አስፈላጊ እየመሰለ መጣ ። ድክመት በሚከሠትበት ወቅት ደግሞ በእንዱ ላይ መላከኩን አቀለለው ። ከዚህም በላይ የእድገት መሥፈርቱ ፖለቲካዊ መሆኑ ቀነሰ ። ባዓዚስት ያልሆኑ መኰንኖች የማዕረግ እድገት ማግኘት ጀመሩ ።

የቴሀራን መንግሥት በመጋቢት 1977 በደቡባዊ የኢራቅ ረግረግ ምድር እንደገና ማጥቃት ጀመረ ። ለተወሰነ ጊዜ የኢራቅ ጦር ኃይል መመከት በጣም ከብዶት ነበር ። ግብፅ ከፉኛ የተፈለገ ጥይት በአውሮፕ

ላን ለኢራቅ አቀረበች ። ኢራናውያን ከባግዳድ ወደ ባስራ ለሚያመራው አውራ ጎዳና አሰጉ ። ነገር ግን በዚህኛው ጊዜ አውራ ጎዳናውን መቁረጥ ተሳናቸው ። ከብርቱ ውጊያ በኋላ ፣ የኢራቅ ወታደሮች ፣ እንደገና በኬሚካል ጦር መሣሪያ በመጠቀም ኢራናውያንን ባሉበት መግታት ችለዋል ። በጥቃቱ መኻል የየርዳኖስ ንጉሥ ሑሴንና የግብፁ ፕሬዚዳንት ሆስኒ ሙባረክ የትግል አንድነታቸውን ለማሳየት ወደ ባግዳድ በረሩ። ከባግዳድ የመሪዎች ጉባኤ ወዲህ አንድ የግብፅ ፕሬዚዳንት ወደ ኢራቅ ሲሄድ የመጀመሪያው ነበር ።

ኢራቅን ከኢራን ግዛት ካስወጣው ከግንቦት 1974 ዘመቻ በመለስ ፣ ከአንድ ዓመት በኋላ ፣ በየካቲት 1978 የተፈጸመው ጥቃት ለኢራን እጅግ የተሳካ ሆኖ ተገኘ ። በአብዛኛው ቀላል መሣሪያ የታጠቁ ወዶዘማች የነበረ አንድ መቶ ሺ የኢራን ጦር በየካቲት 2/1978 ማታ በተዘጋጋና በጭጋጋማ የአየር ጠባይ ተጠቅሞ በስተደቡብ ግምባር ውጊያ ከፈተ ። ከሃያ አራት ሰዓት ባነሰ ጊዜ ውስጥ የፋኦን ልሳነ ምድር በእጁ ማስገባት ቻለ ። ልሳነ ምድሯ ከኢራቅ ወታደራዊ ወደብ ከኡም ቃስር ባትርቅም የኢራቅ ኃይሎች ኢራናውያኑን በደሴቲቱ ውስጥ ፈግተው መያዝ ቻሉ ። በዚህ ውጊያ የሞቱትና የቆሰሉት በዓሥርና በዓሥራ አምስት ሺ መኻል የተገመቱ ፣ ኢራቃውያን ብዛት ለአናሳውና ሐሞቱ ለፈሰሰው የኢራቅ ሕዝብ አገሪቱ ያላት ጦር ሁሉ የተደመሰሰ ያኽል ነበር ።

ተከታዮቹን ሁለት ወራት ፣ ሣዳም የሪፐብሊኩ ዘብ (ሪፑብሊካን ጋርድ) ምርጥ የጦር ክፍል አባላት በተካፈሉባቸው የተጠናከረ መልሶ ከባድ ውጊያ በመግጠም ፋኦን መልሶ ለመያዝ ሞከረ ። ነገር ግን ኢራናውያኑን ከልሳነ ምድሯ ማስወጣት ተሳናቸው ። ሣዳም ፣ ፋኦን መልሶ መያዝ ተሳናቸው ፣ በግንቦት 1978 በማእከላዊ እዝ ግምባር የምትገኝ አንዲት ትንሽ የኢራን ከተማ እንድትያዝ አዘዙ ። ነገር ግን ከወር በኋላ የኢራን ኃይሎች ከተማይቱን መልሶ መያዝ ችለዋል ። ሁኔታው የከፋ መሰለ — ኢራቃውያንን መከላከል ያለመቻል አልለመደ ባቸውም ነበር — እናም ሣዳም ለእርሳቸው እጅግ በጣም ከባድ ሊሆን የተገባው ውሳኔ ወሰኑ ፣ በጦርነቱ የእዝ ሰንሰለት ለጦር አዛዦቻቸው የበለጠ ሥልጣን ሰጡ ።

ከዚህም በላይ ፣ ፋኦን ማጣቷ ኢራቅን እጅግ ተስፋ አስቆርጦ እሥራኤልን ቀርባ እርዳታ እስከመጠየቅ አደረሳት ። ከሁለቱም የተገለሉ



ነን ምንጮች እንደሚመሰክሩት የኢራቅና የእሥራኤል የስለላ መኰንኖች በግብፅ አማካይነት በ1978 መፀው ወቅት አውሮፓ ውስጥ ተገናኙ ። በሐምሌ 1978 ደግሞ እንዲገናኙ ቀን ቀጠሮ ቢይዙም ኢራቆች መገኘት ያመነኘታቸው አልተጣራም ።

ኢራቅ ቀጥላ ፣ ኢራን ከነዳጅ ዘይቷ ሽያጭ የምታገኘውን ገቢ ለማሳጣትና ጦርነቱን እንድታቆም በይነብሔራዊ ግፊት ለመቀስቀስ ባደረገችው ጥረት በሐምሌ 1978 አስቀድማ የኢራንን የንግድ መርከቦች ለመምታት አሰበች ። የባግዳድ መንግሥት በባሕረ ሰላጤው የንግድ መርከብ ስለሌለው ኢራን የኢራቅን ግብረአበሮች ፣ በተለይም የኩዌትን የንግድ መርከቦች በመምታት ለኢራቅ አዲስ ፖሊሲ አፀፋ ሰጠች ። አንድ ኩዌታዊ ዲፕሎማት ያገራቸውን አመለካከት "ፋኦ ኢራናውያንን አስከራቸቀለች ። ሕዝቧ አገራቸው ለኢራቅ የምትሰጠውን ድጋፍ በመቃወም እንዲያምፅ ኩዌትን መከበብ ፈለገ ።" ሲሉ ገልጸውታል ።

ከዚያ ወዲህ በጥቅምት 1978 መጨረሻ ሳምንት አሜሪካና እሥራኤል ለኢራን በምስጢር ጦር መሣሪያ ሲሸጡና ከዚያም የሚያገኙትን ትርፍ ሳያባክኑ ይዘው ኒካራጓ ውስጥ የነበሩትን የኮንትራ አመፀኞች እየደገፉበት መሆኑ በድንገት አደባባይ ወጣ ። የአሜሪካ ፖሊሲ ውጥንቅጡ እንደወጣ ፣ የባግዳዱ መንግሥት ስለጽዮናዊነትና ስለኢምፔሪያሊዝም ሴራ በማማረር የሚያሰማው ወቀሳ ፣ በዚህ ረገድ በአስገራሚ ዕውነታ ፣ መሠረት ያለው መሰለ ።

ነገር ግን በዋሽንግተን አስተዳደር ውትብትብ የፋርስ ባሕረሰላጤ ፖሊሲ ላይ የተጀመረው ክርክር ከማብቃቱ በፊት ኢራን በኢራቅ ላይ የ1979ኙን ጥቃቷን ማድረስ ጀመረች ። ኢራን በታኅሣሥ 1979 መጨረሻ ሳምንት በኃይል ወደባስራ ገፍታ በመግባት የኢራንን ወታደሮች ከባስራ ከተማ በከባድ መሣሪያ ጓላማ ውስጥ እስኪገቡ አቀረባቸው። በሦስት ወር ዘመቻ የኢራን ጦር ኃይሎች (የአሜሪካን ሀውክ ፀረ አውሮፕላን ሚሳይልና ቶው ፀረ ታንክ ሚሳይል ታጥቀው) ከኢራቅ አምስት የመከላከያ ወረዳ አራቱን ጥሰው መግባት ቻሉ ። ብዙ የባስራ ነዋሪዎች ከተማዋን ጥለው ሸሹ ። ለኢራቅ ጦርነቱ ከተጀመረ አንሥቶ ከደረሰባት ጥቃት ሁሉ እጅግ አስቸጋሪው ጥቃት ይህ ነበር ፣ እስከ መጋቢት 22/1979 ድረስ በባስራ ግምባር የኢራናውያን ሰብሮ መግባት ያስከተለው ሥጋት አሳሳቢነት አልቀረም ።

እስከዚያ ፣ የዋሽንግተን አስተዳደር በፋርስ ባሕረሰላጤ አዲስ ፖሊሲ ቀይሷል ። ኩዌት ኃያላን መንግሥታት የነዳጅ ዘይት ወጪ ንግዷን ከጥቃት እንዲከላከሉላት ጠይቃለች ። ግን ሶቪየት ኅብረት ይህን ኃላፊነት ትቀበል እንደሆን ኩዌታውያን ጠይቀዋት መልስ እስኪያገኙ ድረስ የዋሽንግተን አስተዳደር የኩዌትን ጥያቄ ለመመለስ አልተጣደፈም። (በ1982 በቀዝቃዛው ጦርነት ማባራትና በሶቪየት አስጊነት መቅረት ኩዌትን ከጥቃት ለመጠበቅ አሜሪካ ምንም ያኸል ፍላጐት እንደማይኖራት ሳዳም ገምተው ነበር ይሆን?) የሬጋን አስተዳደር የኩዌትን የነዳጅ ዘይት ቦቴ መርከቦች ከጥቃት ለመከላከል ተስማማና የባሕረ ሰላጤውን ጦርነት እንዲያባራ ለማድረግ አንድ ፍቱን የተባበሩት መንግሥታት ውሳኔ እንዲጸድቅ ፈለገ ። ከሐምሌ 13/1979 ጀምሮ የአሜሪካ ባሕር ኃይል የኩዌትን የነዳጅ ዘይት ቦቴ መርከቦች ያጅብ ገባ ። እና የተባበሩት መንግሥታት የጸጥታ ምክር ቤት ሁለቱም ተፋላሚ ወገኖች ከጦርነቱ በፊት ወደየነበሩበት ይዞታ አፈግፍገው ተኩስ ያቆሙ ዘንድ በውሳኔ ቁጥር 598 ጥሪ አስተላለፈ ። ምክር ቤቱ ከሁለቱም ይህንኑ ውሳኔ በማይቀበለው ወገን ላይ የጦር መሣሪያ እገዳ እንደሚጥልም ዛተ ። ኢራቅ ተቀበለችው ። ኢራን ግልጽ መልስ ከመስጠት ታቀበች ፣ እና ውጊያው ቀጠለ ።

ብቻ ግልጽ የሆነው ካለፈ ወዲህ ወደኋላ ሲያዩት ሆኑ እንጂ ፣ የኢራንን በራስ የመተማመን ውስጣዊ ስሜት ብዙ ነገሮች ይሸረሽሩት ጀምረው ኖሯል ። በባሕረሰላጤው የአሜሪካና የአውሮፓ የባሕር ኃይሎች በመሠማራታቸው ፣ ኢራን ከጊዜ ወደጊዜ እየተገለለችና በይነብሔራዊ ግፊት እየተደረገባትም ነበረች ። የዋሽንግተን አስተዳደር በባሕረ ሰላጤው የኢራንን ድል ማየት አይፈልግ እንደነበር ፣ አሜሪካ የባሕር ኃይሏን ወደዚያ በማሠማራቷ ኢራን ተረድታዋለች ። ስለሆነም ኢራናውያን ወደ ሰሜን ራቅ ብለው ሐሳባቸውን በኩርዲስታን ላይ ለማሳረፍ ወሰኑ ። በ1979 በፀደይና በ1980 ክረምት ወቅቶች አንድ ስትራቴጂ ቀየሱ ። የዚህም ዓላማ የኢራን ጦር ኃይል የኢራቅን የኪርኩክ የነዳጅ ዘይት ጉድጓድ መስክ ሊያሠጋ በሚችልበት ደረጃ በሰሜን ኢራቅ አንድ አውራጃ ለመውረርና ለመያዝ ነበር ። ኢራን ስትራቴጂውን ስትቀይስ ከኩርዶች መሪዎች ጋር በመቀራረብ ተማከረለች ። በመጋቢት 1980 የኢራን ጦር በስትራቴጂው መሠረት ገፍቶ ወደሰሜን ኢራቅ



ክልል በመግባት ግምባር ቀደሙ ኃይል ሀላብጃ ደረሰ ። ኢራቅ በዚያ መንደር በኬሚካል ጦር መሣሪያ አፀፋ መስጠቷ ኢራን ይህን ስትራቴጂ ከዚያ በላይ እንዳትገፋበት ቅስሟን ሰበረው ።

የኢራቅ ወታደሮች ፣ ስድስት ዓመት በመከላከል ከቆዩ በኋላ ፣ በግንቦት 7/1980 የፋኦን ልሳነ ምድር በሠላሳ ስድስት ሰዓት መልሰው በመያዝ ከመቅጽበት ራሳቸው ድንገተኛ አደጋ ጣሉ ። ግንቦት 17/1980 የባስራን ምሥራቃዊ መዳረሻ ትንሿን የሰላምጄ ከተማ መልሰው በመያዝ ዳግም በኢራቅ ቁጥጥር ሥር አዋሉ ። ሁለቱ በተከታታይ የተሳካ ጥቃት የኃይል ሚዛኑ ወደባግዳድ እንዲደፋ ጠቆመ ።

ሳዳም ከእሥራኤል ጋር በ1978 ተጀምሮ የተቋረጠውን ግንኙነት ቀጠሉ ። አሁንም በእሥራኤልና በኢራቅ መካል ሽምጋዮቹ ግብጾች ነበሩ። ሁለቱ ወገኖች ፍንጭ ተሰጣጡ ። ሳዳም በግንቦት 1978 የመጨረሻ ሳምንት ለወታደሮች ኒሻንና ሜዳይ የሸለሙበትን ሥነ ሥርዓት አስመልክተው የጀመሩትን ዲስኩር "ጽዮናውያንና እሥራኤላውያን ይህን ጦርነት ለመቀጠል የተሜወቱት ሚና እንዳስቆጫቸው እምናለሁ" በማለት አቋረጡ ። ይህ ኢራቅ ለእሥራኤል የሰጠችው ፍንጭ ነበር ። የሰጡት ደግሞ ሳዳም ራሳቸው ናቸው ። በኢራቅ ሬዲዮ የተላለፈውን ይህን ዲስኩር በቀላሉ ኢየሩሳሌም ውስጥ መከታተል ይቻላል ። በሚቀጥለው ወር የእሥራኤል መከላከያ ሚኒስትር ይስሐቅ ራቢን ፣ "ሐሳቤን ለውሜለሁ ። የኢራንና የኢራቅ ጦርነት የሚያስከትለው የጦር መሣሪያ አሽቅድድም ምክንያት ከእንግዲህ ለእሥራኤል ምንም እርባን የለውም ።" ሲሉ አስታወቁ ። "ሐዓሬትዝ" የተሰኘው የእስራኤል ጋዜጣ እንደዘገበው ፣ የራቢን ቃል "ከባግዳድ ለተላለፈ መልእክት" መልስ ነበር ። እንደሚታመነው የእሥራኤልና የኢራቅ ንግግር እንደገና ሳይካሄድ የቀረ አይመስልም ።

ነገር ግን ረጅሙ የባሕረሰላጤው ጦርነት ወዲያው ወዳልተጠበቀበት አቅጣጫ ዞረ—አባራ ። ሐምሌ 11/1980 ፣ ኾሜኒ የተባበሩት መንግሥታት ዋስትና የሰጠበትን ተኩስ አቁም በድንገት ተቀበሉ ። የኢራን በራስ የመተማመን ውስጣዊ ስሜት ሞቶ የጦርነቱን ማዕበል አቅጣጫ በታላቅ ፍጥነት ያዞረው ይመስላል ። ብዙ ኢራቃውያን ያባራል ብለው ፈጽሞ ያልጠረጠሩት ጦርነት ፣ በመጨረሻ አለፈ ። ብዙ እታቾች ጦርነቱን የአገሮችን ሕዝብ ሕይወትና ንብረት ያልነበረ ያኸል ለውድ

መት በመዳረግና ጎሊናን በላተ ታላቅ ቁጣንቱ እንድን የአውሮፓ ትውልድ ስሜት እስከማንዘር ካቆሰለው ከ1906 እስከ 1910 የዘለቀ ታላቅ (የመጀመሪያው የዓለም) ጦርነት ያነጻጽሩታል ። የኢራቅና የኢራን ጦርነት የያንዳንዳቸው ጦር ኃይሎች ብቻ ሳይሆኑ መላ ሕዝባቸው በከተት ገብቶ የተደራጀበትና የተዋጋበት ከሚገመተው በላይ እጅግ በጣም የገዘፈ ጦርነት ነበር ። በጦርነቱ የሞተውና የቆሰለው ብዛት ባለፈው ዓሥር ዓመት የተካሄደውን ፣ በሁለቱም ወገን ትልቅ ጥፋት ያደረሰውን እስታቂ የእርስ በርስ መጨፋጨፍ ጨምሮ ፣ ባለፉት አርባ ዓመታት በእሥራኤልና በዓረቦች መኻል በተካሄዱት ጦርነቶች ሁሉ ከሞተውና ከቆሰለው የላቀ ነበር ። ሁለቱ አገሮች በደምና በሀብት የከፈሉት መሥዋዕት ፣ በጣም አስከፊ ፣ ላይ ላዩን ሲያዩት ፣ ማስተዋል የማይቻል ነበር ። ሆኖም ግን ምናልባት እንድ በጥልቅ ትርጉም አጣማጊ እንዳች ነገር ሥራውን እየሠራ ነበር ። ጆርጅ ኦርዌል በ"ናይንቲን ኤይቲ ፎር" መጽሐፋቸው ውስጥ ፣ "በጦርነት ላይ ፣ እናም በአደጋ ላይ የመሆን መዘዝ ፣ ስህላዊ ሲባል ሥልጣንን ሁሉ ለትንሽ ምርጥ ወገን (ካስት) መስጠትን የተለመደ ፣ ለማስቀረትም የሚያስቸግር ሁኔታ ያስመስላል ። ··· (እያንዳንዱ) ምርጥ ወገን ብቁ ፣ ትጉህ ሠራተኛ ፣ እና እንዲያውም በተወሰነ ጉዳይ አስተዋይ እንዲሆን ይጠበቃል ፣ ነገር ግን ደግሞ በፍርሀት ፣ በጥላቻ ፣ በውዳሴ ፣ እና በጊዜያዊ ድል ከልክ በላይ በመፈንጠዝ መንፈስ የሚኖር መሆን አለበት ። ግን ደግሞ በቀላሉ ማመን የሚያበዛና ጭፍን ፣ ግትርነት የሚያጠቃው መሆን ያሻዋል ።

ኢራቅ ጦርነቱን በዚህ መንፈስ ጀመረችው ። ሆኖም ፣ በግጭቱ ረጅምና አስደንጋጭ ሂደት በመጨረሻ ኢራቅን ስለገዛው ትንሽ "የተለየ ወገን" ጥያቄ አስነሣ ፣ ይህ ጥያቄ ጦርነቱ እንዲ ካባሪ ግዳምን በአእምሯቸው እየተመላለሰ ያስጨንቃቸው ጀመር ።



፯

## ድል የለ ፣ ሰላም የለ

ስኔ 1/1980 ኢራቅ ከኢራን ጋር የተኩስ አቁም ስምምነት ስታደርግ ባግዳድ በደስታ ፈንደቀች ። በዚህ በሕዝቧ ላይ መጥፎ ስሜት እንዳሳደረ ባት እንደቴህራን ሳይሆን በሚሊዮን የሚቆጠሩ ባግዳዳውያን ሌት ከቀን እየጨፈሩና እየበፈኑ ጐዳናውን ሁሉ አጥለቀለቁት ። ርችት ተኩሱ ፣ ጥይት ወደሰማይ ተኩሱ ፣ በአላፊ አግዳሚው ላይ ውሀ ረጩ ። የኢራቅ እድል በሚያስደንቅ ፍጥነት ተቀየረ ። ልክ ከአራት ወር በፊት ፣ ለረጅም ጊዜ በቀጠለው የመተላለቅ ጦርነት ኢራቅ እየተሸነፈች በመሄድ ላይ ያለች መስላ ነበር ። ነገር ግን ይህ በድንገት ተለወጠ ። እንድ ኢራቃዊ "በጦርነቱ የደረሰባት እልቂት በድንገት ትዝ እያለ ቅዠትና ኅዘን የተቀላቀለበት" ስሜት በባግዳድ ሰፍኖ እንደነበር ገልጿል ።

የተኩስ አቁም ስምምነቱ አከባበር ከዓሥራ አምስት ቀን በላይ በዓል ሆኖ ተከበረ ። ወትሮ ጥብቅ ቁጥጥር ያደርግ የነበረው መንግሥት እንኳ ሕዝቡ የተኩስ አቁም ስምምነቱን በበዓልነት ማክበሩን እን ዲያቋርጥ ማድረግ አልቻለም ። እንድ ኢራቃዊ እንዳለው ፣ በመላው የባዓዚስት አገዛዝ ዘመን በተራው ሰው መኻል እንዲህ ያለ የስሜት መፈንቀል የታየው ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር ። በተኩስ እቁሙ ስምምነት መከበር ኢራቃውያን ከስምንት ዓመት የከፋ ጦርነት በኋላ ኑሮን የማጣጣም ተስፋቸው ለመለመ ። ኢራቃውያን እንበለጽጋለንም ብለው ትስፋ አደረጉ ። ያገራቸውን ኢኮኖሚ ሁኔታ ብዙም ሳያጤኑ — ኢራቅ ግማሹን ከሌሎች የዓረብ አገሮች ፣ ግማሹን ከምዕራባውያን አገሮች የተበደረችው ሰባ ቢሊዮን ዶላር እዳ ገብታ — እያለች — ሕዝቧ የጦርነቱ መቆም ከጦርነቱ በፊት የነበረውን ብልጽግና እንደምንም እንደገና ያቀዳጀናል ብሎ ያምን ነበር ። በጦርነቱ ማግሥት መልሶ ግንባታ ይፋፋማል በሚል ግምት የኢራቅን ገንዘብ የሕገወጥ ምንዛሬ ዋጋ ለአጭር ጊዜ እንዲያሸቅብ ያደረጉት የባሕረ ሰላጤው ነጋዴዎችም እምነት ይዥው ከጦርነቱ በፊት የነበራቸውን ብልጽግና እንደገና

የመቀዳጀት ነበር ። አንድ ኢራቃዊ ተኩስ ከቆመ ከአንድ ወር በኋላ "ለጊዜው ፣ ሕዝቡ ከውጪ የገባ ሸቀጣሸቀጥ መግዛት አቁሟል ። የተኩስ አቁም ስምምነቱ ሲፈረም የዲናር (የኢራቅ ብር) ምንዛሬ ዋጋ ያሻቅብና ማንኛውም ነገር ይረክሳል ብለን እየጠበቅን ነን" ሲል ገልጿል ።

አያቶላህ ኾሚኒ የተኩስ አቁም ስምምነቱን መቀበል ከመርዝ የበለጠ ቀፋፊ እንደሚሆንባቸው ቢያስታውቁም ፣ ኢራቃውያን እንዲህ ዓይነት ስምምነት በፍጥነት ይፈረማል ብለው ይጠብቁ ነበር ። ይህ ስምምነት ደግሞ በኢራን የተያዙ 65 ሺ ኢራቃውያን የጦር እሥረኞች መፈታት ማለትም ነው ። ሕዝቡን ከሁሉ በላይ ያሳሰበው የእነዚህ የጦር እሥረኞች ሁኔታ ነው ።

ብዙ ሕዝብ በጦርነቱ ወቅት የነበረው እገዳ እንደሚላላ ፣ በተለይም ከሰባት ዓመት በፊት የተከለከለው ወደውጪ አገር የመጓዝ ገደብ እንደሚነሣ ተስፋ ያደርግ ነበር ። ባግዳድ በበጋ ከመጠን በላይ ሞቃት በመሆኗ ብቻ ሳይሆን ጉብኝት ጥብቅ ቁጥጥር ካለባት ከዚህች አገር ውጥረት ፣ ምንም ያልተጓደለባቸውን ባለጊዜዎች እንኳ ከሚሰማቸው ውጥረት ጉብኝት እፎይታን ያስገኝ ነበር ። ጦርነቱ የመንግሥቱን ጭቆና ተቀባይነት ስለቀነሰው የጦርነቱ መቆም "የበለጠ ዲሞክራሲ" እንደሚያመጣ አንዳንድ ኢራቃውያን ያስቡ ነበር ። ለአገራቸው ሕይወታቸውን ስለሰጡ ፣ ታማኝነታቸውንም ስላሳዩ ፣ ሳዳም የበለጠ ሊያምናቸው እንደሚገባ ይሰማቸው ነበር ።

ሕዝቡ የጦርነቱ ማብቃት ዓይነተኛ ውጤት ይሆናል ብሎ ከጠበቀው ሰላም ፣ ብልጽግናም ሆነ ዲሞክራሲ አንዱም በቀላሉ ሊጨበጥ አልቻለም ። ሆኖም ፣ እንደዚህ ያሉ ሕዝቡ ይሆናሉ ብሎ የጠበቃቸው ነገሮች ፣ ቢጀመሩም ፣ በመንግሥቱ ላይ ትንሽ ተጽእኖ አሳድረዋል ። እርግጥ ፣ የኢራቅ መንግሥት የሕዝብ አስተያየት ተከትሎ ፖሊሲ በማውጣት አያምንም ። ግን ማንም መንግሥት ለረዥም ጊዜ ሕዝቡን ችላ ማለት አይችልም ። በሥልጣን ላይ ለመቆየት የሕዝቡን የልብ ትርታ ማዳመጥ ያስፈልጋል ፣ ይኸንም ይብዛም ለዚህ ቦታ መስጠቱ ጥንቁቅነት ሊሆን ይችላል ።

ከጦርነቱ በኋላ የኢራቅ መንግሥት ትልልቅ ችግሮች ገጥመውታል። መንግሥቱ በኢራን ላይ ከ "ድሉ" አብዛኛውን ቢቀዳጅም ፣ አገሪቱ ከፍተኛ ዋጋ ከፍላበታለች (120 ሺ ተገድሎባታል ፣ 300 ሺ



ቆስሎባታል ፣ በውጪ እዳ ዘፍቋታል) ። ከጦርነቱ ምንም ያኸል አላገኘችም ። ኢራቅ ከኢራን ጋር በሚያዋስናት በመላው ወንዛማ የሻት አልዓረብ የባሕር መተላለፊያ ቦይ ላይ የይገባኛል ጥያቄ አንሥታ ነበር ፣ ኢራቅ ይህን በእጇ አላስገባችም ፣ እናም የባሕር መተላለፊያው ቦይ እንደተዘጋ ቀረ ።

በጦርነቱ ማክተሚያ የኢራቅ ጦር አንድ ሚሊዮን ደረሰ ። ከኢራቅ ዜጎች ላካለመጠን የደረሰው ሰው ሁሉ ለተወሰነ ጊዜ ፣ ብዙው ጦርነቱ በተካሄደበት ጊዜ በሙሉ ፣ በውጊያ ተሳትፏል ። ወታደር በቀላሉ ወደ ገራምነት አይመለስም ። በግምባር ተውማርቶ ሳለ የለመደበትን ሱስ ይዞ ይመለሳሉ ። ብዙ ጊዜ ደጋግሞ ሞትን ስላየ ፣ ድፍረትን ያበዛል ። ውጊያ ሰዎችን ሊሰነዘርባቸው የሚችለውን ኃይል እንደበፊቱ እንዳይፈሩ በማድረግ ግምባራቸው የማይታጠፍ ፣ ራሳቸውም በኃይል ወደመጠቀም የበለጠ እንዲያዘነብሉ ያደርጋቸዋል ።

በጦርነቱ ወቅት ብዙ ዓሥርት ሺህ ወታደሮች ሠራዊቱን ከድተዋል ። ቢያዙ በጥይት መደብደብ ይጠብቃቸዋል ። በሕጋዊ መንገድ ሥራ መሥራት አይችሉም ፣ በአንድ የሽፍታ ቡድን ተደራጅተው በተለይ በአብዛኛው የየብስ መንገድ ለማይገባው ለጥበቃ አስቸጋሪ በሆነው ረግረጋማ ደቡብ ኢራቅ ውስጥ ተሰግስገዋል ። ከጦሩ ከከዱት መኻል ብዙው ለመኖር ሲሉ በዝርፊያና በቤት ሥርሠራ ወንጀል ላይ ተሠማሩ ።

ባግዳድ ፣ ላይ ላዩን ጸጥታ የሰፈነባት ብትመስልም ፣ ከኢራን ጋር ካካሄደችው ረጅምና አድካሚ ጦርነት የመነጨ የሕዝብ ቁጣ ውስጥ ውስጡን ይመዘምዛት ነበር ። በነቂስ ወታደራዊ ከተታንና አጠቃላይ መሥዋዕት የሚያስከትሉ እንደነዚህ ያሉ ጦርነቶች ወትሮም ለከፍተኛ ማኅበራዊ ለውጦች መንሻ ይሆናሉ ። የማኅበረሰቡ የሰው ኃይልና ሀብት በገፍ ለጦርነቱ አስፈላጊ ለሆነ ጉዳይ ስለሚውል ፣ እንዲህ ዓይነት ጦርነት መዋጋት ብቻ እንኳ ለውጥ ያስከትላል ። ለምሳሌ ፣ ሴቶች ከማጀት እየወጡ ከሠራተኛው ኃይል ጋር እንዲቀላቀሉ ይደረጋሉ ። ከዚህም በላይ፣ ሕዝቡ ከቶም የበለጠ አስቸጋሪ መሥዋዕት እንዲከፍል ሲጠየቅ ፣ እሱም በአፀፋው ምን እንደሚያገኝ በጉጉት ይጠብቃል ።

መንግሥቱ ይህን ሁሉ ያውቅ ነበር ። ከተኩስ አቁሙ በኋላ ኢራቅ ልታገኘው ስለምትችለው በከፍተኛ የኢራቅ ባለሥልጣኖች ዘንድ ያለው ጉጉት ሕዝቡ ካለው ጉጉት የበለጠ መለስተኛ ነበር ። ከጦርነቱ በኋላ

የኢራቅ የኢኮኖሚ ሁኔታ እንደሚሻሻል ሕዝቡ ቢገምትም የውጭ ምንዛሪው ችግር እንዳለ እንደሚቀይ ያስጠንቅቅ ነበር ። ባለሥልጣኖች ስምንት ዓመት በጦር ግምባር ሲጋደሉ የቆዩ ሰዎችን መልሶ የማቋቋም ችግር እንደሚኖር ለሕዝቡ ገለጹ ። እንዲያውም ሕዝቡ ለተኩስ አቁሙ እያስፈሰፈ እንዳለ በኢራቅ የፖለቲካ ለውጥ ወይም የፖለቲካ ሁከት እንደሚኖር የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር ጣሪቅ አዚዝ ገና በሰኔ 1980 በጉብኝት ላይ ለነበሩ የዓረብ የፕሮፌሰሮች ልኡካን ነግረዋቸዋል ። "ዘ ዎል ስትሪት ጆርናል" የተሰኘው የኒውዮርክ ጋዜጣ ሁኔታውን፦ "ከባሕረሰላጤው ጦርነት ተኩስ አቁም ሦስት ወር በኋላ ወደ ኢራቅ ዋና ከተማ መመለስ ልክ በአንድ ግብዣ ቤት ተጋባዦቹ መዳከም ሲጀምሩ እንደመድረስ ነው ።" ሲል አሳምሮ ገልጾታል ።

ሰላሙ ራሱ የማይጨበጥ እየመሰለ ነበር ። የኢራን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የኢራቁን የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር አላነጋግር አሉ ። የተ.መ.ድ ያዘጋጀው የሰላም ድርድር መግባባት ወዳልተቻለበት ደረጃ ላይ ደረሰ ። የምርኮኞች ልውውጥም ተቋረጠ ።

ተኩስ አቁሙ ብልጽግናን እንዳላቀዳጀ ታየ ። በእዚህ ፈንታ፣ መንታ ዘርፍ ያለው ኢኮኖሚ ተከሠተ ። በጦርነቱ ወቅት ብቅ ያለ ትንሽ የግል ይዞታ ክፍለ ኢኮኖሚ ያለመጠን በለጸገ ። አብዛኛውን ሠራተኛ ቀጥሮ አሠሪው የመንግሥት ይዞታ ደሀ ነበር ። በ1980 የመንግሥት ይዞታ ሠራተኛ አማካይ የወር ደሞዝ 125 የኢራቅ ዲናር ነበር ። አንድ የዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር በወር 400 ዲናር ያገኛል ። ግን የአንዲት ትንሽ የአትክልት መሸጫ ሱቅ ባለቤት አንድ ሺ ዲናር ያገኛል ። አንዲት የባስራ ከተማ የቡና ቤት ሠራተኛ 1 ሺ 500 ዲናር ስታገኝ አንድ የታክሲ ሹፌር እንኳ ከአንድ ፕሮፌሰር የበለጠ ገንዘብ ይዞ ይገባል ። በየዓመቱ የገንዘቡ የመግዛት ዐቅም በአርባ ከመቶ እያሽቆለቆለ፣ የመንግሥት ሠራተኞች ጦርነቱ ከተጀመረ አንሥቶ ለስምንት ዓመት የደሞዝ ጭማሪ አያውቁም ። የዲናር ይፋ የምንዛሪ ተመን — ሦስት ዶላር — በሕገወጥ ገበያ ከሚያስገኘው ምንዛሪ ከስድስት እጥፍ በላይ ነበር ። የኢራቅ መንግሥት የበለጠ ዶላርና ዕቃ ወዳገሩ ለማስገባት ሲል ሕገወጡን የምንዛሪ ገበያ ሕጋዊ የሆነ ያኸል ልቅ ስላደረገው በትክክልም እንደሆነው ነፃ ገበያ ተሰኝቷል ። በኢራቅ የመንግሥት ይዞታ እንዱስትሪ የሚመረት ሸቀጣሸቀጥ ውድ ባይሆንም፣ እጥረት ነበረበት ። የግል



ይዞታው ክፍል የሚያስመጣው ሸቀጣ ሸቀጥ እንደልብ ቢገኝም የመንግሥት ሠራተኛ ሊገዛ ከሚችለው በጣም በናረው የዲናር የነፃ ገበያ ዋጋ ነበር የሚሸጠው ። ስለዚህም የአንድ የፎቶግራፍ ማንሻ ጥቅል ፊልም 7 ዲናር ወይም 21 ዶላር፣ አንድ የወንድ ሸሚዝ 30 ዲናር ወይም 90 ዶላር፣ አንድ ጠርሙስ የዮርዳኖስ ሻምፑ 4 ዲናር ወይም 12 ዶላር ያስወጣል ። ትንሽ ትልቁ የባዓዝ ፓርቲ አባል በመንግሥት ይዞታ ክፍለ ኢኮኖሚ ውስጥ ይሠራል ። እንደማንኛውም ሌላ ዘጋ ያጉረመርማል ።

በኅዳር 1981 መጨረሻ ግድም የኢራቅና የኢራን የሰላም ድርድር እንደተቀዛቀዘ የንግግር ነፃነት፣ የሕገመንግሥት መሻሻልና ከባዓዝ በተጨማሪ የፖለቲካ ቡድኖችን መመሥረት የሚፈቅድ "ብዙኀዊነት" (ፕሉራሊዝም)ን ጨምሮ በኢራቅ አዲስ የዲሞክራሲ መርሐ ግብር እንደሚዘረጋ ባግዳድ ውስጥ ለተካሄደው የዓረብ ጠበቆች ጉባኤ ሣዳም ሑሴን በድንገት አስታወቁ ። ሦስቱን ጉዳዮች ለማጥናት በከፍተኛ ደረጃ ሦስት ኮሚቴዎች ተቋቋሙ ። ባግዳድ ውስጥ የሚገኘው እያንዳንዱ ኤምባሲ የየአገሩን ሕገመንግሥት ቅጂ ተጠየቀ፣ እናም "ዲሞክራሲ በኢራቅ" አንዱ የመንግሥቱ ፕሮፓጋንዳ ትልቅ ጉዳይ ሆነ ።

በዚሁ የዲሞክራሲ ዘመቻ መንፈስ ነበር ሣዳም ሑሴን ለፕሬስ ነፃነቱ ኮሚቴ ሰብሳቢ የውጪ ጉዳይ ሚኒስትራቸው ጣሬቅ ኦስዬፍ ጃሲምን ስለመገናኛ ብዙኀን ቅሬታ ያስሙት ። ሣዳም ፕሬሱ አሰልቺ እንደሆነ ለጃሲም ነገሯቸው ። ጃሲም የሣዳምን ቅሬታ ላገሪቱ የመንግሥት ጋዜጦች አዘጋጆች ገለጹላቸው ። ፍጹም መካን ከነበረበት ወቅት ጋር ሲነፃፀር፣ በጥቂት በጣም የተወሰኑ መንገዶች፣ የኢራቅ ፕሬስ የበለጠ ግልጽ ሆነ ። ጋዜጦቹ ሁሉ ለአንባብያን የቅሬታ መግለጫ ገጽ ከፈቱ ። በገጹ አናት "ያለፍርሀት ያሻህን ጻፍ" የሚል የሣዳም ሑሴን ቃል ሠፈረ ። በነገራችን ላይ የሶርያ ጋዜጦች ለረጅም ጊዜ በእናታቸው የሀፌዝ አል አሳድን ቃል ያሠፈሩ ተመሳሳይ ገጾች አሏቸው ። ምናልባትም በዐምባገነን መንግሥት የሚመራን አገር አንዳንድ የአመራር ችግር የመከላት ሐሳብ ለማግኘት ሣዳም የደማስቆውን ተቀናቃኞቻቸውን ይመለከቱ ነበር ።

ከሞላ ጎደል ሁሉም ስለአስተዳደር ችግርና ፖሊስ ስለሚፈጽመው በደል ቅሬታን የሚገልጹ ደብዳቤዎች ጎረፉ ። ለምሳሌ የካቲት 30 1981 የአል—ጁምሁሪያ እትም ላይ — በውስጠ ታዋቂ በፖሊስ ትብብር

በጉልህ በመዘርዘር — መኪናው እንዴት በሌቦች እንደተሠረቀች የጻፈው ደብዳቤ ወጣ ። የሁለት የሙት ልጆች እናት እል — ኢራቅ በተባለው ጋዜጣ ላይ ልክ እንደበፊቱ በውስጠ ታዋቂ በፖሊስ ማብረአበር ነት የቤት ዕቃዋ ከቤቷ እንደተሠረቀ ጻፈች ። የቅሬታው ገጽ በፍጥነት ከስፖርቱ ገጽ እንኳን ሳይቀር ፣ የላቀ ተወዳጅ ሆነ ። ነገር ግን ደብዳቤዎቹ ከቶም የፖለቲካ ጥያቄዎችን አያነሡም ። ሆኖም ፣ ሳባህ አል — ላሚ የተሰኘ የኢራቅ ጋዜጠኛ "በችግር ፍርሀት ስም — የመንግሥት ሠራተኞችን አድላዊነት ፣ ጉቦኝነትና መዝባሪነት እንዴት እንዳያነሡ እንደሚደረጉ" በሚል ርእስ በየካቲት 28/1981 ጽሑፍ ማውጣቱ የሚያስደንቅ ድፍረት ነበር ። የዐምባገነንነት ተጽእኖ አስፈላጊ ባደረገው የጥቅሻ ዘዬ በተጻፈው በዚህ ጽሑፍ ሣዳምን በማወደስ ጀምሮ በማወደስ ጨረሰው። ግን የጽሑፍን ድብቅ ይዘት ማንበብ ኢራቃውያን የለመዱ ስለሆነ በላሚ ድፍረት ተደነቁ ። ላሚ ጹሑፉን የጻፈው ጓደኞቹ እልህ ስላጋቡት እንደሆነ ተናግሯል ። ይህን ጽሑፍ ቢያወጣ ሕይወቱንና ነፃነቱን የሚያጣ መሆኑን እንደነገሩትና እርሱም አንድ ሰው በአላህ የሚያምን ከሆነ አላህ የፈጠረውን መፍራት እንደሌለበት ገልጿል ። ላሚ ከዚያም ለመንግሥት ቅርበት ስላላቸው ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ምሳሌያዊ ጥያቄዎች ይጠይቃል — ምን ለማለት እንደፈለገ የተማሩ ኢራቃውያን በቀላሉ ይረዱታል ፦

> ለያት ቅድመለያቶቹ ዝርዝሮች ስለሆኑት ፣ በምሽትና በቀን መኳል በካሬና ዋክ ቢተመንገሥት (የሀብታም ወይም የለስተዳዳሪ መኖሪያ) የሚኖር ፋልክን (ለሞሬ) ስለሆነው (ለናዳጅ ወና) ስለዛርዘር ያውቃሉ! ጓደኞቼም ምናልባት ነጋዴዎች ነበሩ ብለው መለሱ ። እኔ ገን ነጋደ ብልጥ ሰው ነው ብዬ መለስኩ ። ሞኝ ሚሊዮኔር ነጋደ የሆነበትን ጊዜ ለላስታውስም ። ደህና ፣ ጓደኞቼ ካሏን ለንደ በመጠለዙ ሚልዮኔር የሆነውን ባለዐንቁ ጫማ የአገር ኳስ ተጫዋች ታስታውሳለችሁ ... ለሁን ያገሬቱ የለተበልተ ቦታዎች ሁሉ ባለቤት ስለሆነውና አዚህ ገባ ለይባል ስለነበረው ባለለተበልተ ቦታ ለምታችኋል!... ገጣሚ ነው ስለሚሉኘስ ሰውዩ!

ሣዳም እንኳ እንደዛርዘር ሊታዩ ይችላሉ ። የመጀመሪያው ጥያቄ አንድ ለጆሮ የሚከብድ ጥያቄ ያላስባል — ያገሬቱ አመራርና ባለሥልጣኖች ከየት መጡ ፣ በምን መብቱ ሥልጣን ይዞ በሀብት ላይ ለማዘዝ ቻሉ? ሁለተኛው ጥያቄ ሣዳም በዘፈቀደ ባለጸጋ የዳረጉት እድናን ዲሪጋ የተሰኘ



የእግር ኳስ ተጫዋች ይመለከታል ። ሦስተኛው የሣዳምን አጐትና አሳዳጊ ኬይራላ ቱልፋሀን ይጠቅሳል ። አራተኛው በፊተኛው ዓመት በኢራቅ የግጥም ውድድር አንደኝነትን የተቀዳጁትን ሣዳም የሚወዷቸውን ገጣሚ አብደል — ረዛቅ ዋሥብን ።

ሕዝቡ በኢራቅ ጋዜጦች ላይ ከሚገለጸው እኩል እርስ በርሱም ቅሬታውን ያለልማዱ ይገልጽ ገባ ። መንግሥቱ ባገሪቱ ውስጥ የሠረገውን ብሶት በመገንዘብ ሕዝቡን እንዲተነፍስ አበረታታው ፣ ሕዝቡም ተንፈሰ ። በዚያ ወቅት ኢራቅን የጐበኙ ኩዌታውያን እንዲህ በግልጽ ብስጭታቸውን ሲናገሩ ሰምተው ተገረሙ ። አንዳንድ ኩዌታውያን ሣዳም ችግር ላይ እንደሆነና ምናልባትም መንግሥታቸው ይገረሰሳል ብለው አሰቡ ። ግብፃውያን ግን በራሳቸው ታሪክ እያዩት የተለየ አመለካከት ነበራቸው ። የእነርሱ እምነት ኢራቅ ከ1965ቱ የዓረብ እሥራኤል ግጭት በኋላ ግብፅ በነበረችበት የለውጥ ዓይነት ውስጥ እንደምትገኝ ነበር ፣ ከ1959 እስከ 1965 ግብፅ በጦርነት ላይ የምትገኝ ያኸል ነበረች ። ሰባቱ ዓመት የጦርነት ወቅት ቀበቶን ጠበቅ የማድረግ ቁጠባ የሸማቹን ፍላጐት በማይወርድበት ሁኔታ አንነው ። ግብፅ እንደነገሩ ተሳክቶላት የጥቅምት 1965ቱ ጦርነት አስቸኳይ ሁኔታ እንደ ካለፈ በኋላ ሕዝቧ ጠበቅ ያለ የፖለቲካ ቁጥጥሩን ለመቀበል የነበረው ፈቃደኝነት ቀነሰ ። ግብፅ ውስጥ በ1965ቱ ጦርነት ማግሥት ቀስበቀስ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ቁጥጥር ላላ ። ምናልባትም ኢራቅ ከጦርነቱ ማብቃት በኋላ በተመሳሳይ ምክንያትና ሁኔታ ውስጥ እያለፈች ነበር ።

የሚያዝያ 1981 የኢራቅ ብሔራዊ ሸንጐ ምርጫ ውጤት ሣዳም ሑሴን የአኗር ሳዳትን ፈለግ እየተከተሉ ናቸው የሚለውን የግብፆች እምነት አጸናላቸው ። ምርጫው የተካሄደው መንግሥቱ በዲሞክራሲ ዘመቻ ላይ በነበረበት ወቅት ስለነበር ከዚያ በፊት ከተካሄዱ ምርጫዎች ሁሉ የበለጠ ግልጽ ሆነ ። ለምርጫ የታጩት ሰዎች ለሣዳም ታማኝ መሆናቸው በደንብ እየተጣራ የቀረቡ ቢሆኑም ለወቀሳ የማያደርስ ታማኝነት ያለው ሂደት ተከተለ ። ምርጫውን በበላይነት ለመቆጣጠር የብሪታንያን የሸንጐ አባላት ጨምሮ የውጪ ታዛቢዎች ተጋብዘው ነበር።

የፓርቲ አባላት በ1976 ከሸንጐው መቀመጫዎች ካገኙት 75 መቀመጫ በጣም ያነሰውን 40 መቀመጫ ብቻ አገኙ ። በምርጫው ጥቂት

ትልልቅ ባዓዞች ሲሸነፉ ፣ በምርጫው ያሸነፉ ጥቂት ተመራጮች ጥሬት እንደሌላቸው ታየ ። ለምሳሌ የአንድ በጣም የታወቀ ከሀዲ ባዓዚስት እንት በአንድ የባግዳድ የምርጫ አውራጃ ከአንድ የፓርቲ አባል ከፍተኛ ባለሥልጣን ጋር ተወዳድረው 90 ከመቶ ድምፅ አግኝተው አሸነፉ ።

የኢራቅ ብሔራዊ ሸንጎ በዓመት ሁለት ጊዜ ፣ ለሁለት ወር ይሰበሰባል ። ወሳኝነት ያለው አካል አይደለም ። ሆኖም ያለወትሮው የሆነው የምርጫ ውጤት ሳዳም በገለጹት የፖለቲካ ለውጥ ላይ ኢራቆች የነበራቸውን ጥርጣሬ አስወገደ ። አዲስ የተመረጠው ብሔራዊ ሸንጎ የዐደይ ስብሰባው በግንቦት ከመዘጋቱ በፊት አዲስ ሕገመንግሥት ያጸድቃል ብሎ ያመነ ብዙ ሕዝብ ነበር ። ከዚያም ሸንጎው ሐሳብ የመግለጽ ነፃነት በሚሰጥ መንግሥት አዲስ ምርጫ የሚካሄድበትን መንገድ ለማመቻቸት ይበተናል ። የሸንጎ አባላት ሙሉ የምርጫ ዘመናችንን እንሠራለን ብለው አልጠበቁም ።

ሆኖም ምንም የሆነ ነገር የለም ። ምንም አዲስ ሕገመንግሥት አልወጣ ፣ አዲስ ምርጫ የሚካሄድበት መርሀግብርም አልተነደፈ ። የሸንጎው የሥራ ዘመን ባለቀ በሁለት ሳምንቱ ለመንግሥት ሠራተኞች የ25 ዲናር የደሞዝ ጭማሪ ተደርጐ አማካዩን የመንግሥት ሠራተኞች ደሞዝ በ20 ከመቶ አሳደገው ። ነገር ግን በዘጠኝ ዓመት ለመጀመሪያ ጊዜ ያደገው ደሞዝ በአንድ ዓመት የሚደርሰውን የገንዘብ የመግዛት ኃይል ድቀት ወይም የዕቃ ዋጋ ንረት ግማሽ ብቻ ነው የሚሸፍነው ።

በሐምሌ 1976 ሕዝቡ ተስፋ መቁረጥ ጀመረ ። እንደ ኢራቃዊ መንግሥቱ ግራ የተጋባ መሆኑን አሳምሮ ገልጾታል ። በዚህም ገለጻው ምዕራባውያን ተጽእኖውን ማየት እንደተሳናቸው ፣ መንግሥት ሁሉንም ነገር በቁጥጥሩ ሥር ያዋለ መስሎ ቢታይም ምዕራባውያን ላይ ላዩን ብቻ በማየታቸው ነው እንጂ ሕዝቡን እጅ እጅ ስላለው አንድ ቀን በቁጣ ይነሣብኛል የሚል ሥጋት እንዳለበት አስረድቷል ። እንዲያውም ገለጻውን ካደረገበት ዕለት አንድ ሳምንት በፊት በአውቶቡስ መናኸሪያው ሁከት ተነሥቶ እንደነበር ፣ ከአንድ ትልቅ የእስላም በዓል በኋላ ወታደሮች ወደየክፍላቸው እየተመለሱ መሆናቸውን ተናግሯል ። ሁከቱ የተነሣው አንድም በቂ ትራንስፖርት ስላልነበረ ፣ አልያም ሾፌሮች ከፍተኛ ተመን በመጠየቅ በሁኔታው ይጠቀሙ ስለነበር እንደሆነ ምክንያቱን ለመለየት ግን እርግጠኛ አልሆነም ። ያም ሆነ ይህ ሁከቱ



ከቁጥጥራቸው ውጪ ሲሆን የመለሳቸው ወታደሮች ተኩስ መክፈታቸውና ወደጦር ሠፈራቸው ዘግይተው በመመለሳቸው ብርቱ ቅጣት መቀጣታቸው የማይታበል መሆኑ ኢራቃዊው አስረድቷል ። የመንግሥቱም ሥጋት ይኸው እንደነበርና ለውጥ የሚፈልገውም ስለዚህ መሆኑን አያይዞ ደምድሟል ። ሆኖም ለውጡ እንዴት መሆን እንዳለበት ስላላወቀ ፓርቲው እስከዚያች ቅጽበት ድረስ እየተከራከረበት እንደሆነም ከዚሁ ኢራቃዊ ለመረዳት ተችሏል ። ክርክሩም በዲሞክራሲና ከአገር መረጋጋት የቱ ይሻላል በሚል እንደሆነና በዚህም አንዳንዱ ባለፈው ሃያ ዓመት ውስጥ ኢራቅ የተረጋጋች አገር ሆና በለቀየች ዲሞክራሲ አያስፈልጋትም የሚል ሲሆን ሌሎች ደግሞ በተቃራኒው ለአገር መረጋጋት የበለጠ ዲሞክራሲ ያስፈልጋል ባዮች መሆናቸውን ኢራቃዊው ተናግሯል ።

በኢራቅ ብርቱ ችግር መፈጠሩ ቀጠለ ። ነሐሴ 11/1982 ከኢራቅ ሁለት ዋና ዋና የጦር መሣሪያ ማምረቻ ፋብሪካ ፣ ከባግዳድ አርባ ሰምንት ኪሎሜትር በስተደቡብ በአንዱ — በቃቃ የጦር መሣሪያ ፋብሪካ ምስጢራዊ ፍንዳታ ደረሰ ። የምዕራብ ጋዜጦች በዚህ ፍንዳታ 700 ሰው መሞቱን ዘገቡ ። የኢራቅ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር አደጋውን ያስከተለው የዕለቱ ከፍተኛ ሙቀት መሆኑን ቢናገርም የፍንዳታውን ምክንያት ፈጽሞ በአሳማኝ ሁኔታ ማለትም አሻጥር ይሁን አይሁን ፣ ማን እንዳደረሰው ፣ ግዳዩን ምን ያኸል እንዳስቆጣ ከቶም አልተገለጸም ። ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት የሞከረ ፋርዛድ ባዞፍት የተባለ ጋዜጠኛ ተይዞ ከመንፈቅ በኋላ ተሰቀለ ።

መንግሥቱ አምስት ክፍለ ጦር ለመቀነስ መወሰኑን ባስታወቀበት በመስከረም 1983 መጨረሻ ቀስ በቀስ የኢራቅን ጦር የመቀነሱ ሂደት ፍጥነት ጨመረ ። ጦሩን የመቀነስ ውሳኔም መንግሥቱ በኢራን ላይ ከፍተኛ የበላይነት እንዳለው የበለጠ እየታወቀው እንደመጣ እንፀባረቀ ። ይህ በመጀመሪያ ሙሉ በሙሉ አልታየም ነበር ። ጦርነቱ በእርግጥ ስለ ማብቃቱ የኢራቅ ሕዝብ የበለጠ የተማመነው ኾሚኒ በሰኔ 1982 ካረፉ በኋላ ቢሆንም ፣ ከተኩስ አቁሙ በኋላ በነበሩት የመጀመሪያ ጥቂት ወራት የኢራቅ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ስለኢራን ሐሳብ ጥርጣሬ እንዳላቸው ይናገሩ ነበር ።

ምክንያቱ የኢራቅ ጦር ቅነሳ በመጣደፉ ይሁን ወይም ከእርሱ ጋር በመገጣጠሙ ብቻ ይሁን ኢራቅ ውስጥ በተሠማሩ ግብጻውያን የተልበት

ሠራተኞች ላይ ወዲያው አሳዛኝ ችግር ተፈጠረባቸው ። ኢራቅ ውስጥ ሁለት ሚሊዮን ያኸል ግብጻውያን በሥራ ላይ ተሠማርተው ይኖሩ ነበር ፣ ግን በድንገት ኢራቃውያን ግብጻውያኑን ይገድሉ ጀመር ፣ የኢራቅ መንግሥትም እየጨመረ የመጣ በዜጐቹ የሚገደሉ ግብጻውያንን አስከሬን መልሶ ወደካይሮ መላክ ጀመረ ። በጥቅምት 1983 ከ1ሺ በላይ አስከሬን በአውሮፕላን ወደካይሮ ተመለሰ ። ምንም እንኳን የግብጽና የኢራቅ መንግሥታት ቀውሱን ሊገቱ ቢሞክሩም የኢራቅ መንግሥት ሚና ፈጽሞ ሙሉ በሙሉ ግልጽ አልነበረም ። ኢራቅ ውስጥ በግድያው ላይ ምርመራ ስለመደረጉ የተገለጸ ነገር ካለመኖሩም በላይ ከቶም ለግድያው ተጠያቂ የሆነ የለም ።

ከተኩስ አቁሙ በኋላ ባለፉት ስምንት ወራት ከጦሩ ሲሦ በላይ — 300ሺ ያኸል ወታደሮች ከሠራዊቱ ተሰናበቱ ። ግን ሥራ አልተገኘላቸውም ። አንድ ምዕራባዊ ዲፕሎማት 1981 እንደባተ በሰጡት አስተያየት ሳዳም በወታደር አቀጣጠር ረገድ የሚመጥን የሕግ ረቂቅ ፈለጉ ። ከሠራዊቱ ለሚሰናበቱ ወታደሮች ሥራ ለመፍጠር ኢኮኖሚያቸውን በከፍተኛ የውጪ መዋዕለ ንዋይ አማካይነት ማጎልበት አለባቸው ። ግን ኢራቅ እዳ በእዳ ስለነበረች አከፋፈሏ መልክ የሌለው በመሆኑ ወዳገሪቱ የሚገባ ምንም ያኸል የውጭ መዋዕለ ንዋይ አልነበረም ። በ1982 መጀመሪያ ቁጥራቸው እየጨመረ የመጣ ወጣቶች በባግዳድ አካባቢና በመላ ኢራቅ በሚገኙ ሌሎች ከተሞችና መንደሮች ሲንቀዋለሉ ይታዩ ነበር ።

ታኅሣሥ 27/1982 ሳዳም ሑሴን የዮርዳኖሱን ንጉሥ ሑሴንን በባግዳድ አካባቢ አጅበው በመንገድ ላይ እንዳሉ አቶሞቢላቸው አደጋ ገጥሟት እንደነበር አፈሲሉ የኢራቅ ዜና አገልግሎት ዘገበ ። ሆኖም ፕሬዚዳንቱ በዋና ከተማው በሞተር ብስክሌትና በአቶሞቢል ታጅበው ሲጓዙ ዘወትር ጎዳናዎቹ ለሌላ ተሽከርካሪ ዝግ ስለሚሆኑ አደጋው እምብዛም ከአቶሞቢል በመጋጨት የደረሰ አይመስልም ። ይልቅስ ኮብላይ ኢራቃውያን አራት መኰንኖች ሳዳምን በመትረየስና በሮኬት በሚተኮስ ቦምብ ሊገድሏቸው እንደሞከሩ ያናፈሱት ይበልጥ ይታመናል።

ዓመታዊው የሠራዊቱ ቀን የወታደራዊ ሠልፍ ትርኢት በሚቀተለው ቀን ከድል ቅስቱ በታች በ "ታላቁ የበዓላት አደባባይ" እንዲሆን



ታቅዶ ነበር ። ብዙ ሕዝብ ተጋብዞ ነበር ። ሆኖም በመጨረሻው ደቂቃ ግብዣው ተሠርዞ ብዙው የውጪ ዲፕሎማቶች የሆኑበት የተወሰነ ተጋባዥ በተገኙበት የኢራቅ ጦር ሳዳም ሑሴን ረጅም ክንዳቸውን እንዳነሡ በፊታቸው በሰልፍ አለፈ ።

ከተኩስ አቁሙ በኋላ ባለፉት የመጀመሪያ ዓሥራ ስምንት ወራት ሳዳምን የገጠማቸው ችግር ብርቱ ነበር ። ሌላም ዘንድ የሚከሠተው ሁኔታ አደገኛ ነበር ። በጥቅምት 1980 የዋጋን ውድነት የመቃወም ሁከት አልጄሪያ ውስጥ ተነሣ ። የአልጄሪያ ጦር ሁከተኞውን ለመበተን ሲሞክር አብዛኞቹ በ10ና በ20 ዓመት ዕድሜ መኻል የሆኑ ከ150 እስከ 300 ሰዎች እንደተገደሉ የምዕራብ የዜና ምንጭ ገምቷል ። ከአምስት ወር በኋላ ፣ በመጋቢት 1981 በጐረቤቷ በዮርዳኖስ እንደገና የዋጋን ውድነት በመቃወም ሁከት ተነሣ ። የሁለቱም አገር መሪዎች ሰፊ የፖለቲካ ለውጥ እንደሚያደርጉ ተስፋ በመስጠት የሕዝባቸውን ቁጣ አበረዱት ። በአልጄሪያና በዮርዳኖስ ወዲያው አግባብ ያለው ግልጽ ምርጫ ተካሄደ። በዓረብ አገሮች ዲሞክራሲያዊ ለውጥ ምን ሊያስከትል እንደሚችል ዓይነተኛ ፈር ቀደደ ። በኢራቅ ምንም ተመሳሳይ ነገር አልሆነም ።

ከዚህም በላይ በ1981 መኸር ወራት የምሥራቅ አውሮፓ ኮሙኒስት መንግሥታትን መገርሰስ ኢራቅ አይታለች ። በጥቅምት 1982 መጀመሪያ ሳምንት የሆንጋሪ መንግሥት ሲገረሰስ ፣ እናም በታኅሣሥ 1982 መጨረሻ ሳምንት ኒኮላይ ቻውሴስኩ ተፈንቅለው በጥይት ሲደበደቡ ፣ ሦስት ሌላ ኮሙኒስት መንግሥታት ተገርስሰዋል ። በዓለም ዙሪያ ጽኑ መሠረት የነበራቸው ይመስሉ የነበሩት የነዚህ መንግሥታት መገርሰስ በመላው ዓለም መገረምንና መደነቅን አስከተለ ። ኢራቅ የምሥራቅ አውሮፓ አገር ያለመሆኗ እርግጥ ቢሆንም ግን እዚያ እንደነበሩት መንግሥታት በአንድ ፓርቲ መንግሥት ትመራለች ። ሳዳም በተለይ ልክ እንደቻውሴስኩ ለቤተዘመዳቸው ጥቅም ሲሉ አገራቸውን በአፈናና በግድያ በመምራታቸው ኢራቅን ከሮማንያ ጋር አመሳስለዋታል ።

የምሥራቅ አውሮፓ መንግሥታት መገርሰስ ሳዳምን እንዳሳሰባቸው ማስረጃ አለ ። በአንድ ቃለመጠይቅ ምላሻቸው ሳዳም ለአሜሪካ ቀበርጭት ሬዲዮ ጣቢያ (ኤቢሲ) ጋዜጠኛ ለሶውየር "እኔ ቻውሴስኩ አይደለሁም" ሲሉ ሦስቴ ደጋግመው ተናግረዋል ። ኢራቅ ኩዌትን

በወረረችበት ዕለት ዋዜማ ለአሜሪካዋ አምባሳደር ለኤፕሪል ግላስፒ ይህንኑ ቃል ደግመውላቸዋል ። በኑቂስ የወጣ ሕዝብን መቆጣጠር እንዴት እንዳልተቻለና የደኅንነት አገልግሎቱን ተግባር ማቀናጀት እንዴት እንዳልተቻለ ለመገምገም ቻውሴስኩ እንዴት እንደተፈነቀሉ የሚያሳይ የቪዲዮ ክር እንዲያዩ የሩማንያ መንግሥት ከተገረሰሰ በኋላ ሣዳም የባዝ ፓርቲ ባለሥልጣኖችን ማዘዛቸው "ዘ ኦብዘርቨር" ዘግቧል። ግን ይህ ያልተለመደ ድርጊት ያልተጠበቀ ጦስ አስከትሏል ። የኢራቅ ደኅንነት ባለሥልጣኖች ራሳቸውም አንዱን ሌሊት እንደሩማንያ ደህንነት ባለሥልጣኖች ሊጠቁ እንደሚችሉ በድንገት በመገንዘባቸው ወኔያቸው ተሰለበ።

በኅዳር 1981 ሣዳም ለኢራቅ የዲሞክራሲ መርሀግብር መንደፋቸውን መጀመሪያ ሲያስታውቁ የሰሙ አንድ ከፍተኛ ዓረብ ጠበቃ የገቡት ቃል የት እንደደረሰ ፕሬዚዳንቱን በየካቲት 1982 ይጠይቋቸዋል ። ሣዳምም ሲመልሱላቸው በምሥራቅ አውሮፓ እንዳዩት ፣ ዲሞክራሲ ዓይነተኛው ምርጫ ላይሆን እንደሚችል ይናገራሉ ። ወደፊት እንዴት መራመድ እንደሚኖርባቸውም ጥንቃቄ የሚያሻቸው መሆኑንም አስገንዝበዋቸዋል ። ምሥራቅ አውሮፓ ማንኛውም የድጐማ ለውጥ መርሀግብር በቀላሉ ከቁጥጥር ሊወጣና በመስተዳድሮች ላይ ውድቀት ሊያስከትል እንደሚችል ያለጥርጥር አሳየ ። በኢራቅ ሣዳም በዲሞክራሲ ረገድ ምንም ተጨማሪ ነገር ለማድረግ እቅድ የሌላቸው መሆኑን ነው ጋዜጠኞቹ ከመልሱ የተረዱት ።

ሆኖም የኋላ ኋላ የቻውሴስኩ ውድቀት ፣ እናም ይህ በሆነ በጥቂት ቀናት ውስጥ በእርሳቸው ላይ የተቃጣው የግድያ ሙከራ ከተኩስ አቁሙ በኋላ ሕዝባቸው ላነሣው ጥያቄ ሣዳምን የመጀመሪያ ቀና መልስ እንዲሰጡ አስገደዳቸው ። ጥር 9/1982 በጦርነቱ ወቅት በውጪ አገር ጉዞ ላይ ተጥሎ የነበረው እገዳ ተነሣ ። በዚሁ ጊዜ ግድም ከውጪ የገባ ሸቀጣሸቀጥ ከመንግሥት መጋዘን እየወጣ የባግዳድን ገበያ እያጥለቀለቀ እያለ ሣዳም በልታይ ባይነት ለግብይት ወጡ ። ሆኖም ኢራቅ ለፍጆታ ፣ ከውጭ አገር ለሚገባውም ሆነ ወደውጪ ለመጓዝ የምትከፍለው የውጪ ምንዛሪ አልነበራትም ። እንዲያውም ከተኩስ አቁሙ በኋላ ኢኮኖሚው መሟሟቱን ቀጥሏል ። ኢራቅ በተጨማሪ 10 ቢሊዮን ዶላር እዳ ውስጥ ስትዘፈቅ የዲናርም የምንዛሪ ዋጋ ይብስ ቀነሰ ።



ሣዳምን ከአብዛኞቹ መሪዎች የበለጠ በሥልጣን ላይ ለመቆየት ገንዘብ ያስፈልጋቸዋል ። ሕዝባቸውን አደብ እንዲገዛ ለማድረግ ማንኛውንም የሚነሣ ግርግር ጸጥ ለማድረግ ገንዘብ ያስፈልጋቸዋል ። ለሕዝባቸው አይበገሬ ኃይላቸውን ለማሳየት ዕፁብ ድንቅ የጦር መሣሪያ ሥራ መርሀግብር ጨምሮ ለግዙፎቹ ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቁ የክብር መጠበቂያ ፕሮጀክቶቻቸው ማስጠበቂያ ገንዘብ ያስፈልጋቸዋል ። ለሣዳም በዕረፍት የለሽ እንቅስቃሴና ተዝለፍልፎ በመውደቅ መኻል ምንም ያኽል ልዩነት የለም ። ልክ ብስክሌት እንደሚነዳ ሰው ናቸው ። በጣም ጠባብ መቀመጫ ላይ በመቀመጥ ሣዳም አንድም ወደፊት ይንቀሳቀሳሉ ፣ ወይም ይወድቃሉ ።

## ፳

# ልዩው ግንኙነት

የአሜሪካ ፖሊሲ አውጪዎች የማዳምን ቀልጣፋ የኃይል ሚዛን የመጠበቅ እንቅስቃሴ በአገሪቱ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ሰባተኛ ፎቅ (ወለል) በሚገኘው የጦር ኃይሎች (ፔንታጎን) ጠቅላይ እዝ ፣ በብሔራዊ ደህንነቱ ባለጣውላ ቢሮዎች ውስጥ ሆነው ለዘመናት ተከታትለዋቸዋል። በመጀመሪያ አሜሪካ "ታላቋ ሰይጣን" የምትላትን ኢራንን በለያዘላት ትልቅ አርዶታ ነበር። እንደ አያቶላ ኮሚኒው ሳይሆን ፣ ሳዳም ምንም ምሕረት የለሽ ቢሆኑም አሜሪካ ልትግባባቸው የምትችል መሰለ ፣ እናም የአሜሪካ መንግሥት የኢራቁ መሪ ባይጥሙትም መኖራቸውን አልጠላውም ። ነገር ግን "ብስክሌት እሽከርካሪው" ሳዳም የጨበጡትን መልቀቅ እንደጀመሩ መግባባቱ ወደሥጋት፣ ተለወጠ ። በዚህም በአሜሪካ ዲፕሎማሲ ውስጥ አንድ በጣም ያልተለመደ ግንኙነት ተከሠተ ።

በግንኙነቱ ላይ ያለውም ችግር በአሜሪካ ወዲያው "በቁርጥ ሐሳብ" በመባል ይታወቅ ጀመረ ። በአሜሪካና በኢራቅ መካከል ጠላትነት ፣ መቀዛቀዝ፣ መቀራረብ ፣ ቅር መሰኘት ፣ መደጋገፍ ፣ እንዲሁም ከዕውንታ በራቀ መልክ እንዲሁ ከሌላው ብዙ በመጠበቅ በተለዋዋጭ ክሥተቶች ላይ የተመሠረተ የአርባ ዓመት ግንኙነት ታሪክ አለው ። በሁለቱ አገሮች መኻል በዚህ መልክ ጸንቶ የኖረው ግንኙነት ከበፊቱ ጨርሶ ወደተለየ አዲስ ምዕራፍ የተሸጋገረው በ1970ዎቹ መባቻ በኢራንና በኢራቅ ጦርነት ወታደራዊ ዘመቻው በመንገዳገድ ላይ ሳለ የኢራቁ መሪ አሜሪካና ሌሎች የዓረብ አገሮች ከጐናቸው እንዲሰለፉ ማግባባት በጀመሩበት ወቅት ነው ። አሜሪካ ፣ ኢራቅ ትሉ ድል እንዳትመታ በተደረገ ጥረት የተሻለ ግንኙነት ቀስ በቀስ በምባኅንኑን አለዝቦ ከዚህ ቀልፍ የክልል ኃያል መንግሥት ጋር እንዲያውም ቀረብ ያለ ትብብር ማድረግ ያስችላል በሚል ተስፋ ዝንኛውን ወደባግዳድ የ"ማዘንበል ሐሳብ" ያፈለቀችው ያኔ ነበር ።



ሆኖም አሜሪካ ከኢራቅ ጋር ላላት ግንኙነት እንዲህ ተስፋ ስታደርግ የኢራቅና የኢራን ጦርነት የመጀመሪያው ጊዜ አልነበረም ። ልክ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማግሥት አሜሪካ ተመሳሳይ ከዕውንት የራቀ ዲፕሎማሲያዊ ሐሳብ ነበራት ። በ1920ዎቹ የአሜሪካ መንግሥት በክልሉ በተለይ እጁን አላስገባም ነበር ። መካከለኛው ምሥራቅ ከመጀመሪያው የብሪታንያ ፣ እንስ ባለ ደረጃም የፈረንሳይ ቅኝ ግዛት ነበር። አሜሪካ በክልሉ እጇን ያስገባችው በአብዛኛው በኢኮኖሚው ውስጥ ነበር ፣ የአሜሪካ ጥቅሞች የተወከሉት በነዳጅ ዘይት ኩባንያዎች ስለነበረ ፣ አሜሪካና እነዚህ ኩባንያዎች ተመሳሳይ እንደሆኑ ተደርገው ይታዩ ነበር ።

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማግሥት አሜሪካ ድል በመቀዳጀቷና ከዚህም ጋር የግድ ተጣምሮ በመጣው የአውሮፓ ከወደርየለሽ የኃይል ማእከልነት መውደቅ አሜሪካ በድንገት አደገች ። ሕዝቧ በአንዳንድ መንገድ በእምነትና በድርጊት ቸር ፣ ርህሩህና ጥሩ ባሕርይ ያለው መሆን ይችላል ። አውሮፓን መልሶ ለመገንባት የማርሻል ፕላን እየተጣደፈ ነበር። በምሥራቅ ግን ከኮሙኒዝም ጋር የቀዝቃዛው ጦርነት ትግል እየበረታ ነበር ። በለሆነም ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ አሜሪካ በመካከለኛው ምሥራቅ የምትከተለው ፖሊሲ የሐሳባዊነትና የፀረ ኮሙኒዝም መግለጫ ነበር ። እርግጥ ፣ አንዳንድ የአሜሪካ ባለሥልጣናት በየአገሮቻቸው የአውሮፓውያን የበላይነት ያከትም ዘንድ የሚፈልጉና የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት የጠየቁ ወጣት ዓረቦችን ተቃዋሚ ቡድኖች ደገፉ ። አንዳንዶቹም ፊዩዳል ዓረብ ነገሥታትና ሌሎችንም የፈላጭ ቆራጭ ግግዎች ማስወገድ የአሜሪካን አመለካከት በሚቀበሉ ግለሰቦች የሚመሩ መንግሥታት ከመፍጠሩም በላይ በዓረቡ መካከለኛ ምሥራቅ ከሁሉም የላቀ ፀረ ኮሙኒስት ተገን ይሆናሉ የሚለውን የተቃዋሚ ዓረቦች ሐሳብ ተቀበሉ።

ብዙ የአሜሪካ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ባለሥልጣናት በ"አብዮት" ስም በጥቂቶች ድጋፍ መፈንቅለ መንግሥት የሚያካሂዱ ወጣት የዓረብ መኰንኖችን ኋላቀር ማኅበረሰቦቻቸውን ዘመናዊ የማድረግ ተልእኮ በመወጣት እንደሚያገለግል አዲስ መካከለኛ መደብ ያዩዋቸው ነበር ። አንዳንዴ የስለላ ድርጅቶች ሳይቀሩ እነዚህን ሰዎች ሥልጣን ላይ ለማውጣት መላ በመምታት ይረዱ ነበር ። ማይልስ ኮፕላንድ የተሰኙ አንድ የቀድሞ የአሜሪካ የስለላ መኰንን "ዘ ጌም ኦቭኔሽንዝ" በተሰኘ መጽሐፋቸው በ1941 በዓረብ ዓለም ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የተካሄደውን የሶርያ ሽንጉጥአዊ መንግሥት ግልበጣ አሜሪካ እንዴት እንዳቀደችው ገልጸውታል ። የግብጽ ነፃ መኰንኖች ንቅናቄ በሐምሌ 1944 መፈንቅለመንግሥት ሲያካሂድ በዋዜማው ሲ አይ ኤ ከእርሱ ጋር

ግንኙነት ፈጠረ ። ነገር ግን በአብዛኛው የአሜሪካ መንግሥት ለንገሥታቱ ማድላቱን ቀጠለ ።

በዓረቡ ዓለም ውስጥ ፣ ነዳጅ ዘይት ያልነበራትን ኢራቅን ጨምሮ ፣ ሁልጊዜም እጅግ አስፈሪ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ፍትሕ መጓደል ነበር ፣ ብዙው ሕዝብ በድንቁርናና በጉስቁልና ኖረ ። ንጉሥታቱ ለረዥም ጊዜ በድኾቹ ማኅበረሰቦች አናት ተቀመጡ ። ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በፊት የሜሶፖታሚያ ስም ሲነሣ ወረርሽኝ አብሮ ይታወስ ነበር ። እዚያ የነበሩት የብሪታንያ ጦር አባሎች በኮሌራ ሞተዋል ። ባግዳድ በወትሮ በጤግሮስ ወንዝ ጐርፍ የምትጥለቀለቅ ቆሻሻ ከተማ ነበረች ። ብሪታንያ በ1913 አልጋ ላይ ያወጣቻቸው ንጉሥ ፈይሳል አገሪቱን በልማት በእጅጉ አራምደዋታል ። የንጉሡ መንግሥት የኋላ ኋላ የጤግሮስን ወንዝ ከመፍሰስ ያገደውን ግድብ ገደበ ። የሕዝቡን ጤናና ትምህርትም በሚያስደንቅ ሁኔታ አሻሻለው ። እና በዋሽንግተን መንግሥት ዓይን የንጉሡ መንግሥት ጽኑ የምዕራቡ ዓለም ደጋፊ ነበር ።

በ1946 ኢራቅ ከአሜሪካ ወታደራዊ እርዳታ ተቀብላ በየካቲት 1947 በሌሎች ዓረብ አገሮች ክፉኛ ወደተተቸውና በአሜሪካ አስተባባሪነት ቱርክ ፣ ኢራን ፣ ፓኪስታንና ዩናይትድ ኪንግደም (የታላቋ ብሪታንያና ሰሜን አየርላንድ) ባግዳድ ውስጥ ወደተስማሙበት — የባግዳድ (የጋራ መከላከያና ትብብር) ስምምነት ገባች ።

በ1950 በባግዳድ የጦር ሠራዊት መኰንኖች ምስጢራዊ ድርጅት ንጉሥ ፈይሳልን በመፈንቅለ መንግሥት በገለበጣቸው ጊዜ የአሜሪካ መንግሥት ቅስም ተሰበረ ። አዲሱ መሪ ጀኔራል አብዱል ከሪም ቃሲም ወዲያው ከኢራቅ ኮሙኒስቶች ጋር የቅርብ ግንኙነት መሥርተው በ1951 ከአሜሪካ የሚያገኙትን ወታደራዊ ድጋፍ ሠርዘው ከባግዳዱ ስምምነት ወጡ ። አዲሱ መንግሥት ከምዕራብ ገለልተኛ ነፃ ፖሊሲ ለመቅረጽ ያደረገውን ሙከራ ሶቪየት ኅብረት አደነቀች ። ኢራቅና ሶቪየት ኅብረትም በ1950 ዲፕሎማቲክ ግንኙነታቸውን አደሱ ፣ የሶቪየት ገንዘብና ጦር መሣሪያ ወዲያው ወደኢራቅ ይጎርፍ ጀመር። ነገር ግን ቃሲም ለሕዝባቸው የገቡትን ቃል ማክበር አልቻሉም ። ሲአይኤ የተመረዘ መሀረብ በመላክ ቃሲምን ሊገድላቸው እንደሞከረው ዓይነት መንግሥታቸው ራሱን ለመከላከል ሲል የባሰ ጨቋኝና ያልተረጋጋ ሆነ። አሁንም ፣ የዮርዳኖሱ ንጉሥ ሑሴን እንደገለጹት ፣ በሲአይኤ እርዳታ በ1955 ባዓዞች ላጭር ጊዜ ሥልጣን እስከያዙ ድረስ እስኪያታክት ባለማቋረጥ አንዱ ያልተሳካ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ሌላውን እየተካ ሄደ ። ሲአይኤ ያን ጊዜ የኮሙኒስቶችን ዝርዝር ለባዓዞች እየሰጠ ያሳድናቸው ፣ ቁም ስቅላቸውን እንዲያዩና እንዲገደሉ ያስደርጋቸው ነበር ይባላል ።



በ1959 (በዓረቦችና በእስራኤል መኻል የተካሄደው) የስድስት ቀን ጦርነት የኢራቅን ከአሜሪካ ጋር ሙሉ በሙሉ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ማቋረጥ አስከተለ ። ባዓዝ ፓርቲ በ1960 በሥልጣን ላይ ለመቆየት ተመልሶ ከወጣ በኋላ ኢራቅ ከእስራኤልም ሆነ ከአሜሪካ ጋር ድርድር ለምኑ ብላ ከዋናዎቹ "እምቢ ባይ" አገሮች አንዷ ሆነች ። በ1964 ኢራቅ ከሶቪየት ኅብረት ጋር የነበራትን የወዳጅነት ግንኙነት ሥነሥርዓት ያስያዘውን የዓሥራ አምስት ዓመት የወዳጅነትና የትብብር ስምምነት ተፈራረሙ ።

ነገር ግን በ1967 ኢራቅና ሶብየት ኅብረት ተቻከሉ ። የኢራቅ ጦር ኩርዶችን ካጠቃ በኋላ ሶቪየት ኅብረት ወደኢራቅ ጦር መሣሪያ መላክ አቋረጠች ። አሜሪካ አሁንም እንደገና ቀዳዳ እንደተከፈተ ተሰምቷት ከኢራቅ ጋር መደበኛ ግንኙነቷን ለማደስ ያላትን ፍላጐት አሳየች ። ጥየቃው ቸል ተባለ።

የሆነ ሆኖ በ1971 ኢራን ውስጥ አያቶላ ሩሆላህ ኾሚኒ ሥልጣን ሲይዙ አሜሪካና ኢራቅ ተደናገጡ ። በአሜሪካ ሸንጐ የምርምር አገልግሎት የመካከለኛው ምሥራቅ ጉዳይ ዐዋቂው ሪቻርድ እም ፕሬስ በኅዳር 1972 ቴህራን ውስጥ የኢራን ተማሪዎች ከኀምሳ በላይ አሜሪካውያንን ከኤምባሲያቸው አግተው ከያዙ በኋላ የኢራቃውያንና የአሜሪካውያን ዲፕሎማቶች ግንኙነት እየጨመረ እንደሄደ መዝግበዋል ። እናም ሚያዝያ 4/1973 የአሜሪካ ረዳት ተጠባባቂ የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር ሞሪስ ድሬፐር ባግዳድ ውስጥ ከኢራቅ ባለሥልጣናት ጋር ተገናኝተው በሰሁለቱ አገሮች የወደፊት ግንኙነት ፣ የኢኮኖሚ ጥምረት ፣ እንዲሁም በክልሉ የሶቪየትን ተስፋፊነት ለመቋቋም የሚያስችል "ስትራቴጂያዊ ጠቅላላ ስምምነት" ለመፍጠር የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር አሌክሳንደር ሄግስ ስላወጡት እቅድ ተነጋገሩ ። አሁንም እንደገና አሜሪካ ከኢራቅ ጋር ያላትን ግንኙነት ለማሻሻል የነበራት ተስፋ ለመለመ ። እስራኤል በ1973 (በአሜሪካ በተሠሩ አውሮፕላኖች የአሜሪካን ጦር መሣሪያ ጭነው) ኢራቅ ከፍተኛ ተስፋ የጣለችበትን የኑክሌር ንጥረ ነገር ማመንጫ ፋብሪካ ከአየር ደብድባ ብታወድምም የኢራቅና የአሜሪካ ግንኙነት ቀጠለ ።

ነገር ግን የኢራቅና የአሜሪካ ዕውነተኛ ግንኙነት የተጀመረው ሳዳም በ1972 ኢራንን ከወረሩና ጦርነቱም ለኢራቅ መጥፎ እየሆነባት መሄድ ከጀመረ ወዲህ ብቻ ነው ። በ1973 እና በ1974 በጦርነቱ ይገኝበት የነበረው ወታደራዊ ሁኔታ አስተማማኝነት እያጣ እንደሄደ ከአሜሪካ ጋር ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነታቸውን ለማስፋፋት ፍላጐት እንዳላቸው ሳዳም ደጋግመው ገለጹ ። እስከ 1974 ኢራን በፋኦ የሚገኘውን የኢራቅ ትልቅ የነዳጅ ዘይት ማመንጫ ተቋም እንዳልነበረ አድርጋ የአገሪቱን ሁለተኛ

ትልቅ ከተማ ደቡባዊቷን የባስራ ወደብ ለመክበብ ኢራቅ ግባት ገባች ። በዚያው ጊዜ ውስጥ ሶርያ በክልሏ አቋርጦ የሚያልፈውን የኢራቅ ነዳጅ ዘይት ቧንቧ ቆረጠች ። በዚህም ኢራቅ የገቢ ምንጭ በቱርክ በኩል ወደውጪ የምትልከው ነዳጅ ዘይት ብቻ ሆነ ። በሬጋን ፕሬዚዳንትነት ዘመን በወቅቱ የአሜሪካ ብሔራዊ የደኅንነት ምክር ቤት የመካከለኛው ምሥራቅ ጉዳይ ክፍል ኃላፊ የነበሩት ጂኦፈሪ ኬምፕ በወቅቱ እንዳሉት የታጋቾች ትዝታ አሁንም እንዳለ ነው ፤ አያቶላው አሁንም አሜሪካን "ታላቁ ሰይጣን" እያሏትና የመላውን ባሕረሰላጤ አገሮች መንግሥታት ለማናጋት እየሞከሩ መሆናቸውን ተናግረዋል ። አያይዘውም አሜሪካ ኢራቅ በጦርነቱ እንድታሸንፍ ስለፈለገች ሳይሆን ኢራቅ እንድትሸንፍ ስላልፈለገች መሆኑን ገልጸዋል ።

አሜሪካ ለኢራቅ ድጋፍ ለመስጠት ዓትታ በነበረበት መጠን ሣዳምም ለዚህ ምስጋና የሚያቀርቡ መሆናቸውን አረጋገጡ ። ነገርግን አንድ ትልቅ መሰናክል ነበረ ። በሮምና በቪየናም አውሮፕላን ማረፊያ በ1977 እጅግ የሚዘገንን አደጋ ሊጥል የነበረው አቡ ኒዳል ባግዳድ ውስጥ ይኖሩ ከነበሩ እያሌ ዕውቅ አሸባሪዎች መኻል አንዱ ነበር ። የአሜሪካ ሕግ ደግሞ በአሸባሪነት ዝርዝሩ ውስጥ ላሉ አገሮች ዱቤና ብድር መስጠትንና ብዙ ግንኙነትን መፍጠርን ያግዳል ።

የኢራቅና የአሜሪካ ባለሥልጣናት ብዙ ከተማከሩ በኋላ ፤ አቡ ኒዳል አንዳንድ ሰዎቹንና ቁሳቁስ ባግዳድ ውስጥ አስቀርቶ ጽሕፈት ቤቱን ወደደማስቆ አዛወረ። የአሜሪካ መንግሥት ሸንጐውን ሳያማክር በመጋቢት 1974 ኢራቅ ከአሸባሪዎቹ ዝርዝር እንድትወጣ ተደረገ ። ያኔ በአሜሪካ መከላከያ ሚኒስቴር የፀረ አሸባሪነት መምሪያ ዲሬክተር ኖኤል ኮህ "ዚ ዋሽንግተን ፖስት" ለተሰኘው ጋዜጣ እንደነገሩት ኢራቅ ከዝርዝሩ የወጣችው የአሸባሪዎች መጠጊያነቷን ስለተወች አልነበረም ። ኮህ እንዳሉት ኢራቅ በአሸባሪነት ውስጥ እጇ እንዳለበት የሚጠራጠር ማንም ባይኖርም ከዝርዝሩ እንድትወጣ የተደረገበት ዕውነተኛ ምክንያት ከኢራን ጋር በተያያዘችው ጦርነት እንዲሳካላት ለመርዳት ነው ።

አቡ ኒዳል ሄዶ ነበር ፤ ግን ሌሎች አልሄዱም ። ከሊባኖስ ተገፍተው የወጡ አሚፋሪ የፍልስጥኤም ነፃ አውጪ ድርጅት አክራሪ ቡድኖች 1972 እንደባተ ኢራቅ በስደተኛነት ተቀበለቻቸው ፤ በ1977 "አኪሌ ላውሮ" የተባለችውን ወጪ ወሬጅ (ክሩዝ) መርከብ ጠልፉ ያቀደውን አቡል አባስን ኢራቅ በመቀበል ተይዞ ለፍርድ እንዳይቀርብ ረድታዋለች።

ኢራቅ ከአሸባሪነት ዝርዝር መሠረዟ ሣዳምን በጣም የፈለጉትን እርዳታ ለማግኘት አስፈላጊውን ሁኔታ እንዳሟሉ አስቆጠራቸው ።



በታኅሣሥ 1975 በአሜሪካ የግብርና ሚኒስቴር የሸቀጣሸቀጥ ዱቤ ኮርፖሬሽን ለኢራቅ ሩዝና ስንዴ እንዲሸጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ለ300 ሚሊዮን ዶላር ያኸል ዋስትና ለመስጠት ተስማማ ። ኮርፖሬሽኑ የሰጠው ዱቤ እየባሰ የሄደ የገንዘብ እጥረት ለገጠማት ለኢራቅ ትልቅ ነገር ነበር ። በስምምነቱም መሠረት ኢራቅ ብድሩን ለመክፈል የሦስት ዓመት ጊዜ ተሰጥቷታል ፤ እናም ኢራቅ ባትከፍል ፤ የአሜሪካ መንግሥት እዳውን የመክፈል ግዴታ ገብቷል ።

ሣዳም አሜሪካን ማባበላቸውን ቀጠሉ ። በ1975 ሣዳም በአሜሪካ ምክር ቤት የውጪ ጉዳይ ኮሚቴ ውስጥ የድርጅት ጉዳይ ሠራተኛ ከሆኑት የኒውዮርክ እንደራሴና እንዲሁም የእሥራኤል ጠንካራ ደጋፊ ከሆኑት ከስቲፈን ሶላርዝ ጋር ተገናኝተው የእሥራኤልን የመኖር መብት መሠረተ ሐሳብ ተቀበሉ ። ምናልባት ይህን እንደምስጢር ቆጥረው ለአሜሪካ መንግሥትና ለአሜሪካ አይሁድ ማኅበረሰብ ላለመግለጽ የወሰኑ እንደሆን በማለት ሶላርዝ እንደጋል ግንኙነት የቆጠሩትን ኢራቅ በዜና አገልግሎቷ አማካይነት አሰራጨችው ። ከዚህም በኋላ በግንቦት 1975 ከአሜሪካ የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር ጆርጅ ሹልዝ ጋር ግንኙነት የተደረገ ሲሆን በዚያው ዓመት በጥቅምት 1976 የኢራቅ ረዳት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ወደ ዋሽንግተን ተልከዋል ።

ጂኦፈሪ ኬምፕ እንዳሉት ሬጋን ፕሬዚዳንት እንደሆኑ ኢራቅን በሚመለከት የአሜሪካ ፖሊሲ ምን መሆን እንዳለበት በከፍተኛ ደረጃ ጥናት ቢደረግም ፤ ግን በመሠረቱ በካርተር አስተዳደር ዘመን የነበረው ፖሊሲ ተግባራዊ ሆነ ። ከዚያ በኋላ ፤ በጦርነቱ ኢራቅ እየተዳከመች ስትሄድ ፤ የአሜሪካ መንግሥት ይህ ፖሊሲ እንዲገመገም ወሰነ ። እንደፕሬስ አባባል ፤ የአሜሪካ ብሔራዊ ደኅንነት ምክር ቤት በጥቅምት 1976 ያካሄደው አንድ ጥናት ኢራን ድል ብትመታ በክልሉ የአሜሪካ ጥቅም ብርቱ ጉዳት ላይ የሚወድቅ መሆኑን ደመደመ ። ነገር ግን ፤ አሜሪካ በግጭቱ ውስጥ ወገን እንዳልለየች ገለልተኛ ተደርጋ በይፋ ስለምትታወቅ ኢራቅን በቀጥታ ለመርዳት ልታደርገው የምትችለው ምንም ነገር እንደሌለ በጥናቱ ተጠቅሷል ። ሆኖም በተዘዋዋሪ መንገድ እርዳታ ሊሰጣት ይቻል ስለነበር ወዲያው ተሰጣት ። በሬጋን አስተዳደር ውትወታ ፤ የባሕረሰላጤው አገሮች ለኢራቅ የሚሰጡትን ድጋፍ ለመጨመር ሞከሩ ።

በኅዳር 1977 ፤ ወዲያው ፕሬዚዳንት ሬጋን እንደገና በተመረጡ ማግሥት አሜሪካ ከኢራቅ ጋር ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ሙሉ በሙሉ አደሰች ። የሁለቱን አገሮች የስለላ ድርጅቶች ግንኙነት ጨምሮ ትብብሩ ጠበቀ ። ኢራቅ ለሲአይኤ ከሰጠችው መረጃ አብዛኛው ፤ ማለትም በእጀ

ስለሚገኘው የሶቪየት መግሪያና ስለአሸባሪነት ፣ ፋይዳቢስ ሆኖ መገኘቱን አንድ የአሜሪካ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ባለሥልጣን ተናግረዋል ። ነገር ግን የ"ቀሽንግተን ፖስት" ዘጋቢው ቦብ ውድዎርድ በ1978 እንደዘገበው ኢራቅ ፣ በበኩሏ ፣ ዘመቻዋን አቅዳ እንድታካሂድ የረዳት የኢራንን ጦር እንቅስቃሴ የሚያሳይ ከሳታላይት ፎቶ የተቀረመ መረጃ ተሰጥቷታል ። በሌላ በኩልም ፣ (ግጭቱን ለማብረድ ድርድር አልቀበልላለችው) ለኢራን ጦር መግሪያ የሚሸጡ አገሮች ይህን እንዲያቋርጡ የማግባባት ዓላማ የነበረው "አይበገሬ ዘመቻ" ውጤት ማስገኘት ጀመረ።

ኢራቅ ነዳጅ ዘይቷን በሳዑዲ ዓረቢያ በኩልም ወደ ውጪ ለመላክ በ1978 ሌላ የቧንቧ መሥመር ብትዘረጋም በዚያ ጊዜ በአደገኛ የገንዘብ ይዞታ ላይ ነበረች ። ኢራቅ ለአሜሪካ ከከፈለችው ዕዳ በስተቀር ከማንኛውም ሌላ አገር የተበደረችውን ገንዘብ ቃሏን ጠብቃ ሙሉ በሙሉ በወቅቱ የከፈለችበት ጊዜ የለም ። ኢንተርናሽናል ባንኮች ፣ ተበዳሪ አገሮች የዕዳ አከፋፈል መርሀግብር እንዲሻሻልላቸው ሲጠይቁ የጋራ ድርድር ቢመርጡም ፣ ኢራቅ ዕዳዋን ለመክፈል ከአበዳሪ ባንኮችና አገሮች ጋር በተናጠል ካልተደራደርኩ ብላ ችክ አለች ። የሌሎች አገሮች ባንኮች ለኢራቅ ብድር የመስጠት ገደብ ቢጥሉባትም የአሜሪካ ባንኮች አልተባበሯቸውም ።

ኢራቅ ከአሜሪካ ግብርና ሚኒስቴር የሸቀጣሸቀጥ ዱቤ ኮርፖሬሽን በዱቤ የምትገዛው እኽል ከአራት ዓመት በፊት ከነበረበት 215 ሚሊዮን ዶላር በ1979 በአስደናቂ ፍጥነት ወደ 567 ሚሊዮን ዶላር አሸቀበ ። የግል ባንኮችም ኢራቅን ረዱት ። በተለይም ባንካ ናዚዮናሌ ዴላቮሮ የተሰኘው ኢጣሊያዊ ባንክ የአትላንታ ቅርንጫፍ በ1975 እና በ1982 ፣ 3 ቢሊዮን ዶላር ያኸል ብድር እንድታገኝ አመቻችላት ። ኢራቅ የአሜሪካን ሰንዴ በብዛት በመሸመት በዓለም አምስተኛዋና በብዛት ከሁሉም አገር የበለጠ የአሜሪካ ሩዝ ሸማች አገር ብትሆንም ይህ ሁሉ የብድር ገንዘብ ለስንዴና ለሩዝ ሸመታ አልዋለም ። "ዘ ፋይናንሺያል ታይምስ" የተባለው ጋዜጣ በ1982 እንደጻፈው ለአበዳሪው ባንክ የደረሰው አንዳንዱ የዱቤ ማመሪያ ሰነድ ለወታደራዊ ጉዳይ የታቀደ የሚመስል "ሁለት ጥቅም" የሚሰጥ በጣም አከራካሪ ግዢ ተካሂዶበታል ። በመስከረም 1982 በባንካ ናዚዮናሌ ላይ የቀረበ ክስ በአንድ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲመረመር ነበር ።

ለዘመናት የአቀበትና የቁልቁለት ባሕርያት በነበረው የኢራቅና የአሜሪካ ግንኙነት ኅዳር 1979 ከመቼውም የባሰ ያዘቀዘቀበት ሆነ ። የኢራንና የኮንትራ ግንኙነት ፣ ቅሌትና የሬጋን መንግሥት ለኢራን በምስጢር ጦር መግሪያ የመሸጡ ዜና ግዳዎን አስደነገጣቸው ።



በተከታዩ ዓመት በተገባ አደገኛ ቃል የተጠናከረ በመንግሥት "የብል ሽት ቁጥጥር" በመባል የታወቀ ሂደት በተከታታይ ከልብ ይቅርታ በመጠየቅ ተጀመረ ። ብዙውን የኢራቅ ነዳጅ ዘይት ከኩዌት የሚያጓጉዙ የነዳጅ ዘይት ቦቴ መርከቦችን እንደምታጠቃ ኢራን ከዛተች በኋላ ፣ አሜሪካ እነዚህ የኩዌት መርከቦች የሚያውለበልቡትን ሰንደቅ ዓላማ ለውጣ ደህንነታቸውንም ለማረጋገጥ በባሕረሰላጤው ውስጥ በታጠቁ መርከቦች እንደምታጅባቸው አስታወቀች ። በጣም አከራካሪው የሰንደቅ ዓላማ መለወጥ መርሀግብር አሜሪካ ውስጥ የተጧጧፈ ክርክር አሜረ ፣ ነገር ግን የግዳዎ ሑሴንን ጎዴት አበረደው ።

በ1979 ከአንድ የኢራቅ ጄት የተተኮሰ ፈረንሳይ ሠራሽ ኤክሶሴት ሚሳይል "ስታርክ" የተባለችውን የአሜሪካ መርከብ መትቶ ሠላሳ ሰባት ባሕረኞችን በመግደሉ የሁለቱ አገሮች ግንኙነት ሌላ ያልታሰበ ሳንክ ገጠመው ። ነገር ግን ግዳዎ ፈጥነው እርምጃ ወሰዱ ። ስለደረሰው "አደጋ" የተሰማቸውን ኀዘን በመግለጽ ይቅርታ ጠይቀው በአደጋው ለሞቱት ባሕረኞች ቤተሰብ ሃያ ሰባት ሚሊዮን ዶላር ካሣ ከፈሉ ።

ነሐሴ 1980 የኢራቅና የኢራን ጦርነት በተኩስ አቁም ተፈጸመ ። ኢራን ግዳዎ ሑሴን ከሥልጣን እስከተወገዱ ድረስ እንደምትዋጋ ዝታ ስለነበር ፣ ብዙዎች ተኩስ አቁሙን ኢራቅ ድል የተቀዳጀች ያኸል እንደነበር ተረጉሙት ። አሜሪካ ውስጥ ብዙ ተንታኞች ግዳዎ ወደተበር ጉድጓድ ይመለሳሉ ፣ ጦራቸውን ከግምባሩ ዘመቻ ይመልሳሉ ፣ እናም የደቀቀ ኢኮኖሚያቸውን መልሶ መገንባት ይጀምራሉ ብለው ጠብቀው ነበር ። ግን ይህ አልሆነም ። ከሞላ ጎደል ወዲያው ግዳዎ ያገራቸውን ህዳጣን ኩርዶች በመርዝ ጋዝ አጠቁ ።

የአሜሪካ የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት ጆርጅ ሹልዝ ድርጊቱን እጅግ በከረረ አባባል ነቅፈው ኢራቅ እንዲህ ያለ መግሪያ ከእንግዲህ ላለመጠቀም ቃል እንድትገባ ጠየቁ ፣ ኢራቅም ቃል ገባችላቸው ። ነገር ግን አሁን ጦርነቱ አልቋልና ፣ ብዙዎች ያለ አግባብ ለአንድ ዐምባገነን "መደለል" መስሎ አልታይ ባላቸው ድርጊት ላይ በሸንጎው ውስጥ ተቃውሞው እየጨመረ ሄደ ።

የአሜሪካ ምክር ቤት የውጪ ግንኙነት ኮሚቴ አባል የሆኑት ፒተር ጋልብሬይት በ1979 በኢራቅ የኩርዶች ክልል ባደረጉት ጉብኝት ባዩት ተደናግጠዋል ። ጋልብሬይት ከጉብኝቱ መልስ ያዩትን እንደገለጹት በኩርዲስታን መንደሮች በመደዳ እንዲወድሙ ተደርገዋል ፣ ሥፍራው

"የተወረረ ይመስል" ጭርታና ዱር ወርሶታል ፣ ግርቅጠል ውጦታል ግን በአንድ ወቅት መንደር በመንደርና ሕይወት በሕይወት እናም ሁለት ሚሊዮን ያኸል ሕዝብ የነበረው ክልል በድንገት ወና ነበር ። ከሞላ ጐደል ዘመን መቆጠር ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ የነበሩት መንደሮች እንዳልነበሩ ሆነዋል ። ነዋሪዎቻቸው በጥድፊያ ታላላቅ ከተሞች ዙሪያ ወደተቋቋሙ ማጐሪያ ሠፈሮች ተወስደዋል ።

ከዚያም ኢራቅ የመርዝ ጋዝ አርከፈከፈችባቸው ። በ1980 ሊጸድቅ የቀረበውን የፔል የሕዝብ ጭፍጨፋ መከላከያ አንቀጽ የአሜሪካ የበላይ ምክር ቤት የውጪ ግንኙነት ኰሚቴ ሊቀመንበርና የሮድ ደሴቱ ሊበራል ሴናተር ክሌይቦርን ፔልና ቀንደኛው የሰሜን ካሮላይና ወግአጥባቂ — ሴናተር ጄሲ ሄልምስ ግምባር ፈጠሩ ። የሕግ ረቂቁ ኢራቅ የሕዝብ ጭፍጨፋ ላለመፈጸሟ ፕሬዚዳንቱ ቢያረጋግጡና ኢራቅም ሁለተኛ በመርዝ ጋዝ ላለመጠቀም ቃል የገባች እንደሆን ብቻ ሊነሣ የሚችል የንግድ ማዕቀብ በኢራቅ ላይ ሊያስጥል ይችል ነበር ። የሬጋን መንግሥት የሕግ ረቂቁን ተቃወመ ፣ ሆኖም የበላይ ምክር ቤቱ በአንድ ድምፅ ካሳለፈው በኋላ ተደንግጎ በመውጣቱ ሂደት ላይ በሥነሥርዓት ፖለቲካ ማጥ ውስጥ ገብቶ ቀረ ።

በሌላ በኩልም ፣ የፕሬዚዳንት ምርጫ ውድድሩ ፣ የሬጋንን መንግሥት ከሽባ የባሰ ሽባ አድርጐት መኻል መድረክ ያዘ ። ጆርጅ ቡሽ በፕሬዚዳንትነት ከተመረጡ በኋላ ፣ በአዲሱ መንግሥት ውስጥ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችን ሥልጣን አስመልክቶ ቀልድ ተጀመረ ። እናም አንድ የአሜሪካ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ባለሥልጣን፣—

እና እግሩን መሬት ላይ ለማሳረፍ ጊዜ ፈለገ ፣ በባሕረሰላጤው ላይ በብቃት ያልተተኰረበት ረጅም ጊዜ ነበር ። ያለፈውን ሳስታውስ ባሕረሰላጤውን በተመለከተ አንድም በግልጽ የተቀየሰ ፖሊሲ ያለመኖሩ ወይም እንኳን ምንም ክብደት ያለመስጠቱ መጥፎ አጋጣሚ ነበር ብዬ አገምታለሁ

ብለዋል ።

የኢራቅና የኢራን ተኩስ አቁም በጸና በዓመት ግድም በ1981 በልግ ወቅት በባሕረሰላጤው የአሜሪካ የፖሊሲ አግራጭ ግምገማ የኋላ ኋላ ተግባራዊ ሆነ ። ወትሮ እንዲህ ዓይነቱ ዓይነተኛ የፖሊሲ ሰነድ ሲረቀቅ በበላይነት የሚቆጣጠሩት የቅርብ ምሥራቅና የደቡብ እስያ ጉዳይ ረዳት የውጪ ጉዳይ ሚኒስትሩ ጆን ኬሊ በሥራቸው ላይ መቆየታቸው እንኳ ገና



አልታወቀም ። የብሔራዊ ደህንነት መመሪያ በመባል የታወቀ አዲስ የፖሊሲ ሰነድ ወዲያው ከረምቱን ጸደቀ ። በመሠረቱ ፖሊሲው በአብዛኛው ያው በፊት የነበረው መሆኑን አንድ የመንግሥት ባለሥልጣን ተናግረዋል ። ከዚህም አያይዘው አሜሪካ ባሕረሰላጤውን አስመልክታ የነደፈችው አዲስ ፖሊሲ፣—

ኢራቆች ኑክሌርና ኬሚካል ጦር መሣሪያ ሊያገኙ የሚችሉበትን ቀዳዳ ሁሉ ድፈኑ ፣ በኢኮኖሚ ረገድ ወደአሜሪካና ወደምዕራቡ ዓለም የበለጠ እስጠጓቸው እሠሯቸው ፣ ጠባያቸውንም ለማለዘብ በማስፈራሪያ ፈንታ በማባበያ ለመጠቀም ሞክሩ

የሚል እንደሆነ አብራርተዋል ።

ኢራቅ በኢራን ልትወረር የተቃረበች በመሰለችበት ጊዜ አብዛኞቹ የዋሽንግተን ተንታኞች አሜሪካ በኢራቅ ረገድ የተከተለችውን ፖሊሲ አልጠሉትም ። አንድ የአሜሪካ ሸንጐ አባል እንዳሉት ከሆነ አሜሪካን ከነጠሚት ሁለት መጥፎ ሰዎች ግዳም ሻል ያሉ ስለመሆናቸው በአገር ፣ በሸንጐ ፣ በመከላከያና በመንግሥት ደረጃ እጅግ አመዛኙ የአሜሪካ አመራር ይስማማበታል ። ኢራቅ ያለማሥለስ እንዲያውም እያደገ በመሄድ ላይ በሚገኝ የሰብአዊ መብት ድፍረት ፣ ኑክሌር በምብ በመሥራት ጥረት ፣ የኬሚካል ጦር መሣሪያ ንጥረ ነገሮችን የማግኘት ጥረት ስታደርግ ለተመለከቱ ብዙ ተቺዎቿ ያንን ፖሊሲ ማቆየት ምንም ስሜት አልሰጣቸውም ። ቀደም ሲል የተጠቀሱት የሸንጐ ተወካዩ ሶላርዝ ኢራቅን በተመለከተ የቡሽ መንግሥት እንደዕውነቱ ከሆነ አዲስ የፖሊሲ ሰነድ ያላረቀቀና በአብዛኛው ያንኑ የነበረውን ፖሊሲ በአዲስ ቁጥር ያደሰው እንደሆነ አስረድተዋል ።

ፖሊሲው ባጭሩ ያለአብራሪ በአቶማቲክ መሣሪያ ቁጥጥር እንደሚበር አውሮፕላን (ሰብአዊነት የጐደለው) ነበር ።

አሜሪካ ኢራቅን በተመለከተ ስትከተል የቆየችው ፖሊሲ መንም የነበረበት እንዲያውም ከኢራቅና ኢራን ተኩስ አቁም በፊት እንደሆነ አንዳንድ የአሜሪካ ሸንጐ አባላትና የመንግሥቱ ባለሥልጣኖች ያምናሉ ። አንድ የአሜሪካ ሕዝብ እንደራሴዎች ውስጥ ዐዋቂ ምንጭ እንደገለጹት ከሆነ ኢራቅ ከኢራን ጋር ባካሄደችው ጦርነት እንደማትሸነፍ የአሜሪካ መከላከያ ደህንነት ድርጅት ገና በ1979 መጀመሪያ ደርሶበታል ።

በርካታ ፖሊሲ አውጪዎች እንደሚሉት ፣ አሜሪካ በኢራቅ ረገድ የተከተለችው ፖሊሲ በ1981 እና በ1982 እልፍ እልፍ ቢገመገምም ፣ የቡሽ አስተዳደር ለባሕረሰላጤው ቅድሚያ አልሰጠውም ። "ባለፈው ዓመት ጂም ቤከር የተጠመዱት በሶቪየት ኅብረት ውስጥ በተከናወነው ጉልህ ለውጥና በምሥራቅ አውሮፓ ኮሙኒዝም መገርሰስ ላይ" እንደነበረ፣ "አንድ ባለሥልጣን ሲናገሩ ፣ መንግሥታዊ ምንጮች ደግሞ ቡሽ" ከቶም አድርገውት ፣ ስለመካከለኛው ምሥራቅ ካሰቡም ፣ የሚያስቡት በእሥራኤልና በፍልስጥኤማውያን መካከል እርቀ ሰላም ስለሚወርድበት ሁኔታ ድርድር ስለሚጀምርበት መንገድ ነበር" ብለዋል ። በቡሽ አስተዳደር መሆኑ ቀርቶ በሌላ ፕሬዚዳንት አመራር ዘመን ሆኖ ቢሆን ኖሮ ፣ ምናልባት የበለጠ የበታች ባለሥልጣናት ጉዳዩን መቆጣጠር ችለው የውጪ ጉዳይ ሚኒስትሩንም በሙሉ ልብ እንዲያጤኑት ባላስገደዷቸውም ነበር ። ግን በቤከር በሚመራው የወጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ውስጥ ይህን ማድረግ አልተቻለም ነበር ።

ሌላ የአሜሪካ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ባለሥልጣን እንደሚሉት ወረራው ልክ ከመጀመሩ በፊት በአገሪቱ ሸንጎ ውስጥ በተናገሩት ቃል ጆን ኬሊን ሁሉም ያወግዙቸዋል ። እኚሁ ባለሥልጣን አክለው እንደተናገሩት ቤከር የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር ከሆኑ ወዲህ ጆን ኬሊም ሆኑ ሌላ ማንኛውም ረዳት የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር ፖሊሲ አይነድፍም ። ፖሊሲ አውጪዎቹ ቤከርና በፔንታጉን ሰባተኛ ፎቅ ላይ በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚገኙ ጥቂት ወዳጆቻቸው ናቸው ። ቤከር ከቅርብ ጓደኞቻቸው ጋር ካልሆነ በስተቀር ብዙ አያወሩም ። በመንግሥት ሥራ ላይ ያሉም ሆኑ ከመንግሥት ሥራ ውጪ ያሉ አብዛኞቹ ተንታኞች ከቶም አይሆንም ብለው ባሰቡት ነገር ላይ እነርሱን ማናገር በጣም አስቸጋሪ ይሆን ነበር ።

በስለላ ወንጀል የተከሰሰ አንድ የብሪታንያ ጋዜጠኛ በሞት መቀጣቷን ፣ የአንድ "ልዕለ ጠመንጃ መሣሪያ" መሥሪያ አፈሙዝና የኑክሌር ንጥረ ነገሮች ቃታዎች መውረዷን ፣ ከላቮር ባንክ የአትላንታ ቅርንጫፍ ጋር በተያያዘ ጉቦ መስጠቷ መጠቆሙን የመሳሰለው የኢራቅ ጋጠወጥነት ማስረጃ በ1982 እየበዛ ስለሄደ የአሜሪካ ሸንጎ በግዳም ላይ የኢኮኖሚ ማዕቀብ ይጣል ዘንድ ግፊት ፈጠረ ። የአሜሪካ መንግሥት እንዲህ ዓይነት ድንጋጌ መውጣቱን ተቃወመ ። የአሜሪካ መንግሥት በኢራቅ



ላይ ማዕቀብ እንዳይጣል ቅስቀሳ ለማካሄድ የተላለፈውን ውሳኔ የኢኮኖሚ ጥያቄ ተጽእኖ እያሳደርበትም ቢሉም ፣ ሸንጐው የሚከራከርበት የተለያየ እርምጃ ውድቅ እንዲሆን በማድረግ ብዙ ኩባንያዎችና ገበሬዎች ከፍተኛ ጥቅም ያገኛሉ ።

"ዚ ዋሽንግተን ፖስት" እንደዘገበው ፣ ዕቃው ለወታደራዊ አገልግሎት የማይውል ለመሆን ማረጋገጫ ከተሰጠ በኋላ እስከ 1982 ለኢራቅ 730 ሚሊዮን ዶላር ያህል በሚያወጣ ብርቱ ጥንቃቄን የሚጠይቅ ቴክኖሎጂ ለማጓጓዝ 486 ፈቃድ ተሰጥቷል ። ኢራቅ ኩዌትን በወረረችበት ጊዜ 160 ያህል ተጨማሪ ፈቃድ እንዲሰጣት እየተጠባበቀች ነበር ። ኢራቅ ቀደም ሲል ከተጠቀሰው የአሜሪካው የሸቀጣሸቀጥ ዱቤ ኮርፖሬሽን በ1979 ከነበረው 547 ሚሊዮን ዶላር ወደ 1·045 ቢሊዮን ዶላር አድጓል ። ከ1975 እስከ 1981 በኢራቅና በአሜሪካ መካል የተካሄደው ዓመታዊ የንግድ ልውውጥ ከ571 ሚሊዮን ወደ 3·6 ቢሊዮን ዶላር በመድረስ ሰባት እጥፍ አድጓል ። በዚያ ጊዜ ውስጥ አሜሪካ ከኢራቅ 5·3 ቢሊዮን ዶላር የሚያወጣ ነዳጅ ዘይት ገዝታለች ። ሰባ ያህል ኩባንያዎች የአሜሪካና የኢራቅ የጋራ የንግድ ምክር ቤት አባላት ነበሩ ። ሆኖም የአሜሪካ መንግሥት የፖሊሲውን ለውጥ ያስከተለው የገንዘብ ፍላጐት እንዳልሆነ በከፊል አስተባበለ ። አንድ የአሜሪካ መንግሥት ባለሥልጣን እንዳሉት ከሆነ የቡሽ አስተዳደር ሥልጣን ላይ በቆየበት ወር የመጀመሪያ ሳምንት ፣ ፖሊሲው ከሞላ ጐደል በመንፈስ በ1960ዎቹ መባቻ በአሜሪካና በሶቪየት ኅብረት መካል ከተደረሰበት የኃይል ሚዛን ጋር የሚመሳሰልና የ"የተወሰን የኃይል ሚዛን" ቢባል ባሕርዩን ከሁሉ በተሻለ ይገልጸዋል ። ባለሥልጣኑ ቀጥለውም ኢራቅ ኩዌትን ከመውረሯ በፊት ባለፉት የመጨረሻ ጥቂት ወራት ውስጥ "ከቶም ያላማረበት" ግንኙነት በጣም የባሰ ሻከረ ። ከወረራው በፊት የፖሊሲው ሚዛን 70 ከመቶ ወደማዕቀብ ደፋቶ ማግባቢያው 30 ከመቶ የነበረ ቢሆን ፣ ያ ድልድል ወይም ያ ወደረኛ ተለውጦ ሚዛኑ 90 ከመቶ ወደ ማዕቀብ ደፍቶ ማግባቢያው ወደ10 ከመቶ ወርዷል ።

ይህ ትክክለኛው ፖሊሲ እንደነበር የአሜሪካ አስተዳደር አባላት ባአውሮፓና በዓረቡ ዓለም የአሜሪካ ግብረአበሮች ብርቱ እምነት ያላቸው መሆኑን ባለሥልጣኑ አክለው ገልጸዋል ። ኢራቅ ከጦርነቱ በኋላ በበለጠ ለዘብተኛ ፣ በበለጠ የአሜሪካና የምዕራባውያን ደጋፊ ሆና

የተገኘች መስላ ነበር ። የአሜሪካ ወዳጅ ከሆኑት ከግብጽ ፣ ከዮርዳኖስና ከየመን ጋር ትብብር ስምምነት ላይ ደርሳለች ። ኢራቅ ወደ አሜሪካ መጠጋቷን እንድትቀጥል ያለመቸከር እብደት ይሆን ነበር ። የረጅም ጊዜ ግቡ (ስትራተጂው) ትክክል እንደነበር አጥብቀው የሚያምኑ መሆናቸውን ባለሥልጣኑ አሳውቀው ስለእርሱ ከቶም የተጧጧፈ ክርክር ፈጽሞ እንዳልተካሄደ አስረድተዋል ።

ኢራቅ የፈለገችውን ሁሉ ከአሜሪካ መግዛት ወይም ማግኘት ችላ ነበር የሚለውን ሐሳብም ባለሥልጣኑ ተቃውመዋል ። ይህንንም በማስመልከት ሲያብራሩ አሜሪካ ቁምሳጥኗን ክፍቱን ትታ የማታውቅ መሆኗንና በመጨረሻውም ቢሆን ቁምሳጥኑ ከመስገጠቅ በስተቀር ያለመከፈቱን በማውሳት አሜሪካ "ለልዕለ ጠመንጃ" መሥሪያ በሯን ለሣዳም እንደሚገመተው ሁን ብላ ልቅ እንዳልተወች በዘይቤ ተናግረዋል። በአሜሪካና በኢራቅ መካል ይህ ነው ተብሎ ለመጠቀስ የሚበቃ ወታደራዊ ግንኙነት እንዳልነበረም እኚሁ የኋይት ሀውስ ባለሥልጣን ገልጸው ፣ ስለሆነም አሜሪካ ለኢራቅ መሣሪያ እንዳልሸጠች አመልክተዋል ። ይልቁንም በ1982 ኢራቅ በምስጢር ኮሚሽን ሳታካፍልና ሕገወጥ ግንኙነትም ሳትፈጥር አትቀርም የሚል ጥያቄ ከተነሣ በኋላ የአሜሪካ መንግሥት ኢራቅ ከአገሪቱ የዱቤ ሸቀጣሸቀጥ ሽያጭ ኮርፖሬሽን ስንዴና እኸል በዱቤ እንድትወስድ በበጣት ዋስትና መሠረት የፈቀደላትን 500 ሚሊዮን ዶላር ብድር (በተጠቀሰው ዋስትና መሠረት በየዓመቱ በዱቤ ልትወስደው ከተፈቀደላት ግማሽ ያኸሉን) የአሜሪካ መንግሥት ያገደባት መሆኑን ከባለሥልጣኑ መረዳት ተችሏል ። በተለይም ኢራቅ በሕገወጥ መንገድ "የልዕለ ጠመንጃ" መሥሪያዎችንና ሌሎች "ሁለት ጥቅም" የሚሰጡ ቴክኖሎጂዎችን ገዝታ እንዳትወስድ የአሜሪካ መንግሥት ማገዱ የባግዳድን መንግሥት ያሳፈረው መሆኑን ባለሥልጣኑ ተናግረዋል ። ኢራቅ በስለላ የተወነጀለውን የብሪታንያ ጋዜጠኛ በሞት መቅጣቷንም አውግዛለች ። ባለሥልጣኑ "ከወረራው በፊት የዓረቦች ድጋፍ ሳይለየን ልንለውና ልናደርገው እንችል በነበረው ላይ ገደብ ነበረው" ባይ ናቸው ።

ባለሥልጣኑ "የረጅም ጊዜ ግባችን በቂ ምክንያት ቢኖረውም ምናልባት የቅርብ ጊዜ ግባችን በቂ ምክንያት አልነበረውም ። አሜሪካ በኢኮኖሚ ወይም በድዞታ የተነሣ የሚፈጠር ያለመግባባትን ለመፍታት



ወታደራዊ ኃይል መጠቀምን የማትቀበል መሆኗን የሚያስገነዝብ ግልጽ ማስጠንቀቂያ አልሰጠችም ። የመከላከያ ሚኒስቴሯ ጠበቅ ያለ ማስጠንቀቂያ ሰጠ ። በዚህም ረገድ ምናልባት አባባሉ ፍንትው ተደርጐ ሊነገር ይችል ነበር" የሚል ግምት አላቸው ።

ይህ አመለካከት በአሜሪካ ሸንጐ ተቀባይነት አይኖረውም ። ምክንያቱም ያገሪቱ መንግሥት 30 ከመቶ ማግባቢያውን እንቁልልጭ በማለት ላይ እንዳለ ፣ የሣዳም ጠባይ ያስበረገጋቸው የሸንጐ አባላት ሰባ ከመቶ የሆነውን ማስፈራሪያ መቆጣጠር ፈለጉ ። እስከ ወረራው እጥቢያ ድረስ የአሜሪካ መንግሥት በኢራቅ ላይ ማዕቀብ ለመጣል የሚደረገውን ሙከራ እየተከላከለ ነበር ።

በአንድ ወቅት ፣ ኢራቅ ከአሜሪካ በሚሰነዘርባት የማሳጣት ውርጅብኝ ታውካ እንደነበር ባለሥልጣኑ አመልክተው ውርጂብኙም በኢራቅ ላይ የተሸረበ ሴራ ስለመኖሩ ሣዳም ላገራቸው ለኢራቅ ዜጐችና ለዲፕሎማቶች ጠቁመዋል የሚል እንደነበረ አውስተዋል ። ይህን ነጥብ በመስከረም 1983 መጋባደጃ ሚልተን ቪዮርስት "ዘ ኒው ዮርክ ታይምስ" በተባለው ጋዜጣ ላይ ባሠፈሩት ጽሑፍ ደግመውታል ። ጄሲ ጃክሰንን አጅቦ ወደባግዳድ ሄዶ የነበረው ቪዮርስት የኩዌት የጭነት መርከቦች የሚያውለበልቡትን ሰንደቅ ዓላማ በመለወጥ የኢራቅን ነዳጅ ዘይት ከጥቃት ለመከላከል በሞከረች ፣ "ኩዌትና አሜሪካ ኢራቅን ለማጥፋት አሴረዋል" በማለት የኢራቁ የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር ጣሪቅ አዚዝ መናገራቸውን ጽፏል ።

ከዚህም በላይ ፣ ሣዳም በተባበሩት የዓረብ ኤሚሬቶች ግዛትና በኩዌት ላይ ከዛቱ በኋላ ፣ በባሕረሰላጤው አስቸኳይ ወታደራዊ ልምምድ ይካሄድ ዘንድ የመከላከያ ሚኒስቴሩ ያቀረበውን ሐሳብ የአሜሪካ መንግሥት አጽድቆታል ። የወታደራዊ ልምምዱን መካሄድ ልትደግፈው አስባ የነበረችው የተባበሩት የዓረብ ኤሚሬቶች ግዛት ኢራቅን አስቆጣለሁ ብላ በመፍራት በልምምዱ ውስጥ መሳተፏን በይፋ አስተባብላለች ። በአሜሪካ በኩል ባለው ቀዳዳ እንድትጠቀም ለእርሷ እድሉን መስጠት ያልተለመደ የግልጽነትና የተጠራጣሪነት ድብልቅ ውጤት ነው ። በተከታታይ የአሜሪካ መሪዎች ይህ የኢራቅ ተጠራጣሪ መንግሥት የዘጋውን በር እንዲከፍት ለማስደረግ ሞክሯል ። የአሜሪካ መንግሥት ከኢራቅ ጋር የበለጠ ለመቀራረብ ሰብአዊ መብትንና በዚያች አገር

የሚፈጸሙ ሌሎች አግባብ ያልሆኑ ድርጊቶችን ችል ብሎ ማለፍ ጊዜያዊና ስልታዊ የፖለቲካ አቋም የሚሉትን ፣ በተግባር ግን መሠረታዊ የእምነትና የዓላማ ልዩነት የሆነውን ሁሉ ለመቀበል ራሳቸውን አስገደዱ። በመጀመሪያ ከኢራን ጋር ባካሄዱት ጦርነት ድል ይቀዳጃሉ ብለው ፣ ቀጥሎም የተመታችውን አገራቸውን መልሶ ለመገንባት የአሜሪካ ፣ የምዕራብ አውሮፓና ከለዘብተኞቹ የዓረብ አገሮችም ያንዳንዱ ድጋፍ ያስፈልጋቸው ነበር ። ነገር ግን በጦርነቱ መኻል እንኳ ድምፃቸውን አጥፍተው የሚማስኑለት ሌላ አቅድ ነበራቸው ።



፱

# የእልቂት ሽብረብ

ከአንዲት ደቂቃ ባነሰ ጊዜ ሁሉም ተከውኗል ። እሑድ ፣ ግንቦት 30/1973 ማምሻውን ስምንት የእሥራኤል ኤፍ-16 ተዋጊ ጄቶችና ስድስት ኤፍ-15 ተዋጊ አሰናካዮች በመጥለቅ ላይ ከነበረችው ጀምበር አቅጣጫ ቱር ብለው በመምጠቅ ግብጽ ሠራሽ እጅግ ውድ የኢራቅ የኑክሌር መመራመሪያና መሥሪያ መጣሪያ ደመሰሱ ።

ከባግዳድ ወጣ ብሎ ይገኝ የነበረው ይህ የኑክሌር ሥራ ማቀላጠፊያ መጣሪያ በፈረንሳይ ሠራሽ ሮላንድ ከምድር ወዳየር ተተኳሽ ሚሳይል እየተጠበቀ የነበረ ቢሆንም የኢራቅ ወታደሮች ግን አንድም አልተኮሱ ። ተዋጊ ጄቶች ደግመው ደጋግመው ዝቅ እያሉ ዒላማቸውን በመምታት ላይ እያሉ ፣ አልተናቸውም እንጂ ፣ ወደ አየር ጥይት በመርጨት ለመከላከል የሞከሩት ጥቂት አየር መቃወሚያዎች ብቻ ነበሩ ። አውሮፕላናቹ የኑክሌር ገሳቢውን (ሪአክተር) ቡኒ-አሸዋማ ኮንክሪት የዕንቁላል ቤት ጣራ ፣ ቦምብ አለበሱት ። ቦምቦቹ ጣራውን ነድለው በዕንቁላል ቤቱ ወለል ላይ ዱብ ሲሉ እንዲፈነዱ ታቅዶ ማዘግያ ቫልቮላ ተገጥሞላቸዋል ። ይህም በመሬት ውስጥ ጠልቆ የተቀበረው ገሳቢ ውስጠ ቤት እንዲወድም ነው ። ከአንዲት ደቂቃ ባነሰ ጊዜ ውስጥ ፣ ኦሲራክና የአየር ጥቃቱ ለታሪክ ማኅደር ተላለፉ ።

የአየር ጥቃቱን ተልእኮ ስቲቭ ቫይከማንና ኸርበርት ክሮስኒ ዕውን የሚታይ ያኸል አድርገው እንደተረኩት ፣ ከአንድ ሐሳብ ለተገላገሉት (የወቅቱ) የእሥራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ሜናኼም ቤጊኒ ፣ "እንደስዊስ (የእጅ) ሰዓት አብቅቶለታል ፣ (እንዲያውም) ከስዊስ ሰዓት በባሰ" ተብሎ ተነግሯቸዋል ።

ጥቃቱ በደረሰበት ዕለት ከቀትር በኋላ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽሕፈት ቤት ስለሁኔታው የተሰጠው መግለጫ የበለጠ የለሰለሰና "እሑድ ፣ ግንቦት 30/1973 የእሥራኤል አየር ኃይል ባግዳድ አጠገብ በሚገኘው ኦሲራክ የአቶሚክ ገሳቢ ላይ ጥቃት አካሂዷል ፣ ፓይለቶቻችን ግዳጃቸ

ውን ሙሉ በሙሉ ተወጥተዋል ። ኀባቢው ተደምስሷል ። አውሮፕላኖቻችን ሁሉ በደህና ወደ ሠፈር ተመልሰዋል" የሚል ነበር ።

እርግጥ ፣ ጥቃቱ ትልቅ ዲፕሎማሲያዊና ፖለቲካዊ መዘዝ አስከትሏል ። አሜሪካ ተከታዮቹን ወራት እሥራኤልን የሚያወግዙ በርካታ የተባበሩት መንግሥታት ውሳኔዎችን ከኢራቅ ጋር ስታረቅ ነበር ። ከእነዚህም የበለጠ በተፈጸመው ጥቃትና በኑክሌር ኀባቢው ዕንቁላል ቤት አንድ ፈረንሳዊ መሐንዲስ በመገደሉ ማዘኗን በምሬት የገለጸችው ፈረንሳይ ናት ። ነገር ግን ፈረንሳይ ጥቃቱን በጣም ስሕተትና ጭካኔ እንደተሞላበት አድርጋ ትልቅ ቁጣ ማሰማቷ ለይምሰል ነበር ። ከአንድ ሥልጣንን የተመረኰዘ ምንጭ እንደተገኘው ፣ እሥራኤል ይህን መሰል ጥቃት ለመፈጸም ማቀዷን (በወቅቱ) አዲስ ለተመረጠውና ወዳጇም ለነበረው የፕሬዚዳንት ፍራንሷ ሚትራን ሶሻሊስት መንግሥት ነግራለች። እናም ጥቃቱ ከመፈጸሙ በፊት የተገለጸላቸው የውጪ መሪ ፕሬዚዳንት ሚትራን ብቻ ከመሆናቸውም በላይ (በወቅቱ) አልተቃወሙም ።

አብዛኞቹ መንግሥታት ጥቃቱ ያስደነገጣቸውና የማይደግፉት መሆናቸውን ገለጹ ። ነገር ግን ለብዙዎቹ የኑክሌር ጠበብታቸው ትልቅ ግልግል ነበር ። ፈረንሳዮች ለኢራቅ ውጥን የኑክሌር ኃይል መርሀግብር እጅግ በጣም የሚበዛበት ቴክኖሎጂ ሰጥተዋታል ። አንዳንዱ ፣ ኑክሌር ቦምብ ለመሥራት ብቻ እስባ ካልሆነ በቀር ለሌላ ለምንም ሊውል የማይችል ጭምር ፣ ኢራቅ በ1960ዎቹ በዝግታ ከውጪ ያለማሰለስ የምታስመጣው ሸቀጣሸቀጥ በመላው የምዕራቡ ዓለም ዋና ከተሞች አሳሳቢ ሆኗል ። ኢራቅ እንደ እሥራኤል የኑክሌር ቦምብ ባይኖራትም የኑክሌርን መናኘት የሚቃወመውን ስምምነት ፈርማለች ። ዋሽንግተን ውስጥ ሞገስ ያገኙትን ተንታኝ—ሊኦናርድ ስፔክተርን ጨምሮ አብዛኞቹ የኑክሌር ጠበብት መደምደሚያ ላይ ደርሰዋል ። ይኸው "ኢራቅ በ1970ዎቹ አጋማሽ የኑክሌር ክፍለልማቷን ከማስፋፋቷ በስተጀርባ ያለው ድብቅ ዓላማ ቀስበቀስ የኑክሌር ጦር መሣሪያ የማምረት ችሎታ መቀዳጀት ነው ።"

እርግጥ ኢራቅ በእሥራኤል ጥቃት ተዋርዳለች ። ከምድር ወደ አየር ተምዘግዛጊ ሚሳይሎም የተተከለው በተለይ በውዱ ኑክሌር ኀባቢ ላይ ጥቃት እንዳይደርስ ለመከላከል ነበር ። በመስከረም 1973 ኢራቅ ኢራንን



በወረረች በስምንተኛው ቀን ሌላ የኑክሌር ኀባቢ በአየር ጥቃት ተጐድቶባታል ፣ ይኸኛውን ጥቃት ያደረሱት ግን ኢራናውያን ናቸው እንጂ እሥራኤላውያን አይደሉም ።

ሣዳም ሑሴን ራሳቸው ነበሩ በ1968 በምክትል ፕሬዚዳንትነታቸው ለጉብኝት ወደ ፓሪስ ሄደው በመደራደር የፈረንሳዩን የኑክሌር ኀባቢ የገዙት— ብዙ ጊዜ ከምዕራብ የማያጋጥም ድንገተኛ ዝርፊያ ነበር። ዣይስጋንና ክርስኒ እንደሚሉት ፣ ለሰላማዊ አገልግሎት ነው ተብሎ የታሰበውን ኑክሌር ኀባቢ ሣዳም የትም ገብተው ለማግኘት የሚሞክሩት "ኑክሌር ቦምብ ለመታጠቅ መጀመሪያ ጥረት ካደረጉት ዓረብ መሪዎች" አንዱ ስለሆኑ እንደነበር በ1967 ለአንድ የቤይሩት ጋዜጣ ነግረዋል ።

እሥራኤል ድንገተኛ ጥቃት ከፈጸመች በኋላ ፣ ኢራቅ የኑክሌር ቦምብ ባለቤት እንድትሆን ሣዳም የነበራቸው ምኞት የኑክሌር ኀባቢያቸው እሲሪክ በነበረበት ቦታ ወዳድቆ እንደሚገኘው የኮንክሪት ጓልና ጎል ተሰባብሯል ። ከ1971 ጀምሮ ፕሬዚዳንት የሆኑት ሣዳም ከላቀው የእሥራኤል ወታደራዊና የኑክሌር ቦምብ ፣ ዓለም ለኢራቅ ተገን እንዲሆናት ጥሪ አድርገዋል ። "ሰላም ወዳድ አገሮች እሥራኤል እስካሁን ካላት የተመጣጠነ ኑክሌር ቦምብ ዓረቦች እንዲኖራቸው አሁን መርዳት አለባቸው" ሲሉ ጠይቀዋል ። ልመናቸው ሰሚ አላገኘም ። ሳዑዲ ወጪውን ችላ ፈረንሳዮች እሲሪክን መልሰው ለመገንባት እንደተስማሙ በርካታ ጋዜጦች ቢዘግቡም ኀባቢው እንደገና አልተሠራም ።

ነገር ግን ሣዳም ጥረታቸውን አላቋረጡም ። ድንገተኛ ጥቃት ከደረሰባት ጊዜ ጀምሮ አገራቸው ካሳየችው እንቅስቃሴ ለመገመት እንደተቻለው እንዲያውም የበለጠ ጥረት ታይቶባቸዋል ። ከእንግዲህ መቼም ቢሆን ኢራቅ ለአንድ ዓይነት ወታደራዊ ቴክኖሎጂ በማንኛውም አንድ አገር እንዳትተማመን ሣዳም ከድንገተኛ ጥቃቱ ተገንዝበዋል ። ኢራቅ አንድ የውጪ ጠላት በቀላሉ ጉዳት ሊያደርስባቸው የማይችለውን በጣም የተጠበቀ ኬሚካል ፣ ሥነ ሕይወታዊና የኑክሌር ጦር መሣሪያ በየዓይነቱ ትሠራለች ። እሥራኤል ድንገተኛ ደምሳሽ አደጋ ባደረሰችባት ማግሥት ኢራቅ የጦር መሣሪያ ለመግዛት ብቻ የራሷን ብዙ አጥፊ መሣሪያዎች ለመሥራት የሚያስፈልጋትን ቁስና ቴክኖሎጂ ለማግኘት ሰፊ የረጅም ጊዜ መርሀግብር ዘረጋች ። የውሸት ኮርፖሬሽኖችና ምሥል የንግድ ወኪሎች ተቋቋሙ ። ለጦር መሣሪያ ፋብሪካዎች ልዩ ልዩ

ተገጣጣሚ ክፍሎችን ከሚያመርቱ ያውሮፓ ኩባንያዎች ጋር ምስጢራዊ ግንኙነት ተመሠረተ ፡፡ የተፈለገው ቁስና መለዋወጫ በጣም ሰፊ ዝርዝር ወጥቶ "ለትልቅ ሸመታ" ተሠራጨ ፡፡ በኢራንና በኢራቅ ጦርነት መኻል የባግዳዱ መንግሥት ለሚቀጥለው ውጊያ የሚያስፈልገውን በመገጣጠም ከፍተኛ ጥረት ላይ ነበር ፡፡ ኢራቅ ከእንግዲህ ከቶም አትዋረድ ፡፡

እሥራኤል ድንገተኛ ጥቃት ባደረሰችባት ዓሥር ዓመት በማይሞላው ጊዜ ውስጥ ኢራቅ ዓላማዋን ከግብ ለማድረስ ብዙ ጥራለች ፡፡ እርግጥ የኢራቅና የኢራን ጦርነት በሁለቱም በኩል ከፍተኛ የጦር መሣሪያ ፍላጐት አሳድሯል ፡፡ ኢራቅ በ1976 ብቻ ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርቷ ግማሽ ያኸሉን ፣ 14 ቢሊዮር ዶላር ፣ ለጦር መሣሪያና ለመከላከያ ማውጣቷን የስቶክሆልሙ ኢንተርናሽናል ተቋም ገምቷል ፡፡

የአሪዞናው የአሜሪካ የበላይ ምክር ቤት አባል የሴናተር ጆን ማኬይን ባልደረባ—የመከላከያ ጠቢብ አንተኒ ኤች· ኮርድስማን እንደደረሱበት ኢራቅ ከ1974 እስከ 1981 ፣ 42 ቢሊዮን 800 ሚሊዮን ዶላር የሚያወጣ ጦር መሣሪያ ከውጪ ያስመጣች ሲሆን ከዚህ ውስጥ 17 ቢሊዮን 300 ሚሊዮን ዶላር የሚያወጣውን ከ1974 እስከ 1977 ፣ እንዲሁም 15 ቢሊዮን 500 ሚሊዮን ዶላር የሚያወጣውን ከ1978 እስከ 1981 አስመጥታለች ፡፡ ይህ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ ቢሆንም ፣ ኮርድስማን እንደመዘገቡት አንዳንዱ በግልጥ ወታደራዊ መሠረተ ልማት ቢሆንም በሲቪል በጀት ስለተመዘገበ ጠቅላላው የመከላከያ ወጪ ከተጠቀሰው ምናልባት ከ10 እስከ 30 ከመቶ ከፍ ሳይል አይቀርም ፡፡

የባግዳድ መንግሥት ይህን ከፍተኛ ወጪ ማውጣቱን ለመቀጠል መወሰኑ በነሐሴ 1980 ከኢራን ጋር ተኩስ አቁም ቢፈጸምም ኢራቅ የሰላም ፍላጐት እንደሌላት ያመለክታል ፡፡ ያስፈለገበት ምክንያት ከተወገደ በኋላም እንኳን ለጦር መሣሪያ ወጪ በማውጣት እርካታ የማግኘቱ አባዜ ቀጠለ ፡፡ ባለፈው አምስት ዓመት ጦር መሣሪያ ከውጪ አገር በማስመጣት ኢራቅን የተወዳደራት በዓለም የለም ፣ ብቻዋን በዓለም ከተሸመተው የጦር መሣሪያ ከ9 ከመቶ በላዩን እርሷ ገዝታዋለች፡፡ ኮርድስማን እንደዘገቡት ኢራቅ ከተጠቀሰው የጦር መሣሪያ ሸመታ 40 ከመቶውን ከሶቪየት ኅብረት ፣ 13 ከመቶውን ከቻይና ፣ 15 ከመቶውን ከምዕራብ አውሮፓ አገሮች ነው ያስመጣችው ፡፡



ጦርነቱ እየተራዘመ በሄደ መጠን ፣ የምዕራብ አውሮፓ አገሮች በጦር መሣሪያ ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው ዋና አቅራቢዎቿ ሆኑ ፡፡ ለምሳሌ ፈረንሳይ ከ1973 እስከ 1980 ለኢራቅ ወደ 12 ቢሊዮን ዶላር የሚያወጣ ጦር መሣሪያ ሸጣላታለች ፡፡ እናም ከሰሜን ካሮላይና የበላይ ምክር ቤት አባል ከሴናተር ጄሲ ሄልምስ ጽሕፈት ቤት በተገኘ አኃዝ መሠረት ፣ የፈረንሳይ ኩባንያዎች በተጨማሪም ለጦር መሥሪያ ሊያገለግል የሚችል መሣሪያና ምንዝር ሸጠውላታል ፡፡ ፈረንሳይ ለኢራቅ የጦር መሣሪያ መሥሪያና ምንዝር መሸጥ ያቆመችው ሣዳም ለገዙት ነገር ዕዳቸውን በወቅቱ መክፈል ከተሳናቸው ኩዌት ከመወረሯ ከበርካታ ወራት በፊት ወዲህ ብቻ ነው ፡፡ እርግጥ ይህን ሁሉ እንቅስቃሴ የአሜሪካ መንግሥት አይቶ እንዳለየ ፣ ሰምቶ እንዳልሰማ ለመሆን ፈቅዶ ነበር ፡፡ የአሜሪካ መንግሥት የመሣሪያ ግዢው ኢራቅን በጦርነቱ ከመሸነፍ ያድናታል የሚል እምነት ነበረው ፣ እናም ተኩስ አቁሙ ከጸናም በኋላ ፖሊሲውን አልለወጠም ፡፡ በኮርድስማን አባባል ፣ እንዲህ ባልተገታው የወታደራዊ ክፍሏ እድገት ኢራቅ በጦርነቱ መጨረሻ ፣ በአሸናፊነት መውጣት ብቻ ሳይሆን ፣ "በባሕረ ሰላጤው አንድ ጉልህ ወታደራዊ ኃይል" ሆና ብቅ አለች ፡፡

ለኢራቅ ጥንካሬ አንዱ መሠረት ነዳጅ ዘይት ነው ፣— እንደሌሎች ሩቅ አሳቢ አዳጊ አገሮች ሳይሆን ፣ ኢራቅ የፈለገችውን ለመግዛት የነዳጅ ዘይት ሀብት አላት ፡፡ ደግሞም ግን ኢራቃውያን የገዙትን በመለዋወጥና በማምም በማሻሻል ቀልጣፋ ሆኑ ፡፡ ኢራቅ በየካቲት 1980 ብቻ ረጅም ርቀት እንዲምዘገዘጉ ተደርገው የተሻሻሉ አምስት አዳዲስ ሚሳይሎችን ማንቀሳቀሷን ኮርድስማን መዝግበውታል ፡፡ ከእነዚህ አዳዲስ ሚሳይሎች አል አባስ የተሰኘው የሶቪየት ኅብረት የስከድ ሚሳይል ዓይነት በርቀት የመምታት ኃይሉን ከአጥፍ በላይ ጨምሮ እስከ 1ሺ248 ኪሎ ሜትር ርቀት ተምዘግዝጎ መምታት ይችላል ፡፡ በሚያዝያ 1980 መምከሩን ኮርድስማን ተናግረዋል ፡፡ እሥራኤላዊ ወታደራዊ ምንጮች ሚሳይሉ ለመሞከሩ ምንም ማስረጃ እንዳላዩ ገልጸው ፣ ዳሩ ግን መጀመሪያ በ1979 በተሞከረው በአልሑሴን ሚሳይል እጅግ በጣም የተደነቁ መሆናቸውን አልሸሸጉም ፡፡ አልሑሴን ከኢራቅ ምዕራባዊ ክፍል ቴል አቪቭን ለመምታት ከሚያስፈልገው በላይ ርቀት—በግምት 640 ኪሎሜትር መወንጨፍ ይችላል ፡፡ ከእነዚህ ሚሳይሎች ከ200ው በላይ በኢራን ላይ

ተተኩሰዋል ።

ኢራቅ በታኅሣሥ 1982 ፣ እስከ 1ሺ500 ናውቲካል ማይል ያኸል ርቀት የሚተኮስ አል አቢድ ፣ ወይም አምላኪ የሚባል አዲስ ሚሳይል መወንጨፊያ ወይም ላውንቸር ሞክራለች ። ሁለት ቀን እንዳለፈም ፣ የባግዳዱ መንግሥት ሁለት ተጨማሪ ሚሳይል በፈሳሽ ነዳጅ የሚንቀሳቀ ሰውን በሦስት ደረጃ የሚምዘገዘግ ታሙዝ-1 እርባ ስምንት ቀን ሚሳይልና እንዲሁም በግብጽና በአርጀንቲና ድጋፍ የተሠራውን በደረቅ ነዳጅ የሚንቀሳቀስ ኮንዶር የተሰኘ አዲስ ሚሳይል መሥራቷን አስታወቀች ።

ኢራቅ ኩዌትን ከመውረሯ ከአንድ ዓመት በፊት ከአንድ ደርዘን በላይ አልሑሴን ሚሳይሎችን አንዱ በአገሪቱ ምዕራባዊ ክፍል ሆኖ በሦስት የተወሰኑ ሥፍራዎች በመቀመጥ በመጀመሪያ ግዳም ሌላ ጥቃት ለማድረስ እያቀዱ ናቸው የሚል ስጋት እድሮባቸው እንደነበር የእሥራኤል ወታደራዊ ባለሥልጣኖች ተናግረዋል ። በተለይ በአገሪቱ ምዕራባዊ ክፍል የርዳኖስንና ኢራቅን በሚያገናኘው መንገድ አጠገብ ሚሳይል የተጠመደበት ሥፍራ በእሥራኤልና በሶርያ ውስጥ በሚገኙ ኢላማዎች ላይ የተነጣጠረ ስድስት መወንጨፊያ አለ ። እሥራኤላውያኑ ግራ ተጋብተው ነበር ። ግዳም እሥራኤልን ለማጥቃት እያቀዱ ከሆነ እንዲህ ማንኛውም የስለላ ሳታላይትና የመከላከያ አታሼ የሚያየውን ግልጽ እንቅስቃሴ ለምን ያደርጋሉ ? የእሥራኤል መከላከያ ሚኒስትር ሞሼ አሬንስ ወደአሜሪካ ሄደው ከመከላከያ ሚኒስትር ሪቻርድ ቼኒ ጋር በሐምሌ 1982 በተገናኙበት ጊዜ ብዙ የተወያዩት ስለኢራቅ ነበር ። በውይይታቸውም ቅድሚያ በሰጡት ርእስ ሥር ግራ የሚያጋባው ኢራቅ ያጠመደቻቸው ሚሳይሎች ጉዳይ ነበር ። ነገር ግን በኩዌት ላይ አደጋ ያንዣበበ መሆኑን እሥራኤል አልጠረጠረችም ፣ ያተኮረችው በራሷ ድንበር ላይ ባንዣበበው አደጋ ላይ እንደነበር ግልጽ ነው ።

የኢራቅና የኢራን ጦርነት እንዳበቃ ፣ ሣዳም ተሠርቶ ያለቀ መሣሪያ ከማስመጣት ፋንታ ራሳቸውን ነፃ ለማድረግ ወደነበራቸው ግብ ለመድረስ ትልቅ እርምጃ ተራምደዋል ። እርግጥ አውሮፕላንና የአየር መከላከያ አሁንም ከውጪ መግዛት ነበረባቸው ፣ ግን ኢራቅ የሚሳይል መወንጨፊያ የመሳሰሉ በፋብሪካ የተሠሩ ዓይነተኛ የመሣሪያ ምንዝሮችን ከውጪ ሳትገዛ ትልቅ የምርምርና ሥርቶ ማውጫ ችሎታ ግዳበር



የምትችል መሆኗን አሳይተዋል ። ኮርድስማን እንደሚሉት ፣ "የጦር መሣሪያን ቁጥጥር የሚያከብሩ ጥቂት አገሮች ብቻ እስከሆኑ ድረስ ፣ አንድን ቴክኖሎጂ ወይም ማሚያዎችን ሀብታም ሽማች ሁልጊዜም ከአንድ ሦስተኛ ወገን ሊያገኝ ፣ ወይም አዲስ የግዢ መንገድ ሊቀይስ ስለመቻሉ ኢራቅ ጥሩ ማስረጃ ናት ።

ብዙ የኢራቅ ሚሳይሎችን አሻሽሎ የመሥራቱ ተግባር በከፍተኛ ፍጥነት የነፋስ መሿለኪያዎች ፣ ሞተር መፈተሻ ሸርተቴዎች ፣ የሚሳይል መተኮሻ ክልል ፣ እና የኬሚካልና የኤሌክትሪክ ላቦራቷሮች ባሉት ሳዓድ 16 የኑክሌር ምርምርና ሥራ ማእከል ተከናወነ እንደሚባለው ባገሪቱ ሰሜናዊ ክፍል ሞሱል አጠገብ የሚገኘው ይህ ተቋም ከ200 ሚሊዮን ዶላር በላይ ፈጅቷል ። አሁንም እንደሚባለው የተቋሙ ሳይንቲስቶች ሚሳይል ከመሥራትና ከማሻሻል በተጨማሪ ኬሚካል ጦር መሣሪያ የሚሠሩ ከመሆናቸውም በላይ ፣ ምናልባትም ለኑክሌር ቦምብ ሥራ ሊጠቅም የሚችል ዩራኒየም ለማቀራት ከፍተኛ ሹረት ያለው "ዙሪት" (ሴንትሪፍዩጅስ) ለመሥራት እንኳ ሙከራ ያደርጋሉ ።

የቅርብ ምሥራቅን ፖሊሲ የሚያጠናው የዋሽንግተን ኢንስቲትዩት ተንታኝ—ማይክል አይዝንሽታት እንደገለጹት ለሳዓድ 16 የኑክሌር የምርምርና ሥራ ተቋም ማንኛውንም ነገር የሚያቀርበው ዋና ሥራ ተቋራጭ "ኮንሰን ግሩፕ" የተባለ ፣ ዋና ጽሕፈት ቤቱ በስዊዘርላንድ የሚገኝ ፣ የኮርፖሬሽኖች ሸርክና ማኅበር ነው ። ለኢራቅ የሚሳይል ሥራ መርሀ ግብር የውጪ ቴክኖሎጂና ባለሙያ ያገኘላት ይህ የሽርክና ማኅበር የተጠቀሱትን ያሰባሰበው ከአርጀንቲና ፣ ከሞናኮና ከ(ምዕራብ) ጀርመን ነው ። አይዝንሽታት እያይዘው እንዳስረዱት ኮንሰን ስም የማጥፋት ዘመቻ ስለተካሄደበት ከእንግዲህ ሥራ ለመሥራት እንደማይችል ስለደረሰበት በ1981 መባቻ ሥራውን አቁሟል ። በሽርክና ማኅበሩ የተተወው ሥራ እንደሚባለው "ሹፍኳልተርን ኡንት ፈናንሲሩንግ ኤ·ጂ" (ሹፋግ) በተባለ ሌላ የስዊስ ኩባንያ ተይዟል ።

ስለኢራቅ የጦር መሣሪያ ማምጃ ቤት ጥናታዊ መርሀ ግብር ለመሥራት በ1980 እና በ1981 በሳዓድ 16 ተቋም ለሠራው እንግሊዛዊ መሐንዲስ—ለክርስቶፈር ክሮውሊ ፣ ቢ.ቢ.ሲ. ቃለመጠይቅ አቅርቦለት ነበር ። (ክሮውሊ ኢራቅ ልዕለ ጠመንጃ እንድትሠራ ረድቷል ተብሎ

ተከቧል ።) ተቋሙ "ፍጹም የብልኀ ሥራ ነው ።... ከዚያ ከተለየ የምርምር ተቋም የሚወዳደር (ወይም) እንዲህ እንከን የለሽ መመሪመሪያ መሣሪያ ያለውን ተቋም የሚመስል ምንም በአውሮፓ አይቼ አላውቅም" ብሏል ።

ሰዓድ—16 ትልቁ የኢራቅ የቦሊስቲክ ሚሳይል ምርምርና ሥራ ተቋም ቢሆንም እርሱ ብቻ አይደለም ። አይዝንሽታት እንደዘገቡት ሌሎች ተቋሞች ፉሉጃ አጠገብ የሚገኘውን የምሕንድስና ወርክሾፕ ፣ ግሀሙዲያ አጠገብ የሚገኘውን የሮኬት ውልብልቢት ምርት ተቋም ፣ እንዲሁም ካርባላ አጠገብ የሚገኘውን የሮኬት ሞተርና የሚሳይል መሞከሪያ ተቋም ያካትታሉ ። አይዝንሽታት እንደሚሉት ከሆነ እነዚህ ፕሮጀክቶች ተሠርተው የተጠናቀቁት በ1981 መጀመሪያ ሲሆን እንደሚ ባለውም 400 ሚሊዮን ዶላር ፈጅተዋል ። ኮርድስማን እንደተናገሩት የኢራቅ መርሀ ግብር ስፋት ከአንድ ዓመት ያኸል በፊት ከባግዳድ 48 ኪሎ ሜትር ያኸል በስተደቡብ—አል ሂላል በተባለው የኬሚካልና የንዳጅ ተቋም ላይ በደረሰው የፍንዳታ አደጋ ታይቷል ። ያ ምስጢር ሆኖ የቀረው ፍንዳታ እስከ 700 ሰው ቢገድልም የማምረቱን ተግባር ለብዙ ጊዜ አላቋረጠም ።

እንደ ኦሲራክ ሳይሆን ቢያንስ በንድፈሐሳብ ደረጃ ፣ አዳዲሶቹ የግዳም የኑክሌር ምርምርና ሥራ ተቋሞች ሁሉ በሚገባ የተጠበቁ ናቸው። ለምሳሌም ሳዓድ—16 በአየር መከላከያ ስልት ተከቧል ፣ የበለላ ሳታላይት ካሜራዎችንም ለማታለልና ድንገተኛ የአየር ጥቃት ቢፈጸምም እንደማደናገሪያ ለማገልገል የታቀዱ የውሸት ሕንፃዎች አሉት ።

ቀደም ሲል ደግሞ ያለወትሮው ግልጽ የቦሊስቲክ ሚሳይልና የኬሚካል ጦር መሣሪያ መሥሪጪት ተቺ ፣ የሲ·አይ·ኤ· ዲሬክተር ዊልያም ኤች· ዌብስተር ናቸው ። መጋቢት 1981 ባደረጉት ያልተለመደ ንግግር የምስተኛውን ዓለም አገሮች የኑክሌር ፣ የኬሚካልና የሥነ ሕይወታዊ ጦር መሣሪያ እየሠሩ መሄድ ጨምሮ ፣ እስከ 1992 ፣ 15 ያኸል አገሮች የራሳቸውን ቦሊስቲክ ሚሳይል መሥራት የመቻላቸው ነገር አሳሳቢ አዝማሚያ እንደሆነ አስጠንቅቀዋል ። እርሳቸው አገሮቹን ባይጠቅሱም ፣ ኩዌት ከመወረሯ በፊት ፣ ብዙ ቀደም ብሎ ፣ የአሜሪካ መንግሥት ባለሥልጣኖች የሲ·አይ·ኤውን ዲሬክተር ባሳሰቧቸው አገ



ሮች ዝርዝር ውስጥ ኢራቅን ከወይመጀመሪያዎቹ መኻል ያስተምጢ ታል።

ምስጢር የሚመለከተው ተቋም ዲሬክተሮች ከቶም አድርገውት ከሚያውቁት ዘመቻ በእርግጥ እጅግ ከተናኙት ከጥቂቱ መኻል በሆነው ንግግራቸው እስከ 20 የሚደርሱ አገሮች ቸርችል "ያ ገሀነመ እሳታዊ መርዝ" ብለው የጠቀሱትን ኬሚካል ጦር መሣሪያ ምናልባት ሊሠሩ እንደሚችሉና ለሥነ ሕይወታዊ ጦርነትም የሚያስፈልገው "የሞራል ገደብ ስለመጣሱ" አስጠንቅቀዋል ። አባባላቸው ከሌሎች አገሮች መኻል ኢራቅንም የሚመለከት መሆኑ አያጠራጥርም ።

የቅረብ ምሥራቅ ፖሊሲ የሚመለከታቸው የዋሽንግተን ኢንስቲት ዩት ባልደረባው ደብሊዩ ሴት ካሩስ ባለፈው ያውሮፓውያን ዓመት ባቀረቡት አንድ ዘገባ "ኢራቅ አሁን በሦስተኛው ዓለም ውስጥ ካሉት አገሮች መኻል ሁሉ የተለቀና ምናልባትም ከሁሉም የበለጠ የተራቀቀ የኬሚካል ጦር መሣሪያ መርሀ ግብር አላት ።" እያይዘውም እንዳሉት ከኢራን ጋር ጦርነቷን ካቆመችበት ጀምሮ ኢራቅ ኬሚካል ጦር መሣሪያ ለመሥራት ያላትን ችሎታ መቀጠል ብቻ ሳይሆን እንዲያውም ነንዘቧን ፣ ጊዜዋንና ጉልበቷን አፍስሳበታለች ። ኢራቅ እስተድጣ በኬሚካል ላጠቃቻት አገር አፀፋ ካልሆነ በቀር በኬሚካል ጦር መሣሪያ መጠቀምን የሚያግደውን የጄኔቫ ፕሮቶኮል በ1917 የፈረመች ብትሆንም ፣ የባግዳድ መንግሥትም በ1975 እና በ1976 ከኢራን ጋር ባካሄደው ጦርነት በኬሚካል ጦር መሣሪያ ተጠቅሟል ። ከተኩስ አቁሙም በኋላ እንኳ መንግሥቱ የኩርዶችን አመፅ ለማከሸፍ ተጠቅሞበታል ።

ኢራቅ ምናልባት ግዳም ሥልጣን ከመያዛቸው ብዙ ቀደም ብሎ በ1950ዎቹ የኬሚካል ጦር መሣሪያ መርሀግብሯን እንደጀመረች ካሩስ ተናግረዋል ። የ"ዋሽንግተን ፖስታ" ጋዜጠኛ ዴቪድ ኢግናቲየስ ስለ ኢራቅ የኬሚካል ጦር መሣሪያ መርሀ ግብር ታሪክ ጠንቅቀው ባሠፈሩት ጥናታዊ ጽሑፍ ገና ቀደም ሲል በ1967 "ፀረ ተባይ ማደባለቂያ ፋብሪካ በመትከል ይረዳቸው ዘንድ ኒውዮርክ ውስጥ የሮችስተሩን ፕፋውድለር ኩባንያ ኢራቅ መጠየቋን ዘግቧል ። ፕፋውድለር ስለተጠየቀው ወደኋላ ብሎ ፣ ጥያቄው ሰሚ ቢያጣም ፣ ኢራቅ የበለጠ አነስተኛ ተቋም እንድታቋቁም ለማገባባት ሞከረ ። የባግዳዱ መንግሥት ወዲያው

ከአሜሪካው ኩባንያ ጋር የጀመረውን ንግግር አቋርጦ ፤ ያለምንም ይሉኝታ ወይም ፍርሀት "ኢምፔሪያል ኬሚካል እንዳስትሪዝ" ወደተባለ አንድ የብሪታንያ የንግድ ተቋም ዞረ ። ይህም ተቋም ኢራቅ ምን እያቀደች እንደሆነ ወዲያው ገባውና ከድርድሩ ገሸሽ አለ ። ሆኖም ኮርድስማን እንደሚሉት ሁለተኛው ትሌት ኢራቅን ተስፋ አላስቆረጣትም ። "ኢራቆች ወደ (ምዕራብ) ጀርመን ፤ ወደስዊስ ፤ ወደፈረንሳይ ፤ ወደ ሆላንድ ፤ ወደቤልጂግና ወደኢጣልያ ትንንሽ የንግድና እንዱስትሪ ተቋሞች ዞረው የኋላ ኋላ የፈለጉትን አገኙ ።" በኬሚካል መሣሪያ ጉዳይ የሐሳብ ጽናት ያስፈልግ ይመስላል ።

ለመሣሪያዎች ኬሚካል የሚሠሩ ፋብሪካዎች ሕንፃ በእርግጥም "በከፍተኛ ደረጃ ውሳኔ" ላይ ተደርሶ–ያው በራሳቸው በሳዳም መሆኑ ምንም ያሻል እያጠራጥርም–እዚህ ግብ ላይ በ1977 ሙሉ በሙሉ መደረሱን ካሩስ አውስተዋል ። እርሳቸው እንደጻፉት በዚያ ጊዜ ኢራቅ የሰናፍጭ ጋዝና እንዲሁም ፤ ታቡንና ሳሪን የተባለ ሁለት የተለያየ ዓይነት የነርቭ ጋዝ ጨምሮ ፤ በርካታ ኬሚካል ሉጣምጨ እያመረተች ነበር ። ካሩስ ዌብስተር በሰጠው መረጃ ላይ ተመርኩዘው ፤ ኢራቅ በፊት ከተገመተው በላይ ከአምስት እስከ ሃያ ጊዜ አጠፈታ—ማለትም ከ3ሺ 300 እስከ 13ሺ 200 ቶን በርካታ የተለያየ የኬሚካል ሉጣምጨ በዓመት ማምረት የሚችሉ ፋብሪካዎች እንዳሏት ደመደሙ ። ይህ ምርት በመላ አገሪቱ ስለተሰራጨ ለአየር ኃይል ከፍተኛ አክብሮት የሚሰጡ ሁሉንም ከአየር በቦምብ ማውደም በጣም አስቸጋሪ እንደሚሆን ይናገራሉ ።

የኢራቅ የኬሚካል ጦር መሣሪያ ምርት ክፍሉ በሳዳም የእንጀራ ልጅ በሑሴን ከማል አዛዥነት ሥር መደረጉ ኢራቅ ለዚህ ክፍል ትኩረት ለመስጠቷ ሌላ ጠቋሚ ነው ። ከማል ሑሴን ማንኛውንም ከውጪ የሚያስፈልገውን ጥብቅ የወታደራዊ ግዢ የሚያዘው የኢንዱስትሪና የወታደራዊ እንዱስትሪ ሚኒስቴር የበላይ ናቸው ። ባመዛኙ ለሳዳም ሑሴን "ምስጋና" ይግባቸውና ከአንደኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ እልፎ አልፎ ይከሠት የነበረው የኬሚካል ጦርነት ዛሬ ተመልሶ ባለጊዜ ሆኗል ።

ዋናው የኢራቅ የኬሚካል ጦር መሣሪያ ፋብሪካ ከባግዳድ 112 ኪሎ ሜትር በስተሰሜን ምዕራብ በትንሿ የሳማራ ከተማ አጠገብ ይገኛል። ዌብስተር እንዳለው ፤ የሚገኙበትን ሥፍራ አይግለጽ እንጂ ፤



ሌሎች በርከት ያሉ የኬሚካል መሣሪያ ተቋሞች በኢራቅ ውስጥ አሉ ። ነገር ግን ካሩስ እንደጻፉት ደግሞ ኢራቅ ፎስጂንን ፤ አርሴኒክ ውሕዶችንና ሳይናይድ ውሕዶችን የመሳሰሉ ሌሎች ኬሚካል ሉጣምጨ እያመረተች ይሆናል ።

ኬሚካል ጦር መሣሪያዎች የባዓዞች ወግ የተፈጥሮ ቅጣይ ናቸው ። የባዓዝ ፓርቲ መሪዎች ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ምንም ድምፅ ሳያሰሙ ተቃዋሚዎቻቸውን የሚገድሉ ከባድ ብረታብረት መርዞችንና ኬሚካል ሉጣምጨ ያፈቅራሉ ። ሳሚር አልኸሊል በ"ሪፐብሊክ ኦቭ ፊር" መጽሐፋቸው ውስጥ በ1960ዎቹ መጨረሻ ዘመናት ጥርጣሬ ለማያድርባቸው ጠላቶች ታሊየምና እርሳስና የመሳሰለ በረጅም ጊዜ የሚገድል መርዝ በምርመራ ጊዜ በለስላሳ መጠጥ ውስጥ ጨምሮ መስጠት የተመረጠ አሠራር ሆኖ እንደነበር ጽፈዋል ። በ1973 አምኒስቲ ኢንተርናሽናል የብሪታንያ ዶክተሮች የደረሱበትን መደምደሚያ መግለጫ አግኝቶ እንደገለጸው ቢያንስ ሁለት እንደነዚህ ያሉ ሰዎች ፤ በታሊየም ተመርዘው ተሰቃይተዋል ፤ እናም በዚህ መንገድ ዓሥራ አምስት ኢራቃውያን ተገድለዋል ። በ1973 ፤ "ኒው ሳይንቲስት" መጽሔት በኬሚካሎቹ የተመረዙትን ሰዎች ቃለመጠይቅ ያዘለና የተለያዩ ተመራዦችን ሁኔታ የያዘ በኢራቃውያን ሳይንቲስቶች ላይ የሚካሄድ ጭቆና ዘገባ አውጥቷል። ዘገባው እንዳለው

"ከሊድስ ዩኒቨርሲቲ የተመረቀው አማካሪ የኢንዱስትሪ ኬሚስቱ ሸውካት ኤ-አክራዊ ከአንድ የባግዳድ ሆስፒታል 'በድብቅ' ደውሎ ለአንድ የ'ኒው ሳይንቲስት' ባልደረባ" ነግሮታል ። "በኩርድኛ ፤ እንዲህ አለ ፡ 'የደገሱልኝ አደጋ አልገደለኝም ፤ ስለዚህ እየታከምኩ ባለሁበት ሆስፒታል ውስጥ ታሊየም ሰጡኝ ። እንግዲህ ሁላችሁም ደህና ሁኑ እላለሁ ።' ከዚያ በኋላ የስልክ ግንኙነቱ ተቋረጠ ።"

አሁን ኢራቅ በከፍተኛ ደረጃ የመመረዝ ብቃት አላት ። ነገር ግን ጋዞቹንና የነርቭ ሉጣምጨውን በብዛት መፈብረክ ፈተና ሆኗል ። ሂደቱ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት አገልግሎት ላይ ከዋለ ጀምሮ ብዙም አልተለወጠ ። ለምሳሌ የሰናፍጭ ጋዝ ለመሥራት ኢራቅን መጀመሪያ ለጽሕፈት ቀለምና ጨርቅን ለማቅለም እጅግ በጣም በብዛት የሚውለው ቲዮዲግሊኮል የተሰኘ "ቀድሞ ሂያጅ" ኬሚካል አስፈለጋት ። ቲዮዲግሊ

ኮል እንደልብ ከሚገኘው ከሁለገቡ ሀይድሮክሎሪክ አሲድ ጋር ሲደባለቅ ትይጡ የሰናፍጭ ጋዝ ያስገኛል ። ነገር ግን ቲዮዲግሊኮል በዓለም ሕግ ታግደ ፡ ኢራቅ ደግሞ በ1970ዎቹ መባቻ ልትሠራው አልቻለችም ። እንደካሩስ ከሆነ ቤልጂግ ውስጥ ያለ አንድ የአሜሪካ ኩባንያ ነበር ቲዮዲግሊኮል እንዳይሸጥ መጀመሪያ የተገደደው ።

"ሆኖም ወደፊት ኢራቅ የራሷን ቲዮዲግሊኮል በመሥራት ወደ ውጪ የመላክን ቁጥጥር ገደብ ማለፍ አለባት" ሲል ደምድሟል ። እንደ ዕውነቱ ፡ ኢራቅ "ከፈለገች በአንድ ዓመት ብዙ ሺ ቶን የሰናፍጭ ጋዝ" ማምረት መቻል አለባት ። እናም የሰናፍጭ ጋዝ ከመሥራት ይልቅ የነርቭ ሉጣምጤ ማምረት በጣም የበለጠ ውስብስብ ሆኖ እያለ ፡ በ1970ዎቹ መጀመሪያ የ(ምዕራብ) ጀርመን ኩባንያዎች በዓመት ቢበዛ አርባ ስምንት ቶን ሳሪንና ታቡን መሥራት የሚችል ሁለት ፋብሪካ ሳማራ ውስጥ ተከሉ። ካሩስ እንደገና አበክረው እንዳሉት ኢራቅ የፈለገችውን ተሬ ቅመም ከአውሮፓና ከሌሎች የውጪ አቅራቢዎች መግዛት ችላ ነበር ።

ኢራቅ ጥቂት እንግዳዊ ጉልዳፋነት ያላቸው ከአየር ተወርዋሪ ቦምቦችና ኬሚካል ጦር መሣሪያ የምትተኩስበት ብዙ ሺ ከባድ መሣሪያም ቢኖራት ፡ ኬሚካል የሚተኩሱ ዒላማቸውን በጣም አስተካክለው መምታት የሚችሉ ሚሳይሎችን መሥራት የተሳካላት ስለመሆኑ ምንም ማስረጃ እንደሌለ የእሥራኤል ወታደራዊ ምንጮች ይናገራሉ ። ሆኖም ኢራቅ ይህን ብታከናውን ፡ እስካሁንም ባላት ከፍተኛ የጦር መሣሪያ ክምችት ላይ አሁንም ሌላ ደምሳሽ መሣሪያ ትጨምርበት ነበር ። አንድ የእሥራኤል ወታደራዊ ምንጭ እንዳስረዳው የተለመዱ ፈንጂዎች የጉረሰ አረር ከኢራቅ ወደ ቴልአቪቭ ቢተኩስ በግምት የእያንዳንዱ አረር ፈንጂ ከአምስት እስከ ዓሥር ሰው ይገድላል ። ሕዝቡ የጋዝ ጭምብልና ስለአጠቃቀሙ መሠረታዊ ሥልጠና ካለው ኬሚካል የጉረሰ ሚሳይል በግምት እያንዳንዱ አረር ኀምሳ ሰው ይገድላል ። ኬሚካሎች በማሸበሪያ መሣሪያነትም የሚያገለግሉ መሆናቸውን ሌላ ተንታኝ ያመለክታል ፡ እናም ኢራቅ ከዚህ ቀደም ስትጠቀምበት እንደታየው ሁሉ፡ ያንድን አገር ሕዝብ ሥነልቡና የመስለብ ተጽእኖ አላቸው ።

በሥልጣኔ የበለጠ ኋላቀር ቢሆንም ፡ እንዲያውም የበለጠ አስፈሪው መርሀግብር ኢራቅ በሥነሕይወታዊ መሣሪያዎች ረገድ የምታካሂ



ደው ምርምርና ሥራም ነው ። ኢራቅ እንዲህ ዓይነት መርሀግብር ለመዘርጋት እየሞከረች መሆኗን ብታስተባብልም ፡ እንደካርኩስ አባባል ከሆነ ዋናው የኢራቅ የሥነሕይወታዊ ጦር መሣሪያ ተቋም በሳልማን ፓክ ይገኛል ። የኢራቅ ሳይንቲስቶች ያንጀት ተስቦ ፡ ኮሌራ ፡ አባ ሰንጋ ቱላሬሚያና ኢኳይን ኢንሴፋሊቲስ የመሳሰሉትን በርካታ በጣም የታወቁ በሽታዎች ፡ ምናልባት ይጠቅሙ እንደሁ በማለት ፡ እየመረመሯቸው መሆኑ ታምኗል ። የኢራቅን የጦር መሣሪያ መርሀ ግብር በቅርብ ይከታተላሉ ተብለው የሚታመንባቸው ካሩስም ሆኑ በርካታ የእሥራኤል ምንጮች ኢራቅ እነዚህን በሽታዎች ለ"መሣሪያነት" ለማብቃት ማለትም ዒላማ ወደተደረገ ሕዝብ በትክክል ሊደርሱ የሚችሉበትን መንገድ በሳይንስ ውስብስብ ሂደት እስካሁን ገና አልቻለችበትም ። ኢራቃውያን "ሥነሕይወታዊ ሉጣምጤ በብዛት ለማምረት ከሚያስፈልገው መሣሪያ ብዙውን ስለማግኘታቸው ምንም ጥርጥር አለመኖሩን ካሩስ ደምድመዋል ።

ከዚህ ቴክኖሎጂና መሣሪያ አብዛኛው ከ(ምዕራብ) ጀርመን የመጣ ሲሆን አሜሪካም ሳታውቅ ወይም ሁን ብላ ሳይሆን ድጋፍ ሰጥታ ይሆናል። አትላንታ ውስጥ የሚገኘው የበሽታ መቈጣጠሪያ ማእከል ሳይንሳዊ ምርምር ፡ ሊገድል የሚችል የበሽታ ባክቴሪያና ቫይረስ ምርት ዘወትር በአውሮፕላን ፡ በባቡር ፡ በፖስታና በሐዋላ ሳይቀር ይልካል ። የጦር መሣሪያን ሥርጭት ጉዳይ ብዙ ጊዜ የተከታተሉት የአሜሪካ የበላይ ምክር ቤት አባል—ሴናተር ጆን ግሌንና ባልደረቦቻቸው ዕውነተኛውን ምክንያት ሸፍና ለሐቀኛ የሕክምናና የሳይንስ ምርምር ተብሎ የተላከ የበሽታ ባክቴሪያና ቫይረስ ምርት ለወታደራዊ ምርምር ያለመዋሉን ማረጋገጥ በጣም አስቸጋሪ መሆኑን ያወሳሉ ። የእነዚህን ባለ "ሁለት ጥቅም" ቁሶች ከአገር ወደ አገር በሽያጭ መተላለፍ የመቈጣጠሩ ችግር ሥነሕይወታዊ ሉጣምጤና መርዘሚክሮቦችን ለመቈጣጠር የሚደረገውን ጥረት ብቻ ሳይሆን ሚሳይልንና ከኬሚካል የተዛመደ ቴክኖሎጂንም ጭምር ያውካል ።

በቅርቡ አንድ ኮሚቴ እንዳቀረበው ወደውጪ በሚላኩ ነገሮች ምዝገባ መሠረት ፡ የአትላንታው የበሽታ መቈጣጠሪያ ማእከል የ"ዌስት ናይል ፊቨር" የተሰኘውን በሽታ ቫይረስ በ1977 በሦስት የተለያዩ ጊዜያት ባስራ ወደሚገኝ የምርምር ተቋም ልኳል ። በአሜሪካ የኢንፎር

ሚሸን ነፃነት ድንጋጌ መሠረት ለኤን·ቢ·ሲ· ዜና በቀረበ ሰነድ መሠረት፣ በፎርት ዴትሪክ—ሜሪላንድ ውስጥ በተለይ የሥነሕይወታዊ ጦር መሣሪያ ሎጣምጤን የሚያጠኑ ሳይንቲስቶች ለዚህ በሽታ ክትባት ለማግኘት እየሞከሩ ነበር። እናም በ1981 የ(ምዕራብ) ጀርመን ጋዜጣ ኢራቅ ከአንድ የጀርመን ኩባንያ ጥቂት ማይኮቶክሲን ፣ ማለትም እንዳንዶቹ ሴሎች ፕሮቲን በሳይንሳዊ መንገድ ለማጣመር ያላቸውን ችሎታ በማገጋት ሰውንና እንስሳትን የሚገድሉ በሰንዴና በሳር ላይ በሚገኝ ዘረ እንጉዳይ (ፈንገስ) የሚፈጠር መርዝሚክሮብ መግዛቷን የሚገልጽ ዘገባ አወጣ። "እንዲት አገር የበሽታ ባክቴሪያና ቫይረስ ሰላባዎች የግድ ሥነሕይወታዊ ጦር መሣሪያ እየሞከረች ናት" ማለት እንዳልሆነ አንድ የቤናተር ግሌን ሪዳት ያስጠንቅቃሉ። ነገር ግን ይህ የ"ሁለት ጥቅም" ችግር ሕይወተ ቴክኖሎጂ (ባዮቴክኖሎጂ) መስክ በተደረሰበት እድገት እየታገዘ ሥነ ሕይወታዊ መሣሪያን ከመሥራጨት መግታት እጅግ አስቸጋሪ መሆኑን የመንግሥት ባለሥልጣኖች እንዲደመድሙ ገፋፍቷል። የሥነሕይወታዊ ጦር መሣሪያ ሥርጭት የሚከታተሉት የአሜሪካ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ባለሥልጣን—ኤች·አለን ሆልምዝ በ1981 ለአገሪቱ ሸንጐ የሰጡት የምስክርነት ቃል አለ። ባለሥልጣኑ ለሸንጐው ባሰሙት የምስክርነት ቃል የተጠቀሱትን ሎጣምጤ በተመለከተ በይንብሔራዊ የውጪ ንግድ ቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት ተግባራዊ ሊሆን እንደማይችል ተናግረዋል። ሆኖም ግን መሥራጨታቸው የአሜሪካን ደህንነት ለአደጋ የሚያጋልጠውና፣ ይዋል ይደር እንጂ፣ "አሸባሪዎች ይህን መሣሪያ አግኝተው መጠቀማቸው የማይቀር" መሆኑን ባለሥልጣኑ ተንብየዋል።

በ1982ም የሲ·አይ·ኤው ዲሬክተር — ዌብስተር "ለሥነ ሕይወታዊ ጦርንት ሎጣምጤ ምርት ብቻ ሊጠቀሙባቸው የሚችሉ ተዳሚ ኬሚካሎች ወይም መሣሪያዎች የሉም" ብለው ነበር። እያይዘውም እንዳሉት ማንኛውም መጠነኛ የሕክምና መገልገያ መሣሪያ እንዱስትሪ ያለው አገር ከፈለገ ሥነሕይወታዊ ጦር መሣሪያ ሊያመርት ይችላል።"

ዌብስተር በ1982 በተናገሩት በዚሁ ቃል ቢያንስ ዓሥር አገሮች ያለውን ዓይነት ወይም አዲስ ዓይነት ሥነሕይወታዊ መሣሪያ ለማምረት እየሞከሩ መሆናቸውን አስረድተዋል። እንዳቸውንም በስም ባይጠቅሱም የአሜሪካ መንግሥት ባለ ሥልጣኖች ኢራቅን ደጋግመው ከተጠቀ



ሰው ዝርዝር ውስጥ አስገብተዋታል። አሜሪካንና ሶቪየት ኅብረትን ጨምሮ፣ ከአንድ መቶ ዓሥር በላይ አገሮች በ1964 የተደረገ የሥነሕይወታዊ የጦር መሣሪያ ሥራና ክምችት የሚያግድ ስምምነት አባል ናቸው። ነገር ግን ሁለቱም አገሮች ስምምነቱን ፈርመው ቢያጸድቁም፣ በአሜሪካ ወንጀለኛ መቅጫ ውስጥ አንድ አንቀጽ፣ ግለሰብና የንግድና እንዱስትሪ አገልግሎት ድርጅት፣ እንዲህ ዓይነት ጦር መሣሪያ መሥራትን ይፈቅዳል። ከዚህም በላይ፣ ኢራቅ ስምምነቱን ፈርማለች፣ ግን አላጸደቀችውም፣ ማለትም በሕግ አይጸናባትም። ነገር ግን ይጸናባት ቢሆን ኖሮ እንኳ፣ የኢራቅ ያለዕፍረት የሕግን ድንጋጌ መድፈር ዓለም ከእርዷ ምንም ዋስትና እንዳይኖረው ያደርጋል።

የእሥራኤልና የአሜሪካ የጦር መሣሪያ ቁጥጥር ልዩ ባለሙያዎች ኢራቅን በተመለከተ የሚስማሙበት አንድ ነገር አለ። ይህም ኢራቅ በኬሚካልና በሥነሕይወታዊ ጦር መሣሪያ ምርምርና ሥራ ብትራመድም አካባቢውን ከሁሉም በላይ በአካባቢ ደረጃ ለአደጋ የሚያጋልጠው የኑክሌር መርሀ ግብሯ ነው። ከብዙ ዓመት በፊት ኢራቅ አቶሚክ የጦር መሣሪያ ለመሥራት የሚያስፈልጋትን ቴክኖሎጂና ምንዝሩን ለመግዛት በድምብ የታቀደ፣ በድምብ ወጪ የተመደበለት ፍለጋ ጀመረች። የዚያ ፍለጋ ፍሬዎች መታየት የጀመሩት በቅርቡ ነው።

እንደሊዎናርድ ስፔክተር አባባል ከሆነ፣ ኢራቅ አቶሚክ ቦምብ በሁለት መንገድ ማግኘት ትችላለች። አንደኛ፣ በባለ ሁኔታ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል አንድ ጉልዳፋ የኑክሌር ቦምብ ለመሥራት በበይንብሔራዊ ዋስትና ባከማቸችው የጠራ ዩራኒየም መጠቀም ትችላለች። ፈረንሳይ ለኦሲራክ ማመንጫ ሃያ ሰባት ፓውንድ ያኸል የጠራ ዩራኒየም ለዚህ በደንብ መበተን ለሚችል ጦር መሣሪያ ሰጥታለች። በስፔክተር አስተያየት ይህ ነገር የሚሆን አይመስልም። "መጀመሪያ ነገር፣ አንድ ቦምብ ብቻ ነው ሊሠሩ የሚችሉት፣ ይህ ደግሞ ብዙ አይረዳቸውም" አሉ ስፔክተር። እኚሁ ሰው እሥራኤል ከ200 በላይ ኑክሌር ቦምብ እንዳላት የኑክሌር ጠቢባን እምነት መሆኑን ተናግረዋል። ኢራቅ የራሷን ዩራኒየም ወይ ጦር መሣሪያ ደረጃ እስኪደርስ የምታጠራበት ፋብሪካ ለመትከል የሚያስፈልጋትን ምንዝር ለመግዛት ሙከራዋን መቀጠሏ ሁለተኛውና የበለጠ የሚመስለውም አማራጭ ነው።

ስፔክተር "ኑክሌር አምቢሽንዝ" በተባለ መጽሐፋቸው ኢራቅ በ1972 እና በ1973 "ከብራዚል ፣ ከፖርቱጋል ፣ ከኒዠርና ከኢጣልያ ያለምንም መግለጫ ብዙ የተፈጥሮ ዩራኒየም" ገዝታለች ፣ ብለዋል ። ከዚህ ቁስ ውስጥ የጠራ የዩራኒየም ነዳጅ ያስፈልገው ለነበረው ለኦሲራክ የኑክሌር ገባቢ ጥቅም ላይ የሚውል ምንም የለ ። ስፔክተር እንዳመለከቱት ኢራቅ ውስጥ ቀድሞ ኦሲራክ የኑክሌር ገባቢ በነበረባት በጡዋይታ ፣ ሞሱል ዩኒቨርሲቲ አጠገብ በሳዓድ–16 ፣ በኩርዶች ወሰን አጠገብ በምትገኘው በኤርቢል ፣ እና ጦር መሣሪያ ለመሥራት አስፈላጊ የሆነውን ሄክሳፍሎራይድ እያመረተ ሳይሆን የማይቀረው የፎስፌት ፋብሪካ የሚገኝባት አል—ቃይም ከኑክሌር ጋር የተዛመደ ሥራ እየተሠራባቸው ናቸው ተብለው ከሚታመንባቸው ሥፍራዎች መኻል ይገኛሉ ። የእሥራኤል ወታደራዊ ምንጮች ደግሞ የሥራውን ጠባይም ሆነ ሥፍራውን ለመግለጽ ባይፈልጉም ቢያንስ በሌሎች አምስት ሥፍራዎችም ከኑክሌር ሥራ ጋር የተዛመደ ተግባር እየተከናወነ መሆኑን ተናግረዋል ።

ዩራኒየም ሊጣራበት ለሚችል አዙሪት ሊሠራ የሚችል ፋብሪካ የተላኩ ምንዝሮች ባለፈው ሁለት ዓመት መያዛቸው የኑክሌር ተንታኞችን በመጀመሪያ ካስደነገጧቸው አጋጣሚዎች መኻል ነበር ። በየካቲት 1981 ፣ ኢራቅ የተለዩ ዋና ፓምፖች ለመግዛት ያደረገችውን ሙከራ ያሜሪካ የንግድ ሚኒስቴር አገደ ። እንደነዚህ ያሉ ፓምፖች ለብዙ ኑክሌር ላልሆኑ ጉዳዮች ሊጠቅሙ ቢችሉም በኑክሌር ማጣሪያ ፋብሪካ ውስጥም ሊጠቅሙ ይችላሉ ። በታኅሣሥ 1984 ፣ አንድ የ(ምዕራብ) ጀርመን ኩባንያ ለኢራቅ በ1979 እና በ1981 መኻል የዩራኒየም ማጣሪያ አዙሪት ለመፈብረክ የሚጠቅም ልዩ ርሶ ማሽን በማቅረብ ተከሶ በምርመራ ላይ እንደ ነበር "ዴር ሽፒገል" የተሰኘው የ(ምዕራብ) ጀርመን መጽሔት ዘገበ ። እንዲሁም በ1981 መጨረሻ ኢራቅ በምዕራብ አውሮፓ ውስጥ ፣ ስፔክተር እንደጻፉት ፣ የኑክሌር ማጣሪያ አዙሪት በከፍተኛ ፍጥነት ሲሾር ፣ ባለበት ቦታ ላይ ፈገቶ ለመያዝ የሚጠቅሙ ፣ ከሳማሪየም ኮባልት የተሠሩ ልዩ ማግኔቶች ለመግዛት እየሞከረች እንደ ነበር "ዘ ፋይናንሺያል ታይምስ" ጋዜጣ ዘግቧል ። ቸል የማይሉት ፣ ኢራቅ መግዛቱ ስላልተሳካላት በቻይና መንግሥት እርዳታ ራሷ ማግኔቶቹን ለመሥራት መወሰኗን የሚጠቁም ማስረጃ እንደነበር ጽሑፉ ያመለከተው ነው ። በመጋቢት 1982 ፣ ለኑክሌር ጦር መሣሪያ በቃታነት



ሊጠቅሙ የሚችሉ ለወታደራዊ አገልግሎት ብቃት ያላቸው ፀቃቢ ኤሌክትሪኮች (ካፓሲተርስ) በብዛት ተጭነው ወደ ኢራቅ ከመላካቸው በፊት በፈጣን እንቅስቃሴ ተይዘዋል ። የስዊስ መንግሥት በነሐሴ 1982 በኑክሌር ማጣሪያ ፋብሪካ ውስጥ የአዙሪት ቱቦዎች ሜፍ ከዳን ልከው ይሆናል የተባሉ ኩባንያዎችን እየመረመረ እንደነበር "ኑክሌር ፉዌል" የተሰኘ የተከበረ የንግድ ጋዜጣ ዘገበ ። በዚያው ወር ፣ የ(ምዕራብ) ጀርመን ባለሥልጣኖች ከስዊስ ወደ ኢራቅ በመጓጓዝ ላይ የነበረ ብረታ ብረት ፣ በዩራኒየም ማጣሪያ አዙሪት ውስጥ የሚጠቀሙበት ማራጂንግ የተሰኘ በጣም ጠንካራ ከሰል ፣ ብረት በውስጡ ይገኝና አይገኝበት እንደሆነ ለማጣራት ይዘው እንደነበር "ዘ ዋሺንግተን ፖስት" ዘግቧል ።

ከዚህ ቴክኖሎጂ አብዛኛው የቀረበው በአውሮፓ ኩባንያዎች ነው። የንግድ ልውውጡን በበለጠ ብቃት ለማከናወን ተቂቱ በኢራቅ ኩባንያዎች ተገዝቷል ። ኢራቅ የኑክሌር ምንዝሮችን የሚፈበርክ ሕንፃ ለማነጽና ማሽን ለመትከል የሚያስችላትን መሣሪያ ለማግኘት ባለሥልጣኖችን በጉቦ ለመደለልና የውሸት ኮርፖሬሽኖች በማቋቋም ብዙ ሚሊዮን ዶላር ያጠፋች መሆኑን ወታደራዊ ምንጮች ይገምታሉ ።

ባለ "ሁለት ጥቅም" ቴክኖሎጂን ከአገር በሽያጭ እንዳይወጣ ለመከላከል የሚደረገውን ቀድሞም የተወሳሰበ ጥረት አንዳንዴ በአሜሪካ መንግሥት ውስጥ የሚካሄደው ቢሮክራሲያው ሽኩቻ ያሰናክለዋል ። ለምሳሌም "ኮንሳርክ — ዩ.ኤስ.ኤ" የተባለውን የፊንኮካስ — ነው ጀርሲ ኮርፖሬሽን በተመለከተ የደረሰውን ሁኔታ እንመልከት፦ ኢራቅ ኩዌትን ከመውረሯ ከአንድ ወር በፊት የአሜሪካ መንግሥት የአገሪቱ የንግድ ሚኒስቴር ቴታኒየም ማቅለጫ ልዩ ዕቶን ለኢራቅ በ7 ሚሊዮን 600ሺ ዶላር እንዲሸጥላት ያጸደቀውን ይሸር ዘንድ ለማግባባት ብርቱ ዘመቻ አካሄደ ። የባግዳድ መንግሥት ዕቶኖቹን የፈለገው ከኢራን ጋር ባካሄደው ጦርነት አካላቸው ለተጉዳ እያሌ ወታደሮቹ ሰው ሠራሽ እጅና እግር ለመሥራት የሚጠቅም ብረታ ብረት ለማቅለጥ እንደሆነ ገለጸ ። የአሜሪካ መከላከያ ሚኒስቴር ግን ዕቶኖቹ ለኑክሌር መሣሪያዎችና ለሚሳይሎች ምንዝር መሣሪያም ሊጠቅሙ እንደሚችሉ አመለከተ ።

በመጀመሪያ በ "ዋሺንግተን ፖስት" እንደተዘገበው አንድ የአሜሪካ ጉምሩክ መሥሪያ ቤት ማስታወሻ ማይክል ማኒንግ የተባሉት ያገሪቱ

የንግድ ሚኒስቴር ባለሥልጣን የመከላከያ ሚኒስቴሩ የጀመረውን ምርመራ እስቲመው በ1981 እርሳቸው በፊርማቸው ባጸደቁት መሠረት ሽያጩ እንዲከናወን ለማድረግ ሞከሩ ። ማኒንግ ምርመራውን ለያዘው የጉምሩክ ተወካይ ደውለው ሽያጩ ለምን እንደታገደ ለማወቅ እንደሚፈልጉ ጠየቁት ። "ኩንሳርክ" የሽያጭ ውሉን ሲዋዋል "የእርሱን ምክር ተከትሎ ስለሆነ ሰው የሚጠሩ" መሆኑ ማስታወሻው ላይ ሠፍሯል ። ማኒንግ ሽያጩን ወዳገደው ወደመከላከያ ሚኒስቴር ብዙ ጊዜ ከደወሉ በኋላ ለጉምሩኩ ተወካይ እንደገና ይደውሉና በኩንሳርክ ቢሮዎች አካባቢ ስለምርመራው ተጨማሪ መረጃ ይጠይቁታል ። የጉምሩኩም ተወካይ ይህ ለኩባንያውና ለንግድ ልውውጡ መርማሪዎች ሌላ ነገር ሊመስላቸው እንደሚችል ለማኒንግ አስረዳቸው ። ማኒንግ ግን አሁንም ግፊታቸውን ቀጠሉ ። አሁንም ሌላ ጊዜ ደውለው ፣ በደቡብ ጀሬሲ አካባቢ ትልቅ አሠሪ በሆነው ኩባንያ ላይ ኪሳራ ሊያስከትል ስለሚችል የዕቀባው መታቀብ ያሳስባቸው መሆኑን ለጉምሩኩ ተወካይ ይነግሩታል ።

ማኒንግ በተጠቀሰው ሽያጭ ውስጥ የእርሳቸው ሚና ምን እንደሆነ እንዲገልጹ ተደጋግሞ ቢደወልላቸውም መልስ አልሰጡም ፣ ግን ማኒንግ ጨምሮ ፣ በርካታ ያሜሪካ ንግድ ሚኒስቴር ባለሥልጣናት ለኢራቅ የተሸጠው ቴታንም ለኑክሌር በጥቅም ላይ ሊውል እንደሚችል እያወቁ ያንን ጭብጥ ችል ማለቱን የመረጡ መሆናቸውን የፕሬስ ዘገባዎች ጠቁመዋል ። ኢራቅ ኩዌትን ለመውረር ከአንድ ወር ያነሰ ጊዜ ሲቀራት ስለሽያጩ ጉዳይ ጋዜጦች በዘገቡ ማግሥት የአሜሪካ የንግድ ሚኒስቴር እንዲከናወን የፈቀደውን ሽያጭ የማይፈትድ መሆኑን ጓደት ዘውስ አስታወቀ ።

የንግድ ሚኒስትሩ ሮበርት ሞዝባኸር ሁኔታው እንዳላሳሰባቸው ተናገሩ ። "ቁምንገሩ ያለመሸጡ" መሆኑንም ገልጸው የንግድ ሚኒስቴሩ ባለሥልጣናት የአሜሪካ ሸቀጣሸቀጥና አገልግሎት ወደውጪ እንዲሸጥ የመርዳት ግዴታቸውን መጠጣታቸው እንደነበር አውስተዋል ። ሞዝባኸር እያይዘውም ምናልባት የመግሪያው ለኑክሌር አገልግሎት መዋል መቻል ወደያው መስተባበል ነበረበት ። ምናልባትም የሽያጩ በአገሪቱ ከፍተኛ የሥልጣን አካል – በዚህ ረገድ በብሔራዊ ደኅንነት ምክር ቤቱ መኛር አልነበረበትም ይሆናል ። "ግን ("ዶርን ሲያታልሏት ፣ በመጨኛ



ጣቢት" እንዲሉ) ጉዳዩ አንዴ ላይ (ወዳገሪቱ ከፍተኛ የሥልጣን አካል) እንደረሰ ፣ ሽያጩ በፍጥነት ተቀጨ" ብለዋል ።

የአሜሪካ ምክር ቤት የጦር ኃይሎች ጉዳይ ኰሚቴ ሰብሳቢ – ሊስ አስፒን እንደሚሉት "ሁለት ጥቅም" ባላቸው የቴክኖሎጂ ውጤቶች ወደውጪ አገር በሽያጭ መውጣት ላይ ሥነ ሥርዓትን ለማስከበር የተጀመረው ፣ንቅስቃሴ የአሜሪካ ሸንጐ ከሶቪየት ኅብረትና ከሌሎችም የምሥራቅ አውሮፓ አገሮች ጋር የንግድ ልውውጡን ለማሳደግ ፍላጐት ካደረበት ወቅት ጋር በመገጣጠሙ ያልተጠበቀ ዓይነት ሁኔታ መፍጠሩን አመልክተዋል ። አስፒን ቀጥለውም ፣ ወትሮ ከአሜሪካ መከላከያ ሚኒስቴር ይልቅ "የአሜሪካ ንግድ ሚኒስቴር ይበልጥ ለዚህ ዓይነቱ ሽያጭ የተመቻቸ ነበር ። ስለሆነም ባለፈው ሁለት ዓመት ፣ የአገሪቱ ሸንጐ ወጪ ንግድን የማጽደቁን መሪ ሚና ወደ አሜሪካ ንግድ ሚኒስቴር" እያዞረው እንደነበር አትተዋል ። እናም በተሰጠው ሥልጣን አኳያ ፣ የአሜሪካ ንግድ ሚኒስቴር "ሁለት ጥቅም" ያለውን ሸቀጣሸቀጥ ለወጪ ንግድ እንዳይቀርብ የማገድ ፍላጐቱ ያነሰ ነበር ።

አሁን እየተመራበት ባለው ሥርዓት ፣ አንድ የተለየ የጦር መሣሪያ ዝርዝር ያካተተውን እያንዳንዱን መሣሪያ ማየትና መፍቀድ ወትሮ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ኃላፊነት ነው ። ነገር ግን የንግድ ሚኒስቴሩ "ሁለት ጥቅም" ያለውን ሸቀጣ ሸቀጥ ለኢራቅ በወጪ ንግድ የመላክ የመጨረሻ ሥልጣን አለው ። መከላከያ ሚኒስቴሩ ሽያጩን እንደሚቃወም መግለጽ ቢችልም የንግድ ሚኒስቴሩ ተቃውሞውን ላይቀበለው ይችላል ። አንዳንድ የሸንጐው አባላት አሁን እንደሚከራከሩት ፣ ለእንዲህ ዓይነቱ ሽያጭ ዋናው ኃላፊነት ወደ መከላከያ ሚኒስቴሩ ቢዞር እንኳ በዚህ ዓይነቱ የንግድ ልውውጥ የራሱ ባለሥልጣናትም ቢሆኑ አልፎ አልፎ በሒሳብ ስለሚለያዩ አንዳንድ "ሁለት ጥቅም" የሚሰጥ ሸቀጣ ሸቀጥ ሾልኮ ለወጪ ንግድ ሊቀርብ ይችል ይሆናል ።

የዚህ ዓይነቱን የንግድ ልውውጥ ለማገድ ትልቁ ግፊት በመከላከያ ሚኒስቴር ውስጥ የቴክኖሎጂ ደኅንነት ዘመቻ ጽሕፈት ቤት በመባል ከሚታወቅ ከሌሎች ጋር ሲወዳደር በጣም ትንሽዬ ንኡስ ክፍል ሲመጣ ኖሯል ። ከዓሥር ሠራተኞች ጋር ዲሬክተሩ ማይክል ማልሩፍና ሚጢጢዬዎን ንኡስ ክፍል ከ1917 እስከ 1980 ሲመሯት የቆዩት ስቴቨ ብራይን

ለኢራቅ ብዙ የዚህ ዓይነት ሸቀጣ ሸቀጥ ሽያጭ እንዳይጸድቅ መከልከል ችለዋል ። ግን ሁልጊዜ አይደለም ።

በ1977 እና በ1982 መኻል እስከ ዓሥራ አራት ጊዜ የአሜሪካ የንግድ ሚኒስቴር የቴክኖሎጂ ደኅንነት ዘመቻ ጽሕፈት ቤቱን ተቃውሞ ወደጐን እያለ የባግዳድን መንግሥት ኑክሌር ፡ ኬሚካልና ባሊስቲክ ሚሳይል የመሥራት ችሎታ እንዲያዳብር በቀጥታ የረዳው "ወጪ ንግድ ለኢራቅ በመርከብ እንዲጫንላት መፍቀዱን የ 'ዚ ፋይናንሺያል ታይምስ' አዲስ ፍሪድማን በመስከረም 1983 መጀመሪያ ዘግቧል ። በአንዳንድ ሽያጭ ረገድ የንግድ ሚኒስቴሩ ከነአካቴው ነገሩን ለመከላከያ ሚኒስቴሩ ያለማሳወቁን ፍሪድማን ዘግቧል ። የንግድ ሚኒስቴሩ በየካቲት 1982 ያጸደቀው ከሁሉም በጣም በቅርብ የተፈጸመ ከሚሳይል ጋር የተዛመደ የወጪ ንግድ ፈቃድ "ኢንተርናሽናል ኢሜጂንግ ሲስተምዝ" የተሰኘ አንድ የካሊፎርኒያ ኩባንያ አንድ ኮምፒዩተርና ከእርሱ ጋር የተዛመደ የሚሳይሎች ተወንጫፊው ዒላማቸውን እስኪመቱ የሚፈጁትን ትክክለኛ የጊዜ ፈለግ ለማስላት ሊጠቅም ለሚችል የትሕተ ቀይ (በዓይን ሊታይ የማይቻል የብርሃን ክፍል) ምስል ማጉልመሻ የታቀደ መሣሪያ ወደ ኢራቅ በመርከብ እንዲጭን ፈቅዷል ።

አንድ ሳይከናወን የቀረ ሽያጭም አለ ። ይህም ብሬየን እንደሚሉት ፔንሲልቫኒያ ውስጥ የሆምስቲዱ "ቴስት ሆምስቴድ ኢንጂነሪንግ" ዓሥራ ስድስት ኢንች አፈሙዝ ለመፈብረክ ሊጠቅም የሚችል ብረታ ብረት ማቅለጫና ከእርሱ ጋር የተዛመደ ኮምፒዩተር ወደ ኢራቅ በወጪ ንግድ ለመላክ የነበረው እቅድ ነው ። እንደብሬየን አባባል "ደግነቱ ኢራቅ ልዕለ ጠመንጃ እንዳትገዛ መከልከላችን ነው ። ከፋቱ የተባሉትን ልዕለ ጠመንጃ ለመሥራት ያስችላቸው የነበረውን ፋብሪካ ሊገዙ ተቃርበው ለትንሽ ያመለጣቸው መሆኑ ነው ።"

የአሜሪካ የንግድ ሚኒስቴር ሽያጩን በ1981 ክረምት ወራት አጸደቀ ። ብረታ ብረት ማቅለጫው ሊገዛ የነበረው ለፔትሮ ኬሚካል ምርት ማከማቻ ለመሥራት በሚል ሽፋን ነበር ። መከላከያ ሚኒስቴር ያየው ከብረታ ብረት ማቅለጫው ጋር ተጣምሮ ሊሸጥ የነበረውን ትንሽ ኤሌክትሮኒክስ ብቻ ነበር ። በማልሩፍ የሚመራው የቴክኖሎጂ ደኅንነት ዘመቻ ጽሕፈት ቤት ኤሌክትሮኒክሱ ቢሸጥ ምንም ችግር እንደሌለው ቢታየውም ፡ የንግድ ሚኒስቴሩ ቢከለክለውም ፡ የብረታ ብረት ማቅለጫ



ውን ሥራትና ከምን እንደተሠራ የሚናገር መግለጫ ለመመርመር ጉጉት አድሮበት ነበር። ሐምሌ 1981 የንግድ ሚኒስቴሩ ለመከላከያ ሚኒስቴሩ "የምታቀርቡትን ማንኛውንም ሐሳብ ለመስማት ዝግጁ ነን ።... ሆኖም ፡ የሥነሕይወታዊና የኬሚካል ጦር መሣሪያዎች ፡ እንዲሁም የሚሳይል ቴክኖሎጂ ዘመን ፡ የውጪ ፖሊሲ ቁጥጥር አካል ስለሆኑ ከመከላከያ ሚኒስቴር የሥልጣን ክልል ውጪ ናቸው ።" በማለት ጻፈ ። የአሜሪካ የውጪ ፖሊሲ ቁጥጥር ሚሳይልንና ኑክሌር ቴክኖሎጂን ብቻ እንጂ ብረታ ብረት ማቅለጫን ፡ ዕቶንንና ዝቅተኛ ደረጃ ኮምፒዩተሮችን ስለማይመለከት ፡ የንግድ ሚኒስቴሩ ከሌሎች የመንግሥት ክፍሎች እስኪጣራ ድረስ ፡ የመከላከያ ሚኒስቴሩ ሽያጩ እንዲጸድቅ ድጋፍ ከመስጠት ሌላ ምርጫ የለውም ።

ፕሬዚዳንቱ ቢል ኩክ ፈቃዱ ከተሰጣቸው በኋላ ስንብተው ሐምሌ 17 1981 ከሁለት የውጭ ጉዳይ ባለሥልጣኖች ጋር ስላደረጉት ስብሰባ ቴስት ሆምስቴድ ለንግድ ሚኒስቴር ሐምሌ 23/1982 በጻፈው ደብዳቤ ገለጸ ፡ ነገር ግን ከዚያ በኋላ ወዲያው የዕቶኑን ወይም የከውሩን ሽያጭ መታገድ የፐረስ ዘገባዎች ገለጹ ። ኩክ ለባለሥልጣናቱ ለስሚናዊ ባሕረሰላጤ ጉዳይ ጽሕፈት ቤት ምክትል ዳሬክተሩ ለጆሴፍ ማክጊ ፡ ለምሥራቅ ምዕራብ ንግድ ጽሕፈት ቤት ምክትል ዳሬክተር ለኤድዋርድ ጂ.ግርኮት ብረታ ብረት ማቅለጫውና መቀጥቀጫው "ትልልቅ የከባድ መሣሪያ አፈሙዝን ጨምሮ በጣም የተለያየ ብረታ ብረት በማቅለጥና በመቀጠቀጥ ሊሠራበት እንደሚችል" ደብዳቤው ገለጸ ። በደብዳቤው የተገለጸው በአሜሪካ ውስጥ እደጋ ለመምጣቱ ማስጠንቀቂያ መቀስቀስ ነበረበት ። ኢራቅ ለረጅም ጊዜ በዓለም በትልቅነት ወደር የማይገኝለት መድፍ — "ልዕለ ጠመንጃ" ለመሥራት ሲሞከር የነበረ ጀራልድ ቡል የተባለ ሰው እያሠራች መሆኑ በሚገባ የታወቀ ነበር ። ገና ከጥቂት ወራት በፊት ነበር የአሜሪካ መንግሥት ወደኢራቅ እንዲህ ዓይነቱን ጦር መሣሪያ ለመሥራት የሚያስፈልግ ቁስ ወደኢራቅ በመርከብ እንዳይጓዝ ያገደው ። እናም በመጋቢት 1982 ቡል በምስጢራዊ ሁኔታ ብራሴልስ ውስጥ ተገድሏል ። ነገር ግን ብረታ ብረት ማቅለጫና መቀጥቀጫው ለምንም ጥቅም ይዋል ለምን ፡ እነርሱ "ወደውጪ (ወደ ኢራቅ) እንዲላክ በቀረበው ሐሳብ አሳሳቢ ችግር ያደርሳል የሚል ምንም ስጋት እንዳላስደረ

ባቸው የአሜሪካ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ባለሥልጣኖች ለኩክ ነገሩት ። ግን እርግጠኛ ለመሆን ፤ እንደገና የንግድ ሚኒስቴሩን ስምምነት እንዲጠይቅ ሐሳብ የሰጡ መሆናቸውን አክለዋል ።

ይህ ቁስ ወደኢራቅ እንዳይላክ ያገደው መንግሥት ሳይሆን ኩክ የገዛ ራሳቸው ኩባንያ ምርት ሳልተፈለገ እንልግሎት ሊውል ይችላል የሚል ስጋት ይዟቸው ነገሩን ለባለሥልጣኖቹ እንደገና እንዲያነሡና በመጨረሻም ፤ ከ15 ሚሊዮን ዶላር በላይ የሚያስገኘውን ሽያጭ እንዲሠርዙ ገፋፋቸው ። ሆኖም ከአንድ ሳምንት በኋላ ግዳም ነገሩን አጠራጣሪ አድርገውታል ።

ግን "የሁለት ጥቅም" ቴክኖሎጂን ወደውጪ አገር መላክ በማስቀረት ፤ ሌላ መዋቅራዊ ችግር መኖሩን የጦር መሣሪያን በያገሩ ያለመሠራጨት ጉዳይ ያለመታከት የሚከታተለው የዊስኮንሲን የኑክሌር ጦር መሣሪያ ቁጥጥር ፕሮጀክት ባልደረባ — ጌሪ ሚልሆሊን ደርሰውበታል ። በቅርብ ወሬት ፤ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ቴክኖሎጂን ለመቆጣጠር አሜሪካና ተባባሪዎቿ ያቋቋሙት ቡድን ወደቀድሞው ዋርሶ ስምምነት አባል አገሮችና ሌሎች ኮሙኒስት አገሮች ከፍተኛ ቴክኖሎጂን በመላክ በኩል የነበረውን እገዳ ማስቀረቱን ሚልሆሊን ተገንዝቡ ። እርሳቸውም እንዳሉት በሰኔ 1982 የአሜሪካ መንግሥት ቁጥጥር ካነሣለት ሸቀጣ ሸቀጥ መኻል "ኢራቅ በመጋቢት 1982 ከአሜሪካ በስውር ልታወጣው ሞክራ የነበረው የኑክሌር ጦር መሣሪያ ቃታ ራሱ ይገኛል ።" በዚሁ ወደውጪ የመሸጥ እገዳ በተለይ የዋርሶን ስምምነት አባል አገሮችና ሌሎች ኮሙኒስት አገሮች በተመለከተ እንዲነሣላቸው ከተወሰነለት ሸቀጣ ሸቀጥ መኻል ኢራቅ ለዩራኒየም ማጣሪያ እዙሪቷ መሥሪያ የምትፈልጋቸው ስፒን ፎርሚንግና ፍሎው ፎርሚንግ በመባል የሚታወቁ ማሺኖች ናቸው ። የአሜሪካ ተባባሪ አገሮች ቡድን የቴክኖሎጂ ተቆጣጣሪ ቡድን ወደተጠቀሱት አገሮች በሚደረግ ወጪ ንግድ የከፍተኛ ቴክኖሎጂ እገዳው እንዲነሣ መደረጉ ምናልባት ለኢራቅም ቁምር እገዳው እንዲነሣ ማለት ሊሆን እንደሚችል ሚልሆሊን አስጠንቀቁ ፤ እና ሌሎችም ይስማሙ ። ሚልሆሊን በዚህ ማስጠንቀቂያቸው ማንኛውም የአሜሪካ ተባባሪ ቡድን አባል አገር የተጠቀሰውን ዓይነት ሸቀጣ ሸቀጥ ለፖላንድ ፤ ለሀንጋሪ ፤ ለቼኮዝሎቫ



ኪያ መሸጥ እንደሚችል አመልክተው ይህ ሸቀጣ ሸቀጥ በመርከብ ሲጓጓዝ ሌላው ቀርቶ ዝርዝሩ በመዝገብ ላይ እንኳ ስለማይገኝ "ኢራቅ ምንም ሕግ ሳትጥስ በምሥራቅ አውሮፓ በሚገኙ ኩባንያዎቿ አማካይነት የአሜሪካን የቦምብ ቃታዎች ማዘዝ ትችላለች ።" በማለት ደምድመዋል ። ከዚህም በላይ ለወጪ ንግድ መቆጣጠሪያ ተቆጣጣሪ ቡድኑ ለአብዛኞቹ በምዕራብ አውሮፓ የአሜሪካ ተባባሪ አገሮች ቡድን ያወጣው ዝርዝር ብቻ ስለሆነ ፤ ይህን ሸቀጣ ሸቀጥ ከዚያ ዝርዝር ማውጣት ማለት በመላው አውሮፓ ሳይመዘገቡ ሊሸጡ ይችላሉ ማለት ነው ። አብዛኞቹ የውሮፓ አገሮች እንደአሜሪካ የኑክሌር ጦር መሣሪያን ወይም የቦሊስቲክ ሚሳይሎችን ስርጭት ለማስቆም የተለየ መቆጣጠሪያ ዝርዝር አይዙም ።

ሆኖም ፤ የወጪ ንግዱ ሥርዓት ምንም ድክመት ይኑረው ፤ በጠቅላላው አሜሪካ የዚህ ዓይነቱን ቴክኖሎጂ ሥርጭት ማስቆምን በምትሰጠው ክብደት ከፍተኛ ሞገስ አግኝታለች ። በ1979 ፤ አሜሪካና ስድስት ሌሎች የጦር መሣሪያ አምራች ተባባሪዎቿ እንደ ኢራቅ ላሉ መንግሥታት አደገኛ ቴክኖሎጂ እንዳይተላለፍ የሚሳይል ቴክኖሎጂ ቁጥጥር "ሬጂም" አቋቋሙ ። መንግሥት ሮኬት እንዳይሸጥ ገደብ ጣሉ ፤ ግን ሁልጊዜ የየራሳቸው የግል ኩባንያዎች ለስምምነቱ ተገዢ እንዲሆኑ አልፈለጉም ። እናም "ዘ ኒውዮርክ ታይምስ" ጋዜጣ በቅርቡ ባወጣው ርእስ አንቀጽ ፤ ብራዚል ሚሳይል ፤ ከፍላተ ዓለምን አቋርጦ መወንጨፍ የሚችል ሞተር መሥሪት እንድትችልና የሚሳይሎቿን ማነጣጠሪያ ስልት እንድታሻሽል ፈረንሳይ ፤ ስዊድን ፤ (ምዕራብ) ጀርመንና ቤልጂግ ውስጥ የሚገኙ ኩባንያዎች እንደረዷት ጠቅሷል ። "ሬጂሙ" ብራዚልን ወይም በሶቪየት ኅብረት ፤ በቻይና እና በምሥራቅ አውሮፓ ያሉ የጦር መሣሪያ ሻጮችን የማያካትት ይመስላል ። ኢራቅ የሬጅም ርቀትና ደምሳሽነት ያለውን ኮንዶር ሚሳይል እንድትሠራ የረዳቻት ብራዚል ነበረች ።

ሆኖም ፤ እነዚህን ጥያቄዎች የተከታተሉ ጥቂት ፤ ግን ጊዜያቸውን ፤ ኃይላቸውንና ጉልበታቸውን ለዚህ ተግባር ያዋሉ ባለሙያዎች ፤ የምክር ቤትና የበላይ ምክር ቤት ረዳቶች ፤ የአስተዳደር ባለሥልጣኖችና ጋዜጠኞች የቡሽ መንግሥት የችግሩ ጦስ የበለጠ እየተሰማው ስለመሄዱ ሊአናርድ ስፔክተር በደረሰበት ግምገማ ወደመስማማቱ ያዘነብላሉ ።

ከዚህ በተጨማሪ ፡ በከፍተኛ ቴክኖሎጂ ሽግግር ረገድ የበለጠ ልል የነበሩ የአውሮፓ አገሮችም በለኬሚካል ፡ ስለ ሥነሕይወታዊና ከኑክሌር ጋር ስለተዛመደ ቴክኖሎጂ መሠራጨት ቀስ በቀስ የበለጠ ስጋት እያደረባቸው ናቸው ። አንዳንድ ተቺዎች ስጋታቸው የሚጨምረው በጣም ቀስ በቀስ ነው ይላሉ ። የአሜሪካ የበላይ ምክር ቤት አባል — የሴናተር ሆልምስ ጽሕፈት ቤት ባለፈው ክረምት "የማዳም የውጪ 'ሲጃየን'" የሚለውን ዝርዝር አወጣ ፡ ይህም የውጪ ኩባንያዎች ለኢራቅ መሸጣቸው የተረጋገጠና የተዘገበ ከወታደራዊ ጉዳይ ጋር የተዛመዱ ነገሮችን ዘርዝሯል ። በዚህ ዝርዝር ውስጥ ዓሥራ አራት አገሮች በሻጭነት የተጠቀሱ ሲሆን ፡ (ምዕራብ) ጀርመን የተጠቀሱ ሰባ ኩባንያዎችን ይዛ ቁንጮዋ ሆናለች ። ትንሿ ኦስትሪያ በሻጭነት ከተጠቀሱ ዓሥራ ስድስት ኩባንያዎች ጋር ፈንጠር ባለ ደረጃ በሁለተኛነት ሠፍራለች ። አሜሪካና ዩናይትድ ኪንግደም (እንግሊዝና ሰሜን አይርላንድ) እያንዳንዳቸው የተዘረዘሩ ዓሥራ አንድ ኩባንያዎች ይዘው አብረው የሦስተኛነቱን ደረጃ ተጋርተዋል ።

እዚህም ቢሆን የአሜሪካ መንግሥት አዲስ እርምጃ ጀምሯል ። በሬጋን መንግሥት ዘመን ረዳት የመከላከያ ሚኒስትር የነበሩት ሪቻርድ ፔርል አንድ ጊዜ የፖለቲካ እርምጃን ወይም በፖለቲካ ወደፊት ማምራትን የአሜሪካ መንግሥት ለአደጋ የሚያጋልጥ መሣሪያን ለተጠር ጣሪ አገሮች መሸጥን በተመለከተ የገለጹውን ተቃውሞ "ዲማር ሸማሉ ውስ" ብለውት ነበር ። ነገር ግን አሜሪካ እያከረረችው የመጣው ጥብቅ መልእክት በለዚህ ቴክኖሎጂ በአውሮፓ አገሮች መሠራጨት በውጪ አገሮች እየባሰ በመጣው ስጋት ታግዞ ከዚህ ዓይነቱ የቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ የበለጠ ጥብቅ ምርመራ እንዲካሄድ አስገድዷል ።

ቢሆንም በረጅሙ ሲታይ ባለሙያዎቹ እንዲህ አስቃቂ ጥፋት የሚያደርሱ የጦር መሣሪያዎችን ለማገድ የውጪ ንግድ ሕግን እያጠነከሩ የመሄዱን ሙከራ በመቀጠል ፡ አዳዲስ ስምምነቶችን ከመንደፍ ፡ እና ባሉትም ረገድ ቀዳዳን ከመድፈን በስተቀር አማራጭ እንደሌለ ይታያቸዋል ። ነገር ግን የ "ዘ ዋሺንግተን ፖስት" ጋዜጠኛው — ሆግላንድ በጣም በትክክል እንደጠራት ፡ ኢራቅን ከመሰለ "ሽፍታ (ወይም ሕገወጥ) አገር" ጋር ሊደረግ የሚቻል ነገር ልክ አለው ።

ኢራቅ በይነብሔራዊ ስምምነቶችን የምታከብር ስላለመምሰሏ



በኢራቅ የአሜሪካ አምባሳደር የነበሩት ኤፕሪል ግላስፒ ምናልባት መንገር እያስፈልጋቸውም ። አምባሳደሯ ለዕረፍት ከባግዳድ የወጡ ዕለት ኩዌት የምታመዛዝን እስከሆነች ድረስ የማይመቿት መሆናቸውን ግዳም ካረጋገጡላቸው በኋላ ለሌላ አስቸኳይ ስብሰባ ተጠርተው ነበር ። የኢንዱስትሪና የወታደራዊ ኢንዱስትሪዎች ሚኒስትሩ ሑሴን ከማል ከመሄዳቸው በፊት ሊያገኟቸው ፈለጉ ። ኢራቅ ልትገዛው እየሞከረች ስለነበረው ዕቃን አምባሳደሯ የተነገራቸው ስለመሆኑ ማወቃቸውን ሚኒስትሩ ገለጹላቸው ። ዕቃን እንዲገዛ ያዘዙት እርሳቸው ሳይሆኑ የበፊቱ የኢንዱስትሪ ሚኒስትር እንደነበሩም አረጋገጡላቸው ። እናም ተጥለው ዕቃን በዕውነት የተፈለገው ለሰላማዊ ጉዳይ እንደሆነም ነገሯቸው ። ሽያጩ እንዲፈጸም በማድረግ በእርግጥ ይረዷቸው ዘንድ በመለመን ፡ "በጐዳናዎቻችን ላይ እጅ እግራቸው የጐደለ ወጣቶችን ሁሉ አይተዋል ፡ ከሁሉም ሰው በላይ የቱን ያኽል ሰው ሠራሽ እጅ እግር እንደምንፈልግ ያውቃሉ ።" በማለት ሊያግባቧቸው ሞከሩ ።

ዳሩ ግን ዋሽንግተን ውስጥ የቡሽ መንግሥት ጨርሶ በስሚት በማይመሩ የኑክሌር ባለሙያዎች የሚነገረውን እየሰማ ነበር ። እንርሱ ፡ ዕቃን ለተገለጸው የኢራቅ ዓላማ ከሚያስፈልገው ከማንኛውም ሌላ ነገር ሁሉ በጣም ልቆ የተራቀቀ መሆኑን አስረድተዋል ። ሊሆን የሚችለው ለወታደራዊ አገልግሎት ብቻ እንደሆነ ተስማሙ ። እንዳይሸጥ ተከለከለ።

## ፲

# ጥቁር ወርቅ

ነዳጅ ዘይት የዛሬዪቱ ዓለም ሕመም አደንዛዥና አንቅልፍ ጋባዥ መድኃኒት ነው ። የሚያስገኘው ደስታ ፤ እንዲህ በጣም በገፍና በርካሽ ሌላ የኃይል ምንጭ ሊያጠግብ በማይችለው መጠን ፤ አንድን የኑሮ መንገድ በነዳጅነት ያንቀሳቅሳል ። ሱሱ እንዲለቅ ተሞክሮ የማያስችል ፤ አስቸጋሪና የማይላካ ሆኖ ተገኝቷል ። ዛሬ ልክ እንደ ሱስ አስያዥ ዕፅ ፤ የቤንዚን ንግድ በሕዝብ ደምሥር ውስጥ ብዙ ስለተሠራጨ ሀብታምም ሆነ ደሀ ፤ አብዛኛው አገር ኢኮኖሚውን በዚህ ግሩም ነገር ታግቶ ያገኘዋል ። ይህ የደረሰበት ሁኔታ የስስት ፤ የቁክክርና ሴራ የመሸረብ ትንግርት ነው ። ምንትርቅና ከወጣው የመካከለኛው መሥራቅ ጥልቅ ስሜትና ታላቅ ፍላጐት አንፃር ሊያፋጅ ይችል የነበረውን የኖረና ሥር የሰደደ የርስበርስ ጥላቻ ፤ ብሔራዊ ስሜትና የሃይማኖት ቀናኢነት የሚያዋሕደው ወይም የሚያስተባብረው ነዳጅ ዘይትን ለመቆጣጠር የሚካሄደው ትግል ብቻ ነው ። ዛሬ በፋርስ ባሕረሰላጤ የቀከሠተው ቀውስ መነሾም ያው ትግል ነው ።

ዊንስተን ቸርችል ለብሪታንያ ሮያል ባሕር ኃይል የድንጋይ ከሰልን መሠረታዊ እንቀሳቃሽ የኃይል ምንጭነት ትቶ በነዳጅ ዘይት እንዲጠቀም የባሕር ኃይሉን ጠቅላይ መምሪያ በ1903 ካግባቡበት ጊዜ ጀምሮ በነዳጅ ዘይት እንዱስትሪ በመንግሥትና በግል የንግድ ይዞታ መኻል የነበረው ልዩነት እስከወዲያኛው ተዘበራረቀ ወይም ሥርዓት የለሽ ሆነ ። ይህ በተለይ በመካከለኛው ምሥራቅ በጉልህ ይታያል ። የቸርችል ውሳኔ ግልጽ በሆነ የኢራንን ድፍድፍ ነዳጅ ዘይት አውጥቶ ሥራ ላይ የማዋል ዓላማ ፤ የብሪታንያ መንግሥት በውስጡ የባለቤትነት ዝንባሌ ወደነበረው የእንግሊዝንና የኢራንን የነዳጅ ዘይት ኩባንያ ወደመቋቋም አደረሰ ። በሃያኛው ምእታመት መባቻ የፋርስ ባሕረሰላጤ ወደ ሕንድ የሚያመራውን የባሕር መሥመር ለመጠበቅ ወደዚያ ለሚመላለሱት የብሪታንያ የባሕር ኃይል መርከቦች የነዳጅ ዘይት መቅጃ ጣቢያ በመሆኑ ለብሪታንያ በጣም አስፈላጊ ነበር ።



የብሪታንያ የበላይነት አልቀጠለም ። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማብቂያ ፤ በዓለም ላይ እጅግ ኃይለኛ አገር በመሆን አሜሪካ ተካቻት ። አሁን "ኤክሰን" ለተባለው "የጀሬሲው ስታንዳርድ አይል" ይህ "ብድር በምድር" የሚያስኝና እጅግም ቸር ወሬ ነበር ፤ የነዳጅ ዘይቱን ኩባንያ በይነብሔራዊ ንግድ ተቀናቃኞቹ አውሮፓውያን ፤ በተለይም ብሪታንያ ውያን ተበፋውን አጨልመውበት ነበር ። ለምሳሌም ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ኩባንያው በበርማ የነዳጅ ዘይት ቁፋሮ እንዳያካሂድ ታግዷል ፤ ለተመሳሳይ ተግባር ሊቢያ ለመግባት ሞክሮ ተከልክሏል ፤ አሁንም ለነዳጅ ዘይት ቁፋሮ ወደ ሰሜን ኢራን እንዳይገባ ታግዷል ፤ ወደኢራቅማ ጨርሶ ዝር እንዳይል ተደርጓል ። በከፊል የተሳካለት ሜክሲኮና ቬኔዙዌላ ውስጥ ብቻ ነበር ።

ስለዚህ ስለአውሮፓውያን የ"ዝግ በር" ፖሊሲ ለአሜሪካ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር አቤቱታ አቅርቦ ነበር ። የአሜሪካ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴርም በ1910ሮቹ መጀመሪያ የአሜሪካ ኩባንያዎች መገለላቸውን በመቃወም ለብሪታንያ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር በተከታታይ ጥብቅ መልእክት አስተላልፎ ነበር ። ሚኒስቴሩም በመልእክቱ የቀድሞው የሁስማናውያን ይዞታ የነበረው ክልል ለነዳጅ ዘይት ቁፋሮ ልማት ለሁሉም የዓለም ሕዝብ በእኩል ደረጃ ክፍት መሆን እንዳለበት አጥብቆ ጠየቀ ። የአሜሪካ ሐሳብ መጀመሪያ ቻይናን አስመልክቶ የተነሣው የ"ክፍት በር" ፖሊሲ ፤ ኩዌት ስትቀር ጉረቤቶቿን ፤ ኢራቅን ፤ ሳዑዲ ዓረቢያንና ባሕሬይንን የሚያጠቃልለውን የቀድሞ የሁስማናውያን ይዞታ እንዲያካትት ነበር ።

ሆኖም ኢራቅ ውስጥ "የኢራቅ ቤንዚን ኩባንያ" ያለ አንዳች ተቀናቃኝ ነዳጅ ዘይት የመፈለግና የማውጣት ሙሉ ሥልጣን አለው ። ይህ ኩባንያ "የቱርክ የቤንዚን ኩባንያ" ተብሎ ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በፊት (ስሙን በ1921 ቢለውጥም) የሁስማናውያን ሰፈ ግዛት ሥልጣን የቅርብ ወዳጅ በነበረ ነዳጅ ዘይት ነጋዴ አርመን ልጅ — በካሎስቴ ሳርኪስ ጉልቤንኪያን ተቋቋመ ። ጉልቤንኪያን የኢራቅን ቤንዚን ኩባንያ ያደራጀው ከጀርመን የወለድ አግድና ኢራቅ ከነበሩ የብሪታንያ ባንኮች ባገኘው ብድር ፤ እንዲሁም በሮያል ዳች ሼል ኩባንያ ተረድቶ ነበር ።

እንደኛው የዓለም ጦርነት በ1906 ከመጀመሩ ጥቂት ቀደም ብሎ

የብሪታንያ መንግሥት የኩባንያውን የበላይ ጥቅም ተካፋይነት ይዞ የቆየውን ጉልቤንኪያንን አስወጥቶ በእርሱም እግር የእንግሊዝና የኢራንን የነዳጅ ዘይት ኩባንያ ማቋቋም ቻለ ። ነገር ግን ከጦርነቱ በኋላ ፣ ስለነዳጅ ዘይት ጉልቤንኪያን ከብሪታንያውያን ጋር የተደራደረው የፈረንሳዮች ቡድን አማካሪ በመሆን እንስራራ ።

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ድልን የተቀዳጀው ኅብረብሔር አባል አገሮች በ(1913ቱ) ሳንሬሞ ስምምነት መሠረት ጀርመን በባሕር ማዶ የነበራትን ይዞታ ሁሉ ሲከፋፈሉ ፣ ጀርመን በኢራቅ ቤንዚን ኩባንያ ውስጥ የነበራት ድርሻ ለፈረንሳይ ደረሳት ። ፈረንሳይን ወክሎ ድርሻዋን የሚረከበው "ኮምፓኚ ፍራንሴ ዱ ፔትሮል" የተሰኘው የመንግሥት ድርጅት ነበር ። ጉልቤንኪያንም በኢራቅ ቤንዚን ኩባንያ ውስጥ የነበረውን የገንዘብ ድርሻ ማግኘት ቻለ ። በነዳጅ ዘይት ንግድ መወዳደር ለጉልቤንኪያን እርሙ ነበር ፣ ስለዚህ አሜሪካ ኢራቅ ውስጥ በሚካሄደው የነዳጅ ዘይት ልማት እንድትገባ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴሯ አጥብቆ በጠየቀ ጊዜ ፦ "አሜሪካውያንን ነዳጅ ዘይት ፈላጊና አውጪ ኩባንያዎች አስገቢቸው ፣ አለበለዚያ እነርሱ ጥሰው ይገቡና መድረሻ ይጠፋናል" ብሎ ምክር ሰጠ ። አውሮፓውያኑ ተሻራኪዎች መድረሻ ከማጣት አሜሪካ ለጠየቀችው መንገድ ሰጧት ። ስታንዳርድና አሜሪካውያን ተሻራኪዎቹ ከሁሉም አስቀድሞ "ሶኮኒ–ቫኩም" (አሁን ሞቢል) በኢራቃዊው ኩባንያ ወደ24 ከመቶ ድርሻ አገኙ ።

የአሜሪካ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ስታንዳርድ ለሁሉም የአሜሪካ ኩባንያ በእኩልነት ደረጃ በሩን እየከፈተ እንደሆነ በመገመት የስታንዳርድን አቤቱታ ደገፈው ። ነገር ግን በኢራቅ ቤንዚን ኩባንያ አውሮፓውያን አባላት አእምሮ ያደረው ይህ አልነበረም ። የኢራቅ ኮንሴሲዮን ዝቅተኛ ሊሆን እንደሚችል በ1919 ግልጽ ነበር ። ባባ ጉርጉር በተባለ ሥፍራ መጀመሪያ ከተቆፈሩት ጉድጓዶች ከአንዱ ብቻ በቀን ከ100ሺ እስከ 200ሺ በርሜል ነዳጅ ዘይት ይወጣል ። መላው የቀድሞ የዑስማናውያን ስፈ ግዛት በቀዳ ስፋቱ መጠን የ"ጥቁር" ወርቅ ማዕድን ሊሆን የሚችል መሰለ ። ጉልቤንኪያን በዑስማናውያን ስፈ ግዛት ካርታ ላይ ቀይ መሥመር አሠመረበት ፣ እናም የኩባንያው አባላት ሁሉ ፣ ከእነርሱ ማንኛቸውም በ "ቀይ መሥመሩ ቀዳ ስፋት ውስጥ በሚያገኘው በማንኛውም ኮንሴሲዮን እያገላገላቸው አክሲዮን ለመግዛት ወይም



ለመቋደስ ተስማምተዋል ።

የቀይ መሥመሩ ስምምነት መኖር ሌሎች የነዳጅ ዘይት ኩባንያዎች የባሕሬይንና የሳዑዲ ዓረቢያን የቤንዚን ኮንሴሲዮኖች በበለጠ በርትተው እንዲከታተሉ ገፋፋ ። ይህን ማድረጋቸው በእነዚህ ኮንሴሲዮኖች ውስጥ ጥቅሞቻቸውን ከተሻራኪዎቻቸው ጋር መካፈል ስለማይኖርባቸው ነው ። ይህን ፈለግ የካሊፎርኒያው "ስታንዳርድ ኦይል ካምፓኒ" (አሁን ቼቭሮን) ተከተለ ። ያን ጊዜ "ሶካል" በሚል ምህፃረታል ይታወቅ የነበረው ይህ ኩባንያ መጀመሪያ ባሕሬይን ውስጥ ኮንሴሲዮን አገኘ ፣ ኩባንያው ከዚያም በሳዑዲ ዓረቢያ ለሳኑ ሞድር ነዳጅ ዘይት መኖር አለበት ብሎ በማመን ከሳዑዲው መሪ ከኢብን ሳዑድ ጋር ድርድር ጀመረ። በውጤቱም ፣ ሶካል በሳዑዲ ዓረቢያ ውስጥ ነዳጅ ዘይት ለመፈለግ ብቻውን ኮንሴሲዮን አገኘ ። ሶካል የሳዑዲን ኮንሴሲዮን ግልሚያ ካፒታል ወጪ ያግዘውና በኩባንያውም ስራ የገበያ መዋቅር ለመጠቀም ከጥቅሙ ከፊሉን የሽርከና መደብ (ሼር) ለአሁን ቴክሳኮ ለሚባለው) የቴክሳስ ኩባንያ ሸጠለት ።

በእንግሊዝም የኒው ጀርሲው "ስታንዳርድ ኦይል" በባሕር ማዶ እንቅስቃሴው ለክስረት በጣም በተጋለጠ ደረጃ ላይ የሚገኝ መስሎ ታየ ። ስታንዳርድ መጀመሪያ ውጪ አገር ከሄዱትና እጅግም ታታሪ ከነበሩት የአሜሪካ ኩባንያዎች አንዱ ቢሆንም ፣ የተስፋፋው በተለይ ከነበሩ ኮንሴሲዮኖች የሽርከና መደብ እየገዛ ነው ። ስለዚህም ኢራቅ ውስጥ ከቀድሞዎቹ አውሮፓውያን ተሻራኪዎቹ ጋር ለቀይ መሥመሩ ስምምነት ተገዢ ነው። በቀይ መሥመሩ ክልል አዳዲስ ኮንሴሲዮን ቢያገኝ ይህን በኢራቅ ነዳጅ ዘይት ኩባንያ ውስጥ ካሉት ተሻራኪዎች ጋር የመካፈል ግዴታ አለበት ። ተመሳሳይ ውል ሌላ ዘንድ የሚያጋጥመውን እድል ገታው ።

ስታንዳርድና ሶኮኒ – ቫኩም ይህን ሐቅ በውቀው የሽርከና መደብ በመግዛት ንብረትነቱ የሶካልና የቴክሳስ ወደሆነው ወደ ዓረቢያና አሜሪካ ነዳጅ ዘይት ኩባንያ (አራምኮ) ይገቡ ዘንድ ሐሳብ አቀረቡ ። ጉልቤንኪያንና በኢራቅ የቤንዚን ኩባንያ ውስጥ የሚገኙ ተሻራኪዎቹ ፣ በተለይም ፈረንሳዮቹ ይህን የንግድ ቁማር አጀማመር ተቃወሙ ፣ ነገር ግን ስታንዳርድና ሶኮኒ ፣ በአሜሪካ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ድጋፍ በንግፋ ከመገፋት የማይተቱ መሆናቸውን በመጨረሻ ተገነዘቡ ።

የአራምኮ ድርድር አራቱ የአሜሪካ ኩባንያዎች — ማለትም ቴክሳስ፣ ሶካል ፣ የኒው ጀርሲው ስታንዳርድና ሶኮኒ የዓረቢያን ነዳጅ ዘይት ኮንሴሲዮን ሙሉ በሙሉ በቁጥጥራቸው ሥር እንዲያውሉ አድርጉ በ1966 ተፈጠመ ። ስታንዳርድ ለምርጫ አስቸጋሪት የቆየውን የመጫረት ችግር ፈቶታል ፤ በዓረቢያኑ ኮንሴሲዮን ውስጥ የባለንብረትነት ጥቅም አግኝቷል ፣ ራሱን (እና ሶኮኒ ቫኩምን) ከቀዩ መሥመር ስምምነት ነፃ አድርጓል ። ስለዚህም አውሮፓውያን ተቫራኪዎቹን ሳያስከትል አራምኮ ውስጥ መዋዕለንዋይ ሊጨምር (ኢንቨስት ሊያደርግ) ችሏል ። ሆኖም በተመሳሳይ ጊዜ በ"ኢራቅ የቢንዚን ኩባንያ" ውስጥ የነበረውን የተቫራኪነት ደረጃ አስጠበቀ ። ከሁሉም ይልቅ ፣ ከአውሮፓውያኑ የነዳጅ ዘይት ኩባንያዎች ፣ ማለትም ከሼልና ከእንግሎ ኢራኒያን ፣ በመካከለኛው ምሥራቅ ካሏቸው ሌሎች ነዳጅ ዘይት አምራች ይዞታዎቻቸው ጠቀም ያለ ድፍድፍ ነዳጅ ዘይት ሊገዛቸው የረጅም ጊዜ ስምምነት በመግባት የትብብር ግንኙነቱን አድሷል ። የአራምኮው የኩባንያዎች ሸርክና በአራቱ ተቫራኪ ኩባንያዎች ፣ ማለትም የኤክሶን ፣ የቴክሳኮ ፣ የሞቢልና የሼቭሮን ዘውድ ጌጥ ሆነ ። ወደፊት የሌሎቹ የፋርስ ባሕረሰላጤ ነዳጅ ዘይት አምራች አገሮች ጥቅም ለዚህ ለዓረቢያን ኮንሴሲዮን ከሌሎች ሁሉ የላቀ አሳሳቢ ጉዳይ ጥገኛ እንዲሆን ይደረጋል ። ሕዝብ የበለጠ የሚበዛባቸው ኢራቅና ኢራን የነዳጅ ዘይት ምርታቸው ሕዝብ ከሚሳሳበት ከዓረቢያ ልሳንምድር ባልበለጠ ሁኔታ የተወሰነ መሆኑን እንዳዩት ሁሉ ፣ ውጤቱ የማይሽር የተቃውሞ ፣ የምሬትና የንዴት ቁስል ይሆናል ።

በዚያው የአራምኮ የነዳጅ ዘይት ኩባንያዎች ሸርክና በሳዑዲ ዓረቢያ በተጠናከረበት ወቅት ሌሎቹ ነዳጅ ዘይት አምራች አገሮች ፣ በተለይም ኢራን ፣ ለምዕራባውያኑ የነዳጅ ዘይት ኩባንያዎች የየብቻ መብት የሰጡት የመጀመሪያ የነዳጅ ዘይት ጉድጓዶች ይዞታ ውል እንዲለወጥ በመጠየቅ የመብት ማስጠበቅ ጥያቄዋን እያከረረችው ሄደች ። ኢራን የነዳጅ ዘይት ጉድጓዶቿን ይዞታ ያኮናተረችው በ1893 ነው ። ስሥራ አስቸጋሪና አዋኪዎቹ የዚያ የይዞታ ኮንትራት ውልና የእርሱም ተደጋጋሚ መሻሻል ምዕራባውያን ላካሄዱት ብዝበዛ ዓይነተኛ ቋሚ ምስክር ነው ። የኢራን መሪዎች የይዞታ ስምምነቱ ውል በጣም እንዲለወጥ ጠየቁ ፣ እናም በመጋቢት 1943 ፣ የኢራን ምክር ቤት



በአገሪቱ ውስጥ የነበረውን የእንግሎ–ኢራኒያን ይዞታዎች በማናለብኝነት ለመንግሥት ውርስ አደረገ ። ከሁለት ወር በኋላ ፣ መሐመድ ሞሳዴግ የተባሉ ኮሙኒስት ያልሆኑ ተራማጅ አገር ወዳድ በጠቅላይ ሚኒስትርነት ተመረጡ ። ብሪታንያውያን ወደ ግማሽ ምእታመት ለሚጠጋ ጊዜ የኢራንን የነዳጅ ዘይት እንዲቆጣጠሩ ከተቆጣጠሩ በኋላ ፣ ካገሪቱ ተባረሩ ።

የአሜሪካ መንግሥት ደንግጦ ነበር ። ኢራን የእንግሎ–ኢራኒያን ንብረት እንድትወርስ ከተፈቀደላት ፣ ሌሎች የክልሉ አገሮች የእርሷን ምሳሌ ይከተሉ ይሆናል ።

ጉዳዩን በጥር 1945 በአሜሪካ ብሔራዊ ደኅንነት ምክር ቤት ክርክር ተካሂዶበት የአገሪቱ የውጪ ጉዳይ ፣ የመከላከያና የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴሮች በጥምር አንድ ጥናታዊ ጽሑፍ አወጡ ። ጽሑፉም በመካከለኛው ምሥራቅ ነዳጅ ዘይት አምራች አገሮች ነዳጅ ዘይት ዋነኛው የሀብትና የገቢ ምንጭ ስለሆነ ፣ "ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሀላፊያቸው ነዳጅ ዘይት በሚመረትበት ተመንና የውል ሁኔታ ላይ የተመሠረተ" መሆኑን ደመደመ ። እያይዞም በእነዚህ አገሮች የአሜሪካ ኩባንያዎች የሚያደርጉት የምርት እንቅስቃሴ–ምን ያኽል ነዳጅ ዘይት እንዲመረቱና እንደሸጡ ፣ እናም ለእርሱ የከፈሉት ዋጋ እነዚያን አገሮች በተመለከተ "በማንኛውም ተፈጻሚ ጉዳይ የውጪ ፖሊሲያችን መሠረት ናቸው ።... የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች የሚያደርጉትና የአደራረጋቸውም ሁኔታ ከእነዚህ አገሮች ጋር ያለንን ግንኙነት ጥንካሬና የዐቪየትን በክልሉ መስፋፋትና ተጽእኖ የመቋቋም ችሎታችንን ይወስናል ።" የእነዚህ አገሮች ሕዝብ የምሥራቅንም ሆነ የምዕራብን የቅኝ አገዛዝ ክብርና መብት ተመልሶ በላያቸው መስፈን በተመለከተ አግባብነት ያለው ጥላቻ ያለባቸው ስለመሆኑ ያሜሪካ መንግሥት ሊቸገርበት ላለመፈለጉ የሀልቪዝም "ምንትስ መጣብህ/ሽ ዓይነት" በውሸት (ልጆችን) ማስፈራሪያ አመቺ ምክንያታዊ ማስረጃ ነው ።

የተጠቀሰው በሦስቱ ሚኒስቴሮች በጥምር የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ ቀጥሎም ፣ የአሜሪካ የነዳጅ ዘይት ፖሊሲ መሠረታዊ መንደርደሪያ የነዳጅ ዘይት ኩባንያዎቹና የአሜሪካ መንግሥት ጥቅሞች ተጓዳኝ መሆናቸውን በመገመት ላይ የተመሠረቱ ናቸው ። የአሜሪካን የውጪ ፖሊሲ ከግብ ለማድረስ ኩባንያዎቹ አስተማማኝ መሣሪያዎች ነበሩ ። ከመካከላቸው አምስቱ የአሜሪካ የሆኑ ከሰባት እስከ ስምንት የሚደርሱ ፣

አብረው መሥራት የለመዱ ጥቂት ኩባንያዎች የበላይነትን የያዙበትን በዶንብሔራዊ የነዳጅ ዘይት እንዱስትሪ አሁን ባለበት መልክ ጠብቆ ማቆየት የአሜሪካን ብሔራዊ ጥቅም መከባከብ ነው ። ስለ እንግሎ-ኢራኒያን በተፈጠረው ግጭት ከኢራን ጋር መስማማት አልተቻለም ። የአሜሪካ ቁርጠኝነት በነሐሴ 1945 በሲ·አይ·ኤ· ገንዘብ የተቀሰቀሰ ሕዝብ መንገድ ላይ በመውጣት በሞሳዴግ ላይ የደረሰውን መፈንቅለ መንግሥት በማስነሣት ሻሁ (ኋላ አገሪቱን ለቀው እንዲሸሹ የተደረጉት) ን ወደጣኦሱ (ፒኮክ) ዙፋን መመለስ በማያሻማ ሁኔታ ታይቷል ።

በተከታዩ ዓመት ፡ አዲስ የ "ኢራኒያን" የኩባንያዎች የሽርክና ስምምነት ተፈረመ ። በዚህ ሽርክና ውስጥ 40 ከመቶ ጥቅም በመያዝ ከሁሉም ትልቁ ባለሽርክና እንግሎ-አሜሪካን ነበር ፤ አምስቱ ትልልቅ የአሜሪካ ኩባንያዎች ፤ ማለትም የኒው ጀርሲው ስታንዳርድ ፡ ቴክሳስ ፡ ሶካል ፡ ሶኮኒና ገልፍ-እያንዳንዳቸው ሰባት ከመቶ (ወይም በዑድን 35) ነበራቸው ። ሮያል ደች የዓሥራ አራት ከመቶውን ባለቤትነት አገኘ ። የፈረንሳዩ ኮምፓኝ ፍራንሴ ዴ ፔትሮል ኩባንያ ስድስት ከመቶውን ደረሰው ። ቀሪው አምስት ከመቶ በበርካታ የአሜሪካ ነፃ የነዳጅ ዘይት ኩባንያዎች እጅ ነበር ። የአሜሪካ ትልልቅ ኩባንያዎች በዚህ ዓይነት በመካከለኛው ምሥራቅ የበላይነቱን ተቀዳጁ ። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በፊት ብሪታንያዊው እንግሎ-ኢራኒያን ብቻውን ኢራን ውስጥ የነዳጅ ዘይት ምርትን በብቸኝነት ይዞ የነበረ ቢሆንም ያንን የብቸኝነት ይዞታ ዛሬ የአሜሪካ ትልልቅ ኩባንያዎች እንዲካፈሉት ተደርጓል ። በተመሳሳይ ፡ ከጦርነቱ በፊት ብሪታንያውያን የነዳጅ ዘይት አምራቾቹ የሼኮች ግዛቶች ታማኝ የፖለቲካ አማካሪዎች ነበሩ ። ነገር ግን ከጦርነቱ በኋላ ፡ የአሜሪካ የፖለቲካ ተጽእኖ የበለጠ እየገነነ ይመጣል ። እናም ከሁሉም የበለጠ የታወቀ ክምችት ይዞ ዋና ነዳጅ ዘይት አምራቿ ሳዑዲ ዓረቢያ በአስተማማኝ ሁኔታ ያለጥርጥር በአራት የአሜሪካ ኩባንያዎች እጅ ትገኛለች ።

ይሁንና የመካከለኛው ምሥራቅ የነዳጅ ምርት ዋና ገበያ አሜሪካ መሆኗ ቀርቶ ምዕራብ አውሮፓና ጃፓን ሆኑ ። የአሜሪካ የገንዘብ ሚኒስትር ሮበርት አንደርሰን በኢራን የኩባንያዎች ሽርክና ውስጥ የአሜሪካንን ኩባንያዎች ተሳትፎ የአገሪቱ ብሔራዊ ደኅንነት ምክር ቤት ጥር 1946 ማጽደቁን ለሸንጎው መሪዎች ሲገልጹ ከኢራን የሚወጣው



ነዳጅ ዘይት የሚሸጠው በምዕራቡ ክፍላተ ዓለም ሳይሆን በምሥራቁ መሆኑን አረጋግጠውላቸዋል ። ይህንንም ግንዛቤ ቀጥሎ ሴናተር ሊንደን ቢ· ጆንሰንና የውጪ ጉዳይ ሚኒስትሩ ጆን ፎስተር ዳለስ የተጻጻፉት ደብዳቤ ዋቢ አልፎለታል ። ከሁለት ዓመት በኋላ ፡ በ1948 ቀጥሎ ግጆታ በሆነው ውጅታ የድፍድፍ ነዳጅ ዘይት "በኩታ" በማስገባት ፡ የአሜሪካ ያገር ውስጥ የነዳጅ ዘይት እንዱስትሪ ከመካከለኛው ምሥራቅ በርካሽ ከሚወጣ ድፍድፍ ነዳጅ ዘይት (የገበያ ሽሚያ) ይጠበቅ ነበር ። የአሜሪካ ገበያ በመካከለኛው ምሥራቅ ለሚመረት ነዳጅ ዘይት አስተማማኝ ሁኔታ ተዘግቶ ነበር ። ስለሆነም ያ ነዳጅ ዘይት ወደ ምዕራብ አውሮፓና ወደ ጃፓን ገበያ መውጣት ነበረበት ። የአሜሪካ ትልልቅ የነዳጅ ዘይት ኩባንያዎች በመካከለኛው ምሥራቅ ነዳጅ ዘይት አምራች ተቋራጮች ውስጥ ባላቸው ደረጃ በዚህ የኃይል ምንጭ ገበያ ፍላጎት ከድንጋይ ከሰል ወደነዳጅ ዘይት መዞር ሊጠቀሙበት ይችላሉ ።

ዋሽንግተን የሚገኘው የመካከለኛው ምሥራቅ የምርምርና የመረጃ ፕሮጀክት ባልደረባ — ጆ ስቶርክ በ1940 እና የቤንዚን ላኪ አገሮች ድርጅት በ1952 በተመሠረተበት ዓመት መካከል ያሉትን ዓመታት የነዳጅ ዘይት ኩባንያዎቹ "የወርቅ ዓመታት" ይሏቸዋል ። በዚያ ጊዜ ውስጥ መካከለኛውን ምሥራቅ የከፈሉ መንግሥታትና የነዳጅ ዘይት ኩባንያዎች የሚካፈሉት ግዙፍ ትርፍ ፤ ማለትም ትክክሉን ለመናገር 22·2 ቢሊዮን ዶላር ፤ ተሸንሽኖበት ። ከዚህ ውስጥ መንግሥታቱ 9·4 ቢሊዮን ዶላር ሲደርሳቸው ኩባንያዎቹ 12·8 ቢሊዮን ዶላር ወደየአገራቸው ጫኑ ። በመጨረሻም ገፋ ያለ ገንዘብ ወደነዳጅ አምራቾች አገሮች ገባ ። ከዚያ በፊት ፤ ኢራቅን ጨምሮ ፤ የባሕረ ሰላጤው አገሮች በአንፃሩ ደሀ ነበሩ ። በቤንዚን ላኪ አገሮች ድርጅት አማካይነት የሚያካሄዱት የጋራ ድርድር በአሸዋዎቻቸው ሥር ካለው ጥቁር ወርቅ ትልቅ ድርሻ አስጨበጣቸው ፡ ነገር ግን 1960ዎቹ እንደገቡ ፡ የዓረቦቹ አገሮች መሪዎች ፤ ስርጭቱንና ሽያጩን በኩባንያዎቹ እጅ እንዲቆይ ካደረጉ እንኳን በኋላ ፤ በምርቱና በሽያጩ ዋጋ ላይ ይበልጥ የጠበቀ ቁጥጥር ማድረግ ፈለጉ ። ዓይነተኛውም ጥያቄ "ነዳጅ ዘይትን የሚቆጣጠረው ማን ነው? እና በቁጥጥሩ የሚጠቀመውስ ማን ነው?" ሆነ ።

ከዚያም በዓረብና በእሥራኤል መካከል የአክቶበር ጦርነት በተካሄደ ማግሥት በ1963 በአሜሪካና በሌሎች ምዕራባውያን አገሮች ላይ የነዳጅ

ዘይት ማዕቀብ ተጣለ ። ብሪታንያውያንና ፈረንሳውያን የእነዳውን ፖሊሲ ባስተባበረው የዓረብ ሚኒስትሮች "ወዳጅ" በመባላቸው ማዕቀቡ ከሁሉ አስቀድሞ የተሰነዘረው ለአሜሪካና ለኔዘርላንድስ (ሆላንድ) ነበር። ብሪታንያውያንና ፈረንሳውያን ከመነሻው በአሜሪካና በኔዘርላንድስ ላይ በተሰነዘረው ልዩታ ተጠቅመው ለደንበኞቻቸው የሳዑዲን ነዳጅ ዘይት አቅርቦት ለመጨመር ሞከሩ ። ከዚህም በላይ ፡ የማዕድን ሠራተኞች ማኅበር የቀጣውን የሥራ ማቆም አድማ ለማክሸፍ የዓረቦች ዘይት ለብሪታንያ መንግሥት የማካካሻነት ተስፋ አስገኘላት ፡ ለፈረንሳዮችም በሳዑዲ ዓረቢያ የአሜሪካን ሞኖፖል ለመጣስ ማዕቀቡ እድል ሰጣቸው ።

የብሪታንያና የፈረንሳይ መንግሥት የወዳጅ መንግሥትነትን ደረጃ በመቀዳጀታቸው የነዳጅ ዘይት ኩባንያዎቻቸውን ገንዘብ እንዲከፍሏ ቸው ግፊት አደረጉባቸው ። የዓረብ አገሮችም በበኩላቸው እሥራኤልን በ1959ኙ የስድስት ቀን ጦርነት ከተያዙት ግዛቶች አስገድዶ በማስወጣት ዘመቻቸው የነዳጅ ዘይት ኩባንያዎቹን እርዳታ ፈለጉ ። ኩባንያዎቹ ይህን አላደረጉም ። እንዲያውም ፡ ይባስ ብለው ፡ የሚጓጉዙትን ነዳጅ ዘይት መድረሻ አቅጣጫ በውቅያኖስ ውስጥ እየለወጡ ፡ በእጥረቱ መጠን እንዳር በማካካስ ፡ ዓረቦች በአሜሪካና በኔዘርላንድስ ላይ የጣሉትን የነዳጅ ዘይት ማዕቀብ ተጽእኖ አለዘቡት ። ኩባንያዎቹ ይህን የፈጸሙት በሙሉም ሆነ ከሁሉ አስቀድሞ የአንድ የተወሰነ አገር የውጪ ፖሊሲ መሣሪያ ሆነው አልነበረም ። ለየራሳቸው ሲሉ ጥቅሞችን ማመዛዘናቸው ነበር ፡ እንጂ ። ኩባንያዎቹ በዚህ አድራጎታቸው ከዚያ ወዲህ ብሔራዊ የውጪ ፖሊሲ ጥቅም ተግባራዊ የሚያደርጉባቸው አስተማማኝ መሣሪያ ዎች መሆናቸው መቅረቱን አሳዩ ።

ማዕቀቡና የኩባንያዎቹ ድርጊት ሁለት ዋና ዋና ውጤቶች አስከ ተለ። መጀመሪያ ፡ አሜሪካ ከፋርስ ባሕረ ሰላጤ አገሮች ጋር ያላትን ግንኙነት ከእንግዲህ በነዳጅ ዘይት ኩባንያዎቹ አማካይነት ልትመራ እንደማትችል ገባት ። ከሰላጤው አገሮች ጋር በሚኖራት ድርድር የበለጠ ቀጥተኛ ሚና ለመጫወት ተገደደች ። የነዳጅ ዘይት ምርትና የሽያጩም ዋጋ ውሳኔ ጦር መሣሪያንና ፖለቲካን በተመለከተ ከሚተላለፍ ውሳኔ ጋር በይበልጥ በይፋ የተያያዘ ሆነ ። በ1964 እና በ1965 የሳዑዲው ንጉሥ ፈይሳል አሜሪካውያን "ማንኛውንም ነገር ማጣት" የማይፈልጉ ከሆነ ፡



አገራቸው በክልሉ የምትከተለውን ፖሊሲ ባስቸኳይ መለወጥ የሚያስፈ ልጋት መሆኑን እንዲገነዘቡላቸው በማድረግ የአርማኮን ወዳጅ ኩባንያዎች በመልእክት አድራሽነት ተጠቅመውባቸዋል ። በ1965 ወደዩ ይህን መልእክት የአሜሪካ ፖሊሲ አውጪዎች በአመዛኙ ቸል አሉት ፡ በነዳጅ ዘይት ማዕቀቡ ማግሥት ግን ሳዑዲዎች መልእክት አመላላሽ አላስፈለጋ ቸውም ። ጥያቄያቸውን ፡ በተለይ የተራቀቀ ጦር መሣሪያ ሽያጭ ጥያቄያቸውን ለመመለስ ጉጉ ፖሊሲ አውጪዎች በቀጥታ ይሰሟቸው ነበር ።

ሁለተኛ ፡ የአሜሪካ መንግሥት አገሮቹን ለማስማማት ፡ ወይም ቢያንስ የመካከለኛው ምሥራቅ ነዳጅ ዘይት አሜሪካ ብቻ ሳይሆን ተባባሪዎቿ ምዕራብ አውሮፓና ጃፓን በአስተማማኝ ሁኔታ ማግኘታቸ ውን ለማረጋገጥ ውጥረት ይቀንስ ዘንድ በዓረቦችና በእሥራኤሎች ድርድር መኻል ራሱ በቀጥታ እንዲገባ የበለጠ የሚያስገድደው ምክንያት እንዳለ ተሰማው ።

የአሜሪካ በጉንፉ በቀጥታ መግባት የበለጠ ግልጽ እንደሆነ ፡ ውስጠ ታዋቂ የነበረውም የአሜሪካ የፋርስ ባሕረሰላጤ የነዳጅ ዘይት ከምችት ለራሷና ለተባባሪዎቿ አገሮች ወዳጅ በሆኑ እጅ ውስጥ እንዲቆይ ለማድረግ ያላት ቁርጠኝነት ይፋ እየወጣ መጣ ። የኒክሰን ፖሊሲ የባሕረሰላጤው ሁለት ኃያላን አገሮች — ኢራንና ሳዑዲ ዓረቢያ የአካባቢውን አገሮች መሪነት እንዲጋሩ በማግባባት አሜሪካ የገባችውን ቃል ሊወስን ሞከረ ። እነዚህ "መንታ የመረጋጋት ዐምዶች" በእንዱስ ትሪ የበለጸገው ምዕራቡ ዓለም የፋርስን ባሕረሰላጤ ነዳጅ ዘይት ያለማወላወል ማግኘት መቻላቸውን እንዲያረጋግጡ ታስቦ ነበር ። በአፀፋ ውም የአሜሪካ የጦር መሣሪያ ግምጃ ቤት ለሁለቱም አገሮች ያለገደብ ተከፍቶላቸው ነበር ። የአሜሪካ ብሔራዊ ደህንነት አማካሪ ሄንሪ ኪ ሲንጀር ያለገደብ እጅግ የተራቀቀውን የአሜሪካ መሣሪያ መግዛት ለኢራን እንዲፈቀድላት በ1964 መመሪያ ሰጡ ። እንዲሁም ለሳዑዲዎች ፡ አገራቸውን በገጠማት ሥጋት ትንተና ሳይሆን ፡ ብቻ አሜሪካ "ቀና አመለካከቷን" ለማሳየት መሣሪያ ከተሸጠላቸው በኋላ በጦር መሣሪያ ሽያጭ የአሜሪካ ሸንጐ ያለጥርጥር እንዲስማማ ማባበል ፡ ማስፈራራትና መደለል አስፈልጎ ነበር ።

ይህ የረጅም ጊዜ እቅድ ብርቱ ችግር ነበረበት ። መጀመሪያ ፣ "መንታ ዐምዶቹ" ለራሳቸው ጥቅም ፍሊጋ እንደማይጠቀሙባቸው ዋስትና የለም ። ይህ በተለይ ፈጣን እድገት የሚያስከትለውን ልዩነት ለማስተናገድ የሳዑዲ ንጉሣዊ ቤተሰብ ያለውን ዓይነት የፖለቲካ መጣጣም በሌላት በኢራን ውስጥ በተለይ ይህ የሰላም መናጋት ሊያደርስ ይችላል ። በኢራን የጦር መሣሪያን ከማካባቱ ጐን በጣም ከፍተኛ ጉብኝነትና ከልክ በላይ ፍጆታ አንሠራፋ ። በገንዘብ የመግዛት ዐቅም ማሀቀጥ በኑሮው ዝቅተኛ የሆነውን የኅብረተሰብ ክፍል ከፉኛ ከበደው ። የብዙ ሰው ከገጠር መፈናቀል ሕዝቡን ወደለመደው የኑሮ መልክ የሚመልሰው አንድ ሰው እንደሚንግለት ወደማመንና በዚህም ትንቢትና ተስፋ ወደመኖር እንዲያዘነብል አደረገው ።

ይህንንም ብሶት አንድ ውጤታማና የመሳብ ተሰጥዎ ያላቸው የተሰደዱ ተቃዋሚ የሃይማኖት መሪ በየመስጊዱ በሚደመጠ ዘመናዊ የካሴት ክሮች ገለጹት ።

በ1971 ፣ የኢራን ሻህ የአገራቸው ጦር ኃይል ሊቆጣጠረው ባልቻለው ወይም ባልፈለገው ሕዝባዊ ቁጣ ተገረሰሱ ። እርሳቸውንም ጨርሶ በምዕራቡ ዓለም ያልታወቁ የሙላሆች ሃይማኖታዊ ተቋም የተመራ መንግሥት ተካቸው ። ሻሁ ልክ ኢራንን ከአገሮቹ መኻል አንድ ኃያል አገር ለማድረግ የቋመጡለትን ብልጽግና በመጨረሻ በመቀዳጀታቸው ዓላዩት ሰሰት ፣ እብሪትና ኩራት እየተቀጡ መስሎ ይታያል ። በሂደቱም ላይ ፣ የአሜሪካ የረጅም ጊዜ እቅድ በድዑኘት ዐምድ ላይ የታነፀ መሆኑ ተጋለጠ ። ሙላሆች ሻሁን ብቻ ሳይሆን የራሱንም የሥልጣኔን ሐሳብ እንቀበል አሉ ። የምዕራቡን ዓለም ፈለግ ተከትለው በመሄድ ፈንታ አወገዙት ። እንዲሁም የምሥራች ድምፃቸውን ከአገራቸው ድንበር ባሻገር ለማሰማት ሐሳብ እንዳላቸው ለፈፉ ።

በኢራን የደረሰው ክፉ አደጋ አሜሪካ ለሳዑዲ ዓረቢያ የገባቸውን ቃል የበለጠ አጠንክረው ። የቀድሞው ፕሬዚዳንት ጂሚ ካርተር የሳዑዲን ደኅንነት ከውጪ ወረራ የሚጠብቁ ለመሆናቸው ዋስትና ሰጡ። የቀድሞው ፕሬዚዳንት ጂሚ ካርተር ቃል ኪዳንን በማስፋት የሳዑዲን ሥርዐ መንግሥት ያለማመለስ ሳዑዲን እንዲገ" መደገፍን እንዲያካትት አደረጉ ። በዓሥር ዓመት ውስጥ አሜሪካ በፋርስ ባሕረ ሰላጤ የምትከተለው ፖሊሲ ብዙ ተለዋወጠ ። መጀመሪያ በነዳጅ ዘይት ኩባንያዎቹ



አማካይነት ከልሉን ስትቆጣጠር ቆየች ። ቀጥላም በክልሉ ካሉት መኻል ውለቱን እጅግ ተፈላጊ አገሮች በአካባቢው የታጠቁ ሕግ አስከባሪ አድርጋ መለመለች። በመጨረሻም ከሁሉም ትልቋን ነዳጅ ዘይት አምራች ሳዑዲ ዓረቢያን ከውስጥና ከውጪ ጥቃት የመጠበቅ ኃላፊነቱን ራሷ ለመያዝ ወሰነች ።

እሁንም የዓረቦች የነዳጅ ዘይት ማዕቀብ መጣል ያስከተለው ሌላ ነገር ፈረንሳይ ለረጅም ጊዜ ስትመኘው የኖረችውን አሜሪካ ሳዑዲ ዓረቢያ ውስጥ ያላትን ሞኖፖል የመሻር ዓላማ ከግብ ማድረሷን ነበር። አውሮፓ ፣ በተለይም ከአሜሪካ በጣም በበለጠ በመካከለኛው ምሥራቅ በተለይም በሳዑዲ ዓረቢያ ነዳጅ ዘይት ታምና ያለችው ፈረንሳይ ይህን ነዳጅ ዘይት ማግኘቷን ለማረጋገጥ በአሜሪካ ባለብዙ ብሔር የነዳጅ ዘይት ኩባንያዎች መተማመኑን በ1939 በበርካታ ኩባንያዎች ሽርክና የተደራጀውን አራምኮ ከመሠረተ ጀምሮ ልትታገሠው የማትችለው ጉዳይ ሆኖባታል ።

በ1959 ከስድስቱ ቀን ጦርነት በኋላ ፣ ፈረንሳይ ኢራቅ ውስጥ አዲስ የነዳጅ ዘይት ፍለጋና ቁፋሮ ትልቅ ሥራ አግኝታ ኮንትራት ተቋረጠች ። ይህ በመላው በመካከለኛው ምሥራቅ በአሜሪካና በእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም ላይ እንደተገኘ ታላቅ ድል ተቆጥሮ "እንኳን !" አሰኝቶ ነበር ። በፈረንሳይም እኩል እርካታ አስገኝቶ ነበር ። የተከበረው የፈረንሳይ ዕለታዊ ጋዜጣ — ለ ሞንድ ፣ "በፈረንሳይ የተነሣ ፣ እንግሊዞችና አሜሪካኖች እስካሁን ፍለጋ ወዳልተሄደባቸው የአገሪቱ ክፍሎች እንዳ ችም የመስፋፋት እድል ተነፍገዋል ። በብልጠት ተበልጠዋል ። አደገኛ የፖለቲካ ቀውስ ሳያስከትሉ ፈረንሳይን ካልተነኩት የኢራቅ ክፍሎች ከአንድም ቦታ ሊያስቀሯት አይችሉም ። ባለፈው ጦርነት ማግሥት በዚህ ክልል ፈረንሳይን እንዳትገባ ስለከለከሏት እነሆ የእጃቸውን አገኙ ።" በማለት ጽፎ ነበር ።

ከጥቅምት 1959ኙ ጦርነት በኋላ ፣ በሳዑዲ ዓረቢያ ሃያ አምስት ዓመት የኖረውን የአሜሪካ ሞኖፖሊ ለማፍረስ ለፈረንሳዮች አጋጣሚው ታያቸው። ፈረንሳይ ለሳዑዲዎችና ለሌሎችም የዓረብ አገሮች የጦር መሣሪያ ሽያጯን አጧጧፈች ። የፈረንሳይ ብሔራዊ የነዳጅ ዘይት ኩባንያ ከሳዑዲ ድፍድፍ ነዳጅ ዘይት ለማስመጣት ከሳዑዲ ባለሥልጣናች ጋር ለረጅም ጊዜ የአቅርቦት ኮንትራት ገባ ። እናም በ1971 ጥቂት

መንቻካ ተቃዋሚዎች በመላው እስልምና ካለው ሁሉ የላቀውን ቅዱስ መካን - የመካውን የካባ መስጊድ በያዙ ጊዜ አመጸኞቹን አሳዶ ለመምታት ሳዑዲዎች ፀረ አማጽያን የባለሙያ ምክር የጠየቁት ከአሜሪካ ሳይሆን ከፈረንሳዮች ነው ። ይህን ሁኔታ አሜሪካ ያላየችው እንዳይመስል፡ እርግጥ ፡ እያንዳንዱ የታሪክ ቪቴ ዙረት በክልሉ ደግቅ ፖለቲካ ውስጥ የአሜሪካን ቀጥታ ፖለቲካዊና ወታደራዊ ግልታ ንብነት ወደውስጥ እያጠለቀው ሄደ ።

በዚሁ ጊዜ ነፃነቷንና ደኅንነቷን በመጠበቅ ረገድ ሳዑዲ ዓረቢያ የራሷ ሐሳብ ነበራት ። አገሪቷ ምናልባት በዓለም መኖሪቻው ከታወቀው የነዳጅ ዘይት ክምችቶች ሁሉ መኻል እጅግ በላቀው ጉድጓድ ላይ ተቀምጣለች ። ነገር ግን ሕዝቧ ሰባት ሚሊዮን ብቻ ነው ። (ሳዑዲዎች ሕዝብ እንዲቆጠር በፍጹም ፈቅደው ስለማያውቁ ይህም የተጋነነ ግምት ይሆናል) ። የሳዑዲ ጦር ኃይሎች ከአገራቸው የበለጠ ብዙ ሕዝብ ካላቸው ጐረቤቶቿ ሁሉ መኻል ማንኛውም በቁርጠኝነት ወሯቸው ቢሆን ኖር ፡ ዛሬም ቢወሯቸው ፡ ወደፊትም ቢወሯቸው ፈጽሞ በብቃት ሊያግዱት ባልተሳናቸውም ነበር ። ስለዚህ ፡ ሳዑዲዎች ከጐረቤቶቻቸው እያንዳንዱን በገንዘብ በመደለል የክልሉን ጥቅሞች ሚዛን የመጠበቅ የሩቅ ጊዜ ግብ ሲከተሉ ኖረዋል ። በየጊዜው ለግብጽ ፡ ለኢራቅና ለሶርያ በቀጥታ ድጐማ ተከፍሏል ። በኢራቅ ረገድ ይህ ዘዴ ከሸፈ ።

ኢራቅ ኢራንን ለመግታት ያስፈለጋትን ጦር መግሪያ ዋጋ በመክፈል ሳዑዲ (እና ኩዌትን ጨምሮ በሌሎች የሼኮች ግዛቶች) ፈጣሪውን የሚበላ ልዩ አውሬ በመፍጠር ግብረአበር ሆናለች ። የኢራቅ አመራር እስከዶቃ ማሠሪያው ታጥቆ ፡ በፖለቲካ ልቡ ሞልቶ ፡ ነገር ግን በገንዘብ ረገድ በዕዳ ተዘፍቆ ፡ እያለ የክልሉ የኃይል ሚዛን ለእርሱ ያደላ መሆኑን እምኖበት ነበር ። 1982 እንደባተ ኢራን ድል ተመታና ተዳክማ ነበር። ሶርያ በሊባኖስ አረንቋ ውስጥ ተዘፍቃ ነበር ። ግብጽ በአገር ውስጥ የኢኮኖሚ ለውጥ ጉዳይ ከዓለም የገንዘብ ድርጅት ጋር በመጋጨቷና የባሰ ድህነት ያለበት ኢኮኖሚዋ ከሕዝብ ሁከት አንድ እርምጃ ቀድሞ በመገኘቱ ነቀረ ችግር ፡ የተሽመደመደች መስላ ነበር ። እሥራኤልም ከሩሲያ ለተመለሱ ፈላሾቿ ቦታ በመስጠትና በፍልስጥኤም ጥያቄ ላይ ከአሜሪካ ጋር እየባሰ በመሄድ ላይ በነበረ የከረረ ፍጥጫ ተወጥሮ ነበር ።



ሣዳም ሑሴን ፡ አሜሪካ ከባግዳድ መንግሥት ጋር ለመቀራረብ ስትሞክር ሲያዩ ፡ እናም አሜሪካ የኩዌትን ደኅንነት ለመጠበቅ የገባችው ቃል እንደሌለ ሲያረጋግጡ ለኢራቅ በክልሉ የልዕለ ኃያላን ደረጃ ካባ መደረብ ፡ በኩዌት ላይ ያላትን ታሪካዊ የይገባኛል መብት ማስጠበቅ ፡ እናም ከሁሉ በላይ የተወሳሰበውን የእዳ ችግርና ከኢራን ጋር የተካሄደው ጦርነት ያስከተለውን በመብሰልሰል ላይ ያለ ብሶት በኃይል ማስወገድ መንገዱ የጠራ እንደሆነ ደመደሙ ። በባሕረ ሰላጤው ታላቋ ብሪታንያ በግድ የሚነችውን የግዛት ክልል ትሸረዋለች ፡ በመጨረሻ ወደባሕሩ መግቢያ መውጫ ታገኛለች ፡ ኢራቃውያን ለእንርሱ ሲዋጉ ፡ ሲደሙና ሲሞቱ የባሕረሰላጤው ዓረቦች በጦርነቱ ጊዜ በሙሉ በቅንጦት ሲኖሩ ስለመቆየታቸው በሰፊው ለተበፋፋው ተቃውሞ መተንፈሻ ይሰጣል ።

ሣዳም ሑሴን ኩዌትን እንዲወሩ የገፋፋቸው ምንም ይሁን ምን ፡ የኩዌታውያን ኀዘን ምንም ይሁን ምን ፡ ወረራው ብቻውን ማንኛውንም የአሜሪካ ጥቅም ወዲያው ለሚደርስ አደጋ አያጋልጠውም ። የኢራቅ የኩዌትን የነዳጅ ዘይት ክምችት መቆጣጠር በነዳጅ ዘይት ዋጋ ገበያ ላይ ሚዛን ወደርቧ እንዲደፋ አያደርገም ። ይህን ዓይነቱን ምርት ከዓለም ገበያ ማስቀረት ለኢራቅ የኢኮኖሚ ጥቅም የለውም ። ጉዳዩ የዋጋ ነው ፡ በ1965 የደረሰው የነዳጅ ዘይት ችግር ሙሉ በሙሉ እንዳሳየው የነዳጅ ዘይት ዋጋ በጣም መናር ውድ ዋጋ የሚጠይቅ ክምችትን ፍለጋና ጥቅም ላይ መዋል ያበረታታል ። በተጠቃሚዎቹም አገሮች ውስጥ የበለጠ ጠንከር ያለ የክምችት ጥረት እንዲደረግ ያነግግል ። ይህ ሁሉ ዋጋቸው እንስተኛ ፡ ግን በፖለቲካ በሚያስተማምኑት የፋርስ ባሕረሰላጤ ነዳጅ ዘይት አምራች አገሮች ላይ ያለውን ጥገኝነት ይቀንስዋል ። በቤንዚን ላኪ አገሮች ድርጅት ውስጥ ያለው ነቀረ ንትርክ የተጠቃሚዎቹን አገሮች ጥገኝነት ስለሚሹ የዋጋን ለዘብተኝነት በሚጠይቁ እንደሳዑዲ ዓረቢያ ባሉትና በአስቸኳይ ገንዘብ ስለሚያስፈልጋቸው ከፍ ያለ ዋጋ ለማግኘት ምርቱን ለመወሰን በሚሹት እንደ ኢራቅ ባሉ አገሮች መካከል የሚካሄድ ነው ። ነገር ግን ይህ በመሠረቱ በእንፃሩ ሲታይ በጠባብ ልዩነት ላይ የሚካሄድ ክርክር ነው ።

የቤንዚን ላኪ አገሮች ድርጅት አባል ባልሆኑ ነዳጅ ዘይት አምራች አገሮች ምርቱ ጨምሯል ። ሜክሲኮ ፡ አንጐላ ፡ በሜን ባሕርና ሌላም ዘንድ ያሉ አዳዲስ አምራቾች የቤንዚን ላኪ አገሮችን ድርጅት የእነርሱን

አሠራር እንዲከተል አስገድደውታል ። የእነዚህ ተጨማሪ አምራቾች መኖር ቤንዚን ላኪ አገሮች ድርጅት ውስጥ በዋጋና በምርት የተነጣጣጦት እንዲፈጠር አስገድዷል ። የባግዳዱ መንግሥት የኩዌትን ምርት ከራሱ ምርት ጋር ደርቦ መያዝ ቢሳካለት እንኳ ፣ ይህ የሁለት አመለካከት ሚዛን በመሠረቱ አይለወጥም ። አስገራሚ ቢሆንም እንኳን ፣ ጉዳዩ የኩዌት መወረር አይደለም ፤ ግን ይልቅ ኢራቅ ሳውዲ ዓረቢያን ልትወር ወይም በበላይነት ልትቆጣጠራት የመቻሏ ሥጋት ነው ። ሳውዲ ዓረቢያ ፣ ኩዌትና ኢራቅ በአንድነት ከታወቀው የዓለም የቤንዚን ክምችት አርባ ከመቶውን ይይዛሉ ። ዓለም ከ1960ዎቹ (በ1965 ከመቶ 35 እና በ1971 ከመቶ 43) በፊት ከውጪ ታስመጣ ከነበረው የነዳጅ ዘይት ፍጆታ ድርሻዋ ዛሬ የምታስመጣው (45 ከመቶው) ብልጫ አለው ። ነገር ግን ዛሬ የዓለም ኢኮኖሚ በጠቅላላው በኃይል ምንጭና በተለይም በነዳጅ ዘይት መጠቀሙን በጣም ቀንሷል ። ይህም የሆነው ጥቅም ላይ የሚውለው የኃይል ምንጭ ከጠቅላላ ብሔራዊ ምርት ጋር ፣ እንዲሁም ጥቅም ላይ የሚውለው ነዳጅ ዘይት ጠቅላላው ጥቅም ላይ ከሚውለው የኃይል ምንጭ ጋር ያለው ንጽጽር በመቀነሱ ነው ። ሆኖም ግን ዛሬም የአሜሪካ ዋና ዋና ተባባሪ አገሮች በፋርስ ባሕረሰላጤ ነዳጅ ዘይት በብዛት መጠቀማቸውን እንደቀጠሉ ናቸው ። ስለሆነም በ1981 ፈረንሳይ ከተቀመጠችበት ነዳጅ ዘይት 35 ከመቶው ፣ ኢጣልያ 32 ከመቶው እና ጃፓን 64 ከመቶው ከፋርስ ባሕረ ሰላጤ ያስመጡት ነው ።

የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር ጀምስ ኤ·ቤከር ግልሳይ በአሜሪካ ምክር ቤት የውጪ ጉዳይ ኮሚቴ ፊት ቀርበው በሰጡት የምሥክርነት ቃል፡

> ምናልባት በኢኮኖሚ ረገድ ለእድገ የተጋለጠው የዓለም ወደፋርስ ባሕረሰላጤ የኃይል ምንጭ ሀብት ሊያድርስ በሚያስችል መንገድ ላይ ተገኝ መሆን እንደሆነ እጅግ ግልጽ ነው። ··· ጥያቄው የነዳጅ ዘይት ከኩዌትና ከኢራቅ መምጣት ጠባብ ጥያቄ አይደለም ። ይልቁንስ ብቻውን እየወሰነ ሁላችንም በንግድ ወደኢኮኖሚ ድቀት ወይም እንዲያውም ተንኳሬ ወደማጣት ጽልመት እንገባ እንደሁ ከበላይ ሆኖ በማዘዝ እየወሰነ የዓለምን የኢኮኖሚ ሥርዓት አንቆ እንዳልነበረ ማድረግ በሚችል ሰምባንን ነው ።

ሆኖም ግን ፣ ለዚህ ትዝት ዕውን መሆን ኢራቅ ያልዛተችባትን መቀዳጀት ይኖርባታል ፤— ሳውዲን መያዝ ።

የአሜሪካ ማእከላዊ የስለላ ድርጅት ሲ·አይ·ኤም· ሆነ የአሜሪካ የመከላከያ ስለላ ድርጅት ኢራቅ ሳውዲ ዓረቢያን ልትወር እንደምትችል ገምተው እንደማያውቁ የቡሽ አስተዳደር ባለሥልጣኖች ያምናሉ ።



ባግዳድ ኢራንንም ሆነ ኩዌትን ከመውረሯ አስቀድማ በእነዚህ በዒላማዎቿ ላይ ያላትን ታሪካዊ የይገባኛል ጥያቄ በማጉላት አደገኛሪ ፕሮፖጋንዳ ነዝታ ነበር ። ሳውዲ ዓረቢያን በተመለከተ ግን ሁኔታው ይህ አልሆነም ። እንደዕውነቱ በ1981 ከሳውዲ ዓረቢያ ጋር በወረራ ያለመፈሳለግ ስምምነት ተፈራርማለች ። የአሜሪካ አስተዳደር ባለሥልጣኖች እንደሚሉት ኢራቅ የምታስጋው የባግዳድ መንግሥት "በማስፈራራት" እንደምንም ብሎ የሳውዲን የነዳጅ ዘይት ፖሊሲ መቆጣጠር መቻሉ ላይ ነው ። ኢራቅ በግዙፉ ሠራዊቷና ሕዝብ የሚፈጅ የጦር መሣሪያ ግምጃ ቤቷ የሳውዲ ዓረቢያንና እንዲሁም የትንሾቹን የነዳጅ ዘይት አምራች የተባበሩት የዓረብ ኤሚሮች ግዛት መቆጠጠር ብትችል ከዚያ ወዲያ ከዓለም የነዳጅ ዘይት አቅርቦት ወደግማሹ በሚቃረበው ላይ ጉልህ ተጽእኖ ልታደርግ እንደምትችል ይወሳል ። ለአሜሪካ አስተዳደር አሳሳቢው የኩዌት ጉዳይ ሳይሆን ከፋርስ ባሕረሰላጤ በስተ ዓረቢያ በኩል ያለው ነው ። እነዚህ ባለሥልጣኖች ወረራን ለማስቀረት የተንከፈንና የቁርጠኝነትን አባቤ ለማጉልመስ የአሜሪካ ጦር ኃይል በአከባቢው መገኘት አስፈላጊ መሆኑን ይናገራሉ ። በዚህ ዓይነቱ ፈተና አንፃር ድክመት በፋርስ ባሕረሰላጤ የተከናወነው የአገር ግዛቶች አሸናሸን ቋሚ እንዳልሆነ ከመቀበል ያልተለየ ይሆናል ። እንዲሁም ይጉዖ በዚህ ክልል መረጋጋት እንደ በረሃ ብኙታ የማይደረስበት መሆኑን እንዲተቀበሉት ያስቶጥራል ።

፲፩

# እንበሳውና የበግ ግልገሏ

የኢራቅና የኢራን ጦርነት ለማብቃት ሁለት ዓመት ሲቀረው ፥ በ1978 ፥ ማዝኸር አ-ሀሚድ የተባሉ ዓረብ ተንታኝ ብዙ ርቃ ከምትገኘው ከዋሽንግተን በባሕረ ሰላጤው የተከናወኑትን ነገሮች በጥልቅ አጤኗቸው ። በተመስጦም እንዲህ አሉ፦

> በምንም መንገድ በኢራን ግምባር በመጨረሻ ሰላም ቢመጣ ፥ ልክ በበለጠ ጠብ በበዛበት የባሕታ ገብነት ዘመናት ፥ በመሠረቱ ያው የፖለቲካ አመራር በቦታው ላይ እያለ ኢራቅ እንደገና ሐሳቧን ወደትንንሾቹ የባሕረሰላጤው አገሮች ፊቷን ላለማዞር ማንኛውስ ሰው እንዴት እርግጠኛ ሊሆን ይችላል? ለምሳሌ ከኩዌት ጋር ያለው የወሰን ግጭት አሁንም መፍትሔ ሳያገኝ አለ ። ባግዳድ ገንዘብ ለመንጠቅ ወይም እንዲያውም ራሷ ያኛትን መፍትሔ እስገድዳ ለማስቀበል ከልክ በላይ በሚገባ የታጠቀና አሁን ደግሞ ልምድ ያገኘ ጦር ኃይል አትጠቀም ይሆን!

እንደሰውነቱ ፥ ሀሚድ እየጻፉ እያሉ ፥ ሣዳም ሑሴን በ1972 የጀመሩት ጦርነት መጥፎ አቅጣጫ እየያዘ ሄደ ። በወቅቱ ፥ የኢራቅ መንግሥት ድል ይቀዳጃል—ብሎ ለማሰብ ምንም ምክንያት አልነበረም። በሬጋን አስተዳደር ዘመን አንድ ከፍተኛ የመከላከያ ሚኒስቴር ባለሥልጣን የነበሩት ሪቻርድ ኤል·አርሚቴጅ ኢራቅ በኢራን እንደምትሸነፍ አብዛኞቹ የዓረብ ፥ ያውሮፓና የአሜሪካ ተንታኞች "በስጋት ነጥተው" እንደነበር አስታውሰዋል ። በትክክል እንዴትና በማ እንደሆነ በዕውነት ባይታወቅም—ነገሩ ሁሉ ተስፋ ወደማስቆረጥ ደርሶ በመጨረሻ የጦርነቱን አመራር ለባለሙያ የጦር መኰንኖችና ስትራተጂስቶች እንዲለቁ ሣዳም ሑሴንን ማግባባት ተችሎ ነበር ።

ግን ሀሚድና ሌሎች ጥቂት ተንታኞች ቀደም ሲል እንደመዘገቡት በኢራቅና በኩዌት መኻል አይቀሬ ባይባልም ጦርነት የሚነግ መስለ ። የባዓዝ ፓርቲ ለዓረብ ብሔረተኝነት ያደርኩ ነኝ እያለ ቢናገርና ከቴህራን



መንግሥት ጋር በተካሄደው ጦርነት ወቅት ኩዌት ለባግዳዱ መንግሥት ብዙ ቢሊዮን ዶላር ብትረዳም ፥ ኢራቅ ግዛቷን ይዛብኛለች የምትላትን ደካማና ለበሳሴ ጐረቤቷን ትንቃት ነበር ።

በባህልና በዘዬ ያለው ከፍተኛ ልዩነት አይንግና ፥ በኩዌትና በኢራቅ መኻል ሰፍና ያለው ውጥረት ጥልቅ የታሪክ ፥ የመልክአምድርና የአመለካከት መሠረት አለው ። ከኩዌት ወረራ ጀምሮ የባግዳድ መንግሥት እንግሊዝኛ ጋዜጣ "ዚ ባግዳድ ኦብዘርቨር" ኢራቅ በኩዌት ላይ ያላትን የይገባኛል ጥያቄ ታሪካዊ መሠረት የሚመለከት ጽሑፍ ከምላ ጕደል በየቀኑ ሲወጣ ነበር ። ለምሳሌ በነሐሴ 1982 የወጣ አንድ ዘገባ ኢራቅ ከክርስቶስ ልደት በፊት በሁለት መቶ ዓመት ኩዌትን ታጠቃልል እንደነበር ይናገራል ። ለዚህ እንደማስረጃ የቀረበው የአሶርያውያንን ነገሥታት የሚመስል የጡብ ሐውልት በፊይላካ የኩዌይቲ ደሴት መገኘት ነው ። ሁለተኛው ማስረጃ ፥ ኩዌት በስምንተኛው ምእታመት ካርታዎች የኢራቋ ከተማ ባስራ በ8ኛው ምእታመት ካርታዎች ላይ በኢራቅ ከተማ በባስራ በሚገኘው የዓርብ ጦር ጠቅላይ ሠፈር ተመዝግባ መገኘቷ ነው ።

ኢራቅ ትውልዷን 5ሺ ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ከነበረችው ከሜሶፖታሚያ የዘር ግንድ ሐረግ ስትመዝ ኩዌት ግን ያን ያኸል አትንጠራራም ። የአ-ጠብ ጐሳ አባል የሆነው የሳባህ ቤተሰብ ፥ ምናልባት ውሀ በመከተል ከማእከላዊ ዓረቢያው የነጅድ ክፍለአገር በዓሥራ ስምንተኛው ምእታመት መባቻ ወደ ኩዌት ፈለሰ ። ዛሬ ኩዌት ከተማ በምትገኝበት ቦታም ሠፍሮ አንድ ትንሽ ምሽግ ዐምባ አነጸ ። በባሕረ ሰላጤው ኩዌት የሚለው ስም የ"ኩት" (KUT) ማለትም "ትንሽ ምሽግ" ማለት ነው ። በምሽጓም ዙሪያ የተከተመችው ትንሽ ከተማ ኑሮዋ በማስገርና ዕንቁ በመልቀም ፥ እንዲሁም በንግድ ላይ ተመሠረተ ። "ድኸውስ" የተባሉት በባሕር በሩ ላይ እንደ ነቁጥቋጥ ይነዙ የነበሩት ደማቅ ቀለም የተቀቡ ዓይነገብ ባለሸራ ታንኳዎቿ በአንድ ወቅት ውድ ወይም ዕንቁን የመሳሰለ የከበረ ጭነት ተጭነው እስከ ምሥራቅ አፍሪካ ርቀው ይጓዙ ነበር ።

እስከ አንደኛው የዓለም ጦርነት ድረስ ኩዌት ለስሙ በዑስማናው ያን ማእከለ አህጉር ሥር ነበረች ። በተለይ በዊላያ ፥ ወይም በባስራ

እውራጃ አስተዳደር ክልል ውስጥም ነበረች ። ኩዌትን ከ1748 ጀምሮ የሚገዛው የሳባህ ቤተሰብ ቱርኮች ፣ ዋሀቢዎች (ኋላ ሳዑዲዎች የሆኑት)ም ሆኑ ወይም ብሪታንያውያን ፣ በብልሀት አንዱን ካንዱ በማጋጨት ለራሱ የተወሰነ ነፃነት ሊያገኝ ችሏል ።

ለምሳሌ በ1889 በባግዳድ የነበረው ዑስማናዊ ገዢ ኩዌትን አስገብሮ ለመቆጣጠር በፈለገ ጊዜ ፣ ሼክ ሙባረክ አልሳባህ ከቱርኮች ለማምለጥ ብሪታንያውያን በሞግዚትነት ተገን እንዲሆኗቸው የጠየቁ መሆናቸውን ታሪክ መርማሪው ጃኮብ ጐልድበርግ ጽፈዋል ። ብሪታንያውያን ፈቃደኛ በሆኑ ጊዜም ሼክ ሙባረክ ለተቀናቃኞቻቸው ለሩሲያውያን (ለመርከቦቻቸው ነዳጅ) የድንጋይ ከሰል መጋዘኛ ማቢያ ኩዌት ውስጥ ሊሰጧቸው ስለማሰባቸው በአደባባይ አንገራገሩ ። ብሪታንያውያንም ሐሳባቸውን ለወጡ ። ሙባረክ ያለብሪታንያ ስምምነት እርሳቸውም ሆኑ ወራሾቻቸው ምንም ግዛት አሳልፈው ላይሰጡ ወይም የውጪ ወኪል ወይም እንደራሴ ላይቀበሉ ቃል በመግባት በ1891 ስምምነት ፈረሙ ። ብሪታንያውያንም በልዋጩ ፣ የብሪታንያን ሕንድ ገንዘብ—15ሺ ሩፒ ፣ እና ስምምነቱ በጥንቃቄ እስከተከበረ ድረስ "የግርማዊት መንግሥት ፣ ለእርስዎ ፣ ለአልጋ ወራሾችዎና ለወራሾችም ባለው ሥልጣን ሁሉ በጐ የሚያደርግ መሆኑን" የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ሰጧቸው ። ይህ ብሪታንያ ኩዌትን በበላይነት ለመጠበቅ የተስማማችበት ይፋ ያልወጣ ስምምነት ሆነ ። ብሪታንያውያን በበላይነት እንዲጠብቋቸው ያቀረቡት ይህ ጥያቄ ከዚህ በኋላ ለሚያቀርቧቸው ተመሳሳይ ጥያቄዎች የመጀመሪያው ነበር ። ምክንያቱም ዛሬ ወደኋላ ስናስበው ትክክል መሆኑን እንደምንገነዘበው ኩዌት ሁልጊዜም ኃይለኛ የበላይ ጠባቂ የሚያስፈልጋት መሆኑ ይሰማት ነበር ።

ከ1891 በኋላ የኤሚሬቷን የውጪ ፖሊሲ ታላቋ ብሪታንያ ስትወስን ብትቆይም ፣ የሳባህ ቤተሰብ የኩዌትን የውስጥ አስተዳደር በጣም በጥሩ ሁኔታ ይመራ ነበር ። ነገር ግን ቱርኮችና ብሪታንያውያን ሁልጊዜም የማይበለጡትን ሙባረክን ወደየራሳቸው ለመሳብ ይደልሏቸው ገቡ ። በአውሮፓ የጦርነት ጥቁር ደመና ሰማዩን እያጨለመው ሳለ ፣ ብሪታንያውያንና ቱርኮች በሐምሌ 1905 በዑስማናውያን ማእከለ እህጉር ውስጥ የኩዌትን ራስ ገዝ አውራጃነት ዐውቀው ስምምነት ላይ ከመድረሳቸውም በላይ የሼኳ ግዛት ዳር ድምበርም በውል ተከለለ ። ነገር ግን



ወዲያው ከጀርመን ጋር ያበሩት ዑስማናውያን ስምምነቱን በፊርማቸው ሳያጸድቁት ቀሩ ። ብሪታንያም ፣ በበኩሏ ፣ በ(ሁለተኛው የዓለም) ጦርነት ዋዜማ በባሕረ ሰላጤው ጥቅሟን ለማስጠበቅ በማሰብ ፣ ኩዌትን ከዑስማናውያን ነፃ እንደሆነች ዐወቀች ። በልዋጩም ፣ በመጪው (ሁለተኛው የዓለም) ጦርነት ኢራቅ ውስጥ ዑስማናውያንን በመጻረር ሙባረክ ከብሪታንያ ጋር ተባበሩ ።

ሆኖም ፣ ሙባረክ የገቡት ቃል ቢኖርም ፣ ከሁሉም ወገን ጋር ኮንትሮባንድና ንግድ ቀጠሉ ። ደግሞ እኮ ምናልባት ገንዘብ ታገኝበታለች፣ ያውም ገና ደሀ የጐሳ አገር የነበረችው ኩዌት ። ያም ሆኖ ከጦርነቱ በኋላ ብሪታንያ ሙባረክን በሁለት ቢላዋ በላንታቸውን ዋጋ አስከፈለቻቸው ። ብሪታንያ በ1914 በባሕረ ሰላጤው የኡቋይር ወደብ ሳዑዲ ዓረቢያን ፣ ኢራቅንና ኩዌትን ያካተተ ጉባኤ ጠራች ። ጉባኤውን በባግዳድ የብሪታንያ የበላይ አስተዳዳሪ ሰር ፔርሲ ኮክስ ነበሩ የመሩት ። የሳዑዲው መሪ ኢብን ሳዑድ ለኢራቅ እንዲለቁ በተገደዱት ግዛት ምትክ በ1905 ከተከለለው ድምበሯ በስተደቡብ ከባሕር ጠረፍ ገባ ብሎ ያለው ግዛት ከኩዌት እጅ ወጥቶ በገለልተኛ ቀጣናነት የሳዑዲ ዓረቢያና የራፁ የኩዌት ጐሳዎች በጋራ እንዲጠቀሙበት ተወሰነ ። የኢራቅና የኩዌትም የጋራ ድንበር በሰር ፔርሲ ፊርማ ጸደቀ ።

በዚህ ማእከለ እህጉራዊ የመሬት ሥሪት (ካርቶግራፊ) ኢራቅ ያለ ባሕር በር ቀረች ። በባሕረሰላጤው ላይ ያላት የባሕር ጠረፍ 41·6 ኪሎ ሜትር ብቻ ርዝመት ያለው ነው ። ወደባሕረሰላጤው ያላት አንድ መዝለቂያ በሻት አል ዓረብ የባሕር መተላለፊያ በይ በኩል ያለው ነው ። ይህ ደግሞ በተፃራሪ ኃይል በቀላሉ ሊዘጋባት ይችላል ። በአንፃሩም ኩዌት ከባሕረሰላጤው 192 ኪሎ ሜትር የባሕር ጠረፍ ፣ እንዲሁም ከክልሉ ተወዳዳሪ የሌለው ተፈጥሮ ሠራሽ የመርከብ መጠጊያ አላት ። ስለዚህ ኢራቅ በስተደቡቧ የምትጐራበታትን ሚጢጢ አገር ብትቋምጥ አያስደንቅም ።

የኩዌትና የኢራቅ የጋራ ወሰን ክልል ኢራቅ በ1924 ነፃነቷን እንደተቀዳጀች ጸደቀ ። ነገር ግን ከዚያ በኋላ ወዲያው ፣ ባግዳድ ፣ እንደሚባለው ቢሆን የኢራቅ ነበሩ ፣ የምላቸውን ከኩዌት የባሕር ጠረፍ ፈንጠር ያሉ ደሴቶች ለአያሌ ዓመታት በኮንትራት የመያዝ መብት

እንዲሰጣት ንዝንዝ ጀመረች ። ከዚህም በላይ በ1925 የኢራቁ ንጉሥ ፈይሳል ካረፉ በኋላ ባግዳድ የኩዌትን የሳባህ የአመራር አባላት የሚጻረር ቅስቀሳዋን በማባባሷ ከኩዌት ጋር ያላት ግንኙነት ይብስ ሻከረ ። በገዢው በሳባህ ቤተሰብና የዚህን ቤተሰብ ሥልጣን ለመወሰን በሚፈልጉ ሌሎች የንጋዴ ቤተሰቦች መኻል ውጥረት እየከረረ መጣ ። የነዳጅ ዘይት ፍለጋው ተስፋ እየታየ እያለ አንድም የሚረባ የልማት ፕሮጀክት አልተዘረጋ ። በእነዚህ ሁኔታዎች ግፊት ተቀናቃኝ ቡድኖች በኩዌት ውስጥ ብቅ ብቅ አሉ ። በወጣቱ የኩዌት ምሁራን መኻል የዓረብ ብሔረተኝነት እያደገ ነበርና የሼኩ ግዛት በፖለቲካ ሴራ ተተበተበች ።

በ1929 የኢራቁ ንጉሥ ጋዚ በቤተመንግሥታቸው ከሚገኝ የግል ሬዲዮ ጣቢያ ኩዌትን የሚዘልፍ ንግግር ማሠራጨት ጀመሩ ። ለዓረብ ብሔረተኝነት ጥልቅ ስሜት ኖሯቸው ልምድ የሚጐድላቸው ወጣቱ የኢራቅ መሪ በዚሁ የዘለፋ ሥርጭታቸው ከኩዌት በተጨማሪ ሶርያ ውስጥ ያለውን የፈረንሳይ አገዛዝ ፤ በፍልስጥኤም ምድር የጽዮናውያንን የይገባኛል ጥያቄ ፤ እናም ብሪታንያ በባሕረ ሰላጤው ያላትን ተጽእኖ ማውገዛቸውን ታሪክ መርማሪው ፈቢግር ጽፈዋል ። ኩዌትን በተመለከተ ግን በኢራቅ እንድትጠቀለል አሳስበዋል ። በተለይ ይህ የግዛት ይገባኛል ጥያቄ የቀረበው ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር ። ንጉሥ ጋዚ በሬዲዮ ዘለፋቸው የኩዌትን አሚር በብሪታንያውያን ፤ ሥልጣን ላይ እንዲቆዩ የተደረጉ ዘመን ያለፈባቸው ፊዩዳል ንጉሥ እንደሆኑ አድርገው አቀረቧቸው ። ይህ ከኀምሳ ዓመት በላይ በኋላ በሌላ አቀራረብ ዛሬም ግዳም የሚያንፀባርቁት ጭብጥ ነው ። የንጉሡ ዘለፋ ኩዌት ውስጥ ደም አፈላ ። በ1930 አሚሩ ከሥልጣናቸው እንዳንዱን እንዲለቁ የኩዌት የንጋዴ ቤተሰቦች አስገደዷቸው ። ያውም ብሪያንያ ጣልቃ ገብታና ትንሽ እድልም ታክሎ የሳባህን ቤተሰብ ድምጥማጥ ከመጥፋት አዳኑት ። በ1931 ንጉሥ ጋዚ ጨምቢራቸው እስኪያር ሰክረው አቶሞቢላቸውን በከፍተኛ ፍጥነት እያበረሩ ከኤሌክትሪክ ምሰሶ አጋጩት ። የሳባህ ቤተሰብ ሥልጣኑን እንደያዘ ቆየ ።

ሰኔ 12/1953 ብሪታንያ ኩዌትን ሙሉ ነፃነት አቀዳጀቻት ። የዚያን ጊዜው የኩዌት መሪ ሼክ አብዱላ አሳባህ ወዲያው ብሔራዊ ሸንጎ ማቋቋምና ሕገመንግሥት ማርቀቅ ጀመሩ ። ታሪክ መርማሪው ማር



እንደሚሉት ሼኩ ይህን ያደረጉበት ከፊል ምክንያት አገራቸው ከኢራቅ የተለየችና ሉዓላዊነት ያላት መሆኗ ሕጋዊ መሠረት እንዲኖረው ለማድረግ ነው ። ኩዌት ነፃነቷን በተቀዳጀች በስድስተኛው ቀን የኢራቁ መሪ አብዱል ከሪም ቃሲም የአሚሩን ግዛት የኢራቅ አንድ አካል ክፍል በማለት የይገባኛል ጥያቄ አነሡ ። ቃሲም ይህንን አስመልክተው በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ኩዌት በዑስማንውያን ግእከለ አህጉር ሥር በባስራ ክፍለ አገር ውስጥ አንድ አውራጃ ስለነበረች የኢራቅ ናት በማለት አበክረው ገለጹ ። ኩዌትን ከእናት አገሯ መልሶ ለማዋሐድ በኃይል ለመጠቀም ሐሳብ እንደሌላቸው ቃሲም ቢናገሩም ይህ ከቶም በኃይል አልጠቀምም ማለታቸው እንዳልሆነ አብራርተዋል ። እንዲያውም በኢራቅና በኩዌት ወሰን ስለወታደሮች ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ ጭምጭምታ ነበር ። ነገር ግን እንደ ዕውነቱ የኢራቅ ጦር ኃይል በሙሉ በአገሪቱ ሰሜናዊ ክፍል የኩርዶችን አመፅ እየተቋቋመ ስለነበር ወደ ኩዌት ድንበር ጨርሶ ምንም ወታደር ያለመላኩ ብቻም ሳይሆን ሊላክም አይችል ነበር ። በደቡብ ኢራቅ እንዲቆይ የተደረገው አንድ ብርጌድ ጦር ብቻ ነበር ።

ነገር ግን ቃሲም ጋዜጣዊ መግለጫ በሰጡ ማግሥት አሚር አብዱላ በአዲሲቱ አገራቸው ላይ የተሰነዘረውን ዛቻ ጠቅሰው ድጋፋቸውን በመጠየቅ ለሁሉም የዓረብ ነገሥታትና ፕሬዚዳንቶች ቴሌግራም አስተላለፉ ። ሳዑዲ ዓረቢያ ብቻ ልትረዳት ቃል ገባችላት ። እናም አብዱላ አሁንም እንደገና የብሪታንያን የበላይ ጠባቂነት ጠየቁ ። በሐምሌ 1953 የብሪታንያ ጦር ኃይሎች ወደኩዌት ዘው አሉ ። ዘግይቶም በዚያው ወር ፤ የዓረብ ሊግ (የዓረብ መንግሥታት ማኀበር) ኩዌትን በአባልነት ተቀበለ። ነገሩ ኢራቅን ክፉኛ አስቆጣት ። በዚህም አላበቃች ። በድንገት ከሊጉ በመሰናበት ኩዌትን ካወቁ አገሮች ሁሉ እንደራሴዎቿንና አምባሳደሮቿን ጠራች ። ኢራቅን ከኩዌት ላይ ለመከላከል ግንባር ቀደሙ የዓረብ ሊግ የጦር ኃይል በመስከረም 1954 ኩዌት ደረሰ ። ይህ ጦር ኃይል ከ1982፣ ይልቅ ከ29 ዓመት በፊት በ1953 የኩዌትን ሕጋዊነት እንደታዩ ውም ተቀብለው በነበሩት በዮርዳኖሱ ንጉሥ ሑሴን የተላኩ ወታደሮችን ያካተተ ነበር ። ቀውሱ ወዲያው አለፈና እስከ 1955 የዓረብ ጦር ኃይሎች ወደያገራቸው ሄዱ ። ኩዌትም ከኢራቅ ከተቃጣባት የመጀመሪያ ጥቃት

ተገላገለች ። የቓሲም ኩዌትን የመቀጀት ሙከራ መክሸፍ ባገር ውስጥ አሳፍር አዳከማቸው ። በ1955 የባዓዝ ፓርቲ እርሳቸውን ፈንቅሎ የኢራቅን መንግሥት በቁጥጥሩ ሥር አስገባ ። በቃላት ሶሻሊስት ፥ ግን በመንፈስ አድርባዩ የባዓዝ ፓርቲ ፥ ባገር ውስጥ ለጠላቱ አይምሬ ጨቋኝ ቢሆንም ለዘብተኛ የውጪ ፖሊሲ ዘረጋ ። ፓርቲው በፍጥነት ኩዌትን በተመለከተ ቓሲም ይከተሉት የነበረውን ፖሊሲ ለውጦ በጥቅምት 1956 የኩዌትን ነፃነት በወቀ ። ለረጅም ጊዜ የቆየው የወሰን ግጭት የተወገደው ኩዌት ለኢራቅ በልዋጩ ጠቀም ያለ ገንዘብ ከከፈለቻት በኋላ ሳይሆን እንዳልቀረ ግልጽ ነው ። በተለየ ስምምነት ፥ ኢራቅ በየዕለቱ ለኩዌት ከሻት አል ዓረብ 24 ሚሊዮን ሊትር ውሀ ልትሰጣት ፈቀደች ። በኅዳር 1856 ኢራቅና ኩዌት በመካከላቸው የሚካሄደውን ንግድ ሙሉ በሙሉ ከቀረጥ ነፃ የሚያደርግ የኢኮኖሚ ስምምነት ተፈራረሙ ።

ይሁንና ይህ አዲስ የተመሠረተ መጣጣም ፥ ብዙም አልዘለቀ ። ባዓዝ ፓርቲ በ1955 ሥልጣን መንግሥት ከያዘ በኋላ በዘጠኝ ወሩ ከሥልጣን ተወገደ ። ነገር ግን በሌላ መፈንቅልም ቢሆን በ1960 በትረ መንግሥቱን መልሶ ጨበጠ ።

ይህ ካለፈው ይብስ እንካሳ ፥ እጅግ ይብስም መናኛ የባዓዝ ፓርቲ መንግሥት ተዳፍኖ የቆየ ጠብ አጫረ ። በመጋቢት 1965 የኢራቅ ወታደሮች በሰሜን ኩዌት የምትገኘውን የአል ሳሚታህ የጠረፍ ጥበቃ ጣቢያ እንደያዙ ውጥረቱ ከረረ ። በዚህኛው ጊዜ ግጭቱ የተነሣው የኢራቅን የባሕረ ሰላጤ ወታደራዊ ወደብ የዑም ቓስር መግቢያ መውጫ በሚቆጣጠሩት ሁለት የኩዌት ደሴቶች — በቡቢያንና በዋርባህ ላይ ነበር። ሁለቱም ወገኖች ከዚያ የጦር ኃይላቸውን ያነሡት ገና በ1969 ነው።

በዚህ ጊዜ በተጨማሪ በኢራቅና በኢራን ግንኙነት እየሻከረ መሄድ ባግዳድን በኩዌት ላይ ማትኩሯን እያስጣላት መሄድ ጀመረ ። እና በመስከረም 1973 ኢራቅ ኢራንን በወረረቻት ጊዜ ኩዌታውያን ቢያንስ የባግዳድ ጣቻ ጋብ እንዳለ ተሰምቷቸዋል ።

ከኢራቅና ከኩዌት የበለጠ የተለያየ ሁለት ማሰብ ይከብዳል ። ኢራቅን በመልክአምድርና ታሪክ በቀኖና በፍርሀት እጅለው ሆዴ



የማይገኝና ተጠራጣሪ አድርገዋታል ። በአንፃሩም ፥ የኩዌት ሕዝብ ግልጽ ፥ ከሁሉ ተግባቢና ይልቁንም ከልክ በላይ ለነገ የማያውቅ ለንብላው ባይ ነጋዴ ማኅበረሰብ ነው ።

ኩዌትን ኢራቅ ከወረረቻት በኋላ ፥ ወዲያው እርቢኑ የሚተቹ ጽሑፎች በምዕራብ ጋዜጦች ላይ ወጡ ። ዘጋቢዎችና ዓረብ ተንታኞች ኩዌትን በውስጠታዋቂም በሰላጤው ውስጥ የሚገኙ ሌሎች የሼክ ግዛቶች ስንደቅ ዓላማ ያለው ኩባንያ እየር ማቀዝቀዣ የኅባላት አደን ፥ "ወይም እንዳቸውን" በዓለም በትልቅነት ወደርየለሹ የሽቀጣሽቀጥ መታያ ገረገራ ይሏቸዋል ። በኢራቅ የተወረረችውን ኩዌትን መተቸት በድንገት ፋሲጥ ሆነ ።

ነገር ግን በ1970ዎቹ ኢራቅ የጦር መሣሪያ ፋብሪካ ስትከፍትና ኬሚካል ጦር መሣሪያ ስታከማች ፥ ኩዌት በዓረቡ ዓለም የመጀመሪያውን የዓለም ገንዘቦች መመንዘሪያ — ሱቅ አል-ማናካት ስታስመርትና ኩዌታውያንም በዓለም አቀፍ ደረጃ ኩዌት ባሠራችው የመጀመሪያ ደረጃ የገበያ አዳራሽ አል ኻሊጂያ ተመርቆ በሚከፈትበት ሥነ ሥርዓት ላይ ለመገኘት ይጉርፉ ነበር ። ኢራቃውያን ከኢራን ጋር ረጅሙን ጦርነት በመዋጋትና ለኑክሌር ቦምብ ወይም ለረቀቀ ሚሳይል ምንዝር ለመግዛት ፥ ወይም ለመስረቅ በመላው ዓለም የውሸት ኮርፖሬሽን በማቋቋም ላይ በነበሩበት ወቅት ኩዌታውያን የውሀ ሸርተቴ ይጫወቱ ወይም ስታ ለመግዛት ከሱቅ ሱቅ ይዞሩ ነበር ።

ባግዳድ በመፈንቅለ መንግሥትና በሹማምንት ከሥልጣን መወገድ ጥምጥምታ ስትለታለት ኩዌትውያን በብሔራዊ ሸንጎቸው ውስጥ በስድብ ይተጋተጉ ነበር ። ሸንጉው በ1978 ውካታቸው ለአሚሩ በጣም ከጣራ በላይ እስከሆንባቸው ድረስ ፥ በባሕረ ሰላጤው በሕዝብ ምርጫ የተመሠረተው እርሱ ብቻ ከመሆን አልፎ በዓይነቱም በዓረቡ ዓለም ካሉት ጥቂት ተቋሞች አንዱ ነበር ።

ኢራቅ ከውጪ ለገቡ የቀን ሠራተኞች የምትከፍለው ገንዘብ ሲቸግራት ፥ ኩዌት እንዲህ ዓይነት ችግር አልነበረባትም ። ስለሆነም ብዛታቸው አእምሮን እስከሚያስጨንቅ ድረስ ትቀበላቸው ነበር ። በኩዌትና በሌሎቹም የባሕረሰላጤው አገሮች የሕዝብ ብዛት ግምት ሁልጊዜም አያስተማምን ። ሆኖም ከኢራቅ ወረራ በፊት በኩዌት ይኖር

ከነበረው አንድ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሺህ ሰው ሁለት-ሲሶው የውጪ ዜጎች ነበሩ ። ከእነዚህም በሰላጤው በሚገኙ አገሮች ሁሉ ይበልጥ በብዛት የተከማቹባት 350 ሺው ፍልስጥኤማውያን ናቸው።

ለማግኘት ሳምንታት ፣ አንዳንዴም የወራት ልምምጥ የሚጠይቅ ልዩ ቪዛ ካልሆነ በስተቀር ባግዳድ ጨርሶ ለውጪ ጋዜጠኞች በሯን ዘግታለች ። ኩዌት ግን በአርባ ስምንት ሰዓት ውስጥ ቪዛ ትሰጣለች ። በኢራቅና በኢራን ጦርነት ወቅት ኩዌት የውጪ ጋዜጠኞች ዜና ለመከታተል የሚመርጧት ኬላ ነበረች ።

በጋዜጣ ረገድ ከሁለቱ ማኀበረሰብ "ተራማጁ" ኢራቅ ናት ። ሶሻሊስትና ሃይማኖት የግል የሆነባት ዓለማዊ ናት ። በአንፃሩም ኩዌት አልኮልና ሌሎች ምዕራባዊ ልማዶች የሚነወሩባት ፣ ሴቶቿ በምርጫ ላይ ድምፅ መስጠት የተነፈጉባት ፣ የባለርስትና የጭሰኛ ግንኙነት የሠፈነባት ፣ በበላይ ሃይማኖታዊ ገዢ የምትመራ አገር ናት ። ሆኖም ፣ በተግባር ኢራቅ በአብዛኛው እንደተገኘ በሽብርና በማስፈራራት ትገዛለች ፣ ኩዌት ግን በአንፃሩ ባለሥልጣኖች ድንጋጌን አይቶ እንዳላየ የመሆን አዝማሚያ ያሳዩባት የነበረች ፣ ወይም ሲመስላቸው ድንጋጌን የሚከተሉባት አንፃራዊ ግልጽነትና ቻይነት የሰፈነባት አገር ነበረች ።

ኩዌት ከወረራው በፊት ምን ዓይነት አገር ነበረች? ከሞላ ጎደል በማንኛውም ዓይነት ደረጃ እጅግ ግሩም አገር ነበረች ። የነፃነት አየሯ ፣ የመጻፍና የመናገር ነፃነቷ እንዲሁም የነፃነት መንፈሷ ከእስታቀቀው የእርስ በርስ ጦርነት በፊት የነበረችውን ሊባኖስ ስለምታስታውስ ፣ በዓረቡ ዓለም "የባሕረ ሰላጤው ቤይሩት" በመባል ትታወቅ ነበር ። ኩዌት ከነዋሪዋ ከግማሽ በላይ በኩዌት ከተማ እንደመኖሩ በብዙ ረገድ ከተሜ አገር ናት ። ያለጥርጥር ኩዌት ከባሕረ ሰላጤው አገሮች መኻል በዕውቀት የላቀች አገር ናት ። እናም ሕዝቧ (ከሞላ ጎደል በአሜሪካ የፊላዴልፊያን ያኽል) ዓሥራ ሦስት ማለት ሰባት ዕለታዊ (አምስቱ ዓረብኛ ፣ ሁለቱ እንግሊዝኛ) እና ስድስት ሳምንታዊ በድምሩ ዓሥራ ሦስት ጋዜጣ ይከታተላል ። በኩዌት ዩኒቨርሲቲ ዓሥራ ሰባት ሺህ ወንድና ሴት ተማሪዎች ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ነበሩ ። ሥርዓተ ትምህርቱም የአሜሪካ ኮሌጅ ዓይነት ነበር ። "የኒውዮርክ ታይምስ" ጋዜጠኛ ዩሱፍ ኢብራሂም እንደዘገበው የኩዌት አጠቃላይ ትምህርት ፣ እንዲሁም የሕክምናና የበጐ አድራጐት ሥርዓት "የዓረቡ



ዓለም ከፍተኛ የበጐ አድራጐት አገር" አደረጋት ። እና የአሜሪካ ባለሥልጣናት መደበኛ ማጣቀሻ የሆነው "ኤሪያ ሀንድቡክ ፎር ዘ ፔሪፌራል ስቴትስ ኦቭ ዘ ዓረቢያን ፔኒንሱላ" ፣ "በዓለም እጅግ በለሙ አገሮችም እንኳን የኩዌትን ብዙ አካታች የሕዝብ አገልግሎት የሚወዳደሩት አገሮች አሉ ለማለት አያስደፍርም ።"

በያዝነው ምእታመት መጀመሪያ ሕዝቧ ከ50ሺ የማይበልጥ እጅግ ደሀ ኋላቀር አገር ነበረች ። በ1970ዎቹ አጋማሽ ሕዝቧ በዓለም የመጨረሻው ከፍተኛ አማካይ የነፍስ ወከፍ ገቢ በዓመት 15ሺ ዶላር ያገኝ ነበር ። በ1963 በአቶሞቢልና በቪዲዮ ካሴት መትረጫ የነፍስ ወከፍ ዓመታዊ ድርሻ በዓለም ወደመጨረሻው ከፍተኛ ደረጃ ላይ ከደረሱት አገሮች መኻል ትገኛለች ። ኩዌታውያን ቀረጥ አይከፍሉም ። ጠቀም ያለ የመኖሪያና የመሬት አበል ይቀበላሉ ። በመንግሥት ወጪ በዓለም የትም ሄዶ መማር ይቻላል ። ኢራቅ ኩዌትን በወረረችበት ወቅት 1ሺ,500 ያኽል ኩዌታውያን አሜሪካ ውስጥ በትምህርት ላይ ነበሩ ።

ከኔክቲከት ከተሰኘችው የአሜሪካ ፌደራዊ ክፍለ አገር ትንሽ አነስ የምትለዋና ቆዳ ስፋቷ 2ሺ 384·8 ኪሎ ሜትር ካሬ ኩዌት በአብዛኛው ከሞላ ጎደል ምንም የተፈጥሮ ውሀ የሌላት የለየላት በረሀ ናት ። የኩዌትን ከተማና እየደራ ያለውን አካባቢዋን ለማስዋብ መንግሥቱ ከአንድ ሚሊዮን በላይ ዛፍና ቁጥቋጦ ተክሎ ከፋርስ ባሕረ ሰላጤ ጨዋማ የባሕር ውሀ እያጣራ እያጠጣው ነው ። ደን ልማቱም የታቀደው የሚያቀናጡ ለእብነበረድና ከመሥተዋት የተሠሩ የምድር መኖሪያ ቤቶችን ፣ ባለሦስት ኮከብ ሆቴሎችን ፣ የጠፈር ዘመን ሰማይ ጠቀሶችን ፣ እንዲሁም ስድስት መንታ ጎዳናዎችን በክረምቱ የአሸዋ ማዕበል ወቅት የትም መግባት ከሚችለው የአቧራና የአሸዋ ጉም ለመከለል ነው ። ኩዌት ኩረብታ ብርቅ የሆነባት ፣ ተራራ የማይታወቅባት ጭው ያለች ሜዳማ አገር ናት ።

ኩዌታውያን የአየር ጠባያቸው ከሌሎቹ የባሕረ ሰላጤው አገሮች መለስ ያለ መሆኑን መናገር ቢወዱም እንኳ ፣ በጋቸው ለሳምንታት ለመቋቋም የሚከብድ ወበቅ ሊኖረው ይችላል ። እና አገሪቱ "ሻማል" (ሰሜናዊ) የተሰኘውን ከኢራቅ የሚነፍሰውን ጠንካራ ሰሜን ምሥራቃዊ በየአቅጣጫው የሚነፍስ አቧራና አሸዋ አዘል ነፋስ ትቋቋመዋለች ። በበጋ 115 ዲግሪ የሙቀት መጠን አዲስ ነገር አይደለም ። እናም የአየር

ማቀዝቀዣ ከመምጣቱ በፊት ኩዌት ውስጥ ያገለገሉ ብሪታንያውያን ዲፕሎማቶች ላመል ታኸል የንፋስ ሽውታ ለማግኘት ሲሉ በኤምባሲያቸው ቪላ ጣሪያ ላይ ይተኙ እንደነበር ያስታውሳሉ ።

ኩዌት መኖር ቀላል አልነበረም ። ስለሆነም ኩዌታውያን ፣ በተለይ ከንጋት እስከ ምሽት በሚጾምባት የረመዳን የእስልምና ወር ፣ እንዲሁም ወደ ፈረንሳይ ሪቪራ ፣ ወደስዊዘርላንድ ተራሮች ፣ እናም ወደሚያፈቅሯት ለንደን ሺ በሺ በሚጎርፉበት በበጋ ታላቅ ቱሪስት ይወጣቸዋል ። ኩዌትን የሙቀኝ ብለው የሚተዉት መዓዝ የማይወዱት አሚር ጃብር አል አህመድ አል ሳባህ ብቻ ናቸው ።

እንደኢራቅ ሁሉ ፣ የኩዌትን ከበደዊ (ዘላን) ደሳ ቶሎ ቶሎ ወደምታድግ ከተማ መለወጥ ያመጣው ነዳጅ ዘይት ነው ። ኩዌት ነዳጅ ዘይትን ገበያ በሚወጣ መጠን ማምረት የጀመረችው ገና በ1941 ቢሆንም፣ ከሃያ ዓመት በኋላ በዓለም ስድስተኛዋ አምራች ሆናለች ። ሳዑዲ ዓረቢያ ገንዘቧን ከነዳጅ ዘይት ጋር በተዛመደ እንዱስትሪ ፣ በዘመናዊ መሠረተ ልማት ፣ በጦር መሣሪያና በብዛት በትርፍ የለሽ ያገር ውስጥ ንግድ ላይ በገፍ ታውላለች ። በአንፃሩም ፣ ኩዌት ከነዳጅ ዘይት ምርቷ ሽያጭ የምታገኘውን ትርፍ በውጪ አገር በሥራ ላይ በመዋል ወለድ የሚያስገኝ እያንዳንዱ 40 ቢሊዮን ዶላር ያኸል የሆነ ሁለት ግዙፍ የመዋዕለ ንዋይ (አበዳሪ) ድርጅት አቋቁማለች ። ራስ ሐማሉና ወለዱ እስከ 1993 ዓመተ ምሕረት ድረስ እንዳይነካ የተደረገው ከሁለት አንዱ "ፈንድ ፎር ፊዩቸር ጄኔሬሽንዝ" የተባለው የገንዘብ ድርጅት ፣ በየዓመቱ ኩዌት ከነዳጅ ዘይቷ ሽያጭ ከምታገኘው ትርፍ ዓሥር ከመቶውን ይቀበላል ። ኩዌታውያን ገንዘባቸውን የትና እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚያውሉና ለዚህም አማካሪ በብልሀት ስለሚመርጡ ፣ ይህ ከውጪ አገር የሚያገኙት ትርፍ ቀስበቀስ ከነዳጅ ዘይት ከሚያገኙት ትርፍ በለጠ። ስለሆነም ፣ የነዳጅ ዘይት ዋጋ በአንድ አፍታ መናር የኩዌት ዋና የገቢ ምንጭ የተመሠረተበትን ሼር ፣ የባለፅዳንት ማረጋገጫ ሰነድና የገንዘብ ምንዛሬ ገበያ ዋጋ ሲያሳገበው ስለሚችል ኢራቅ እንደፈለገችው የነዳጅ ዘይትን ዋጋ እንዲያሻቅብ በመፍቀድ ኩዌት ምንም ፋይዳ አታገኝም ።

ከእርሷ ደህየት ባሉት ጎረቤቶቿ ብቻ ሳይሆን ፣ እንዲያውም



የበለጠ ችግር ባስከተለ መልክ ፣ በተለይ በነዳጅ ዘይት ትድንድና በተዛመደ እንዱስትሪ ውስጥ የቤት ሠራተኛ ዓይነት ወደመሥራት የሚያዘነብሉ በተለይ ከ350ሺ በላይ ፍልስጥኤማውያን ፣ ከ300ሺ በላይ ግብጻውያን ፣ እና ከ200ሺ በላይ ሕንዶች ፣ ፓኪስታኖችና ፊሊፒኖች ኩዌታውያን ያልሆኑ የአሚሩ ግዛት ነዋሪዎች ላይ ከሚታለመው በላይ ለመሆን ምንም ያኸል የማይቀረው የኩዌት ብልጽግና ቅናት አሳድሪባቸው ። ስለዚህም ኩዌታውያን አሠሪዎቻቸውን ለመግለጽ ደጋግመው የሚጠቀሙበት ቃል "ትዕቢተኛ" ነበር ። እነዚህ እንደ ዕውነቱ ከቡሩን ነዳጅ ዘይት ከመሬት የሚያወጡ የውጪ አገር ዜጎች ኩዌታውያን የማይሠሩ መሆናቸውን ይናገሩሉ ። ደግሞ እኮ ፣ ኩዌታውያን ከሠራተኛው ኃይል ዓሥራ ስምንት ከመቶው ብቻ ናቸው ። ከዚህም በላይ በኩዌት ዜግነት በደም እንጂ እዚያ ብዙ በኖርሽ ወይም ታማኝ በሆንሽ የሚገኝ አይደለም። ሌላው ቀርቶ ኩዌት ውስጥ የተወለዱ ኩዌታውያን ያልሆኑ ነዋሪዎች ወንድና ሴት ልጆች ወትሮ የኩዌት ዜጋ ሊሆኑ አይችሉም ። መጪ ሠራተኞች ቪዛቸው እንዲታደስላቸው ፣ ለኩዌታዊ አሠሪዎቻቸው መክፈል ለምን እንዳስፈለገ በመጠየቅ ፣ ብዙ ጊዜም ዕውነትም በሚያስገኘው አድራጎት ላይ አምርረው ሮሮ አሰሙ ። በፖለቲካ ረገድ "የማይፈለጉ" የውጪ ዜጋ ሠራተኞች ብዙ ጊዜ ኮንትራታቸው ካለቀ በኋላ ጋማቸውን ተይዘው ካገር ውጪ ይሸቀነጠሩ ነበር ። ኩዌታዊ ያልሆነ የግል መሬት ወይም ቤት ሊኖረው አይችልም ።

በኢራንና በኢራቅ መካከል በ1972 ጦርነት መነሣቱ በኩዌት ላይ ትልቅ ጉዳት አስከትሎባታል ። ኩዌት ለስሙ ገለልተኛ የነበረች ብትሆንም ፣ ሳዑዲ ዓረቢያና ሌሎቹ የባሕረ ሰላጤው አገሮች እንዳደረጉት ሁሉ ፣ አሚሩ የባግዳዱን መንግሥት በሙሉ ልብ አስታጥቀውና ደግፈውታል ። ኩዌትና ሳዑዲ ዓረቢያ ፣ በአንድነት ፣ ለኢራቅ በየዕለቱ ወደ 310ሺ በርሜል ድፍድፍ ነዳጅ ዘይት በቦቴ መርከብ ይልኩ ነበር ። ስለዚህ ጦርነቱን ተመልሶ ኩዌት ከተማ መድረስ ብዙ ጊዜ አልፈጀበትም ።

በ1975 በአሜሪካና በፈረንሳይ ኤምባሲዎች ፣ እንዲሁም በአውሮፕላን ማረፊያና በነዳጅ ዘይት ተቋሞቿ ላይ ስድስት ሰዎች የተገደሉበትና ከሰማንያ በላይ የቆሰሉበት የአጥፍቶ ጥፋ የቦምብ አደጋ ተጣለ ።

የቦምብ አደጋው ኩዌትን ራሷን አሥራት ። እርሷም ወዲያውኑ ኢራንንና ደጋፊዎቿን በአደጋው ተጠያቂ አደረገች ። ከአንድ ዓመት በኋላ አንድ የኩዌት አየር መንገድ አውሮፕላን ወደቴህራን ተጠለፈ ። ይህንንም ተጨማሪ የቦምብ አደጋና ምስጢራዊ የፈንጂ አደጋ ተከተለው ። ለሁሉም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ኢራን ተጠያቂ ሆነች ፤ ዘግይቶም ሁለት አውሮፕላን ተጠለፈ ። በመጨረሻም አሚሩ ራሳቸው አቶሞቢል ውስጥ እንዳሉ በአሸባሪዎች የአጥፍቶ ጠፊ ተኩስ ተከፈተባቸው ። ነገር ግን በጨረፍታ ብቻ ተመትተው ቢተርፉም አደጋው የገደለውን ቤተሰብና አገሪቱን ዳር እስከ ዳር አመሳቸው ። ከአንድ ዓመት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ሽብር እየበዛና የንዳጅ ዘይት ዋጋ እየተቀነሰ በመሄድ ላይ እያለ የምክር ቤት መኖር ለአገሪቱ የሚከብድባት ቅንጦት መሆኑን የሳባህ ቤተሰብ ወሰነ ።

አሚሩ ምክር ቤቱን በመበተንና በአገራቸው ስሚታዊ ጋዜጦችና መጽሔቶች ላይ የፕሬስ ሳንሱር በመጣል "ዲሞክራሲ እየተናወጠ ነው" አሉ ። ሁሉም መጪ የሆኑ አርባ ዘጠኝ ያኸል ዋና ዋና የጋዜጦችና የመጽሔቶች አዘጋጆችና ጋዜጠኞች ካገር ተባረሩ ። ከእንዚህም ብዙዎቹ ጋዜጦችንና መጽሔቶችን የተፈጥሮ ጸጋና በጉልህ የመጻፍ ነፃነት ያጐናጸፋት ፍልስጥኤማውያን ነበሩ ። ጋዜጦችና መጽሔቶች የተጣለባቸውን ሳንሱርና የምክር ቤቱን መታገድ ደግፈው በመጻፋቸው ምን ያኸል የመንፈስ መታወክ እንደሠረጸ አንፀባረቀ ። በፊት ስሚታዊና ግንባር ቀደም የነበረው "አልሲያሳ" የተሰኘ የኩዌት ጋዜጣ "ወደፊት እኛም ከጐናችሁ ነን" በማለት ጻፈ ። ጋዜጣው "እያደነም ተግባራዊ ባልሆነ የንግግር ነፃነት መፈክሮች አንድ ማኅበረሰብ ተለያይቶና ተበታትኖ ማየት አንመኝም" ሲል አተተ ። አንድ ኩዌት ውስጥ የሚኖር የመረረው የውጪ ዜጋ ለ"ዘ ኒውዮርክ ታይምስ" እንደነገረው "ኩዌታውያን ከዲሞክራሲ ይልቅ ገንዘብን ይመርጣሉ" ነገር ግን የቦምብ አደጋውና ጥብቅ ቁጥጥርም ቀጠለ ። በ1978 ፤ 26ሺ 898 ያኸል ሰው በደኅንነት ምክንያት ካገር እንደተባረረ የፖሊስ ባለሥልጣናት ዘገቡ ።

በዚህች በሱኒዎች በምትመራ የአሚር ግዛት ውስጥ ካገሪቱ ሕዝብ ሩብ ያኸሉ ብዙኃን የኩዌት ሺዓዎች በውጪ ኃይል ሊደለሉ እንደሚችሉ ያለው ጥርጣሬ እየጨመረ ሄደ ። ግልህ ሱለይማን አል-አጣር



የተባሉ አንድ ሀብታም ሺዓ ነጋዴ በ1979 በኩዌት ጋዜጦች የግምባር ገጾች ላይ ሕዝቡን ይቅርታ በመጠየቅና ለአሚሩ ግዛትም ያላቸውን ታማኝነት በመግለጽ አስታወቁ ። ከጥቂት ቀናት ቀደም ብሎ አንድ የቤተሰባቸው አባል ከሌላ ሺዓ ጋር ሆኖ ኩዌት ከተማ ውስጥ በፈረንሳይ አየር መንገድ·ቢሮ ደጃፍ ላይ የመኪና ቦምብ ለማፈንዳት ሲሞክር ተገድሎ ነበር ። አጣር በጋዜጦቹ ባወጡት ይቅርታ መጠየቂያና ታማኝነት ማረጋገጫ ጽሑፍ "ይህ አደጋ በኩዌትና በሕዝቧ ላይ ተቃጣቶ የነበረ ከሆነ እንግዲያውስ ፍርዱን ከአላህ አግኝተውታል ። እናም ኩዌትን ለመጉዳት የሚፈልጉ አንዳንድ ወገኖች ወይም አንጃዎች አሳስተዋቸው ከሆነ ለሕዝባችን በሙሉ ፤ ለአሚራችን ፤ ለአልጋ ወራሻቸውና ለኩዌት ሕዝብ ድጋፋችንን እንገልጻለን ።" ሲሉ ጽፈዋል። መንግሥቱ ሺዓዎች ለሳባህ ቤተሰብ የታመኑ ሳይሆኑ በምስጢር ለሺዓዎቹ የኢራን ገዢዎች ያደሩ ናቸው ብሎ ስለፈራ በሠራዊቱና በደህንነት አገልግሎት ውስጥ ካሉ ቁልፍ ሥራዎች ያገልላቸው ጀመር ።

ሆኖም ግን ፤ ኩዌት ባገር ውስጥ እየተባባሰ በመሄድ ላይ የነበረ የደህንነት መደፍረስ ቢታይባትም ፤ ኢራቅ ከኢራን ጋር ጦርነት ላይ በቆየችባቸው ዓመታት የሚያስደንቅ ብርታት አሳየች ። በ1975 በፈረንሳይና በአሜሪካ ኤምባሲዎች ላይ የቦምብ አደጋ አድርሰዋል የተባሉ ዓሥራ ሰባት ያኸል ጽሕፈት ቤቱ ኢራን ውስጥ የሆነው "አልዳዕዋ" የሺዓዎች ቡድን አባሎች ተይዘው ፤ ተመረመሩና ተፈረደባቸው ። ዳዕዋም ዓሥራ ሰባቱ እንዲለቀቁና ያለበለዚያም አባሎቹን ለማስለቀቅ ማንኛውንም አስፈላጊ ነገር የሚያደርግ መሆኑን በመግለጽ አስጠነቀቀ ። ከዚህ በኋላ ከደረሰው የፈንጂ አደጋና የአሸባሪ ጥቃት ብዙው ይህንኑ ቁርጠኝነት ለማስገንዘብ የተፈጸመ መሆኑን የኩዌት ባለሥልጣናት ያውቁ ነበር ፤ ግን የሳባህ ቤተሰብ ፍንክች አላለም ። ጥቃት እንዳይደርስ የተጠረጠሩና የተፈረደባቸውን እንኳ አሸባሪዎች እንደለቀቁ ሌሎች አገሮች ሳይሆን ፤ ኩዌት ድርድር ሳትቀበል ቀረች ።

ከዓሥራ ሰባቱ ሁለቱ የተፈረደባቸውን አምስት የእሥራት ዘመን በሙሉ ከፈጸሙ በኋላ ብቻ በመጨረሻ በታኅሣሥ 1981 ተለቀቁ ። ከመካከላቸው ሦስቱ የሞት ቅጣት የተፈረደባቸው ፤ ቀሪዎቹ የኢራቅ ሠራዊት የኩዌትን ከተማ አጥቅቶ እስከያዘበት ጊዜ ድረስ በሳሊቢዩህ ወህኒ ቤት ቆዩ ። ከመስከረም 1981 በኋላ አሸባሪዎቹ ምን እንደሆኑ

በውል ባይታወቅም አንዳንድ ስደተኛ ኩዌታውያን ፣ ኢራቃውያን ዋና ከተማዋን ከያዙ በኋላ እሥረኞቹ ከኩዌቱ እሥር ቤት ሸሽተው እንደጠፉ ሲናገሩ አንድ የኢራንን ሁኔታ በቅርብ የሚከታተሉ የቡሽ አስተዳደር ባለሥልጣን ደግሞ ኢራቃውያን ወረራውን ባካሄዱ በአርባ ስምንት ሰዓት ውስጥ ዓሥራ አምስቱን ከእሥር ቤት ሆን ብለው እንደወሰዷቸው ተናግረዋል ። ከዚህም በመቀጠል በመስከረም 1981 መጀመሪያ አሸባሪዎቹ ወደባግዳድ ተወስደው የተባበሩት መንግሥታት በኢራቅ ላይ የጣለውን ማዕቀብ እንዳያደናቅፉባቸው በብልሀት በማገድ ረገድ የቴህራንን መንግሥት ድጋፍ ለማግኘት ይረዳቸው ዘንድ ኢራቃውያኑ ለተንኮል መልሰው ለኢራናውያን የሰጧቸው መሆኑን አስረድተዋል ።

በውጪ ፖሊሲ ፣ ኩዌት ደግሞ በራሷ ብልጠት ተጠቀመች ። ከባሕረ ሰላጤው አገሮች ዋነኛዋ የአሜሪካ የፍጆታ ሸቀጣሸቀጥ ሸማች ሆና እያለች ፣ በፖለቲካ ታላቅ አመራረጧ—በመኻሏ ብዙ መቶ ሺ ፍልስጤማውያን ስላሉ እንደሆን እንጂ ብዙ ጊዜ በዓረቡ ዓለም እጅግ የጎላና ፀረ አሜሪካና ፀረ እሥራኤል ድምፅ ከሚያሰሙት አገሮች መኻል ነበረች ።

ለምሳሌ ፣ ከ1959ኙ የስድስት ቀን የዓረብና የእሥራኤል ጦርነት በኋላ ኩዌት ወደ አሜሪካ ነዳጅ ዘይት መላኳን አቋርጣ የእሥራኤልን ሸቀጣሸቀጥ ላለማስመጣትና ከእርሷም ጋር የንግድ ግንኙነት ካላቸው ኩባንያዎች ጋር ማንኛውንም ግንኙነት ላለማድረግ የተያዘው የመላ የዓረብ አገሮች ጥረት ደስተኛ ተካፋይ ሆነች ። የኩዌት "ከእሥራኤል ግንኙነትን የማቋረጥ ጉዳይ ጽሕፈት ቤት" እስከ ቅርብ እስከ 1980 ድንጋጌዎች ሲያወጣ ነበር ። ለምሳሌ ፣ በመስከረም 1981 ጽሕፈት ቤቱ ከዓረቡ ዓለም ተወዳጅ መጠጦች በአንዱ በኮካ ኮላ ላይ ሃያ አንድ ዓመት ተጥሎ የቆየውን እገዳ በመጨረሻ አንሥቷል ።

ነሐሴ 1975 ብራንደን ኢች·ግሮብ (ታናሽዩው) በኩዌት የአሜሪካ አምባሳደር ሆነው ቢሾሙ "ቀደም ሲል በምሥራቅ ኢየሩሳሌም በዋና ቆንሲልነት በማገልገላቸው ኩዌት አልቀበላቸውም በማለት ማሳፈሯ የዋሽንግተንን አስተዳደር አስቆጥቶታል ። ኩዌት "በዓረቡ ዓለም ፣ እናም በተለይ በባሕረሰላጤው ለሚደርስ ለማንኛውም ስቃይ አሜሪካን ተጠያቂ ማድረጉን ልማድ" አድርጋው እንደነበር የዋሽንግተን ፖስት



ጋዜጠኛ–ዴቪድ ኦታዌ በ1976 አጤኖታል ። ኩዌት በአሜሪካ ላይ ስትሰነዝር የቆየችውን ዘለፋ እንድታለዝብ ያነሣሣት ኢራን በኩዌት መርከቦች ላይ እያየለ በመሄድ ላይ የነበረ ጥቃት ከከፈተች ወዲህ ብቻ ነበር ።

ኩዌት ኃያላን መንግሥታት በእርስ በርስ ትራኔ ድክመታቸውን እንዲገላለጡ የማድረግ ረጅም ልምዷ መቀጠል ስለቻለች ጭምር ዘታላት የመፋለም መከራዋም ተሳክቶላታል ። አሜሪካ የኩዌት ተገን በመሆን የድሮውን የብሪታንያ ሚና የመጫወት ኃላፊነት የወደቀባት ይመስላል ። እናም እንደብሪታንያ በሩሲያ ኃይል መጨመር ስጋት እርምጃ ወደመውሰድ ልትገፋፋ ትችላለች ። ለምሳሌ በ1976 ፣ ኩዌት ዒላማን በማግኘት እጅግ አስተማማኝ ፀረ አውሮፕላን ሚሳይሎችና ኤፍ–16 ተዋጊ ጄቶች ከአሜሪካ ላይ ለመግዛት ፈለገች ። አሜሪካ ግን ይህን ጥያቄ መቀበል ትታ በምትኩ በአነስተኛ የመራቀቅ ደረጃ ላይ የሚገኝ ቴክኖሎጂ ያካተተ 82 ሚሊዮን ዶላር የሚያወጣ የአየር መከላከያ መሣሪያ እንድትገዛ ፈቀደች ። ቲዎዶር ድሬፐር ከሦስት ዓመት በኋላ እንደዘገበው ፣ "ከዚያ ኩዌት ወደሶቪየት ኅብረት ሄዳ 327 ሚሊዮን ዶላር ያወጣ ጦር መሣሪያ ለመግዛት ተስማማች ።" አሜሪካ ስለግብይቱ ከሰማች በኋላ በፍጥነት ሐሳቧን ለውጣ እስከ 1977 ለኩዌት 1ቢሊዮን 500 ሚሊዮን ዶላር ያወጣ ጦር መሣሪያ ሸጠችላት ። ድሬፐር እንደሚከራከረው ይህ ያለመጨበጥ ፈጣን እንቅስቃሴ በመሠረቱ የሬጋን አስተዳደር ወደኋላ ለሚወስደው ይበልጥ ለአደጋ የሚያጋልጥ ውሳኔ የመጨረሻ መለማመጃ ነው ። ይህ ውሳኔ ከኢራን የሚሰነዘረውን ጥቃት ለመመከት ወደ ባሕረ ሰላጤው የአሜሪካን አውሮፕላን ተሸካሚ መርከብ በመላክ የኩዌትን አንዳንድ የነዳጅ ቦቴ መርከቦች የአሜሪካን ሰንደቅ ዓላማ እንዲያውለበልቡ በማድረግ ከፋርስ ባሕረሰላጤ በመርከብ የሚጓጓዘውን ነዳጅ ዘይት ለመቢዠት በ1979 ያሳለፈው ውሳኔ ነው ።

አሁንም እንደገና ፣ ኩዌት ኃያላን መንግሥታትን እርስ በርሳቸው በማጋጠምና በኢራቅ—ኢራን ጦርነት ችግር ላይ በመጣል ራሷን ለመከላከል ወሰናለች ። ኩዌት መርከቦቿ የአሜሪካን ሰንደቅ ዓላማ እንዲያውለበልቡ ጠይቃ የዋሽንግተን መንግሥት መልስ ቢዘገይባት ባለሥልጣኖቿ ወደሞስኮ ዞሩ ። ሶቪየቶቹ ቢያንስ ሦስት የነዳጅ ዘይት ቦቴ መርከብ በኪራይ ለኩዌት ስለሚሰጡበት ሁኔታ ስምምነት ላይ መድረሱን

ዋሽንግተን ከሰማች በኋላ ፤ የሬጋን አስተዳደር በዚህ ጨረታ ሶቪየቶችን ለማሸነፍ ወሰነ ። ሶቪየቶች የተስማሙበት ሁኔታ በታወቀ በአምስተኛው ቀን ኩዌት ራሷ ልክ በመጀመሪያ የጠየቀችላቸውን ዓይነት እንደ መርከቦቿን ከጥቃት ለመጠበቅ አሜሪካ ሰንደቅ ዓላማዋን የምትሰቅልባቸው መሆኗን አስታወቀች ። "ዩ·ኤስ·ኤስ· ስታርክ" (ምናልባት ባጋጣሚ) በአንድ የኢራቅ ሚሳይል ከተመታች በኋላ ፤ እነዚያን የአሜሪካ ሰንደቅ ዓላማ የሚያውለበልቡ መርከቦች ለመጠበቅ የሬጋን አስተዳደር ወደ አካባቢው የሚልከውን ሠራዊት ብዛት ጨመረ ።

ካለፈ በኋላ ብቻ ምን አስመልክቷቸው ኖሯል፤ በሚያሰኝ ሁኔታ የኩዌቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ሼክ ሳዓድ አል አብዱላህ አል ሳባህ አሜሪካ የኩዌትን የመርከብ ንግድ አገልግሎት ከጥቃት በመጠበቅ ላይ እያለች ልትገባበት ከምትችል ማንኛውም ግጭት አገራቸውን በሐምሌ 1979 አገለሉ ። ሼክ ሳዓድ ሰንደቅ ዓላማ የተለወጠላቸውን ዓይነት እንደ የነዳጅ ዘይት ቦቴ መርከቦች በማስመልከት ሲናገሩ ፤ "እነዚህ አሁን የአሜሪካ መርከቦች ናቸው ። አሁን ለአየር ኃይል ጦር ሠፈርም ሆነ ለባሕር ኃይል ጦር ሠፈር አልተዘጋጀንም" አሉ ።

ኩዌት ከ1980ው የኢራንና የኢራቅ ተኩስ አቁም በኋላ አሁንም በድጋሚ የውጪ ፖሊሲ መንገዷን ቀየረች ። ከኢራን የተፈራው ጥቃት አልፏል ። የኩዌት ባለሥልጣኖች ኢራቅ ሠራዊቷን በመቀነስና አገሪቱን መልሶ በማቋቋም ትጠመዳለች ብለው አሰቡ ። ስለዚህ የአሜሪካ መርከቦች አካባቢውን ለቀው እንዲወጡ ተጠየቁና በዝግታ እንደተባለው አደረጉ ። "የሰላጤው የትብብር ምክር ቤት" የተሰኘ በሳዑዲ የሚመራ የኩዌትና የሌሎች የሰላጤው አገሮች ፖለቲካዊና ወታደራዊ የቃል ኪዳን ድርጅት እንቅስቃሴውን አቀዘቀዘ ። አሁን የኩዌትንና ብዙውንም የባሕረ ሰላጤውን ክልል የእርደታ ሽውታ ዳሰሰው ። ኩዌታውያንም በባለአየር ማቀዝቀዣ ጃጉ ምግባቸውን ይዘው ወደ በረሀው ሽርሽር በመሄድ ድንኳን እየተከሉ መዝናናትን ወደመሳሰለው ተወዳጅ ጊዜ ማሳለፊያቸው ተመለሱ ። ሃያ አራት ሰዓት የሚሠራው የአል ሡልጣን የገበያ አዳራሽ ገበያ እየደራ ሄደ ። ጋዜጦችና መጽሔቶችም መዳፈራቸውን እንደገና ተያያዙት ።

የኩዌት ቤት ወንዱ "ዲዋኒያስ" በተባለው ለዘመናት የኖረ ማታማታ የመሰባሰብ ትውፊት ላይ እርስበርሳቸው የሚያወሩት ሁሉ



ተቀየረ ። ዲዋኒያስ የዚህ በጣም የተለየ ማኅበረሰብ ዕውነተኛ የልብ ለልብ መገናኛ ወቅት ነው ። በኢራንና በኢራቅ መኻል ጦርነት እየተካሄደ በነበረባቸው ዘመናት ረጭ ያለ መንፈስ አይሉበት ነበር ። ኩዌታውያን ወዳጆቻቸውንና ባለሥልጣኖችን ለመጠየቅ ሲሄዱ ብዙውን ጊዜ የሚያሳልፉት ሕይወታቸውና ኢኮኖሚያቸው ለኢራቅ ጥቃት የቱን ያኽል እንደተጋለጠ በመወያየት ነበር ። ነጠላ ጫማዎቻቸውን በራፍ ላይ እየተዉ ፤ በአንድ እጃቸው ሲጋራ ፤ በሌላኛው ሙስባህ ይዘው ሻይ እየጠጡ ፤ ቴምር ፤ ለውዝና ዘቢብ እየበሉ አጥለስ በተነጠፈበት አይቆርቁሬ ዘመናዊ የዕንጨት መደብ ላይ ጋደም ብለው ያወሩ ነበር ። ወሬው ኢራን በመጨረሻ ስለከፈተችው ጥቃት ፤ ኢራቅ ስለሰነዘረችው አፀፋ ፤ ስለነዳጅ ዘይት ቦቴ መርከቦች ጦርነትና "የታላላቅ ከተሞች ጦርነት" ፤ ኢራቅና ኢራን እንዱ በሌላው ዋና ከተማ ላይ ስላትመዘዘው ሚሳይል የሚሰማቸውን በእርጋታ ይጫወታሉ ።

ከጦርነቱ በኋላ ጭውውቱ በይበልጥ ስለተለያዩ እርእስተ ጉዳዮች ሆነ ። ዲዋኒያ በጣም ዝቅ ብሎ ትውፊታዊውን መልክ ያዘ ። የበለጠ ሆሚት ሳይቀር የንግድ ስልቱ ይፈልፈል ፤ ቅሬታ ይገለጽ ፤ በፖለቲካ ላይ ሐሳብን መገላለጽና የፖለቲካ አስተያየትም ይሠርጽ ነበር ። እናም ከሁሉም ዓይነተኛው አንድ አዲስ ነገር ይነፍስ ነበር—ስለ "ዲሞክራሲ" ማውራት ።

በመጋቢት 1982 ዲዋኒያስ በኩዌት ከዋና ዋናዎቹ የዲሞክራሲ መሠረተ ሐሳብ ማሳወቂያዎች አንዱ ሆነውና በረፈ ። እንዲሁም ደግሞ ምክር ቤቱ ተመልሶ እንዲከፈትና በጦርነት ስም የተጣለው ሳንሱር እንዲነሣ ዲዋኒያስ በሳባህ ቤተሰብ ላይ ትልቅ የግፊት ምንጭ ነበረ ። ባሕረ ሰላጤው ፤ ብሎም መላው የዓረብ ዓለም ድፍረት በተመላ ጭውውት እንደ ንብ እየተንጠባጠበ (ወይም እንደደራ የጉሊት ገበያ እያውካካ) ነው። ምሥራቅ አውሮፓንና የላቲን አሜሪካ ክፍል በ1981 የረበበበት ዲሞክራሲን የማስፈን ንቅናቄ በመጨረሻ የዓረብን የባሕር ዳርቻዎች ሊታኞቸው ይችል ይሆን ?

በየካቲት 1982 ፤ በአንድ ዳዋኒያ ላይ ኩዌታውያን አህመድ አልኻቲብ ወደተባሉ የቀድሞ የምክር ቤት አባል ቤት ይጉርፉ ነበር ። አነጋዳቸው እኚህ ሰው በኩዌት ውስጥ የነበረውን የአንድ ቤተሰብ

ነገድነትና ዕውነተኛ ነፃነት የሌለበትን ኑሮ በቀጥታ ሲያወግዙ ለማዳመጥ ነበር ። ኸቲብ በዚሁ ውግዘታቸው ፣ በዮርዳኖስ ወንዝ ምዕራባዊ ዳርቻና በጋዛ ሠርጥ የተካሄደው የፍልስጥኤማውያን አመፅ የሚጠራበትን ዓረብኛ ቃል በመጠቀም ፦

> እኛ እንደኢንቲፈዳ ነን ። በመጀመሪያ የፍርሀትን ገደብ ጥሰናል ፣ ከዚያም እንተዋወቃለን ። የኩዌት ሕዝብ በድንጋጌ ከመገዛት የተሻለ አንዳች ነገር ይገባዋል ። ዲሞክራሲያዊ ትውፊት ፣ ብዙ ጂ የተማሩ ወንድና ሴት ፣ እንዲሁም ራሳችንን የመምራት መብት አለን ።

ብለው ተናገሩ ።

የዚያን ዕለት ሞቅ ያለ ዲስኩራቸውን እንደምንም ወደ ቤት ተጋፍቶ ገብቶ ማዳመጥ ያልቻሉት ውጪ በቆሙት ሜርሴደስ የስፖርት አቶሞቢሎችና ቢ·ኤም·ደብሊዩ ሴዳኖች ውስጥ በነበሩ ልዩ ሬዲዮኖች አዳመጧቸው ። በኩዌት የዲዋኒያስ ልማድ መሠረት ሴቶች በተለዩ ክፍሎች ውስጥ ሆነው በቪዲዮ ሲናገሩ አዩዋቸው ።

የዲሞክራሲ ዲዋኒያስ ማታ ማታ የኩዌትን ከተማ አዳረሳት ። ብዙ ጂ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችና እንዲሁም ፍልስጥኤማውያንና ግብጻውያን መምህራቸው ዲሞክራሲያዊ ተቋሞች እንዲያንሠራሩ በመጠየቅ በድጋፍ ሠልፍ ላይ ተሳተፉ ። የአቤቱታ መጠየቂያ ዝርዝርም ፈረሙ ። ነጋዴዎችም ለንግድ ዲሞክራሲ ጥሩ መሆን አለበት ፣ እያሉ ከተማሪዎችና ከመምህራን ጋር ተደባለቁ ።

በመጋቢት 1982 የገዢው ቤተሰብ የምክር ቤት እንደገና መቋቋም ሥልጣን ላይ የመቆየት መብቱን ካልተፈታተነው ስለመቋቋሙ ለመወያየት ፈቃደኛ መሆኑን ልዑል አልጋወራሽ ሳዓድ አል አብዱላህ አል—ሳባህ ጠቆሙ ። በሕዝብ ድምፅ የተመረጡ ኀምሳ አባላትና በሳባህ የተሰየሙ ሃያ አምስት አባላት ያሉት አዲስ ብሔራዊ ሸንጎ የመጀመሪያ ጉባኤ በሚያዝያ 1982 ተጠራ ።

አዲሱ ሸንጎ እንደቀድሞው ምክር ቤት ዲሞክራሲያዊ ፣ ኃይለኛም ስላልነበረ ፣ ይበልጥ ነጠቅ ያለ ለውጥ እንዲደረግ ግፊቱ እየበረታ ሄደ ። ጃሰም አልቃጣሚ የተባሉ አንድ የቀድሞ የኩዌት ምክር ቤት አባል እርሳቸውና ሌሎችም ከዚህ የበለጠ ለመራመድ እንደፈለጉ ፣ ለዚህም ሲባል ገዢው ቤተሰብ ሕገመንግሥታዊ የበላይ ገዢ እንዲሆን ጠየቁ ። እኒሁ የቀድሞ አማካሪ በወቅቱ እንዲህ ብለዋል እየተባሉ ተጠቅሰዋል ፦



> እኛ ከብሪታንያ እንሻላለን ፣ መቆጣጠር ፣ መተቸት ፣ እናም የሕዝቡን ፍላጐት ሊነገርለት ወይም ጥያቄውን ሊያቀርብለት የሚችል ነፃ ምክር ቤት እያሻቸው ፣ የተከበረም የበላይ ገዢ አላቸው ። በዚህ መንገድ ግንም ገዢ በሥልጣኑ ያላግባብ ተጠቅሞ ወደሠለጠነው ዓለም ሊደባለት እንደማይችል ማረጋገጥ እንችላለን ። ታዲያ እኛስ ለምን አይኖረንም !

ከወራት በኋላ የዩሱፍ ኢብራሂም "ኒው ዮርክ ታይምስ" ውስጥ በኩዌት እየተነሣ ያለው ጥያቄ በዕውነቱ የሳባህ ቤተሰብ የመግዛት መብት አልነበረም ፣ ሊኖራቸው የሚገባ የሥልጣን ገደብ እንጂ ።" የሚል አባባል ያነባል ። የሳባህ ቤተሰብ እንደሳዑዲ ቤተሰብ ሳይሆን በአብዛኞቹ ኩዌታውያን ተቀባይነት አለው ። ለዚህ ምክንያቱ ሳዑዲዎች ሥልጣን የያዙት በዓረቢያ ልሳነምድር ካሉት ሌሎች ጐሳዎች ጋር ተዋግተው ድል በመቀዳጀት ሲሆን ፣ ሳባሆች ግን ከሌሎች ገናና የነጋዴ ቤተሰቦች ጋር ተደራድረው ሥልጣን መጨበጣቸው ነው ። ስለዚህ በትውፊት ፣ እና በኩዌት ሕዝብ ፈቃደኝነት ገዙ እንጂ በኃይል አይደለም ፣ ይህ ደግሞ በዓረብ ዓለም ያልተለመደ ነገር ነው ።

ሳዑዲዎችና ሌሎችም የዓረብ ገዢዎች እንዲህ ዓይነቱ የድፍረት አነጋገር ተላላፊ በመሆኑ ተንገርግረው ነበር ። በመላው መካከለኛ ምሥራቅ ዓረብ ምሁራን የገዢዎቻቸውን ሕጋዊነት መፈታተን እየጀመሩ ነበር ። ያለው ምርጫ የአንድ ሰው ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ወይም በምግባንን ብቻ እንደሆነ ፣ እነዚህ ብዙ ጊዜ በሥልጣን ያላግባብ የሚጠቀሙ መንግሥታት ባንድ ወቅት ነፃነት ስላቀዳጁት ብቻ ሕዝቡ ለእነርሱ ታማኝ የመሆኑንም ተገቢነት ይጠይቁ ነበር ። እነዚህ በዕውነት አብዮታዊ ነበሩ ፣ እናም ስለዚህ ለገዢው ወገን አስፈሪ፣ አስተሳሰቦች ነበሩ ።

ኢብራሂም "በኩዌት ዲሞክራሲ እንዲሰፍን እያየለ መሄድ እንደነበረበት በበኩሌ አልጠራጠርም ፣ እስካሁን ከበሕረ ሰላጤው እጅግ በጣም የጨዋና የዘመናይ ሕዝብ አገር የሆነችው ኩዌት ከዚህ ብዙ ወደፊት ለመራመድ ዝግጁ ነበረች ።" በማለት ሳገራቱ ተናግረዋል ። ነገር ግን ኢራቅ በወረራዋ ከገደለቻቸው እጅግ ከሚያሳዝኑት መኻል አንዱ የዲሞክራሲው ንቅናቄ ነበር ። ኩዌት ውስጥ ከቤተ መንግሥቶች ፣ ከቪላዎችና ከሰማይ ጠቀስ ሕንፃዎች ጋር—ብት ብት በማለት ላይ እያሉ የነበሩት ዓርማዎች ፣ ለፖለቲካ ቅስቀሳ የሚሠራጩ በራሪ ጽሑፎችና

ሑሳቦች ከሁለት ሺ በሚበልጡ የኢራቅ ታንኮች ተረምርመዋል ። ኢራቅ አንዲት አገር መግደል ብቻ አይደለም ፣ አንድ ምኞትም አምክናለች

ኢራቅ የፈጸመችው ወረራ አንደ ከፍተኛ አሜሪካዊ የጦር መኰንን እንዳሉት በማንኛውም አቅጣጫ ልክ ኬክ እንደሚያበሽልመው "ኬክ ዎክ" የተሰኘ ጉምለል ጉምለል የሚባልበት የአሜሪካ ዳንስ ዓይነት ነው። በአምስት ሰዓት ውስጥ አንድ መቶ ሺ የኢራቅ ወታደሮች ፣ ከፊሉ በአውቶቡስ ፣ ድምበር ተሰው ዋና ከተማይቱን ከበቧት ። አንድ የአሜሪካ ምክር ቤት የጦር ግዳጅ ኮሚቴ ጉዳይ ወታደራዊ ባለሙያ ፣ "ያለፕርፕር የአሚሩን ቤተሰብ አባሎች ለመማረክ ጥረት አድርገዋል — ጠላትን በሥጋዊ አካልንቱ በቀጥታ በብሔራዊ ሀላዊ ተምሳሌነቱም እንገቱን ለመሆዮፍ ።" በማለት ተናግረዋል ። ሆኖም ከአንድ ሺው የሳባሀ ቤተሰብ አባሎች ሦስት/አራቱ ብቻ ነበሩ — የተያዙት ። የአሚሩ ታናሽ ወንድም ፋሀድ የዳስማንን ቤተመንግሥት አላስደፍርም ፣ ብለው ሲከላከሉ በመሥዋዕትነት ወደቁ ፣ ግን አሚሩና ሌሎች በርካታ የንገሮው ቤተሰብ አባላት ፣ እንደሚባለው ኢራቆች ወደቤተመንግሥቱ ሊደርሱ በድስት ደቂቃ ብቻ ስትቀራቸው ፣ በሊሞሲን አቶሞቢል አጀብ ተከታትለው የሳውዲን ድንበር በማቋረጥ አመለጡ ።

በቁጥር ሃያ ስድስት ለአንድ የተበለጠው የተበታተነና ያልተደራጀ የኩዌት ጦር ሠራዊት ከሞላ ጎደል ወዲያው ተፈታ ። ላጭር ገዜ ብቻውን በጀግንነት የተከላከለው የአየር ኃይሉ ነበር ። ቀደም ሲል የተጠቀሱት ወታደራዊ ባለሙያ ፣ "ወዲያው ጦርነቱ በተጀመረባቸው ደቂቃዎች ውስጥ በሰሜናዊው የአውሮፕላን ማረፊያ ማኩብኩቢያውን በፈንጂ አረሰው" በማለት አስረዱ ። ቀጥለውም "ከዚያ በኋላ በረራው በኢራቅ ውያን ላይ አንድ ጊዜ ቦምብ ጣሉ ፣ ተመልሰው መጡ ፣ አውሮፕላኖቻቸውን በእጃቸው ጭነው ፣ ለሁለተኛ ጊዜ በረው አደጋ ጣሉ ። በሁለት ሰዓት ውስጥ ፣ አውሮፕላን ማረፊያቸው ከመወረሩ በፊት ሁለት ጊዜ ለግዳጅ በረዋል ። ጥቃቱ ከሌሊቱ ሰባት ሰዓት እስከዘጠኝ ሰዓት መካሄዱን ፣ አየር ኃይሉ ፈጽሞ ልምድ የሚጐድለው መሆኑ ሲታይ ፣ እጅግ በጣም የሚያስደንቅ ነው ።" ብለዋል ። በደቡባዊው አውሮፕላን ማረፊያም ደግሞ ፣ አብራሪዎቹ ከነአውሮፕላኖቻቸው ወደ ሳዑዲ ዓረቢያ ለመሸሽ ከመገደዳቸው በፊት— ለመከላከል ተልእኮ በረዋል ። ኢራቃውያን ወረራውን ካካሄዱ በኋላ በሁለትና በሦስት ሰዓት ውስጥ የዓረቦች ቡድን



እየተደራጀ ነበር ። ወታደራዊ ባለሙያው ስለዚህም ሲያብራሩ ፣ "ይህ ፈረንሳዮች በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ካደረጉት በጣም በይበልጥ የፈጠነ ነበር ። ደግሞ እኮ የሚደበቁበት ተራራም ሆነ ሜካ አልነበረም ። ይህ የከተማ ዐርበኝነት ነበር።" ብለውታል ።

ኢራቃውያን የወረራውን በሦስት ዓይነት የጦር ኃይል ክፍሎች ያካሄዱ ይመስላል ፦— በመጀመሪያ በፊታውራሪነት ድምበር ጥሶ በማምባር የገባው በኢራቅ—ኢራን ጦርነት በውጊያ የፈረጠመውና የተረፈው 'የሪፐብሊኩ ዘብ ሪፐብሊካን ጋርድ' የተሰኘው የላቀ የውጊያ ብቃት ያለው ኃይል ነበር ፣ ተጥሎ ከየቦታው ከወጣ ብልሹ ሥነሥርዓት የጐደለው ገበሬና ግጅራት መቺ ከተሜ የተውጣጣ በአሊ ሐሰን አል መጂድ የተመራ "ሕዝባዊ ሠራዊት" ተጥሎ መጣ ፣ በመጨረሻም በደጀን መደበኛው ጦርና እሥራትንና አካላዊ ቅጣትን በበላይነት የሚቆጣጠር ተፈሪው "ሙኻባራት" የተባለው የምስጢር ፖሊስ ነበር።

በሚቀጥሉት ጥቂት ሳምንታት አገር ጥሎ ከሚሸሸው ዘግናኝ የስደተኛ አጀብ ጋር የዝርፊያ ፣ ቤቶችን የመድፈር ፣ የሞት ቅጣት አፈጻጸምና ጭካኔ የበዛበት አካላዊ ቅጣት ወሬ ቀስ በቀስ ይነፍስ ጀመር ። ወንድ ልጆቻቸውን ድምበር ላይ በመነጠቃቸው የሚያለቅሱ እናት አባት፣ እናም ወደኋላ የቀሩ ወዳጆችና ፍቅረኞች እንደሰገጨት የሚያደርቅ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነበር ። አንድ ኩዌታዊ ሐኪም "እጅግ የምወደውን ጓደኛዬን ፣ ቤዳርን ፣ ወስዱት እና በማግሥቱ ሬሳውን ጉዳና ላይ ጣሉት ፣ ራሱን በኩዌት ሰንደቅ ዓላማ ጠቅልለው ጭንቅላቱ ላይ በሦስት ጥይት መተውታል ።" በማለት ለ"ኒው ዮርክ ታይምስ" የሚዘገንን ትዝታውን ገልጿል ።

ሌላው ስደተኛ ፣ የሃያ አምስት ዓመቱ ጀማል አል ኢብራሂም ፣ ኢራቃውያን ያደረጉትን ለ"ታይምስ" ዘጋቢው ለጀምስ ለሞይ ለማሳየት ሸሚዙን ገለጠ ። አፍሰው ወስደው ስለመረመሯቸው ሌሎች ወጣቶችም ነገረው ። "የዚህ ሰው ጀርባና ክንድ እንደሚታየው በብርቱ ድብደባ ፣ ጥቁርና ሰማያዊ ሰንበር ተሸፍኗል" ሲል ለሞይ ዘገበ ። ዘጋቢው እያይዩ እንዳሠፈረው "ልክ ትንሽ ታንክ ፈለግ እየተወበት ተመላልሶ በሥጋው ላይ የሄደበት ይመስላል" ይኸው ኢብራሂም የተሰኘ ወጣት የኢራቅ ወታደሮች በአቶሞቢሉ ውስጥ የኩዌቱን አሚር ፎቶግራፍ ካገኙ በኋላ

ዶጋግመው እንደ ደበደቡትና በኤሌክትሪክ ንዝረት እንዳሠቃዩት ተናግሯል ።

ኢራቅ ቀደም ሲል በግዛቷ ለሚኖሩ ክፍል ኩርዶችን እንዳደረገችው ሁሉ ፣ የኩዌትን ሕዝብ እንዳልነበረ አድርጋ የራሷን ሕዝብ ለማስገባት እየሞከረች ስለመሆኗ የአሜሪካ ባለሥልጣኖች ያደረባቸውን ስጋት በመስከረም 1983 መጀመሪያ በይፋ ገልጸዋል ። ይህ የነበረውን ጭብጥ ጨርሶ በቦታው እንዳልነበረ ማድረግ ከኢራቃውያን የአረመኔነት ባሕርያት አንዱ ነው ። ኢራቅ ኩዌትን በወረረችበት ጊዜ አንድ መቶ ሺ ኩዌታውያን ለበጋ ዕረፍት ወራት ካገራቸው ውጪ እንደነበሩና እስከ መስከረም 1983 መጀመሪያ ደግሞ ሁለት መቶ ሺ ኩዌታውያን ካገራቸው መባረራቸውን ሲ.አይ.ኤ. መገመቱን የአሜሪካ ባለሥልጣናት ገልጸዋል ። አንድ የአሜሪካ አስተዳደር ባለሥልጣን ይህን እንደገለጹት “እንዲወጡላቸው ፈለጉ ፣ በቀጥታ የልደትና የዜግነት መዝገቦችን አጎሳቡ ፣ በገፍ እንዲዘረፍና ቃጠሎ እንዲነግ የሚደረገው በአንድ በኩልም ካገራቸው የሚባረሩት ኩዌታውያን ወደ አገራቸው የሚመለሱበት ምክንያት ጨርሶ እንዳይኖራቸው ለማረጋገጥ ታቅዶ ነው።”

አንዳንድ የአሜሪካ ባለሥልጣናት በመስከረም 1983 አካባቢ ፣ ባገር አማንም ፣ አብዛኞቹ ኩዌታውያን እድል ካገኙ ካገራቸው ይወጣሉ—የሚል ተስፋ ነበራቸው ። እነዚህ ባለሥልጣናት አክለው እንደሚያስረዱት ፣ አገራቸውን ጥለው ለመሄድ ፈቃደኛ ያለመሆናቸውን የሚገልጹ ፣ በኢራቅ ደረጃ እንኳን ፣ ማንኛውም ነገር እንዲከብዳቸው ይደረጋል ። አንዱ ለሰለስ ባለ እንደበት እንዳሉት “የኩርዲስታን ‘ሰው አራጁ’ መጂድ ማንኛውንም የጎርበኝነት ንቅናቄ ባለበት ያኩላሹ ዘንድ መድበውታል ። እነዚያ ምስኪን ሰዎች ለምን እንደገቡ የሚያውቁት ነገር የለም ።”

ሁለተኛ ፣ በኢራቅና በኢራን መካከል ጦርነት በመካሄድ ላይ በነበረበት ወቅት ኩዌት “ከልክ በላይ እምነት” አድርጋባት እንደነበር ኮስቲነር ያምናሉ ። የኩዌት መሪዎች ሣዳም ኢራቅ ውድ መሥዋዕት ከፍላ ከኢራን በተቃጣው አደጋ ላይ ለተቀዳጀችው ድል ኩዌት በቂ ወሮታ ያልከፈለች ቢመስላቸውም አገራቸውን ከ10 ቢሊዮን ዶላር በላይ በረዳችው አገር ላይ ፈጽሞ እርምጃ የምትወስድ አልመሰላቸውም ።



ኮስቲነር በተጨማሪም ኩዌት በለጋሥነትና በአስታራቂነት በምትጫወተው ሚና የተነሣ ፣ ዛሬ ወደ ኋላ ሲታወስ ምንም መተማመኛ ሳይኖራት ቀስትና የማግኘት ስሜት አደረባት ። በኢራቅ ዓይን ፣ በባለቤትነቷ ጥያቄ ላይ አከራካሪ በሆነችው በቡቢያን ደሴት ላይ መከተም በመጀመሯ ኩዌት ኢራቅን ተንኩሳታለች ።” ብለዋል ።

በመጨረሻና ከሁሉም በላይ ለሞትና ለውድመት ከገዛ ራሷ ታሪክ ያገኘችውን ትምህርት ቸል ብላዋለች ። ቴዎዶር ድሬፐር በ1979 እንዳቀረቡት ፣ የውጭ ፖሊሲዋ ገለልተኝነት እንደሆነ በግልጽ በመናገር ትረካ የነበረችው ኩዌት ፣ “እንዳይተዋት እጅግ ባለጸጋና ራሷንም ለመከላከል እጅግ ደካማ” ነበረች ። በሌላም አባባል ከየትም በላይ ድምፅ በሚበዛበትና ለመቆጣጠር አስቸጋሪ በሆነው የዓለም ክፍል የምትገኝ ትንሽ ደካማና በነዳጅ ዘይት የበለጸገች አገር ሁሉጊዜም በማያቋርጥ ሁኔታ የሚደርስላት ያስፈልጋታል ። በ1891 ፣ ብሪታንያውያን ነበሩላት ፣ በ1979 ፣ አሜሪካውያን ነበሩላት ። በ1982 ፣ ማንም አልነበረላት ።

# መ ደ ም ደ ሚ ያ

ፕሬዚዳንት ቡሽ የምድር ጦራቸውን ወደባሕረሰላጤው ለመላክ ስለመወሰናቸው በርካታ ምክንያት ደረደሩ ። ውሳኔውን ያደረጉት የአሜሪካን ሕዝብ ወይም ወኪሎቹን አማክረው አይደለም ። በተለያየ ጭብጥ ላይ በርካታ አማራጭ ከሞከሩ በኋላ “ያሜሪካው ያንን የኑሮ ስልት” ለመጠበቅ ዘመቻውን መረጡ ።

አሜሪካውያን ወደሰላጤው የሄዱት “ያሜሪካውያን የኑሮ ስልት” በእጅጉ ለተመሠረተበት ለነዳጅ ዘይት መሆኑን በበለጠ በግልጽ መናገር አይችሉም ነበር ።

እኒህ ፕሬዚዳንት የአሜሪካን ሕዝብ እንዲህ ፊት ለፊት ሊጋፈጡት አይቻላቸውም—በእርግጥም ማንኛውም የአሜሪካ ፕሬዚዳንት አይችልም ። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማግሥት ጀምሮ አገሪቱ ነዳጅ ዘይት እንዳሻት በእንስተኛና በማይለዋወጥ ዋጋ እንድታገኝ ማድረግ በአሜሪካ የውጪ ፖሊሲ የላቀ ድጋፍ ሲሰጠው የኖረ ነው ። ግን አሜሪካውያንን በሚገባ ስለታወቀው ሱሳቸው ቢያሳስቧቸው ጥሩ ፖለቲካ አይሆንም ። ለዚህም ሱሳቸው ሙቁለት ብሎ መጠየቅም ቢሆን እንዲሁ ጥሩ ፖለቲካ አይሆንም ።

ስለዚህ ፣ ከሦስት ዓመት በፊት ስለ አንድ ከዚሁ ጋር ስለተዛመደ የውጪ ፖሊሲ ቀውስ ቲዎዶር ድሬፐር እንደጻፉት ፣ የአሜሪካ አስተዳደር የብሔራዊ ደህንነት ፣ የኢኮኖሚ አደጋ ፣ ባሕርና ውቅያኖስን በመርከብ የመተላለፍ ነፃነት ፣ ለወዳጆቻቸውና ለግብረአበሮቻቸው ሰላምና ደህንነት ጥበቃና የሰላም ጥበቃ መርሆቻውን ሁሉ አዘግይቶ ሲያበቃ በሙሉ ኃይል ተግባራዊ ለማድረግ የተገደደ መሰለው ። የያኔው



መከላከያ ሚኒስትር ካስፐር ዋይንበርገር እንዳሉትና ምናልባትም በአገራቸው የተተኩት ሪቻርድ ቼኒ በአንድ የሸንጎ ውይይት ላይ እንደደገሙት ለአደጋ የተጋለጡት የሥርዓት አልበኝነትንና የዐምባገነንነትን ኃይሎች ለመጋተር የተዳረጉት የነፃው ዓለም መሪዎች ናቸው ።

አንድ መርህ ከተጨባጭ ሁኔታ ጋር ሳይገናዘብ ሥራ ላይ ለመዋሉ አንዱ እርግጠኛ ምልክት የሚገለገሉበት ቋንቋ መሆኑን ድሬፐር አስረድተው “ዋና ጥቅም ፣ ብሔራዊ ደህንነት ፣ ነፃ ዓለምና ሰላም ለአደጋ ተጋልጠዋል” የሚሉት ሐረጎች ካልቀሩ ፣ ምናልባት ትንሽ አሳብ አድርጉ ፣ ፖሊሲውን በበለጠ በቀለለና በተብራራ አባባል መግለጽ ማስፈለጉን ድሬፐር አያይዘው ተናግረዋል ።

ከፕሬዚዳንቱ ባለሥልጣናት አንዳንዱ በበለጠ ግልጽ አድርገው ተናግረዋል ። ለምሳሌም እንደፕሬዚዳንት ቡሽ ተሹመው ወደዋሽንግተን ከመምጣታቸው በፊት የነዳጅ ዘይት ጉዳይ ባለሙያ የነበሩት የንግድ ሚኒስትሩ ሮበርት ሞዝባኸር ሲናገሩ ትንሹም ትልቁም በነዳጅ ዘይት የሚንቀሳቀስ መሆኑን ገልጸዋል ።

በባሕረሰላጤው የተገኙበትን መነሾ ማሰብ ከሁሉ አስቀድሞ የተባለውን ፣ ግን ሀሰትነት ያለውን ምክንያት ማስቀረትን ይጠይቃል ። መጀመሪያ ነገር አሜሪካ ከ150ሺ (በኋላ ከ470ሺ) በላይ (የደረሰ) የጦር ኃይል ወደበረሃው የላከችው ሣዳም ሑሴን አንድ ተንኮለኛ መንግሥት ስለሚመሩ ፣ ጨካኝ ስለሆኑ አይደለም ። አዎን ፣ ሣዳም ሑሴን ብዙ ሺ ዜጎቻቸው የተሰቃዩበትንና የሞቱበትን ምሕረት የለሽ የዐምባገነን መንግሥት መምራታቸው አይካድም ። ግን ሣዳም የነበሩት ጨካኝ ኢራቅ ከኢራን ጋር ባካሄደችው ጦርነት አሜሪካ ለዚህች አገር ባደላችበት ጊዜ ነው ። እየተሸነፉ በነበረበት ጦርነት የረዳቸውን መረጃ የአሜሪካ መከላከያ ሚኒስቴር ከሰለላ ሳታላይት በመቅዳት ይሰጣቸው በነበረበት ጊዜ ሣዳም ሑሴን ጨካኝና ነፍሰገዳይ ነበሩ ። በኢራን ወታደሮች ላይ ፣ ቀጥሎም በሰላማዊ ዜጐቿ ላይ ፣ በመጨረሻም በራሳቸው ዜጎች ላይ የተኩስ አቁም ስምምነት ከተፈረመ ከወራት በኋላ የመርዝ ጢስ ረጭተው ነበር ። ተቀናቃኞቻቸውን በገዛ እጃቸው ሲያሰቃዩና ሲገድሉ ኖረዋል ። አሸባሪነትን እንደሕጋዊ የውጭ ፖሊሲ ክፍል ሲገለገሉበትም ኖረዋል ። አዎን ፣ አገራቸውን የእርሳቸው ሰብእና አምልኮ የባዓዝን

ፖርቲና የኢራቅን ባህልና ተቋማት ወደተካበት የዛቻና የፍርሀት ምሽግ ለውጠዋታል ።

ነገር ግን አንድ የኋይት ሀውስ ባለሥልጣን እንዳሉት ፤ ይህ ሁሉ ግዳም ሑሴን በአካባቢው መኖራቸውን ፤ በአካባቢው የአንድ ኃይለኛ አገር መሪ መሆናቸውንና አሜሪካ ከእርሱ ጋር ግንኙነት ማድረግ እንዳለባት ከማወቅ አላገዳትም ።

ምናልባት ልክ እንደሚዳምም ጨካኝ አይሁን እንጂ ዓለም በከፍተኛ ሥልጣን ላይ ባሉ ሌቦችና ነፍሰገዳዮች የተሞላች ናት ። ነገር ግን የሶርያው ሀፊዝ አል አሳድም ምናልባት ከኢራቁ ሪባም ባዓዛዊ አቻቸው በእጥፍ ተንኮለኛ መሆን የአሜሪካን የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር ጄምስ ቤከርን በኢራቅ ላይ ለሚካሄደው በይነብሔራዊ ዘመቻ ድጋፋቸውን ለመጠየቅ በመስከረም 1983 ወደ ደማስቆ ከመመላለስ አልገታቸውም ። እርግጥ ቤከር በግል ባያበረታቷቸውም ኖሮ አሳድ የረጅም ጊዜ ተቀናቃኛቸውን በመገዝገዝ ምናልባት ይደሰቱ ነበር ይሆናል ። ጋን እም በረራ ቁጥር 103 የአሜሪካን የመንገደኛ አውሮፕላንና በውስጡ የነበሩ በመቶ የሚቆጠሩ አሜሪካውያን በሰማይ ላይ እንዳሉ ያቃጠሉትን አሸባሪዎች በክብር ሲቀበል ከነበሩና ካሉ ሰው ጋር መገናኘት ያስፈልግ ነበር?

በአሁን ጊዜ ከሁለቱ ክፉት የአሳድ መሻሉን የኋይት ሀውስ ቤተመንግሥት ባለሥልጣኖች ተናግረዋል ። ነገር ግን የኢራን አያቶላ ፋሆላ ኾሜኒ ወደኢራቅ ዘልቀው በመግባት በጦርነቱ ድል የሚቀዳጁ መስለው በነበረ ጊዜ አንድ የቀድሞ የአሜሪካ መንግሥት ባለሥልጣን ስለግዳም ሑሴን የተናገሩት ልክ ይህንኑ ነበር ። ግዳምን ከኩዌት በግድ ለማስወጣት በአሜሪካ መሪነት በመካሄድ ላይ ባለው ጥረት አሜሪካ አሳድን ማሳተፏ ከነፍሰገዳይ የምትመርጠው ቸርና አድርባይ መሪ መሆኑን አሳይታለች ። ስለዚህ አሜሪካ ወደሰላጤው የሄደችው ግዳም ሑሴን ክፉ ስለሆኑ አይደለም ። በዕውነት አስፈሪ መሆናቸው አሜሪካውያንን ኃይሎቻቸውን ለማዝመት በመወሰናቸው ያለነገር እንደሆነ እንዲሰማቸው ያደርጋቸው ይሆናል ፤ ግን አሜሪካ እዚያ ከመገኘቷ ምክንያት ጋር መምታታት የለበትም ።

ፕሬዚዳንቱ እንዳሉትም የአሜሪካ ጦር ኃይሎች በባሕረሰላጤው የሚገኙት የኩዌትን ሕጋዊ መንግሥት ወደሥልጣኑ ለመመለስ ነው



ግለት አይቻልም ። መከላከያ የለሿ ኩዌት በባሕረሰላጤው ፤ እንዲያውም በመላው የዓረብ ዓለም እጅግ ከሠለጠኑት አገሮች መኻል ናት ። ለዓላማቸው የይስሙላ ድጋፍ ቢሰጡ የቆዩ ብዙ ሌሎች የዓረብ አገሮች እንቀበልም ያሏቸውን ብዙ ፍልስጥኤማውያን ተቀብላለች ። ኩዌት የሳባህ ቤተሰብ ከ1748 ጀምሮ የአሜሪካ መሪዎች አገራቸውን ከመሩበት ይበልጥ ፤ በግልጽም ከግዳም ጨካኝ በዓዞች ይበልጥ ፤ ለረዘሙ አያሌ ዘመናት አገሩን መርቷል ። ኩዌት በወታደር ሳይሆን በንጋዴ የምትመራ ደግ ፤ በጠቅላላውም ለቤትጄም ሆነ ለውጪ ቤጋ የተመቸች አገር ነበረች።

ነገር ግን ኩዌት ከካርታ ላይ እንድትጠፋ የተደረገችው ፤ አሜሪካ የጦር ኃይሏን ወደባሕረሰላጤው የላከችው ኩዌት ጥሩ አገር ስለሆነች አይደለም ። ፈረንሳዩ ተንታኝ ፍራንሷ ሀይስቡርግ እንዳለው ከ1937 ወዲህ "የተሠዋ" አገር ባይኖርም ሌሎች ጥሩ አገሮች እንዳልነበሩ ሆነዋል ። ቲቤትን እንያት ። ብሔራዊ ህላዌዋን በማጣቷ አሜሪካ ውስጥ እስከዚህም ያዘነላት የለም ።

ከዚህም በተጨማሪ ፤ ("በወደቀ ዛፍ – ምሳር ይበዛበታል" እና) የዓረብ ምሁራን እንዷ ዘመን ያለፈበት ፤ እንዷ በኢራንና በኢራቅ ጦርነት ተጽእና ዲሞክራሲን ሕገወጥ ባደረገ አንድ ፈላጭ ቆራጭ የምትገዛ ፊዩዳላዊ አገር ፤ እያሉ ኩዌትን መዝለፍ ሲጀምሩ የተወረረችባቸው የኢራቅ ታንኮች ያስነሡት አቧራ ገና መሬት መያዙ ነበር ። የሳባህ ቤተሰብ ምን ነው "ሕጋዊ"? እያሉም ተዘባበቱባት ። ግዳም ጦራቸውን ቢያስወጡም እንኳ የኩዌት ወደነበረችበት ሁኔታ መመለስ ዘበት መሆኑን ያላመነ ማግኘት ላሳር መሆኑን ቶዓድ አጃሚ የተባሉ አስተዋይ የዓረብና የአሜሪካ ፖለቲካ ተንታኝ ተንብየዋል ። ተንታኙ እያይዘውም በኩዌት የዘመናዊ መንግሥት አስፈላጊነት ጥያቄ እየጉላ በመምጣቱ በትክክል መመለስ እንዳለበት አመልክተዋል ። በትንተናቸው የደረሱበ ትን ከመግለጽ ወደኋላ የማይሉ ተንታኞች ፤ ለምሳሌ ኩዌት ነጻድ ዘይት የሌላት የሠሀራ በስተደቡብ አፍሪካዊ አገር ብትሆን ኖሮ እንድም የአሜሪካ ወታደር ሊከላከልላት እንዲዘምት አይደረግ እንደነበር ያም ናሉ። ስለሆነም አሜሪካ በባሕረሰላጤው የተጠመደችው የሉዓላዊነትን መርህ መጣስ የመከላከል ወይም የኩዌትን መሪዎች ወደተዋቡት የገበያ አዳራሾቻቸውና ቤተመንግሥቶቻቸው የመመለስ አባዜ ይዟት አይደለም።

የአሜሪካ ጦር ኃይሎች ወደ እዚያ የዘመቱት በቋፍ ላይ ከነበረው የኩዌት ዲሞክራሲ ጋር እንኳ ሊነፃፀር የሚችል ዲሞክራሲ የሌለውን ዕውነተኛ በአንድ ፈላጭ ቆራጭ ፊዩዳል የሚመራውን የሳዑዲ መንግሥት ከጥቃት ለመከላከልም አይደል ። በዕውነቱ የሳዑዲ ቤተሰብ ከእስልምና በስተቀር ሁሉንም ዓይነት ሃይማኖት ሕገወጥ የማድረግ መብት እንዳይገፈፍ ፤ የቤተሰቡ በሴቶች ላይ የሚፈጽመው የረቀቀ የኃይል ጭቆና እንዳይወገድ ፤ ወይም ዘማውያን በድንጋይ ወገር መግደሉና ወይም የሌቦችን እጅ ፤ በሠይፍ መቁረጡን እንዲቀጥል መከላከልን አሜሪካ ጉዳዬ ብላው ነበር ? በበረሀማው የንጉሥ ግዛት ያለመስማማት ድምፅ ያለመኖሩን ጉዳዬ ብላው ነበር ? በሳዑዲ ውስጥ ነፃነትን ከመገፈፍና ሰብአዊ ክብርና ከመደፈር ለመከላከል ነው ፕሬዚዳንቱ የጦር ኃይል የላኩት ብሎ ለመከራከር የደፈረ የአሜሪካ ባለሥልጣን የለም ።

ዳሩ ግን ፤ ኢራቅ ኩዌትን እንድትወር ምክንያት ለሆኑ በርካታ ምክንያቶች አጸፋውን እየሰጡ ነበሩ ። እርምጃ የወሰዱት ከዓለም የነዳጅ ዘይት ክምችት አርባ ከመቶውን በያዘው በዚያ የዓለም ክፍል በተለይ ሣዳም ሑሴን ፤ በተለይ ያችን መከላከያ የለሿን ኩዌትን መዋጡን በመምረጣቸው ምክንያት ነው ።

ባጭሩ ፤ የአሜሪካ የጦር ኃይሎች ወደሳዑዲ ዓረቢያ የተላኩት አገራቸው ነዳጅ ዘይት የምታገኝበትን ሥፍራ ለመከላከል ነው ።

አሜሪካ በ1960ዎቹ መጀመሪያ በዝቅተኛና በማይለዋወጥ ዋጋ ነዳጅ ዘይት የምታገኝበት አስተማማኝ ሥፍራ በከልሉ የአሜሪካ ደጋፊ በመሰሉ ጠላቶቿ ለመጀመሪያ ጊዜ ፈተና ላይ በወደቀበት ወቅት ከደረሰው የነዳጅ ዘይት እጥረት በተገኘው ግንዛቤ መሠረት ተጠንቅታ ቢሆን ኖር የቡሽ መንግሥት በነሐሴ 1982 ያደረገውን ለማድረግ የተገደደ ባልመሰለውም ነበር ። የባሕረሰላጤው ፍጥጫ በከፊል የሠረፀው ከሣዳም ሑሴንና ከአሜሪካ ስሰት ነው ። በሬጋን መንግሥት የአገሪቱ የነዳጅ ዘይት ፍጆታ እያደገ መሄድ ጀመረ ። የ“ቁጠባ” ነገር ቦታ አጣ ። ነዳጅ ዘይት ጥንቡን ጣለ ፤ አገሪቱ ነዳጅ ዘይት የማከማቸቱን ነገር ከአጀንዳዋ ላይ ሠረዘች ፤ እናም ከውጪ አገር ፤ በተለይም ከባሕረሰላጤው በሚመጣ ነዳጅ ዘይት መተማመኑ በጉልህ ጨመረ ። አሜሪካ ከፈተኛው



የነዳጅ ዘይት እጥረት በኋላ በነዳጅ ገቢ ቁጥር በነዳጅ ታክስ እማካይነት የነዳጅ ዘይትን ዋጋ ከፍ አድርጋው ቢሆን ኖር ፤ ሸንጉ ነዳጅ የማከማቸትን ግዴታ የሚያደርግ ደንብ ደንብቶና ለጥሩ የኃይል አጠቃቀም ማበረታቻ ፈጥሮ በነበረ ፤ መንግሥት በፀሐይ ፤ በተፈጥሮ ጋዝ ፤ በድንጋይ ከሰልና በኑክሌር የኃይል ምንጮች ለመጠቀም ሞክሮ በነበረ አሜሪካ በገባችበት ጣጣ ውስጥ እትገባም ነበር ። ነገርግን ሣዳም ሑሴንን የመቋቋሙን ጀግንነት ያገኙት ፕሬዚዳንት ቡሽ ሰዓቱ በማይቷልና ግብግቦውም አልቻል ብለው በቀጥታ ለአሜሪካ ሕዝብ ለመንገር የፖለ
ቲካ ጀግንነት ጥሪ ሊያቀርቡ አልቻሉም ።

ዓረቦችን በአካባቢው የእሥራኤል መገኘት ምን ያኽል እንዳበሳጫቸው አይነግና የከልሉን የእርስ በርስ መቆናቆንና በማኅበረሰብ ውስጥና በአገሮች መኻል በሀብታምና በደሀው መኻል ያለውን ልዩነት በብልሀትና ተግባራዊ ሊሆን በሚችል የውጪ ፖሊሲ ማስወገድ ያለመቻሉ መካከለኛው ምሥራቅ በግጭት መታመሱን የሚቀጥል መሆኑን ያረጋግጣል ። አሜሪካ ይህን ቀላል ዕውነታ ስለተቀበለች ይሆናል ባለፈው ዓሥርተ ዓመት ከሮናልድ ሬጋን “ፍጆታዊነት” (Consumerism) የተለየ ስትራቴጂ (የፍቅ ግብ) ወደመከተል የመራት ። አሜሪካ በባሕረሰላጤው ላይ ያላትን ጥገኝነት ለመቀነስ ሁነ ብላ የማያወላውልና በኢኮኖሚ ረገድ
እስቸጋሪነት ያለው ጥረት የማድረግ አቋም በያዘች ነበር ።

ምናልባትም ያን ጊዜ አሜሪካውያን ራሳቸውን ከባድ ጥያቄ በጠየቁ ነበር ። ለምሳሌም ለምን ተብሎ ነው ርካሽ ነዳጅ ዘይት ከአገሪቱ “ዋነኛ ጥቅሞች” አንዱ የሚሆነው? ወይም አሜሪካና ሌሎቹ የኢንዱስትሪ ኃያላን አገሮች ከምን ተነሥተው ለየትኛውስ ግብ ነው በባሕረሰላጤው ያለማቋ ጣል ለመግባት የሁሉንም ድጋፍ የፈለጉት ? ከባሕረሰላጤው ያለማቋረጥ ነዳጅ ዘይት ለማግኘት መሆን ይኖርበታል ? ወይስ የመካከለኛው ምሥራቅ ፖለቲካ ተለዋዋጭነት እንዲህ ያለማወለስ ከዚያ ነዳጅ ዘይት ለማግኘት ለመፍቀዱ በእርግጠኛ ይጀምር ?

ይልቁንስ አሜሪካና ከታላላቅ ተባባሪዎቿ አብዛኛው እስከወዲያኛው የባሕረሰላጤውን ርካሽ ነዳጅ ዘይት አቅርቦት ይዞ መቆየት የመቻላቸው ሐሳብ እንደተጠናወታቸው ናቸው ። የቡሽ መንግሥት የወቅቱን ቀውስ በ“ፖሊሲ ክስረት” ሊቋቋመው ባለመቻሉ የሚሰነዘ

ረው የተደጋገመ ክስና ውቅስ ሲታይ የሬጋንና የቡሽ መንግሥታት መልክአምድራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዕውነታን ለመቀበል ፈቃደኛ ካለመሆናቸው ጋር ሲነፃፀር ኢምንት ይሆናል ። በቃ የመካከለኛው ምሥራቅ ነዳጅ ዘይት ከእንግዲህ በሸማቾቹ ቁጥጥር ሥር ላይቆይ ይችላል።

ፕሬዚዳንት ቡሽ ቀውሱ ከተከሠተ በኋላም እንኳን ስለኃይል ምንጭ ፖሊሲ ለሕዝቡ ያልተለመደ ጥቆማ አስተላለፉ ። የአሜሪካ ብሔራዊ ጥቅሞች ከቡሩን ነዳጅ ዘይታቸውን እንቀው በመያዛቸው ከሆን ፣ የቡሽ ያገር ውስጥ የኃይል ምንጭ ፖሊሲያቸው አፀፋ የነዳጅ ዘይት ኩባንያዎች በዋጋ ተመን ፖሊሲ "እንዲገቱ" ጥሪ ማድረግ ሆኖ! እናም ቡሽ እንዲገታ ስንኩል ጥሪ ቢያደርጉም አሜሪካውያን የነዳጅ ዘይት ዋጋ ሲንር በማየት ላይ ሳሉ እርሳቸው ሲጋራ በተሰኘችው ነዳጅ በል ጀልባቸው በኬንባንክፖርት ጠረፍ ላይ መንሸራሸሩን የማይተዉት ለምንድነው ! ቀውሱ ከተጀመረ ወዲህ የቡሽ መንግሥት ባለው ተወዳጅ ጊዜ ማሳለፊያ-በፖለቲካ ጥፋት ማላከኪያ ፍለጋ ተጠምዷል ። የዊስኮንሲን የሕዝብ እንደራሴ – ሌስ አስፒን ፣ ቻንጋይ ሼክ ከሥልጣን ከወረዱ በኋላ ቀኝ ክንፉ "ቻይናን ከእጃችን እንድትወጣ ያደረገው ማነው ?" በሚል ዘመቻ ፕሬዚዳንት ትሩማንንና ፕሬዚዳንት አይዘንሀወርን መወረፉን ጠቅሶ "እርግጠኛ ባትሆንም ኩዌትን እንድናጣት ያደረገው ማነው?" የሚል ዘመቻ አሁንም በጥቂቱ ሊሰማህ ይችላል" ብለዋል ።

ብዙዎች ለዚህ ተጠያቂ እንደሆኑ ተጠቅሷል ።

ከነዚህም መካከል በኢራቅ የአሜሪካ አምባሳደር የነበሩት ሴት ሳይጠራጠሩ ከዋሽንግተን የሚሰጣቸውን ወዳጅነትን የማፍራት መመሪያ በመቀበላቸውና የሣዳምን ዛቻ መስማት ወይም ከእርሱ ጥንቃቄ ማድረግ ስለተሳናቸው ተጠያቂ ሆነዋል ። የአሜሪካ የምሥራቃዊና የደቡብ እስያ ጉዳይ ረዳት የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር መንግሥቱ የሚከተለውን የሣዳምን መንግሥት የመርዳት ፖሊሲ ሳይለውጡ በነበሩበት እንተው መቆየታቸው ተጠያቂ ያደርጋቸዋል ፣ እስካሁን ተደጋግሞ እንደተነገረን የአሜሪካ ጥቅም ለአደጋ የተጋለጠበትን የዓለም ክፍል ችላ ማለታቸው የውጪ ጉዳዩን ጀምስ ቤከርን ተጠያቂ ያደርጋቸዋል ። ፕሬዚዳንት ቡሽ የአሜሪካን ወታደሮች ወዳገራቸው የሚመለሱበትን አሳማኝ እቅድ ሳያወጡ ፣ ምናልባት በውጊያ ፣ ድልን እንዲቀዳጁ አልያም



እንዲሞቱ ወደሳዑዲ በረሀ በማዝመታቸው በተጠያቂነት ተጠቅሰዋል ። ወደፊት በጋራ ተጠያቂ የሚኮንበት ከልክ በላይ የፖሊሲ ጉድለት ሊኖር ይችላል ፣ ወይም ከቀና በጋራ ክብርን መቀዳጀት ሊመጣ ይችል ይሆናል ።

የአሜሪካ መንግሥት እስካሁን የተሰነዘረበትን ቀና ጊስ የተቀበለበት መልክ የሚስብ ነው ። አንዳንድ ባለሥልጣናት ከሣዳም ጋር ሞት ያለ ወይም ቢያንስ ከእርሳቸው ጋር በሥራ መግባባትን ከመፍጠር እርሳቸውን የ"ማለዘብ" እንዲያው "ዕውነታ"ን ለተከተለ ፖሊሲ ቆመዋል። ደግሞ እኮ ሣዳም በኬሚካል ጦር መሣሪያ ላለመጠቀም ቃል እንዲገቡ ከጠየቀች በኋላ ኢራቅ በመጨረሻ የከፋ ሁኔታ ካልተፈጠረ በስተቀር ከቶም እንደገና በኬሚካል ጦር መሣሪያ ላለመጠቀም ተስማምታለች ። የሣዳም መንግሥት የብዙ ሌላ አገር ባንክና መንግሥታት ያለባቸውን እዳ በዚያም ሆነ በዚህ በጊዜው አልከፈሉ ይሆናል ፣ የነበረባትን የአሜሪካ እዳ ግን ከቀኑ ዝንፍ ሳይሉ ከፍለውታል ። ነገር ግን የቡሽ መንግሥት ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ሁሉ ባልጠበቁት ወረራ ኩምሽሽ ማለታቸውን ይናገራሉ ። ሁሉም ዕውነት ከሆነ ይበቃል ።

አንዳንድ ባለሥልጣናት ከዚህም አልፈው አሜሪካ ከወረራው በፊት ባለፉት ወራት በኩዌት ላይ ጥቃት እንዳያደርሱ ግፊት አድርጋም ቢሆን ኖሮ ፣ እናም በተለይ በባሕረሰላጤው ወታደራዊ እርምጃ እንዳይወስድ ሊሰጥ የሚችለውን የመጨረሻ ጥብቅ ማስጠንቀቂያ ሰጥታም ቢሆን ኖሮ ጨካኙ ኢራቃዊ ኩዌትን መያዛቸው አይቀር እንዳልነበር ይገምታሉ። በሌላ በኩልም ሣዳም ማስጠንቀቂያ ስላልተቀበሉ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸው ቢሆን ኖሮ ምን ያደርጉ እንደነበር ማወቂያ መንገድ የለም ። ምን ያደርጉ ወይም እያደርጉ እንደነበር ዓለም ከቶም ሊያውቅ አይችልም። ዓለም የሚታመን ማስጠንቀቂያ ሳይሰጣቸው ያደረጉትን ብቻ ታውቃለች ።

ከዚህም በላይ ፣ አሜሪካ ምንም አለች ወይም ለማድረግ ዛተች ፣ ሣዳም መውረር ከፈለጉ የእርሳቸውን መንግሥት በ"ማለዘብ" ተስፋ የቡሽ እርሳቸውን የመለወጥ ፖሊሲ በተጨባጭ እንደታየው እንኳን አለበት — በእርግጥም ቀጋቢስ ። ሣዳም በዚያም ቢኗቸው በዚህ የሚኗቸውን የማይሰሙ ከሆኑ አሜሪካ የሚዘጋጉነውን የሰብአዊ መብት ድፍረታቸውን ፣ ኬሚካላዊ ፣ ሥነ ሕይወታቸውና ኑክሌር ጦር መሣሪያቸ

ውን ለማምረት የሚያስፈልጋቸውን ለመግዛት ወይም ለመስረት የሚያደ
ርጉትን ምሕረት የለሽ ዘመቻና ፣ እንዲሁም ያለማቋረጥ ጉረቤቶቻቸውን
ማስፈራራታቸውን ያቆሙ ዘንድ ካደረገችው በጣም በጠነከረ መልክ
ልታስጠነቅቃቸው በተገባት ነበር ። አሜሪካ ምንም አለቻቸው ምን
ሣዳም ኩዌትን መውረራቸው አይቀርም ነበር ማለቱ የአሜሪካ የማግባ
ባት ፖሊሲ ተጀምሮ እስኪጨረስ እርባን እንደሌለው ማመን ነው።

እልፍ ሲያዩት በሰብአዊ መብትና በክልል መረጋጋት ረገድ
ከተገለጹ የአሜሪካ መርሆች ጋር ወጥነት ያለው አንድ ጠንካራ የአሜሪካ
አቋም በኢራቅ ተሰሚነትን ሊያገኝ ይችል ነበር ይሆናል ፤ ፖሊሲ
አውጪዎች እንደሚሉት ደግሞ ኢራቅ ከአሜሪካ ጋር ያላትን ጠቃሚ
የኢኮኖሚ ፣ የዲፕሎማቲክና የፖለቲካ ግንኙነት ለመቀጠል ጉጉት አላት ።
አሜሪካ የፖሊሲዋን ከስረት ማመኗ ሣዳም ጉረቤታቸውን የመውረራቸ
ውን ትክክለኝነት አያሳይም ወይም ይቅርታ አያስደርግላቸውም ። ግን
የአሜሪካ መንግሥት ሣዳም እንዲህ በአስከፊ መልክ ፣ ባዩት ፖሊሲ ላይ
ለምን እስከዚህ ለረጅም ጊዜ ሙዝዝ እሉበት የሚለውን ጥያቄ ያስነሣል።

ሣዳም ሑሴን ከተዘፈቁበት እዳ ለመውጣት ከሌላው ሲነፃፀር ዋጋ
የማይጠይቅ መፍትሔ አድርገው በማየትና በተጨባጭ በየብስ የተከበበ
ችውን አገራቸውን የባሕር በር እንዲኖራት ሲሉ ኩዌትን በመውረር
ፈንታ ለገዛ አገራቸው ሀላቂ ሲሉ ተገደው ወረዋት ቢሆን ኖሮ አሜሪካን
ከሚያኽል ኃያል መንግሥት ጠንካራና አስገዳጅነት የሚኖረው ማስጠን
ቀቂያ ከወረራው እንዲታቀቡ ያደርጋቸው ነበር ይሆን ? አንድ ከፍተኛ
የኢራቅ ባለሥልጣን እንዳቀረቡት ሣዳም አሜሪካን በመገናኛ ብዙኃን
ያሁኝ ልቀቁኝ ከማለት እንደማታልፍ — አጉል ፍሩኝ ባይ "የወረቀት
ነብር" ቆጥረዋት ከነበረ እንግዲያው የአሜሪካ መንግሥት በመካከለኛው
ምሥራቅ በሚከተለው ፖሊሲ ላይ ኒስ የሚሠነዝሩ ፣ ፕሬዚዳንት ቡሽ
እንድን በምባንኑን ማባበላቸው አቅጣጫ የላተ ፤ ፍቱንነት የሌለውና
ከተገለጸው የአሜሪካ መርህ ጋር ሥምረት የሌለው ነው ቢሉ ትክክል
ናቸው ።

አሁን እያሌ ሙቶ ሺ የብዙ አገሮች ወታደሮች በሳዑዲ ዓረቢያ
ስለሚገኙ አሜሪካ የከሰረ ፖሊሲዋን ጦስና የሣዳምን ወረራ መመከት
አለባት ። ውስጥ ለውስጥ የአሜሪካን ተገንነት የጠየቁና ግን የአሜሪካን



በአካባቢው መገኘት በይፋ የተቃወሙት ኩዌትና ሌሎችም የሰላጤው
አገሮች በየራሳቸው ላይ ችግር እንዲመጣ መርዳታቸውን ሊገነዘቡት
ይገባል ። በአንድ ጨኸት በሚበዛበት ጠንካራ የዓለም ክፍል አንዲት
ትንሽ ደካማ አገር ሁሉም ነገር ሁሌ እንዲኖራት ማድረግ አትችልም ።
ከዚህም በላይ ፡ በኩዌት የምክር ቤት ሞቶ ያለ የፖለቲካ ክርክር
ያለመኖሩ አቅጣጫውን የሳተው የሳባህ ቤተሰብ የውጪ ፖሊሲ ያለተቃ
ውሞ ኖረ ማለት ብቻ ሳይሆን ፡ የኩዌት ጎያስያን የመንግሥቱን
ሕጋዊነት የሚቀናቀኑበት መሠረት አላቸው ማለትም ነው ። በአብዛኛው
የዓረብ ዓለም ክፍል የምክር ቤቶችና የዲሞክራሲያዊ ተቋሞች መኖር
ከይስሙላ ብዙም ላይርቅ ይችላል ፤ ነገርግን እንዚህ በኩዌት ኖረው
ቢሆን ሣዳም የሳባህን ቤተሰብ መፈንቀላቸውን ምዕራባውያን መቋቋግ
ቸው የበለጠ ልባዊ በሆነ ነበር ።

ሳዑዲዎች ለጊዜው አንድ ነገር አምነው እንዲቀበሉ መጠየቅ
አለባቸው ፤ አሜሪካ የእነርሱን ነዳጅ ዘይት የምትፈልገውን ያኽል
እነርሱም እርዷን ይፈልጓታል ። እናም የአገራቸውን ሳዑዲን ድንበር
የሚከላከሉትን የአሜሪካ ወታደሮች በመጠኑም ቢሆን መቻል አለባ
ቸው። በሳዑዲ የእስልምና ሕግ ትርጉሚ መሠረት ከእስልምና በስተቀር
ሌላ ሃይማኖት መከተል ክልክል ስለሆነ ብቻ የወታደሮቹ ንስሐ አባቶች
ከልብስ ተክህኖዎቻቸው ላይ መስቀልና የዳዊት ኮከብ ምስሎችን
እንዲያወልቁ ፤ ወይም ራሳቸውን "የግብረገብነት መኰንኖች" ብለው
እንዲጠሩ መጠየቅ የለባቸውም ። የዓረቢያን ነዳጅ ዘይት ከጥቃት
የሚከላከሉት 900 አይሁዳውያን ወታደሮች ፤ አይሁድነት በሳዑዲ ላይ
የተቃጣ ሴራ ይመስል ፤ የአይሁድን ሁለት ዋና ዋና በዓላት — ሮሽ
ሀሻናህንና ዮም ኪፑርን በምስጢር ለማክበር በስውር መወሰድ የለባቸ
ውም ። አንድ የሳዑዲ ወታደር ከወገብ በላይ ራቁቷን የሆነች ሴት ሲያይ
ተዝለፍልፎ ሊወድቅ ይችላል ተብሎ ሳዑዲዎች የሚበሩበትን አውሮፕ
ላን የሚጠግኑ አሜሪካውያን ሴት ወታደሮች በ120 ዲግሪ ሙቀት
መንፈር የለባቸውም።

ዘመናዊ የጦር መሣሪያ ለመጠቀም ዕውቀቱ ወይም ፍላጐቱ
የሌለው ሕዝብ መሸጥ የንግድ ሚዛኗን ለመጠበቅ እንደሚረዳት ብታው
ቅም ፤ ለአንድ ወዳጅ አገር መከላከያ ምንም ያኽል ድጋፍ እንደማይሰጥ
አሜሪካ እስካሁን ሊታወቃት ይገባል ። ባለፈው ዓሥርት ዓመት ኩዌት

አኮ ፣ ምናልባት የጦር ኃይሏ ወደሳዑዲ ከሸሸ በኋላ አብዛኛው በኢራቅ እጅ የገባ ብዙ ሀውክ ሚሳይል በብዙ ሚሊዮን ዶላር ገዝታለች ። በመስከረም 1983 በሸንጎ ተጽእኖ በመጠኑ የእሥራኤልን ምኞት በማንፀባረቅ ፣ ግማሹን እስከ 1983 ሁለተኛ አጋማሽ እንዲያስተላልፍ ባያስገድደው ኖሮ የአሜሪካ መንግሥት ለሳዑዲ 20 ቢሊዮን ዶላር ያኽል የሚያወጣ አዳዲስ የጦር መሣሪያ ሸጦላታል ።

ደግሞ አሜሪካ በባሕረ ሰላጤው የግ ጥቅም ከጥቃት እየተጠበቀ መሆኑን መወሰን ይገባታል ። ከአሜሪካ ይበልጥ አውሮፓውያን ግብረአበሮቿ ከመካከለኛው ምሥራቅ ነዳጅ ዘይት የሚያገኙ ከሆኑ ይህንኑ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሐቅ የሚያንፀባርቅ የጋራ ደህንነት ጥበቃ ሥርዓት መዘርጋት አለበት ። የአሜሪካው የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር — ጀምስ ቤከር ጃፓንና የምዕራብ አውሮፓ አገሮች ወደ በረሀው የዘመቱትን የአገራቸውን ጦር ኃይሎች ወጪ እንዲደጉሙ መማጸናቸው፣ ምዕራቡ ዓለም ፣ ሚኒስትሩ ይደርሳል ፣ ብለው የገመቱትን ጠቅላላ አደጋ አብሮ ይቀበላል የሚለውን የአሜሪካ ግምት ዕውነት እንዳልሆነ አሳየ ። ተንታኙ ቶማስ አምስታድ በቅርቡ እንዳሠፈሩት ዕውነታው በሙሉ የተለመደ ነው ፣ "ዋና ዋና ግብረአበሮቿ በኢኮኖሚክስ ላይ ሲያተኩሩ አሜሪካ ጂኦፖለቲካዊ ትግሏን ትቀጥላለች ።" በሌላም አነጋገር ፣ ግብረአበሮቿ የየራሳቸውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እያሳደዱ ሳለ ፣ አሜሪካ ፣ እንደተለመደው ፣ በእንዱስትሪ የበለጸገውን የዓለም ክፍል ደህንነት የመጠበቁን እጅግ ከፍተኛ ወጪ ትችላለች ። ሠለጠኑ እየተባሉ የሚጠሩት አገሮች ሳዳም ኩዌትን በመውረራቸው ለአደጋ የተጋለጡ ከመሰላቸው እርሳቸውን ለመግታት ተመጣጣኝ የሰው ኃይልና ገንዘብ ማቅረብ አለባቸው ። ያለማቅረብን ከመረጡ ግን ምናልባት ስጋቱ፣ ፕሬዚዳንት ቡሽ እንደሚሉት ፣ እስከዚህ ትልቅ አይደለም ።

በፖሊሲ አውጪዎች ከሁሉም ያነሰ ግምት ቢሰጣቸውም ፣ ለአሜሪካ ጦር ኃይሎች ወደ ሰላጤው መዝመት ቢያንስ ሁለት ጠንካራና ሕጋዊ ምክንያት አለው ። የመጀመሪያው ፣ ፕሬዚዳንት ቡሽ በሳዳም ላይ የኢኮኖሚ ማዕቀብ ለመጣል ያደረጉት ሙከራ በወታደራዊ ኃይል ካልተጠናከረ ምናልባት ሊሠራ ያለመቻሉ ነው ። ቡሽ የአሜሪካን ወታደሮች ወደክልሉ ለማዝመት በቅጽበት ባይወስኑ ኖሮ ፣ ከአሜሪካ



ጋር የተሻረኩ የዓረብ አገሮች ምናልባት ሳዳምን ደፍረው እርሳቸውን ለመቃወም "ዓረባዊ አቋም" አይዙም ነበር ። ሳዑዲ ከቶም አገሯን አቋርጦ የሚያልፈውን የሳዳምን የነዳጅ ዘይት ቧንቧ ለመቁረጥ አትስማማ ነበር ። ባጭሩ ፣ ኢራቅን ያለወታደራዊ ኃይል ከኩዌት በግድ የማስወጣቱና በንድፈ ሐሳብ ደረጃ ተመራጩ መንገድ — ማዕቀብ ሳዳምን ለመግታት ፍቱን አማራጭ ሊሆን አይችልም ነበር ።

ሁለተኛውን ምክንያት ሳዳም ራሳቸው የሶቪየት ኅብረት ከልዕለ ኃያልነት ደረጃዋ ላይ መውረድ የመካከለኛውን ምሥራቅ ፖለቲካ እንደሚለውጠው በየካቲት 1982 ጠቅሰውታል ። ለዘመናት የሕዝቦችን በሙል ያርቁ የነበሩ ደንቦች ከሶቪየት ኃይል መቀነስና ከቀዝቃዛው ጦርነት ማክተም ወዲህ ተሸረዋል ። የምሥራቅ አውሮፓ ነባር መንግሥታት በ1981 ከተገረሰሱ በኋላ ፣ የዓለም በሁለት ተቃራኒ ጎራዎች መከፋፈል ማብቃትና የበለጠ የተረጋጋና ግልፍተኝነት የሚቀንስበት ሥርዓት የሚጀምርበት ዓለም መጀመሪያ እንዲሆን የአሜሪካ ተንታኞች ተስፋ አድርገው ነበር ። አሁን ግን ዕውነቱ የተገላቢጦሽ ይመስላል ። ኃያላን መንግሥታትን እርስ በርስ ተከባብረው እንዲኖሩ ያደረገው በኑክሌር ኃይል የመደምሰስ ስጋት ቀንሷል — እናም የኃያላን መንግሥታት አስታጋሽ እጅ ከጫንቃቸው ላይ ሲነሣ የቀድሞ የኃያላን መንግሥታት ደምበኞች የበለጠ ነፃነት ተሰምቷቸው በጉረቤታቸው ጉዳይ ጥልቅ ማለት ጀመሩ ።

ሁኔታው ምንም ይሁን ምን ፣ የቀዝቃዛው ጦርነት ማብቃትና የሶቪየት ኅብረት ኃያልነት መቅረት ፣ ሕዝቦች አዲስ የግንኙነት መንገድ በተጨባጭ አዲስ የዓለም ፖለቲካ ደንቦችን ይማራሉ ። አሁንም ፣ ሬይሞንድ አሮን አንድ ጊዜ እንዳሉት የጦርነት አደጋ የአገሮች ህላዌ ፣ መፈጠር ወይም እንዳልነበሩ መሆን ነው ። ሳዳም ኩዌትን እንደያዙ መቅረት ቢፈቀድላቸው ፣ በአሜሪካ አሳሳቢነት ተቀባይነት ያገኘው አጠቃላይ በዘመን ቅኝ አገዛዝ የተከለሉ ድንበሮች ተቀባይነት ማጣት መሬትን አፈፍ አድርጎ መያዝ በመላ መካከለኛው ምሥራቅና በተቀረውም የሦስተኛው ዓለም ይሠፍናል ። ዓለም አተፍ ወንጀል እንደማይክስና ሳዳም ሑሴንም ለወረራቸው ምንም ሰለባ ለማግኘት ሳይችሉ ያለምንም ሁኔታ ተገደው ከኩዌት መውጣታቸውን ማረጋገጥ የአሜሪካ ጉዳይ እንደሆነ የቡሽ መንግሥት ያምናል ። (አሜሪካ ፓናማን ወርራ

መሪዋን ከሥልጣን ለማስወገድና በምትኩ የምትፈልገውን ሰው ለማስቀመጥ ስትወስን ምንም እንዳላመነታች ዕውነት ነው) ። ደንቡ ቀጥተኛ ነው፡— ትልልቅ አገሮች ፤ በተለይም በነዳጅ ዘይት የበለጸጉ ባልሆኑ የዓለም ክፍሎች ፤ ትንንሾቹን በድንገት አፈፍ አድርገው እንዲዉጡ ሊፈቀድላቸው አይገባም ። ነገር ግን ሌሎች አገሮች በፍጥነት የተረዱት ተለቅ ያለ ጉዳይ ነበር ። ጉራ ተለዋዋጭ በሆነበት ከጊዜ ወደ ጊዜ እንደተደፈረ የመጣው ብሔራዊ ድንበር መከበር ነበረበት ።

ሣዳም ሑሴን ድል መንሣትና ድል ነሺውም ከብዙ አገሮች የተውጣጣ ጦር ኃይል መሆን እንዳለበት ፤ አሜሪካ ብቻዋን እርምጃ ብትወስድ ግን ፤ ዛሬም የዚህ ዓይነት ስሜት መቀስቀሱ ያልቀረ ቢሆንም ፤ የዓረቦችን ተቃውሞ የሚያስነሣበት መሆኑን ፕሬዚዳንት ቡሽ በደመነፍስ ተገንዝበውታል ። ነገር ግን ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ድል አድራጊዎች አንዷና እስከዛሬ ብቻዋን የቀረችው ልዕለ ኃያል አሜሪካ ብቻ የዓለምን አስተያየት ማስተባበር አዲሱን የአገሮች ግንኙነት ደንብ በመወሰን ወይም የነበሩትን ደንቦች መልሶ በማጽናት እንዲከበሩ ማስገደድ የምትችል እሷ ብቻ እንደሆነችም ቡሽ ያምኑ ነበር ።

ስለዚህ የአሜሪካ መንግሥት ክፉ ተግባርን መቃወም ፤ በበይነ ብሔር መርሁም እንደገና የዓለም ጸጥታ አስከባሪ ለመሆን መወሰኑን በምክንያት መደገፍ መርጧል ። በነዳጅ ዘይት አስፈላጊነትና በሣዳም የማያከራክር ወረራ እኳያ አሜሪካ ይህን ሚና መጫወቷ አስፈላጊ ሆኖ ይሆናል ። ነገር ግን በፕሬዚዳንት ቡሽ ንግግር ውስጥ ጉልቶ ያልታየ የመጀንን ዓይነት ነገር አለ ፤ ፕሬዚዳንቱ ከማይቀረው የታክስ ጭማሪና በከፊል የገዛ ልጃቸው እየጨመረ ትልቅ ሚና የተጫወተበት ሰፊ የገንዘብ ማወናበድ ቅሌት ያስከተለውን የኢኮኖሚ ክብደት ሕዝቡ እንዳያጤነው ቀልቡን ለመስለብ ጓጉተው ታይተዋል ። እና ደግሞ በነዳጅ ዘይት ሳይሆን በመርህ ስም ግምባራቸውን ሲቋጥሩ የቱን ያኽል የበለጠ ያረካቸው ይሆን?

ቡሽ ምንም ቢቆንኑ በግል ግጭቱ ወደዕውነተኛ ፍልሚያ ተግባር በሺ የሚቆጠሩ አሜሪካውያንን ሞት ሊያስከትል የመቻሉ ነገር እጅግ ያሳሰባቸው መሆኑን ገልጸዋል ። በዋሽንግተንና በሌላም ሥፍራ አንዳንዶች አሜሪካ ጦር ኃይል ወደክልሉ ማዝመቷ ካልቀረ ለክልሉ ሰላምና መረጋጋት ለረጅም ጊዜ ስጋት ላይ የሚጥል መስሉ የታያትን ማስወገድ



አለባት ይላሉ ። እሥራኤልና አሜሪካውያን ደጋፊዎቿ ብቻ ሳይሆኑ ብዙ አውሮፓውያንና አብዛኞቹ የሣዳም ጎረቤቶች ይህ እምነት አላቸው። የሣዳም እስከነአካቴው መወገድ በብዙ አሜሪካውያን ይደገፋል ። በከረምቱ መጨረሻ የጦርነት ፍላጐት የሚታይና የሚሰማ ነው ። እንደማይቀረውም "የነጥሎ መቺ የምድርና የአየር ጥቃት ወሬ አለ ። አንድ የኒውዮርክ ታይምስ ጋዜጣ ዘጋቢ ብዙ ጊዜ ተመላልሶ ሀኖይን በአየር ያጠቃ አሜሪካዊ አብራሪ አነጋግሮ ያገኘው መልስ እንዲህ ዓይነቱ የአየር ጥቃት" በዕውን ሊደርስ እንደማይችል" ገልጾለታል ።

ፕሬዚዳንት ቡሽ ፤ ከቀዝቃዛው ጦርነት በኋላ ላለችው ዓለም የሥነምግባር ደንብ ለማውጣት ወስነው ሲያበቁ ፤ ሣዳምን የዓለምን ነዳጅ ዘይት ከመቆጣጠርና ኃይላቸውን ወደ ሰላጤው ከማስፋፋት ለመግታት የአሜሪካንና የዓለምን የሰው ፤ የስንቅና ትጥቅ ሀብት አዝምተው ሲያበቁ ፤ አሁን ሣዳም ሑሴን ከተጠመዱበት ባላንስ የራሳቸው ፖሊሲ ያጠመዳቸው ይመስላል ። ለቀውሱ ሣዳምን ከፍተኛ ሰለባ ይዘው ከኩዌት መውጣት በማስቻል ያለጥርጥር ኢራቅ በወራሪነቷ የሚከስ ዓረባዊ መፍትሔ ለሣዳም ግልጽ ድል ይሆናል ። ይህም ማለት አዲሱን ደንብ ቡሽ ሳይሆኑ ሣዳም ደነቡ ማለት ነው ። እናም ምናልባት ሌላ ጊዜ የበለጠ ጠንክረው ፤ በልጽገውና የኑክሌር ባለቤት ሲሆኑ ጎረቤቶቻቸው ፤ በመጨረሻም ዓለም ከእርሳቸው ውጊያ የሚገጥሟቸው ይመስላል ማለት ነው ።

ሪፐብሊካዊውን ስትራተጂስት ኬቨን ፊሊፕስን የመሳሰሉ ጥቂት ተንታኞች ቡሽ ከግባቸው ቢደርሱ እንኳ ፤ አሜሪካ ከእንግዲህ የተለመደውን የዓለም ጸጥታ አስከባሪነት ሚናዋን የምትጫወትበት ሀብት እንደሌላት የአሜሪካ ሕዝብ መረዳት እንደሚገባው አስጠንቅቀዋል ። በአሜሪካ ፤ በኮሪያና በቬየትናም ጦርነት ወቅት ሌሎች አገሮች የገንዘብ እርዳታ እንዲያደርጉላት አልተማጸነችም ። ነገር ግን በዚህ ቀውስ ውስጥ አሜሪካ ተቀጣሪ ልዕለ ኃያል ሆነች ። የአሜሪካ መንግሥት ምክር ቤት አባሉ ሴናተር ዳንኤል ፓትሪክ ሞይኒሀን ይህን "ዓረቦች የራሳቸውን ውጊያ እንድንዋጋላቸው የቀጠሩን እስኪመስል በአደገኛ ሁኔታ ተጠጋን" ሲሉ ገልጸውታል ።

ቀደም ሲል የጠቀስናቸው ኬቨን ፊሊፕስም በተጨማሪ እንዳሉት አሜሪካ ብቸኛዋ ቀሪ ልዕለ ኃያል ብትሆንም በእንፃሩም በዓለም እንደ

እርሷ በእዳ የተዘፈቀ አገር እንደሌለ የሸማችነት አባካኝነቷ (consume-rism) አርባ ዓመት በዓለም ወደር የለሽ የነበረውን ኢኮኖሚ በመጨረሻ ያዳከመበት በመንገዳገድ ላይ ያለች የኢኮኖሚ ኃያል አገር ናት ። እኒሁ የተጠቀሱት ፊሊፕስ ፣ በበኩላቸው ፣ የሰላጤውን ቀውስ "(ቢያንስ በይፋ) አሜሪካ በኢኮኖሚክስ በተለይ በነዳጅ ዘይት የተነሣ ከተቃ የተዋጋችበት የመጀመሪያ ጦርነት ነው" ብለውታል ። ይህ ከሞላ ጐደል ቀኝ ገዢዎች ውድ የተፈጥሮ ሀብትንና የንግድ መሥመሮችን ለመቆጣጠር ያካሄዱበት ወደነበረው ወደዓሥራ ዘጠነኛው ምእት ዓመት እንደመመለስ ነው ። ተጠቃሹ ፊሊፕስ እንደሚሉት ከሆነ "የአሜሪካ እጅ በመካከለኛው ምሥራቅ መግባት በወታደራዊ ድል ካበቃ ለቀውሱ ተጠያቂው ሳዳም ሑሴን ይሆናሉ ። ነገር ግን ከኢኮኖሚያዊ አመለካከት አኳያ አሜሪካ በሰላጤው ወታደራዊ ኃይል ማስገባቷ ዘመን እይሽሬውን ከደረጃው እየወረደ ያለ ልዕለ ኃያልነት የትናንት ክብሩን ይዞ ለመቆየት እዳ በመግባት አጉል ተጠንራርቶ ግቡን የሳተበት ይመስላል ።" ፊሊፕስ ከዚህም ሌላ "የአሜሪካ ችሎታዎች ፈተና የላቀው ይሆናል ፡ ምክንያቱም እርሱ ፣ ልክ ስፖኝ በ16ኛው ምእታዓመት ግድም ወይም ብሪታንያ በ19ኛው ምእታዓመት ግድም እንደነበረችው ሁሉ የአያሌ ስትራተጂያዊ ግዴታ (ወይም ኃላፊነት) ተረኛ ነውና ።... አሜሪካ አሁን ፣ የቀደምት ኃያላን መንግሥታት እንዣሥና አወዳደቅ የታሪክ ምሁራን በደምብ እንደሚያውቁት ፣ ከሞላ ጐደል ልክ እንደሞፈር ዘመት በገጸ ምድር (የቅኝ ግዛት) ይዞታ ከልክ በላይ መስፋት ሊያስከትል እንደሚችለው እንደቁማር ለውድቀት ሊዳርጋት ይችላል ።" በማለት የሰነዘሩት አስተውሎት ፖል ኬኔዲ "The Rise and Fall of the Great Powers"(የኃያላን መንግሥታት እንዣሥና አወዳደቅ) በተሰኘው መጽሐፋቸው ላይ ያሠፈሩትን ያስተጋባል ።

ግን በመስከረም 1983 እንዚህ ቃላት ምንም ያኽል ስሜት አይሰጡ ወይም አያስተጋቡም ነበር ። አብዛኛውን አሜሪካዊ ፣ ልክ እንደ ፕሬዚዳንቱ ፣ ኃይሉን ለማሳየትና ከፍተኛ እርምጃ የሚወስድበት ጊዜ ናፍቆት ነበር ። ኢራቅን ከኩዌት ለማስወጣት በባሕረ ሰላጤው የሚከፈተው ድንገተኛ ጥቃት አሜሪካ በእጭር የገናናነት ዘመኗ ጀምበር መጥለቂያ ወቅት ከምትመፈጽማቸው የመጨረሻ ጀብዱዎች አንዱ ነው፣



የሚለው አስተሳሰብ ለአብዛኞቹ አሜሪካውያን ዝምታን ያስመርጣቸዋል። ሆኖም ግን ምናልባት ይህ የሰላጤው ቀውስ ጭብጦችን እንድትተው በለ አሜሪካን ማስገደድ ይጀምራል ፣ ስለራቢኗ ስለግዜ ያላትን ለረጅም ጊዜ ከፋኛ አቅጣጫ ያሳታትን ዕውይነት እርግፍ አድርጋ እንድትተው ያስገድዳት ይሆናል ። በሰላጤው ምንም ይሁን ምን ፣ ያንን ሐሳብ አሜሪካ በዜጐቿ ከባድ መከራ ታስተላልፈዋለች ።

የመካከለኛው ምሥራቅ የዓረብ አገሮች ወሰን በብዛት የተከለለው ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በብሪታንያና በፈረንሳይ ነበር ። በክልሉ የነበሩትን የዑስማናውያን አገር ግዛቶች እንዲያካልሉ የፈቀደላቸው የመንግሥታቱ ማኀበር ነበር ። በሶርያና በሊባኖስ ፣ ፈረንሳይ ሬፐብሊኮች ለመመሥረት ሞከረች ። በዮርዳኖስና በኢራቅ ውስጥ ብሪታንያ የዘውድ አገዛዝ መሥርታ ዓረቦች በቱርክ ላይ ያካሄዱትን አመፅ የመራውን የሀሽማይት ቤተሰብ አባላት በዙፋን ላይ አስቀመጠች። በግብጽ ፣ በማእከላዊ ዓረቢያና በኩዌት የለንደኑ መንግሥት ለረጅም ጊዜ ወዳጄ የነበሩ ሌሎች ባህላዊ መሪዎችን ደገፈ ። እንነዚህ አገሮች ሁሉ አሁን ሙሉ በሙሉ ነፃ ናቸው ፣ ግን በአገዛዙ ረገድ ከዲሞክራሲ አሠራር ይልቅ ኃይል ወይም ወግ አጥባቂ ተስዕኖ (ኢነርሺያ) ወሳኝ ባሕርያት ሆነው ተገኝተዋል ። በዚህም ሆነ በዚያ ደረጃ አብዛኞቹ ዐምባገነን እንደሆኑ ቆይተዋል ።







፲፪

# የባሕረ ሰላጤው ጦርነት



















፲፪

— ሀ —

## የባሕረሰላጤው ጦርነት "የበረሃ ጋሻ ዘመቻ"

ሣዳም ሑሴን እስከ ጥር 7/1983 ድረስ የጦር ኃይላቸውን ከኩዌት በፈቃዳቸው እንዲያስወጡ የጊዜ ገደብ ሰጥቶ ይህን ባያደርጉ ግን ዓለም በኅብረት እንዲወጋቸው የጸጥታ ጥበቃው ምክር ቤት ኅዳር 20/1983 በመወሰን አስጠንቀቃቸው ። ከዚህ በኋላ የአሜሪካና የኅብረ ብሔሩ ጦር ኃይሎች ለየብስ ፣ ለባሕርና ለአየር ጦርነት ዝግጅታቸውን ጀመሩ — ፖለቲከኞችና ዲፕሎማቶች ገለል ብለው ወታደሮችና ጦር መሣሪያ ዎች ተተኩ ።

የአሜሪካና የኅብረብሔሩ ጦር ኃይሎች በአብዛኛው የከተቱት በሳዑዲ ዓረቢያ ውስጥ ነበር ። በርካታ ስንቅና ትጥቅ ፣ እንዲሁም ተዋጊና የጭነት ማመላለሻ አውሮፕላኖችና ሄሊኮፕተሮች ወደዚያው ጎረፉ ። የተለያየ የጦርና የጭነት ማጓጓዣ መርከቦች ወደባሕረሰላጤውና ወደ አካባቢው ባሕር ገቡ ። የመካከለኛውን ምሥራቅ ዓረብ አገሮች ጨምሮ ከአሜሪካ ጐን ለጦርነት የተሰለፉት አገሮች 28 ሲሆኑ ፣ የሣዳምን እቋም የደገፉ ደግሞ ፣ የመን ፣ ሱዳን ፣ ሊቢያ ፣ አልጄሪያ ፣ የፍልስጥኤም ነፃ አውጪ ድርጅት ፣ ኩባና ቻይና ናቸው ። እሥራኤል ግን ፣ በአሜሪካ የሚመራውን ፣ እንደሰንቀላል በጥንቃቄ መያዝ ያለበትን ፣ የኅብረት ኃይሉን ላለመበታተን በጦርነቱ ውስጥ እንዳትገባ በፕሬዚዳንት ቡሽ መስተዳድር ተጠይቃለች ።

በአውሮፓ የነበረው የአሜሪካ የምድር ጦር ኃይል ሳዑዲ ዓረቢያ በመግባት ለእግረኛ ጦር ውጊያ ዝግጅቱን ቀጠለ ። በተለይ የምድር ውጊያ ዘመቻውን ለመጀመር የጦር ልምምድና የውጊያ ብቃት መሰና ዶው በአጣዳፊ ተጧጧፈ ።

በኋይት ሀውስ ባለሥልጣኖች አባባል መሠረት የምድር ውጊያ እንዲጀመር ፕሬዚዳንት ቡሽ ትእዛዝ የሚሰጡበት ጊዜ ገና ነበር ። ነገር ግን ፣ በዚህ የመጀመሪያው ፣ የበረሃው ጋሻ ዘመቻ (እፕሬሽን ዴዘርት



ሺልድ) ከተቱ ተፋፋመ ። ለምድር ጦርነቱ መጀመር ግን እንዳችም የፖለቲካ ግፊት አልነበረም ፣ የነበረው ግፊት ፣ በጠቅላላ የጦርነቱ መጀመር እንዲቆይ ነበር ።

## ለፖለቲካዊ ድል

የሣዳም ጦር ኃይል በማጥቃት ስልት የተካነ አይደለም ፣ በመከላ ከል ውጊያ ግን ፣ በዓለም ከታወቁት መካከል አንዱ ነው ፣ ለዚህም የስድስት ወር ዝግጅት ወስዶበታል ። በተቀበረ ፈንጂ ፣ በዘረ ታንክና በተጠናከረ ምሽግ በመጠቀም በቆራጥነት እንደሚዋጋ ተጠብቆ ነበር ። ሆኖም ይህ ስልቱ ዘመን ያለፈበት ፣ በአንደኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ የተሠራበት ነው ። የአሜሪካ የጦር እቅድ አውጭዎች በመርዛማ ጋዝ ይዋጋል የሚል ግምት ነበራቸው ።

የሣዳም ዕቅድ ብዙ የኢራቅ ወታደሮችን መሥዋዕት በማድረግ የአሜሪካን በርካታ ወታደሮች ለማስጨረስና ይህንንም የአሜሪካ ሕዝብ ሊታገስ የማይችል ስለሚሆን የፖለቲካ ድል ያስገኛል የሚል ነበር ።

የኢራቅ ውጊያ እያጠቁ መከላከልንና ፈንጂ መቅበርን ፣ መሰናክል ጉድጓዶችንና ቦዮችን መቆፈርንና በግምባር ጠንካራ ምሽግ መገንባትን የሚያጠቃልል ሲሆን ፣ ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎችንና ተዘዋዋሪ ከባድ መሣሪያዎችን በማጥመድ ፣ የአሜሪካና የኅብረብሔሩ ወታደሮች ወደ መኻል እንዲገቡ በማፈግፈግ ፣ ከቦ ለመጨፍጨፍ የታቀደ ነበር ። እንደዚህ በማድረግ በ1972 እ.ጋማሽ ላይ ከኢራን ጋር በአደረጉት ጦርነት፣ —ከእሥራኤል ፣ ከብሪታንያና እንዲያውም ከሁሉም በላይ ከታወቀው ከሶቪየት ኅብረት ብረት ለበስ ክፍለ ጦር በላይም ከፍተኛ ውጤት አስመዝግበዋል ።

ዳሩ ግን አብዛኛው የኢራቅ ወታደሮች በተጠቀሰው ስልት ልምድ አልነበራቸውም ። በሳዑዲ ሰሜን ድንበር ላይ የተሰለፉት በዚህ ያልሠለጠኑ ጠረፍ ጠባቂ ወታደሮች ነበሩ ። በግንባር ቀደም የተሠለፉት የኅብረ ብሔሩን ጦር ኃይል ወጥመድ ውስጥ ለማስገባት ወደኋላ እያፈገፈጉ እንዲዋጉ ፣ ወይም ደግሞ ፣ ለጥይት ማብረጃ በየቆሙበት እንዲሙቱ ፣ ጥቂትም ቢሆኑ ፣ የአሜሪካ ወታደሮች እንዲገደሉ ሕይወታቸ

ውን እንዲሰጡ የተደረጉ ነበሩ ። በአጭሩ አንድ የአሜሪካ ወታደር እንዳለው ፣ በግንባር የተሰለፉት የኢራቅ ወታደሮች ውሻን ለመጥራት ወይንም ለማባባል እንደሚባለው ፣ "የውሻ ሥጋ" ነበሩ ። እንደ እትዱማ እነሱ የጥይት እራት እየሆኑ የአሜሪካን ወታደሮች እያታለሉ ዒላማ ውስጥ እንዲገቡ የሚያደርጉ ነበሩ ።

አንድ የዋሽንግተን የመከላከያ ጉዳይ አማካሪ ድርጅት እንዳለው ፣ — በደጀንነት የተሰለፈው የኢራቅ ብረት ለበስና ሜካናይዝድ እግረኛ ክፍለ ጦር ፣ የተሻሉ ወታደሮችን የያዘ ነበር ። በሣዳም እቅድ መሠረት በተጠባባቂነት የሚገኘው የሪፐብሊኩ ዘብ (ሪፐብሊካን ጋርድ) በጣም የሠለጠነና እጅግ ሲበዛ ብሔረተኛ የጦር ኃይል ነው ።

በአሜሪካ ወታደራዊ ኮሌጅ ጥናት መሠረት ፣ በ1980 ዓ.ም ከተፈጸመው የኢራቅና የኢራን ጦርነት ለመገንዘብ እንደተቻለው ፣ በምዕራቡ ዓለም የጦር ስልት ከሆነ ፣ ተጠባባቂ ጦር ኃይል ድልን ለማግኘት ተጨማሪ ኃይል ሆኖ ይዋጋል ፣ ወይም መልሶ ለማጥቃት ይዘምታል ፣ የኢራቁ ግን ፣ ከዚህ ይለያል ፣ የሚጠባበቀው በመሸነፍ ላይ ያለን የጦር ኃይል ለማዳን ወይንም ወጥመድ ውስጥ የገባውን የጠላት ጦር ኃይል ከቦ ለመጨፍጨፍ ብቻ ነበር ።

## የጦር መሣሪያ

የኢራቅ ጦር ኃይል ፣ ብዙ መሰናክሎች ነበሩበት ። አንደኛው የአየር ከለላ ያልነበረው መሆኑ ሲሆን ፣ ይህን ለማካካስ በመርዛማ ጋዝ መጠቀምን እንደ አማራጭ ማድረጉ ሌላው ነበር ። ኢራቅ በኬሚካል ጦር መሣሪያ እንደምትጠቀም በተደጋጋሚ ዝታ ነበር ። ቀድሞ በኢራን ወታደሮችና በኩርድ ብሔረሰብ አማጽያን እንዳደረገችው በኬሚካል ጦር መሣሪያ ለመጠቀም ሳታስተንትን አልቀረችም ። የሥነ ሕይወታዊ ጦር መሣሪያና ሌሎችም የበሽታ ተውሳኮች ያዘጋጀች መሆኗ ታውቋል ። በዚህ ዓይነት ጦር መሣሪያ መጠቀም የኢራቅ የተለመደ ስልት ነው ። እንዚህን ለመጠቀም የሚወስነው በሣዳም ጠቅላይ መምሪያ ጽሕፈት ቤት ነበር ። አንድ የአሜሪካ ባለሥልጣን በቅድሚያ ሲያስጠነቅቁ ፣ "ሣዳም ከተጠቁ ያለጥርጥር የኬሚካል ጦር መሣሪያ ይጠቀሙ ይሆናል ።" ብለው ነበር ።

የኢራቅ ኬሚካል ጦር መሣሪያ ቆዳን የሚያቃጥል ፣ ወደ ውስጥ ከተተነፈሰ ደግሞ ፣ ሳንባን የሚበጣጥስ የሰናፍጭ (ማስታርድ) ጋዝ



እንዲሁም የሰዎችን ነርቭ በመዝጋትና በማደንዘዝ ከመቅጽበት የሚገድል ነርቭ ጋዝ ያካትታል ። እነዚህ የኬሚካል ጦር መሣሪያዎች በጠላት ላይ የሚነዙት በተዋጊ አውሮፕላን ፣ በሄሊኮፕተርና በሚሳይል በመተኮስ ሲሆን ፣ ኢራቅ የምትንዛቸው ግን ፣ በከባድ መሣሪያ በመተኮስ ነበር ። የኢራቅ 155 ሚሊ ሜትር ሀዊትዘር እስከ 36·8 ኪሎ ሜትር ርቀት ለመተኮስ የሚችልና የስድስት የእግር ኳስ ሜዳ ያኸል አካባቢ በኃይል ለመመረዝ የሚችል ነው ። ኢራቅ በምትዋጋበት ግንባር ለመጠቀም የምትፈልገው የኬሚካል ጦር መሣሪያ ፣ ፈጥኖ በኖ የሚጠፋውን ሳሪን የሚባለውን ነው ። የሰናፍጭ ጋዝ ወይም ከባድ የነርቭ ጋዝ ለመጠቀም የምትፈልገው ከጠላት በስተጀርባ ባሉት የእዝ ጣቢያዎች ፣ ከባድ መሣሪያዎች ባሉበት ሠፈር ፣ ወይም የስንቅና ትጥቅ መጋዘን አካባቢ ፣ እንደ አየሩ ሁኔታ መርዙ ሳይጠፋ ለብዙ ጊዜ እንዲቆይ በምትፈልግበት ክልል ነበር ።

የአሜሪካና የኅብረ ብሔሩ ጦር ኃይል በመርዝ ጋዝ እንዳይጠቃ በቅድሚያ ልዩ ልዩ ጥንቃቄ አድርጓል ። በምሥራቅ ሳዑዲ ዓረቢያ ውስጥ በሚገኘው በአንድ የአየር ኃይል ጦር ሠፈር ፣ እንደ ውሻና ድመት ሰውን ለመቅረብ በጣም የተላመደ ባሮርድ የተባለ አውራ ዶሮ ዘብ ይቆም ነበር ። ባሮርድ በሕይወት እስካለ ድረስ የአየር ኃይሉ ደኅንነት ይሰማው ነበር ። ይሁን እንጂ ስለመርዝ ጋዝ በቅድሚያ ለማስጠንቀቅ ባሮርድ አስተማማኝ አልነበረም — በኬሚካል ጦር መሣሪያ ከዶሮ ይልቅ ሰዎች በቀላሉ ሊጠቁ ይችላሉ ።

የአሜሪካና የኅብረ ብሔሩ ጦር ኃይል የመርዝ ጋዝ መከላከያ ጭምብልና የኬሚካል መከላከያ ልዩ ልብስ ነበረው ። ከዚህም ሌላ ፣ በመርፌ የሚሰጥ ፀረ ነርቭ ጋዝ አትሮፒን የተሰኘውን መድኃኒት በነፍስ ወከፍ ይይዛል ፣ ለስምንት ሰዓት ጋዙን የሚከላከል የሚዋጥ ኪኒንም ነበረው ። በመርዝ ጋዝ መጠቃቱ የማይቀር መስሎ ከታየ ኪኒኑን መዋጥ ግዴታ ነበር ። የኬሚካል ጦር መሣሪያ መጠቀም ከተጀመረ የምድር ጦርነቱን ሊያራዝመው እንደሚችል ተገምቶ ነበር ።

የሣዳም ፍላጎት ጦርነቱ እንዲራዘም ነበር ፣ ጦርነቱ ከተራዘመ ደግሞ መልክአምድር ያግዛቸዋል ። የሰውና የጭነት ማመላለሻ ካሚዮኖችንና ታንኮችን የሚያሰናክሉ በረጅሙ በአግድምና በ"ሠ" ቅርጽ

የተቆፈሩ ቦዮችና ጉድጓዶች በብዛት ነበሩት ። የኅብረት ጦር ኃይሉ እነዚህን መሰናክሎች ወደ ጐን በመተው አልፎ በመሄድ በስተምዕራብ ክፍል በኩል ብሪት ሰበስ ተሽከርካሪዎቹን አሾልኮ በማሳለፍ ፤ በደጀንነት የተሠለፈውን የሪፐብሊኩን ዘብና ሌሎቹንም ክፍለ ጦሮች ማጥቃት እንዳለበት አቅዶ ነበር ።

በአሜሪካ ወታደራዊ ግምት መሠረት አንድ ታንከኛ ክፍለ ጦር 5ሺ ቶን ጥይት ፤ 2 ሚሊዮን 119ሺ 768 ሊትር ነዳጅ ዘይት ፤ 1 ሚሊዮን ፤ 135ሺ ፤ 390 ሊትር ውሀና ለ80ሺ ሰው ለአንድ ጊዜ የሚቀርብ ምግብ ለአንድ ቀን የብርቱ ውጊያ ውሎ ይጠቀማል ። የኅብረት ኃይሉ የኢራቅን የመከላከያ ወረዳ ጥሶ ለመግባት አራት ወይም አምስት ክፍለ ጦር ተካፋይ መሆን እንዳለበት እንደሚጠበቅና በአጠቃላይ ለሠላሳ ቀን ዘመቻ 312 ሚሊዮን 824ሺ ሊትር ነዳጅ ዘይት እንደሚያስፈልገው ታውቋል ።

በባሕረ ሰላጤው ጦርነት አሜሪካዊው የጦር ኃይል አዛዥ ጄኔራል ሽዋርዝኮፍ እንዳሉት የአየር ቦምብ ድብደባው ዘጠና ከመቶ የሚሆነውን የኢራቅን ጦር ኃይል ስንቅና ትጥቅ አቅርቦት እንዲቋረጥ አድርጐታል ። የኅብረት ኃይሉ ተዋጊ ጄቶች በኤፍራጥስ ወንዝ ላይ የነበረውን ድልድይ በማፈራረሳቸው ፤ የኢራቅ ታንኮች ለማፈግፈግ አልቻሉም ። የሪፐብሊኩን ዘብ ጦር ኃይል አጣብቂኝ ውስጥ አስገብቶታል ። የኅብረት አየር ኃይሉ የክልሉን ሰማይ በቁጥጥሩ ሥር በማዋሉ ፤ የባግዳድ ተዋጊ ጄቶች ለእግረኛው ጦር ኃይላቸው የአየር ከለላ ለመስጠት አልቻሉም ። የዘመናዊው ጦርነት ዓይነተኛ ባሕርይ የየብስ ፤ የባሕርና የአየሩን ጦር ኃይል በማቀናጀት የሚደረግ ሲሆን ፤ ባግዳድ ይህን የተባበረ ጦር መምራት ተሳናቸው ። ስለዚህ ባግዳድ የአየር ቃኚ በሌለበት በጭፍን መዋጋት ነበረባቸው ። ቀደም ሲል የተደረገው ጦርነት (ድንበርን በመጣስ) አንደኛው ዓላማ ከኅብረት ጦር ኃይሉ በስተጀርባ ያለውን ሁኔታ ለማወቅ የተደረገ ብቻ ነበር ። በዚህ ዓይነት የባግዳድ ጦር ኃይል ሊያጋጥመው የሚችለው በ1959 በመካከለኛው ምሥራቅ እንደተደረገው ጦርነት ፤ እንደ ግብጽና የዮርዳኖስ ጦር ኃይል ፤ ከአየር በሚጣለው ቦምብ አፈር ድቤ መብላት ብቻ ነበር ።

ይሁን እንጂ የባግዳድ ጦር ኃይል ምሽጉ ውስጥ ገብቶ አልወጣም ካለ



በቀላሉ ለመደምሰስ አስቸጋሪ ይሆናል የሚል ስጋት ነበር ። ሆኖም ከምሽጉ እንዲወጣ ለማድረግ የኅብረት ኃይሉን ብዙ መሥዋዕትነት ሊያስከፍለው አልቻለም ። የጄኔራል ሽዋርዝኮፍ እቅድም የባግዳድ ጦር ኃይል ምሽጉን ለቆ እንዲወጣ ማስገደድና የኅብረት ጦር ኃይል ተዋጊ ጄቶችና ብሬትሰበስ ተሽከርካሪዎች በግላጭ እንዲያገኟቸው ማድረግ እንደሚሆን ተገምቶ ነበር ። የምዕራቡ ግምባር ግዙፍ ኃይል ጥቃት ወደ ባስራ መቃረቡን ለመከላከል የሪፐብሊኩን ዘብ እንዲወጣ ያደርገዋል ተብሎም ታስቦ ነበር ። አንዳንድ የአሜሪካ ወታደራዊ ተንታኞች በ1934 ጋዛላ በተባለው ቦታ ጀርመናዊው ጄኔራል ኤርዊን ሮሜል አፍሪካዊ ኮር የተሰኘ ጦሩን ወደ ብሪታንያ ክፍለ ጦር መከላከያ ወረዳ መኻል እንዲገቡ በማድረግ በብሪታንያ ጦር ኃይል የተቀበረውን ፈንጂ ለፊት ወራሪውና ለደጀን ጦር ኃይሉ መከላከያ በማድረግ በጀብዱ የተሞላ ድል እንደገና ጄኔራል ሽዋርዝኮፍ ይደግሙታል ብለው ገምተው ነበር ። ቢደግሙትም ኖሮ ፤ "የበረሃው ተኩላ" በመባል እንዲታወቁ ባያደርጋቸውም ፤ ከአየር የቦምብ ድብደባ የተረፈውን የባግዳድን የጦር ኃይል ለመደምሰስ ያደረጉት ዘመቻ ለባሕረሰላጤው ጦርነት ውጤት ወሳኝነት ነበረው ።

በሌላ በኩል ከኩዌት እየወጣ ወደ አገሩ የሚሸሸውን የኢራቅ ጦር ኃይል መውጫ ለማሳጣት የኅብረ ብሔሩ ጦር ኃይል ከሳውዲ ዓረቢያ በብዙ አቅጣጫ ወደሰሜን ምዕራብ በመዝመት የኩዌትን ምዕራብ ድንበር ለመዝጋት እንደሚሞክርም ተገምቶ ነበር ፤ የዚህም ውጊያ አሰላለፍ ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ ፤ በምሥራቅ ኩዌት ባሕር ዳርቻ የአሜሪካ ባሕር ኃይል ኮር ፤ በሰሜን ምሥራቅ ሳውዲና ኩዌት ድንበር ላይ የኅብረ ብሔሩ ጦር ኃይል ፤ በሰሜን ሳውዲ ድንበር ላይ የአሜሪካ ሰባተኛ ኮርና በሰሜን ምዕራብ ሳውዲ ድንበር ላይ የአሜሪካ 18ኛ ኮር እንደሚሆን ታቅዷል ።

በዚህ በአሸዋማው በረሃ ውስጥ ለጦርነት ፊት ለፊት የተፋጠጡት ኃይሎች ያሰለፉትን ታንክ በማነፃፀር እንመልከት ፤

ኢራቅ ቲ—72 የሚባል ታንክና ጂ—5 የተሰኘ ከባድ መሣሪያ ነበራት ። ቲ—72 ታንክ በበረሃ ውጊያ የተፈተነ ሶቪየት ሠራሽ ታንክ ሲሆን ኃይለኛና ዒላማውን የማይስት 125 ሚሊሜትር ከባድ መሣሪያ የተጠመደበት ነው ። ሆኖም ቶው በሚባለው ሚሳይልና ሮኪ ክላስተር

ቦምብ በቀላሉ ሊደመስስ የሚችል ነው ። ጂ—5 የሚባለው መሣሪያ ደግሞ 155 ሚ.ሊ. ሜትር ሆዊትዘር የሚባል ከባድ መሣሪያ ሲሆን ፣ በዓለም ከአሉት መሰል መሣሪያዎች ሁሉ የተሻለ መሆኑ ይታወቃል ። እስከ 36.8 ኪሎ ሜትር ርቀት ሄዶ በመምታቱ የአሜሪካን ከባድ መሣሪያዎች ሁሉ ይበልጣል ። በተጨማሪም ዒላማውን ከሌሎቹ ይበልጥ አስተካክሎ በመምታት የታወቀ ነው ።

የኅብረት ኃይሉ ያሰለፈው ኤም—1 ኤብራምስና ኤም—2ብራድሌይ የሚባሉትን የታንክ አይነቶች ነው ። ኤም—1 ኤብራምስ እንደዑልዶዘር የሚባሉትን... ሆኖ የተሠራ ታንክ ነው ። ኤም—1ኤ1 የአሜሪካ ዋና ታንክ ፊትለፊት በመቅደም የተቀበረ ፈንጂ ይጠርጋል ። ይህ ታንክ ከቲ—72 ይበልጥ ጠንካራ የሆነ ከባድ መሣሪያ የተጠመደበትና እጅግ በጣም ከጠንከረ ብረት የተሠራ ነው ። ኤም—2 ብራድሌይ ደግሞ ፣ ግዙፍ ብረት ለበስ ታንክ ሲሆን ፣ "ለእግረኛ ተዋጊ የሚያገለግል ተሽከርካሪ" ነው ። በአንድ ጊዜ ሰባት ወታደሮችና የጦር መሣሪያቸውን መጫን ይችላል ። ከዚህም ሌላ ፣ ከቀላል ብረት የተሠሩትን ተሽከርካሪዎችና ታንኮች ይደመስሳል ።

በተጨማሪም ፣ ሁለቱም ወገኖች ልዩ ልዩ ፀረ ሰውና ፀረ ታንክ ተቀባሪ ፈንጂዎች ነበሯቸው ። ከዚህም ውስጥ የኅብረት ኃይሉ ኤም—16 ኤ1 እና ኤም—21 የሚባሉ ሁለት የታወቁ በመሬት ውስጥ የሚቀበሩ የፈንጂ ዓይነቶች ነበሩት ። ኤም—16ኤ1 የሚባለው ፀረ ሰው ፈንጂ ሲሆን፣ ሜትሩን ከብደት በተጫነው ጊዜ ሲፈነዳ ፣ ከውስጡ የሚበታተነው ስለታም ቁርጥራጭ ብረት የሰውን አካል ቆራርጦ ይጥላል ፣ ወይም ይገድላል ። ኤም—21 የተባለው ደግሞ ፀረ ታንክ ተቀባሪ ፈንጂ ነው ። የማቀጣጠያው ብረት ሜፍ ከብደት ሲያርፍበት በመፈንዳት ዝርግ ግህን የሚያክል ብረት በማፈናጠር ታንክ ይቀረድዳል ። እንዲሁም ቢቲ የተሰኘው ፀረሰው ተቀባሪ ፈንጂ ሲፈነዳ 6 ሜትር ወደ ላይ በመጓን በሚያፈናጥረው ስለታም ቁርጥራጭ ብረት ዙሪያውን በ8ጠና ሜትር ርቀት ላይ የሚገኘውን ሰው ይገድላል ። አንዳንድ በቀላል ግፊት የሚፈነዱ ፀረ ታንክ ፈጣን ፈንጂዎች ደግሞ ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎችን በመበሳሳት እየተቀጣጠለ የሚፈነዳ የቀለጠ ብረት ይረጫሉ ።



## ወረዳውን ለመያዝ

በመሬት ውስጥ በተቀበሩ ልዩ ልዩና በርካታ ፈንጂዎች የታጠረ ውን "የማዳምን የመከላከያ ወረዳ" ወይም በኅብረት ኃይላት አባባል "የማዳምን መሥመር" ጥሶ ለመግባት በቅድሚያ ፈንጂዎቹን ለመጠራ ረግ ልዩ ጥበብ አስፈልጓል ። በዚህ ተግባር የተካነው የጦር ኃይል ክፍል መሐንዲስ ክፍለ ጦር ይባላል ። ይህም የተቀበረ ፈንጂ ጠራጊ መሐንዲስ ክፍል ምንም እንኳ ለአደጋ የተጋለጠ ቢሆንም የተቀበረ ፈንጂን በማስወገድ ረገድ በተለያየ ዘዴ የሠለጠነ ነው ።

"የማዳም መሥመር" ተብሎ የሚጠራው የውጊያ ግንባር ፣ በማዕከላዊ አውሮፓ ፣ በአንደኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ የነበረውን አደገኛ ጦር ግንባር ያስታውሰናል ፦ የአሸዋ ዕርዱ ፣ ረጅም የቦይ ቁፋሮ ሥራው ፣ የታንክ ማጥመጃ ጉድጓዱ ፣ ባለ እሾህ የሽቦ አጥሩና ፈንጂ የተቀበረበት ሜዳው የተዘረጋው ፣ ከባሕረሰላጤው ጀምሮ የሳዑዲ–ኩዌትን ድንበር ተከትሎ በመሄድ እስከ ኢራቅ ዘልቆ ይገባል ። በዚህ አስቸጋሪ ቦታ ውስጥ የሚገቡ ተዋጊዎች ለመውጣት ሲግቡን ወደ "ግድያው ቀጠና" ከመግባትና በኢራቅ ወታደሮች የተኩስ ዒላማ ውስጥ ከመግባት በስተቀር መውጫ አልነበራቸውም ።

በዚህ በማንም ባልተያዘው መሬት ላይ በመጀመሪያ የሚያልፈው የኅብረት ኃይላት ታንከኛ ወይም እግረኛ ክፍለ ጦር እንደማይሆን ፣ "የማዳምን የመከላከያ መሥመር" ጥሶ የመግባቱ ሥራ የአሜሪካና የብሪታንያ ፈንጂ ጠራጊ ተዋጊ መሐንዲስ ድርሻ መሆኑ ታውቋል ። ከባሕረ ሰላጤው የባሕር ዳርቻ ጀምሮ እስከ ኢራቅ በተዘረጋው ሰፊና አስፈሪ "የማዳም ሑሴን የመከላከያ ወረዳ" ላይ የተቀበረውን አደገኛ ፈንጂ በመጠራረግና ጥሶ በመግባት ከፍተኛ ሚና አላቸው ። እግረኛ ወታደሮችና ብረት ለበስ ክፍለ ጦሮች እያጠቁ ወደፊት ከመግፋታቸው በፊት ፣ መሐንዲሶቹ በልዩ ታንክ እየታገዙ በተቆፈሩ ቦዮች ውስጥ አንድ ላይ የተጠፈሩ የፕላስቲክ ቧምቧዎችን በመሙላት ጊዜያዊ የመሸጋገሪያ ድልድዮችን በመሥራት የታንከና የእግረኛ ወታደር ማለፊያ መንገድ ያመቻቻሉ ። እንዲሁም አንዳንድ ትልቅና ሰፊ ቦዮችን በታንክ ላይ የተጫኑትን የብረት ድልድዮች በመዘርጋት በቀላሉ ለመሻገር እንዲቻል

ያደርጋሉ ። ሌሎች ከባድ ተሽከርካሪዎች ደግሞ የአሸዋ ቁልሎችን በመደልደል ፣ አሸዋውን ከተቀበረ ፈንጂ ነፃ በማድረግ መንገዱን ይከፍታሉ ። ከዚህም ሌላ ፣ መሐንዲሶቹ በፈጣን ፈንጂዎች የተሞሉ የአትክልት ማጠጫ ፕላስቲክ ቱቦዎች በሮኬት እያውለበለቡ ወደፊት በመወንጨፍ በመሬት ውስጥ የተቀበሩ ፈንጂዎች እንዲፈነዱና ባለእሾክ የሽቦ አጥሮችን እንዲበጣጠሱ በማድረግ 12 ሜትር ካሬ ያኸል ስፋት ያለው መንገድ ይጠርጋሉ ። ኤም—9 ኤስ የተባለው ጠንካራ ብረት ለበስ ቡልዶዘር ደግሞ 12 ሜ.ሜ ከፍታ ያለውን የአሸዋ ቁልል ዕርድ በመቦደስ ቀዳዳ ይከፍታል ። ከዚህም ጋር ከፍልሚያው በስተጀርባ የኅብረት ኃይላት ተዋጊ ጀቶች "ሪፐብሊካን ጋርድ" የተባለውን የኢራቅ ጦር ኃይል ምሽግ በመደብደብ ምሽጉን ያስለቅቁታል ።

ይህ ሁሉ የሚከናወነው ተኩስ ተከፍቶ ጦርነት በመካሄድ ላይ ሳለ ነው ። በዚህ ጊዜ ከኢራቅ ጦር ኃይሎች ጋር ፊት ለፊት ተፋጠው የሚጋፈጡት ሦስት የጦር ክፍሎች ፣ ፈንጂ ጠራጊ መሐንዲስ ፣ እግረኛና ብረት ለበስ ነበሩ ። የጦር ኃይሎች ወታደራዊ ግብ ለመምታት የመሐንዲስነትን ተግባር አስፈላጊነት ከተገነዘቡት ቆይቷል ። እሶርያውያን በምሽግ ዙሪያ ለመከላከያ የሚሞሉ የውሃ ቦዮችን ለመሻገር በአየር በተሞላ የእንስሳት ቆዳ በመንሳፈፍ ተጠቅመዋል ። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ለወሳኙ ፍልሚያ (ዲ—ደይ) ለመንደርደሪያ በኖርማንዲ ምድር ለመቆናጠጥ የአሜሪካ ፈንጂ ጠራጊዎች የጀርመኖችን የተቀበሩ ፈንጂዎች መሰናክል ለመሻገር ቤቶችን በማፈራረስ ፣ ቤቶቹ በነበሩበት ቦታ ላይ አልፈዋል ። በጥቅምት 1975ቱ ጦርነት በግብጽ ተዋጊ መሐንዲሶች ወደ ምሥራቅ ስዊዝ ቦይ ዳርቻ ጥሶ ለመዝለት በእሳት አደጋ መከላከያ ተሽከርካሪ ውሃ በመርጨት ተጠቅመዋል ።

የምድር ውጊያው ዘመቻ ከመጀመሩ በፊት ግዙፍ የመሐንዲስነት ተግባር ተከናውኗል ። ቦምብ ጣይ ተዋጊ ጀቶች እያንዳንዱን የኢራቅ መከላከያ ወረዳ በመደብደብ ከፈንጂ እንዲጸዳ አድርገዋል ፣ ሆኖም አብዛኛው ድብደባቸው የሚያተኩረው በደጀንነት በተሰለፈው ከባድ መሣሪያና ታንክ ላይ ነበር ። በአሜሪካ ጦር መመሪያ መሠረት ፣ ብዙ ብረት ለበስ ክፍለ ጦሮች በማሰለፍ ፣ መብረቃዊ በሆነ ፍጥነት ጥሶ መግባት አንዱ እርምጃ ሲሆን ፣ መሰናክሎችን በፍጥነትና በትክክል ለማስወገድ ደግሞ የተዋጊ መሐንዲስ ተግባር ወሳኝ ነበር ። ፍጥነቱና



ትክክለኛነቱ ቢበላሽ ኖሮ ፣ የኢራቅ ከባድ መሣሪያ ተኳሾች ዘግተው ስለሚይዙ የሚሞተው ወታደር ብዛት ይጨምር ነበር ።

የኅብረት ኃይላት ጦር ዘመቻ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በብዛት የተደገፈ ቢሆንም የተዋጊ መሐንዲስን ተግባር ሊያስቀረው የማይችል ጉዳይ ነበር ። የብረት መንሽ ያላቸው ታንኮች ፈንጂን ለመጥረግ የበረሃውን አሸዋ ያበራዩታል ፣ 165—ሚሊ ሜትር ከባድ መሣሪያ የተየመደባቸው የብሪታንያና የአሜሪካ ታንኮች የኢራቅን ጠንካራ ምሽግ ምንቅርቅሩን ያወጡታል፣ አሜሪካ ሠራሹ ታንክ ከ3ሺ ሜ.ሜ ርቀት ላይ ሆኖ በኮንክሪት የተሠራውን ጠንካራ ምሽግ ሰባት ኢንች ስፋት ይሸነቁረል ፣ ሌላው ብረት ለበስ ተሽከርካሪ ዕርዱን እየደረመሰ ሲደለድል ፣ በአየር ግፊት የሚሠራው 60 ሜ.ሜ ርዝማኔ ያለው ድልድይ ይዘረጋል ፣ ወይም የፕላስቲክ ቧምቧ እሥር በተቆፈረ ቦይ ላይ በመሙላት መሸጋገሪያ ያዘጋጃል ። የበረሃው ማዕበል አሸዋውን በማስነሣት አቧራ ፈጥሮ መሐንዲሶች በኢራቅ እንዲሙቱ ወይንም ደግሞ ፣ በጠላት የመሰናክል ጉድጓድ ላይ የተሞላው ተቀጣጣይ ፈሳሽ በሚፈጥረው ጭስ እይታን በመጋረድ ድልድይ እንዳይዘረጋ ሊያደርግ ይችላል ።

## ፈንጅ ጠረጋ

ከሁሉም ይበልጥ ተዋጊ መሐንዲሶችን ያሳሰበው ተቀባሪው ፈንጂ ነበር ። በዓለም ጦር መሣሪያ ገበያ ላይ ርካሽ ዋጋ ያላቸውን ፀረ ሰውና ፀረ ታንክ ፈንጂዎች ኢራቅ ባለፉት ጊዜያት በብዛት ስትገዛ ቆይታለች ። የኅብረት ጦር ኃይላት ባለሥልጣኖች እንደሚገምቱት በአገር ውስጥ ከተሠሩት ብዛት ካላቸው ፈንጂዎች ሌላ ጣዳም 500ሺ ፈንጂዎችን በመላው ኩዌት ማስቀበራቸው ተገልጿል ። እነዚህ ፈንጂዎች ክብደት ሲያርፍባቸው የሚፈነዱትን ቀድሞ በሶቪየት ኅብረት የተሠሩትን ፣ ከርቀት በመቆጣጠሪያ ሞገድ (በኤሌክትሮ ማግኔት) ወይም በመሬት መንቀጥቀጥ (በሴስሚክ) ሞገድ የሚፈነዱትን ዓይነቶች ሁሉ ያጨም ራሉ ።

የአሜሪካና የብሪታንያ መሐንዲሶች በሮኬት እየተወነጨፉ በመውለብለብ ሄደው የተቀበሩትን ፈንጂዎች የሚያፈነዱ ፈጣን ተቀጣጣይ ፈንጂዎች የጎረሱ የውሀ ማጠጫ የፕላስቲክ ቱቦዎች ነበሯቸው ። ተመሳሳይ የፕላስቲክ ቱቦ ፣ የብሪታንያው ሞዴል ጃይንት ቫይፐር

(ግዙፉ መርዛማ እባብ) እየተባለ የሚጠራው 12 ሜትር ወርድና 240 ሜትር ቁመት ያለውን ቦታ ከፈንጂ ነፃ ያደርጋል ። ሆኖም የብሪታንያውም ሆነ የአሜሪካው በቀላሉ የሚፈነዱ አደገኛ ከመሆናቸው ሌላ ፤ ለጠላት ተኩስ የተጋለጡ ነበሩ ።

የብሪታንያና የአሜሪካ ፈንጂ ጠራጊ መሐንዲሶች ለወር ያኸል ከባድ ሥልጠና የተሰጣቸው ሲሆን ፤ የብሪታንያ መሐንዲሶች የረጅም ጊዜ ልምድ ነበራቸው ። ከዚህም በተጨማሪ ለፈንጂ ጠረጋ የሚያገለግሉት አስፈላጊ መሣሪያዎች ነበሯቸው ። የብሪታንያው ብረት ለበስ ክፍለ ጦር ሦስት የተሟላ የመሐንዲስ ክፍለ ጦር ነበረው ። እንዲሁም የዚሁ ጦር የባሕር ኃይል ክፍል ፤ አንድ ሻለቃ መሐንዲስ ክፍል ነበረው ። አሜሪካም በበኩሏ የመሐንዲስ ተዋጊ ኃይሏን ለማጠናከር ፤ ሥልጠናቸውን ጨርሰው ከተመረቁ በኋላ በመላው ዓለም በመሠራጨት በየቦታው የተመደቡትን አሰባሰባለች ። ምናልባትም የሚካናይዝድ ተዋጊ መሐንዲስንት ተጨማሪ ሥልጠና ተሰጥቷቸው ወደ ባሕረ ሰላጤው ተልከዋል ። ያም ሆኖ ሥልጠና አንድ ነገር ሲሆን ፤ በተግባር ማዋል ደግሞ ሌላ ነገር ነው ፤ ሁለቱንም ማቀናጀት ደግሞ "የሣዳም(ን) የመከላከያ መሥመር" ፈጥኖ ለመስበር ምን ያኸል ጊዜ እንደሚወስድ ወሳኝ ነበር ።

## በየብስ ለመቆናጠጥ

በኩዌት የባሕር ዳርቻ ባለው ግንባር ደግሞ የኅብረት ኃይላት የባሕር ኃይል ጦር የየብስ ላይ ዘመቻ ለማካሄድ በከፍተኛ ዝግጅት በመጠባበቅ ላይ ነበር ። ኢራቃውያን ሳያውቁት የባሕር ኃይል ጦር በአንድ በኩል ኩዌት ውስጥ ባለው የኢራቅ ጦር ኃይል ላይ ዘመቻውን ከጀመረ ቆይቷል ። የአሜሪካ ጦር ኃይል ቡድን የኩዌትን የባሕር ዳርቻ በማሰስ ፤ ከአሸዋው መጥበትና መላላት ጀምሮ እስከተቀበረው ፈንጂ ብዛትና ዓይነት ድረስ በመቶ የሚቆጠሩ ዝርዝር ጥናቶች አካሂዷል ።

ሳተላይቶችና የስለላ አውሮፕላኖች ስለ ኢራቅ የመከላከያና መልሶ ማጥቃት ኃይል መረጃ ሰጥተዋል ። የአሜሪካ የባሕር ኃይል በጥር 1983 መጨረሻ ሳምንት ላይ 8ሺ የአሜሪካ ባሕረኞች አማን ምድር ላይ በማረፍ የጦር ልምምድ አድርገዋል ። ከዜና አዳኝ ጋዜጠኛ ዓይን ውጭ የባሕር ኃይሉ የሚያርፍበት ቦታ ተመርጦ ዘመቻው ሊጀመርባቸው የሚችሉ ቀናት ጭምር ተይዘው ነበር ።



የዘመቻው ተልዕኮ ወታደራዊ ተግባር ምንድን ነበር ? ዓላማው በጠበቀ ምስጢር የተያዘ ነበር ። ነገር ግን ፤ በባሕረሰላጤው ውስጥ 40 የሚሆኑ የባሕር ኃይል ጦር መርከቦች የየብስ ዘመቻ ለመጀመር ተዘጋጅተው ነበር ። ይህም ኃይል በ1942 ኮሪያ ውስጥ ኢንቺዮን ከተወረረች ወዲህ የመጀመሪያው ግዙፍ ኃይል ነበር ። ዓላማውም ኩዌት ውስጥ ያለውን የኢራቅ ተከላካይ ኃይል በስተሰሜን ለሚያጠቃው የኅብረት ኃይላት ጦር የታንክ ድጋፍ ለመስጠት የሚደረግ ጥረት መስሎ ታይቷል ። ሌላው ግቡ በደቡባዊ ኩዌት ውስጥ ከኢራቅ መከላከያ ወረዳ ግንባር በስተጀርባ ወታደሮችን ለማሥፈርና ምናልባትም የኩዌትን ከተማ እንደገና ለመውሰድ ዓላማ ሊኖረው እንደሚችል ተገምቶ ነበር።

ሳዳም ሑሴን ሁለቱንም ነገሮች ይሆናሉ ብለው ገምተዋል ። በዚህም ከሁለቱ በአንዱ ዕቅዳቸው መሠረት ሰባት ሚሊዮን በርሜል ነዳጅ ዘይት በማፍሰሳቸው ወደግራ የሚዞረው የሞገድ ሽክርክሪት ነዳጅ ዘይቱን የብስ ላይ ለማረፍ ወደሚያሳልፈው የባሕር በር አመጣው ።

በአሜሪካዊው አዛዥ በጀኔራል ሽዋርዝኮፍ አባባል መሠረት ከባሕረ ሰላጤው በመውጣት በየብስ ላይ በመቆናጠጥ ለማጥቃት መንደርደር ፤ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኖርማንዲና በፓሲፊክ ውቅያኖስ ደሴቶች ላይ ለማድረግ ከተሞከረው ይበልጥ አደገኛ ነበር ። ዘመቻው መጀመር ያለበት ጊዜ ሌሊት ሆኖ ፤ እንቅስቃሴውም ፈጣንና ድንገተኛ መሆን ነበረበት ። ከባሕር ወተቶ የብስ ላይ የማጥቃቱ ርምጃ ዓይነተኛ ባሕርይ ከባሕር ዳርቻው 40 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ከሚገኘው ከተዋጊ ጀት ተሸካሚ ጦር መርከብ በመነሣት ከጠላት የባሕር ዳርቻ የመከላከያ የወረዳ በስተጀርባ በቦምብ ጣይ ጀቶችና ሄሊኮፕተሮች በፍጥነት ማጥቃት ሲሆን ፤ ዋናው የማጥቂያው መንሻ ከባሕር ነበር ። ከባሕር ተነሥቶ በየብስ ላይ ጥቃት ለመሠንዘር የሚደረገው የአየር ከበባ ሁለት ዙር ሂደት አለው ፦ የመጀመሪያ ዙር ከባሕር ዳርቻው በሚገኘው የብስ ላይ ለመቆናጠጥ ሲሆን ፤ ሁለተኛው ደግሞ ለመጠናከር ኃይል መጨመር ነበር ። በየብስ ላይ እርፎ መሰባሰብና ጠላትን መልሶ የማጥቃቱ ርምጃ መውሰድ ያለበት ጊዜ በ በዛ 90ደቂቃ መሆን ነበረበት ።

ሳዳም ግን ፤ ይሆናል ብለው ግምት የነበረባቸው ፤ ከሁሉም በፊት፣ በወረራ የያዙት የኩዌት ባሕር ዳርቻ የመከላከያ ወረዳቸው ከአየርና ከባሕር በመደጋገም እንደሚደበደብ ፤ ከዚያም በአሜሪካ ጦር መርከቦች

ላይ ከባድ ጉዳት ያደርሳል ፣ ብለው ተስፋ የጣሉበት "ሲልክ ዎርም" የተባለው ሚሳይል መወንጨፊያ ቦታዎች በኤፍ — 14 ፣ ኤ — 6ና ኤፍ/ኤ — 18 ተዋጊ ጀቶች ከለላ ሥር ፣ ከጀት ተሸካሚ ጦር መርከብ በሚተኮስ ከባድ መሣሪያ እንደሚመቱ ነበር ። ከዚህ ሌላ በባሕር ዳርቻው የነበረ ከባድ መሳሪያቸው ሁሉ እንደሚደመሰስና እንዲሁም የኅብረት ኃይላቱ ባሕር ወለድ ጦር በየብስ ላይ ለማረፍ እንዲችል ፣ ኢራቅ ለመከላከል ያላትን ኃይል ሽባ ለማድረግ ፣ ከምድር ጦር ሰፈር በመነሣት ቢ — 52 ቦምብ ጣይ አውሮፕላኖች ተካፋይ እንደሚሆኑ ፣ በተጨማሪም የአውሮፕላኖችን እንቅስቃሴ የሚጠቁመውና የሚቆጣጠረው መሣሪያ (ራዳር) ወይም የመገናኛ ማእከሎችን ለመደምሰስ ከተፈለገ ኤፍ — 117ኤ፣ ስቴልት ተዋጊዎችን ወዲያውኑ መጠቀም እንደሚቻል ሁሉ ግዳም መገንዘብ ነበረባቸው ።

ከዚህ ቀጥሎ በባሕረ ሰላጤው ውስጥ ከአሉት የአሜሪካ ጦር መርከቦች ሌላው የመቅጣት ዙር ተከትሏል ። ከታጠቁት ጦር መሣሪያዎች መካከል ፣ ቶማሀውክ ክሩዝ ሚሳይል ሌላ ፣ ዩ.ኤስ.ኤስ. ሚዙሪና ዊስኮንሲን የተባሉት የጦር መርከቦች በ36.8 ኪሎ ሜትር ርቀት መምታት የሚችል ፣ 16 ኢንች ከባድ መሣሪያ ይገኝበታል ፣ ይህም የባሕር ዳርቻውን አካባቢ በመደብደብ ፣ ለባሕር ወለዱ ጦር ማረፊያ ስፍራ ቦታ ከፍቷል ። ከዚህም በላይ ፣ ከጦር መርከቦቹ የሚነሡት ጀቶች ከጦር መርከቦች የከባድ መሣሪያ ተኩስ በታች በመብረር ፣ የኢራቅ ጦር ኃይል የሚገኝበትን ፣ የባሕር ዳርቻውን መሥመር ተከትሎ በስተጀርባ ያለውን ቦታ ይደብድበዋል ። ከዚህም ጋር የባሕር ወለዱ ኤ-2ሲ ሀውክ የተባለው በቅድሚያ የሚያስጠንቅቀው አውሮፕላን ኤክሶሴት ሚሳይል የሚነ ሚራጅ ኤፍ-1 የተባሉት የኢራቅ ተዋጊ ጀቶች መምጣታቸውን ለማየት ሰማዩን በመቃኘት ይቆጣጠር ነበር ።

በመጨረሻም ፣ ባሕር ወለዶች ይመጣሉ ፣ የዚህ ቀዳሚ አጥቂ ክፍል አካል አንዱ የጦር መሣሪያ የሚያወርዱ 21 አየር ላይ የሚቆሙ አውሮፕላኖች ሲሆኑ በ50 ሥፍራዎች ላይ ጦር መሣሪያ ያወርዳሉ ። አንዱ አውሮፕላን ለምድር ውጊያ የሚያገለግሉ መሠረታዊ የሆኑ እስከ ሦስት መኪና ወይም ቀላል ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎች ይጭናል ። ሌላው ቢቀር ጎሥር ሜግ ስፋት ባለው ቦታ እንኳ በደህና ያወርዳቸዋል ፣ ወይንም ደግሞ ከባሕር ዳርቻው 1.6 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ባሕሩ ውስጥ ያወርዳቸዋል ።



የመጀመሪያው ባሕር ወለድ አጥቂ ጓድ እንደወረደ ሌላው ይቀጥላል ። ብዛት ያለው የሄሊኮፕተር ዓይነት ይመጣል ። ሲኤች — 46ኢ ሲ ናይት እና ሲኤች — 53ሲ — ስታሊየን ፣ እንዲሁም ሱፐር ስታሊየን የሚባሉት በተከታታይ ይመጣሉ ። በዚህ ጊዜ አንድ ሻለቃ ባሕር ወለድ ጦር በባሕር ዳርቻው የብስ ላይ ወርዶ በመቆናጠጥ ፣ በደቂቃ ውስጥ ወደ ዋናው መሬት በመንደርደር 8 ኪሎ ሜትር መያዝ ይችላል ። 20 ሚሊ ሜትር ልዩ ከባድ መሣሪያ የተጠመደበት ከአየር የሚተኩስ ኤ.ኤች-1ሲ ኮብራ የተባለው የባሕር ወለድ ሄሊኮፕተር ሄልፋየር እና ቶው ፀረታንክ ሚሳይል በመያዝ ፣ እንዲሁም ከባሬና ቀን የሚመጣ ተዋጊ ጀት የሚመታ ሌላ ሚሳይል በመደገን ፣ የኢራቅን አግረኛ ጦር ተኩስ ለመከላከል ይንቀሳቀሳል ።

በመጀመሪያ ከባሕር ወጥቶ የብስ ላይ የሚቆናጠጠው ባሕር ወለድ ጦር ከባድ መሣሪያ አይታጠቅም ፣ ሆኖም በኮብራ ሄሊኮፕተሮችና በሃሪየር ኤቪ — 8ቢ የአየር ከለላ ያደርግለታል ። ቀላል ነፍስ ወከፍ መሣሪያ የረጅም ርቀት ዒላማን መምታት የሚችል 81 ሚሊ ሜትር ሞርታር ግን ይይዛል ። ለአጭር ርቀትም በትከሻ ተደፎ የሚተኮስ ድራጉን ሚሳይልና ቀላል ፀረ ብረት ለበስ ተሽከርካሪ መሣሪያ ጭምር ይይዛል። እንዲሁም የኢራቅን አግረኛ ጦር የሚበትን በመደበኛው ኤም — 16ኤ2 ጠመንጃ ላይ የሚገጠም 40 ሚሊ ሜትር የቦምብ መተኮሻ ነበረው ። ከዚህም ሌላ ሁለንተናዊ የማጥቃት ስልት ለመጠቀም የሚያስችልና የምድር ውስጥ ምሽጐችን የሚያፈራርስ ትከሻ ላይ ተደፎ የሚተኮስ መሣሪያ እንደሚይዝ ታውቋል ።

ከዚህ ቀጥሎ በሁለተኛ ዙር የሚመጣው በአንድ ጊዜ ለመደምሰስ የሚያስችል ምት የሚያሳርፍ ኃይል ነው ። በዚህኛው ዙር የሚመጡት ሄሊኮፕተሮች በአየር ላይ በአንድ ቦታ ላይ ቆም ብለው ለጦር መሣሪያና ለአውሮፕላን ማረፊያ ፍራሽ ያወርዳሉ ። ከነሱም ጋር መሬት የሚያርቱ አውሮፕላኖች ይመጣሉ ። እነዚህም ወታደርና ባሕር ወለዶች ፣ እንዲሁም ኤም — 1ኤ1 ታንኮች ያራግፋሉ ። የነዚህም መምጣት ሌላ ዙር ሄሊኮፕተሮች እንደሚመጡ ያበሥራል ። እነዚህ ቀጥለው የሚመጡት ሄሊኮፕተሮች 105 ሚሊ ሜትር እና 198 ሚሊ ሜትር ሀዊትዘሮችን ይዘው ይደርሳሉ ። የኅብረት ኃይሉ የአየር ውጊያውን የበላይነት ይዞ በመቆየት የተጠናከረውን የኢራቅ ታንከኛ ጦር መልሶ ማጥቃት በመከላ

ከል ፣ ሃያ አራት ሰዓት ሙሉ ባሕር ወለድ ጦር ከባድ መሣሪያ በማስመጣትና እስከ 150 ታንኮች በማከማቸት የኢራቅን ጦር ከግራና ቀኝ ክንፍ ወይም ከበስተጀርባው ለማጥቃት የሚችል ነበር ።

ይህ ሁሉ ሆኖም ግንም ዘመቻው ያለአንዳች እንከንና ያለብዙ ጉዳት ይፈጸማል ፣ ብሎ አላመነም ። የኅብረት ኃይሉ ዕቅድ አውጭዎች ፣ ተስፋ በቆረጠው የኢራቅ ጦር ላይ እስደናቂ ውጊያ እካሂደዋል ። ሌላው ችግር ደግሞ ፣ የነዳጅ ዘይቱ ፍሳሽ ነው ። ዕቅድ አውጭዎቹ ከባሕር በመውጣት የብስ ላይ በማረፍ የሚሽከረከሩ ብረት ለበስ የወታደር ማጓጓዣዎችን ፍጥነት ይቀንሳል ፣ የሚል ስጋት አድሮባቸው ነበር ። የባሕር ወለዱ መረጃ አጠናቃሪ መኰንኖች እንደሚያምኑት የኢራቅ ጦር የኤሌክትሪክ ኃይል ሽቦ ጒትቶ በማምጣት አንዳንድ የኩዌት ባሕር ዳርቻ አካባቢዎችን ማጠሩ አልቀረም ። በተጨማሪም ፣ የኩዌትን የባሕር ዳርቻ ክልል ሁሉ ፈንጂ በመቅበር አጥሯል ። የብስ ላይ የሚያርፈውን የባሕር ወለድ ጦር መሣሪያ በፈንጂ ለመደምሰስ ዝግጁ ነበር ። ከዚህም በላይ ፣ በባሕር ዳርቻው በሺ የሚቆጠሩ የታንክ ወጥመድ ጉድጓዶችና የመከላከያ አጥሮች እንደሚኖሩ ታውቋል ። ይህ ብቻ አይደለም ፣ ከባለ እሾኹ የሽቦ አጥር ሥር ከተቀበረው የፈንጂ ንጥረ ነገር ውሕድ ጋር ፣ ነጭ ፈሳሽ ጋዝ የተሞላ በርሜል ተቀብሯል ፣ ይህም ሲፈንዳ ናፓልም እንደተባለው መርዘኛ ጋዝ በመቀጣጠል ሊሠራጭ እንደሚችል ተገምቶ ነበር ።

ይህ ሁሉ መሰናክል ከፊታቸው ቢጋረጥም ፣ ባሕር ወለዶች ሊጋፈጡት እጅግ በጣም ቸኩለው ነበር ። በመንደርደሪያነት በየብስ ላይ መቆናጠጫ ቦታ ለመያዝ የሚካሄደው ዘመቻ የተሳካ እንደሚሆን ባሕር ወለዶች አስበዋል። አንድ አሜሪካዊ የባሕር ወለድ ከፍተኛ መኰንን ሲናገር ፣ "ቤይሩት ውስጥ ከፍተኛ ጉዳት ደርሶብናል ፣ በፓናማ ደግሞ በጠላት ጦር ኃይል የበላይነት ሥር ወደቅን ፣ ስለዚህ እኛ የባሕር ወለድ አባላት ምን ማድረግ እንደምንችል — ለአሜሪካ አዲስ ትውልድ ሕዝብ ለማሳየት ዕድል ማግኘት አለብን ፣" ብለዋል ።

## ከታሪክ ልምድ

ከኮሪያ ጦርነት ወዲህ ባለው የቀዝቃዛ ጦርነትና የሰላም ጊዜ ፣ በባሕርና በምድር ጦር ኃይሎች መካከል የነበረው መራራ ክርክር ፣ "አንድ ተልእኮ ለመፈጸም የትኛው የአሜሪካ ጦር ኃይል ይሰለፍ?"



የሚል ሲሆን ፣ በዚህ የባሕረሰላጤው ጦርነት ላይ ፣ እያንዳንዱ ኃይል ተግባሩን በሚገባ እንዳከናወነ በተገኘው ውጤት ታይቷል ።

ከባሕር ወደ የብስ በመሸጋገር በባሕር ወለድ ጦር ስለሚካሄደው ጦርነት ከታሪክ የተገኘ ብዙ ልምድ አለ ። እርግጥ ድል የሚገኘው ከፍተኛ መሥዋዕትነት ከተከፈለ በኋላ ነው ። ከባሕር ወደ የብስ በመቆናጠጥ የሚደረግ ጦርነት ቀደም ብሎ የተጀመረ ቢሆንም ፣ በጣም አደገኛ እንደሆነ የታወቀ ነው ። በጣም አሳዛኝና ደም አፋሳሽ የሆነው የፓሲፊክ ውቅያኖሱና በኋላም በኮሪያ የተደረጉት ጦርነቶች ለዚህ በቂ ማስረጃዎች ናቸው ። ከታሪክ ለመማር ዝግጁ ከሆነው ኅብረተሰብ ውስጥ የአሜሪካ ወታደራዊ ኃይል አንዱ መሆኑ በግልጽ የሚታወቅ ነው ። በኅዳር 1935 በጉልበርት ደሴት ላይ ለማረፍ ሲሞከር የደረሰውን ከባድ ጉዳት የማያስታውስ ባሕር ወለድ የለም ፣ ይህንን የታሪካዊ ልምድ የሚረሳው አይኖርም ። ያን ጊዜ የነበረው የአካባቢ መረጃ ጥንቅር የተሳሳተ ስለነበር የአሜሪካ ባሕር ወለድ ጦር በደሴቲቱ ለመቆናጠጥ ሙከራ ሲያደርጉ ማዕበል ስለተነሣ ፣ ጀልባዎች ከባሕሩ ቋጥኞች ጋር እየተጋጩ ሰመጡ ፣ የጃፓን ጦር ኃይል ተኩስ ከፍቶ ባሕር ወለዱን ጦር ያለምሕረት አጨደው ። በዚህም በ76 ሰዓት ውስጥ 1ሺ 112 ባሕር ወለድ ጦር ሲሞት ፣ 2ሺ290ው ቆሰለ ። ይህም ጦርነት የባሕር ወለዱ በቅድሚያ ዝግጅት ማድረግ እንዳለበትና የአየር ከለላና ድጋፍም እንደሚያስፈልገው ትምህርት ሰጠው ፣ ለተቀረው ጦርነትም አገለገለው፣ ለባሕረ ሠላጤው ጦርነትም አገልግሎታል ።

የባሕር ወለዱ አባላት ሳዑዲ ዓረቢያ የገቡት በነሐሴ 1982 ነበር ። እንደመጡም የኢራቅን የመሬት አቀማመጥ አስመስለው በማዘጋጀት ፣ በሌሊት የሚካናይዝድ ጦር ውጊያ ልምምድ ለማድረግ ሙከራ አደረጉ ፣ ነገር ግን በጨለማው በመደናገር ሙከራው ውጤት አልባ ሆነ ። የእርምት እርምጃ ተወሰደና ሁሉም ነገር ተስተካከለ ። ከዚያ በኋላ የኢራቅን መሰናክሎች ለመበጣጠስና የኬሚካሉን ጥቃት ለመቋቋም ፣ የጨበጣ ውጊያም ጭምር ለማካሄድ በአስተማማኝ ሁኔታ ተዘጋጁ ። የመርዝ ጋዙን አይፈሩም ፣ ሥልጠናውና የመከላከያ መሣሪያው አላቸው። በአጠቃላይ በጉድጓድ ፣ በቦይና በጠንካራ ምሽግ ውጊያ ሠልጥነዋል ፣ ችግሩ ግን ቢተሰብንና የምቾት ኑሮን ትቶ ለረጅም ጊዜ በአሸዋማው ሞቃት በረሃ መቆየቱ ነበር ። በበረዶ የተሸፈኑ አረንጓዴ መስኮች ፣

ታኅላትና ሰማይ ጠቀስ ሕንፃዎች ፣ ውበት ያላቸውን አውራ መንገዶችና ሕዝባቸው ማየት ስለናፈቃቸው ጦርነቱን ትተው ጨርሰው ለመሄድ ጓጉ ። አቋራጩ ወደ ሰሜን ፣ ወደ ኩዌት መገስገስ ነበር ።

ለምድር ጦርነቱ አስፈላጊው ዝግጅት ተደርጐ ከአበቃ በኋላ ፣ በወሳኙ ጦርነት ዋዜማ ፣ ደሞዝ ከፋዮች ገንዘብ ሲሰጡ ፣ የፖስታ ቤት ሠራተኞችም ወደቤተሰብ ገንዘብ የሚላኩበትን ሀዋላ ሸጡ ። የኑክሌር ፣ የሥነ ሕይወትና የኬሚካል ጦር መሣሪያ ጥቃት መከላከያ ልብስና መሣሪያ ባለሙያዎችም ፣ ስሕተት እንዳይኖር ፣ በመከላከያ ልብሶችና መሣሪያዎች ላይ የመጨረሻውን ፍተሻ አደረጉ ። የጦርነቱ ጊዜም እየተቃረበ በመጣ ጊዜ ብዙዎቹ ባሕር ወለዶች ወደራሳቸው ወደውስጥ በማሰብ በዝምታ መዋጥ ጀመሩ ። ሐቁን በመሸፈን ፣ አደገኛ ግንባር ላይ አለመሆናቸውን በማረጋገጥ ቤተሰቦቻቸውን በማጽናናት የመጨረሻውን ደብዳቤ ጻፉ ። አንዳንዶቹም ከቤተሰባቸው የተጻፈላቸውን ደብዳቤ ፖስታ እየቀደዱ አሸዋው ላይ በመቅበር ያነብቡ ነበር ። አንድም የጦር አባል ስምና አድራሻ ፣ ወይም ስለግለታሪኩ የሚገልጽ ጽሑፍ መያዝ እንደሌለበት ተነግሯል ። ቢማረክ ለጠላት ሥነልቦናዊ ጦርነት ፍንጭ የሚሰጥ ነገር በኪሱ መኖር የለበትም ። አንዳንዶቹ የሚወዷቸውን ሰዎች ፎቶግራፍም ሆነ አድራሻ ወደቤተሰባቸው መልሰው ልከዋል ። አንዳንዶችም በጣም ውድና ብርቅ አድርገው የሚያዩትን ፎቶግራፍ ወይም ጽሑፍ ያለስምና አድራሻ ከሆነ ፣ ከነሱ መለየት እንደሌለበት ተከራክረዋል ፣ መሆን ግን አልነበረበትም — ምናልባት ሊማረኩ ይችላሉና ።

## የሣዳም ዝንኝነት

ሣዳም ሑሴን ጦርነቱን ባያሸንፉም ፣ ከባሕረ ሰላጤው ጦርነት የሚያተርፉት ነገር ቢኖር ፣ የዝናንና የአድናቆትን ቅርስ ነው ።

ኸሊድ ኻዋልዲ በምርና በኩራት መንፈስ ፣ ራሱን "የጦር ዕቅድ አውጭ" ብሎ ይጠራል ። የአየር ኃይል ፣ የእግረኛና የፈረሰኛ ጦር ኃይል አዝማችነቱን እጁን በማውለብለብ ያሳያል ። "እዚህ የኢራቅ ክፍለ ጦር አለ ፣ እዚያ ደግሞ የአሜሪካ" ካለ በኋላ ፣ "ኢንሻላህ ድሉ የሣዳም ነው" ብሎ ይናገራል ። ከዚያም በዛኸራት ማዳየን ትምህርት ቤት የልጆች መጫወቻ ቦታ ጦርነት ይጀምራል ። የጦር መሣሪያቸው ይንቀሳቀሳል፣ የአሜሪካ አውሮፕላኖች ለውጊያ ይበራሉ ፣ ትርምሱ ይቀጥላል ፣ ሚቼና



ቁስለኛው ይበዛል ፣ ውጤቱ ግን ገና ከመጀመሪያው ግልጽ ሆኗል ። የ11 ዓመቱ ኸሊድ አሸናፊውን ይወስናል ፣ እናም በዚህ በዮርዳኖስ ትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ኢራቃውያን ፈጽመው አይሸነፉም ። በአሜሪካ ወገን ሆኖ እንዲጫወት የተመረጠው የ12 ዓመቱ ሌይ መሐመድ የልቡን ሲናገር ፣ "የዕውነት ቢሆን ኖሮ ሁላችንም የምንሰለፈው ከኢራቅ ጋር ነበር ፣" ብሏል ።

ሣዳም ጦርነቱ በተከፈተ በሁለት ሳምንት ውስጥ ፣ በዓረቡ ዓለም ዝናቸው እየተስፋፋ ሄደ ። የስከድ ሚሳይላቸው እሥራኤልን መምታት ፣ በጀግንነት በኅፍረጂ የሠነዘሩት ጥቃት ከጠላቶቻቸው መኻል ሳይቀር አክብሮትን አስገኝቶላቸዋል ። ከዋሽንግተን ጐን የተሰለፉት የዓረብ አገር መሪዎች ፣ ሣዳም ለአንድ ዓላማ የተሰለፉትን የዓረብ አገሮች በመከፋፈል ለአካባቢው አገሮች ውድቀትን አምጥተዋል ሲሉ ወቅሰዋቸዋል ። አልሙሰወር የሚባለው የካይሮ ሳምንታዊ መጽሔት አዘጋጅ ፣ ማክራም መሐመድ አህመድ ፣ "ግብጻውያን ሣዳምን የሚያውቋቸው በጣም መጥፎ ሰው እንደሆኑ ፣ እንደ ምሕረት የለሽ ሀምባገነን ፣ እና ለእስላም ሕዝብ ውድቀት እንደመጡ አድርገው ነው ፣" ይላሉ ። በተጨማሪ ፣ "ብዙዎች ደግሞ ሣዳምን ያደንቃሉ ፣ ምክንያቱም 'ለሚያምኑበት ቆመዋል'" በማለት አህመድ ያስገነዝባሉ ። ከዚህ ሌላ "ኒውስዊክ" የተባለው መጽሔት ጋዜጠኛ በዚያ ፣ የጀግና ያለህ! እያለ በሚጮኸው ፣ የንግግር ሰዎች በዝተው የተግባር ሰዎች በጠፉበት አካባቢ ፣ ሣዳም በጦርነቱ ቢሞቱም ፣ ቢተርፉም ፣ ለትውልድ የሚተረው ጠቃሚው ነገር ዝናቸው እንደሆን ዘግቧል ።

ሣዳም በባሕረሰላጤው ያካሄዱት ጦርነት በእስላሙና በክሌው ዓለም መካከል የሚካሄድ ትግል አስመስለው ማቅረባቸው በብዙኃን የዓረብ ሕዝብ ዘንድ ትልቅ ግምት አስጥቷቸዋል ። በአማን ትምህርት ቤት ውስጥ ፣ ልጆች የቀልድ ጦርነት ሲጫወቱ ፣ ከስምንት ምእታመት በፊት ፣ ኢየሩሳሌምን ለማስመለስ ሳላዲን ክርስቲያኖችን ድል እንዳደረጋ ሁሉ ፣ ሣዳምም አሜሪካንና እሥራኤላውያንን ድል እንዲያደርጉ ጥሪ ያደርጋሉ ። የዮርዳኖስ ሥነ መንግሥት ሊቅ ፣ ካሚል አቡ ጃቢር ፣ "የመስቀል ጦርነት (ኢየሩሳሌምን ለመያዝ በክርስቲያንና በእስላም መካከል የተደረገ) የሚለው ቃል አፈታችን ድቅን ይላል ፣ ቦታው እኮ መካከለኛው ምሥራቅ ነው ፣ አፈታሪክና ዕውነተኛ ታሪክ መደበላለቅ

ሁልጊዜም አለ ፡" ብለዋል ።

የሣዳም ሑሴን ልባዊ መልእክት በጎረቤቶቻቸው አገሮች ብቻ አልተወሰነም ፤ ቦርንዮ በምትባለው የኢንዶኔዥያ የእስላምና ዓለም ውስጥ ፤ ጦርነቱ በተነሣ የመጀመሪያ ሁለት ሳምንት የተወለዱ 18 ኢንዶኔዥያውያን ሕፃናት ስማቸው ሣዳም ሑሴን ተብሎ ተሰይሟል ። እንዲሁም ደቡብ ሊባኖስ ውስጥ ወኔያምና ወይም ጠንካራ ጡንቸኛ የሆነ ሁሉ "ስከድ" ተብሎ ይጠራል ። መንግሥት ገለልተኛ ሆኖ ለመታየት በሚሞክርባት በዮርዳኖስ ውስጥ ፤ ብዙኃኑ ሕዝብ ሣዳምን ይደግፋል ፤ ዐምባገነኑ አፈታሪካዊ ዝናን አግኝተዋል ። ጋዳ የምትባል የ11 ዓመት ልጅ ፤ "እሥራኤልን የመታውን ፤ የመጀመሪያውን ሮኬት የተኮሱት ሣዳም ራሳቸው መሆናቸውን ሰምቻለሁ ።" ብላለች ። በኻፍጂ የተካሄደው ጥቃት ፤ ከሩቅ ጊዜ ምናባዊ ዓለም ታሪክ ፤ ከዘመነ ሲንድባድ እና አላዲን ጋር ተመሳሳይነት አለው ። እንደሚተረከው ፤ የኻፍጂ ከተማ ጠባቂ ዘቦች፡ ከዕለታት አንድ ቀን ፤ ጥበቃቸውን ትተው ከሄዱበት ተይዘዋል ፤ ምክንያቱም — ከወረራው በፊት ፤ ኢራቃውያን ፤ ማታ ማታ፤ ጋባቢ የሌላቸው ግመሎች ፤ በኮርቻቸው ላይ መብራት እንጠልጥለው እየለቀቁ ፤ ድንበር ተሻግረው እንዲዘዋወሩ በማድረግ ፤ የሳውዲን ወታደሮች ፍርሀት እንዲለቁባቸው ስለአደረጉ ነው ።

እንዲሁም ሣዳም በልዩ ልዩ የመገናኛ ብዙኃን አማካይነት እንደሚታወቁት ኮከብ ተዋንያን ዓይነት ዝናን አግኝተዋል ። ስለጦርነቱ በቴሌቪዥን ያዩ የዮርዳኖስ ልጆች ፤ ጦርነቱ የአሻንጉሊት ጨዋታ ጦርነት ይመስል ፤ የሣዳምን ፎቶግራፍ ፤ ልጆቹ ከሚያመልኳቸው ጀግኖቻቸው ከነሲልቨስተር ስታሊዮኒና ከጠፈር ከዋክብት መሪ ሬልም ተዋንያን ጋር "በአማልክት ቤተመቅደሳቸው" — በአልበማቸው ውስጥ አስቀምጠዋል ። ከዚህም ሌላ ፤ የባለቤትነትን መብት ሳይጠብቁ ፤ በድብቅ ዘፈኖችን በካሴት እየገለበጡ በማባዛት ከሚሸጡት ሱቆች በአንዱ ፤ በአማን ሱቅ ፤ "የዓረቦቹ ሣዳም" የተባለው ፈጣን ጀግና አወዳሽ ዘፈን፡ ማዶና ከምትባለው ታዋቂ የአሜሪካ ዘፋኝ ካሴት ይበልጥ ተሸጧል — ብልጫው 50 ለ 1 ነበር ። እንዲሁም አልአፍጋኒ ከሚባለ ሁ የገጸ በረከት መደብር የስከድ ቁልፍ መያዣ ስንሰለትና "ቡሽ ሐሳዊ ራምቦ ነው ፤ ሣዳም ግን ዕውነተኛው ነው ፡" የሚልና ሌሎችም በደረት ላይ የሚለኩ የመታሰቢያ ጌጦች ለመግዛት ወረፋው ከመጠን በላይ ነበር።



ሆኖም እንደዚህ ዓይነቱ ጊዜያዊ ፈንጠዚያ እንደ ፋሽን ለጥቂት ጊዜ ታይቶ የሚረሳ ነው ። አሜሪካ ውስጥ የተማረ አንድ ሊባኖሳዊ ሺዓ ሲናገር ፡ "ስከድ ሚሳይሉ ቴሌቪዥን መምታቱ የሚያጽናና ቢሆንም ፤ ማወቅ ያለብን ግን ፣ ሣዳም እንዳለቀላቸው ነው ፤ አገሬቸውም አልቀላታል ፤ እሥራኤል ከዚህ ጦርነት ከምንጊዜውም ይበልጥ ጠንክራ ትወጣለች ። ሁሉም ነገር የሚደረገው በቀቢጸ ተስፋና በቁጣ እንጂ ፤ በርጋታና በማስተዋል አይደለም" ብሏል ።

ሁልጊዜ የኢራቁን ዐምባገነን ከግብጹ ጀማል አብዱል ናስር ጋር ያመሳስሏቸዋል ። ናስር የብዙኃኑን የዓረብ ሕዝብ ስሜት ከልብ የሚቀሰቅሱ የመጨረሻው መሪ ነበሩ ። ሣዳም በናስር እግር ተተክቻለሁ ቢሉ ፤ እስከ ጦርነቱ ጊዜ ድረስ የማስመሰል ፤ የዕብሪትና የጉራ ይመስል ነበር ። ናስር በንግግር ችሎታቸውና ግርማ ሞገስ ባለው ስብእናቸው ፤ የአካባቢውን ሕዝብ ወኔ ይቀሰቅሱት በነበረበት ዓይነት ፤ ሣዳምን ሲያዩዋቸው እንደበረዶ የቀዘቀዙና አፈ ጉልዳፋ መስለው ይታያሉ ። አንድ ሣዳምን በቅርብ የሚያውቋቸው የዮርዳኖሳዊ አስተያየቱን ሲሰጥ "እጅግ በጣም ጨካኝ ናቸው ፤ ከናስር ጋር አይወዳደሩም" ብሏቸዋል ። የፍልስጥኤም የታሪክ ምሁር ፤ አሚን ማሕሙድ በበኩላቸው ሲያስረዱ ፤ "ናስር ሊያሟሉት የማይችሉትን ከፍተኛ የተስፋ ቃል ይሰጣሉ ፤ በዚህም ምክንያት ብዙ ፤ ተስፋ የመቁረጥ ሁኔታዎች ነበሩ ። ሣዳም ግን ፤ እምነታቸውን በቃላት ወይም በቅኔ ላይ አልመሠረቱም ፤ በተጨባጭ ቀስ በቀስ በማሳየት ተወዳጅነትን አተረፉ ። የብዙኃኑን ሕዝብ አድናቆት ያስገኙላቸው ተግባራቸው ነው ።" በማለት ገልጸዋል ።

የዛሬው የሣዳም ዝነኛነት አርአያ — የነገው አፈታሪክ ፤ በጦርነት ጊዜ ድል ሳያገኙ ፤ ወይም በሰላሙ ጊዜ ብልጽግናን ሳያመጡ ፤ ከሃያ ዓመት በላይ በሥልጣን ላይ ለቆዩት የዓረብ አገዛዞች ፤ በቀጥታ ተፈታታኝ ሳይሆን አይቀርም ። ግብጻዊው የግራ ክንፍ ጋዜጠኛ ፤ መሐመድ ሰይድ አህመድ ሲናገሩ ፤ "ሣዳም ፕሬዚዳንት ቡሽን መቋቋማቸው ለመካከለኛው ምሥራቅ የታሪክ ሂደትን የሚያፋጥን ተግባር ነው ፤ ሣዳም በጦርነቱ እንደማያሸንፉ እናውቃለን ፤ የማናውቀው ነገር ግን ፤ የአንድ ሣዳም መወገድ ፤ ሌላ መቶ ሣዳም ይፈጥር እንደሆነ ነው ።" ብለዋል ።

እንደሌላው የዓረብ ዓለም ሁሉ ፣ የርዳኖስ ውስጥም ከሕዝቡ አርባ ከመቶ ያኸሉ ዕድሜው ከአሥራ አምስት ዓመት በታች ነው ። በእሻንጉሊት ጀቶችና ታንኮች ጦርነት ሲጫወቱ ፣ የትምህርት ቤት ጓደኞቿን እያየች ፣ የዓሥራ አንድ ዓመቷ ሪማ ስትናገር ፣ "ግዳም ቢሞቱ ፣ ግዴታቸውን የሚፈጽሙ እሳቸውን የሚመስሉ ሌሎች ብዙዎች ይና ራሉ።" ብላለች ። እሷ እንዳለችውም ፣ ገና ከአሁኑ "የጦር እቅድ አውጭዎቹ" ብቅ ብቅ እያሉ ነው ።

## የአውሮፓ መልፈስፈስ

በሌላ በኩል — በባሕረ ሰላጤው ጦርነት አሰላለፍ ላይ የአውሮፓ አገሮች ከወደመጀመሪያው ልፍስፍስነት አሳይተዋል ። የብሪታንያ ምክትል የመከላከያ ሚኒስትር አላን ክላርክ ፣ "አውሮፓ ለባሕረሰላጤው ጦርነት ተረ የሰጠችው ምላሽ ልፍስፍስ ነው ፡" በማለት መናገራቸው ተዘግቧል ። ከዚህም ጋር በማያያዝ "ለንደን ሰንደይ ታይምስ" የተባለው ጋዜጣ ፣ "በቻንስለር ሄልሙት ኮል የምትመራው ጀርመን ስለባሕረሰላ ጤው ጦርነት የሰጠችው መልስ እጅግ በጣም አሳፋሪ ነው" ሲል ፣ ጽፏል። የአውሮፓ ኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ዋና ሥራ አስኪያጅ ጃክ ዶሎር በበኩላቸው ፣ "ጦርነቱ የአውሮፓን ድክመት በግልጋሎት አጋልጧል ።" ሲሉ በመጸጸት ተናግረዋል ። እጅግ ሲበዛ የአውሮፓ አንድነት ደጋፊ የሆኑት ፣ ኢጣሊያዊው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጅያኒ ዴ ሚሸል ደግሞ ፣ "ጦርነቱ ያውሮፓን የውሕደት ሂደት ዕለት ውስንነት እንደገና አሳይቶ ናል ፡" በማለት ሽንፈታቸውን ገልጸዋል ። የአውሮፓ አገሮች ያሜሪካ ተባባሪ በመሆን ፣ በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ከአሜሪካ ጋር በሐሳብ የመለያየታቸውን ያኽል ፣ የባሕረሰላጤውን ጦርነት በሚመለከት ረገድ ደግሞ አንድ ሆነዋል ። በአጠቃላይ የአውሮፓ አገሮች ከወደ መንሻቸው ስለጦርነቱ ያሳዩት እንቅስቃሴ ፣ — በድክመት የተመላ ፣ መለያየት የበዛበትና ዋራል የሚሰብር ነበር ።

ብሪታንያ ውስጥ በሰፊት የሚነበቡ ጋዜጦች ፣ የአውሮፓ አህጉር ተባባሪ አገሮችን ፣ "ፈሪዎች ፣ ራስ ወዳዶች ፣ የግዳም ሐሴን አባባይና ተለማማጮች ፡" በማለት ወርፈዋቸዋል ። የቀርክ ፣ ፕሬዚዳንት ቁርጉት አባልም ፣ "ጀርመን የናጠጠች ከበርቴ በመሆን ስለተለሳለሰች ፣ ለመዋጋት አልቻለችም ፡" በማለት ወቅሰዋታል ።



በአውሮፓ መንግሥታት ውስጥ መፍረክረክ እንደነበር በግልጽ ታይቷል ። የፈረንሳይ ሶሻሊስት መከላከያ ሚኒስትር ዥን ፒር ሼቨንማ ፕሬዚዳንት ፍራንሷ ሚተራን ፀረ ኢራቅ ኀብረት ኃያላትን መደገፋቸውን በመቃወም ሥራቸውን በፈቃዳቸው ለቀዋል ። በባሕረሰላጤው የኢጣ ሊያ ባሕር ኃይል አዛዥ ፣ ሬር አድሚራል ማሪዮ ቡራስኪይ ፣ በተደረገባቸው ጫና ሥራቸውን ሲለቁ ፣ ለጋዜጠኞች በሰጡት ቃለ ምልልስ ፣ በዲፕሎማቲክ ጥረት በኩል ጦርነቱ ሊወገድ ይችል እንደነበር አስረድተዋል ። ስትራስቡርግ ውስጥ በተደረገው አስቸኳይ የአውሮፓ ፓርላማ ጉባዔ ፣ "የብሪታንያ ሠራተኛ ፓርቲና የጀርመን ሶሻል ዲሞክራቶች ፓርቲ ሥርዓት ተጓድሏል" በማለት ከጮኹ በኋላ ፣ ጦርነቱን ለመደገፍ የሚደረገውን ጥረት በመቃወም ድምፅ ሰተዋል ።

ለአንድ ሳምንት ያኸል መንቃቀቱ እንደቀጠለ ፣ የሕዝብ አስተያየ ትና ድጋፍ ጥናት ተካሄደ ። ብሪታንያ ውስጥ ብሔራዊ የሕዝብ አስተያየት መስጫ ባደረገው ጥናት መሠረት 84% በአሜሪካ በሚመ ራው የኅብረት ኃይል ለሚካሄደው ጦርነት ድጋፉን ሰጠ ፣ እንዲሁም በኔዘርላንድስ 84% ፣ በፈረንሳይ 66% ፣ በጀርመን 66% እና በቤልጅግ 62% የሚሆነው ሕዝብ ጦርነቱን ደገፈ ። በመጀመሪያው ሳምንት ውስጥ፡ አውሮፓ በጦርነቱ መግባት የለባትም ፣ የሚል ብዙ ሰላማዊ ሠልፍ ነበር ፣ ቀስ በቀስ ግን የሰላም ፈላጊዎች ስሜት እየቀዘቀዘ ሄደ ። አበው የሰላም እንቅስቃሴ መሪዎች ደግሞ ፣ በ1980 መጀመሪያ ላይ የአሜሪካ ኑክሌር ጦር መግሪያ በአውሮፓ ውስጥ መተከሉን በመቃወም የጀርመንና የኔዘርላንድስን መንገዶች በማጥለቅለቅ ያደረጉትን ሰላማዊ ሰልፍ በናፍቆት አስታወሱ ።

የጀርመኑ ኮል ፣ ለሳምንት ያኸል ጀርመን በጦርነቱ እንዳትገባ ከተከላከሉ በኋላ ፣ የሕዝብን ፍላጐት መከተል ጀመሩ ። ከሁሉም በፊት ፣ ጠንካራ የብልሽት ተቆጣጣሪ ኮሚቴ አቋቋሙ ፣ ቀጥለውም ሮላንድ እና ሀውክ ፀረ አውሮፕላን ሚሳይሎች ከ600 ተኳሽ ወታደሮች ጋር ወደ ደቡብ ምሥራቅ ቱርክ ለመላክ መወሰናቸውን አስታወቁ ። እንዲሁም ለጦርነቱ ያደረጉትን ወጭ ለመሸፈን ለአሜሪካ 5.5 ቢሊዮን ዶላር ፣ ለብሪታንያ ደግሞ 535 ሚሊዮን ዶላር ለመስጠት ቃል ገቡ ። በተጨማ ሪም ፣ የጀርመን ውጪ ጉዳይ ሚኒስትር ሀንስ ዲትሪሽ ጌንሸር ቴልአቪቭን ጐብኝተው ከተመለሱ በኋላ ፣ ለእሥራኤል 700 ሚሊዮን ዶላር ፣

ወታደራዊና ሰብአዊ እርዳታ እንደሚሰጡ አስታወቁ ። ኮል ለጀርመን ፓርላማ (ቡንደስታግ) ባሰሙት ረጅም ዲስኩር ፣ ለሳምንት ያኸል ግልጽ ስላልነበረው ፣ ጀርመን በባሕረሰላጤው ስላላት ድርሻ በማብራራት ፣ የናቶ አባሏን ቱርክን ጨምሮ ፣ ኢራቅ ተባባሪ አገሮችን ከአጠቃች አጸፋውን እንደምትመልስ ገለጹ ።

ሚተራን በበኩላቸው ፣ ፈረንሳይ አስተማማኝ ተባባሪ አገር መሆኗን በመግለጽ ቀደም ሲል የነበረውን የውጪ ገጽታዋን ለወጡ ። የውጪ ጉዳይ ሚኒስትራቸውን የሸቨንማን ሥራ መልቀቅ በመቀበል ፣ በፓርቲያቸው ውስጥ ካሉት ግራ ክንፍ ሰላም ፈላጊ ወገኖች ራሳቸውን አራቁ ። እንዲሁም ተዋጊ ጀቶቻቸው ፣ በአሜሪካ እዝ ሥር ፣ በውጊያው ተካፋይ በመሆን ፣ በኢራቅ ሳይሆን ፣ ኩዌት ውስጥ ያሉትን ዒላማዎች ብቻ እንዲመቱ ፈቀዱ ። ዳሩ ግን ፣ ከጊዜ በኋላ ኢራቅን እንዳይመቱ ያቀረቡትን ሐሳብ እርግፍ አድርገው ተዉ ። የፈረንሳይ ብቸኛ ዲፕሎማሲ ብዙ ትችት ቢያስከትልም ፣ ጦርነቱ የዲፕሎማቲክ መፍትሔ እንዲያገኝ መሞከራቸውን አላቋረጡም ።

እያንዳንዱ የአውሮፓ አገር ፣ ብሔራዊ ጥቅሙን ለማስከበር ፣ ድብቅ ዓላማና ፍላጐት እንዳለው በጦርነቱ መጋለጡ አልቀረም ፣ እያንዳንዱ የአውሮፓ አገር የራሱ የውጪ ፖሊስ አጀንዳ ነበረው ። የብሪታንያው ጠቅላይ ሚኒስትር ጆን ሜጀር የቆየውን የወግ አጥባቂውን ፓርቲ (የቶሪ) ልማድ በመከተል አገራቸውን በቀጥታ ከአሜሪካ ጐን አሰልፈዋል ። ይህም እርምጃቸው ፣ በአገራቸው ውስጥ ከፍተኛ የሕዝብ ድጋፍ አስገኝቶላቸዋል ። የሆላንዱ (ኔዘርላንድስ) ክርስቲያን ዲሞክራቲክ ፓርቲ ጠቅላይ ሚኒስትር ፣ ሩድ ሉበርስ የጆን ሜጀርን ፈለግ በመከተላቸው ጥሩ ውጤት አግኝተውበታል ። ስፓኝ ፣ ኢጣሊያና ፈረንሳይ ፣ ምንም እንኳን የኅብረት ኃይሉ አባል ቢሆኑም ፣ ከዓረብ አገሮች ጋር የነበራቸውን የቆየ መልካም ግንኙነት ለመቀጠል ፈልገው ነበር ፣ ከብሔራዊ ጥቅም አንፃር ሲታይ ግን፣ ስውር አካሄዳቸው ሁሉ ትክክለኛ ነበር ። ሁሉም በአብዛኛው በዓረብ ነዳጅ ዘይት ተጠቃሚ ናቸው ፣ እንዲሁም ሁሉም አገሮች በርካታ የዓረብ ዜጐች የሆኑ ሠራተኞች ከማስተናገዳቸው ሌላ ፣ በዓረብ አገሮች ያሉት የራሳቸው ዜጐች ደግሞ በጠላትነት እንዲታዩ አይፈልጉም ።



ጀርመን የተዋሐደቻትን የቀድሞዋን ምሥራቅ ጀርመንና መላውን ምሥራቅ አውሮፓ መልሳ በማቋቋም በርካታ ገንዘብ ወጭ በማድረግ ተግባር ላይ በመጠመዷ ፣ "ከናቶ አባል አገሮች ውጭ ፣ ወደ ባሕረሰላጤው ወታደሮቼን መላክ ሕገ መንግሥቴ አይፈቅድልኝም" የሚል የመከራከሪያ ነጥብ ከማንግቷ ሌላ ፣ ማእከላዊ ባንኳ የብድር ወለዱን ከፍ በማድረጉ መላው ተባባሪ አገሮች ፣ የተዘቀዘቀው ኢኮኖሚያችን በፍጥነት እንዳያንሰራራ ተፅእኖ ያደርግብናል ፣ በማለት በቁጣ ተነሡባት ።

ከአውሮፓ ግዙፍ ምድር ጋር በእግሯ አውራ ጣት ብቻ የምትገናኘው ቱርክ ፣ ከሁሉም ይበልጥ ከፍተኛውንና ውስብስቡን ሚና ተጫውታለች ። የአሜሪካ አውሮፕላኖች ፣ በደቡብ ቱርክ ኢንሲርሊክ ከሚገኘው የናቶ ጦር ሠፈርና ከደቡብ ምሥራቅ ቱርክ ከባትማን እየተነሡ ወደኢራቅ እንዲበሩ ፕሬዚዳንት ኦዛል ፈቅደዋል ። በዚህም ለውጥ ከምዕራብ የኢኮኖሚ እርዳታ ፣ የንግድ ፈቃድና ስድስት ቢሊዮን ዶላር የሚያወጣ የጦር መሣሪያ እንደሚያገኙ ይጠበቃል ። የአውሮፓ ኢኮኖሚ ማኅበረሰብ አባል ለመሆን ያቀረቡት ጥያቄም አወንታዊ ምላሽ እንደሚያገኝ ተስፋ አድርገዋል ። በሌላ በኩል ደግሞ ፣ የእስላሙ ክፍል ቱርክ በብዙ አቅጣጫ ድንበሯን ለዓረብ ጐረቤቶቿ ክፍት በማድረግ ጸጥ ብላ ትመለከት ነበር ፣ ለምሳሌ 50 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን የመይራ ዘይት ከቱርክ ወደ ሶርያ ተልኮ ከዚያም አብዛኛው በዮርዳኖስ በኩል ወደ ኢራቅ ገብቷል ።

በምሥራቅ አውሮፓ የኮሙኒዝም ሥርዓት ከተገረሰሰ ወዲህና ከ1984 በኋላ የአውሮፓ ኢኮኖሚ ማኅበረሰብ በነፃ ገበያ ላይ የተመሠረተ ጠንካራ ኢኮኖሚ በስፋት ለመዘርጋት የነበረው ተስፋ የአውሮፓን ፍላጐት ለውጦታል ። ከጦርነቱ አንድ ሳምንት ቀደም ብሎ ፣ የአውሮፓ ኢኮኖሚ ማኅበረሰብ አባል አገሮች ሮም ላይ በመገናኘት ፣ ምንም እንኳ ብሪታንያ ብትጠራጠርም ፣ የፖለቲካ አንድነት ፣ በውጪ ጉዳይና በመከላከያ ረገድ የጋራ ፖሊሲ ለመንደፍ አቅደው ነበር ። ይህም አውሮፓ፣ የምዕራብና የምሥራቅ ኃያላን አገሮች ፣ ሁሉም ለደኅንነታቸውና ለጸጥታቸው ኃላፊነቱን ወስደው በኃያላን መካከል አውሮፓ ተገቢ ቦታዋን ይዛ ፣ በሰላም የሚኖርበት አዲስ የዓለም ሥርዓት ይፈጠራል የሚል ተስፋ ተደርጐ ነበር ፣ ይህ ግን አልሆነም ፣ ዓሥር የአውሮፓ

ኢኮኖሚ ማኅበረሰብ አባል አገሮች ፣ ግዳም ኩዌትን ለቀው ቢወጡ ለመካከለኛው ምሥራቅ ዘላቂ ሰላም የሚያስገኝ ጉባዔ ለመጥራት ያቀረቡትን ሐሳብ ፣ ብሪታንያና ኔዘርላንድስ ውድቅ አደረጉት ። ሚተራን ለማንም ሳይናገሩ በስተመጨረሻ ጊዜ ለግዳም የሰላም እቅድ አቅርበው ስላልተቀበሏቸው ሃፍረት ላይ ወደቁ ። ስፓኝ ፣ ቤልጅግና ግሪክ ለጦርነቱ ወታደር ያቀረቡት ለይስሙላ ብቻ ነበር ።

የአውሮፓን ወታደራዊ ኃይል ፣ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ፣ አሜሪካና ካናዳን ሳይጨምር ፣ አብዛኛውን የናቶ አባል አገሮች የያዘው ፣ የምዕራብ አውሮፓ የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ መምራት ነበረበት ። ነገር ግን የኅብረት ኃይሉን የምትመራው አሜሪካ ሆነች ። ግራ ክንፍ ፖለቲከኞች እንደነ ሸቨንማ ያሉት "የኅብረት ጦር ኃይሉ በኢራቅ ላይ የመስቀል ጦርነት እንዲያካሂድ ቀሽንግተን እየመራች ነው ፣ የአሜሪካ ዓላማ ኩዌትን ነፃ ከማውጣት አልፎ ይሄዳል ፤" በማለት ተቃወሙ ።

በስተመጨረሻ ፣ የአውሮፓ መሪዎች ወደየራሳቸው ግብ ለመድረስ በሽሚያ ተሯሯጡ ። ጆን ሜጀር አውሮፓ ፣ "ለአንድነትና ለጋራ ተግባር ገና አልተዘጋጀችም" አሉ ። በካምብሪጅ ዩኒቨርሲቲ የአውሮፓ ጥናት መምህር ፣ ጂኦፈሪ ኤድዋርድስ ፣ "ሌሎች የአውሮፓ አገሮች ብሪታንያ ከአሜሪካ ጋር ያላትን የቅርብ ግንኙነት መቃወም ይችላሉ ። የብሪታንያን አቋም በመከተል የግድ መስማማት የለባቸውም ።" ሲሉ ፣ በሌላ በኩል ፣ በጉ ጉትን ብቻ የተመለከቱ ደግሞ ፣ "ይህ ሁሉ የሐሳብ ልዩነት ቢኖርም ፣ የብሪታንያና የፈረንሳይ ጦር ኃይል ከአሜሪካ ጉን በመሠለፍ በርትቶ በመዋጋት ላይ መሆኑ ኅብረቱ አለመላላቱን ያሳያል" አሉ ። እንዳሉትም በኅብረት ኃይላት መካከል የነበረው አለመግባባት የጦርነቱን ሂደት አልገታውም ፡ አውሮፓና አሜሪካ ኩዌትን ነፃ የማውጣትና የግዳምን ኃይል ሽባ የማድረግ ተመሳሳይ ፍላጉት ነበራቸው ።



፲፪

— ለ —



## የባሕረሰላጤው ጦርነት — የበረሀው ማዕበል

አስፈሪ የአየር ኃይል በኢራቅ ላይ ባካሄደው ዘመቻ የመጀመሪያውን ግምባር ከፈተ ።


### የአየር ጥቃት መጀመር

በቶምሀውክ ሚሳይል ውንጨፋ ነጉድጓዳዊ ውርጂብኝ የአሜሪካና የተባባሪዎቿ ዘመናዊ ጦርነት ሙሉ ግርማ ሞገስ ኢራቅን መገርመም ፣ መለብለብ ፣ ማቃጠልና ማጋየት ጀመረ ። የመጀመሪያው ውጤት ድንቅና አስፈሪም ነበር ። ግራ የተጋቡት የባግዳድ ተከላካዮች የምሽቱን ሰማይ ያለውጤት እያወሸዩት እያለ ፀረ ግዳም ጥምር ኃይሎች በጦር ኃይል በተበለጠው የኢራቅ የምድር ውስጥ ምሽግና የእዝ ማእከሎች ላይ በአትጣሚ አመልካች የሚመሩ መሣሪያዎቻቸውን ሰደዱባቸው ። ሁሉም ብዙ ጥረት የማይጠይቅ ፣ እንዲያውም ለማመን የሚያስቸግር መሰለ ፤— ሌላው ቢቀር ከአጥቂዎቹ መካል የመሞትና የመቁሰል አደጋው እስከዚ ሀም ሆን ፡ ብዙ ቢሊዮን ዶላር የፈጀው የጥምር ኃይሎች ከፍተኛ ቴክኖሎጂ የጦር መሣሪያ ኢላማዎችን እየነጠለ በማያዳግም ሁኔታ አደባየ ።

በዓለም ዙሪያ ፣ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የቴሌቪዥን ተመልካቾች የከፍተኛውን ቴክኖሎጂ ጥቃት ተከታተሉ ፣ ዘመቻው እየቀጠለ በሄደ ቁጥር የአሜሪካና የአውሮፓ ሕዝብ ለዘመቻው የሚሰጠው ድጋፍ እያደገ ሄደ ። በእንፃሩም ይህ ጦርነት ልክ እንደቪየትናሙ በአንድ ወቅት ይሰናከላል ፣ ወይም በእሥራኤል ላይ እየወረደ የነበረው ስከድ ሚሳይል እንዳች የተለቀ አርማጌዶን የመምጣቱ ምልክት ነው የሚል ሥጋት ማደሩ አልቀረም ። እዚህ አገራችንም ውስጥ ቢሆን "ኬኔዲ በፖላንድ ተገኘ ፣ መላእክት በቴሌስኮፕ ፎቶግራፍ ተነሡ ፤ የኖስትራ ዳሙስ ትንቢት ሊደርስ ነው ፣ ማርያም ግብፅ ውስጥ ወርዳ የጡት ካንሰር ቀዶ

## መተላለፊያ ለመክፈት

ሚሳይሎች ፀረራዳር ወይም "ሀርም" ሚሳይል የጠላትን ራዳር በዳይ (ትራንስሚተር) በማጥፋት ወደ [illegible] ይገባል ።



## ማስናከያ ፖድ፦

አውሮፕላኑ ያዘለዉ አስናካያ ፖድ [illegible] ራዳር [illegible] መጠን [illegible] የጠላትን ራዳር [illegible] ያደርጋል ።


## እብቅ (ትቢያ ቀማሚ)፦

ከአውሮፕላኑ ራዳር እንዳይታይ የአሉሚኒየም ጭራት ተዋቅ አውሮፕላኑ ከጠላት ራዳር ውስጥ እንዲንፀባረቅ ያደርጋል ።

## ልዕለቀይ ፍም፦

ከአውሮፕላኑ የሚለቀቅ ተግባር ላይ [illegible] ያለ የሙቀት ምንጭ በመፍጠር የጠላትን መተላለፊያ ሙቀት አነፍናፊ ሚሳይል ያስታል ። በዘመናዊ የአየር ውጊያ ኤሌክትሮኒክ ፀረ እርምጃ (ኢሲኤ) "[illegible] ጋር እንደ አካል" ሆኖ [illegible] የአየር [illegible] የራዳር ሚዲያ (ማስናከያ) [illegible] የአየር ኃይል አውሮፕላ[illegible] የጠላትን ራዳር [illegible] ሚሳይሎችና [illegible] "የአሰሳ መተላለፊያ" [illegible] ።
[illegible] አውሮፕላን የጠላት ራዳር






[illegible]

ሕክምና ፈጸመች ፡ …" ከሚሉት ጋር ከመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት በመጥቀስ ጦርነቱ ወደምጽአት ወይም ወደ ሦስተኛው የዓለም ጦርነት ሊያመራ ይችላል ብለው የገመቱም አልጠፉ ።


ያም ሆነ ይህ ፡ ያም ተባለ ይህ ፡ የአሜሪካ ስማርት ቦምቦች በሚያስደንቅ ትክክለኛነት በምድር ውስጥ ምሽጎች በር እየገቡ ፈንዳዱ ። ከሩቅ አውዳሚ ሮቦቶች በቀይ ባሕርና በፋርስ ባሕረሰላጤ ከሚገኙ ጦር መርከቦች እየተምዘገዘጉ ባግዳድ ወርደው የኢራቅን የመከላከያ ሚኒስቴርና የፕሬዚዳንት ሣዳምን ቤተመንግሥት ገረሰሱ ። የፀረ አውሮፕላን ተኩስና የቦምብ ፍንዳታ ትንታግ ጭለማውን ሌሊት ወገግ እያደረገው ። ወጣ ብሎም በየበረሀው የኢራቅ የአየር ኃይል በተጠናከረ መጠለያው ድምጡን አጥፍቶ ዐረፈ ። ከመኻሉ አጥቂዎቹን ለመቋቋም የተነሡትም እንድም ወዲያው ተመተው ወደቁ ፡ አልያም ፊታቸውን ወደሰሜን በማዞር ኸል ብለው አመለጡ ።

የዘመቻው ስም ጥር 10 ቀን 1983 "የበረሀው ጋሻ" መባሉ ቀርቶ "የበረሀው ማዕበል" በመሰኘት የአየር ኃይል ጦርነት ከፍተኛ ቴክኖሎጂ መሣሪያዎች ያለምንም ሳንክ በመሥራት ወደ አዲስ ምዕራፍ የተሸጋገረ መሰለ ። የፔንታጐን ምንጮች እንዳሉት የአሜሪካ ባሕር ኃይል ቶምሆውክ በጦርነት ላይ ለመዋል የመጀመሪያዋ ክሩዝ ሚሳይል ሆነች ። በመጀመሪያ ከተምዘገዘጉት 150 ቶምሆውኮች ከሰማንያ አምስት ከመቶው በላይ ኢላማቸውን መተዋል ። የአሜሪካ የምድር ጦር ፓትሪዮት ሚሳይልም በውጊያ ላይ ሌላ ሚሳይል መትቶ ለመጣል የመጀመሪያዋ ሆነች ። ኤሌክትሮኒክ ፀረ እርምጃዎችም የኢራቅን የአየር መከላከያዎች ቀለዱባቸው ። በጨረር ሥራ ፡ በልዕለ ቀይ ምሥልና በቴሌቪዥን ሥዕሉች የተመሩ በምቦችና ከአየር የተተኮሱ ሚሳይሎች ኢላማዎችን እያከታተሉ አደባዩ ።

የአየር ጦርነቱ እየቀናቸው ቢሄድም የተባበሩትን ኃይላት የመጀመሪያ ምቶች በመቻል ጉልበታቸውን ኋላ ለሚከተለው ደመሰች የምድር ውጊያ እየቆጠቡ ይሆናል የሚል ፍራቻ የአሜሪካን ባለሥልጣናት እንቅልፍ ነሥቷቸው ቆየ ።


ቡሽ ኢራቅ ያለምንም ቅድመሁኔታ ከኩዌት እንድትወጣ በማድረግ ግባቸው ላይ ቢያተኩሩም ሣዳም ነገሩን እያደፈረሱባቸው ዓርብና






ቶምሆውክ






'ስማርት' ቦምብ በግዳጁ ላይ

ስማርት ቦምብ



ቅዳሜ ከምዕራብ ኢራቅ ስከድ ሚሳይል ወደእስራኤል ተኩሱ ። ሒሳባቸው በኩዌት ላይ የሚካሄደው ጦርነት እስራኤልን ተንኩሶ ጦርነቱ ውስጥ በማስገባት ግጭቱ በዓረቦችና በእስራኤል መኻል እንዲሆን ለማድረግ ነበር ። ዳሩ ግን ቡሽ የተባበሩት ኃይላት ጦር አውሮፕላኖች የሣዳምን የስከድ ላውንቸሮች እያሰሱ መሆናቸውን በመግለጽ እስራኤልን በመማፀናቸው አፀፋ ከመተኩስ ታቀበች ።

ጦርነቱ በተጀመረ በዘጠኝ ቀን የምድር ውጊያ ለመጀመር ታቅዶ የነበረ ቢሆንም በዚያ ጊዜ ውስጥ ቢያንስ ኢራቅ 50 የስከድ ላውንቸሮች ስለቀሯትና በአካባቢው ለአየር ጥቃት የማያመች የአየር ጠባይ በመከሰቱ የምድር ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት የአየር ጥቃቱ እንዲቀጥል አስገደደ ።

ከዚህ ሌላ ዘመቻውን ከመጀመሪያው የገጠመው ምንም እክል አልነበረም ። በጦርነቱ መጀመሪያ አሜሪካና የአየር ጥቃት አጋሮቿ ብሪታንያ ፣ ፈረንሳይ ፣ ሳዑዲ ዓረቢያ ፣ ኢጣልያ ፣ ካናዳና የኩዌት ስደተኞች እድለኞች ነበሩ ። ብዙ ነገሮች ተመቻችተውላቸው ነበር ። እነዚህም ፡— አይነተኛ የአየር ጠባይ ፣ አይነተኛ የጊዜ አጋጣሚ ፣ አይነተኛ የመሬት ገጽታ ፣ አይነተኛ የኢላማ ስርጭትና አይነተኛ ጠላት ነበሩ ።

1· ዓይነተኛው የአየር ጠባይ– ጦርነቱ የተጀመረበት ሌሊት ጠፍ ጨረቃ የሆነበት የመጀመሪያ ሌሊት ከመሆኑም በላይ ሰማዩ የጠራ ነበር። ይህ ደግሞ ለተባበሩት ኃይላት ተዋጊ ቦምብ ጣዮች እና ለስማርት ቦምቦቻቸው የምሽት ማያ መሣሪያ ምቹ ሁኔታ ነበር ። የአየር ጠባዩ ለክሩዝ ሚሳይልም ዓይነተኛው ነበር ። ነገር ግን ከ36 ሰዓት በኋላ አየሩ ወደ ዳመናማነት በመለወጡ በማንኛውም የአየር ጠባይ ጥቃት ማድረስ የሚያስችል መሣሪያ ቢጠመድባቸውም ተልእኳቸውን ሳይፈጽሙ ለመመለስ የተገደዱ ተዋጊ ቦምብ ጣዮች ይገኙባቸዋል ።

2· ዓይነተኛው ጊዜ– የመጀመሪያዎቹ የአየር ጥቃቶች በጣም ውስብስብ የነበሩ ቢሆንም ጦርነቱ እስኪጀመር ድረስ በፈጀው አምስት ወር ውስጥ የተባበሩት ኃይላት አባሎች ለማቀድና ጦሩን ለማለማመድ በቂ ጊዜ ነበራቸው ። በዚህ ጊዜ ውስጥ በሳዑዲ ውስጥ የአውሮፕላን ማረፊያዎች ለመሥራት ከመቻሉም በላይ በአውሮፕላን ተሸካሚ መርከቦች ላይ



ለሚያርፉ የጦር አውሮፕላኖች የነዳጅ ማደያ ጣቢያዎች ተዘጋጅተውላቸዋል ። ይልቁንም ደግሞ በየክልሉ የተሠማራው የተባበሩት ኃይላት ጦር ኃይሎች አዛዥ ጄኔራል ኖርማን ሽዋርዝኮፍ ከጥቃት በፊት መርሀግብሩ ለክሩዝ ሚሳይል መገጠም ያለበትን የተብራራ ዲጂታል ካርታ አውርተው አስገጥመዋል ።

3· ዓይነተኛው ገጸምድር– የኢራቅና ኩዌት ገጸምድር ጫካ ወይም ደን እንደሚበዛበት ገጸምድር ሳይሆን አውላላ በመሆኑ መሣሪያን የሚመሩና በምሽት የሚያሳዩ ስልቶች ኢላማን በትክክል ሊያሳዩ የሚችሉበት ነበር። ጦርነቱ ከሌሎች ሲነፃፀር በትንሽ ክልል ለተባበሩት ኃይላት የአየር ኃይል ሠፈሮችና መነሻ ምፍራዎች ቀርበው ተገኝተዋል ።

4· ዓይነተኛው ማሳየት– ጦርነቱ በብዛት በቴሌቪዥን ጋዜጠኞችና በራሳቸው በተዋጊ ቦምብ ጣይ ጂቶቹ ተቀርጾ እየተመረጠ ለዘጋቢዎች እንዲታይ ተደርጓል ።

5· ዓይነተኛው ጠላት– ኢራቅ የምትመራው በዐምባገነን መሆኑ ታምኖበታል ። ሳዳም ስለዘመናዊ ጦርነት በቂ ግንዛቤ ያላቸው አይመስሉም ። በዐምባገነን የሚመራ ጦር ፣ ጠንካራ አስተያየትና ግላዊ ጥረት ስለማይበረታታ ፣ ብዙ ጊዜ ለአኩሪ ውጤት የሚያበቁ መኰንኖች እጦት ያጠቃዋል ። ጦርነቱም እንደተጀመረ ኢራቃውያን የትኩረት አቅጣጫን ለማሳት በእስራኤል ጥቃት ከማድረሳቸው በስተቀር የሚይዙ የሚጨብጡት ጠፍቷቸዋል ።

ማክሰኞ ጥር 7/1983 ከቀኑ 5 ሰዓት ግድም ፕሬዚዳንት ቡሽ በኋይት ሀውስ ቤተመንግሥት ዕንቁላል ቤት ቢሯቸው ከብሔራዊ ደህንነት አማካሪዎቻቸው ጋር ባካሄዱት ስብሰባ በመጨረሻው ደቂቃ ዲፕሎማሲያዊ መፍትሔ ካልተገኘ በስተቀር የአሜሪካና የተባባሪዎቿ ጦር ኃይል በኢራቅ ላይ ጦርነት እንዲከፍት የሚያዝ መመሪያ ፈረሙ ። በዚያው ዕለት ከቀትር በኋላ የመከላከያ ሚኒስትራቸው ዲክ ቼኒ መመሪያውን ተግባራዊ የሚያደርግ "የማስፈጸሚያ" ትእዛዝ ፈረሙ ።

ረቡዕ ጥር 8/1983 ቡሽና ቤከር ጥቃቱ ያን ዕለት ምሽት እንደሚከፈት ለአሜሪካ ብሔራዊ ሸንጐ መሪዎች ፣ ለተባባሪ አገሮች አምባሳደሮችና ለሌሎችም አሳወቁ ። በዚያው ዕለት እኩል ቀን ግድም ስለጥቃቱ ለቀድሞው ፕሬዚዳንት ሪቻርድ ኒክሰን ይነግሯቸዋል ። የውጪ ጉዳይ

ሚኒስትር ጄምስ ቤከርም ለአዲሱ የሶቪየት ኅብረት የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር ለአሌክሳንደር ቤስሜርትኒኽ ጦርነቱ ከመከፈቱ በፊት አንድ ሰዓት ቀደም ብለው ወደሞስኮ ደውለው ውሳኔውን ይነግሯቸዋል ። ቤስሜርትኒኽም ወዲያው ለፕሬዚዳንት ሚኻኤል ጐርባቾቭ ያሳውቋቸዋል ። ጐርባቾቭም ለፕሬዚዳንት ቡሽ በመደወል ለቀድሞ ተባባሪያቸው ለኢራቁ መሪ ከኩዌት ይወጡ ዘንድና አለበለዚያም ሊከተል ስለተቃረበው ጥቃት የሶቪየትን የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ እንዲሰጡ እድል ያገኙ ዘንድ ቡሽን ይጠይቋቸዋል ። ቡሽ ስላልተቃወሙ ጐርባቾቭ ደብዳቤ ወዲያው ጽፈው በባግዳድ የነበሩት አምባሳደራቸው ለሳዳም እንዲያደርሱ ይልካሉ ። በጣም ዘግይቷል ። አምባሳደሩ የኢራቁን ፕሬዚዳንት ማግኘት ስላልቻሉ ለውጪ ጉዳይ ሚኒስትራቸው ለጣሪቅ አዚዝ በአንድ የምድር ውስጥ ምሽግ ይሰጧቸዋል — ያውም ጦርነቱ ከተጀመረ በኋላ ።

6· በኢላማ ማነጣጠሪያ "መስቀል" ውስጥ– ጦርነቱ በተጀመረበት የመጀመሪያ ሌሊት አንዱ ስትራተጂያዊ ኢላማ የኢራቅ የአዝና የቁጥጥር ማእከል ነበር ። ይህም ባግዳድን ባገሪቱ ውስጥ ከተሠራጩ የምድር ጦር ጠቅላይ መምሪያዎችና ከአገሪቱም አራት የአየር መከላከያ ማእከሎች የሚያገናኙ የቴሌፎን መሥመሮችና የማይክሮዌቭ መገናኛዎች አውታር ነው ። ዋና ከተማዋ ራሷ ከምድር ወደ ሰማይ በሚወነጩ ሚሳይሎች (ሳም) ፣ በፀረ አውሮፕላን ከባድ መሣሪያዎችና በተዋጊ አውሮፕላኖች ትጠበቅ ነበር ። ስለዚህ የአሜሪካ የጦርነት እቅድ አውጪዎች ባግዳድ ውስጥ የሚገኘውን ዋና የቴሌኮሙኒኬሽን ሕንፃ በኤፍ–117 ስቴልት ተዋጊ በምብ ጣይ ጄቶች ማጥቃት መረጡ ። ይህ ባለማዕዘን ጄት ለዚህ ጥቃት የተመረጠው ዝግ ብሎ በመብረሩ ሳይሆን ለራዳር የማይታይ ያኽል ስለሆነ ነው ። ለጥቃቱ ከተላኩት ኤፍ–117ቶች መኻል አንዱ በሕንፃው ላይ 908 ኪሎ ግራም የሚመዝን በጨረር የተመራ ስማርት ቦምብ አስተካክሎ ጣለበት። ቦምቡ ሕንፃውን እንደመታው ከያቅጣጫው ፍርስራሹ ሲረጫጭ ከአውሮፕላኑ ላይ በቪዲዮ ቴፕ ተቀርጿል ።

ጦርነቱ በተጀመረበት ዕለት የተመቱ ሌሎች ኢላማዎች የአየር መከላከያዎችን ፣ የሚሳይል ላውንቸሮችንና የወታደሮችን ከምችት ያካትታሉ ። አንዳንድ የተባበሩት ኃይላት አውሮፕላኖች የኢራቅን



ራዳሮች አክሽፈዋል ወይም ደምስሰዋል ። የብሪታንያን ቶርኔዶዎች ጨምሮ ፣ ሌሎች የኢራቅን የአየር ማረፊያዎች ማኰብኮቢያ ምሰሶ ለጊዜው እንዳያገለግሉ አደረጓቸው ። የአሜሪካ የባሕር ኃይል ኤ–6ኢ.ዎች እና ኤፍ/ኤ–18ቶች እሥራኤልን ያሰጋውን በምዕራባዊ ኢራቅ የሚገኘውን የስከድ ሚሳይል ክልል በቦምብ ደበደቡ ። በኩዌትና በአቅራቢያዋ የሚገኙ የኢራቅ ወታደሮች ታንክ በሚያነክቱ ኤ–10 ሮችና አፓቼ ሄሊኮፕተሮች ፣ እንዲሁም በግዙፉ ቢ–52 ተጠቁ ።

እጅግ ከረቀቁ ጥቃቶች አንዳንዱ በትክክል ወደኢላማው በታለመ ነጠላ ቦምብ ወይም ሚሳይል በተጠመደበት ነጠላ ጄት ተከናወነ። ይህ መሆኑ ጄቶቹ በበዙ መጠን በሚነዙት ጩኸና በሚያስነሡት አቧራ አንዱ በሌላው አቅጣጫ አመልካች ስልት ግራ እንዳይጋባ በማለት ነው ። ሆኖም እያንዳንዱ አጥቂ ጄት ወደየኢላማው ለመድረስ የተለያየ ሚና ባላቸው አውሮፕላኖች ቡድን ታጅቦ ይበርራል። በመከላከያ የታጠረ ኢላማን ለማጥቃት በመደበኛው የአሜሪካ የውጊያ ስልት መሠረት መጀመሪያ "መከላከያ ማደናገሪያ" ኢኤፍ–111 ይላካል ። ይህም የኢራቅን የረጅም ርቀት ራዳር በማክሸፍ ከምድር ወደአየር ተምዘግዛጊ (ሳም) ሚሳይል ተኳሾች የራሳቸውን መግሪያ ራዳር እንዲጠቀሙ ያስገድዳቸዋል ። ከዚያም ኤፍ4–ጂ ዋይልድ ዊዝል ራዳሩን ሚሳይል ተኩሶ ሳሞቹ የታወሩ ያኽል እንዳይሠሩ ያደርጋቸዋል ።

ቀጥሎ ኤፍ–15 እና ኤፍ–16ን የመሳሰሉ ተዋጊ አውሮፕላኖች አጥቂ አውሮፕላኖችን ከጥቃት ለመከላከል ይነሣሉ ። በመጨረሻም እንደየግዳጁ ከስድስቱ ዓይነት አጥቂ አውሮፕላኖች የተፈለጉት ይነሣሉ። በዚህ ቡድን ውስጥ የሚሠማሩት አውሮፕላኖች ከተለያየ የአየር ኃይል ሠፈር በተለያየ ፍጥነት እየበረሩ የሚሄዱ ቢሆንም እስከ ኢላማው አብረው መብረር የለባቸውም ። ይልቅስ ፣ በተጨናነቀው የጠላት የአየር ክልል በአዋክስ (ባለራዳር) የእዝ አውሮፕላኖች ትራፊክነት በትክክል በታወቀ ሰዓት በቅደም ተከተል ኢላማው ወደሚገኝበት ሥፍራ ይደርሳሉ።

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ጦርነቱ ተጀምሮ ለ36 ሰዓት ከሞላ ጐደል ያለምንም ችግር የአየር ጥቃቱ ከተካሄደ በኋላ የአየር ጠባዩ ዳመናማ ሆነ ። በቀን እንኳ ቦምብና ሚሳይል ጭነው የተነሡ አውሮፕላ

ኖች በአየር ጠባዩ ምክንያት ጥቃት ማድረስ ተስኗቸው ተመለሱ ። በዚህ ጊዜ የአሜሪካ አውሮፕላኖች ከቱርክ እየተነሡ የሰሜን ኢራቅን ኢላማ ዎች ደበደቡ ።

ማድረስ ተስኗቸው ተመለሱ ። በዚህ ጊዜ የአሜሪካ አውሮፕላኖች ከቱርክ እየተነሡ የሰሜን ኢራቅን ኢላማዎች ደበደቡ ።

7· ከሳታላይት ተጠልሎ— ኩዌት ውስጥና በአቅራቢያዋ የተወሟ ራው የሪፐብሊኩ ዘብ ሠራዊትና ሌላ ምርጥ የምድር ጦር የአየር ጥቃቱ አዳዲስ ኢላማዎች ሆኑ ። ነገር ግን ቀደም ሲል ጀምሮ ስከድ ሚሳይሎችን ከጥቅም ውጪ ለማድረግ የነበረው ግብ አልተደረሰበትም ። የተተኰሱ የስከድ ሚሴይል ላውንቸሮች አብዛኞቹ የተደመሰሱ ቢመስልም ከተንቀ ሳቃሾቹ ላውንቸሮች አንዳንዶቹ ከዚያም በኋላ በእሥራኤል ላይ ሮኬት ለመወንጨፍ ይችሉ ነበር ። መደበኛ ወይም መርዛማ ጋዝ በስከድ ሊወነጨፍ የመቻሉ ሥጋት በዚህ ጊዜም ነበር ። እነዚህን መሣሪያዎች በሳታላይት ተከታትሎና ፈልጐ መደምሰስ እንዳይቻል በምድር ውስጥ በተቆፈሩ ምሽጐች ውስጥ ተደብቀዋል ።

በቴክኖሎጂ የላቁ ቢሆኑም የጥምር ኃይሉ ወጣት ፓይለቶች በልምድ ማነስ የተነሣ ፍርሀት ያድርባቸው ነበር ። እንደፈሩትም አልቀረ የኢራቅ የአየር መከላከያ ደካማ ቢሆንም አንዳንዱ መምታቸው አልቀ ረም ። ጦርነቱ እንደተጀመረ በሁለት ቀን ውስጥ የአሜሪካ ፥ የብሪታንያ ፥ የኢጣልያና የኩዌት አውሮፕላኖች እየተመቱ ወድቀዋል ። መጀመሪያ የጠፋው ከዩኤስኤስ ሳራቶጋ አውሮፕላን ተሸካሚ የጦር መርከብ ላይ ተነሥቶ በግዳጅ ላይ እንዳለ በሳም ሚሳይል የተመታው የአሜሪካ አውሮፕላን ኤፍ/ኤ—18 የተሰኘ የጦር አውሮፕላን ነበር ።

በከፍተኛ ቴክኖሎጂ የሚንቀሳቀሱት አውሮፕላኖች የሚጥሏቸው ቦምቦችና የሚተኩሷቸው ሚሳይሎች በሲቪሎች ላይ አደጋ ያለማድረሳ ቸው ፓይለቶቹን ያጽናናቸው ነበር ። የዘመናይ መሣሪያ ሥራ ዐዋቂዎችን ኢላማን የመምታት ብቃት መተኮሻዎቹን ትንንሽ አረር እንዲያጕርሱ አድርጓቸዋል ። ለምሳሌ ማቬሪክ ከአየር ወደ ምድር ተወንጫፊ ሚሳይል ታንክ ወይም የምድር ውስጥ ምሽግ የሚነድል ነው ። ነገር ግን በ10 ሜትር ርቀት ነው ጉዳት ማድረስ የሚችለው ። ስለዚህም ኢላማን ከአካባቢው ነጥሎ መምታት በባሕረሰላጤው ጦርነት በግዳጅ ላይ የዋለ የከፍተኛ



ቴክኖሎጂ ባሕርይ ነው ።

8· *መሣሪያው ይሠራል*— ምሳሌነት ያለው ኢላማን በቦምብ የማደባየት ተግባር እየተመረጠ በቪዲዮ ቴፕ ተሰባስቦ በባሕረሰላጤው የአሜሪካ አየር ኃይል አዛዥ በነበሩት በሌተና ጀኔራል ቻርለስ ሆርነር አማካይነት ለጋዜጠኞች ታይቷል ። አንዱ ከር ሁለት ስማርት ቦምቦች ወደ አንድ ስከድ ሚሳይል የምድር ውስጥ ማከማቻ ሲገቡ ያሳያል ፤ በሌላው ቴፕ ላይ ባግዳድ ውስጥ በኢራቅ አየር ኃይል አዛዥ ቢት መስኮት ስማርት ቦምብ ሲገባ ያሳያል ። የተባበሩት ኃይላት በኢራቅና በኩዌት ባደረሱት የአየር ጥቃት ከተተኰሰው ሚሳይልና ከተጣለው ቦምብ ኢላማውን የሳተው 20 ከመቶው ብቻ ሆነ ። ዕውነትም ከሚታመነው በላይ ዘመናዊው የከፍተኛ ቴክኖሎጂ የጦር መሣሪያ ሠርቷል ።

በተመቻቸ ሁኔታ ፤ ሰው አልባ መሣሪያ ከዚህ የበለጠ ይሠራል ። ክሩዝ ሚሳይሎች ከቦምብ ጣይ አውሮፕላኖች የበለጠ የተሳካ ጥቃት አድርሰዋል ። አቅጣጫን የሚያሳይ ዝርዝር መርሀግብር እስኪጻፍለት ጊዜ ከተገኘ ፤ ትክል ኢላማን ለመምታት ተምሀውክ ክሩዝ ሚሳይል ይመረጣል ። በዳህራን አየር ኃይል ማረፊያ ላይ የኢራቅን ስከድ በአየር ላይ ሲያጋየው እንደታየው ፓትሪየት ፀረ ሚሳይል ሚሳይልም አንጀት አርስ ነው ።

የበረሀው ማዕበል የከፍተኛ ቴክኖሎጂ ጦር መሣሪያ ኢላማን የማግኘት ችሎታ ባለፉት ጦርነቶች ሁሉ ከታየው ልቆ ተገኝቷል ። ይህም ልክ እንደቀዶ ሕክምና ኢላማ ተፈልፍሎና ተንጥሎ የሚመታበት ዘመን መቃረቡን አሳይቷል ። ከዚህም በላይ የሲቪል ሕይወትን ጥፋት በመቀነስ ፥ የንብረት ውድመትን በመወሰንና ለፈጣን ውጤት በማብቃት የኑክሌር ፡ የኬሚካል ፥ የሥነሕይወታዊና የቦሊስቲክ ሚሳይል አረር መጉረስና መተኮስ የሚችለው የስማርት ቦምብ ፍቱንነት ተፈትኖበታል።

**የአሜሪካንና የዓለም ሕዝብ ሲያስጨንቁ የቆዩ ጥያቄዎች**

1· እሥራኤል ለሚተኰሱባት ስከድ ሚሳይሎች አፀፋ በመስጠት ኢራቅን ትመታ ይሆን? ይህን ብታደርግ ጥምር ኃይሉ ምን ያኽል ይፍረከረክ ይሆን?

2· ሣዳም በጥምር ኃይሉ እየተደበደቡ ኬሚካዊና ባክቴሪዮሎጂያዊ ጦር መሣሪያ ሳይተኩሱ ምን ያኽል ይታገሱ ይሆን?

3· አሜሪካና ተባባሪዎቿ የእግረኛ ውጊያ መቼ ይጀምሩ ይሆን? ምን ያኽል መሥዋዕት ይጠይቅ ይሆን?

የጦር መሣሪያ

## ከፍተኛ ቴክኖሎጂ ሲከስ

ውድ ጦር መሣሪያ ለመጀመሪያ ጊዜ ለጦርነት ውሎ ምንነቱን አረጋገጠ ። በባሕረ ሰላጤው ጦርነት የተሳተፈውን ያኽል የጦር መርከብ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ የተሳተፈበት ጦርነት አልተካሄደም ። ጦርነቱ በኢራቅና በኩዌት ውስጥ በነበሩ ኢላማዎች ላይ ከ1ሺ በላይ የጦር አውሮፕላኖችና 100 ክሩዝ ሚሳይሎች ባደረሱት ጥቃት ተጀመረ ። በዚህም ኅብረብሔሩ ፣ የአሜሪካ ጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማጆር ሹም ጄኔራል ኮሊን ፓውል እንደገለጹት "ስለታዊ ዱብ እዳ" ነበር ። መልሱም አሜሪካ በከፍተኛ ቴክኖሎጂ የጦር መሣሪያ ያላት የበላይነት የኢራቅን የአየር መቃወሚያ እንዲታወርና እንዲሽመደመድ አደረገው ። የኤሌክትሮኒክ ጦርነት የመጨረሻ ደረጃ ታየበት ።

ከጄኔራል ኮሊን ፓውል በፊት የአሜሪካ ጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማጆር ሹም – አድሚራል ዊልያም ክሮው የኅብረብሔሩ ጦር በአስደናቂ ሁኔታ የተሳካለት መሆኑን ከተናገሩ በኋላ "መሬቱት በጣም ጠቅሞናል" ብለዋል ። ጦርነቱ በተጀመረ በ14 ሰዓት ውስጥ በተካሄደው ከ1ሺ 300 በላይ የአውሮፕላን ድብደባ አንድ የአሜሪካና አንድ የብሪታንያ አየር ኃይል አውሮፕላን ብቻ ነበር የደረሱበት ያልታወቀው ። በአሜሪካ የተመራው ኅብረብሔር ፣ የነበሩና ከዚህ በፊት ጨርሶም በጦርነት



ያልተሞከሩ አዳዲስ ዓይነት የጦር መሣሪያዎች ታጥቆ ነበር ።

ቶም ሀውክ ክሩዝ ሚሳይል ፣ ከባሕር ኃይል መርከብ የሚተኮስ ፣ ከንግድ አውሮፕላን የማይፈጥን ፣ ዲጂታል የካርታ ሥራ ቴክኖሎጂ ተጠቅሞ ከኢራቅ ራዳር እይታ ዝቅ ብሎ በመብረር አልፎ ኢላማውን በ18 ሜትር ርቀት የሚመታ ነው ። የጦር አውሮፕላኖችን በዘመቻ ወቅት ሲመራ የቆየው የአሜሪካው አየር ኃይል ኤፍ—117ኤ ስቴልት ተዋጊ ጄት ነበር ። የኢራቅ ራዳሮች ኤፍ—117ኤ ሲበር ማሳየት ቢችሉም በኢላማ ውስጥ ገብቶ እስኪነጣጠርበት ሊከታተሉት አይችሉም ። "ኤፍ—4ጂ ዋይልድ ዊዝል"ን ጨምሮ ከተዋራሪው ወገን የጦር መሣሪያዎች የሚወጣውን ሙቀትና ጢስ በማነፍነፍ ሄደው የሚነድፉ ሚሳይሎችን የታጠቁ ናቸው ። ይህም ኢራቆች ሳም (ከምድር ወደ አየር ተምዘግዛጊ) ሚሳይሎቻቸውንና አየር መቃወሚያዎቻቸውን እንዳያስተባብሩ አገደ ።

ከኤፍ—15ኢ ኢግልና ኤፍ—16 ተዋጊ ፋልከን አጥቂዎች አንዳንዶቹ ከኢራቅ አነስተኛ ካሊበር የመምታት አቅም በላይ እስከ 600 ሜትር ርቀት ላይ ሆነው የከባድ መሣሪያ ተኩስና የቦምብ ናዳ ያዘንባሉ ። እንርሱና እንደዚሁም የባሕር ኃይሉ ኤፍ/ኢ—18 ሆርኔቶች በጨረር የሚመራ ወይም ሌላ "ስማርት" ቦምብ በኢላማቸው ላይ ያራግፋሉ ።

ጦርነቱ በከፍተኛ ቴክኖሎጂ መካሄዱ ቀደም ያሉ ፣ በውጊያ የተፈተኑ የጦር መሣሪያዎችን ሁሉ ዘመን ያለፈባቸው አላደረጋቸውም ። ከአዲሱ ቴክኖሎጂ ብዙው ቀደም ላሉ አውሮፕላኖች ተገጥሞላቸዋል ። ለምሳሌም ለሠላሳ ዓመት የስትራቴጂያዊውን የአየር ኃይል እዝ ሥራ ቀጥ አድርገው ሲያከናውኑ የቆዩት ባለስምንት ሞተር ቢ—52 ቦምብ ጣይ አውሮፕላኖች ኑክሌርና መደበኛ ቦምቦች ብቻ ሳይሆን ወደ ኢላማቸው እስከ 88 ኪሎ ሜትር ያኽል ርቀት መተኮስ በሚያስችሉ ትንንሽ ጄቶች የሚመሩ ኤጂ ኤም—142ኤ ሚሳይሎችንም መሸከም ይችላሉ ። እነዚህ ትልልቅ ቦምብ ጣዮች ከሳዑዲ ዓረቢያ እየተነሡ ፣ የሣዳም ሑሴን ምርጥ የሪፐብሊኩ ዘቦች ተመሽገውባቸዋል ተብለው የታመኑ ይዞታዎችን ጨምሮ ፣ በበርካታ ኢላማዎች ላይ ሰፊ ውድመት አስከትለዋል ።

## ስከድ ሚሳይል

ስከድ ሚሳይል ከኢላማው እስከ ሁለት ኪሎ ሜትር ርቆ በመውደቅ ሊፈንዳ የሚችል ፣ ዘመን ያለፈ መሣሪያ ነው ። ከርፋፋነቱ አደጋም አለው። ይህ በቴሌአቪዥና በሀይፋ ታይቷል ። ዲዛይኑ በሶቪየቶች የተሠራው ስከድ ሚሳይል የታለመው በአጭር ርቀት የኑክሌር አረር አዝሎ እንዲያደርስ ነበር ። ፍቱንነቱ የተወሰነ ኢላማ ለመምታት ሳይሆን በትላልቅ ከተሞች ውስጥ ወድቆ በመፈንዳት ሕዝብን ለማሸበር ነው ። በኢራንና በኢራቅ ጦርነት ባግዳድና ቴህራን ወደየከተሞቻቸው ስከድ ሚሳይል ተታኩሰው በመቶ የሚቆጠሩ ሲቪሎችን ፈጅተውበታል ።

የባሕረ ሰላጤው ጦርነት ከመጀመሩ በፊት ሣዳም ሑሴን ከ500 እስከ 800 ስከድ ሚሳይልና ለዚህም ማወንጨፊያ 32 የተተከሉ ላውንቸሮችና በባለ 8 ጐማ ግዙፍ ከባድ የጭነት ካሚዮኖች ላይ የተጠመዱ ቢያንስ 36 የስከድ ሚሳይሎች ተንቀሳቃሽ ላውንቸሮች እንደነበሩቸው ተገምቷል ። በአሜሪካ የተመራው የኅብረ ብሔር አየር ኃይል የመጀመሪያውን የአየር ጥቃት በኢራቅ ይዞታዎች ላይ ካደረሰ በኋላ ከ15 ተንቀሳቃሽ ስከዶች በስተቀር ከተተከሉት መኻል የአብዛኞቹ ላውንቸሮች ተደምስሰዋል ። አንድን ስከድ ጠምዶና አቀባብሎ ለተኩስ ለማዘጋጀት አምስት ሰዓት ያኸል ይፈጃል ።

ርዝመቱ 11 ሜትር የሆነው ስከድ ሚሳይል ዲዛይን በ1930ዎቹ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማብቂያ ዋዜማ ናዚ ጀርመናች ወደለንደን ከወነጨፉት ባለውልብልቢት ቪ−2 ሮኬት የተገኘ ነው ። ኔቶ "ኤስኤስ−1ኤ ስካነር" ብሎ የሰየመው ሲሆን በምሕፃረቃልም የኮድ ስሙ "ስከድ" ተሰኘ ። ተለቅ ያለው ባለረጅም ርቀት ስከድ−ቢ ፣ "ስከድ−ኤ"ን በማሻሻል የተሠራ ነው ።

ሶቪየት ኅብረት በ1970ዎቹ መጀመሪያ ፣ ስከድ ማምረት እየተወች እምድር ለምድር ተምዘግዛጊውን የተሬቀቀ ኤስኤስ−23 ሚሳይል ወደማምረቱ እየተሸጋገረች ናት ። ሆኖም ፣ ሞስኮ ማምረቱን እያቆመች



ቢሆንም መሸጡን እንደቀጠለች በመሆኗ ደምበኛዋ ኢራቅ ርቀቱን ከ(ቦሊስቲክ) 280 ኪሎ ሜትር ድረስ የሚተኩሰውን ስከድ−ቢ ገዝታት በማሻሻል 625 ኪሎ ሜትር ርቀት የሚተኩሰውን አል ሑሴን ሞዴልና 870 ኪሎ ሜትር ርቀት የሚምዘገዘገውን አል አባስ ሞዴል አውጥታለች ።

ኢራቅ ያደረሰችባት የስከድ ጥቃት ለእሥራኤል የመጀመሪያዋ አልነበረም ። በ1965 የዓረብ — እሥራኤል ጦርነት መጨረሻ አካባቢ ግብፅ በሲና በረሃና በውጊያው ግምባር በነበሩ የእሥራኤል ኢላማዎች ላይ ሦስት ስከድ−ቢ ሚሳይል ተኩሳ ምንም ያኸል ጉዳት ሳታደርስ ቀርታለች ። የኢራቅን ከግብፁ የሚለየው ኢራቅ ኬሚካል ጦር መሣሪያ ልትተኩስበት የመቻሏ ስጋት ነበር ።


## ስኩድን በፓትሪየት












ከምርኮኝነት ማዳን፡ ለአደጋ በጣም የተጋለጠ ፡ በጣም የሚከስ

ከመንኛው ጀምር የበረሰው ማዕበል በመቻ ከምር
ኩኝነት ማዳንን ከፍተኛ ትድሚያ ሰጠው ፡
አደራረጉ እንዲህ ነው፡



1· አጥቂ ፡ … አውሮፕላን ተመቶ ፡ … ይወድቃል

3· እንግሥ

2· ከምርኮኝነት የሚያድነው ቡድን በር ይደርስለታል



## የጭለማ ቦምብ

ዱሮ የተዋጊና የቦምብ ጣይ አውሮፕላን አብራሪዎች "የቦምብ ጣይ ጨረቃ" ሲሉ በምዕራቡ ዓለም ሕዝብ ይሰሙ ነበር። ግን ያ በዛሬ ጊዜ ዝቅተኛ ቴክኖሎጂ ይባል ጀምሯል ። ዛሬ ለአየር ጥቃት ከሁሉም ይልቅ የሚመረጠው ሁኔታ ዓይን ቢያወጡ የማይታይበት ድንጉር — ጥቁር ጭለማ ነው ። ልዕለ ቀይ ነገሮችና በጨረር የሚመሩ ቦምቦች ፓይለቶችን ቡሎ በመሰለ ጽልመት ዒላማን አይቶ መምታት ያስችሏቸዋል ። የጨረቃ ብርሃን የተገላቢጦሽ አውሮፕላኖቻቸው ለአየር መቃወሚያ ተኳሾች ይበልጥ እንዲታዩ ብቻ ነው የሚረዳው ። ኢራቅና ኩዌት ውስጥ ጥር 7/1983 ከሦስት ጨረቃ አልባ ሌሊት የመጀመሪያው ነበር። አሜሪካ በኢራቅ ላይ ጦርነት መክፈት የፈለገችው በባግዳድ ጥር 8 ከቢቱ 2 ሰዓት ነበር — በአሜሪካ ግን እኩለ ሌሊት ነበር ። የሚቀጥለው ቀን ሌሊት ፖለቲካዊና የአየር ጠባይ (ሥነፈለካዊ) ሁኔታው ለጦርነት ያመቸበት ቀረብ ያለ ጊዜ ሆነ ።

በመካከለኛው ምሥራቅ ከሌሊቱ ሰባት ሰዓት ከመሙላቱ በፊት በሳዑዲ ዓረቢያ ከሚገኙ የአሜሪካ የአየር ማረፊያዎች የጦር አውሮፕላኖች እየተግሸጉደጉዱ በማኮብኮብ ሲነሡ እንደነጐድጓድ መሬቱን ሲያንቀጠቅጡት ዘጋቢዎች ሰሙ ። አውሮፕላኖቹ ወደሰሜን ወደ ኩዌትና ወደ ኢራቅ አመሩ ። በዚያው ወቅት ተጨማሪ ጀቶች በፋርስ

ባሕረሰላጤውና በቀይ ባሕር ከሚገኙ ስድስት የአሜሪካ አውሮፕላን ተሸካሚ መርከቦች እየተነሡ መክነፍ ቀጠሉ ። ወዲያውም 2ሺ ያኸል የአሜሪካ ፣ የብሪታንያ ፣ የፈረንሳይ ፣ የኢጣሊያ ፣ የካናዳ ፣ የሳውዲ ዓረቢያና በስደት ላይ የነበረው የኩዌት መንግሥታት ጦር አውሮፕላኖች በመላዋ ኢራቅና ኩዌት ዒላማዎችን ደበደቡ ። እርግጥ በተለይ የፈረንሳይ ጄቶች በኩዌትና በኢራቅ ውስጥ የነበሩ የኢራቅ አውሮፕላን ማረፊያዎችና ጦር ኃይሎች ነበር የደበደቡት ።

የውጪውም ዓለም የመጀመሪያውን ዜና ባግዳድ ውስጥ ከረሺድ ሆቴል የቴሌቪዥን ጋዜጠኞች የአየር ጥቃት ማስጠንቀቂያ ጥሩምባ መስማታቸውን ፣ አየር መቃወሚያ አብሪ ጥይት ሲተኮስ ጭለማውን ሰማይ ወገግ ሲያደርግ ማየታቸውን በመግለጻቸው ሰሙ ። ለተወሰነ ጊዜ ምንም የቦምብ ፍንዳታ አይሰማም ነበር ። በዚህ ጊዜ በኋይት ሀውስ ቤተመንግሥት ቴሌቪዥን ያዳምጡና ያዩ የነበሩት ጆርጅ ቡሽ ትንሽ መናደድ ጀመሩ ። በመጨረሻ ፣ ያለጠርጥር በባግዳድ ኀሙስ ጥር 9/1983 ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ፣ በአሜሪካ ከምሽቱ በአንድ ሰዓት የቦምብ ፍንዳታ ተሰማ ። አፈቀላጤያቸውን ማርሊን ፊትዝወተርን "ኩዌትን ነፃ ማውጣቱ ተጀምሯል" ብለው እንዲነግሩ የላኩት ጆርጅ ቡሽ "ልክ በመርሐግብሩ መሠረት" በማለት ተናገሩ ።

ከሁለት ሰዓት በኋላ ፕሬዚዳንቱ ብዙ ሳምንት ሙሉ ሲዘጋጁ የነበረ ዲስኩራቸውን ለሕዝብ ለማሰማት በቴሌቪዥን ቀረቡ ። በዚህም ዲስኩራቸው የአሜሪካ ዓላማ "ኢራቅን ድል መቶ መያዝ ሳይሆን ኩዌትን ነፃ ማውጣት ነው" አሉ ። ቡሽ ከዚህም አያይዘው "ሳዳም ሑሴንን ኑክሌር ቦምብ የማምረት ዐቅም ልናሳጣቸው ቆርጠን ተነሥተናል ። የኬሚካል ጦር መሣሪያ ማምረቻ ተቋሞቻቸውንም እናደባየዋለን" ብለዋል ።

## የኻፍጂ ጥቃት

በሰሜን ሳውዲ ዓረቢያ ድንበር ላይ ኻፍጂ በምትባለው የሳውዲ የባሕር ዳርቻ ከተማ ውስጥ የተካሄደውን ውጊያ "ወታደራዊ የታሪክ ጸሐፊዎች 'የ1983 ዓ.ም የባሕረ ሰላጤው ጦርነት—የመጀመሪያው የምድር ጦር ግጭት' በማለት ምናልባት ይጽፉት ይሆናል ፣ በዚያ ውጊያ ውስጥ ለተካፈሉት ሁሉ ግን ዕውነተኛው አስፈሪና ትልቅ ጦርነት ነበር"



ሲል አንድ የአሜሪካ ጋዜጠኛ ዘግቧል ። በእርግጥ ጋዜጠኛው እንዳለው ፣ የአሜሪካንና የኀብረ ብሔሩን ጦር ኃይሎች የውጊያ ብቃትና የጦር መሣሪያ ዓይነት ለመፈተሽ የኢራቅ ጦር ኃይል በተከታታይ በፈጸመበት በዚህ ትንኮሳ ጥቃት ጊዜ ነበር የአሜሪካ የባሕር ኃይል አባላትና የተባባሪዎቹ የዓረብ አገሮች ወታደሮች ለመጀመሪያ ጊዜ ከዕውነተኛው ዘመናዊ ጦርነት ፍልሚያ ውስጥ የገቡት ።


በዚህ ውጊያ ትልቅ ጥቃት አልደረሰም ፣ ምናልባትም የኀብረት ኃይላት አየር ኃይል በአደረገው ከባድ የአጸፋ ቦምብ ድብደባ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም ። በዚህ የአየር ላይ ውጊያ ከነበሩት የአሜሪካው አየር ኃይል ሻለቃ ሪቻርድ ፓውሎ አንዱ ነበር ። እርሱ ተካፋይ በሆነበት የኤ—10 ዋርት ሆግስ ተዋጊ አውሮፕላን ስኳድሮን (አንድ የተዋጊ አውሮፕላን ቡድን) ለቦምብ ድብደባ ተልዕኮ ይመላለሱ ፣ ከዚያም ወታደር የጫኑ መቶ የኢራቅ ካሚዮኖች እንደ ባቡር ቀርጐ ተከታትለው በመንገድ ላይ እንዳሉ ደረሱባቸው ፣ በዚህ ጊዜ የመጀመሪያውንና የመጨረሻውን ካሚዮኖች በቦምብ በማደባየት ሌሎቹን በአጣብቂኝ ውስጥ አስገቧቸው ፣ ቀጥለውም በዚሁ መኻል የነበሩትን ታንኮችና ወታደር የጫኑ ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎች አወደሙ ።

ሻለቃ ፓውሎ ስለፈጸመው ጀብዱ ሲተርክ ፣ "መጀመሪያ ለመቀስቀስ ያኸል 1 ሺ 100 ኪሎ ግራም ክብደት ያለው ቦምብ ጣልኩባቸው ፣ አጸፋውን ተኮሱ ፣ ቀጥሎም በቅደም ተከተል በአንድ መሥመር ይጓዙ የነበሩትን ካሚዮኖች ፣ ታንኮችና ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎች እኔና ስኳድሮኔ በቦምብ ወቃናቸው ። ከዚያም በኋላ በጨለማ በሚያሳየው ባለጨረር መነፅር አዘቅዝቄ ስመለከት የኢራቅ ወታደሮች ከካሚዮኖቻቸው እየወረዱ በእሳት ከተቀጣጠሉት ታንኮችና ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎች ውስጥ ወታደሮቹን እየጐተቱ ሲያወጡ ነበር—ድል አደረግን ሌሊቱ የኛ ሆ!" በማለት ይደመድማል ። የኢራቅ ጦር ኃይል በተደጋጋሚ ድንበርን በመሻገር በውንበዴው የማጥቃት ዘመቻ የኻፍጂን ከተማ ያዘ ። ከ36ቱ ሰዓት በኋላ ግን ፣ የሳውዲና የኳታር ወታደሮች በአሜሪካ ጦር ኃይል እየታገዙ ከተማዋን መልሰው ያዙ ። በዚህም ጊዜ ኢራቅ 30 ወታደሮች ሲሞቱባት 300 ደግሞ ተማረኩባት ።

ከኀብረ ብሔሩ ጦር ኃይል ደግሞ ሁለት ሰዎች ተማርከዋል ።



በሻፍጂ የባሕር ዳርቻ "ኮሞራንትስ" የተሰኘችው የአዕዋፍ ዝርያ ከተዘፈቀችበት የነዳጅ ዘይት ፍሳሽ ውስጥ ለመውጣት ስትንቦጫረቅ






ሁለቱም አሜሪካውያን ሲሆኑ ፤ ሚሊሳ ኤ ራዝባን ኤሌይ እና ዲቪድ ሎኪት የሚባሉ ሴትና ወንድ ወታደሮች ናቸው ። ሁለቱም የጠፉት በሳዑዲ ዓረቢያ ድንበር ላይ ለተዋጊዎች ስንቅና ትጥቅ ጭነው በመጓዝ ላይ ሳሉ ነበር ። የሁለቱም ከባድ የጭነት ካሚዮናች በአሸዋ ተውጠው ለመንቀሳቀስ ባለመቻላቸው በኢራቅ ወታደሮች ተማርከዋል ።

የሴት ወታደር የጦር እሥረኛ ሆኖ መያዝ ፤ በወታደራዊ ተግባር ውስጥ የሴቶች ሚና ምን መሆን አለበት ? የሚለውን አዲስ ጥያቄ ሊያስነሣ ችሏል ። በታሪክ ውስጥ አሜሪካ የተማረኩባት የሴት ወታደር ጦር እስረኞች መቶ አይሞሉም ። ይህም በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ የተማረኩትን 88 እና በቪየትናም ጦርነት ደግሞ የተማረኩትን ሁለት ይጨምራል ። ቀደም ሲል እንደነበሩት ጦርነቶች ሁሉ ፤ በዚህ ውጊያ የተመደቡት ሴቶችም በግንባር ከመፋለም ተግባር የተከለከሉ ነበሩ ። በባሕረሰላጤው ጦርነት ውስጥ ግን ፤ በግንባርና በደጀን ያለው የሥራ ክፍፍል በግልጽ ባለመለየቱና በመወራረሱ የሴት ወታደር የጦር ምርኮኛ ቁጥር ከፍ ይል ይሆናል ፤ የሚል ግምት አሳድሮ ነበር ። ጥያቄው የሴት ወታደሮች በጠላት ተማርከው — ምናልባትም ሲንገላቱ — ሕዝቡ ሲመለከት ምን ይላል ? በወታደራዊ ተግባር ውስጥ እኩልነት ደረጃ ላይ ለሚደርሱ ሴቶች የሚያስከፍለው ዋጋ አስፈሪ ችግሮችን ያዘለ ሊሆን እንደሚችል ያስገነዝባል ።

የኢራቅ ድንገተኛ ጥቃት በዋሽንግተን የታየው ኩዌትን ነፃ ለማውጣት ፤ የሳዳም ሑሴንን የጦር ኃይል ለመደምሰስ የኅብረ ብሔሩ ጦር ኃይል ለሚያካሂደው ዘመቻ በትድሚያ እንደተደረገ ሙከራ ተደርጐ ነው ። የአሜሪካ የጦር አዛዦች እስከ በታች የመሥመር መኰንኖች በአደረጉት ግምገማ መሠረት የውጊያው ውጤት አርኪ ነበር። በኅብረ ብሔሩ ጦር ኃይል ላይ የደረሰው ጉዳት ቀላል ከመሆኑም ሌላ ፤ የተጠናከረውን የሳዳም ጦር ኃይል ለመደምሰስ ተችሏል ። አሜሪካዊው የኅብረ ብሔሩ ጦር ኃይሎች አዛዥ አርሚ ጄኔራል ኤች ኖርማን ሽዋርዝኮፍ ስለኢራቅ ድንገተኛ ጥቃት ሲናገሩ ፤ "ትንኝን ከዝሆን ጋር ፤ … ከማለት በስተቀር ትርጉም የለውም ።" ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል ። በተጨማሪም ፕሬዚዳንት ጆርጅ ቡሽ በሰጡት መግለጫ ፤ "የባሕረሰላጤውን የምድር ውጊያ ማካሄድ አስፈላጊ ቢሆንም ፤ የሚጀመ

ረው ግን ፣ በሣዳም ሑሴን የጊዜ ሠሌዳ ሳይሆን ፣ በራሳችን የጊዜ ሠሌዳ መሠረት ነው" ሲሉ ተናግረዋል ።

በኻፍጂ የተካሄደው ውጊያ የሚያሳየው የሣዳም ሑሴንን ጀብደኝነት ነው ። የኢራቅ ጦር ኃይል ከደቡብ ኩዌት ምሽጉን ጥሎ መውጣቱ ለሁለት ቀንና ሌሊት የአየር ቦምብ ድብደባ አጋልጦታል ። በሌላ በኩል ደግሞ የኢራቅ ጦር ኃይል ቀደም ሲል ከታመነው በላይ በጨለማ ውስብስብ እንቅስቃሴ ለማድረግ ችሎታ እንዳለው ለማወቅ ተችሏል ። የእዝና የቁጥጥር ተግባሩ በአብዛኛው ሥራውን ለማከናወን የተጠናከረ መሆኑ ታይቷል ። አንዳንድ የጦር ክፍሎቹ በጨለማ ለማሳየት የሚችል መሣሪያ ሳይታጠቁ እንዳልቀሩ ተገምቷል ። የኅብረት ኃይላት ወታደራዊ ባለሥልጣኖች በድንገተኛው የማጥቃት ዘመቻ እስከ 2ሺ የኢራቅ ወታደሮች ተካፋይ እንደነበሩ መደምደሚያ ላይ ደርሰዋል ። ከፔንታጐን ዜና ምንጭ በተገኘው መረጃ መሠረት ደግሞ ፣ በኻፍጂ ጥቃት ላይ ተካፋይ የነበረው የኢራቅ ጦር ኃይል 60ሺ ወታደሮችና 1ሺ ታንኮች እንደነበሩና እንቅስቃሴውም በሳዑዲ ዓረቢያ ውስጥ ምናልባት በሰፊት ለማጥቃት ታስቦ እንደነበር የዘመቻው አዛዥ ዘገባውን በሰሙ ጊዜ ተደናግጠዋል ።

ከዚህ የኻፍጂ ጦርነት የተገኘው ትምህርት የኢራቅን ወታደሮች የማጥቃት እንቅስቃሴ ለመተንበይ አስቸጋሪ መሆኑና በመከላከል ረገድም የማይበገሩ መሆናቸው ሲሆን ፣ የአሜሪካና የኅብረ ብሔሩ እግረኛ ወታደሮች ለወሳኙ ፍልሚያ በቂ ዝግጅት ማድረጋቸውን ነበር ። በአጠቃላይ ኩዌትን ነፃ ለማውጣት የተደረገው የምድር ውጊያ ከግምት በላይ ፈጣንና አዲሱ ወታደራዊ ትውልድ የሚፈተንበት እንደሚሆን ነው።

በኻፍጂ የሣዳም አጥፍቶ መጥፋት ጥቃት በባሕረሰላጤው ጦርነት ውስጥ የመጀመሪያው የምድር ላይ ውጊያ ተካሂዷል ። ነገር ግን ፣ የኢራቅ ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎች ያለአየር ከለላ ወደ ኻፍጂ ለመግባት ያደረጉት ሙከራ ለመጥፋት ብቻ ነበር ።

የኢራቅ ወታደሮች ኻፍጂን ከ24 ሰዓት በላይ ይዘዋል ። ከተማዋ በሐምሌው የወረራ ጦርነት ሕዝቡ ጥሏት የሄደ እና ስትሆን ፣ ለመከላከል የማትመች ለአደጋ የተጋለጠች ስለነበረች ፣ የኢራቅ ወታደሮች ወደዚች ከተማ መግባት ከወታደራዊ ስልት አንፃር ሲታይ ቀጋ ቢስ ነበር ።



ወደከተማዋ የገባው የሳዑዲ ጦር ኃይል ፣ የንጉሥ አብዱል አዚዝ ብርጌድ አምስተኛ ክፍለ ጦር ሲሆን የኢራቅ ጦር ኃይል ደግሞ የአየር ከለላ ስላልነበረው ዘመቻው ገና ከጅምሩ የከሸፈ ነበር ። ወደኻፍጂ የገቡት የኢራቅ ወታደሮች እንደተገመተው በጨለማ የሚያሳይ መነጽር ፣ የተኩስ አቅጣጫን የሚጠቁም ኮምፒዩተርና ሌላም የተራቀቀ መሣሪያ አልነበራቸውም ። የነበራቸው የመርዝ ጋዝ መከላከያ ጭምብል ብቻ ነበር ። የመከላከያ ወረዳቸውን እስኪያልቁ ድረስ ለመጠበቅ የመጡ ኋላቀር ወታደሮች ነበሩ ። ቀላል ራሽን በመቀበልና ለማብሰያ ማገዶ የበረሃውን ጭራሮ በመለቃቀም ፣ በራሽን መልክ በሚታደላቸው ውሀ ብቻ የሚኖሩ ነበሩ ። ኑሯቸው ከኢያሪኮ ግምብ ውጭ የኢያሱ ወታደሮች ወይም በ1935 ቱኒዝያ በረሃ ውስጥ አንድ የጀኔራል እለን ፓተን ወታደር እንዳደረገው ዓይነት ነበር ። እንዳይከዱ በተቀበረ ፈንጂ ዙሪያውን ታጥረዋል ፣ የማምለጫ መንገዱንም እንዳያውቁት ፈንጂውን ቀብሮ የሄደው ሌላ ክፍለ ጦር ነበር ። መሄጃ ስለሌላቸው በቀበሮ ጉድጓድ ውስጥ ተንጋለው ወደ ሰማይ በማንጋጠጥ መኖር ብቻ ነበር ። በዚህም ላይ የኅብረ ብሔሩ ጦር ኃይል ቢ—52 ተዋጊ ጀት ቦምብ ያወርድባቸው ነበር ፣ በዚህም ምክንያት ኩዌት ውስጥ የነበረው የኢራቅ ወታደር በፍርሀት እየተናጠ ፣ በመፍረክረክ ላይ ነበር ።

ጭንቀት እንዳለባቸው በግልጽ ከፊታቸው የሚነበበው ሣዳም ግን፣ "የኅብረ ብሔሩ ጦር ኃይሎች የጦርነቶች ሁሉ እናት ይጠብቃቸዋል ፣ ሽንፈቱንም ወደ ድል እንለውጠዋለን ።" ካሉ በኋላ በማስከተል ፣ በኻፍጂ የተሠነዘረው ጥቃት 'ከድሎቹ መካከል አንደኛው ነው '" በማለት ተናገሩ ። ይሁንና ይህ የጦርነቶች ሁሉ እናት የተባለው ወይም ደግሞ ጋዜጠኛው እንዳለው ከልጆቿ አንዱ ቢሆንም ፣ ከመወለዱ በፊት ተጨናግፏል ።

ኢራቅ በምድር ውጊያ የሚገጥማትን ሽንፈት ወደ ፖለቲካዊ ድል ለመለወጥ አስባ ነበር ። በሰሜን ሳዑዲ ዓረቢያ የተካሄደው ውጊያ ዕውነተኛው የምድር ጦርነት መጀመሩን አላረጋገጠም ። ዕውነተኛው ጦርነት የተከፈተው የአሜሪካና የኅብረ ብሔሩ ጦር ኃይል ከያቅጣጫው የማጥቃት ዘመቻውን ሲጀምር ነበር ።

## የአየር ጥቃት መፋፋም

አሜሪካና ተባባሪዎቿ የሣዳም ሑሴንን ወታደራዊ ተቋም አንድ ሳምንት ሲያደቁ ከቆዩ በኋላ ለተወሰኑ ቀናት ሰማዩን ሸፍኖት የቆየው ጉም በመገፈፉ በመላዋ ኢራቅ የተሰራጩ ኢላማዎች ያለማሠለስ በአየር ተደበደቡ ። ሳይደበደብ የቆየው በኩዌትና በደቡባዊ ኢራቅ 4ሺ ታንክ ይዞ የሸመቀውና በሪፐብሊኩ ዘብ – ምርጥ ጦር የተመራ ከግማሽ ሚሊዮን በላይ የኢራቅ ሠራዊት ነበር ። በዚህ ጦር ላይ ሊሰነዘር ስለታቀደው ጥቃት የአሜሪካ ጠቅላይ ኤታ ማጆር ሹም ፣ ጄኔራል ኮሊን ፓውል ሲገልጹ "ይህን ጦር የምናጠቃበት ስትራተጂ በጣም በጣም ቀላል ነው ። መጀመሪያ ከበስተጀርባ ገብተን ልንቆርጠውና ፣ ከዚያም ልንተጨው ነው" ብለዋል ።

የምድር ውጊያው ከጥቂት ፣ አልፎ አልፎ ከሚደረጉ ግጭቶች በቀር አልተካሄደም ። በተሽጐደጐደው የአየር ጥቃት ግን የኢራቅ የአየር መከላከያ ክፉኛ ተጐድቷል ። ራዳሮቿ በአብዛኛው ጸጥ ብለዋል ። የጦር አውሮፕላኖቿ በምድር ውስጥ ተደብቀዋል ። የኅብረብሔሩ አየር ኃይል በልምምድ ላይ እንኳ ከሚደርሰው ባነሰ አደጋ ሰማዩን እንደልቡ እየከነፈበት ነበር ። ከሣዳም ሑሴን ድንፋታና ዛቻ አንፃር ከኢራቅ በኩል የሚሰነዘረው አፀፋ በሚያስደንቅ ሁኔታ የሌለ ያኸል ሆነ።

ሆኖም የቱንም ያኸል ቢሳካላቸው የተባበሩት ኃይላት ሣዳምን ሲሻቸው የስከድ ሚሳይል ውርጅብኝ ከማዝነብና የኩዌትን ነዳጅ ዘይት ወደባሕረ ሰላጤው ከማፍሰስ ሊገቷቸው አልተቻሉም ። ከዚህም በተጨማሪ ፣ ከሚቀጥለው የጦርነቱ ሂደት ዘገባ እንደምንረዳው የአየር ጥቃቱ ዘመቻ በተጠበቀበት ጊዜ ካለማብቃቱም በላይ አንዳንድ ኢላማ ይስት ነበር :–

1. ለዘጠኝ ቀን የታቀደው የአየር ጦርነት በአየር ጠባዩ መለወጥና በስከድ ላውንቸሮች አሠሣ ምክንያት ከመንሻው ለአንድ ሳምንት ተጓተተ ።

2. የቦምብ ጥቃቱ የተገመተውን ያኸል ጉዳት አላደረሰም ። ጉዳት የደረሰባቸውን የአየር ማረፊያዎች ፣ መንገዶችና ድልድዮች አሜሪካ ከገመተችው በፈጠነ ሁኔታ ኢራቅ መጠገን ችላለች ። የሪፐብሊኩም ዘብ 24 ሰዓት በአየር ከተወቀጠ በኋላ የመከላከል ኃይሉ የቀነሰው 5 ከመቶ ብቻ ነበር ።



3. ኅብረብሔሩ ጥንቃቄ ቢያደርግም በሰላማዊ ሕዝብ ላይ የደረሰው አደጋ ሁለቱም ተፋላሚዎች ካመኑት ፣ በተለይ በደቡባዊ ኢራቅ በምትገኘው በባስራ ከተማ በጣም በልጦ መገኘቱ በአሜሪካ ሳታላይት በተነሣ ፎቶግራፍ ተረጋገጠ ።

4. ሆኖም የተባበሩት ኃይላት አጠቃላይ የአየር የበላይነቱን ተቀዳጅተው የኢራቅን የኑክሌር ፣ የሥነሕይወትና የኬሚካል ጦር መሣሪያ ተቋማት በጣም መጉዳታቸውና ጄኔራል ፓውል እንደተናገሩት ሁለት የኑክሌር ማመንጫዎቿ "ያበቃላቸው" መሆናቸው ተስፋ የሚያሰጥ ሆነ ።

እርግጥ አንድ የኋይት ሀውስ ባለሥልጣን እንደገለጹት የኢራቅ ኃይል "ለሞት እስኪያጣጥር" አሜሪካ "የምድር ጦር ውጊያ አትጀምር" ስለነበረ የአየር ጥቃቱ መራዘሙ አያስደንቅም ።

ጦርነቱ በተጀመረ በሁለት ሳምንት ውስጥ እንኳ ኢራቃውያን በከፊል ደንቁረው ፣ ዱዳ ሆነውና ታውረው ለመዋጋት ተገደዋል ። በባሕረ ሰላጤው የተሠማራው ኅብረብሔር ጦር ጠቅላይ አዛዥ ጄኔራል ሽዋርዝኮፍ እንደገለጹት ጦራቸው በአየር ጥቃቱ የ"ሣዳምን የቴሌኮሙኒኬሽን ችሎታ" አድቅቋታል ። ከኢራቅ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መረብ ውስጥ የሳሳበት ሥፍራ ድምበሯ አትራቢያ ተደርሶበታል ። ይህ ሥፍራ ከራዳር እይታ ክልል ውጪ የነበረ ክፍተት ነበር ። ስቴልት የጦር አውሮፕላኖችና ክሩዝ ሚሳይሎች የመጀመሪያውን ጥቃት እያደረሱ እያለ ፣ በዚህ ክፍተት በኩል የአሜሪካ ኮማንዶዎች በሄሊኮፕተር ወደ ኢራቅ እንዲገቡ ተደረገ ። እነሱም ሁለት የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ የራዳር ጣቢያ በቦምብ በማጋየት ክፍተቱን አሰፉት ። ይህም ፣ ጥቃት ለሚያደርሱ አውሮፕላኖች ከራዳር የተገለለ በር ከፈተ ። ከዚህም እንዳንዱ በኢራቅ ደቡባዊ ክፍል የነበረውን የአየር መከላከያ መቆጣጠሪያ ማእከልና ራዳሮች አደባዩ ። ራዳሮቹ ሁሉ ፊታቸውን ወደ ደቡብ ያዞሩ ስለነበሩ የጦር አውሮፕላኖቹ እነሱን አልፈው ለማጥቃት ወደሰሜን አሸቀቡ ።

ጦርነቱ በተጀመረበት ሳምንት ለውጊያ የመጣ ጥቂት የኢራቅ አውሮፕላኖች በፍጥነት የምላቸውን እንዲያገኙ ተደረጉ ። በውጊያው ላይ ከተሳተፉት የተባበሩት ኃይላት አየር ኃይል ፓይለቶች መካል ሁለት

የኢራቅን ጀቶች መትቶ ለመጣል የመጀመሪያው የመሆን እድል የገጠማቸው ካፒቴን እይድ ሽል ሻምራኒ የተሰኙ ሳዑዲያዊ ኮሎኔል ናቸው ። ፓይለቱ መትተው የጣሉት ቦምብና ኤክሶሴት ካየር ወደ ምድር ተምዘግዛጊ ሚሳይል ጭነው ወደደቡብ በመብረር ላይ የነበሩ አንድ ኤፍ – 15 እና አንድ ፈረንሳይ ሠራሽ ሚራዥ – 1 ነበሩ ።

ኢራቃውያን የአየር ኃይል ጀቶቻቸውን ከደበቁባቸው ምሽጎች አውጥተው በውጊያ ላይ እንዲሠማሩ ባለማድረጋቸው ከአየር ኃይላቸው አብዛኛውን ፣ ማለትም በፔንታጎን ግምት ጦርነቱን ከጀመሩት 809 አውሮፕላኖች ከ750 በላዩን ከአደጋ ጠብቀዋል ። የአየር ኃይሉንና የአየር መቃወሚያውን አዛዦች በውጊያ ብቃት ማነስ ምክንያት ሣዳም ተናድደው የገደሏቸው መሆኑን ኢንተርፋክስ የተሰኘ የሶቪየት የዜና አገልግሎት ገልጿል ።

ኢራቅ ፣ ምናልባት የሕዝቧ ወኔ እንዳይሰለብ ፣ በሰላማዊ ነዋሪዎች ሠፈር የደረሱ አደጋዎችን በሙሉ ሳታምን ቆይታለች ። ነገር ግን አንዳንድ የሰላማዊ ዜጎች መኖሪያዎችን መተዋል ፣ በማለት አሜሪካን ማውገዝ ጀምራ ነበር ። ከነዚህም መኻል የአሜሪካ ባለሥልጣኖች ያገሪቱ ዋና ሥነሕይወታዊ የጦር መሣሪያ ፋብሪካ መሆኑን የደረሱበትና ኢራቅ ግን "የሕፃናት ወተት ፋብሪካ ነው" ብላው የነበረው ተቋም ይገኛል ።

የአየር ጥቃቱ ከተጀመረበት ከጥር 8/1983 ረቡዕ ምሽት እንሥቶ የተባበሩት ኃይላት ጦር ወደ ኢራቅና ወደ ኩዌት ያደረጋቸው በረራዎች ሁሉ የጥቃት ብቻ አልነበሩም ። የነዳጅ ዘይት ቦቴ አውሮፕላኖች ፣ መጓጓዣ አውሮፕላኖች ፣ ራዳር አውሮፕላኖችና ሌሎችም በውጊያ ላይ ያልተሠማሩ አውሮፕላኖች ነበሩባቸው ። መሣሪያ ከጫኑት አጥቂ የጦር አውሮፕላኖች ሌላ የአየር ሽፋን የሚሰጡ አጃቢ ጀቶች በኤሌክትሮኒክ ራዳሮችን የሚያሰናክሉ ወይም የሚያጭበረብሩ ጀቶችና ፣ የስለላ አውሮፕላኖች ነበሩ ።

የተባበሩት ኃይላት በምድር ጦር ጥቃት በከፈቱበት ዋዜማም የአየር የቦምብ ውርጅብኛቸውን ወደኢራቅ የግምባር መሥመሮች እያቀረቡ መጡ ። በአዳዲስ የጦር መሣሪያም ጥቃታቸውን ማካሄድ ጀመሩ ። በመጀመሪያ የምድር ውጊያ ጥቃት ለመጀመር ለእግረኛና ለታንክ መሸጋገሪያ መንገድ ለመክፈት ፈንጂውን እያፈነዱ ለመጥረግ ነዳጅ



የአየር ቦምብ የመሳሰለውን መጣል ተያያዙት ። የአየር ጠባዩም አመቺ ። ሌቱ ጨረቃ ሆን ። የተባበሩት ኃይላት የሌሊት መዋጊያ ትጥቅና ሥልጠና ከኢራቆች የላቀ ስለነበር የፈለጉት ነበር ። የባሕር ሞገድ በመነሣቱም በኩዌት የባሕር ጳርቻ ለአሜሪካ ባሕር ወለድ ጦር ምድር ላይ ለመቆናጠጥ አመቺ ።

ሣዳም "የውጊያዎች ሁሉ እናት" ለመጀመር ለረጅም ጊዜ ሲደነፉ እንደቆዩት እንደዳንጉት ያደርጋሉ ፣ ተብሎ ሲጠበቅ በወቅቱ የውጪ ጉዳይ ሚኒስትራቸው በጣሪቅ አዚዝ የተጻፈ የተመድን ውሳኔ ቁጥር 660 ኢራቅ ስለመቀበሏ የተጻፈ ደብዳቤ ለተመድ ይደርሳል ። "የውጊያዎች ሁሉ እናት" ውጊያ እየተባለ ሲደነፋ የነበረው ትኩረትን ማዘናጊያ ውጊያ መሆኑ ቀርቶ ዲፕሎማሲያዊ ማዘናጊያ ሆኖ በረፈው ። አሜሪካም ሆነች የሌሎች የኅብረብሔሩ አባል አገሮች የኢራቅን የድርድር ጥያቄ አልተቀበሉትም።

እንዲያውም የአየር ጥቃታቸውን በኢራቅ ውስጥ ባሉ ወታደሮቿ ፣ በመሣሪያዎቿና በምሽጐቿ ላይ አፋፋሙ ። በዚህም የተፋፋመ ጥቃት ኩዌት ከገቡት ጠቅላላ የኢራቅ ታንኮችና ሌሎች ከባድ መሣሪያዎች እንደ ሦስተኛ ያኸሉ ፣ ከ4ሺ 280ው ታንክ 1ሺ300ው ፣ ከ2ሺ870 ብረት ለበስ ተሽከርካሪ 800ው ፣ ከ3ሺ110 ከባድ መሣሪያ 1ሺ100ው ተደመሰሰ ።

በዚሁ ጦርነቱ በተጀመረ በአንድ ወር ውስጥ በተገኘው ውጤት በጦርነቱ መነሻ በኩዌት ግምባር ከተሰለፈው ከ500ሺ እስከ 546ሺ ጦር መኻል ከ50ሺ እስከ 100ሺ የሚደርሰው ተደምስሷል ወይም ቆስሏል ተብሎ ተገምቷል ። በዚህ መኻል የኢራቅ ጦር ሞራል ወድቆ ፣ በቂ ስንቅና ትጥቅ ፣ እንዲሁም በውጊያው መኻል ፋታ በማጣቱ ግማሹ ለተባበሩት ኃይላት እጁን እየሰጠና እየከዳ ፣ ግማሹ መሣሪያውን እየጣለ ወደኋላ መፈርጠጥ ጀመረ ።

አዝማሚያው የተባበሩት ኃይላት የምድር ውጊያ መጀመሩ ቀደም ሲል ከታሰበው ባነሰ መሥዋዕትና ጊዜ የሣዳምን የምድር ጦር ለመደምሰስ ፣ መንግሥታቸውን ለማስወገድና በመካከለኛው ምሥራቅ ያላቸውን ሥፍራ ለማሳጣት የቀለለ መስሎ ታየ ። ግን ኢራቅ አንዳንድ ቅድመ ሁኔታዎች ከተሟሉላት ፣ ኩዌትን ለቃ ለመውጣት ፈቃደኛ መሆኗን ለምን እንዲህ ዘግይታ ገለጸች?

## የንብረት ኃይላት አስተዋጽኦ

### የንብረ ብሔሩ መርከቦች

| | |
|---|---|
| 1· [illegible] | [illegible] |
| 2· [illegible] | [illegible] |
| 3· [illegible] | [illegible] |
| 4· [illegible] | [illegible] |
| 5· [illegible] | [illegible] |
| 6· [illegible] | [illegible] |
| 7· [illegible] | [illegible] |
| 8· [illegible] | [illegible] |
| 9· [illegible] | [illegible] |
| 10· [illegible] | [illegible] |
| 11· [illegible] | [illegible] |
| 12· [illegible] | [illegible] |
| 13· [illegible] | [illegible] |
| 14· [illegible] | [illegible] |
| 15· [illegible] | [illegible] |
| 16· [illegible] | [illegible] |
| 17· [illegible] | [illegible] |

### የንብረት ኃይላት ጦር አውሮፕላኖች

| | |
|---|---|
| 1· [illegible] | [illegible] |
| 2· [illegible] | [illegible] |
| 3· [illegible] | [illegible] |
| 4· [illegible] | [illegible] |
| 5· [illegible] | [illegible] |
| 6· [illegible] | [illegible] |
| 7· [illegible] | [illegible] |

### ሌላ የምድር ጦር

| | |
|---|---|
| 1· [illegible] | [illegible] |
| 2· [illegible] | [illegible] |
| 3· [illegible] | [illegible] |
| 4· [illegible] | [illegible] |
| 5· [illegible] | [illegible] |
| 6· [illegible] | [illegible] |
| 7· [illegible] | [illegible] |
| 8· [illegible] | [illegible] |
| 9· [illegible] | [illegible] |

### ኤቪ - 8ቢ ሀሪየር

[illegible]

### ኤ 64 አፓቼና ኤ-ኤች 1ደብልዩ ሱፐር ኮብራ

[illegible]


### ለስሜይ ሞትን ማዝነብ



### ኤ 10 ተንደርቦልት

[illegible]





### የምድር ውስጥ መሸሸጊያ የሒቢን ሂልተን

[illegible]

### በምድር ውስጥ የተቀበሩትን ፈንጂዎች ለመቀረጥ



[illegible]

### ብረት ለበስን ለመብሳት

[illegible]

1. ሳዳም ተንፈስ ማለት ስለፈለጉ ይሆን ?

የምድር ጦርነቱን ለማዘግየትና የአየር ጥቃቱ እንዲቋረጥላቸው ወይም ቀለል እንዲልላቸው ሳዳም ተስፋ ያደረጉ ይመስላል ። የምድር ጦርነቱ ቢዘገይ ፣ በይበልጥም የተኩስ አቁም ቢጸና ድርድሩ እየተካሄደ ኢራቃውያን እንደገና ተሰባስበው ለበለጠ ውጊያ ራሳቸውን የሚያዘጋጁበት ጊዜ ያገኛሉ ። እንዲያውም የሶቪየቱ ፕሬዚዳንት ሚኻይል ጐርባቾቭ የወቅቱ የኢራቅ የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር ጣሪቅ አዚዝ ሞስኮ ደርሰው እስኪመለሱ የምድር ጥቃቱ እንዲዘገይ አሳስበው ዋሽንግተን መስማማቷ ተወርቷል ።

2. ኢራቅ በጦር ሜዳ መቀዳጀት የማትችለውን እንደገና በዲፕሎማሲ ለመቀዳጀት እየሞከረች ነበር ፦ ባግዳድ ውስጥ በአንድ የአየር ጥቃት መጠለያ ውስጥ እንደተሸሸጉ በአሜሪካ የአየር ጥቃት በአሜሪካ ቦምቦች ተመተው የሞቱ ሰላማዊ ሰዎችን ሬሳ ከተጋነነ መግለጫ ጋር በቴሌቪዥን ለዓለም በማቅረብ መጠነኛ የፕሮፓጋንዳ ስኬት አግኝተው ነበር ። አሜሪካ በበኩሏ የምድር ውስጥ መጠለያው የወታደራዊ እዝና ቁጥጥር ማእከል ሆኖ ስለማገልገሉ ማስረጃ እንዳላትና ሰላማዊ ሰዎችም ያጠቀሙበት እንደነበር አለማወቋን ሙዝዝ ብላ ገለጸች ። ይሀም ሆኖ አንዳንድ የዓረብ አገሮችንና ገለልተኛ ናቸው ተብለው የሚገመቱ ቻይናን የመሳሰሉትን አገሮች በአስቸኳይ ተኩስ እንዲቆም ግፊት ያደርጉ ዘንድ አነሣሥቷል ። ይህ ደግሞ የተባበሩትን ኃይላት ጦርነቱን ለመቀጠል በቂ ሰበብ በማሳጣት ጦርነቱ ያለገደብ በመቆም የበለጠ ዘላቂ ወደሆነ መፍትሔ ያመራል የሚል ተስፋ በኢራቅ ላይ ሊያሳድርባት ችሏል ።

የሳዳም ተስፋ ይህ ከነበረ እርሳቸው ያልጠበቁትን አጋጣሚ መያዝም ይችል ነበር ። ቡሽ ኢራቅ ኩዌትን እንደያዘች የተኩስ አቁም ስምምነት ይደረግ የሚለው ግፊት ከጠነከረባቸው የምድሩን ጥቃት በጥቂት ቀናት እንዲጀምሩ ሊያደርጋቸው ይችል ነበር ። ይህን እንዲያደርጉ በስደት ላይ የነበረው የኩዌት መንግሥት ፣ ሳዑዲ ዓረቢያ ፣ ግብጽና ብሪታንያ ቡሽን ገፋፍተዋል ። ኢራቅ ግን የሶቪየት ኅብረትን ዲፕሎማሲያዊ ርዳታ የማግኘት እድል ነበራት ።

ኢራቅ እንደዱብ ዕዳ የሰነዘረችው ብዙ ውስብስብ ቅድመ ሁኔታ ያከተተ ከኩዌት የመውጣት ሁኔታ የተሰነዘረው የጐርባቾቭ የግል መልእክተኛ ባግዳድ ደርሰው በተመለሱ በሁለት ቀን በመሆኑና እንደተ



መለሱም "የተስፋ ጭላንጭል" ማየታቸውን በመግለጻቸው በኢራቅ የሰላም ጥያቄ የሶቪየት ኅብረት ግፊት እንደነበረበት ባግዳድ ራሷ ለተመድ ባስተላለፈችው የእርቅ ጥያቄ ደብዳቤ በግልጽ ተመልክቷል ።

3. ሳዳም መሸነፋቸውን ስላወቁ የተሻለ ውጤት ለማግኘት እየተንፈራገጡ ነበር ። ኢራቅ አንድ ወር ሙሉ ያለማቋረጥ ከአየር በቦምብ ናዳ ስትደበደብ በመቆየቷ በጣም ስለተዳከመች የሳዳም የተባበሩትን ኃይላት የምድር ጥቃት የመቋቋም ተስፋ መንምኗል ፣ በዚህም ሆነ በዚያ ከኩዌት መውጣታቸው አልቀረም ። ስለዚህም ሁሉንም በማጣት ተዋርዶ ከመውጣት በክብር ተደራድሮ መውጣት የሳዳምን በሥልጣን ላይ የመቆየትና እንዲያውም የዓረቡ ዓለም ጀግና እስከመባል እድል ሊሰጣቸው ይችላል ተብሎ በወቅቱ ታምኖበታል ።

በመካከለኛው ምሥራቅ የድርድር ልማድ "ጥቁር ወተት እምጡ" ዓይነት ፣ ሊመልሱት የማይችሉትን ጥያቄ ማቅረብ ከተደራዳሪዎች መቅረቡ የማይቀር መሆኑን ላወቀ ሳዳም ከኩዌት ለመውጣት ያቀረቡት ቅድመ ሁኔታ ለጆሮ መክበድ አያስደንቅም ። አንድ የአሜሪካ ባለሥልጣን ነገሩን እንዳዩት ይህ ለሳዳም "የመጨረሻቸው ጃርጃርታ" እንደሆነ ተገምቷል።

ሆነ ብለውም ሆነ በአጋጣሚ ሳዳም ከረር ያለ ቅድመ ሁኔታ አሳዝለው ከኩዌት የመውጣት ሐሳብ በማቅረባቸው በራሳቸውም ላይ ጉድ ጠምጥመዋል ። የሳዳም ከኩዌት የመውጣት ጥያቄ በባግዳድ ከቁጥጥር ውጪ የሆነ ፈንጠዚያ ቢያስከትልም የመረረው የቅድመ ሁኔታ ብዛት ያንን ፍንደቃ ውሀ አፍስሶበታል ። የሰላም ተስፋው ብልጭ ብሎ ድርግም ማለት ደግሞ የሕዝቡ ጀርባ ከዚያ በኋላ የቦምቡን ውርጅብኝ የሚያስችል ወኔ እንዲያጣ አድርጎታል ።

ይህ ሁሉ ሰላም ቀርቧል ማለት አይደለም ። የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ቡሽ ፣ የፈረንሳዩ ፕሬዚዳንት ፍራንሷ ሚተራና የእንግሊዙ ጠቅላይ ሚኒስትር ጆን ሜጀር የተ.መ.ድ ኢራቅ ያላንዳች ቅድመ ሁኔታ ባስቸኳይ ከኩዌት እንድትወጣ ያሳለፈው ውሳኔ ካልተከበረ ፣ ወይ ፍንክች ብለው እንደጸኑ ነበሩ ። እንዲያውም ሦስቱም መሪዎች ከኩዌት እወጣለሁ የሚለው ቃል ብቻ እንደማይበቃና ሳዳም ሠራዊታቸውን በብዛት ለማስወጣት ካልጀመሩ ምንም ያልሆነ ያኸል ጦርነቱ—በተለይም በአየር የሚካሄደው የቦምብ ድብደባ እንደሚቀጥል ተናገረዋል ።

ቡሽ ደግሞ ጦርነቱን ለማቆም ሌላ ሐሳብ አቅርበው ነበር— ሣዳም ከሥልጣን እንዲወገዱ ። ይህም ሣዳም ከወረዱ ኢራቅ ከኩዌት ከመውጣት አትቆጠብም በሚል ነው ።

በሌላ በኩልም ሣዳም እሥራኤልን ቢተነኩሱም ፣ የኩዌትን የነዳጅ ዘይት ጉድጓ ሰብረው ወደባሕረ ሰላጤው ቢያፈሱም ፣ ዓለም አቀፍ ሽብር ለመንዛት ቢዝቱም የፖለቲካ ድል የመቀዳጀት ተስፋቸው ተሰበተሰ ተንደባቸዋል ።

ሰንካላ እፀፋ፡—

ፕሬዚዳንቱ ኩዌትን ነፃ የማውጣቱ ጦርነት መጀመሩን ለዓለም ባሳወቁበት ሰዓት ፡ ማደባየቱ በሚገባ እየተፋፋመ ነበር ። የመጀመሪያውን ጥቃት አድርሰው የተመለሱ ፓይለቶች ብዙ ኅብረቀለማት ያለው የፀረ አውሮፕላንና የአንዳንድ ቦምብ ተኩስ ምድር ሰማዩን ወገግ ሲያደርገው ማየታቸውንና ይህም የገና ዛፍ ወይም የአሜሪካ የነፃነት ቀን (ጁላይ 4/1777) ሲከበር በአሜሪካ እንደሚታየው ርችት ዓይነት እንደነበር አወሱ ። አንድ የብሪታንያ የቴሌቪዥን ዘጋቢም ከሩዝ ሚሳይል በነበረበት የባግዳድ ሬሺድ ሆቴል አጠገብ እንዴት አልፎ አትራቢያው የሚገኘውን የኢራቅን የመከላከያ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት መምታቱን እንዳየ ዘገበ ።

የአየር ጥቃቱ ኢላማውን የማግኘቱ ነገር ድንቅ ነበር ። በጨረር የሚመሩ ቦምቦች በምድር ውስጥ ምሽግ በር ገብተው የኢራቅን የስኩድ ሚሳይሎች ሲያጋዩ ፣ በባግዳድ ረጃጅም ሕንፃዎች አየር መውጫ ቧንቧ እየገቡ የአየር ኃይሉን ማእከላዊ እዝ ሕንፃ የላይ ፎቆች ፣ የሣዳም ቤተመንግሥት ሳይቀር ፣ ሲደረምሱ በቪዲዮ ተቀርጸው ታይተዋል ።

ሣዳምን ፣ አሜሪካ ዝም ብላ የምትደነፋ መስሏቸው ይሁን ፣ ስለዘመናዊ የአየር ኃይል ፣ የሚሳይል ኃይልና ርቅቀት ምንም ሐሳብ ስላልነበራቸው ይሁን ፣ ወይም ኢራቅ እንዲህ ዓይነቱን ጥቃት ለመመከት የቴክኒክ ዕውቀት ስላልነበራት ይሁን አይታወቅም — ብቻ የኢራቅ ጦር ለረጅም ጊዜ በሙሉ ተጠንቶት ላይ ቢሆንም አሜሪካ በገፍ የአየር ጥቃት እንደምትፈጽም ደጋግማ ብትዝትም ፣ ከኢራቅ በኩል ምንም ያኽል መከታ አልታየም ።

ዘመናዊ ጥቃት በተለይም በኢራቅ ላይ የተሰነዘረው በዚህ ቅደም ተከተል ነው ፦ የጠላትን የአየር መቃወሚያ ተቋሞች በማጥቃት



ተጀመረ። ከሩዝ ሚሳይሎች ለራዳር እይታ በሚያስቸግር ሁኔታ ዝቅ ብለው በመምዘግዘግ በሰው በሚነዱ አውሮፕላኖች ለማጥቃት በጣም አደገኛ የተባሉ ኢላማዎችን ይመታሉ ። በተለይ በባግዳድ ላይ በተካሄደው ጥቃት ከመጀመሪያዎቹ ሰንዘራዎች መኻል ከሌሉ ርቀው በፋርስ ባሕረሰላጤ ከነበሩ መርከቦች የተተኮሱ ቶምሆውክ ሚሳይሎች ነበሩ ። የመጀመሪያዎቹ ፈንጂዎች ከተማዋን እንዳንቀጠቀጧት የኢራቅ ፀረአውሮፕላኖች ገና ባልነበሩ አውሮፕላኖች ላይ ወደሰማይ መጠቁ ። በመጀመሪያው ጥቃት ለመሳተፍ ከራዳር እይታ አሸምቀው አለፉ ። ከዚያም በከፍታ የሚበሩ አውሮፕላኖች ፣ አንዳንዱ ከሩቅ ሚሳይል እየተኮሱ ፣ የጠላትን ራዳር አስናከሉ ወይም ግራ አጋቡና አንዳንድ ፀረ አውሮፕላኖች እና ተከላካይ አውሮፕላኖች ፣ እንዲሁም ያውሮፕላን ማረፊያዎች አጠቁ ። በመጨረሻ ፣ መንገዱ ከተጠረገ በኋላ ኢላማን በበለጠ በትክክል ለማግኘት ዝቅ ብለው በመብረር ቦምብ ጣዮችና ተዋጊ ቦምብ ጣዮች ጥቃት አደረሱ ።

የመጀመሪያው ሳምንት ጥቃት በዚህ መልክ በተሳካ ሁኔታ ተከናወነ ። ከመጀመሪያው ጥቃት በኋላ የአሜሪካና የተባባሪዎቿ አውሮፕላኖች በመላ ኢራቅና ኩዌት የነበሩ ኢላማዎችን እንደ መጀመሪያው በመንረፍ ሳይሆን እየተንቈረቈሩ ሌት ተቀን ወቀጡ ። ኢላማዎቻቸውን ያገኙ የነበረው በየቀኑ በኮምፒዩተር ከሚጠናቀር ባለ600 ገጽ የሥራ ድርሻ መጽሐፍ ነበር ። ከሳምንት ሳምንት ያጠቁ የነበረው ሚሳይሎችን ፣ የእዝና የቁጥጥር ክፍሎችን ፣ የወታደር ከምችትንና ከባድ መሣሪያዎችን ነበር ። ቅዳሜ ጥር 11/1983 ከመንጋቱ በፊት የባግዳድን የኤሌትሪክና የውሀ ፣ እንዲሁም ማእከላዊ የቴሌፎን ማዞሪያ መቱ ። እስከ እሑድ ከ4ሺ ቢያጆ በላይ (አንድ አውሮፕላን አንድ ጊዜ) ጥቃት አድርሰዋል ። ከነዚህ 80 ከመቶ ያኽሉ ኢላማቸውን መተዋል ።

እስከ እሑድ ጥር 12/1983 ጧት ስድስት የአሜሪካ ፣ ሁለት የብሪታንያ ፣ አንድ የኢጣልያና አንድ የኩዌት የጦር አውሮፕላን በኢራቅ የአየር መቃወሚያ ተመትቶ ወድቋል ። ዘጠኝ የአሜሪካ ፣ አራት የብሪታንያ ፣ ሁለት የኢጣሊያና አንድ የኩዌት የአየር ኃይል ባልደረባ የደረሱበት ሳይታወቅ ቀይቷል ። የኢራቅ አየር መቃወሚያዎች አንዳንዴ ብርቱ እርምታ ቢተኩሱም ኢላማዎቻቸውን አይመቱም ነበር ። የአሜሪ

ካንና የተባባሪዎቿን የአየር ድብደባ ለመቋቋም የተነሡት የኢራቅ ጄቶች በጣም አነስተኛ ነበሩ ። ግዳም የአየር ጥቃቱን በአየር ኃይላቸውና በሚሳይላቸው ለመከላከል ያልቃጡት ፤ በኋላም መልሶ ለማጥቃት ብለው በምድር ውስጥ ተጠናክረው በተቆፈሩ ምሽጎች አቆይተዋቸው ከሆነ ተብሰተዋል ። አሜሪካና ተባባሪዎቿ በአካሄዱት ድብደባ እንደነዚህ ያሉ በርካታ ምሽጎችን ከመደርመሳቸውም በላይ የአየር ኃይል ማኮብኮቢያዎ ችን በሙሉ ፣ አርሰዋቸዋል ።

የአሻንጉሊት ጠመንጃ አፀፋ፡—

ግዳም ገና ከመጀመሪያው እሥራኤልን በመርዝ ጋዝ ሚሳይል ለመምታት ሲዝቱ ቆይተዋል ። ዓላማቸው እሥራኤልን ተንኩሰው በአፀፋው ጥቃት ስታደርስ ጦርነቱን በአርቢና በዓረቦች መሻል እንዲካ ሄድ በማድረግ ግብፅና ሦርያን ሌሎች የዓረብና እስላም አገሮች በአሜሪካ መሪነት ከተባበሩት ፀረ ግዳም አገሮች ወጥተው ከኢራቅ ጐን እንዲሰለፉ ለማድረግ ነበር ። ሳዑዲ ዓረቢያም ብትሆን ውጊያውን እንድታቆም ከባድ ግፊት ይደረግባታል ፣ የሚል እምነት ነበራቸው ።

አሜሪካ ዛቻውን በማጤን እሥራኤል ጦርነቱ ውስጥ እንዳትገባ በቅድሚያ ተማጽናለች ። በአፀፋውም በእሥራኤል ላይ በምዕራብ ኢራቅ የተደገኑትን ስከድ ሚሳይሎች በጦርነቱ መጀመሪያ የምታደባያቸው ስለመሆንም ቃል ገብታላታለች ። ጦርነቱ በተጀመረ ወቅት አሜሪካ የገባችውን ቃል ከማክበሯም በላይ በመጀመሪያው 24 ሰዓት ውስጥ ኢራቅ እንደዛተችው ባለማድረጓ ግዳም እቅዳቸውን ከመፈጸም ተገትተ ዋል ፣ የሚለው ተስፋ ለመለመ ።

እንደተመኙት ሳይሆን ቀረና ዓርብ ጥር 10/1983 ኢራቅ በቴልአ ቪቭ ፣ በሀይፋና በራማላህ አካባቢ ስምንት ስከድ ሚሳይል ተኰሰች ። በዚህም 12 ያኸል ሰው ሲቆስል በልብ ድካምና በመርዝ ጋዝ መከላከያ ጭምብል አጠቃቀም ጉድለት የተነሣ አራት አረጋውያንና አንዲት የሦስት ዓመት ልጅ ሞቱ ። ግዳም ያደርሳሉ ተብሎ በአሜሪካና በእሥራኤል ከተፈራው አንፃር የስኩዱ ጥቃት የአሻንጉሊት ጠመንጃ ተኩስ ያኸል ታየ ።

እሥራኤል የበቀል ጥቃት እንዳትከፍት አሜሪካና ብሪታንያ



26) ኅዳር 19/1983፡— በጸጥታው ምክር ቤት በውሳኔ ቁጥር 677 ያለምንም ተቃውሞ የተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ በድብቅ የወጣውንና ኩዌት ከመወ ረሯ በፊት ያለውን የኩዌት ሕዝብ ብዛት የሚያሳየው ሰነድ እንዲጠብቅ ወሰነ ።

27) ኅዳር 20/1983፡— በውሳኔ ቁጥር 678 የጸጥታ ጥበቃው ምክር ቤት ኢራቅ እስከ ጥር 7/1983 ድረስ ከኩዌት በፈቃዷ ለቃ ባትወጣ ፤ ኢራቅን ከኩዌት ለማስወጣት መንግሥታት አስፈላጊውን ኃይል እንዲጠቀሙ ወሰነ ። ኩባና የመን ሲቃወሙ ቻይና ድምፀ ከመስጠት ተቆጥባለች ። ውሳኔው ዓሥራ ሁለት የድምፅ ድጋፍ አግኝቶ ነበር ።

28) ጥር 10/1983፡— ንጋት ላይ ኢራቅ ወደ እሥራኤልና ወደ ሳዑዲ ዓረቢያ ስከድ ሚሳይል ተኰሰች ። ከእነዚህም መኻል ወደእሥራኤል የተተኰሱት ስምንት ሲሆን ሁለቱ በቴልአቪቭ ፣ አንዱ በሀይፋ ፣ ሦስቱ ሕዝብ በማይኖርበት አካባቢ ሲወድቁ አንዱ የወደቀበት አልታወቀም ። በእነዚህው ሰዓት ሰው ቆሰሏል። በዚሁ ዕለት ንጋት ወደ ዳህራን ከተማ ሳዑዲ ዓረቢያ ከባስራ — ኢራቅ የተተኰሰ አንድ ስከድ ሚሳይል በአምስት ሺ ሜትር ከፍታ ለመጀመሪያ ጊዜ በጥቅም ላይ በዋለው የአሜሪካ ፓትሪየት ፀረ ሚሳይል ሚሳይል ተመቶ ወድቋል ።

29) የካቲት 20/1983፡— ኩዌት ነፃነቷን መልሳ እንድትቀዳጅ መደረጉን ፣ የባሕረሰላጤው ጦርነት በመሠረቱ ማብቃቱንና የኅብረብሔሩ ጦር ተኩስ የሚያቆም መሆኑን የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆርጅ ቡሽ በቴሌቪዥን በተላለፈ ዲስኩራቸው ገለጹ ።

## ዋቢ መጽሔቶች

1. NEWSWEEK, January 14, 1991 No2
2. NEWSWEEK, January 28, 1991 No4
3. NEWSWEEK, February 4, 1991 No5
4. NEWSWEEK, February 11, 1991 No 6
5. NEWSWEEK, November 12, 1990 No 46
6. TIME, February 25, 1991 No 8
7. TIME, December 17, 1990 No 51
8. BEIJING REVIEW, MARCH 18 – 24, 1991 Vol. 34, No 11
9. TIME, January 28, 1991 No 4



## ደራስያኑ

ጁዲት ሚለር በ1969 በኒውዮርክ ሄራልድ ሥራ ላይ ተወማራች ። ከዚያ ወዲህ ፡ በክልሉ የጋዜጣዋ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ሆና ያገለገለችባትን ካይሮን ጨምሮ ፡ ከበርካታ መዲናዎች በሰራው ዘግባ ለች። ጁዲት በአሁኑ ወቅት ረዳት የመገናኛ ብዙኃን (የሚዲያ) አዘጋጅ ናት ።

ላውሪዬ ማይልሮይ ባሁኑ ወቅት በሀርቫርድ ዩኒቨርስቲ የመካከለኛው ምሥራቅ ጥናት ማእከል ፡ በብራድሌይ ፋውንዴሽን ድጋፍ ፡ በምርምር ላይ ትገኛለች ። ኢራቅን ብዙ ጊዜ ተመላልሳ ጐብኝታለች ።

ሣዳም ሑሴን ሐምሌ 26/1982 ኩዌትን በመውረር ዓለምን ቀዝቃዛው ጦርነት ካባራ ወዲህ ታይቶ ወደማይታወቅ እጅግ ብርቱ ቀውስ ውስጥ ዘፈቁት ። ዛሬ ለሚረካ ከቬየትናም ጦርነት ወዲህ ባሕር ማዶ ካዘመተቻቸው ጦር ኃይሎ ሁሉ በበዛው ከ700ሺ በላይ ጦር የተመራ የኅብረብሔር ጦር ኃይል "የበረሀው ማዕበል" በተሰኘ ዘመቻ የአርባ ሁለት ቀን ከፍተኛ የሌት ተቀን ጦርነት ኩዌትን ከኢራቅ ወራሪ ጦር ነፃ አውጥቷታል ። ይህ መጽሐፍ የሣዳም ሑሴንን ለነሣሥ ፣ ኢራቅን በዓለም ካሉት በፈላጭ ቆራጭ በምባገነን መንግሥት ከሚመሩ አገሮች አንዷ ለመሆን ስለማብቃታቸው ፣ ኩዌትን ስለወረሩበት ምክንያት ፣ በመካከለኛው ምሥራቅ መረጋጋት ላይ ሳላሳደሩት ሥጋት ለብጠልጥሎ ያስረዳል ። ደራስያኑ ስለሣዳም ሑሴን ማንነትና ሕይወት ብዙ ጭብጥ በማስያዝ ከዘመናዊቱ ኢራቅ አመሠራረት ጋር በተዛመደ ሁኔታ የጎረብን የእኔ አበልጥ እኔ አበልጥ ባላንጣነት ከተነተኑ በኋላ፣ ቀውሱን ለትልተው ለቅርበውልናል ። ይህ በፋርስ ባሕረሰላጤ ግጭት ለንኮፍ ስለሆኑት ሶውዱና ስለሀገሮቹውም አገር በበቂ መረጃ የደለበ መጽሐፍ እዝነ ኅሊናን ይዘልቃል ። በአሜሪካ የተመራው ከ28 አገሮች የተውጣጣ የኅብረብሔር ጦር ለ3ኛው የዓለም ጦርነት የደገሰውን ከፍተኛ የጦር መሣሪያ ቴክኖሎጂ በኢራቅ ላይ እንዴት እንደፈተሸባትም በጉልህ ያሳያል ።

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት